ዳግ ሂዋርድ ሚሊስ

# የመሪነት ጥበብ

ሁለተኛ እትም

መቅድም በዶክተር ዴቪድ ዮንግ ቾ

ከመጋቢነት አገልግሎት ርዕሶች

# የመሪነት ጥበብ

## ዳግ ሂዋርድ ሚልስ

ትርጉም፡- እስራኤል ጥበቡ

እና

መጋቢ ቢኒያም ገ/ማርያም

አርታኢ፡-  ያሬድ ጆሴፍ ስለሺ

ካልተገለፀ በቀር፣ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም. ከታተመው የአማርኛ መፅሐፍ ቅዱስ ነው።

Email Dag Heward-Mills:
bishop@daghewardmills.org
evangelist@daghewardmills.org

Find out more about Dag Heward-Mills at:
www. daghewardmills.org
www. lighthousechapel.org
www.healingjesuscrusade.org

Write to:
Dag Heward-Mills
P.o.Box 114
Korle-Bu
Accra
Ghana

ላይትሃውስ ቻፕል ኢንተርናሽናል
መ.ሳ ቁጥር 15134
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ይህንን መፅሐፍ በሙሉም ሆነ በከፊል ያላሳታሚው ፈቃድ ማባዛት የተከለከተለ ነው።

መታሰቢያ

ለናትናኤል ኒ ላንኬይ ሂዋርድ ሚልስ

ለእኛ ስላደረክልን ሁሉ አመሰግንሃለሁ።

አንተን የመሰለ አባት ስለነበረኝ ምስጋናዬ እጅግ የላቀ ነው።

# ማውጫ


1. ሊደር ለሚለው የእንግሊዘኛ ቃል አርባ የተለያዩ ስያሜዎች......... 1
2. መሪነት በመጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደተብራራ......................... 4
3. ልታስወግደው የሚገባህ የአመራር ዓይነት................................ 6
4. የሕፃን አመራር.......................................................................... 7
5. የሴት አመራር......................................................................... 22
6. የስልታዊ እርምጃዎች ባለቤት ሁን .......................................... 28
7. በዚህች ዓለም ውስጥ ካሉት ምርጥ መሪዎች አንዱ ለመሆን ወስን ............................................................................................. 33
8. ከታላላቆችም ሆነ ከታናናሾች ጋር ሕብረት አድርግ................... 38
9. የራስን ሃቀኝነት ጠብቅ ............................................................ 42
10. ለሰዎች ተስፋ ስጥ ................................................................... 43
11. ሥልጣንን በፍጹም ያለ ጥበብ፣ ጥበብንም ያለ ሥልጣን አትጠቀም! ............................................................................................. 45
12. ሕይወት አልባ መሪ አትሁን ጽኑ እምነት ይኑርህ!................... 47
13. ዘመንህ እስኪመጣ ጠብቅ......................................................... 49
14. በአንድ ነገር ላይ የማተኮርን ምሥጢር ተጠቀም ....................... 50
15. በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች በሕይወታቸው ታላላቅ ተግባራትን እንዲያከናውኑ አግዛቸው......................................................... 53
16. ሰዎች በደስታ እንዲታዘዙህ አድርግ.......................................... 56
17. አሰላስል፣አገናዝብ፣አሳቢ ሁን እናም በዙሪያህ የምትመለከታቸውን ነገሮች ልብ ብለህ አጢን........................................................ 64
18. ለልቀት ተጋደል....................................................................... 67
19. ሁሉም ነገር በአመራሩ ላይ የተደገፈ ነው................................. 69
20. ሰዎችን በዙሪያህ አሰባስብ ...................................................... 74
21. ከመልካምና ቀላል ነገሮች ይልቅ ከባድና አስቸጋሪ ነገሮችን ምረጥ ............................................................................................. 79

22. አዳዲስ አሳቦችን ለመቀበል የተዘጋጀህ ሁን ............................. 82
23. ለሰዎች ትልቅ ዋጋ ስጥ ...................................................... 85
24. መጽሐፍ ለማግኘት የትኛውንም ያህል ገንዘብና ጊዜ ከማውጣት ወደኋላ አትበል.................................................................... 87
25. አሻግረህ ተመልከት! ለወደፊት ተዘጋጅ!.................................. 91
26. ሁልጊዜ አዳዲስ ነገሮችን ተማር ............................................ 93
27. ጠንካራ ጎኖችህን ተረድተህ ተጠቀምባቸው!.............................. 94
28. ለረዥም ተጋድሎ ተዘጋጅ!.................................................... 96
29. ሳንቲሞችህን ቁጠር!............................................................ 97
30. እውነትን ተናገር ............................................................... 99
31. ትኩረትህን አትሳት ........................................................... 100
32. የታላቅ ሥራን አነስተኛ ጅማሬዎች ለይተህ እወቅ................. 103
33. ሰዎችን በእኩልነት እያስተናገድክ፣ ልዩነቶችን ግን ግልጽ አድርግ ..................................................................................... 105
34. ጠቅለል ባለ መንገድ የወደፊቱን ሁኔታ ተንብይ .................... 109
35. መራርነት እንዲበክልህ አትፍቀድ......................................... 111
36. የሰዎችን አስተሳሰብ ለውጥ................................................ 114
37. እየተከናወነ ስላለው ነገር ሁሉ መጠነኛ ግንዛቤ ይኑርህ.......... 118
38. ስሜት ያለው መሪ ሁን...................................................... 119
39. የተሰጠህን ልዩ መብት በተገቢው ጊዜ እና ለተገቢ ምክንያት ተጠቀም.......................................................................... 122
40. ከግለሰቦች እና ከብዙሃኑ ጋር ግንኙነት ፍጠር........................ 126
41. ታሪክን በማጥናት የወጣትነትንና የልምድ ማጣትን ጉዳት ተቋቋም ..................................................................................... 128
42. ኃላፊነትን ተቀበል እና ተጠያቂ ሁን ..................................... 131
43. የኃይል ምንጭህን አትተው!................................................. 132
44. ቆራጥ ሁን! ይህ የአንድ መሪ ትልቁ መገለጫ ነው ............... 134

45. ስለ ልምዶች ኃይል በማወቅ ጥሩ ልማዶችን አዳብር............... 142
46. የደረስክበትን እወቅ! ያልደረስክበትንም እወቅ! ከዚያም ወዴት እንደምትሄድ ታውቃለህ!.................................................... 148
47. በራስህ የተነሳሳህ ሁን ከውጪ መመሪያና ማበረታቻ አትፈልግ 149
48. ተለማጭ ሁን ግትርነት ዋጋ ያስከፍላል!.............................. 152
49. ወታደሮችህን እዘዝ............................................................ 154
50. ቅድሚያ የምትሰጣቸውን ጉዳዮች ሚዛናዊ አድርግ................. 156
51. የቡድን ሥራን አመክኒዮአዊ ደንቦች አክብር.......................... 157
52. አንዳንድ ጊዜ ተቆጣ.......................................................... 159
53. የምትመራቸውን ሰዎች በትምህርት ኃይል ተቆጣጠር............ 160
54. ታላቅ መሪ ሁን ተጨማሪ ምዕራፍ ሂድላቸው....................... 162
55. ምን ተቋቁመህ አልፈሃል?................................................... 163
56. የሌሎችን ሰዎች ስጦታዎች እውቅና ስጥ........................... 172
57. የፈጠራ ጥበብ ይኑርህ......................................................... 173
58. መርሆችን ብታከብር ታላቅ ድርጅት ትገነባለህ...................... 175
59. ከምትመራቸው ሰዎች ምን ያህል ገንዘብ ልታገኝ እንደምትችል አታስብ። ምን ያህል ልትረዳቸው እንደምትችል አስብ............ 178
60. ተፅዕኖ በማድረግ እደግ........................................................ 180
61. የግል ምሳሌዎችንና በቅኔ የሚነገሩ አባባሎችን አዳብር........... 184
62. ተከታዮችህን ወክለህ ከባለሥልጣኖች ጋር ተደራደር............... 185
63. ታላላቅ መሥዋዕትነቶችን እንዲከፍሉ ሰዎችን አሳምናቸው። ... 187
64. ሁሉንም ሰው ከአንተ ጋር ወደ ከፍታ ውሰድ........................ 189
65. መሪ ከሆንክ አንድ ነገር ገንባ!............................................... 192
66. የሕወትህን ራእይ ሁልግዜ አስተውል.................................... 194
67. ሁልጊዜ አንድ እርምጃ ቀድመህ ተገኝ.................................. 196
68. ሐሳብ የሚበትንን ነገር አስወግድ.......................................... 198
69. ሰዎች አንተ በሌለህበት እንዲታዘዙህ አድርግ........................ 201

70. እንደ እባብ ተደብቀህ አብብ ........................................................ 203
71. ስለማንነትህ የሚነገሩ የወሬዎች፣ የጥያቄዎችና ውዝግቦችን ተፅዕኖ ተቋቋም ........................................................ 206
72. ያንን ውሳኔ ወስን! ያም ሆነ ይህ ብዙ ውሳኔዎች ከሁለት መጥፎ አማርጮች አንዱን መምረጥ ስለሚጠይቁ! ........................................................ 208
73. የማይገቡ ነገሮችን በሕዝብ ፊት በመናገር አገልግሎትህን አታውድም ........................................................ 212
74. አርቲፊሻል መሪ አትሁን እውነት የሆኑ የአመራር ክህሎቶችን አዳብር ........................................................ 214
75. ድካም ማመካኛ እንዲሆን አትፍቀድ ........................................................ 217
76. የቤት ውስጥ ሕይወትህን በብቃት ተወጣ ........................................................ 219
77. እውነተኛ እንጂ ግብዝ አትሁን ........................................................ 220
78. ውስንነቶችህን እወቅ ........................................................ 221
79. ብርቱ ሁን ........................................................ 223
80. ሰዎች ወደ አንድ ቦታ እንዲከተሉህ አድርግ ........................................................ 224
81. የበለጡ ተከታዮች ለማግኘት እውነትን ከጸጋ ጋር አዋህድ ........................................................ 225
82. ስምንቱ የመሪ ታላላቅ ውሳኔዎች ........................................................ 230
83. መካሪዎችህን በጥንቃቄ ምረጥ ........................................................ 232
84. ሰዎችን አነሳሳ ........................................................ 235
85. መፍትሔዎችን በማግኘት ችግሮችን ፍታ ........................................................ 237
86. የምታስብ ሁን ........................................................ 240
87. ራስህን በሌሎች ውስጥ አብዛ ........................................................ 243
88. እችላለሁ የሚል መሪ ሁን ........................................................ 245
89. የብቸኝነትን እውነታ ተቀበል ........................................................ 249
90. የረዱህን አትርሳቸው ........................................................ 252
91. ራእይህን ወደ እውነታ ለውጥ ........................................................ 254
92. ቀድመህ ሂድ ሰዎች ወደምትሄድበት ይከተሉሃል ........................................................ 255

93. ተከታዮችህ እንዲወዱህ አድርግ በአንተ ቅር እንደማይሰኙ እርግጠኛ ሁን። ................................................................ 257
94. ቅሬታን ተጠንቀቅ ወሳኝ በሆነ ሁኔታ ደግሞ ምላሽ ስጠው...... 259
95. በተቺ ሰዎች ላይ ምንም ጊዜ አታጥፋ.................................... 263
96. መላመድ የአመራር አደጋ ነው። በአስቸኳይ ምላሽ ስጠው....... 267
97. ልታሸንፍ የምትችላቸውን ውጊያዎች ብቻ ዋጋ ....................... 272
98. እንዲመሩህ መገለጫዎችንና ምልክቶችን ተጠቀምባቸው.......... 274
99. ታማኝ መሪ ሁን................................................................. 276
100. ጥላቻንና ተቃውሞን ተቋቋም ................................................ 279
101. የአንተ “ዓይነት” ያልሆኑ ሰዎችን ጨምሮ ከሁሉም ዓይነት ሰዎች ጋር ተዛመድ ........................................................................... 282
102. በውስታቢስነት አትደነቅ ........................................................ 284
103. ሰዎች አንተን ማመንና መከተል እንዲችሉ እንያውቁህ ፍቀድላቸው።.................................................................. 286
104. በምሳሌነት በሰዎች ላይ ተፅዕኖ አሳድር ................................. 287
105. ፍላጐትህ ለመሪነት የመጠራትህ መገለጫ መሆኑን ዕውቅና ስጠው ..................................................................................... 289
106. ከአንድ ድንገተኛ ሁኔታ ወደ ሌላ አትቻኮል.......................... 292
107. ሁልጊዜ አስታውስ፡ “ሁላችን እስክናሸንፍ ድረስ ማንም አያሸንፍም!” ...................................................................... 296
108. የብዙ ሰዎችን ስም እወቅ...................................................... 298
109. በራስህ ላይ ሥራ ................................................................ 300
110. ለጊዜ ዋጋ ስጥ፤ ጊዜን ተቆጣጠር .......................................... 302
111. ታላላቅ ውጤቶች ታላቅ ሥነ ሥርዓትን ይጠይቃሉ ............... 304
112. ራእይ ይኑርህ..................................................................... 305
113. ታላቅ መሪ በተገኘበት የምታሳልፈውን እያንዳንዱን ደቂቃ ዋጋ ስጠው ............................................................................... 306
114. ኃላፊነት ውሰድ!................................................................ 308

115. ገንዘብን የመሰብሰብ ጥበብ ተካን ........................................ 309
116. ምሕረትን የምታደርግ ሁን ................................................ 311
117. የልብ ጓደኞች ይኑሩህ ........................................................ 313
118. በዙሪያህ ካሉት ሁሉ ይልቅ ጠንክረህ ሥራ .......................... 314
119. በትህትና ጀምር በትህትና ጨርስ......................................... 316
120. ሰዎችን እንዲያምኑብህ አሳምናቸው..................................... 319
121. የምታናግረውን ሰው እንደማንነቱ አይተህ ብዙ ተናገር ወይም ምንም አትናገር.................................................................. 322
122. የደረጃ የማዕረግን መርህ ተቀበል ......................................... 326
123. በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች ወደተሻሉ ሰዎች ለውጣቸው ............ 329
124. ወደ ትክክለኛው ምድር በመሄድ ሽቅብ ውጣ...................... 332
125. የሥጋዊ ስሜቶችህን ተቆጣጠር............................................ 335
126. በሀሳባዊውና በእውኑ መካከል ያለውን ልዩነት ተረዳ.............. 337
127. በድርጅትህ ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ዓይነት ሠራተኞች ለይተህ እውቅ።.......................................................................... 339
128. ሰዎችን በአንድነት የማቆየት ጥበብን አዳብር.......................... 342
129. ስለምተጠየቅበት ቀን ያለማቋረጥ አስብ................................. 346

# መቅድም

*የመሪነት ጥበብ* በሚል ርዕስ የቀረበውን ይህን የዶክተር ዳግ ሂዋርድ ሚልስ አዲስ መጽሐፍ እንድታነብ የምጋብዝህ በታላቅ ደስታ ነው።

ዶክተር ዳግ ሂዋርድ ሚልስ ብሩህ አእምሮ ያላቸው የእግዚአብሔር ሰው እና በእዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለሚያስተምረው ምሳሌ ነው። የመጽሐፉን መመዘኛዎች ተከትለው የሚኖሩ ሲሆን፣ ሌሎች ቁጥር የሌላቸውን ወገኖች ወደዚሁ የላቀ ጎዳና የመምራት ብቃት አላቸው። ያልኖርነውን የሕይወት ተሞክሮ ለሌሎች ልናስጨብጥ አንችልም፣ በመሆኑም ይህ መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የታዩትን ታላላቅ መሪዎች ሁሉ ጎዳና የሚያስቃኝ ነው።

ይህ መጽሐፍ መሪ ለመሆን የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎችን እና ወደፊት መሪ የመሆን እምቅ ላላቸው ሰዎች ግብ ምን መሆን እንዳለበት ያብራራል። ይህ መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፣ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ብቻ የሚገኙትን የመሪነት ብቃቶችን ያቅፋል።

ዶክተር ዳግ ሂዋርድ-ሚልስ ከረዥም ዓመታት አገልግሎታቸው ታላቅ እውነቶችን ተምረዋል። በርካታ መሪዎችን መርተዋል፤ በዓለም ዙሪያ ብዙ የላይትሃውስ ቻፕል ቤተ ክርስቲያናትን መሥርተዋል። የተዋጣላቸው ደራሲ ሲሆኑ፣ በአንደበተ ርዕቱነታቸው በተለያዩ ታላላቅ ጉባኤዎች ላይ የመናገር ግብዣ በተደጋጋሚ ይቀርብላቸዋል።

እንዲሁም በቸርች ግሮውዝ ኢንተርናሽናል ውስጥ ላለን ሁሉ እውነተኛ አነሳሽ ሆነዋል፣ በተጨማሪም ከተከበሩት የቦርድ አባላችን አንደኛው ናቸው።

እርሳቸው ክርስቶስን እንደሚከተሉት እኚህን አገልጋይ ብትከተል፣ ጥበባቸው፣ አርቆ የማየት ችሎታቸውና ተሞክሯቸው በከፍተኛ ደረጃ ሊያነቃቃህ ይችላል። ዶ/ር ሂዋርድ-ሚልስ ወደፊት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚሆኑ የኢየሱስ ክርስቶስን ደቀ መዛሙርት የማጎልበት ፍላጎት አላቸው።

የመምራት ጥበብ የእውነተኛ መሪ የመሆንን ምስጢር መንገድ ያሳይሃል እንዲሁም መመሪያን ይሰጥሃል። መሪነት ጥበብ ስለሆነ፣ ልትማረው ይገባሃል። ይህ መጽሐፍ በዚህ ዘመን ላለችው ቤተ ክርስቲያንና የአዲሱ ሚሊኒየም ቤተ ክርስቲያን ስለ አመራር ልታውቅ የሚገባህን ወይም የምትሻውን ነገሮች በሙሉ ያስተምርሃል።

ኖቬምበር 02/ 2001 ዓ.ም

ዋና መጋቢ ዶክተር ዴቪድ ዮንግ ቾ

ዮዲዮ ፋል ጎስፐል ቤተክርስትያን

ሲዖል፣ ደቡብ ኮሪያ

## *ምዕራፍ 1*

# ሊደር ለሚለው የእንግሊዘኛ ቃል አርባ የተለያዩ ስያሜዎች

*ኃያሉንም፥ ተዋጊውንም፥ ፈራጁንም፥ ነቢዩንም፥ ምዋርተኛውንም፥ ሽማግሌውንም፥ የአምሳ አለቃውንም፥ ከበርቴውንም፥ አማካሪውንም፥ ብልሁንም ሠራተኛ፥ አስማት አዋቂውንም ይነቅላል። አለቆቻቸው እንዲሆኑ ብላቴኖችን አስነሣባቸዋለሁ፥ ሕፃናቶችም ይገዙአቸዋል።*

ኢሳያስ 3፡2-4

መሪ ለሚለው ቃል የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብዙ ተመሳሳይ ቃሎች አሉት፡፡ እነዚህ የተለያዩ ስሞች በዓለም ላይ የሚገኙትን የተለያዩ ዓይነት መሪዎች ይገልጣሉ፡፡ ለእያንዳንዱ የክንውን ዘርፎች መሪዎች አሉ፤ እያንዳንዱ የሙያ ዘርፍ ደግሞ ለመሪው የተለየ ስም ይሰጣል፡፡ በመርከቦች ያሉ መሪዎች ካፒቴን ይባላሉ፡፡ በአውሮፕላን ውስጥ ያሉ መሪዎች ፓይለት ይባላሉ፤ የወታደር መሪዎች ደግሞ ጄኔራል ይባላሉ፡፡ በፖለቲካው ዓለም ደግሞ የአገር መሪዎች ፕሬዚዳንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስቴር ሲባሉ የዩኒቨርስቲ መሪዎች ደግሞ “ቻንስለር” ይባላሉ፡፡ በሃይማኖቱ ዓለም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መጋቢ ሲባሉ የመስጊድ መሪዎች ደግሞ ኢማም ይባላሉ፡፡ በአረብ አገር የከተማ መሪዎች “ሼክ” ሲባሉ በጋና አገር ደግሞ መሪዎች “ቺፍ” ተብለው ይጠራሉ፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ጥቂት ስያሜዎች መሪ ለሚለው ቃል አቻ የሚሆኑ ናቸው፡፡ እነዚህ ማዕረጎችና ስሞች አስፈላጊ ናቸው፡፡ ምክንያቱም አንተ ከምታውቀው አካባቢ ውጪ እንኳን በሌሎች የሥራ ሕይወት ውስጥ መሪነትን እንድትረዳ ያደርግሃል፡፡ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ቢሆኑ እንኳን መሪዎች በአብዛኛው አንዳቸው ለሌላው ዕውቅና ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ የእኔ የአመራር ብቃቶች በአንድ እግዚአብሔር የለም ባይ እና በቤተ ክርስቲያን በማያምን ሰው ዕውቅና ተሰጥቷቸው ያውቃል፡፡ እንዲህም ሆኖ ይህ ሰው ሊደመጥ እንደሚገባ መሪ እንደሆንኩ ሊለየኝ ችሏል፡፡

ለሃይማኖት ወይም መንፈሳዊ አስተምህሮቶቼን ዕውቅና ባይሰጥም በአመራር ክህሎቶቼ ዕውቅና ሰጥቶ እነዚህም ክህሎቶች ለሌሎች

በእግዚአብሔር ለማያምኑ ሰዎች እንዳካፍላቸው ጠየቀኝ። ሃይማኖታዊ መሪ ከሆንክ ነጋዴዎች፣ ፖለቲከኞች፣ እግዚአብሔር የለሾች ወይም የሌላ ሃይማኖት መሪዎች ቢሆኑ እንኳን ለሌሎች መሪዎች ዕውቅና ትሰጣለህ።

በሌላ ጐኑ፣ መሪ ካልሆንክ አንድን መሪ አይተህ አትለየውም። ለምሳሌ፣ በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉ ብዙ ፖለቲከኞች እነርሱ ራሳቸው መሪ ስላልሆኑ በሌላ መስክ ያሉ መሪዎችን አይለዩአቸውም ደግሞም አይቀበሏቸውም። ፖለቲከኛ ሆኖ ሁሉንም የሚያስደስት ነገርን በመናገር የሰዎችን ድጋፍ ማግኘት እና ሰዎችን ወደ ስኬትና ዕድገት መምራት አንድ አይደለም።

ከላይ በተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ በኢየሩሳሌም ከተማ የነበሩትን የተለያዩ ዓይነት መሪዎች ታያለህ። የጌታ ቅጣት ሁሉንም የተለያዩ ዓይነት መሪዎች ከማህበረሰቡ ማስወገድ ነበር።

1. መሪዎች ካፒቴይን ይባላሉ።
2. መሪዎች "ቺፎች" ይባላሉ።
3. መሪዎች "ኮማንደሮች" ይባላሉ።
4. መሪዎች ፕሬዚደንቶች ይባላሉ።
5. መሪዎች ጠቅላይ ሚኒስቴሮች ይባላሉ።
6. መሪዎች እረኞች ይባላሉ።
7. መሪዎች ጄኔራሎች ይባላሉ።
8. መሪዎች አገረ ገዢ ይባላሉ።
9. መሪዎች መካሪዎች ይባላሉ።
10. መሪዎች መጋቢዎች ይባላሉ።
11. መሪዎች አለቆች ይባላሉ።
12. መሪዎች ራሶች ይባላሉ።
13. መሪዎች ሥራ አስኪያጅ ይባላሉ።
14. መሪዎች ኃላፊዎች ይባላሉ።
15. መሪዎች ገዥዎች ይባላሉ።
16. መሪዎች የተከበሩ ዜጐች ይባላሉ።

17. መሪዎች "ካውንስለሮች" ይባላሉ።
18. መሪዎች ፓይለቶች ይባላሉ።
19. መሪዎች የበላይ ተጠሪዎች ይባላሉ።
20. መሪዎች የበላዮች ይባላሉ።
21. መሪዎች ሽማግሌዎች ይባላሉ።
22. መሪዎች ሰላም አስከባሪዎች ይባላሉ።
23. መሪዎች ተቆጣጣሪዎች ይባላሉ።
24. መሪዎች አስፈጻሚዎች ይባላሉ።
25. መሪዎች ዳይሬክተሮች ይባላሉ።
26. መሪዎች ማስተር ይባላሉ።
27. መሪዎች ጌቶች ይባላሉ።
28. መሪዎች አምባገነኖች ይባላሉ።
29. መሪዎች ንጉሶች ይባላሉ።
30. መሪዎች ፊር ቀዳጅ ይባላሉ።
31. መሪዎች ቀዳሚዎች ይባላሉ።
32. መሪዎች ቆንስላዎች ይባላሉ።
33. መሪዎች ሼኮች ይባላሉ።
34. መሪዎች መሳንፍቶች ይባላሉ።
35. መሪዎች ኤክስፐርቶች ይባላሉ።
36. መሪዎች ስፔሻሊስት ይባላሉ።
37. መሪዎች ጀግኖች ይባላሉ።
38. መሪዎች አፈ ጉባኤዎች ይባላሉ።
39. መሪዎች ፋና ወጊዎች ይባላሉ።
40. መሪዎች ታዋቂዎች ይባላሉ።

## ምዕራፍ 2

# መሪነት በመጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደተብራራ

መሪነት በመጽሐፍ ቅዱስ ወሳኝ ርዕስ ነው፡፡ ብዙ መጽሐፍ ቅዱሶች ርዕሰ ጉዳዩን ሲያብራሩ መሪ የሚለውን ቃል አይጠቀሙም፡፡ በዚህም ምክንያት የአመራር ርዕሰ ጉዳይ ለአነሳሽ ተናጋሪዎችና ለሌሎች ዓለማዊ ፍላጎቶች ተትቷል፡፡

ይሁንና *መሪ* በሚለው ቃል ፈንታ በጥቅም ላይ የዋሉትን የተለያዩ ቃሎች መረዳት ይህን ርዕስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመለየት ይረዳሃል፡፡ የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመሪዎችን የተለያዩ መገለጫዎች ያሳያሉ፡፡

1. መሪነት በሐዋርያው ጳውሎስ *መንግሥት* ተብሎ ተጠርቷል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥ በመካተቱ መሪነት ከእግዚአብሔር የሆነ *ስጦታ* ተደርጎ ተቆጥሯል፡፡

**እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ እርዳታንም፥ አገዛዝንም፥ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጎአል።**

**1ኛ ቆሮንቶስ 12፥28**

2. መሪ በሐዋርያው ጳውሎስ *ገዢ* ተብሎ ተገልጿል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥ በመካተቱ መሪነት ከእግዚአብሔር የሆነ ስጦታ ተደርጎ ተቆጥሯል፡፡

**የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤ የሚምር በደስታ ይማር።**

**ሮሜ 12፥8**

3. የመጽሐፍ ቅዱሳዊው የአመራር ዘይቤ ዓለም ከሚሰጠው የአመራር ዓይነት ይለያል፡፡

**እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ፤ ነገር ግን ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ፥ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን።**

ሉቃስ 22፡26

4. በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሰው አንዲትን ሴት መምራት ከቻለ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት ብቁ እንደሆነ ይቆጠራል። በዚህ ውስጥ እንደሚታየው መሪነት ጥቂት ሰዎችን (ሁሉንም ማለት አይደለም) እንደማስተዳደር ተቆጥሯል።

ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?

1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡5

5. የእስራኤል መሪዎች አንዴ መሳፍንት ተብለው ተጠርተዋል። በሌላ ጊዜ ደግሞ ነገሥታት ተብለው ተጠርተዋል። የአመራር ዘይቤዎቻቸውና ስኬቶቻቸው በመጽሐፍ መሳፍንትና ነገሥት ላይ ተገልጿል።

እግዚአብሔርም መሳፍንትን አስነሣላቸው፥ ከሚማርኩአቸውም እጅ አዳኑአቸው። ሌሎች አማልክትን ተከትለው አመነዘሩ ሰገዱላቸውም እንጂ መሳፍንቶቻቸውን አልሰሙም አባቶቻቸውም ይሄዱበት ከነበረ መንገድ ፈጥነው ፈቀቅ አሉ አባቶቻቸው ለእግዚአብሔር ትእዛዝ እንደ ታዘዙ እንዲሁ አላደረጉም።እግዚአብሔርም መሳፍንትን ባስነሣላቸው ጊዜ እግዚአብሔር ከመስፍኑ ጋር ነበረ እግዚአብሔርም ስለሚጋፉአቸውና ስለሚያስጨንቋቸው በጩኸታቸው ያዝን ነበርና በመስፍኑ ዘመን ሁሉ ከጠላቶቻቸው እጅ አዳናቸው።መስፍኑ ግን ከሞተ በኋላ ይመለሱ ነበር፥ ሌሎችንም አማልክት በመከተላቸው እነርሱንም በማምለካቸውና ለእነርሱ በመስገዳቸው አባቶቻቸው አድርገውት ከነበረው የከፋ ያደርጉ ነበር የእልከኝነታቸውን መንገድና ሥራቸውን አልተዉም ነበር።

መሳፍንት 2፡16-19

እግዚአብሔር ከጌታዬ ከንጉሥ ጋር እንደ ነበረ እንዲሁ ከሰሎሞን ጋር ይሁን፥ ዙፋኑንም ከጌታዬ ከንጉሡ ዳዊት ዙፋን የበለጠ ያድርግ።

1ኛ ነገሥት 1፡37

## ምዕራፍ 3

# ልታስወግደው የሚገባህ የአመራር ዓይነት

*ሕዝቤንስ አስገባሪዎቻቸው ይገፉአቸዋል፥ አስጨናቂዎችም ይሠለጥኑባቸዋል። ሕዝቤ ሆይ፥ የመሩአችሁ ያስቱአችኋል የምትሄዱበትንም መንገድ ያጠፉሉ።*

ኢሳይያስ 3፡12

እግዚአብሔር ሴቶችና ሕፃናት ሕዝቡን እንደሚመሩ አውጇል። **የዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አነጋገር የተወሰኑ ክፍል ሕዝቦች በሴቶችና በሕፃናት መመራት እርግማን ወይም ቅጣት እንደሆነ ያሳየናል።** ከላይ ሲታይ ትንሽ ሀይለኛ ቢመስልም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉን ትርጉም ማሰላሰልና መረዳት የመምራት ችሎታህን እንድታዳብር ይረዳሃል። በእግርጥ እነዚህ ሁለት እርግማኖች ልትረዳቸውና የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ከፍለህ ልታስወግዳቸው ይገባሃል። እነዚህን አባባሎች ሳትሳማ አትቀርም "እንደ ሕፃን ያደርግሃል!" ይህንን ንግግር ሰምተህ መሆን አለበት "እንደ ሕፃን እየሆንክ ነው!" ከዚህ ቀደም እንዲህ ብለህ መሆን አለበት "እኔ ሕፃን አይደለሁም!" እነዚህ አባባሎች የሚባሉበት ምክንያት አንዳንድ ጊዜ ትላልቅ ሰዎች እንደ ሕፃን ስለሚሆኑ ነው። የሚያሳዝነው ግን በከፍተኛ ቦታዎች ላይ ያሉ መሪዎች ብዙ ጊዜ እንደ ሕፃን ይሆናሉ፤ ይህም በዙሪያቸው ያለውን ሰው ሁሉ ይጐዳል።

እንዲሁም በርካታ መሪዎች በውሳኔዎቻቸውና በአመራር ዘይቤአቸው እንደ ሴት ይሆናሉ። በመንፈስ ቅዱስ እና በእግዚአብሔር ቃል ያልተሰራች ሴት ሥር ሆኖ መቀመጥ አደገኛ ሰው ሥር እንደመቀመጥ ሊሆን ይችላል። ጠቅለል ባለ አነጋገር ሴቶች ተገቢ፣ ተስማሚና ተፈላጊ መሪዎች ለመሆን ሊለሰልሱና መልካም ንግግር ሊማሩ ያስፈልጋል።

1. ከሕፃን ልጅ አመራር ጋር የሚመሳሰልን የአመራር ዘይቤ ልታስወግድ ይገባል።

2. ከሴት አመራር ጋር የሚመሳሰልን የአመራር ዘይቤ ልታስወግድ ይገባል።

# ምዕራፍ 4

# የሕፃን አመራር

*ሕዝቤንስ አስገባሪዎቻቸው ይገፉአቸዋል፥ አስጨናቂዎችም ይሠለጥኑባቸዋል። ሕዝቤ ሆይ፥ የመሩአችሁ ያስቱአችኋል የምትሄዱበትንም መንገድ ያጠፉሉ።*

ኢሳይያስ 3፡12

## 1. የሕፃን አመራር የሚገለፀው በዝርክርክነት ነው፡፡

*አለቆቻቸው እንዲሆኑ ብላቴኖችን አስነሣባቸዋለሁ፥ ሕፃናቶችም ይገዙአቸዋል።*

ኢሳይያስ 3፡4

የራስህን ክፍል በሥርዓት የማትጠብቅ ከሆነ ሕፃን መሆን አለብህ፡፡ የምትኖርባቸውን ሥፍራዎች ማፅዳት የማትችል ከሆነ ሕፃን መሆን አለብህ፡፡ ከተማህን ማፅዳት የማትችል ከሆነ ሕፃን መሆን አለብህ፡፡ ምንም እንኳን ሁሉ ሰው ከንቲባው ወይም ሚኒስቴሩ ብሎ ቢጠራህም ሕፃን ነህ፡፡

አመራርን ማጥናት፣ አመራርን መረዳትና ተገቢ የአመራር መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አስተሳሰብ ልትመራቸው ትችላለህ፡፡ የሕፃን አመራር መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚተነብየው ግርግር እና ረብሻን ያስከትላል፡፡ ረብሻን፣ ትርምስምስን፣ ዝርክርክነትን እና መደናገርን ስታይ የሕፃን ልጅ አመራር በሥራ ላይ እንዳለ መገመት ትችላለህ፡፡

## 2. የሕፃን አመራር የሚገለፀው የአሳሳቢ ጉዳዮችንና ትላልቅ አደጋዎችን ስመረዳት ባለመቻል ነው፡፡

*ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር፥ እንደ ልጅም አስብ ነበር፥ እንደ ልጅም እቈጥር ነበር፤ ጎልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ።*

1ኛ ቆሮንቶስ 13፡11

አመራርን ማጥናት፣ አመራርን መረዳትና ተገቢ የአመራር መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አስተሳሰብ ልትመራቸው ትችላለህ፡፡ የሕፃን አእምሮ አሳሳቢ ጉዳዮችንና የተጋረጡ አደጋዎችን ባለመረዳት የተሞላ ነው፡፡

መሪ የለሽ ሰዎች በአብዛኛው ቆሻሻ የመመገቢያ ሥፍራዎችና ቆሻሻ መፀዳጃ ቤቶች አሏቸው፡፡ ትናንሽ ልጆች በቆሻሻ ቦታ ሲኖሩ ምን ማለት እንደሆነ አይረዱም፡፡ ሕፃናት ለብቻቸው ከተተዉ እድፈትና ቆሻሻ ይበራከታል፡፡ ማንም ሕፃናትን ለብቻቸው የማይተዋቸው ለዚህ ነው፡፡ ምንም ነገር አያጥቡም፣ አያፀዱም ወይም አያስናዱም፡፡

ለዚህ ነው ሕፃናት መሪዎች በሆኑባቸው አገሮች ቆሻሻ መፀዳጃ ቤቶችና እስከ ደጃፉ በአደገኛ ጥራጊ የተሞሉ ትላልቅ የፍሳሽ ማስወገጃዎች ያሏቸው፡፡ በሕፃናት የሚመሩ ከተሞች ዋና ባሕሪያት በየቦታው የሚገኝ ጥራጊ እና ለሕይወት አስጊ የሆነ ቆሻሻ ናቸው፡፡ እንደ ሕፃን የሆነው አመራር እነዚህ ነገሮች ሞት የሚያመጡና በሕዝቡ ጤና ላይ የሚያስከትሉትን ችግሮች አይረዳም፡፡ ቢረዱ እንኳን ምን መደረግ እንዳለበት አያውቁም፡፡ የሚፈልጉት እናት ወይም አባት መፍትሔ እንዲሰጧቸው ነው፡፡

መሪ የሌላቸው አገሮች የሚያደርጓቸውን ነገሮች ምን እንደሚያስከትል ካለማወቅ የተነሳ የአገሮቻቸውን የትምህርት ተቋማት አጥፍተዋል፡፡

## 3. የሕፃን አመራር የሚገለፀው ትንሽ ውስብስብ የሆነውን ነገር ሁሉ ባለመረዳት ነው፡፡

*ወንድሞች ሆይ፥ በአእምሮ ሕፃናት አትሁኑ፤ ለክፋት ነገር ሕፃናት ሁኑ እንጂ* **በአእምሮ የበሰሉ ሁኑ።**

**1ኛ ቆሮንቶስ 14፡20**

አመራርን ማጥናት፣ አመራርን መረዳትና ተገቢ የአመራር መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አስተሳሰብ ልትመራቸው ትችላለህ፡፡ አንድ ሰው በአመራር ውስጥ ሆኖ የሕፃን አስተሳሳብ ቢኖረው ጥቂት ውስብስብ የሆነን ነገር አይረዳም፡፡

አንድ ያልተማረ ሰው በአንድ ጉዳይ ላይ መሪ ሆኖ ሲቀመጥ በደንብ ያስታውቃል፡፡ የሚናገረው ነገር ምን እንደሚያስከትል አያውቅም፡፡ አንድ የአፍሪካ መሪ የአገሪቱን ዕዳ በፍጹም እንደማይከፍል በድፍረት አውጇል፡፡ ሌላ እንዲህ ዓይነት መሪ እያንዳንዱ የውጭ ዜጋ ቢበዛ ሃያ አራት ኪሎ ሻንጣ ብቻ ይዘው አገሪቱን ለቀው እንዲወጡ ሃያ አራት ሰዓታት ብቻ ሰጣቸው፡፡ እንዲሁም ሌላ መሪ ቢሊዮንና ትሪሊዮን ዶላር ገንዘቦችን ለሕዝቡ ዳቦ መግዣ እንዲሆን አትሟል፡፡ በእርሱ አመራር ጊዜ የአንድ ዳቦ ዋጋ እስከ አንድ ቢሊዮን ዶላር የአገሪቱ ገንዘብ ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰዎች ስለሚያናግሯቸውም ሆነ ስለሚያደርጓቸው ነገሮች አያነቡም ወይም አይረዱም፡፡

የድሀ አገራት መሪዎች የግሎባላይዜሽንና የነፃ ገበያን ፅንስ ሀሳቦች ከኢንዱስትሪ መቀነስ፣ ግብርና መቀነስና ከከተሞች የሕዝብ ቁጥር መቀነስ አሉታዊ ጐኖቻቸው ጭምር እንዳሉ ተቀብለዋቸዋል። በቀሪው የአገሪቱ ክፍል ላይ የሚኖራቸውን ውስብስብ እንደምታ ሳይረዱ እነዚህን ፖሊሲዎች በልበ ሙሉነት በተቀበሉ አገራት ውስጥ ያሉ ኢንዱስትሪዎች እርሻዎች ከነአካቴው ጠፍተዋል። እንደ አሜሪካ እና አውስትራልያ ያሉ የበለፀጉ አገራት የራሳቸውን ኢንዱስትሪዎች አለማልማትን የሚያስከትለውን ችግር በመረዳት ከእንግሊዝ አገር ጋር በነፃ የመገበያየቱን ሀሳብ ፈፅመው ተቃውመዋል። ድንበሮቻቸውን ለርካሽ የገቢ ዕቃዎች በቀላሉ መክፈት የሚያመጣውን ውስብስብነት ተረድተዋል።

እንደ ሕፃናት ለሆኑ መሪዎች እነዚህ ውስብስብነቶች ግልፅ አይደሉም። ትኩረታቸው በግብርና ላይ እንደሚሆን የሚናገሩ መሪዎች አይፓዶችን፣ አይፎኖችን እና አይፖዶችን የሚሸጥ ሰው ብርቱካንና ካካዎ ከሚሸጥ ሰው ይልቅ የበለጠ የሚጠቀም የመሆኑን እውነታ በቀላሉ አይረዱትም።

ያነሰ ትርፍ፣ የበዛ ትርፍ ተግባራት፣ ቅንጅት፣ የአዲስ ነገር ፈጠራ፣ ፍጹም ገበያዎች፣ ፍጹም ያልሆኑ ገበያዎች የመሳሰሉትን ቃሎች ተጨባጭ ውጤት እንዴት አንድ ሕፃን ሊረዳ ይችላል? ይሁንና መላው ህዝብ እነዚህን ነገሮች በትምህርት ቤት ሳሉ ባጠኗቸው ነገር ግን እንዴት በአገሮቻቸው እንደሚተገበሩ በማያውቁ ሰዎች ነው የሚመሩት።

## 4. የሕፃን አመራር የሚገለፀው በጨዋታና በጭፈራ ነው።

> *እንግዲህ የዚችን ትውልድ ሰዎች በምን አስመስላቸዋለሁ? ማንንስ ይመስላሉ? በገበያ የሚቀመጡትን ልጆች ይመስላሉ፥ እርስ በርሳቸውም እየተጠራሩ። እንቢልታ ነፋንላችሁ አልዘፈናችሁምም፤ ሙሾ አወጣንላችሁ አላለቀሳችሁምም ይላል።*
>
> ሉቃስ 7፥31-32

አመራርን ልታጠና፣ አመራርን ልትረዳ እና ተገቢ የአመራር መርሆችን ልትተገብር ይገባል፣ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አስተሳሰብ ልትመራ ትችላለህ። ሕፃን መጫወት፣ መጫወት፣ መጫወት! ይወዳል። የመሪነት ጥበቦችን ካላዳበርክ ስለ ወሳኝ የመምራት ሥራ ሳይሆን ስለ መደሰት፣ መዝናናት፣ ክብረ በዓላትና ጭፈራዎች ብቻ እንደሚያስብ ሕፃን ትሆናለህ።

የሕፃን አእምሮ የነገሮችን የገንዘብ ወጪ እና የሚያስከትሉትን ውጤቶች ባለመረዳት የተሞላ ነው። መሪነትን መረዳት አለብህ፤

ምክንያቱም ጥሩ የአመራር ችሎታዎች በሌሉበት መሪ ተብለው የሚጠሩ ነገር ግን ሀብታቸውን ከቋሚ ነገሮች ይልቅ በዝግጅቶች በክብረ በዓላትና በአልባሳት ላይ የሚያጠፉ ሰዎች ነው የሚኖሩህ።

ሕፃናት ስለማይችሏቸውና ስለማያደርጓቸው ነገሮች ይናገራሉ። ሕፃናት ዘማሪዎች፣ የጠፈር ተመራማሪዎችና ሐኪሞች እንደሚሆኑ ቢናገሩም ከእነዚህ የቱንም አይሆኑም። የሕፃን ልጅ የአመራር አስተሳሰብ ያለው ሰው በርካታ ትርጉም የለሽ ኮንፈረንሶችን መካፈል፣ ንግግር ማድረግ እና ትላልቅ ግቦችን ማወጅ ይወዳል፤ ከእነዚህ ግን የትኛውንም አይተገብርም።

## 5. የሕፃን አመራር የሚገለፀው ብዙ አሻንጉሊቶችን ለማግኘት በመመኘት ይገለጣል።

*ንጉሥሽ ሕፃን የሆነ፥ መኳንንቶችሽም ማልደው የሚበሉ፥ አንቺ አገር ሆይ፥ ወዮልሽ!*

መክብብ 10፡16

መሪነትን ልታጠና መሪነትን ልትረዳ እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አስተሳሰብ ልትመራቸው ትችላለህ። የሕፃን የአመራር ዘይቤ ብዙ መጫወቻዎችን ለማግኘት ባለ ምኞት ይገለጣል።

ሕፃን ከማንም ይልቅ ብዙ መጫወቻዎችን ይፈልጋል፤ ሌላ ማንም ሰው መጫወቻ ባይኖረውም ግድ አይለውም። በአይቮሪ ኮስት ውስጥ ሁለት ሕፃናት በአሻንጉሊት እየተጣሉ ነው፣ ያም የአይቮሪ ኮስት ሕዝብ ነው። እንደ ሕፃን የሆነው መሪ አሻንጉሊቶችና መጫወቻዎች እንዲኖሩት ይወዳል ይህም ለበሰለው መሪ ምንም ማለት አይደለም።

ለዚህ ነው እንዲህ ዓይነት መሪዎች በመጀመሪያ የሚገዟቸው ነገሮች በአብዛኛው መኪና፣ የፕሬዘዳንት የግል አውሮፕላኖች እና ትላልቅ ቤቶች ናቸው። በልጅነት ሕልሞቻቸው የሚያደንቋቸውን ነገሮች በመስገብገብ ይሰበስባሉ። በቅርቡ በአንድ ድሀ የአፍሪካ አገር አዲስ መንግሥት ሥልጣን ላይ ወጣ። ብታምንም ባታምንም ለሳምንታት ዜናውን የተቆጣጠረው እነርሱ ስለሚጠቀሟቸው መኪናዎች የተነሳ ክርክር ነበር። አዲስ መጫወቻ እንዳገኘ ሕፃን ዋና ትኩረታቸው ሁሉም ሰው ስለሚይዘው መኪና ነበር። እንዲህ ዓይነት መሪዎች አይኖቻቸው ያሉት በገንዘብ፣ በመኪናዎች፣ በሴቶች (አሻንጉሊቶች) እና ትላልቅ ቤቶች ላይ ነው። በእርግጥ ንጉሷ፣ መሪዋ፣ ፕሬዚዳንቷ፣ መጋቢዋ፣ ጠቅላይ ሚኒስቴሯ፣ አዛዧ ሕፃን ለሆነ ምድር ወዮላት።

## 6. የሕፃን አመራር የሚገለፀው ለችግሮች ዕውን ሲሆኑ የሚችሉ ተግባራዊ መፍትሔዎችን ማግኘት ባለመቻል ነው፡፡

*ጠቢብ ድሀ ሰውም ተገኘባት፥* **ያችንም ከተማ በጥበቡ አዳናት** *ያን ድሀ ሰው ግን ማንም አላሰበውም።*

**መክብብ 9፡15**

*መሪነትን ልታጠና፣ መሪነትን ልትረዳ እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን ልትተገብር ይገበል፤ አለበለዚያ የሕፃን አመራር ለነገሮች መፍትሔ ማግኘት ባለመቻል ስለሚገለጥ ያለው ብቸኛ መፍትሔም አባትን ወይም እናትን መጥራት ስለሆነ ሰዎችን በሕፃን አስተሳሰብ ልትመራ ትችላለህ፡፡ ይበልጥ እንደ ሕፃን በሆንክ ቁጥር እናትህ ወይም አባትህ ሁሉን ነገር እንደሚያውቁና ለሁሉ ችግሮችህ መፍትሔ እንዳላቸው ታምናለህ፡፡ ልጆቼ ክፍሌ ውስጥ እንዳሉ በማመን ከፀሐይ በታች ያለውን ነገር ሁሉ ጠይቀውኛል፡፡ መቀስ፣ አግራፍ፣ ኘላስተር፣ ባትሪዎች፣ ቻርጀሮች፣ ገመድ፣ መርፌ፣ ገንዘብ እነዚህን ነገሮች የሆነ ቦታ እንደደበቅሁ ያስባሉ፡፡ ሕፃን መጽሐፍ ቅዱስ ጥበብ (ፍሮኒሞስ) ብሎ የሚጠራው ነገር ይጐድለዋል፡፡*

*አንድ ሰው በአመራር ላይ ሆኖ የሕፃን አእምሮ ሲኖረው ለሁሉም ችግር ያለው አንድ መፍትሔ ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ ሕፃን ችግሮችን የሚፈታው "ለአባቴ እናገራለሁ፤ አባቴ ይመታሃል" በማለት ብቻ ነው፡፡*

*ሕፃን መሪ ሲሰራ ከአንድ ሰው ወይም ከአንድ ቦታ ገንዘብን ስለማግኘት ብቻ ነው የሚያስበው፡፡ ችግር ሲገጥመው "የሀብት እጥረት ነው፡፡ እባክህ ካለህ ትንሽ ስጠኝ" ይላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች በአብዛኛው ለችግራቸው ብቸኛ መፍትሔ ገንዘብ እንደሆነ ያስባሉ፡፡*

*ደግሞ፣ ሕፃናት የበርን ቁልፍ እንኳን ማዞር አይችሉም፡፡ በአንዳንድ አገሮች ሕፃናት በሩን ለመክፈት ቁልፉን የማዞርን ቀላል ተግባር መወጣት ባለመቻል ሕፃናት ራሳቸው ላይ ሊቆልፉ ስለሚችሉ በመኝታ ክፍሎች በር ላይ ቁልፍ ማድረግ አይፈቀድም፡፡ በተግባር ነገሮችን መጠገን፣ ማሰናዳት፣ ማዘጋጀት፣ ማሸግና ማቀናበር አይችሉም፡፡ ብዙ ጊዜ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡*

*ብዙ የአፍሪካ አገሮች ለሕዝባቸው ችግር መፍትሔዎችን ማግኘት እንደማይችሉ አሳይተዋል፡፡ ብዙ የአፍሪካ አገሮች ለሕዝቡ ትክክለኛ ችግሮች ተጨባጭ መፍትሔዎችን ከማግኘት ብቃት ማነስ የተነሳ ዳግም ቅኝ ለመገዛት አሳማኝ ምክንያት ፈጥረዋል፡፡*

ለብዙ ሕፃናት ችግሮች ብቸኛው መፍትሔ ወላጅ እንደሆነ ሁሉ ጥቁር ሰው የሚያስበው ብቸኛው መፍትሔ ደግሞ በአብዛኛው ነጭ ሰው እና ገንዘብ ናቸው። ከሁሉም የባሰበት መሪ ደግሞ ችግሮቹ ሁሉ ገንዘብን በመቀበል እንደሚቃለሉ የሚያስብ ነው።

ዘመኔን በሙሉ በአፍሪካ ላሉ ሰዎች ተግባራዊ መፍትሔዎችን ጠቁሜአለሁ። በአብዛኛው ለእነርሱ ጅልነት መስሎ ነው የሚታያቸው። በቁጣ በእኔ ላይ ይነሳሉ፣ ችግሮችን መፍቻ የሚሆነውን ተግባራዊ ጥቆማዎቼንም አጥብቀው ይቃወማሉ።

ብዙ የአገር ሚኒስቴሮች እነርሱ ከሚቆጣጠሯቸው ውሎች ከመቶ የተወሰነ እጅ ተቆራጭ መቀበላቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። እነዚህ ገንዘቦች በመጪዎቹ ዓመታት ሊጠቀሟቸው በውጭ አገር የባንክ ሒሳቦች ውስጥ ይደበቃሉ። አንድ ቀን በአንድ ስብሰባ ላይ የአገር ሚኒስቴሮች በህጋዊ መንገድ ባለጠጋ እና ግብር ከፋይ እንዲሆኑ፣ እነርሱ ከሚያስተዳድሯቸው ብዙ ገንዘብ ካለባቸው ትላልቅ ውሎች ከመቶ የተወሰነ እጅ ያህል እንዲሰጣቸው ሀሳብ አቀረብኩ። ይህም ከሚሠሩት የመንግስት ሥራ ከሚገባቸው ገቢ ሌላ ተጨማሪ ገቢ እንዲሆን ነበር። በተጨማሪም ይህ በህጋዊ መንገድ ስለተገኘ ሀብታቸውን በአገሪቱ ውስጥ እንዲያቆዩ ያደርጋቸዋል አልኩ። የሚገርመው አእምሮውን እንደሳተ ሰው አድርገው ሰዎች በእኔ ላይ ተነሱብኝ። አንድ ሰው "ግብረ ገባዊነቱና ሕሊናው ይህንን እንዲያደርግ አይፈቅድለትም" አለ። ሰዎች በሀሳቡ ተናደዱ። ሆኖም በአፍሪካ ለሚያገኙት ሙስና እና ግብዝነት እጅግ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መፍትሔን ስለማንቀበል አሁንም በድብቅ ሚሊየነሮች የሆኑና ገንዘባቸውን በሚቻለው መጠን ከአፍሪካ አርቀው የሚያስቀምጡ ሚኒስቶሮች ያሏቸው አፍሪካዊ አገሮች አሉን።

ሕፃን ልጅ ንድፈ ሀሳባዊ ነው የአመራር ዘይቤውም እንዲሁ ለሁሉም ነገር ሊተገበሩ የሚችሉና ዕውን የሆኑ አካሄዶች የሌሉት በመሆን ይታወቃል።

ሊተገበርና ዕውን ሊሆን የሚችል አካሄድ የሌላቸው መሪዎች ረቂቅ፣ ገለልተኛ እና ምናባዊ ናቸው። ብዙ ነገሮች ለእነርሱ የሚቻሉ አይደሉም። እነርሱ ነገሮችን የሚከውኑባቸው መንገዶች በሁኔታው ውስጥ ሊተገበር የማይችሉ ናቸው። እነርሱ በመሬት ላይ ያለውን እውነታ ሊፈቱ ስለማይችሉ ሙዚየም ውስጥ ነው መቀመጥ ያለባቸው። በርካታ ስብሰባዎችና ስለ ፕሮጀክቶች አዋጪነትና አመቺነት የሚሰጡ ግምቶች ምንም የማይወጡ መሪዎችን ይገልጧቸዋል። ንድፈ ሀሳባዊ የሆነን ሰው መሪዋ ያደረገች አገር ወይም ቤተ ክርስቲያን ወዮላት። "በዚያን ጊዜ መንግሥተ ሰማያት

መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ሊቀበሉ የወጡ አሥር ቆነጃጅትን ትመስላለች፤

ከእነርሱም አምስቱ ሰነፎች አምስቱም ልባሞች ነበሩ"(ማቴዎስ 25፡1)

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ "ጠቢብ" የሚለው ቃል ፍሮኒማስ ከሚለው ቃል የመጣ ነው፡፡ ትርጓሜውም በተግባር ጠቢብ፣ አስተዋይ፣ ብልጥ ማለት ነው፡፡ ተግባራዊና አስተዋይ ያልነበሩት ወደ ሠርግ እራቱ አልደረሱም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ተግባራዊና አስተዋይ ያልሆኑት በዚህ ሕይወት አይሳካላቸውም፡፡

## 7. የሕፃን አመራር የሚገለፀው ምንም ባለመገንባት ነው፡፡

> እነርሱም ወደ ኢየሱስ መጥተው። ይህን ልታደርግለት ይገባዋል፤ ሕዝባችንን ይወዳልና ምኵራብም ራሱ ሠርቶልናል ብለው አጽንተው ለመኑት።
>
> ሉቃስ 7፡4-5

መሪነትን ማጥናት መሪነትን መረዳት እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ የሕፃን መሪነት የሚገለጠው ምንም ሳይገነቡ ነገሮችን በመጠቀም በመሆኑ ሰዎችን በሕፃን አእምሮ ልትመራ ትችላለህ፡፡ አገርህ በሕፃን የምትመራ ከሆነ ወዮላት፡፡

ሕፃን ገንቢ አይደለም፡፡ ሕፃን ጨዋታዎችን ይጫወታል ቀድሞ በተገነባውም ነገር ይጠቀማል፡፡ ምንም ካልተገነባ የሌለውን ባለመረዳት ባለው ይኖራል፣ ደግሞ ይደሰትበታል፡፡

የአፍሪካ ከተሞችና መንደሮች የተገነቡ አይደሉም፡፡ የአፍሪካ አገሮች መሬትን ለማግኘትና ልማትን መጀመር በማይችሉ ሰዎች የተሞሉ ናቸው፡፡ በምዕራባውያኑ ከተሞች፣ መንደሮች እና በአፍሪካውያኑ ከተሞችና መንደሮች መካከል ያለው ጉልህ ልዩነት የሕንፃዎች፣ መንገዶችና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮች አለመኖር ነው፡፡ የሕፃን አእምሮ ሲገዛ ሕንፃዎች፣ ልማት፣ ጥገና እና የመሠረተ ልማት አውታሮች የሉም፡፡

## 8. የሕፃን አመራር የሚገለፀው ትኩረት በማጣት ነው፡፡

> እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኰል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ **እየተፍገመገምን** ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊትአይገባንም፥
>
> ኤፌሶን 4፡14

መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳት እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ የሕፃን ልጅ አመራር

ትኩረት በማጣት የሚገለጥ ስለሆነ ሰዎችን በሕፃን አእምሮ ልትመራ ትችላለህ። ሕፃናት አጭር የትኩረት ቆይታ ነው ያላቸው። መሪ በዋና ተግባሮቹ ላይ ሳያተኩር ሲቀር ምንም ሊያደርግ አይችልም። ከጦርነት ቁልፍ መርሆች አንዱ ኃይሎችህን ሁሉ ልታሸንፍ ወደ ምትፈልገው ማሰባሰብ ነው። ለዚህ ነው አንድ ድልድይ የጦር ኃይሉ ዒላማ ቢሆን የአየር የየብስና የባህር ኃይሎች በሙሉ ያንን በማውደም ላይ የሚያተኩሩት። ኃይሎች ሁሉ ከፊት ለፊት ባለው ዒላማ ላይ እይታቸውን ማድረግ አለባቸው።

የአፍሪካ መሪዎች የተመረጡትን ሥራ ለመስራት ጊዜውም ሆነ ትኩረቱ ስለሌላቸው እምብዛም ውጤታማ አለመሆናቸው የሚያስደንቅ አይደለም። በአገሪቱ ችግሮች ላይ ከማተኮር ይልቅ ያለማቋረጥ የእርባና ቢስ ጐብኚዎች ልዑካንን በቢሮአቸው ይቀበላሉ።

ብዙ የአፍሪካ የመንግስት ቢሮዎች ውለታን፣ ሥራንና የተለያዩ እርዳታዎችን በሚፈልጉ ዘመዶች፣ ጓደኞችና አላፊ አግዳሚዎች የተጨናነቁ ናቸው።

በአፍሪካ የአገሪቱ መሪ ከሃይማኖተ መሪዎች እስከ ዘፋኞች፣ የእግር ኳስ ተጫዋቾች፣ ቀብር ነጋሪዎች፣ ጐብኚ ባሕላዊ መሪዎችና ሹማምንት፣ የአዳዲስ የእርዳታ ድርጅቶች መሪዎችና የራሳቸውን ልዩ ስብስብ ለመሥራት ከኘሬዘዳንቶች ጋር ፎቶ መነሳት የሚፈልጉን ሰዎች ሳይቀሩ የተለያዩ ዓይነት ልዑካንን የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ሲያደርጉ ማየት እንግዳ ነገር አይደለም።

## 9. የሕፃን አመራር የሚገለፀው በሥልጣን በመጣላት ነው።

**እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም።ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤**

**1ኛ ቆሮንቶስ 3፡1-2**

አመራርን ማጥናት፣ አመራርን መረዳትና ተገቢ የአመራር መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አስተሳሰብ ልትመራቸው ትችላለህ። አንድን ሕፃን ምንም ባልሆነ ነገር በጣም ሲደሰት ማየት እንግዳ ትዕይንት አይደለም። ሕፃናት በመኪና ውስጥ መስታወት ጥግ ሲቀመጡ፣ ገላቸውን መጀመሪያ ወይም መጨረሻ ሲታጠቡ ይደሰታሉ። ለትላልቆችም ምን ማለት ያልሆኑ ሥልጣኖች ያስደስቷቸዋል።

ዓይነተኛው አፍሪካዊ መሪ በደኸዩ ሰዎች የተሞሉ አቧራማ መንደሮች ላይ የተሾመ ነው። ለመሪነት ሥልጣንና ምንም እርባና

የሌለው የሆነ ነገር መሪ ለመሆን ይጣላል:: መሪው ማዕረጉንና ሥልጣኑን ይፈልጋል፤ ለሕዝቡ ግን ምንም አይሰራም::

## 10. የሕፃን አመራር የሚገለፀው እንደ ጣፋጭ ያሉ ማበረታቻዎችን በመፈለግ ነው::

አመራርን ማጥናት፣ አመራርን መረዳትና ተገቢ የአመራር መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አስተሳሰብ ልትመራቸው ትችላለህ::

ሕፃናት ማድረግ የሚገባቸውን እንዲያደርጉ ጣፋጭ፣ ስጦታዎች እና ማበረታቻዎች ይፈልጋሉ::

መጥፎ መሪዎችም እንዲሁ ሥራቸውን እንዲሰሩ ለማድረግ ተቆራጮች ከመቶው እጅ የሚታሰብ ነገር እና ጉቦ ይፈልጋሉ:: የሚገፋፋ ነገር ሳይኖር ምንም መሠራት እስከማይችል ድረስ ይህ የአፍ ቁስል ይዛመታል::

## 11. የሕፃን አመራር የሚመሰለው ሰዎች ምርጫው ቢኖራቸው ከእርሱ ሥር ሆነው ለመሥራት የማይፈልጉበት ነው::

> እስራኤልም ሁሉ ንጉሡ እንዳልሰማቸው ባዩ ጊዜ ሕዝቡ ለንጉሡ። በዳዊት ዘንድ ምን ክፍል አለን? በእሴይም ልጅ ዘንድ ርስት የለንም። እስራኤል ሆይ፥ ወደ ድንኳኖቻችሁ ተመለሱ ዳዊት ሆይ፥ አሁን ቤትህን ተመልከት ብለው መለሱለት። እስራኤልም ወደ ድንኳኖቻቸው ሄዱ።
>
> 1ኛ ነገሥት 12፥16

አመራርን ማጥናት፣ አመራርን መረዳትና ተገቢ የአመራር መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አስተሳሰብ ልትመራቸው ትችላለህ:: የሕፃን አመራር ምርጫው ቢኖራቸው ማንም በእርሱ ሥር ለመሥራት የማይፈልግበት ነው:: የሚያደርገውን እንደማያውቅ ሁሉም ያውቃሉ:: ይህ የአብዛኛው የአፍሪካ ሁኔታ ነው:: ምርጫው ቢኖራቸው ማንም በአብዛኛው የአፍሪካ ክፍል ውስጥ አይኖርም:: እንደ ሮብአም ከአስራ ሁለት ሰዎች አስራ አንዱ ሄደው ዘመዶቻቸውና በቀጥታ ተጠቃሚ የሆኑት ብቻ ይቀራሉ::

ከተወሰኑ ዓመታት በፊት በአፍሪካ የባሕር ዳርቻ ላይ ባለች ከተማ የሚገኝ የባሮች ማቆያ ግንብን እጎበኝ ነበር:: አስጎቢኚው ስራውን በሚገባ ያውቃል፣እናም የተያዙ ባሮች ይቀመጡበት ወደ ነበሩ የተለያዩ ክፍሎችና አስፈሪ ጨለማ ቤቶች ወሰደን:: በጉብኝቱ ማብቂያ ላይ "የማይመለሱበት በር" ወደተባለ ትንሽ በር መጣን::

በዚህ በር የሚያልፍ ማንኛውም ሰው ወደ አፍሪካ አፈር ዳግም እንደማይመለስ ነገረን። በባሮች መርከብ ላይ በባህር ይጠፋል ወይ ባሪያ ሆኖ በአሜሪካ ይሞታል።

"ዋው" አልኩኝ "አሰቃቂ ነበር" ቀጥዬም አንድን ጥያቄ ጠይቄ አብሮኝ የነበሩትን አፍሪካ አሜሪካዊ ጐብኚዎች ያስደነቀ መልስ አገኘሁ።

"ይህ የባሮች መርከብ ተመልሶ ወደዚህ የባሮች ማቆያ ግምብ በድጋሚ ባሮችን ወደ አሜሪካ ለመውሰድ ቢመጣ ሰው የሚወጣበት ይመስልሃል? በአፅንዖት "ተራ መርከብ ማለቴ አይደለም። እንደ ቱሪስት ሳይሆን እንደ ባሪያ ሊወስድህ ማለቴ ነው" አልኩ።

አስጐብኚው እንዲህ ሲል መለሰ "መርከቡ እስከሚችለው ድረስ ይሞላል፤ ከመጠን በላይ በመጫኑም ሊሰምጥ ይችላል። ባሮች ሆነን ወደ አሜሪካ ለመሄድ በመቻኮል ወደ መርከቡ ላይ እንወጣ ነበር።" አፍሪካ አሜሪካዊ ጐብኚዎቼ ጆሮአቸውን ማመን አቃታቸው።

ማንም ለምን ወደ አሜሪካ ባሪያ ሆኖ መሄድ ለምን ይፈልጋል? በአፍሪካ ከሚገኘው መልካም የአየር ሁኔታ ለማምለጥ እየሞከሩ ነው? አብዛኛው የተፈጥሮ ሀብት ከሚገኝባት ከሁሉም ባለጠጋ ከሆነች አህጉር ለመሸሽ እየሞከሩ ነው? መልሱ አይደለም ነው። አፍሪካን ወደ ተመሰቃቀለች ምድረበዳነት ከለወጣት ይኸውም ሕንፃዎች፣ መንገዶች፣ ሆስፒታሎችና ትምህርት ቤቶች የሌሉባት እንዲሁም አግባብ ያለው አመራር በሰፈነበት ቦታ ያለን መሠረታዊ እድገቶች እንዳይኖራት ካደረጉ የአመራር ዓይነት እያመለጡ ነው!

## 12. የሕፃን አመራር የሚገለፀው በአርቆ ማስተዋል እጦት ነው።

**በዚያን ጊዜ ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ፦ አባት ሆይ፥ የሰማይና የምድር ጌታ፥ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤**

**ማቴዎስ 11፡25**

ስለወደፊቱ የሚያስቡ ጥቂት ሕፃናት ናቸው። መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳትና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አእምሮ ለትመራ ትችላለህ።

ሕፃን በሁሉም ነገር ላይ የተሾመ ዕውርና አጭር ዕይታ ያለው ሰው ነው። አጭር ዕይታ ያለው ስትሆን ብልህነት ይጐድልሃል።

ሕፃን ለወደፊት የሚያስፈልገውን ነገር ሲያባክን አይታወቀውም። መሪነትን መረዳት አለብህ ምክንያቱም ጥሩ የአመራር ችሎታዎች በሌሉበት ትናንሽ ብክነቶችን በመዋጋት ገቢህን ልታሳድግ

አትችልምና። በሕፃን መሪዎች ወደሚመራ ትምህርት ቤት የሄደችን አንድን ወጣት ሴት አውቃለሁ። ይህ ትምህርት ቤት ከመቶ ሰባ ዓመታት በፊት ለሁለት መቶ ሃምሳ ሴት ተማሪዎች ነበር የተሰራው። ከመቶ ሰባ ዓመታት በኋላ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ተማሪዎችና በበፊቶቹ ተቋሞች እንዳሉ ናቸው ። መንግሥት ወይም የትምህርት ቤቱ ባለቤቶች ከመቶ ሰባ ዓመታት ቆይታ በኋላ የበለጠ አገልግሎት ማምጣት እንዳልቻሉ ራስህን መጠየቅህ አይቀርም።

## 13. የሕፃን አመራር የሚገለፀው በትንታኔና እና በአመክንዮአዊ አስተሳሰብ እጦት ነው።

ሕፃን መረጃን ወይም ሳይንስን ስለማይጠቀም የነገሮችን ትክክለኛ ሁኔታ አያውቅም። ክርስቶስ ግን ኃይል ብቻ አይደለም። ጥበብም ጭምር ነው። ኃይሉ ያስፈልገናል፤ ጥበቡም ያስፈልገናል። ያለ ትንታኔና አመክንዮአዊ ትንታኔ ሁሌም ድህነት አለ።

የሕፃን ዓይነት አመራር በሁሉ ነገር ትንታኔ-አልባ እና ምክንያት የሌለው ነው። ሕፃናት ጭራቆችን ይፈራሉ። በገና አባት፣ በሲንደሬላ እና የካርቱን ምስሎች ያምናሉ። እንደ ሕፃን የሆኑ መሪዎች በይበልጥ የሚመሩት በጥንቆላ ነው፤ የሚያስተዳድሩትም ከተግባራዊ አመክንዮአዊ አስተሳሰብ ይልቅ በዚሁ ነው።

## 14. የሕፃን አመራር የሚገለፀው የብዙ ነገሮችን ዋጋ ባለማወቅ ነው።

መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳት እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አእምሮ ልትመራቸው ትችላለህ። ሕፃን የብዙ ነገሮችን ዋጋ አያውቅም። ሕፃን የአጐት፣ አክስት፣ ጓደኞችና ዘመዶችን ዋጋ አይረዳም። ሕፃን ምን እንደሆኑ ስለማያውቅ መጻሕፍትህን ይቀድዳል፣ የከበሩ ብረቶችን ያወድማል፣ ቀለበቶችንና ጌጣጌጦችን ይወረውራል። የነገሮችንና የሰዎችን ዋጋ የማያውቁ ሰዎች ማህበረሰቡን ይገዛሉ። እንደዚህ ዓይነት መሪዎች ለተፈጥሮ ዋጋ አይሰጡም፣ ዛፎችንና ጫካ ይጨፈጭፋሉ፣ የባህር ዳርን እንደ ሽንትቤት ይጠቀማሉ። የሚታዩ የዱር አራዊትን ሁሉ ይገድላሉ። እነዚህ መሪዎች ለነገሮች ሆነ ለሰዎች ክብርና ዋጋ ሰለማይሰጡ ጫካዎችን እንደመነጠሩ እና እነርሱ እያዩ የዱር እንስሳት እንዲገደሉ ይፈቅዳሉ።

ሕፃናት በማንኛውም ቦታ ይፀዳዳሉ ስለ እንዲህ ዓይነት ነገሮችም ግድ የላቸውም። ሕፃናት በቤት ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ ያወድማሉ። የቤት እቃዎችን ይቆርጣሉ፣ በግድግዳ ላይ ይጽፋሉ።

# ሕፃን ዋጋ እንዳላቸው የማይቀበላቸው ስምንት ነገሮች

## 1. መልካም ስም

**መልካም ስም ከብዙ ባለጠግነት ይሻላል፥** መልካምም ሞገስ ከብርና ከወርቅ ይበልጣል።

ምሳሌ 22፡1

## 2. መልካም ሚስት

ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቍ እጅግ ይበልጣል።

ምሳሌ 31፡10

## 3. ስለክርስቶስ መነቀፍ

ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ፤ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና።

ዕብራውያን 11፡24-26

## 4. ቤተክርስቲያን

ከአእላፍ ይልቅ በአደባባዮችህ አንዲት ቀን ትሻላለች በኃጥኣን ድንኳኖች ከመቀመጥ ይልቅ፥ በእግዚአብሔር ቤት እጣል ዘንድ መረጥሁ።

መዝሙር 84፡10

## 5. ቃሉ

ከከንፈሩ ትእዛዝ አልተመለስሁም የአፉን ቃል በልቤ ሰውሬአለሁ።

ኢዮብ 23፡12

## 6. ጥበብ

ጥበብን ማግኘት ምንኛ ከወርቅ ይሻላል! ማስተዋልንም ማግኘት ከብር ይልቅ የሚመረጥ ነው።

ምሳሌ 16፡16

## 7. ነፍስህ

ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?

ማቴዎስ 16፡26

8. መጋቢህ

ወንድሞች ሆይ፥ በመካከላችሁ የሚደክሙትን በጌታም የሚገዙአችሁን የሚገሥጹአችሁንም ታውቁ ዘንድ፥ ስለ ሥራቸውም በፍቅር ከመጠን ይልቅ ታከብሩአቸው ዘንድ እንለምናችኋለን። እርስ በርሳችሁ በሰላም ሁኑ።

1ኛ ተሰሎንቄ 5፡12-13

## 15. የሕፃን አመራር የሚገለፀው ብዙ ባለማንበብ፣ ብዙ ባለማጥናትና መጻሕፍትን ባለመግዛት ነው፡፡

ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው።

ዕብራውያን 5፡14

መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳት እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አእምሮ ልትመራቸው ትችላለህ፡፡ ትናንሽ ሕፃናት ማንበብ ስለማይችሉ አያነቡም፡፡ እንደሕፃን የሆነ መሪ አያነብብም ራሱንም አያሻሽልም፡፡

## 16. የሕፃን አመራር የሚገለፀው የሌሎችን፣ በተለይም ከእይታህ ውጭ ያሉትን ሰዎች ፍላጐት ባለማሟላት ነው፡፡

ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ።

ገላትያ 6፡2

መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳት እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አእምሮ ልትመራቸው ትችላለህ፡፡ የሕፃን አመራር ለሌሎች በተለይ ከእይታህ ውጭ ያሉትን ፍላጐት ባለማሟላት ይገለጣል፡፡ ሌሎችን የሚንከባከቡት የበሰሉ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር የበሰሉት ሰዎች ሌሎችን እንዴት እንዲያገለግሉ እንደሚጠብቅባቸው እንመለከታለን፡፡

ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም።

ዕብራውያን 5፡12

ብዙ የአፍሪካ የአገር መሪዎች ወደ እነርሱ የሚወስዱ ጥሩ መንገዶች ያሏቸው ቤተ መንግሥቶች የተንጣለሉ ንጉሣዊ ቤቶች አሏቸው፡፡ የቧንቧ ውሃ እና የኤሌክትሪክ ኃይል አላቸው፡፡ የጤና ሁኔታቸውም በውጭ አገር ሐኪሞችና በላቁ ልዩ ባለሙያዎች ይጠበቃል፡፡ ልጆቻቸው በአውሮፓና በአሜሪካ በሚገኙ ምርጥ ትምህርት ቤቶች

*ይማራሉ። ይሁንና ለአገሪቱ ተራ ሰዎች ትምህርት ቤቶችን ማቅረብ አይችሉም። እንደ ሕፃን የሆነ መሪ ለቤተሰቡ ምርጥ ልዩ ስፔሻሊስቶችን ማቅረብ ቢችልም ለገዛ አገሩ ሰዎች ሆስፒታሎችን ማቅረብ አይችልም። እንደ ሕፃን የሆነ መሪ ለተቀረው አገር ውሃ እና የኤሌክትሪክ ኃይል ማቅረብ ባይችልም ለራሱ ግን በፕሬዚዳንታዊ ቤተመንግሥቱ ውስጥ ማቅረብ ይችላል።*

*ለሌላ ለማንም ማቅረብ የማይችሉና እንደ ሕፃን የሆኑት እነዚህ መሪዎች ለራሳቸው በሚያምር ሁኔታ የተሰሩ መንገዱን ተከትሎ የዘንባባ ተክል የተተከሉባቸው ወደ ቤተመንግሥታቸው የሚመሩ ጎዳናዎችን መሥራት ይችላሉ። የሚያሳዝነው ቀሪው የአገሪቱ ክፍል አቧራ እንዲጠጣ ተትቷል። ባጭሩ፣ ሕፃናት የሌላ የማንንም ፍላጐት አያሟሉም።*

## 17. የሕፃን አመራር ያለውን መጠቀም ባለመቻል ይገለጣል።

**ነገር ግን እላለሁ፥ ወራሹ ሕፃን ሆኖ ባለበት ዘመን ሁሉ፥ ምንም የሁሉ ጌታ ቢሆን ከቶ ከባሪያ አይለይም፥ነገር ግን አባቱ እስከ ቀጠረለት ቀን ድረስ ከጠባቂዎችና ከመጋቢዎች በታች ነው።**

**ገላትያ 4፡1-2**

*መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳት እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሕፃን አእምሮ ልትመራቸው ትችላለህ። የሕፃን አመራረ የሰጠሃቸውን በሚገባ ሊኖሩበት ባለመቻላቸው ይገለጣል። ለዚያ ነው ሰዎች ለሕፃናት ብዙ ገንዘብ የማይሰጡት። ብዙ ቁጥር ያለውን ገንዘብ ማስተዳደር አይችሉም። በአብዛኛው በርከት ያለ ገንዘብ ከመስጠትህ በፊት ሕፃኑ እስኪያድግ ትጠብቃለህ። ሰራተኛን በብዙ ገንዘብ እንደማታምነው ሁሉ ሕፃንን በብዙ ገንዘብ አታምነውም።*

*ለብዙ ገንዘብ ሊታመኑ እንደማይችሉ ደግመው ደጋግመው ስላረጋገጡ ብዙ የአውሮፓ እና የምዕራባውያን አገሮች ለአፍሪካ ገንዘብ መስጠት አቁመዋል።በአሜሪካ የጦር መርከብ ላይ ያለ አንድ ክሩዝ ሚሳኤል የብዙ የአፍሪካ አገሮችን ችግሮች ሊፈታ ይችላል። ነገር ግን አሜሪካ አንድ ክሩዝ ሚሳኤል ለአፍሪካዊት አገር መስጠት እምብዛም ለውጥ እንደማያመጣ ጠንቅቃ ታውቃለች።*

*በቅርብ፣ የአንድ ድሀ ምእራብ አፍሪካዊት አገር መሪ ፓሪስን ለሃያ ቀናት ጐበኘ። በባለ አምስት ኮከብ ሆቴል ውስጥ አርባ ሶስት ክፍሎችን ተከራይቶ ለሃያ ቀን የሆቴል ክፍያው ወደ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ዶላሮች ገደማ አወጣ። ይህ እንግዲህ የሚስቱና የአጃቢዎቹ የግዢ ወጪ የመሳሰሉትን ሌሎች ወጪዎችን*

ሳይጨምር ነው። ምን እያደረገ እንዳለ ባለመረዳቱ ሀብቱን ሁሉ እያባከነ ያለ ሕፃን መገኘቱን የፈረንሳይ መንግሥት አውቋል።

አፍሪካውያን ባላቸው ነገር ከመሥራት ይልቅ ብድር፣ እርዳታ እና ስጦታ ይለምናሉ። በተደጋጋሚ የአፍሪካ መሪዎች ገንዘብ ተስጥቷቸው ቢሆን ኖሮ ምን መስራት እንደሚችሉ ይናገራሉ ። ትናንሽ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን እንዴት እንደሚጀምሩ አያውቁም፤ ይልቁኑ ብዙ ገንዘብ ይጠራሉ። ያላቸውን አይኖሩበትም፤ ሀሳባቸው ግን በውጭ የገንዘብ ምራጮች ላይ ተንጠልጥሏል።

## ምዕራፍ 5

# የሴት አመራር

*ሕዝቤንስ አስገባሪዎቻቸው ይገፉአቸዋል፥ አስጨናቂዎችም ይሠለጥኑባቸዋል። ሕዝቤ ሆይ፥ የመሩአችሁ ያስቱአችኋል የምትሄዱበትንም መንገድ ያጠፉሉ።*

ኢሳይያስ 3፡12

መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳት እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሴት አስተሳሰብ ልትመራቸው ትችላለህ። በእርግጥ በመንፈስ ቅዱስ የተገራች ሴት የተወሰኑ መልካም ባሕሪያት ታንፀባርቃለች። ይሁንና በሴቶች በወንዶችና በሕፃናት መሐከል ልዩነቶች አሉ። ወንዶችም ሴቶችም ተመሳሳይ መጥፎ ነገሮች ያስቸግሯቸዋል። ይሁንና ወንዶች ለአንዳንድ ነገሮች በይበልጥ እንደሚያዘነብሉ ሁሉ ሴቶችም ለተወሰኑ ነገሮች የበለጠ ዝንባሌ ያላቸው ናቸው። ሴቶች መሪነትን የሚጣረሱ ባሕሪያትን ወደ ማሳየቱ ያዘነብላሉ።

## ወንዶችም ሴቶችም በክፋት የተዋጡ ናቸው

ባልበሰለ መልኩ የሴት መሪነት አደገኛ ነገር ነው። ያልተጣሩና ጩኸኝ የሆኑ ሴቶች ለአመራር ጉጂ፣ አበላሽ እና ጠንቅ በሆኑ በርካታ ባሕሪያት የተጠቁ ናቸው። እግዚአብሔር ሴቶችን ልዩ አድርጐ ነው የሰራቸው፤ ከአሰራራቸውም የተነሳ ወንዶች ከሚያዘነብሉባቸው ይልቅ ወደ ተወሰኑ ክፋቶች ያዘነብላሉ። ወንዶችም እንዲሁ በክፋት የተሞሉ ናቸው፤ ይሁንና እነርሱ የሚጠቁባቸው ክፋቶች መሪነት ላይ በተመሳሳይ አሉታዊ መንገድ ተፅዕኖ አያደርጉም።

ወንዶች ከሴቶች እጅግ በሚከፉ በመንፈሳዊና በባሕሪያዊ ችግሮች የተሞሉ ቢሆኑም እንኳን ሴቶች ያሏቸው ችግሮች ከወንዶቹ "ክፋት" ይልቅ መሪነት ላይ ተፅዕኖ ያደርሳሉ። ለምሳሌ፣ አንድ ሰው እንደ ካንሰር ያለ ከባድ በሽታ ቢኖርበትም መኪና የመንዳት ችሎታው ላይ ተፅዕኖ ላያመጣ ይችላል። ነገር ግን የውስጥ እግር ላይ የወጣ ቁስል (ከባድ ችግር ባይሆንም) የፍሬንና የነዳጅ መስጫ ፔዳሎችን የመርገጥ ችሎታህ ላይ ተፅዕኖ ያመጣል። ስለዚህ የውስጥ እግርህ ላይ ቁስል እያለ ማሽከርከር አስቸጋሪና አደገኛ ነው።

ለማለት እየሞከርኩ ያለሁት ማሽከርከር ላይ ከሌሎች ይልቅ ተፅዕኖ የሚያመጡ አንዳንድ እንከኖች፣ ሕመሞች ወይም ችግሮች አሉ ነው። ሴቶች ያሉባቸው ጉዳዮች ነገሮች ወንዶች እንደሚሰቃዩባቸው ጉዳዮች ነገሮች የከፉ ባይሆኑም እንኳን እውነታው የሴቶች ችግር የመምራት ችሎታቸውን በእጅጉ ይቀንሳል። ለምሳሌ ወንድ በተፈጥሮ በዓይን ምኞት ክፋት ይሰቃያል። ይህን ችግር ሰዎችን ወደራሱ እንዲያቀርብ ያደርጋል፤ ይህ ደግሞ ለአመራርና ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ጥሩ ነው። ሴት በስጋት የተጠቃች ናት፤ ይህም አስጊ እንደሆኑ የምታስባቸውን ሰዎች እንድታስወግድ ያደርጋታል። በግልፅ እንደሚታየው ሰዎችን በዙሪያህ ማሰባሰብን እንጂ ማጥፋትን ከሚጠይቀው ከመሪነት ጋር የሚጣረስ ነው።

በምለው ነገር አትናደድብኝ። መጽሐፍ ቅዱስን የፃፍኩት እኔ አይደለሁም። መቆጣት ከፈለግህ በእግዚአብሔር ተናደድ።

## 1. የሴት አመራር በከንቱነትና በጭቅጭቅ ይገለጣል

> በአንድ አሳብ በጌታ እንዲስማሙ ኤዎድያንን እመክራለሁ ሲንጤኪንንም እመክራለሁ።አንተም ደግሞ በሥራዬ አብረህ የተጠመድህ እውነተኛ ሆይ፥ እንድታግዛቸው እለምንሃለሁ፤ ስሞቻቸው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት ከቀሌምንጦስና ደግሞ ከእኔ ጋር አብረው ከሠሩት ከሌሎቹ ጋር በወንጌል ከእኔ ጋር አብረው ተጋድለዋልና።
>
> ፊልጵስዩስ 4፡2-3

መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳት እንዲሁም ተገቢ የአመራር መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ "የሴት አሉታዊ ባሕሪያት" የምትሰራውን ሥራ ሁሉ ያበላሽብሃል። አእምሮዋ በመንፈስ ቅዱስ የማይመራና በእግዚአብሔር ቃል የልጠራ ሴት ሀሳቧ በከንቱ ነገር የተሞላ ነው። እነዚህ "ሴት" መሪዎች ዋና ጉዳዮች ሳይነኩ እንዳሉ በማይረቡ ጉዳዮች ላይ እንደሚከራከሩ ታስተውላለህ።

ቤተ መንግሥት ከገነባች በኋላ አኒቨርሰሪ ካስትል ወይም ኃይት ሃውስ ካስትል ይባል በሚለው ላይ ለወራት የተከራከረችን አንዲት አፍሪካዊት አገር አውቃለሁ። ተቃዋሚዎቻቸው ሰለገነቡት አዲሱ መንግሥት በተገነባው ፕሬዚደንታዊ ቤተ መንግሥት አልገባም ያለበትን አፍሪካዊ አገር አውቃለሁ።

> ዮሐንስ ሄሮድስን። የወንድምህ ሚስት ለአንተ ልትሆን አልተፈቀደም ይለው ነበርና። ሄሮድያዳ ግን ተቃውማው ልትገድለው ትፈልግ ነበር አልቻለችም፤
>
> ማርቆስ 6፡18-19

አእምሮዋ በመንፈስ ቅዱስና በእግዚአብሔር ቃል ቁጥጥር ሥር ያልሆነና ያልጠራ ሴት አስተሳሰቧ በጠብ ይታወቃል፡፡ እንዲህ ያሉ መሪዎች ከሌሎች ጋር ያለማቋረጥ በአንድ ወይም በሌላ ጉዳይ ጠብ ላይ ናቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያንን የምትመራው ሴት ብትሆን መጋቢው ያለማቋረጥ ከሌላ ቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ጋር ይነታረካል፡፡

የሆኑ መጋቢዎች በቴሌቪዥን ላይ አንዱ ሌላውን የእግዚአብሔርን ኃይል ሳይሆን ጥንቆላውን ነው የምትጠቀመው በሚል ሲካሰሱ ተመልክቻለሁ፡፡ በግልፅ ተጨቃጨቁ እንዲሁም አንዱ ሌላውን በመጋፈጥ እስከ መንፈሳዊ ፍልሚያ ድረስ ደረሱ፡፡ ራሳቸውን መሳቂያ አደረጉ! እነዚህ መልከ መልካም መጋቢዎች በሰው ሁሉ ፊት እንደ ሴት ሲሆኑ ማየት የሚያሳዝን ነበር፡፡

## 2. የሴት አመራር በቅናት ይገለጣል

ስመጣ፥ እንደምወደው ሳትሆኑ አገኛችሁ ይሆናል እኔም እንደምትወዱት ሳልሆን ታገኙኝ ይሆናል ብዬ እፈራለሁና፤ ምናልባት ክርክር ቅንዓትም ቁጣም አድመኛነትም ሐሜትም ማሾክሾክም ኩራትም ሁከትም ይሆናሉ፤

2ኛ ቆሮንቶስ 12፡20

የካህናት አለቆች በቅንዓት አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና።

ማርቆስ 15፡10

መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳት እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ "የሴት አሉታዊ ባሕሪያት" ውሳኔዎችህን ያበላሻሉ፡፡ አእምሮዋ በመንፈስ ቅዱስ የማይመራና በእግዚአብሔር ቃል የልጠራ ሴት አስተሳሰቧ በቅናት የተቃኘ ነው፡፡ እንደ ሴት የሚንቀሳቀስ መሪ በቅናት ወደ መነዳት ያዘነብላል፡፡ በሴት መሪዎች የሚመሩ አገራት በቅናት የሚነዱ ፖሊሲዎች ነው ያሏቸው፡፡ ሀብታም ሰዎች ባለጠጋ በመሆናቸው ምክንያት ከአገር ተሰደው እንዲወጡና እንዲሰቃዩ ይደረጋሉ፡፡ ኃብታሞች ሀብታቸውን መደበቅ ያለባቸው አገሮች አውቃለሁ፡፡ ሥልጣን የሚረከበው መንግሥት ሁሉ በቀድሞው አገዛዝ ሥር የበለፀጉትን ሰዎች ፈልጋልና፡፡

## 3. የሴት አመራር ኃይልንና ሥልጣንን ያለ አግባብ በመጠቀም ይገለጣል

ለወልደ አዴርም መልእክተኞች። ለጌታዬ ለንጉሥ። ለእኔ ለባሪያህ በመጀመሪያ የላክህብኝ ሁሉ አደርጋለሁ ይህን ግን አደርገው ዘንድ አይቻለኝም በሉት አላቸው። መልእክተኞችም ተመልሰው ይህን አወሩለት። ወልደ አዴርም። ለሚከተለኝ ሕዝብ

የሰማርያ ትቢያ ጭብጥ ጭብጥ ይበቃው እንደ ሆነ፥ አማልክት ይህን ያድርጉብኝ ይህን ይጨምሩብኝ ብሎ ላከበት።የእስራኤልም ንጉሥ መልሶ፦ በቃ ለሰልፍ የሚታጠቅ ጋሻ ጦሩን እንደሚያወልቅ አይመካ አለው።ወልደ አዴርም ያን ነገር በሰማ ጊዜ ከነገሥታቱ ጋር በድንኳኑ ውስጥ ይጠጣ ነበር ባሪያዎቹንም። ተሰለፉ አላቸው እነርሱም በከተማይቱ ትይዩ ተሰለፉ።እነሆም፥ ነቢይ ወደ እስራኤል ንጉሥ ወደ አክዓብ ቀርቦ። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ይህን ብዙ ጭፍራ ሁሉ ታያለህን? እነሆ፥ ዛሬ በእጅህ አሳልፌ እሰጠዋለሁ፥ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃለህ አለ።አክዓብም። በማን? አለ እርሱም፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በአውራጆቹ አለቆች ጒልማሶች አለ እርሱም፦ ሰልፉን ማን ይጀምራል? አለ እርሱም፦ አንተ አለው።የአውራጆቹንም አለቆች ጒልማሶች ቈጠረ፥ ሁለት መቶም ሠላሳ ሁለት ነበሩ ከእነርሱም በኋላ ሕዝቡን ሁሉ፥ የእስራኤልን ልጆች ሁሉ፥ ቈጠረ፥ ሰባትም ሺህ ነበሩ።ቀትርም በሆነ ጊዜ ወጡ ወልደ አዴር ረዳቶቹም ሠላሳ ሁለቱ ነገሥታት እየጠጡ በድንኳን ውስጥ ይሰከሩ ነበር።

1ኛ ነገሥት 21፡9-16

መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳት እና ተገቢ የመሪነት ተግባሮችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሥልጣንን አላግባብ መጠቀም የምታደርገውን ነገር ሁሉ ያበላሽብሃል፡፡

አእምሮዋ በመንፈስ ቅዱስ የማይመራና በእግዚአብሔር ቃል ያልጠራ ሴት ሀሳቧ ኃይልንና ሥልጣንን ያለ አግባብ በመጠቀም የተቃኘ ነው፡ ፡ እንደ ሴት የሆነ መሪ ሥልጣንን ያለ አግባብ የመጠቀም ዝንባሌ አለው፡፡

## ሞቡቱ፡- ለፓርላማ አባል ለሆነው መርቪን ዲማሊ

“ግልፅ እንደሆነው በአውሮፓ የባንክ አካውንት የለኝም ብል መዋሸት ይሆንብኛል፣ አለኝ፡፡ በባንክ አካውንቴ ሊጠቀስ የሚችል ገንዘብ የለኝም ብል ውሸት ይሆንብኛል፡፡ አለኝ

አዎን፣ በቂ የገንዘብ መጠን አለኝ፡፡

ያም ሆኖ፣ በአጠቃላይ በግምቱ ከ50 ሚሊዮን ዶላር ትንሽ አነስ የሚል አለኝ፡፡

በእንዲህ ዓይነት ትልቅ አገር ውስጥ ለሃያ ዓመታት የአገሪቱ መሪ ሆኖ ለተቀየበት ታዲያ ይህች ምንድን ናት?

1998 ኤሊዮት እና ዳይማሊ፣ገፅ 25

## 4. የሴት አመራር በክፋነት ይገለጣል

ሄሮድያዳ ግን ተቃውማው ልትገድለው ትፈልግ ነበር አልቻለችም፤ ሄሮድስ ዮሐንስ ጻድቅና ቅዱስ ሰው እንደ ሆነ አውቆ ይፈራውና ይጠባበቀው ነበር፤ እርሱንም ሰምቶ በብዙ ነገር ያመነታ ነበር፤በደስታም ይሰማው ነበር። ሄሮድስም በተወለደበት ቀን ለመኳንንቱና ለሻለቆቹ ለገሊላም ሹማምንት ግብር ባደረገ ጊዜ ምቹ ቀን ሆነላትናየሄሮድያዳ ልጅ ገብታ ስትዘፍጥረትን ሄሮድስንና ከእርሱ ጋር የተቀመጡትን ደስ አሰኘቻቸው። ንጉሡም ብላቴናይቱን። የምትወጂውን ሁሉ ለምኚኝ እሰጥሽማለሁ አላት፤የመንግሥቴ እኩሌታ ስንኳ ቢሆን የምትለምኚውን ሁሉ እሰጥሻለሁ ብሎ ማለላት።ወጥታም ለእናትዋ። ምን ልለምነው? አለች። እርስዋም፡- የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ አለች። ወዲያውም ፈጥና ወደ ንጉሡ ገብታ። የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ በወጭት አሁን ልትሰጠኝ እወዳለሁ ብላ ለመነችው።ንጉሡም እጅግ አዝኖ ስለ መሐላው ከእርሱም ጋር ስለ ተቀመጡት ሊነሣት አልወደደም።

ማርቆስ 6፡19-26

መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳት እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን በሴት ዘይቤ እና አእምሮ ልትመራ ትችላለህ።

አእምሮዋ በመንፈስ ቅዱስ የማይመራና በእግዚአብሔር ቃል የልጠራ ሴት አስተሳሰቧ በክፋት የተቃኘ ነው። ስለዚህ እንደሴት የሆነ መሪ ወደ ክፋት ያዘነብላል።

የሂትለርና የስታሊን ጭካኔ ይህንን መንገድ የተከተሉ መሪዎች ምሳሌ ናቸው።

## 5. የሴት አመራር በፍርሀቶችና ባለመረጋጋት ይገለጣል

ሣራም ግብፃዊቱ አጋር ለአብርሃም የወለደችለትን ልጅ ሲስቅ አየችው።አብርሃምንም፡- ይህችን ባሪያ ከነልጅዋ አሳድድ የዚህች ባሪያ ልጅ ከልጄ ከይስሐቅ ጋር አይወርስምና አለችው።ይህም ነገር በአብርሃም ዘንድ ስለ ልጁ እጅግ ችግር ሆነበት። እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፡- ስለ ባሪያህና ስለ ብላቴናው አትዘን ሣራም የምትነግርህን ቃል ሁሉ ስማ በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃልና።የባሪያይቱን ልጅ ደግሞ ሕዝብ አደርገዋለሁ፥ ዘርህ ነውና። አብርሃምም ማልዶ ተነሣ፥ እንጀራንም ወሰደ፥ የውኃ አቁማዳንም ለአጋር በትከሻዋ አሸከማት፥ ብላቴናውንም ሰጥቶ አሰወጣት እርስዋም ሄደች በቤርሳቤህም ምድረ በዳ ተቅበዘበዘች።

ዘፍጥረት 21፡9-14

መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳት እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ አለማመንህ የምታደርገውን ሁሉ ያበላሻል።

አእምሮዋ በመንፈስ ቅዱስ፣ በቃሉ ያልጠራ ወይም ራስ በሆነ ሰው ቁጥጥር ሥር ያለሆነች ሴት አስተሳሰቧ ጥንካሬአቸውን ለጋራ ጥቅም ከመጠቀም ይልቅ አስጊ ሰዎችን ለማስወገድ ባለ ምኞት የተሞላ ነው። ስለዚህ እንደ ሴት የሆነ መሪ አለመረጋጋቱን ለእርሱ አስጊ እንደሆኑ የሚያስባቸውን ሰዎች በማስወገድ ይገልጣል።

ፍርሀት እጅግ መጥፎ ነገር ነው። ጥንቆላ፣ አስማት፣ ጣኦትን ማምለክና ነፍስን ማጥፋት ጋር ተመሳሳይ ፍሬዎች ስላሉት እኩል ደረጃ ላይ ነው የተቀመጠው። ፍርሀት በአብዛኛው አለመረጋጋት ይባላል።

## 6. የሴት አመራር ለማስደነቅ በመሞከር ፍላጐት ይገለጣል

**ከሰው ክብርን አልቀበልም፤...**

**ዮሐንስ 5፡41**

መሪነትን ማጥናት፣ መሪነትን መረዳት እና ተገቢ የመሪነት መርሆችን መተግበር አለብህ፤ አለበለዚያ ሰዎችን ለማስደነቅ ያለህ ፍላጐት የምታደርገውን ነገር ያበላሽብሃል። አእምሮዋ በመንፈስ ቅዱስ፣ በቃሉ ያልጠራ ወይም ራስ በሆነ ሰው ቁጥጥር ሥር ያልሆነ ሴት አመራር መልካም አድናቆትን ለማትረፍ ባለ ተነሳሽነት የተቃኘ ነው። ሴቶች በእውነታው ትክክል ያልሆነን ነገር እንደሆነ አድርገው ማቅረብ ይፈልጋሉ። ሴቶች በገፅታቸው አሳሳች ወደ መሆን ያዘነብላሉ። በጥሩ ሁኔታ ለብሰው የምታያቸው ቆንጆ ሴቶች መታጠብ ላይወዱ ይችላሉ።

## ምዕራፍ 6

# የስልታዊ እርምጃዎች ባለቤት ሁን

### ስትራቴጂ (ስልት) የተወሰነን ግብ ለመምታት የሚካሄዱ ተከታታይ የብልጠት ዘዴዎችና እርምጃዎች ናቸው፡፡

## ስለ ስልት ማወቅ ያለብህ ሰባት ነገሮች

### 1. ታላቅ ወይም ወሳኝ መድረሻ ያለው ነገር ሁሉ ወደዚያ የሚያደርሱ የተወሰኑ እርምጃዎችን ይጠይቃል፡፡

ጥሩ መሪ የትኛውም ታላቅ ስኬት አንድ እርምጃ ብቻ እንደማያካትት ሊቀበል ይገባዋል፡፡ ተከታታይ ደረጃዎች፣ ተከታታይ እንቅስቃሴዎች ወይም ተከታታይ ብልሀቶችን ያካትታል፡፡ እነዚህ ተከታታይ እርምጃዎች እንቅስቃሴዎችና ብልሃቶች ስልት በመባል ይታወቃሉ፡፡

ስልት የተወሰነ ግብን ለመምታት የሚደረጉ ተከታታይ እንቅስቃሴዎች በሚል ይገለፃል፡፡ ሞኞች ስልትን ይቃወማሉ፡፡ የሚፈልጉት የሆነ ነገር እንዲደረግላቸው ብቻ ነው፡፡ ኃላፊነቱን ከወሰዱ ከአንድ እርምጃ በላይ የሚጠይቅ ምንም ነገር አይፈልጉም፡፡

### 2. ኃላቀር መሪዎች ነገሮችን ለማሳካት ምንም እርምጃዎችን አይወስዱም፡፡ ኃላቀር መሪዎች አንድ ነገር እንደሚደረግላቸው በመጠበቅ ውስጥ ነው የሚኖሩት፡፡

አስተሳሰባቸው የሆነ ሰው የሆነ ነገር ሊከፍላቸው እንደሚገባ እና የሆነ ሰው የሆነ ነገር ለእነርሱ እና ስለ እነርሱ ሊያደርግላቸው እንደሚገባ ነው፡፡ ይህ በአብዛኛው ቀደም ሲል ባሮች የነበሩ ሰዎች አስተሳሰብ ነው፡፡ እንዲሁም ይህ ቅኝ ተገዝተው የነበሩና ሌሎች ስለ እነርሱ ሲያስቡላቸው የለመዱ ሰዎች አስተሳሰብ ነው፡፡ የሆነ ነገር ሊሰጣቸው ወይም ሊያስረክቧቸው እንደሚገባ ነው የሚረዱት፡፡ እንዲህ ዓይነት መሪዎች የሆነ ሥፍራ ያለን በጐ አድራጊ ልብ እንደሚነካ ተስፋ በማድረግ ያለማቋረጥ እርዳታን የሚጠይቅ እና

ሐዘናቸውን፣ ጉድለቶቻቸውን እና እጥረቶቻቸውን የሚገልፁ ንግግሮቻቸውን ያነብባሉ።

ከብዙ ዓመታት በኋላ እንኳን ያሉበት አስከፊ አዘቅት እና አሳዛኝ ሁኔታ በዚህ ራስ ወዳድ ዓለም ውስጥ የብዙዎችን ልብ እንደማይነካ አይረዱም። ዜሮ-እርምጃ ያላቸው መሪዎች ማንም ለፍቶ ያገኘውን ሀብት በጭኖቻቸው ላይ እንደማይዘረግፍ ለመረዳት ዓመታት ይፈጅባቸዋል። እንደዚህ ዓይነት መሪዎች ባለጠጋ ጉብኚዎች፣ የዕርዳታ ድርጅት (NGO) ዳይሬክተሮች፣ ዘፋኞች፣የእግር ኳስ ኮከብ ተጫዋቾችና ምዕራባውያን ዲፕሎማቶች ሲጎበኟቸው በአእምሮአቸው ጓዳ የሆነ ነገር እንደሚሰጣቸው ወይም እንደሚደረግላቸው ስለሚጠብቁ ደስ ይላቸዋል።

## 3. መጥፎ መሪዎች ወደ ግቡ አንድ እርምጃ ብቻ ነው መውሰድ የሚፈልጉት

መጥፎ መሪዎች ከባሱት መሪዎች ጥቂት የማሻሉት ወደግባቸው ቢያንስ አንድ እርምጃ ስለሚወስዱ ነው። ይሁንና ብዙ ነገሮች አንድ እርምጃ በመውሰድ አይከናወኑም። ብዙ ሰዎች የጸሎትን እርምጃ ይወስዳሉ።

ብዙ አፍሪካውያን በየዓመቱ የመፆምና የመፀለይና አንድ እርምጃ ይወስዳሉ።

ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባላት የበለፀጉ ለመሆን አንድ የመዝራት እርምጃን ይወስዱሉ። ነገር ግን አንድ እርምጃ የትም አያደርስም።

ይህንን መጽሐፍ እያነበብክ በወንበርህ ላይ እንደተቀመጥክ አንድ እርምጃ ብቻ ብትራመድ ምን ያህል ትርቃለህ?

በአንድ እርምጃ መፀዳጃ ቤት እንኳን አትደርስም!

ሰዎች ግን ማድረግ የሚፈልጉት ይህንኑ ነው። ወደ ግባቸው አንድ እርምጃ ብቻ መውሰድ ይፈልጋሉ። በአንድ እርምጃ ብቻ የሚደርሱ ካሉ ጥቂት ነገሮች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ “.... ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ.....” ይላል። አንድን ነገር ቆንጆ ወይም ስኬታማ ለማድረግ ብዙ ነገሮች በአንድነት ይሰራሉ። ብዙ ነገሮች አንድ አዲስ ወጥ ወይም ሾርባ ለመስራት በሆነ መንገድና በተወሰነ የሰዓት ቅደም ተከተል ይደባለቃሉ። ቆንጆ ወጥ እንዲኖርህ የሚያደርገው አንድ ነገር (ጥሩ ሥጋ) መኖሩ ብቻ አይደለም። ብዙ ነገሮች በአንድነት ይሰራሉ።

አንድ እርምጃ የትም ስለማያደርስህ የተወሰደው አንድ እርምጃ እንዳልሰራ ተደርጎ ይታያል። በዚህ ምክንያት የመፀለይን አንድ

እርምጃ ወይም የመፃምን አንድ እርምጃ ወይም ዘርን የመዝራትን አንድ እርምጃ የተራመዱ ሰዎች ያ አንዱ እርምጃ አይሠራም በማለት ያጉረመርማሉ፡፡

## 4. ግቡ በተለቀ ቁጥር መውሰድ የሚኖርብህ እንቅስቃሴዎችንና እርምጃዎችም ይጨምራሉ፡፡

ግቡ በተለቀና በይበልጥ ለአንተ የማይቻል በሆነ ቁጥር እዚያ ለመድረስ የበዙ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርብሃል፡፡ ትላልቅ ግቦችን ለማሳካት ብዙ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርብሃል፡፡

## 5. በስልት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ እርምጃ እምነትና ትዕግሥትን ይጠይቃል፡፡

በስልት ጥበብህ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ጥቂት እርምጃዎች ከሁሉም የላቀ ትዕግሥትና ከሁሉም የላቀ እምነት ይጠብቀብሃል፡፡ ከምትወስዳቸው እርምጃዎች አንዱ የራስህ የጥሞና ጊዜ እንዲኖርህ ከሆነ ውጤቱ በሕይወትህ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያመጣ በማመን ሳታሰልስ የጥሞና ጊዜ እንዲኖርህ ብዙ እምነት እና ትዕግሥት ያስፈልግሃል፡፡

> በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ፥ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን።
>
> ዕብራውያን 6፡12

## 6. ወደ አንድ ሥፍራ ለመድረስ ወይም የትኛውንም ነገር ለማሳካት የታሰቡ ስልቶች ወደ አራት እርምጃዎች ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ በአራት እርምጃዎች በዚህ ዓለም ወደ የትኛውም ሥፍራ ወይም ሰው መድረስ ትችላለህ፡፡

## 7. የሚያስፈልገውን ያህል ብዛት ያላቸውን ስልታዊ እርምጃዎች የሚወስድ ሰው ሁን፡፡ ዜሮ እርምጃ ያለው ሰው ከመሆን ወይም አንድ እርምጃ ብቻ ያለው ሰው ከመሆን ወደ ሌላኛው ተሸጋገር፡፡

# የያህዌ ሰባት ስልቶች

### 1. ምድርን የመሙላት ስልት

እርምጃ 1 ወንድን በገነት ማስቀመጥ

እርምጃ 2 ሴትን በገነት ማስቀመጥ

እርምጃ 3 ለወንዱ ምኞትና የወንድ የወሲብ ዕጢን መስጠት

እርምጃ 4 ሴቷን ወደ ማትወደው ነገር እንድትሳብ መርገም

## 2. እስራኤልን የማዳን ስልት

እርምጃ 1 አንድ ሌዋዊ ሌላዋን እንዲወድ ማድረግ

እርምጃ 2 የሚወለደው ሕፃን በፈርኦን ሴት ልጅ እንዲገኝ ማድረግ

እርምጃ 3 ሕፃኑ ልጅ በአመራር እንዲሰለጥንና ቤተ መንግሥትንና መሪነትን እንዲለምድ ማድረግ

እርምጃ 4 ወደ ምድረበዳ እንዲሰደድ ማድረግ በዚያ ማሰልጠን ትሁትም ማድረግ

እርምጃ 5 በምድረበዳ መገናኘትና መቀባት

እርምጃ 6 ብዙ ተአምራት መሥራት እንዲችሉ የፈርኦንን ልብ ማደንደን

እርምጃ 7 ሙሴን ፅድቅንና ሕግን ለማስተማር መጠቀም

## 3. ዓለምን የማዳን ስልት

እርምጃ 1 እስራኤላውያን በጠላቶቻቸው እንዲቀጡና ለሙሴ ሕግ የተሰጡ እንዲሆኑ ማድረግ

እርምጃ 2 ልጁን ከድንግል እንዲወለድ ወደ ዓለም መላክ

እርምጃ 3 የእግዚአብሔር የመጀመሪያ እርምጃ ትክክለኛውን ጊዜ መጠበቅ ነበር። እግዚአብሔር ትክክለኛውን ጊዜ ከጠበቀ በኋላ ልጁን ኢየሱስን ላከ።

## 4. ዲያቢሎስ በሰው ልጅ ላይ ያለውን ጉልበት የማውደሚያ ስልት

እርምጃ 1 ቃሉን እንዲሰብክና ለዓለም ስለ መንግሥተ ሰማያት እንዲናገር ኢየሱስን መላክ

እርምጃ 2 በሁሉም መንገድ በዲያብሎስ እንዲፈተንና እንዲጕመጅ መተው

እርምጃ 3 ዲያብሎስን እንዲያሸንፍና በአጋንንት ሁሉ ላይ የበላይነቱን እንዲያሳይ ማድረግ

እርምጃ 4 የማይጠፋን ፍቅር እንዲያሳይ ማድረግ

እርምጃ 5 ደሙን እንዲያፈስና እንደ እኛ ዓይነት ኃጢያተኞች ወደ መንግሥተ ሰማይ ያለ ጥያቄ መግባት የሚገባንን ሕጋዊ ምክንያት ማቅረብ

እርምጃ 6 ስለዚህ መሥዋዕት ሰዎች ለዓለም ሁሉ እንዲናገሩ መላክ።

እርምጃ 7 ኃጢያተኞችና ደካሞች እንዲሁም የወደቁ ሰዎች ኃይለኛውን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል እንዲያውጁ ለመርዳት መንፈስ ቅዱስን መላክ።

## 5. ሰው በራሱ መንግሥተ ሰማይ እንዳይደርስ የታገደበት ስልት።

እርምጃ 1 ሰዎች እያካሄዱት ስላለው ሥራ ምንም አለማለት

እርምጃ 2 ለሁሉም ሰው የተለያየ ቋንቋ መስጠት

እርምጃ 3 እርስ በእርሳቸው እንዳይግባቡ ማድረግ

እርምጃ 4 እንዲጣሉ ማድረግ

እርምጃ 5 ይህ የባቢሎን ፕሮጀክት በራሱ እንዲገታ ያደርጋል።

## 6. የወንጌልን መልዕክት ለመላው ዓለም የመላክ ስልት

እርምጃ 1 በአንድነት ለሶስት ዓመታት እነርሱን ማሰልጠን

እርምጃ 2 እነርሱን ማስተማር

እርምጃ 3 ወጥተው እንዲሄዱ በመላክ ተግባራዊ ልምምድ እንዲያገኙ ማድረግ

እርምጃ 4 እንዴት መሥዋዕትነት እንደሚከፍሉ ማሳየት

እርምጃ 5 ወደ ዓለም መላክ

## 7. ክርስቶስ እንዲታወቅ የማድረጊያ ስልት

እርምጃ 1 መልካምና መጥፎው እንዲያድጉ መተው

እርምጃ 2 ሙሉ በሙሉ ሲያድጉ እንዲታጨዱ ማድረግ

እርምጃ 3 የሮማ መንግሥት ዓለምን ሁሉ እንዲገዛ መተው

እርምጃ 4 የሮማ ገዢን መለወጥ

*ምዕራፍ 7*

# በዚህች ዓለም ውስጥ ካሉት ምርጥ መሪዎች አንዱ ለመሆን ወስን

ለአገልግሎት ተጠርቻለሁ የሚል እምነት ካለህ፣ በእርግጥም ለመሪነት ተጠርተሃል። ለዚህ ነው ይህ መጽሐፍ ለሕይወትህ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው። መጽሐፉን ካነበብህ በኋላ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም መሪ ትሆናለህ። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክቱ መልካም መሪ ለመሆን የሚያስችሉትን አንዳንድ ነገሮችን እንዲያደርግ ነግሮታል። መልካም የሆኑ መሪዎችና መጥፎ የሆኑ መሪዎችም አሉ። መልካም አገልጋይ ለመሆን ወስን!

. . . የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም አገልጋይ ትሆናለህ።

1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡6

በአገልግሎትህ ስኬታማ ለመሆን ከፈለግህ፣ ስለ አመራር መማር አለብህ። ወደ መጽሐፍ መደብር በምሄድበት ጊዜ ሁሉ ፣ ራሴን የማገኘው የመሪነት መጽሐፍ ወደሚገኝበት መደርደሪያ ስሳብ ነው። መሪነትን አስመልክቶ የተጻፉትን እጅግ በርካታ መጻሕፍት አንብቤአለሁ። ይህን በጣም አስፈላጊ ርእስ አጥንቼአለሁ። ምክንያቱም የተዋጣለት መሪ መሆን እሻለሁና። መልካም ነገሮች ልክ እንደ በሰለ ማንጎ ከዛፍ የሚለቀሙ እንዳይመስልህ። መማር ያለብህን ነገር ሁሉ በትጋት ማጥናትና ማግኘት ይኖርብሃል።

ለሁላችንም ግልጽ እንደሆነው በዙሪያችን ብዙ መልካም መሪዎች አይገኙም። ከተገኘ ግን እኔና አንተ በቀላሉ ለይተን ልናወጣቸው እንችላለን! በዙሪያችን ያሉ ስኬታማ መሪዎች ለምን ጥቂት ብቻ እንደሆኑ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ አምናለሁ፤ ከዛ በፊት ግን እስቲ ሰዎች መሪ ለመሆን የማይፈልጉባቸውን ምክንያቶች እንመልከት!

## ሰዎች የመሪነትን ኃላፊነት የማይፈልጉባቸው አምስት ምክንያቶች

### 1. ብዙ ሰዎች መሪ መሆናቸውን አያውቁም

የማያውቁበት ምክንያት መሪ እንደሆኑ የነገራቸው ማንም ሰው ስለሌለ ነው! የመሪነት ብቃት እንዳላቸው አያውቁም። አንዳንድ

ሰዎች መሪ ለመሆን የሚወለዱት ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው ብለው ያስባሉ። ለመሪነት የተወለዱ ጥቂቶች ብቻ ናቸው ብዬ አላምንም። ብዙ ሰዎች የመሪነት ብቃት ይዘው እንደተወለዱ አምናለሁ ዳሩ ግን መሪ ለመሆን የሚያስከፍለውን ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ  አይደሉም።

> እንዲሁ ኋለኞች ፊተኞች፥ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ፤ የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና።
>
> ማቴዎስ 20፡16

> የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና።
>
> ማቴዎስ 22፡14

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው፣ ብዙ ሰዎች ለአገልግሎት ተጠርተዋል። ማንም ሰው ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ራሱን ከሰጠ፣ ወዲያውኑ መሪ ይሆናል። *የወንጌል አገልጋይ የሆነ ሰው የመሪነትን ጥራት እና ብቃቶችን ሁል ጊዜ ማሳየት አለበት።*

አንተም ጌታን ለማገልገል ከተጠራህ፣ በእርግጥም መሪ ልትሆን ተጠርተሃል። ይህን ጥሪ ልትተወው አትችልም!

## 2. ሰዎች ክስና ጥላቻ ይደርስብኛል ብለው ይፈራሉ

ብዙ ጊዜ መሪዎች ስውር ዓላማ እንዳላቸው ተደርጎ ይወነጀላሉ። ብዙዉን ጊዜ መጥፎ ፍላጎት አላቸው የሚል ክስ ይሰነዘርባቸዋል። አንዳንድ ሰዎች አገልጋይ የሆነው ገንዘብ ፍለጋ ነው ብለው እንደወነጀሉኝ በሰማሁ ጊዜ በጣም ተገረምሁ። ይሁን እንጂ ጌታ በአገልግሎት ውስጥ እስካለሁ ድረስ ነቀፋ እንደሚደርስብኝ ተናገረኝ። ማንኛውም መልካም መሪ ብዙ ጠላቶች አሉት። እያንዳንዱ መልካም መሪ ካጋጠሙት ሁኔታዎች በመማር ጉዞውን ይቀጥላል። ይህ ማለት ደግሞ ከመስመር አልፈህ አንዳንድ ሰዎችን ልትጎዳ ትችላለህ ማለት ነው።

> ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።
>
> ሉቃስ 14፡27

ከብዙ ዓመታት በፊት ለአንድ ወንድም የሆነ ሕብረት ውስጥ መሪ ለመሆን እንደማልፈልግ ነገርሁት። ዝምተኛና የግል ሕይወቴን መምራት የምፈልግ ዓይነት ሰው መሆኔን ገለጽሁለት። መስበክና የአገልግሎት መሪ መሆን እንደማልፈልግ አስታወቅሁት። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለእኔ ዓላማ ስለነበረው ዛሬ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ መሪ ነኝ። መሪ መሆን የሕይወት ዋጋ እንደሚያስከፍልህ የታወቀ ነው። እኔ ከግል ሕይወት የቀረኝ ትንሽ ነው። ብዙ ሰዎች

ስለ እኔ ብዙ ነገሮችን ያውቃሉ፡፡ ሰዎች በቤታቸውና በመኪናቸው ውስጥ ስለ እኔ ያወራሉ፡፡ እንደ ሁሉም መሪዎች፣ አንዳንድ ሰዎች ሲያመሰግኑኝ፣ ሌሎች ደግሞ ይተቹኛል፡፡ ይህ የመሪነት እጣ-ፈንታ ነው፡፡ ለዚህ ነው አንዳንድ ሰዎች ከመሪነት የሚሸሹት፡፡ ይሁን እንጂ ኢየሱስ መስቀልህን ተሸክመህ እንድትከተለው ተናግሯል፡፡ ክርስትና መሥዋዕትነትን ይጠይቃል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ መሆን መታደል ነው፡፡

## 3. ሰዎች ብዙ ስመ ጥር መሪዎች እንደደረሰባቸው ዓይነት ውርደት እና ጥላቻ እንዲደርስባቸው አይፈልጉም

ብዙ መሪዎች የመሪነትን መጎናጸፊያ ካነሱ በኋላ ፍጻሜአቸው ውርደት ሆኗል፡፡ ሌሎች ደግሞ አስደንጋጭ ጉዳቶችና መራራ ገጠመኞች ደርሶባቸዋል፡፡ አንዳንዶች በሚመሯቸው ሰዎች ተሰቅለዋል፡፡

እኔ እራሴ መሪዎች ለብዙ ዓመታት አገልግሎታቸው እንዴት ክፉት እንደተከፈላቸው አይቼአለሁ፡፡ በርካታ (በርካታ ስል በርካታ ማለቴ ነው) ቤተ ክርስቲያናት መሪዎቻቸው ለዘመናት ካገለገሏቸው በኋላ አሽቀንጥረው ሲጥሏቸው አይቼአለሁ፡፡ ከፍተኛ ዋጋ እየከፈሉ ለብዙ ዓመታት ያገለገሉ መጋቢዎች ላይ ምእመናን ሲሳለቁባቸው እና ሲያንጓጥጧቸው ተመልክቼአለሁ፡፡ መጋቢዎች እንደ ቤት እና መኪና በመሳሰሉ ነገሮች ምክንያት ሲገፉ አይቼአለሁ፡፡ እንዴት አሳዛኝ ነው! ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት ዓመት ተኩል ካገለገለ በኋላ እንዴት እንደተሰቀለ ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ለሕዝቡ የሚያበራ ብርሃን ከሆነ በኋላ የቀረበለት ሽልማት ይህ ነበር፡፡

በአገሬ ብዙ የአገር መሪዎች ለብዙ ዓመታት አገሪቷን ከመሩ በኋላ በአሰቃቂ ሁኔታ እንዴት እንደተገደሉ አውቃለሁ፡፡ ብዙ ዳኞችም ትክክል ነው ብለው ያሰቡትን ፍርድ ካስተላለፉ በኋላ በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደሉባቸው ጊዜያት ነበሩ፡፡ ታዲያ ማነው እንዲህ ባለው ሁኔታ ውስጥ መሪ ለመሆን የሚፈልግ? በዙሪያህ ያሉ መሪዎችን እጣ-ፈንታ ስታጠና፣ ሰዎች ከመሪነት ርቀው ሰላም የሰፈነበት የግል ሕይወት ለመምራት መምረጣቸው አስገራሚ አይሆንብህም፡፡ አንድ ሰው ውሸታም ፖለቲከኞችና ሙሰኛ መሪዎች ካሉበት ዓለም ራሱን ማራቁ ምክንያታዊ እንደሆነ ይገባኛል፡፡

በዚህ መጽሐፍ የክርስቲያናዊ አመራርን መጎናጸፊያ እንድታነሳ ላበረታታህ እፈልጋለሁ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የመሪነት ጥሪ ለመቀበል ዝግጁ እንድትሆን አበረታታሃለሁ፡፡ የሚገባው ነውና! በቤተ ክርስቲያንና በዓለም ውስጥ ያለው ተግዳሮት በጣም ተመሳሳይ ነው፡፡ ክሶቹም ያው ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የሚገባው ነው!

ዓለማውያን መሪዎች የሚሠሩት እንደ ገንዘብና ክብር ላሉት ለሰው ሽልማቶች ነው። ይሁን እንጂ እንዲህ ያሉት ሽልማቶች ጠፊዎች ናቸው። ለኢየሱስ ክርስቶስ ስትሠራ፣ ዘላለማዊ ሽልማት ትቀበላለህ።

> . . . እነርሱ ዓላፊ ጠፊ የሆነውን አክሊል ለማግኘት ይደክማሉ። እኛ ግን ለዘላለም የማይጠፋውን አክሊል ለማግኘት እንደክማለን።
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 9፡25

በመሪነት ቦታ ላይ በመሆን የሚደርሱ ህመሞችን ያሳለፍኩባቸው ብዙ ጊዜያቶች አሉ። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በታማኝነት የሚፈጽሙ ሰዎች የሚያገኟቸውን ሽልማቶች ሳስብ፣ እበረታታለሁ። አንድ ቀን በሁሉም ነገር ደስ እንደምሰኝ አውቃለሁ።

> የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና። በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ ከሐጢአተኞች በደረሰበት እንዲህ ባለ መቃወም የጸናውን አስቡ።
>
> ዕብራውያን 12፡2-3

## 4. ሰዎች መሪ ለመሆን ብቁ እንዳልሆኑ ያስባሉ

አንዳንድ ሰዎች ለመሪነት ደረጃ በስነ-ምግባር ብቁ እንዳልሆኑ ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ ፈጽሞ የመሪነት ብቃት እንደሌላቸው ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ መሪ እንዳይሆኑ የሚያደርጓቸው እጅግ ብዙ ግላዊ ችግሮች እንዳሉባቸው ያስባሉ። በመሆኑም፣ ወደ ሌሎች ሰዎች ችግሮች እጃቸውን የሚያስገቡበት ሁኔታ ሊኖር እንደማይችል ያስባሉ።

ዛሬ ግን ለአንተ አንድ የምስራች አለኝ! እግዚአብሔር ፍጹም ከሆኑ ሰዎች ጋር አይሰራም። የሚሰራው ፈቃደኛ ከሆኑ ሰዎች ጋር ነው። እርሱ ልብን ነው የሚያየው ሰዋዊ ድክመትህንም ይረዳል። ኢየሱስ ፍጹም ሰዎችን ቢፈልግ ኖሮ፣ ላረጋግጥልህ የምችለው ነገር ከደቀ መዛሙርቱ የትኛውም ለቤተክርስቲያን በመሪነት ስፍራ በቂ አይሆኑም ነበር። ለምሳሌ ጴጥሮስን እንውሰድ፣ ለአገልግሎት ከመሾሙ ከጥቂት ሳምንት በፊት ሦስት ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስን ክዶታል። ከዚህ በፊት ከእርሱ ምንም ስልጠና እንዳልተቀበለ በመማል እና በመገዘት ገልጿል። ይሁን እንጂ ጌታ ተጠቅሞበታል። ሌሎችንም ደቀመዛሙርቶችን ተመልከት፣ በመንግሥተ ሰማይ ስለሚኖራቸው የሥልጣን እርከን ይከራከሩ ነበር። እንዲህ ብለው ጠየቁ “ማን ታላቅ ይሆናል?”

> ደግሞም ማናቸውም ታላቅ ሆኖ እንዲቈጠር በመካከላቸው ክርክር ሆነ።
>
> ሉቃስ 22፡24

ማን ታላቅ እንደሚሆን ከተከራከሩ በኋላ፣ ሁላቸውም ክርስቶስ በሚፈልጋቸው ወሳኝ ሰዓት ላይ ከድተውታል። እንዲህ ያሉትን ሰዎች ታምናለህ? እንደዚህ ያሉትን ሰዎች ትጠቀምባቸዋለህ? ይሁን እንጂ ጌታ አደርጎታል! መሪ ለመሆን የግድ ፍጹም መሆን አይጠበቅብህም። ያ ቢሆንማ፣ በዓለምም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ ባልተገኘ ነበር። ይህ ማለት ደግሞ ምንም ዓይነት የመሪነት መለኪያ አያስፈልግም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር የላቀ የባሕርይና የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲኖረን ይፈልጋል። ይህም ሆኖ፣ ፍጹም ካልሆኑ ሰዎች ጋር ይሠራል።

እግዚአብሔር ልብን ነው የሚያየው። ልብህ ትክክል መሆኑን እርግጠኛ ሁን ከዚያም እግዚአብሔር ይጠቀምብሃል።

> . . . እግዚአብሔር የሚያየው፣ ሰው እንደሚያየው አይደለም። ሰው የውጭውን ገጽታ ያያል፤ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል አለው።
>
> 1ኛ ሳሙኤል 16፡7

## 5. ብዙ ሰዎች መሪ ለመሆን የማይፈልጉት ራስ ወዳዶች ስለሆኑ ነው

እንዲህ ዓይነት ሰዎች የሚያስቡት ስለራሳቸው ጉዳይ ብቻ ነው። ደህንነት በማግኘታቸው ደስ ይላቸዋል። መንፈስ ቅዱስን በመሞላታቸው ደስተኞች ናቸው። ሀብትን በማካበታቸው ደስ ይላቸዋል። ዳሩ ግን እንዲህ ያሉት ሰዎች ስለማንም ግድ የላቸውም። “እኔ ደህና ከሆንሁ፣ ሁሉም ነገር ደህና ይሆናል” ብለው ያስባሉ። ያም የራስ ወዳድነት መንፈስ ነው።

ራስ-ወዳድ የሆነ ሰው መሪ ለመሆን የሚከፈል መሥዋዕትነት ወይም ሥልጠና ለመውሰድ አይፈልግም። የሌሎችን ነፍስ ለመታደግ አንዲትም ኃይል ማፍሰስ አይፈልግም። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ሳይመጣ በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ በምቾት ቢመላለስ ኖሮ፣ ይሄን ጊዜ ምን ይውጠን ነበር? እርሱ መቃብሩን ፈነቃቅሎ ሲወጣ፣ አንተ ግን ከአልጋህ መነሳት አልቻልህም። የስንፍናና የራስ ወዳድነትን መንፈስ እገስጻለሁ! ስለ ሚስዮናውያን እግዚአብሔር ይመስገን። የማያውቁትን ሰው ለማዳን ሲሉ ለእነርሱ ባዕድ ወደሆነበት ምድር ስለተጓዙት የወንጌል ሰዎች እግዚአብሔር ይመስገን።

*ምዕራፍ 8*

# ከታላላቆችም ሆነ ከታናናሾች ጋር ሕብረት አድርግ

መልካም መሪ ከሁለት ዓይነት ሰዎች ጋር ሕብረት የማድረግ ብቃት አለው፣ ከታላላቆች (በሰው አገላለጽ) እና ከታናናሾች (በሰው አገላለጽ) ሰዎች ጋር። ታላላቅ የሚባሉት ሰዎች መኳንንት፣ ሀብታሞች፣ተጽዕኖ የማሳደር ችሎታ ያላቸውና በማኅበረሰቡ ውስጥ ኃያላን የሆኑ ሰዎች ናቸው። እንዲሁ ዓይነት ሰዎች እምብዛም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሉም።

> ወንድሞች ሆይ፥ መጠራታችሁን ተመልከቱ፤ እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች፥ ኀያላን የሆኑ ብዙዎች፥ ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች አልተጠሩም።
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡26

"ታናናሽ" የሚባሉት ደግሞ በኑሮቸው ዝቅ ብለው የሚገኙ፣ በሕብረተሰባቸው ልዩ የከበሬታ ስፍራ የሌላቸውና ብዙ ቁሳዊ ሀብት የሌላቸው ሰዎች ናቸው።

## ከታላላቅ ሰዎች ጋር ሕብረት መፍጠር አስፈላጊ የሚሆንባቸው አራት ምክንያቶች

### 1. ኢየሱስ ከታላላቅ ሰዎች ጋር ሕብረት ነበረው

ኢየሱስ ከኒቆዲሞስ ጋር በግል ተነጋግሯል። እየሱስ ብዙ ግብዛዎችን በመቀበል ተጽዕኖ የማሳደር ችሎታ ካላቸው ሰዎችና ኃያላን ከሆኑ ሰዎች ጋር ተገኝቶ ገበታ ተቋድሷል። እነዚህ ሕብረቶች አስፈላጊዎች በመሆናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጸዋል።

> ከፈሪሳውያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ . . .
>
> ዮሐንስ 3፡1-2

> በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለ ጠጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ፥ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበረ፤
>
> ማቴዎስ 27፡57

## 2. ታላላቅ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚጫወቱት ሚና አላቸው

ከእንደዚህ ዓይነት ሰዎች አንዳንዶቹ ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ከእንዲህ ዓይነት ሰዎች መካከል የኢየሱስን አስክሬን በመቅበሩ በኩል አስተዋጽኦ ያደረገው የአርማትያው ዮሴፍ አንዱ ነው። ይህ ጠቃሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ፍጻሜ ነበር።

> በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለ ጠጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ፥ . . . ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንጹሕ በፍታ ከፈነው፥ ከዓለት በወቀረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው. . .

ማቴዎስ 27፡57፣59፣60

## 3. ታላላቅ ሰዎች ወንጌልን በገንዘባቸው እንዲደግፉ እግዚአብሔር ይጠቀምባቸዋል

ሁሉም ሰው ለወንጌል አገልግሎት እኩል የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል ብለህ የምታስብ ከሆነ አላዋቂ እና በቂ ልምድ የሌለህ ነህ ማለት ነው። የአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ገቢ ከሌሎች የላቀ ነው ይኸውም እግዚአብሔር በገንዘባቸው የሚያገለግሉትን ሰዎች ስላስነሳ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ቃል ለድሆችም ሆነ ለባለጸጎች እንዲዳረስ ጠቃሚ የሆነ ሚዛናዊነትን ይፈጥራል።

> እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ፦ ብዙ ያከማቸ አለተረፈም፥ ጥቂትም ያከማቸ አላጎደለም።

2ኛ ቆሮንቶስ 8፡15

## 4. የአንድ ተጽኖ ማሳደር የሚችል ሰው አስተዋፅዖ ለአንድ አገር ሙሉ በሙሉ መዳን ምክንያት ሊሆን ይችላል

ሐማ መላ የእስራኤልን ሕዝብ እንዳያጠፋ የአስቴር ከንጉሡ ጋር የነበራት ወሳኝ ግንኙነት አንደኛው ምክንያት ነበር። አጎቷ እግዚአብሔር ሆን ብሎ ሕዝቡን ለማዳን ሲል በንጉሡ ቤተ መንግሥት ውስጥ እንዳስቀመጣት አስታውሿታል።

> . . . ደግሞስ ወደ መንግሥት የመጣሽው እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደሆን ማን ያውቃል?

አስቴር 4፡14

የአንድ አገር ፕሬዝዳንት ወዳጅ የሆነ አንድ በቢሊዮን የሚቆጠር ሀብት ያለው ክርስቲያን ወንድም ከፕሬዝዳንቱ ጋር ያለውን ግንኙነት

በመጠቀም በአገሪቱ በሕግ ታግዶ የነበረውን የወንጌል ጀማ ስብከት ለማካሄድ ፈቃድ ማግኘት መቻሉን ገለጸልኝ፡፡

# ከድሆች ጋር ሕብረት አስፈላጊ የሚሆንባቸው ሦስት ምክንያቶች

## 1. የክርስቶስ ዋንኛ ጥሪ ለድሆች ነበር

ኢየሱስ በሕይወቱ ላይ ስለው ቅባት ሲናገር፣ ቅባቱ ማን ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ግልጽ አድርጓል፡፡ የተቀባው ወንጌልን ለድሆች ለመስበክ እንደነበረም በግልጽ ተናግሯል፡፡ እኛ የክርስቶስ አካል ነን ያም ቅባት በእኛ ላይ ነው፡፡

> የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል
>
> ሉቃስ 4፡18-19

## 2. በዓለም ላይ የሚገኙት አብዛኞቹ ሰዎች ድሆች ናቸው፡፡ በመሆኑም፣ አገልግሎታችን ድሆችን መድረስ ይገባዋል፡፡

ብዙ ፍሬ ማፍራት ካለብን አብዛኛው ፍሬ የሚገኘው በድሆች መካከል ነው፡፡

## 3. የከፍተኛ ቅባት ምልክት ድሆችን ማገልገላችን ነው፡፡

ዛሬ ብዙ አገልጋዮች ከአንድ አገር ፕሬዘዳንት ጋር የመገናኘት እድል ቢገጥማቸው በመደነቅ ይሞላሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት እድል ከደረሳቸው ከፕሬዚዳንቱ ጋር ፎቶ በመነሣት በወርሃዊ መጽሔታቸው ላይ ያወጡታል፡፡ ይህን ማድረጉ ችግር የለውም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ ታላቁ የመሲሕነት አገልግሎት ወደ ምድር ደርሶ እንደሆነ ሲጠየቅ፣ “ለድኾችም ወንጌል እየተሰበ ነው” ሲል መለሰ፡፡ ድሆችን ለማገልገል ከፍተኛ ቅባት ይጠይቃል፡፡

> ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው አንተ ነህ? ወይስ ሌላ እንጠብቅ? ሲል ጠየቀ፡፡ ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤ ሄዳችሁ የምትሰሙትንና የምታዩትን ለዮሐንስ ንገሩት፤ ዕውሮች ያያሉ፤ አንካሶች ይራመዳሉ፤ ለምጻሞች ይነጻሉ፤ ደንቆሮዎች ይሰማሉ፤ ሙታን ይነሣሉ፤ ለድኾችም የምሥራች (ወንጌል) እየተሰበከ ነው፤
>
> ማቴዎስ 11፡3-5 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

# ድሆችን ማገልገል አስቸጋሪ የሚሆንበት ሦስት ምክንያቶች

1. ድሆች ወንጌልን በገንዘብ የመደገፍ አቅም የላቸውም

አብዛኛው ለድሆች የሚደረግ አገልግሎት ቅድመ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ሊሆን ይገባል። ለመጽሕፍት፣ ለጀማ ስብከተ ወንጌል፣ ለደመወዝ፣ ወዘተ... የሚያስፈልጉ ወጪዎች በሌሎች ሰዎች መሸፈን አለባቸው።

2. ድሆች ወንጌልን አይረዱም

ድሆች ብዙ ችግሮች አሉባቸው። አስተሳሰባቸው ዙሪያቸውን በከበቡት ብዙ ችግሮች ተፅእኖ የታጠረ ነው። ድሆች ብዙውን ጊዜ ተስፋ የቆረጡና ለጭንቀት የተጋለጡ ናቸው። ነገሮች በምድር ላይ እንዲህ መጥፎ ሆነው ሳለ እግዚአብሔር ለምን መንግሥተ ሰማይን እንደሚሰጠን ሊገባቸው አይችልም። በመጀመሪያ በምድር ላይ አንዳንድ ለውጦችን ማምጣት አይችልም? በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ችግሮቼ ሊቃለሉ የሚችሉት እንዴት ነው?

3. ድሆች አንዳንድ ጊዜ አንተን የችግሮቻቸው መንስኤ እንደሆንህ አድርገው ያዩሃል።

ድሆችን በማገለግልበት ጊዜ አብዛኞቹ የሚረዳቸውን ሰው የችግራቸው ምንጭ እንደሆነ አድርገው እንደሚመለከቱ ተረድቻለሁ። በተጨማሪም አብዛኞቹ ድሆች ከኩራታቸው የተነሳ እርዳታ ለመቀበል ፈቃደኞች አይደሉም።

## ልትረዳቸው የማትችላቸው አምስት ዓይነት ሰዎች

1. ለችግሮቻቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መፍትሔ የማይቀበሉ ሰዎች
2. ችግሮች እንዳሉባቸው የማይገነዘቡ ሰዎች
3. ከሌሎች ድጋፍ ለመቀበል በጣም ኩራት የሚሰማቸው ሰዎች
4. ችግራቸው አንተ እንደሆንህ አድርገው የሚያስቡ ሰዎች
5. የችግሮቻቸው መንስኤ አንተ እንደሆንህ አድርገው የሚያስቡ ሰዎች

## ምዕራፍ 9

# የራስን ሃቀኝነት ጠብቅ

ሃቀኝነት (INTEGRITY) ምልዓት ነው። ሙሉ በሙሉ ወይም ፍጹም ጤናማ መሆን ማለት ነው። ሃቀኛነት አለህ ማለት፦ ቀጥተኛ፣ ቅን፣ ታማኝ እና ንጹሕ ነህ ማለት ነው። መልካም መሪ ለመሆን ሃቀኝነት ሊኖርህ ይገባል።

ውሸትና ሽንገላ ሃቀኝነት የመሸርሸር አቅም አላቸው። በፖለቲከኞች የምናምን ጥቂቶች የመሆናችን ምክንያት ሃቀኝነታቸው በቀድሞ የፖለቲካ መሪዎች ማታለል በብዙ መሸርሸሩ ነው።

እራስህን የምትገዛ ነህን? ምሉዕ ነህን?

*ምዕራፍ 10*

# ለሰዎች ተስፋ ስጥ

በቤተ ክርስቲያንህ ወይም በድርጅትህ ውስጥ ለምን ማንም ለረዥም ጊዜ እንደማይቆይ በማሰብ ተደንቀህ ታውቃለህን? ምናልባት የወደፊት ተስፋ በብዛት ስለሌለ ነው። ምናልባትም ለወደፊት ለእነርሱ የሚሆኑ መልካም ነገሮችን መመልከት ስላልቻሉ ይሆናል።

## ለሰዎች ተስፋ የምንሰጥባቸው ስድስት መንገዶች

### 1. ቃል ግባ ደግሞም ቃልህን ጠብቅ

ቃልህን ባፈረስክ ቁጥር ሰዎች በአንተ ላይ ያላቸውን እምነት ትሸረሽራለህ። ሰዎች በአንተ እንዲያምኑ ማድረግ አስቸጋሪ ነው። ሰዎች የማይተማመኑብህ ከሆነ ሊከተሉህ አይችሉም። የኢየሱስ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ወደፊት በሚፈጸሙ የተሰፋ ቃሎች ላይ ያማከለ ነበር።

> . . . ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።
>
> ዮሐንስ 14፡2-3

የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ለወደፊቱ መልካም ነገሮች እንደሚጠብቋቸው ተረድተው ነበር። ኢየሱስ ቃሉን እንደሚጠብቅ ያውቁ ስለነበረ፣ ተስፋ ነበራቸው።

### 2. የእግዚአብሔርን ቃል ስበክ

የእግዚአብሔር ቃል በተስፋ የተሞላ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰብክ ሰው ተስፋ መቁረጥን፣ ሀዘንንና ግራ መጋባትን አያሰራጭም።

### 3. ከቅጣት ይልቅ ስለ ሽልማት አብዝተህ ተናገር

ደቀ መዛሙርቱ ታላቅ ተስፋ ነበራቸው። ይህም ተስፋ የመንግሥተ ሰማይ ክብርና ሽልማት ነው። ይህ ለእነርሱ ከፍተኛ የተነሳሽነት ምንጭ ነበር። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ለወንጌል አገልግሎት

ከነበራቸው መነሳሳት የተነሳ መተዳደሪያቸው የነበረውን ሥራ ትተው ወደ አገልግሎት መሰማራታቸውን ልትረዳ ይገባሃል። በመጨረሻም ለእምነታቸው ሞተዋል።

## 4. ተስፋን የሚያነሳሱ አዎንታዊ ምሳሌዎች አሳይ

በመሥሪያ ቤትህም ሆነ በቤተ ክርስትያንህ ሰዎችን ማነሳሳት አስፈላጊ መሆኑን ልትቀበል ይገባል። የተነሳሱ ሰዎች የማግኛ ቁልፉ “የወደፊት ተስፋ” ነው። ለዚህ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መንግሥተ ሰማይ እና ታማኝ አገልጋዮቹ ስለሚጠብቋቸው ሽልማቶች አዘውትሮ ይናገር የነበረው። ለምሳሌ የአውሮፕላን አብራሪዎች ማነሳሳት ከፈለግህ፣ ምን ያህል የአውሮፕላን አብራሪዎች ለአመታት በስኬታማነት እንደበረሩና በመጨረሻም ጡረታ እንደወጡ አሳያቸው። እንደዚህ ዓይነቱ ምሳሌ ነው ተስፋን ሊሰጥ የሚችለው። መጋቢዎችን ለማነቃቃት ከፈለግህ በአገልግሎት የተሳካላቸውን አገልጋዮች ምሳሌ አሳያቸው።

## 5. ተስፋ አስቆራጭ እና የሚያስጨንቁ ምሳሌዎችን ከመጠቀም ተቆጠብ

እንዴት ሌሎች ለአስከፊ ሁኔታዎች እንደተዳረጉ ሲሰሙ፣ ሰዎች ተስፋ ይቆርጣሉ። የራሳቸውም ፍጻሜ እንደነዚህ ሰዎች እንዳይሆን ይሰጋሉ “አንድ ቀን የኔም መጨረሻ እንዲህ ነው የሚሆነው” ይላሉ። አውሮፕላን አብራሪ ብትሆን በበረራ ታሪክ ውስጥ የተከሰቱትን አስከፊ የአውሮፕላን አደጋዎች አንስቶ መወያየቱ ጠቀሜታ የለውም።

## 6. ቋሚ የሆነ መዋቅር ገንባ

ሰዎች በቋሚ ነገሮች ላይ ተስፋቸውን ይጥላሉ። ሰዎች በተፈጥሮ ቋሚ ወደሆኑ ነገሮች ይሳባሉ። የሕንጻ ግንባታ የሚያካሂድ መጋቢ የምእመኑን ተስፋ ያጎለብታል።

*ምዕራፍ 11*

# *ሥልጣንን በፍጹም ያለ ጥበብ፣ ጥበብንም ያለ ሥልጣን አትጠቀም!*

*መሪ ጥበብን እንደ አንድ ወሳኝ የሕይወት መሣሪያ የሚጠቀም ሰው ነው።ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን መንፈስና የእግዚአብሔርን ጥበብ በማዋሃድ የመጠቀም ኃላፊነት አለባቸው። ይህም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እያንዳንዱ ክርስቲያን መሪ ጥበብንና ሥልጣንን ሚዛናዊ በሆነ መልኩ መጠቀም የሚችልበት ደረጃ ላይ መድረስ አለበት።*

> **ለተጠሩት ግን፥ አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ፥ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው።**
>
> **1ኛ ቆሮንቶስ 1፡24**

*"ኃይል" እና "ጥበብ" በሚሉት ቃላት ላይ አፅንዖት አድርጌባቸዋለሁ፤ ይህንን መጽሐፍ ስታነብብ እንድታገኝ የምፈልገው ይህንን ነው። ክርስቶስ ኢየሱስ ኃይላችን ብቻ አይደለም። እርሱ ኃይል እና ጥበብ ነው።*

*የእግዚአብሔርን ኃይልና ጥበብ ውጤታማ በሆነ መንገድ ማዋሃድ ስትችል በአመራርህ ውስጥ ስኬትን መለማመድ ትጀመራለህ። አስታውስ አንዱ ያለ ሌላው በቂ አይሆንም።*

*መጋቢ ከሆንህ፣ በመንፈሳዊ ምሪት ላይ ብቻ መደገፍ ማተኮር የለብህም፤ መጋቢዎች አእምሯቸውንም መጠቀም እንዳለባቸው አትዘንጋ። አእምሮህን ከተጠቀምህ፣ እግዚአብሔር አገልግሎትህን ላቅ ወዳለ ደረጃ ያደርስልሃል።*

*በአንድ ወቅት ዝምታ በሰፈነበት መኖሪያ አካባቢ በሚገኝ የግለሰብ ቤት ውስጥ ፕሮግራም የምታካሂድ ቤተ ክርስቲያን ተመለከትሁ። እኔ ያለሁት ከአንድ መቶ ሜትር ርቄ ቢሆንም፣ በአገልግሎቱ ውስጥ የሚባለውን ነገር ሁሉ በሚገባ ለመስማት እችል ነበር። ፀሎቱ፣ አምልኮውና ዝማሬው አካባቢውን በሚያውክ የድምፅ ማጉያ የታጀበ በመሆኑ፣ በአካባቢው የሚገኙ ሰዎች በራሳቸው ጉዳይ ላይ ትኩረት ማድረግ አልቻሉም ነበር። መጋቢው የተቀባ በመሆኑ የእግዚአብሔር*

ኃይል በላዩ ላይ እንደነበረ ግልጽ ነው። እንዳለመታደል ሆኖ ግን ጥበብን አልተጠቀመም ነበር።

በስብሰባው ላይ የተገኙት ሰዎች ጥቂቶች ቢሆኑም፣ በትልቅ አዳራሽ ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሊጠቀሙበት የሚገባውን የድምፅ ማጉያ ይጠቀሙ ነበር። ኢየሱስ ምንም ዓይነት የድምፅ ማጉያ መሣሪያ ሳይጠቀም ነበር ለአምስት ሺህ ሰዎች የተናገረው። እኔም “ይህች ቤተ ክርስቲያን ብዙም ሳይቆይ በሕዝቡ ወይም በፖሊስ ልትዘጋ ትችላለች” ብዬ አሰብሁ። ያች ቤተ ክርስቲያን ብዙም ሳይቆይ ልትቆጣጠር የማትችላቸውን ጠላቶች እንደምትጋፈጥ አውቄ ነበር። ኃይልን ያለ ጥበብ፣ ጥበብን ደግሞ ያለ ኃይል በፍጹም አትጠቀም!

## ምዕራፍ 12

# ሕይወት አልባ መሪ አትሁን ጽኑ እምነት ይኑርህ!

ሐዋሪያው ጳውሎስ ጽኑ እምነት ያለው ሰው ነበር። በእግዚአብሔር ላይ ጠንካራ እምነት የነበረው እና ለዚህም ሕይወቱን አሳልፎ ለመስጠት የተዘጋጀ ነበር። በአንድ ወቅት "ለመሞት ዝግጁ ነኝ" ሲል ተናግሯል።

**በመሥዋዕት እንደሚደረግ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና፣ የሚሄድበትም ጊዜ ደርሶአል፡፡**

**2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡6**

ራስህን እንደ መሪ አድርገህ የምትቆጥር ከሆነ፣ ስለ አንድ ነገር ጽኑ እምነት ሊኖርህ ይገባል! ጽኑ እምነት የሌለው መሪ ሕይወት አልባ ማንነት የተላበሰ ነው። ዓለምን የሚመሯት ጽኑ እምነት ያላቸው ሰዎች ናቸው። በአጥፍቶ መጥፋት ንጹህ ዜጎችን የሚገድሉ ሰዎች ትክክለኛ ተግባር እያከናወንን ነው የሚል ጽኑ እምነት አላቸው። ከዚህ የጭካኔ ተግባራቸው የተነሣ መንግሥተ ሰማይ እንደሚገቡም እምነት አላቸው። ጽኑ እምነት ያላቸውን ሰዎች በቁጥጥር ስር ማዋል አስቸጋሪ ነው። እነዚህን ሰዎች ሳጥን ውስጥ ልታስቀምጣቸው አትችልም። አስረህ ልታስቀምጣቸው አትችልም። እንዳይነቃነቁ ልታደርጋቸው አትችልም። ቅስማቸውን ልትሰብር አትችልም።

ብዙ ሕይወት አልባ መሪዎች የሚጎድላቸው የዓላማ ጽናት እንደሆነ ጽኑ እምነቱ ነው። የማደርጋቸውን ነገሮች የማደርገው ለምንድር ነው? ምክንያቱም ለዛ ነገር የጸና እምነት ስላለኝ ነው። በመንግሥተ ሰማይና በሲኦል መኖር እምናለሁ። አንድ ቀን ክርስቶስ ለዚህ ምድራዊ ሥራዬ ሁሉ እንደሚሸልመኝ ጽኑ እምነት አለኝ። ኢየሱስ ሞትን አሸንፎ የተነሣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ። መንግሥተ ሰማይ መግባት የሚቻለው በኢየሱስ በኩል ብቻ እንደሆነ አምናለሁ። ለዚህም እውነታዎች አእምሯዊ እምነት ብቻ አልሰጥም። በሙሉ ልቤ አምናቸዋለሁ። ይህ አንቀሳቃሽ ኃይል ነው የህክምና ሥራዬን እንድጥል ያደረገኝ።

የእምነት አቋም የሌለው መሪ ሕይወት አልባ፣ የተጻፈ ንግግር አቅራቢና ስሜት የሌለው አሻንጉሊት ነው። ማንም ሰው ልብ

አይለውም፡፡ ማንም የሚናገረውን አያምንም፡፡ ማንም አይከተለውም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ስለምን አይከተሉኝም ብለህ ተገርመህ ታውቃለህ? ምናልባት ጽኑ እምነት ስለሌለህ ሊሆን ይችላል፡፡ ጽኑ እምነት ያለው ሰው ለእምነቱ ብዙ ነገሮችን ለመሠዋት ዝግጁ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ተጠርተናል እያሉ ለጥሪያቸው ምንም መሥዋዕትነት ለመክፈል የማይፈልጉትን ሰዎች በምመለከትበት ጊዜ፣ እውነት ተጠርተው ይሆን? የሚል ጥያቄ በአእምሮዬ ውስጥ ይፈጠራል፡፡ ጥሪ ለጌታ እንድንሠራ የሚያደርገን ጽኑ እምነት ነው፡፡

በፖለቲካው ዓለም ብዙኃኑ የሚከተሉት ጽኑ እምነት ያለው የሚመስለውን ነው፡፡ ከልቡ የሚናገረውን ይከተላሉ፡፡ ላመነበት ለመሞት የተዘጋጀውን ይከተላሉ፡፡

እውነተኛ መሪ ነህን? የጽኑ እምነት ሰው ለመሆን ወስን፡፡ የምን ጽኑ እምነት ነው ሊኖረኝ የሚገባው? የሚል ጥያቄ ሊኖርህ ይችላል፡፡ እግዚአብሔር እንድታከናውን ለጠራህ ጉዳይ ጽኑ እምነት ይኑርህ፡፡ በሕይወትህ ዘመን መፈጸም ላለብህ ነገር ሁሉ ጽኑ እምነት ይኑርህ፡፡ እግዚአብሔር ለነገረህ ነገር ሁሉ ጽኑ እምነት ይኑርህ፡፡ በእነኚህ ጽኑ እምነቶች ኑር! ያመንክባቸውን ነገሮች ከፍጻሜ ለማድረስ የትኛውንም ነገር ለመተው ዝግጁ ሁን፡፡

## *ምዕራፍ 13*

# ዘመንህ እስኪመጣ ጠብቅ

**እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፥ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል፤ የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።**

**መዝሙር 1፥3**

የእግዚአብሔር በረከቶች ሁሉ የራሳቸው ጊዜ አላቸው፡፡ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ጊዜ አለው፡፡ የደረጃ እድገት ጊዜ አለው፡፡ የግል ብልጽግናም ጊዜ አለው፡፡

መሪ የሚፈልጋቸው በረከቶች ሁሉ በአንድ ጀንበር እንደማይመጡ ያውቃል፡፡ በመሆኑም፣ጥርመሳ እና ዕድገት እስኪገኝ ድረስ በስፍራው ለመጠበቅ ዝግጁ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ የሆነ ዕድገትህን መጠበቅ የማትችል ከሆነ፣ መሪ አይደለህም፡፡ ብዙ ነገሮችን ለማግኘት ለብዙ ዓመታት ለመጠበቅ የተገደድኩባቸው ጊዜያት ነበሩ፡፡

በአንድ የማንጎ ዛፍ ላይ ያሉትን ፍሬዎች ለመብላት እስኪበስሉ ድረስ መጠበቅ የማትችል ከሆነ መቼም አታገኘውም፡፡ ሁሌም ከመብሰላቸው በፊት ትቀጥፋቸዋለህ፡፡ ልብ በል፣ በሳሉ ማንጎ ከጥሬው በጣም የተለየ ነው፡፡

እጅግ ውድ መኪና የገዛ አንድ መጋቢ አውቃለሁ፡፡ ለበርካታ ወራት ጠቅላላውን የቤተ ክርስቲያን ገቢ በመጠቀም ዕዳውን መክፈል ነበረበት፡፡ ይህም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነውጥ እንዲፈጠር አደረገ፡፡ የዚህን ውድ መኪና ዋጋ ለመክፈል አስጨናቂ ገንዘብ የማሰባሰብ ጥረቶች ተደረጉ፡፡ በመጨረሻው ግን በረከቱ ወደ ውዝግብ ተለወጠ፡፡

> **ለሁሉ ዘመን አለው፥ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው. . . ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው፤ እግዚአብሔርም ከጥንት ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ድረስ የሠራውን ሥራ ሰው መርምሮ እንዳያገኝ ዘላለምነትን በልቡ ሰጠው።**

**መክብብ 3፥1፣11**

እግዚአብሔር ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ይሠራል፡፡ መሪ ነህ? ከሆንህ መሪ ዘመኑን ለመጠበቅ ዝግጁ የሆነ ሰው መሆኑን በፍጹም አትዘንጋ፡፡

*ምዕራፍ 14*

# በአንድ ነገር ላይ የማተኮርን ምሥጢር ተጠቀም

*. . . ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ*

ፊልጵስዩስ 3፡13

## በአንድ ጉዳይ ላይ ስለማተኮር መሪዎች ሁሉ ሊያውቁ የሚገቧቸው አሥራ ስድስት ነጥቦች

1. **እያንዳንዱ የሰው ልጆች ታላላቅ ክንውኖች በሙሉ ትኩረት የመሰጠት ውጤቶች ናቸው፡፡**
2. **እያንዳንዱ ታላላቅ የጦር ድሎች የተገኙት ሁሉንም ኃይሎች በአንድ ዓላማ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ በማድረግ ነው፡፡**
3. **እያንዳንዱ ታላላቅ አገልግሎቶች ለእግዚአብሔር ውጤታማ ተግባር ማከናወን የቻሉት በአንድ ራእይ ላይ ትኩረት በማድረግ ነው፡፡**

የዩኒቨርስቲ ተማሪ በነበርሁበት ጊዜ ከብዙ ክርስቲያናዊ ቡድኖች ጋር የመሆን ዕድል አጋጥሞኛል፡፡ በኋላ ግን ከአንደኛው የአገልግሎት ቡድን ጋር ብቻ ለመሆን ወሰንሁ፡፡ ይህንንም ያደረኩት ጊዜዬን በካምፓስ ውስጥ ላሉ ክርስቲያን ቡድኖች ሁሉ ላከፋፍል እንደማልችል በመረዳቴ ነበር፡፡ በአንድ ነገር ላይ ብቻ ትኩረት ለማድረግ በመቻሌ ዛሬም ድረስ ውጤታማ ሆኖ በመሥራት ላይ የሚገኝ አገልግሎት ለመመሥረት ችያለሁ፡፡

4. **በአንድ ጉዳይ ላይ ማተኮር ሰዎች በፍጥነት እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡**
5. **በፍጥነት በምትሠራበት ጊዜ የበለጠ ጉልበትና ፍላጎት ይኖርሃል፡፡**

6. **ተግባርህን በዝግታ ባከናወንህ ቁጥር ደግሞ ይበልጥ እየደከምህና ተግባርህን ለማከናወን የሚኖርህ ፍላጎት እየቀነሰ ይመጣል፡፡**

7. **ፕሮጀክቶች በእንጥልጥል በቆዩና በዘገዩ መጠን ሁሉም ሰው ተስፋ እየቆረጠ ይመጣል፡፡**

የዘገየ ተስፋ ልብን ያሳዝናል፡፡

የምትዘገይ ተስፋ ልብን ታሳዝናለች፤ የተገኘች ፈቃድ ግን የሕይወት ዛፍ ናት።

ምሳሌ 13፡12

8. **በአንድ ጉዳይ ላይ ትኩረት ማድረግ ጥቅም ያለውንና ጥቅም የሌለውን ለይቶ በማወቅ ችሎታ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡**

አስፈላጊ የሆነው ነገር የትኛው እንደሆነ ለመወሰን የማይችል ማንኛውም ሰው በአንድ ነገር ላይ ትኩረት የማድረግን ኃይል ሊጠቀምበት አይችልም፡፡ አጣዳፊ በሆኑ ጥሪዎች፣ ጥያቄዎች፣ ግብዣዎች ድንገተኛ ጉዳዮች እና አስጊ በሆኑ ሁኔታዎች አትታለል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ፣ የአፋጣኝነት ባህርይ ያላቸው ነገሮች እምብዛም አስፈላጊዎች አይደሉም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አስፈላጊ ነገሮች አጣዳፊ አይደሉም፡፡

9. **በአንድ ጉዳይ ላይ ያለህን ትኩረት የሚሰርቀው ትልቁ ነገር ስልክ ነው፡፡**

ጸሎት ከመጀመሬ በፊት ስልክ አጠፋለሁ፡፡ ይህ ደግሞ በጌታ ላይ ብቻ እንዳተኩር ያስችለኛል፡፡

10. **ሌላው ትኩረትህን የሚሰርቅብህ ነገር ፋይዳ የሌለው ማኅበራዊ ግንኙነት እና ቴሌቪዥን ነው፡፡**

11. **በፕሮጀክቶችህ ሁሉ ላይ የጥድፍያ ስሜት አክል፡፡**

ይህ ሰዎች በሥራው ላይ እንዲያተኩሩ ያስችላቸዋል፡፡

12. **በአንድ ጉዳይ ላይ ትኩረት ማድረግ ሰዎችን ከሀሜት፣ ከቅናት፣ ከምቀኝነትና ከአድመኝነት ይጠብቃቸዋል፡፡**

## 13. ብዙ *ሥራዎችን* በአንድ ጊዜ ማከናወን የሚችሉ ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡

በመሆኑም፣ በአንድ ጊዜ አንድን ተግባር ብቻ አከናውን፡፡

## 14. ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች በአንድ ጉዳይ ላይ እንዳታተኩር ያደርጋሉ፡፡

ያልተጠናቀቁ *ሥራዎች* በወደፊት ጉዳዮች ላይ እንዳታተኩር ያደርጋሉ፡፡ አሳብህን በመበታተን ወዳለፈ ነገር ይጎትቱሃል፡፡ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር በሰጣቸው *ሥራዎች* ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ሰዎች ማኅበራዊ ኑሮ የማይገባቸው፣ ኩሩዎች፣ የወዳጅነት መንፈስ የሌላቸው፣ የአገር ፍቅር ስሜት የሌላቸው እና ወደ ውስጥ ራሳቸውን ብቻ የሚመለከቱ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ ነገር ግን ጥበብ በልጆቿ ትጸድቃለች፡፡

## 15. ቤተ ክርስቲያን በመልካም *ሥራና* ማኅበራዊ ተቀባይነት በማግኘት ስም ትኩረቷን ለአራት አበይት ነገሮች ትከፋፍላለች፡፡ እነዚህም፡- ጤና፣ ትምህርት፣ የዕርዳታ አገልግሎቶችና ክርስቲያናዊ ትምህርት ናቸው፡፡

ከዚህ አንጻር፣ ሌሎች ሃይማኖቶች በከፍተኛ ፍጥነት መስፋፋታቸው አስገራሚ አይሆንም፡፡ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በሰጣት ግብ ላይ ብቻ ብታተኩር ይህንን ሁኔታ መቀየር ይቻል ነበር!

## 16. በአንድ ነገር ላይ ትኩረት ማድረግ ሁሉም ነገር እንዲያድግ ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ 15

# በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች በሕይወታቸው ታላላቅ ተግባራትን እንዲያከናውኑ አግዛቸው

*ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፥ ወደ እርሱም ሄዱ። ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥ ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ፤ ስምዖንንም ጴጥሮስ ብሎ ሰየመው፤ የዘብዴዎስንም ልጅ ያዕቆብን የያዕቆብንም ወንድም ዮሐንስን ቦአኔርጌስ ብሎ ሰየማቸው፥ የነጎድጓድ ልጆች ማለት ነው፤ እንድርያስንም ፊልጶስንም በርተሎሜውስንም ማቴዎስንም ቶማስንም የእልፍዮስን ልጅ ያዕቆብንም ታዴዎስንም ቀነናዊውንም ስምዖንን፥ አሳልፎ የሰጠውንም የአስቆሮቱን ይሁዳን።*

ማርቆስ 3፡13-19

በዚህ ክፍል ውስጥ የተዘረዘሩት ሰዎች ከኢየሱስ ጋር እስከ ተገናኙበት ጊዜ ድረስ የጎላ ማንነት አልነበራቸውም፡፡ እርሱ ግን ታላቅ ገድል እንዲያከናውኑ አስችሏቸዋል፡፡ ተቀብተው ለሰባኪነት እስኪደርሱ ድረስ መርቷቸዋል፡፡

በኢየሱስ አምንታዊ ተፅዕኖ ሕይወታቸውን ሰውተው የቤተ ክርስቲያንን መሠረት ጥለዋል፡፡ አብዛኞቹ ለቤተ ክርስቲያን መሠረት በመጣሉ ሂደት ውስጥ ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡ የኢየሱስ አመራር ተራ ሰዎችን ወደ ታላቅነት ለውጧቸዋል፡፡

እግዚአብሔር ለመሪነት ከጠራህ፣ ታላላቅ ነገሮችን የምታደርገው አንተ ብቻ እንደሆንክ አድርገህ አትመልከት ፡፡ ከዚህ ይልቅ ሌሎች ለእግዚአብሔርና ለራሳቸው ታላላቅ ነገሮችን እንዲያከናውኑ እየረዳህ እንደሆነ አድርገህ ተመልከት፡፡ የእውነተኛ መሪ ልብ ይህ ነው፡፡ መሪነት የሚመነጨው ከልብ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች የሚፈጽሟቸው ድርጊቶች በሙሉ ከልብ እንደሚመነጩ ይናገራል፡፡

*አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።*

ምሳሌ 4፡23

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ማንም ሰው መሪ እንድትሆን ሊያስለጥንህ አይችልም፡፡ ይህ ከልብህ የሚመጣ ጉዳይ ነው፡- ከትክክለኛ ልብ የሚመጣ ነው፡፡ ትክክለኛ ልብ ሲኖርህ ትክክለኛ ተግባራትን ታከናውናለህ፡፡ የአንድን መሪን ልብ እስካላየህ ድረስ እውነተኛ መሪ ልትሆን አትችልም፡፡ *የቤተ ክርስቲያን ወይም የድርጅት መሪ ሆነህ*

ሳለ የሌሎችን የጥረት ውጤት ለማፌን የምትሞክር ከሆነ፣ የእውነተኛ መሪ ልብ እንደሌለህ በእርግጠኝነት እነግርሃለሁ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ራሱ ካደረጋቸው የላቁ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ነበር የፈለገው (ዮሐንስ 14፡12)

ብዙውን ጊዜ በዙሪያዬ ያሉት ታዳጊ መጋቢዎች ለእግዚአብሔር ታላላቅ ተግባራትን እንዲያከናውኑ እጸልያለሁ። በአገልግሎታቸው ልቀው እንዲነሱ ያለማቋረጥ አበረታታቸዋለሁ፣ እጸልይላቸዋለሁም። አንዳንድ ሰዎች እኔ የሌለኝ የጸጋ ስጦታ እንዳላቸው አያለሁ። ከእነርሱ ጋር ያለኝ ኅብረት ለጌታ ታላላቅ ነገሮችን ለማከናወን እንዲያስችላቸው እፈልጋለሁ። እያንዳንዱ መሪ በዙሪያው ላሉት ሰዎች ግብ ሊኖረው ይገባል። እነዚህ ግቦች ከሌሉህ መሪነትህን አጥብቄ እጠራጠራለሁ።

# አንድ መሪ ለተከታዮቹ ሊኖረው የሚገባ አራት ግቦች

## 1. በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲሳካላቸው አልም

የምትመራቸው ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲበለጽጉ መሻት ሊኖርህ ይገባል።

> ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለኝም።
>
> 3ኛ ዮሐንስ 4

## 2. ተከታዮችህ በገንዘብ እንዲበለጽጉ አልም

የሚከተሉኝ ሰዎች በገንዘብ አቅማቸው እንዲጎለብቱ ብርቱ መሻት አለኝ። በድርጅቴ ውስጥ የሚሠራ እያንዳንዱ ሰው የራሱ መኖሪያ ቤት፣ ከበቂ በላይ የሆኑ መኪናዎች እና በቂ ገንዘብ እንዲኖረው ራእይ አለኝ። ይህ ራእይ ደግሞ ቀስ በቀስ እውን እየሆነ በመሄድ ላይ ነው። መሪ ማለት ስለ ለሌሎች የሚያስብ ሰው ነው። ስለ ራስህ ብቻ የምታስብ ከሆነ፣ መሪ አይደለህም። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይከተሉት ስለነበሩት ሰዎች የገንዘብ አቅም ያስብ ነበር። ቤቶች፣ መሬትና በቂ ገንዘብ እንዲኖራቸው ይፈልግ ነበር። ብዙ ሰዎች ኢየሱስ ለተከታዮቹ እነዚህን ነገሮች ቃል እንደገባላቸው አያውቁም።

> ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ። እውነት እላችኋለሁ፥ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ቤትን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ፥ አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን ወንድሞችንና እኅቶችንም እናቶችንም ልጆችንም እርሻንም መቶ እጥፍ፥ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም።
>
> ማርቆስ 10፡29፣30

## 3. ተከታዮችህ በአካል፣ በማኅበራዊና በትዳር ሕይወታቸው ጤናማ እንዲሆኑ አልም

*ወዳጅ ሆይ፥ ነፍስህ እንደሚከናወን፥ በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ።*

**3ኛ ዮሐንስ 2**

*በዚያን ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም፡፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል፡፡ እስከ አሁን በስሜ ምንም አለመናችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ፡፡*

**ዮሐንስ 16፥23-24**

ስለምንድን ነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱ ደስታ ፍጹም እንዲሆን የፈለገው? ምክንያቱም መልካም መሪ የተከታዮቹ ሕይወት በሁሉ አቅጣጫ ደስተኛ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡

## 4. ተከታዮችህ አገልግሎታቸውን እንዲፈጽሙ አልም

ትልቁ ቅንአቴ ያስነሳኋቸው ሰዎች አገልግሎታቸውን ሲፈጽሙ መመልከት ነው፡፡ ማንኛውም አባት ልጆቹ አገልግሎታቸውን እንዲፈጽሙ ይፈልጋል፡፡ አንተም መልካም መሪ ከሆንህ፣ ራእይህ እና ቅንአትህ ለራስህ ሳይሆን ለምትመራቸው ሰዎች ነው፡፡

*አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፥ መከራን ተቀበል፥ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፥ አገልግሎትህን ፈጽም።*

**2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥5**

*ምዕራፍ 16*

# ሰዎች በደስታ እንዲታዘዙህ አድርግ

**ምሳ ከበሉ በኋላም ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን። የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው። አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው። ግልገሎቼን አሰማራ አለው።**

**ዮሐንስ 21፡15**

ኢየሱስ ሰዎች ትእዛዙን እንዲከተሉት ለማድረግ ችሏል። ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን መንጋ እንዲመግብ በነገረው ጊዜ ይህንኑ ነበር ያደረገው። መሪ ነኝ ብለህ የምታስብ ከሆነ፣ “ሰዎች ትእዛዜን ይፈጽማሉ ወይ?” ብለህ ራስህን ጠይቅ። ሰዎች አንዳንድ መሪዎችን የሚታዘዙትና ሌሎችን ግን የማይታዘዙት ለምንድነው? ሰዎች እንዲታዘዙህ የማድረግን ጥበብ አጎልብት። ይህንን ለማድረግ ልታከናውን የምትችላቸው አያሌ ነገሮች አሉ።

## ሰዎች ትእዛዝህን በደስታ እንዲፈጽሙ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘጠኝ መንገዶች

### 1. ምክንያታዊ ያልሆነ ትእዛዝ አትስጣቸው።

ሰዎች ክፉ እና ምክንያታዊ ባልሆኑ ሰዎች ላይ ያምጻሉ።

### 2. አንዳንድ ነገሮች ለምን መፈጸም እንዳለባቸው ለተካተዮችህ አስተምር

የሚከተሉህ ሰዎች የምትሰጣቸው መመሪያ ለራሳቸው ጥቅም እንደሆነ ማየት እንዲችሉ አድርግ። ሰዎች አንድን ተግባር ለምን እንደሚፈጽሙ ሲገነዘቡ፣ አብዛኛውን ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ያከናውኑታል! ለዚህ ነው ለምሳሌ ያህል “ክርስቲያኖች ነፍሳትን ለምን መማረክ እንዳለባቸው የሚያሳዩ ሃምሳ ምክንያቶች” በሚል ርዕስ ላይ የምሰብከው። ሰዎች የኢየሱስን የመጨረሻ ትእዛዝ እንዲረዱ እፈልጋለሁ።

## 3. ሁሉም ሰው ትእዛዛቱን በሚገባ መረዳት እንዲችል ዝርዝር ማብራሪያ ስጥ

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ትእዛዝህን የማይፈጽሙት ስላልገባቸው ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡

## 4. እንደማታዳላ ወይም ወገንተኛ እንዳልሆንክ አሳያቸው

## 5. አንተው ራስህ ትእዛዛቱን እንደምትፈጽም አሳያቸው

ብዙ ዓመፀኛ ሰዎች በድርጊቶቻቸው ለተከታዮቻቸው አመጸኝነትን እያስተማሩ መሆናቸውን አያስተውሉም፡፡ ወደ ኢየሱስ የመጣው የመቶ አለቃ ይህንን ምሳሌ በግሩም ሁኔታ አሳይቷል፡፡

> እኔ ደግሞ ከሌሎች በታች የምገዛ ሰው ነኝ፥ ከእኔም በታች ወታደሮች አሉኝ፥ አንዱንም። ሂድ ብለው ይሄዳል፥ ሌላውንም ና ብለው ይመጣል፥ ባሪያዬንም ይህን አድርግ ብለው ያደርጋል።
>
> ሉቃስ 7፡8

ይህ ሰው እርሱ የሰጣቸውንና ሰዎች የታዘዟቸውን ትእዛዞች እየገለጸ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አዛዥ ብቻ ሳይሆን *እርሱም ከሥልጣን ስር እንደሆነ* አመልክቷል፡፡ በሌላ አነጋገር፣ እርሱም ራሱ ትእዛዞችን ይታዘዝ ነበር፡፡ ብዙውን ጊዜ አንድ የጦር አዛዥ ሰዎችን ወደ ሞት ይመራል፡፡ ለመሆኑ በአስፈሪ የጦርነት አውድማ ላይ ወጣቶች ሕይወታቸውን እንዲሠዉ የሚያደርገው እንዴት ነው? ይህንን የሚያደርገው እርሱ ራሱ የታዘዘውን በመፈጸም ነው፡፡ ሰዎች ለወትሮው ለማከናወን የማይፈልጓቸውን ነገሮች በደስታ እንዲያከናውኑ ካላደረግህ፣ መሪ አይደለህም ማለት ነው፡፡ ይህንን ሰዎች በደስታ የሚታዘዙበትን ጥበብ ካጎለበትክ መሥዋዕትነት መክፈል እና ማገልገልን በሚወዱት አብረውህ በሚሰሩ ቡድንህ ይደነቃሉ፡፡

## 6. የሚያማርሩ እና የሚያጉረመርሙ ሰዎችን አስወግድ

እንዲህ ያሉ ሰዎች አካባቢውን በመበከል ሌሎች ሰዎች መልካም ባልሆነ ስፍራ እንዳሉ እንዲሰማቸው ያደርጋሉ፡፡ በሥራ ቦታ የደስታ መንፈስን እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ የሚያማርሩ እና የሚያጉረመርሙ ሰዎችን ከዙሪያህ አስወግድ፡፡

## 7. የተሳሳቱ አመለካከቶች ፈጽሞ ወደለየለት አለመታዘዝ እና አመጽ ከማደጋቸው በፊት የእርምት እርምጃ ውሰድ

## 8. የማይታዘዙ ሰዎችን ቅጣ

ሰዎች ጥፋት ሲፈፀም ፍርድ እንደሚከተል ካልተገነዘቡ ድርጅትህ ሊፀና አይችልም፡፡ ፍርድ አንድን አገርን ስለሚያፀና መልካም ነገር ነው፡፡ ብዙ ሥርዓት-የለሽ ድርጅቶች እንዲያ ሆነው የሚታዩት ማንም ስለማይባረር ነው፡፡ ማስጠንቀቂያዎች ቢሰጡም፣ ቅጣቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚደፍር ግን የለም፡፡ ሕግን ስታፈርስ፣ ሕግ እንደሚያፈርስህ ሰዎች ሁሉ ሊገነዘቡ ይገባል! ሕጉን በፍትሃዊነት በምታስፈጽምበት ጊዜ ሁሉም በሕጉ ብርታት ላይ አመኔታ በማሳደር በደስታ ይታዘዙሃል፡፡ አንዱ ሕግ ለተወሰኑ ሰዎች፣ ሌላው ደግሞ ለሌሎች ልዩ ሰዎች እንደሚሠራ በሚገነዘቡበት ጊዜ፣ በትእዛዞችህ ላይ ያምፃሉ፡፡

> ፍትሕን በማስፈን ንጉሥ አገርን ያረጋጋል፤ ጉቦ ለማግኘት የሚጎመጅ ግን ያፈራርሳታል፡፡
>
> ምሳሌ 29፡4

## 9. ሰዎችን እንደሚገባቸው ሸልም

ኢየሱስ እንኳ ሽልማትን ይጠባበቅ ነበር፡፡

> በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ፥ ከኃጢአተኞች በደረሰበት እንዲህ ባለ መቃወም የጸናውን አስቡ።
>
> ዕብራውያን 12፡3

ኢየሱስ ሽልማቱን እያሰበ ለአገልግሎቱ ይነሳሳ ነበር፡፡ ሰዎችን በከፍተኛ ደረጃ ለሥራ ከሚያነሳሱት ነገሮች አንዱ ሽልማት ነው፡፡ አንድ አትሌት በየቀኑ ለሰዓታት ሲሮጥ የሚውለው ለምን ይመስልሃል? ቦክሰኞች ለሕይወታቸው አስጊ የሆኑ ቡጢዎች በራሳቸው ላይ እንዲያርፉባቸው የሚፈቅዱት ለምን ይመስልሃል? ይህንን የሚያደርጉት በቡጢ መደብደቡን ተከትሎ ከሚመጣው በሚልዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚገኘውን ደስታ በማሰብ ነው፡፡

ሰዎች ከፊታቸው ላለ ደስታ ማንኛውንም ተግባር ከመፈፀም ወደኋላ አይሉም፡፡ ሽልማት ሰዎች ማንኛውንም ተግባር እንዲፈጽሙ ያነሳሳቸዋል፡፡ ስለ ክርስቶስ ራሳቸውን በፈቃደኝነት ለሞት አሳልፈው የሰጡት ሰዎች ይህንን ያደረጉት ከፊታቸው የሚጠብቃቸውን ሽልማት በማሰብ ነው፡፡

ኢየሱስ ከጴጥሮስ ጋር በተነጋገረ ጊዜ የማይፈልገው ዓይነት አሟሟት ሊደርስበት እንደሚችል ገልጾለት ነበር።

**እውነት እውነት እልሃለሁ፥ አንተ ጐልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር፤ ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ፥ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል አለው። በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን አለ። ይህንም ብሎ፡- ተከተለኝ አለው።**

**ዮሐንስ 21፡18-19**

ኢየሱስ ጴጥሮስ እስከዚያ ፍጻሜ ድረስ እንዲከተለው ነገረው። ጴጥሮስም ፈቃደኛ እና ታዛዥ ነበር። ምናልባትም፣ ጴጥሮስ ለዚህ ሞት ፈቃደኛ እንዲሆን ያደረገው ቁልፍ ጉዳይ የኢየሱስ ምሳሌነት ሳይሆን አይቀርም። ኢየሱስ በመከተል ውስጥ ያለውን ትልቅ ሽልማት አሳይቷል። አየህ፣ አመራር ምሳሌነት የማሳየት ጉዳይ ነው። አንድ መሪ ራሱ ቀድሞ መንገዱን በሚያሳይበት ጊዜ ቃሎቹ የበለጠ ኃይልን የተላበሱ ይሆናሉ። ሰዎች ቃልህን እንዲያከበሩ ትፈልጋለህን? ሰዎች ለአንተ ሲሉ ለሞት የተዘጋጁ እስከሚሆኑ ድረስ እጅግ ኃይለኛ መሪ መሆን ትፈልጋለህን? ምላሽህ አዎንታዊ ይሆናል ብዬ አስባለሁ! ይህንን ለማሳካትና በምሳሌነት ለመምራት ጊዜው አሁን ነው።

የወርሲስተር እና ግሎውሲስተር ጳጳስ የነበሩት ማስተር ጆን ሁፐር የኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ተማሪና ምሩቅ ነበሩ። እኚህ ሰው ጌታን ካገኙ በኋላ ለመጽሐፍ ቅዱስ ከፍተኛ ፍቅር አደረባቸው። በ1555 እ.አ.አ ወደ ካቶሊክ እምነት እንዲመለሱ፣ ለጳጳሱ ቅዱስነት እና ስለ ጳጳሱ የቤተ ክርስቲየኒቱ ራስነት እውቅና እንዲሰጡ ተጠየቁ። ይህንን ካደረጉ የጳጳሱን ቡራኬና የንግሥቲቱን ምሕረት እንደሚያገኙ ቃል ተገባላቸው።

የሚስተር ሁፐር ምላሽ ጳጳሱ ከክርስቶስ አስተምህሮ የሚቃረን ትምህርት እንደሚያስተምሩ ነበር። የቤተ ክርስቲያን ራስ ለመሆን ብቁም እንዳልሆኑ ተናገሩ። ከዚህም የተነሳ በምንም ዓይነት መንገድ እንዲህ ላለው ችሎት እንደማይንበረከኩ ገለፁ። ጳጳሱ ራስ ሆኖ የሚመራት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ነች የሚል እምነት እንደሌላቸው አብራሩ።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ድምፅ ብቻ ተከታይ እንደሆነችና ከእንግዳ ድምፆች እንደምትሸሽ ተናገሩ። ይሁን እንጂ ንግሥቲቱን የሚያስቀይም ነገር ተናግረው ከሆነ፣ ምሕረትን እንደሚጠይቁ

ገለጹ፡፡ "ምሕረት በንጹህ ሕሊናና እግዚአብሔርን በማያስቀይም መንገድ መከናወን አለበት" በማለት ጨምረው ተናገሩ፡፡

አንቶኒ ኪንግስተን የተባለው የረዥም ጊዜ ጓደኛቸው ለሁፐር እንዲህ አላቸው፡፡

ኪንግስተን፡ ራስህን በሞት ጉዳና ላይ አስቀምጠሃልና በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነህ በማየቴ አዝናለሁ፡፡ ሆኖም ግን ሕይወት ጣፋጭ ሞት ደግሞ መራር መሆኗን ማገናዘብ አለብህ፡፡ ስለዚህ ሊኖርህ የሚችለውን ሕይወት እያየህ ከእንግዲህ ያለው ሕይወት መልካም እንዲሆን መኖርን ተመኝ፡፡

ሁፐር፡ በእርግጥ እውነት ነው ማስተር ኪንግስተን፡፡ በዚህ እርስዎ ጳጳስ በሆኑበት ቀጠናም ሆነ በተለያዩ ቦታዎች እስካሁን ድረስ ያመንኩበትን የቀደመውን እውነት ባለመቃወሜ ራሴን ለሕይወቴ ፍፃሜና ለሞት አሳልፌ ሰጥቻለሁ፤ የምፈልገውን ያህል ባይሆንም እንኳ ስለ ወዳጅነት ምክርህ አመግናለሁ፡፡ ማስተር ኪንግስተን ሞት መራር መሆኗ ሕይወት ደግሞ ጣፋጭ መሆኗ እውነት ነው፣ ይሁንና ሊመጣ ያለው ሞት ይበልጥ መራር፣ ሊመጣ ያለው ሕይወት ደግሞ የበለጠ ጣፋጭ መሆኑን ማጤን አለብህ፡፡ ለአንደኛው ያለኝ ምኞትና ፍቅር እንዲሁም በሌላኛው ያለኝ መሸበርና ፍራቻም ያንኑ ያህል ነው፡፡ ሞትን እምብዛም አላጤነውም ለዚህኛው ሕይወትም ብዙ ዋጋ አልሰጠውም፤ይህንን የቃሉን እውነት ከምክድ ይልቅ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብርታት አሁን በተዘጋጀልኝ ኃይለኛ እሳት ጭንቅና ሥቃይ ውስጥ ማለፍ እንደምችል ራሴን አሳምኛለሁ፡፡ እስከዚያው አንተና ሌሎችም የእግዚአብሔር ምሕረት በእኔ ላይ እንዲሆን እንድትለምኑልኝ እመኛለሁ፡፡

ኪንግስተንም፡ "ጌታዬ ሆይ፣ አሁን አሳብህ መመለሻ እንደሌለው ተረድቻለሁ፡፡ እንግዲህ ልሰናበትህና ልሂድ፡፡ እግዚአብሔር እንዳውቅህ ስለፈቀደልኝ አመሰግነዋለሁ፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር እኔ የጠፋሁት ልጁን ለመጥራት አንተን ወደ እኔ ልኮሃል፡፡"

ሁፐርም መለሰ፡ "እኔም እግዚአብሔርን ለዚህ ጉዳይ ከፍ አድርጌ አመሰግነዋለሁ፡፡ ባለማቋረጥም እርሱን በመፍራት እንድትመላለስ እጸልያለሁ፡፡"

ሁፐር ለከንቲባው ያደረገው የመጨረሻው ንግግር ደግሞ እግዚአብሔርን ለመታዘዝና እውነትን ለመታዘዝ ያለውን ቁርጠኝነት በይበልጥ የሚገልጽ ነበር፡፡

“ማስተር ከንቲባ ለእርስዎና እኔን እንደ እስረኛና ወንጀለኛ ሰው እጄ እንዲያዝ ፍቃድ ለሰጠሃቸው የተቀሩት አባላትህ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ለእኔ ያለህ የቆየ ፍቅርና ወዳጅነት ከነአካቴው እንዳልጠፋ ግልፅ በመሆኑ ደስ ይለኛል። እግዚአብሔርን ይፈራ በነበረው ሟች ንጉሳችን በዚህ የአንተ ጳጳስና መጋቢ ሆኜ በተሾምኩበት ወቅት ያስተማርኩህ ነገሮች ከነአካቴው እንዳልተረሱም አምናለሁ። እጅግ እውነትና ታማኝ የሆነውን አስተምህሮ ሌሎች እንዳልተረሱም አምናለሁ። እጅግ እውነትና ታማኝ የሆነውን አስተምህሮ ሌሎች በርካታ ሰዎች እንደሚያደርጉት ውሸትና የሐሰት ትምህርት ነው በሚለው ባለመስማማቴ በንግስቲቱ ትዕዛዝ ለመሞት ወደዚህ ተልኬአለሁ። ይህንንም በደሜ ለማጽናት ወዳሰብኩበት ወደዚህ መጥቻለሁ።

አሁንም ማስተር ሽሪፍ ከእነዚህ መልካም ሰዎችና በፊታቸው ሞገስና ክብር ካገኘሁት እንዲሁም እንደ እስረኛ ለአንተ በእስር ከተሰጡሁባቸው የቅርብ ጓደኞቼ (ጠባቂዎቹ) ነገ ወደ መሞቻ ሥፍራዬ እንደምወሰድ ተረድቻለሁ።

የምጠይቀው አንድ ነገር ሁሉን ለመቋጨት ፈጣን እሳት እንዲኖር ብቻ ነው፤ እስከዚያው እኔ እንደምትፈልገው ታዛዥ እሆናለሁ።

በእዚህ ያለሁት ለሞት እንደተገደደ ሰው ሳይሆን እግዚአብሔርን በመናቅና በማሳዘን በእንግሊዝ ንጉሳውያን ተቀባይነት ያገኘውንና የተዘጋጀውን የሮማን ጳጳስ ሃይማኖት ከመቀበል ሕይወቴን ለመሰዋትና ለመስጠት እንደሚፈቅድ አንድ ሰው ነውና በማንኛውም መንገድ ጤነኛ ያልሆነ እንደሆንኩ የምታስብ ከሆነ ተረጋጋ። ነገ እግዚአብሔር ጸጋ የእግዚአብሔር ታማኝ ሠራተኛና የንግስቲቱ ታዛዥ ዜጋ ሆኜ እንደምሞት አምናለሁ።”

ወደ አንድ ሰዓት ገደማ የፈጀው በእሳት ውስጥ ተቃጥሎ የሞተበት አሟሟቱ የሆነውን ነገር ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው።

ለሞት ወደ ተቀጠረለት ሥፍራ ሲመጣ ሰላም በተሞላ አኳኋን አዘውትሮ ይሰብክበት ከነበረው የቁስ ኮሌጅን የሚሸፍነው ትልቅ ዛፍ ካለበት አጠገብ የሾላውን ተክል እንጨትና ሌሎች ለእርሱ የዳረጉ መሰናዶዎችን ተመለከተ።

በቤቶቹ ዙሪያ ያለው ሥፍራ በሰው ተሞልቶ ነበር፤ በኮሌጅ መግቢያ በር ላይ ባለት ክፍሎች ዳግም ተኩላ መሳል ደም መጣጮቹና የኮሌጁ ቄሶች ቆመው ነበር ከዚያም ለሰዎቹ ንግግር እንዲያደርግ ስለማይገደድ ተንበረከ። ወደ ጥልቅ ጸሎት ከገባ በኋላ በንግስ ቲቱ

ትዕዛዝ የሚዞር ሣጥን በወንበር ላይ ተደርጐ ከፊቱ መጥቶ ተቀመጠ። ይህንን ሲያይ "ነፍሴን ከወደድክ ውሰደው! ነፍሴን ከወደድክ ውሰደው!

ጸሎቱ እንዳለቀ ራሱን ለሸላው እንጨት አዘጋጀ። ልብሱን አወላልቆ ለሽሪፎቹ ለልብሱ ባለቤት እንዲመልሱለት ነገሯቸው ሰጣቸው። ከዚያም የተቀረውን ልብሱንና የውስጥ ልብሱን አወላለቀ። ሆኖም ግን በራስ ወዳድነታቸው ምክንያት ሽሪፍ ይህንን አልፈቀዱም፤ በታዛዥነት የሚሉትን አደረገ እናም የውስጥ ልብሱና ጋዋኑ እንዲወልቅ ተደረገ። ከዚያም በካናቴራ ስለቀረ ካናቴራውን በእግሮቹ መሃል አሰረ። እዚያም አንድ ፓውንድ ባሩድ ተደረገ በሁለቱም ክንዱ ሥርም ተመሳሳይ መጠን በጠባቂ ተደረገለት።

ሕዝቡ ከእርሱ ጋር የጌታን ጽሎት አብረውት እንዲሉ እየጠየቀ ወደ እንጨቱ ወጣ። ለወገቡ የተዘጋጀው ክብ ብረት መጣ። በሌሎች ሁለት ክብ ብረቶች አንገቱና እግሮቹ እንዲታሰሩ ሲጠየቅ ግን በጭራሽ እምቢ አለ። በዚህ ሁኔታ ከተዘጋጀ በኋላ በደንብ የሚታዩትን (ረጅም ስለሆነና ከፍ ባለ ወንበር ላይ በመቆሙ) ሁሉን ሰው ተመለከተ፤ በየጥጋጥጉ የሚታየው የሚያለቅሱ ሐዘንተኛ ሰዎች ብቻ ነበሩ። ከዚያም ዓይኖቹንና እጆቹን ወደ ሰማይ አንስቶ በልቡ ጸለየ። ጊዜው ሲገፋ እሳቱን እንዲለኩስ የታዘዘው ሰው ወደ እርሱ መጥቶ ይቅር እንዲለው ጠየቀው። ሁፐርም በእርሱ ላይ ምንም በደል አለመፈፀሙን እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ለምን ይቅር እንደሚለው ጠየቀው። "ኦ ጌታዬ እሳቱን እንድለኩስ የተሾምኩት እኔ ነኝ" አለ። በዚያም ምክንያት ሚስተር ሁፐር "ለማሳዘን ምንም ሥህተት አልሰራህም። እግዚአብሔር ኃጢያትህን ይቅር ይበል። እባክህ ሥራህን ቀጥል።

ከዚያም ሁለት ጥቅሎች ከተሰጡት በኋላ አቅፎ ሳማቸው በአንደኛው ክንዱ ሥር አንድ አደረገ ሌላውም እንዴት እንደሚደረግ አሳየ። እሳቱ እንዲለኮስ ማገዶው እስኪነድድ ትንሽ ጊዜ ፈጀ። እሳቱ በዙሪያው ቢነድድም ነፋስ እየበተነው ምንም እሳት አልነካውም።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ብዙ ደረቅ እንጨት መጣና አዲስ እሳት ተለኮሰ፤ የታችኛው የአካሉን ክፍል ቢያቃጥልም ለላይኛው የአካሉ ክፍል ብዙ ኃይል አልነበረውም። በንፋሱም ምክንያት ፀጉሩን አላቃጠለም። እሳቱ መንደድ ሲጀምር ረጋ ባለ ድምፅ "ኦ የዳዊት ልጅ ኢየሱስ ማረኝ ነፍሴንም ተቀበላት" ብሎ ፀለየ። ከዚህ በኋላ ዓይኖቹን ጠራርጐ ወደ ሰዎቹ እያየ "በእግዚአብሔር ፍቅር እሳት ጨምሩልኝ" አለ ከፍ ባለ ባልተቆራረጠ ድምፅ። ይህም ሁሉ የሆነው የታችኛው

የአካሉ ክፍል እየተቃጠለ ሳለ፣ ማገዶዎቹ እጅግ ጥቂት ስለነበሩ ግን ነበልባሉ የላይኛውን አካሉን ሳያቃጥል ነበር።

ሶስተኛው እሳት ከአፍታ በኋላ ተለኮሰ። ከበፊቶቹ ከሁለቱም ይልቅ ኃይለኛ ነበር። ከዚያም በከረጢቶቹ ውስጥ የነበረው ባሩትኀ ተቀደደ። ያኔም ንፋሱ ሊያጠፋው አልቻለም። በእሳት ውስጥ እያለ ጮክ ባለ ድምፅ "ጌታ ኢየሱስ ማረኝ፣ ጌታ ኢየሱስ መንፈሴን ተቀበል" ሲናገር የሰሙት የመጨረሻ ቃላት እኚህ ነበሩ።

አፉ ከጠቆረና መናገር እስካይችል ምላሱ ካበጠ በኋላመ እስኪኮመሽሹ ድረስ ከንፈሮቹ ይንቀሳቀሱ ነበር። ከዚያም አንደኛው እጁ እስኪወድቅ ድረስ ደረቱን በእጆቹ ይመታ ነበር። አሁንም በሌላኛው እጁ ደረቱን መምታት ቀጠለ። የንጉሰው ደምና ውሃ ከጣቶቹ ይፈስ ነበር፤ እርሱ ግን እሳቱ እስኪያይል ድረስ ቀጠለ ወዲያውኑም አጉንብሶ ሕይወቱ አለፈች።

ከዚህ በኋላ ለተጨማሪ አርባ አምስት ደቂቃዎች ተቃጠለ። እንደ በግ ሕመሙን በትዕግስት ተቀበለ። ከዚያም ወደ ፊት ወደኋላ ወይም ወደ ጐን ሳይንቀሳቀስ በአልጋ ላይ እንዳለ ሕፃን በፀጥታ ሞተ። አሁንም የተባረከ ሰማዕት ሆኖ ከምድር መሠረት በፊት ለታማኝነቱ ሁሉም ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑ ለተገባው ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ ለሆኑት በተዘጋጀው በሰማይ ደስታ ውስጥ አለ።

## *ምዕራፍ 17*

# አሰላስል፣አገናዝብ፣አሳቢ ሁን እናም በዙሪያህ የምትመለከታቸውን ነገሮች ልብ ብለህ አጢን

እኔም ተመለስሁ፥ ከፀሐይ በታችም የሚደረገውን ግፍ ሁሉ አየሁ፤ እነሆም፥ የተገፉት ሰዎች እንባ ነበረ፤ የሚያጽናናቸውም አልነበረም፤ በሚገፉአቸውም እጅ ኃይል ነበረ፥ እነርሱን ግን የሚያጽናናቸው አልነበረም። እኔም እስከ ዛሬ በሕይወት ካሉት ይልቅ በቀድሞ ዘመን የሞቱትን አመሰገንሁ፤ ከእነዚህም ከሁለቱ ይልቅ ገና ያልተወለደው ከፀሐይም በታች የሚደረገውን ግፍ ያላየው ይሻላል። ደግሞም የሰውን ድካምና የብልሃት ሥራውን ሁሉ ተመለከትሁ፥ በባልንጀራውም ዘንድ ቅንዓት እንዲያስነሣ አየሁ፤ ይህም ደግሞ ከንቱ ነፋስንም እንደ መከተል ነው። ሰነፍ እጆቹን ኮርትሞ ይቀመጣል፤ የገዛ ሥጋውንም ይበላል። በድካምና ነፋስን በመከተል ከሁለት እጅ ሙሉ ይልቅ አንድ እጅ ሙሉ በዕረፍት ይሻላል። እኔም ተመለስሁ፥ ከፀሐይ በታችም ከንቱን ነገር አየሁ። አንድ ሰው ብቻውን አለ፥ ሁለተኛም የለውም ልጅም ሆነ ወንድም የለውም፤ ለድካሙ ግን መጨረሻ የለውም፥ ዓይኖቹም ከባለጠግነት አይጠግቡም። ለማን እደክማለሁ፥ ሰውነቴንስ መልካሙን ነገር ለምን እነፍጋታለሁ? ይላል። ይህም ደግሞ ከንቱ ነገር ክፉም ጥረት ነው።

መክብብ 4፡1-8

ጥበብን አውቅ ዘንድ በምድር የሚሆነውንም ድካም አይ ዘንድ ልቤን ሰጠሁ በቀንና በሌሊት እንቅልፍን በዓይኑ የማያይ አለና ከፀሐይም በታች የተደረገውን ሥራ መርምሮ ያገኝ ዘንድ ለሰው እንዳይቻለው የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ አየሁ፡፡ ሰውም ሊፈልግ እጅግ ቢደክም መርምሮ አያገኘውም ደግሞ ጠቢብ ሰው፡-ይህን አወቅሁ ቢል እርሱ ያገኘው ዘንድ አይችልም ፡፡

መክብብ 8፡16-17

ጻድቃንና ጠቢባን ሥራዎቻቸውም በእግዚአብሔር እጅ እንደ ሆኑ፥ ይህን ሁሉ እመረምር ዘንድ በልቤ አኖርሁ፤ ፍቅር ወይም ጥል ቢሆን ሰው አያውቅም ሁሉ ወደ ፊታቸው ነው።

መክብብ 9፡1

እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የጻፈው በዘመኑ ፖለቲካዊ መሪ የነበረው ንጉሥ ሰሎሞን ነው፡፡ "ተመለከትሁ" የሚለውን ቃል ልብ በል፡፡ "ልቤን ለጥበብ ሰጠሁ…" የሚሉ ቃላቶችን

ልብ በል። ራስህን በተመለከተ እውነተኛ መሪ ነኝ ብለህ ታስባለህ? በአእምሮህ ነገሮችን ማገናዘብና በጥልቀት ማሰብ የምትጀምርበት ጊዜ ነው። በጥልቀት አስብ።

በዙሪያህ እየተከናወኑ ያሉትን ነገሮች አስተውል። በዚህ ጊዜ ጥበብን ታገኛለህ። ይህ ጥበብ ደግሞ የተሻልህ መሪ እንድትሆን ያስችልሃል። አንዳንድ ሰዎች ለምን ስኬታማ እንደሆኑ አስተውል። ሌሎች ደግሞ ለምን ስኬታማ እንዳልሆኑ መርምር።

አንዳንዶችን አሸናፊ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ምን እንደሆነ አስብ። እውነተኛ መሪ በጥልቀት የሚያስብ ነው። አንዳንድ ሰዎች ለምን ታማኝ እንዳልሆኑ ሳሰላስል ነበር። ከዚህም ነው ታማኝነት እና ታማኝ አለመሆን የሚለው መጽሐፌ የመጣው። ስለ ብዙ ጉዳዮች በማሰላስልበት ጊዜ ለትምህርቴ መሠረት የሚሆን መገለጥ አገኛለሁ።

# የአእምሮ ነጋዴው

አእምሮ ለመግዛት ወደ ገበያ ስለ ሄደ ሰው የሰማሁት አንድ ታሪክ አስታውሳለሁ። አራት ዓይነት አእምሮዎች ለሽያጭ ቀርበው ነበር። ሻጩ ይህንን አእምሮ ለመግዛት የመጣውን ግለሰብ ለመርዳት ደፋ ቀና ይላል።

ገዥው "ካሉህ አእምሮዎች ምርጥ የሆኑትን ለመግዛት እፈልጋለሁ።"

ሻጩ በመደብሩ ውስጥ ያሉትን አሳየው።

እንዲህ አለ፣ "እነዚህ አእምሮዎች የመጡት አውሮፕላኖችን፣ ሮኬቶችን እና መንኮራኩሮችን ከፈለሰፉ አገሮች ነው።"

ቀጥሎ "እነዚህ አእምሮዎች የመጡት ቴሌቪዥኖች፣ ቪዲዮዎች፣ ስልኮች፣ ራዲዮኖች፣ ስትሮዮ ኤሌክትሮኒክሶች ከፈጠረ አገር ነው" ይለዋል።

በመቀጠልም፣ "እነዚህ ሦስተኛው ዓይነት አእምሮዎች ደግሞ የመጡት ግሩም ከተሞች፣ መንገዶች፣ ድልድዮች፣ የባቡር ሃዲዶች፣ የአውሮፕላን ማረፊያዎችን፣ ወዘተ፣ ከፈጠረ አገር ነው" ይለዋል።

ከዚያም አራተኛውን የአእምሮ ምድብ በማሳየት፣ "እነዚህ አእምሮዎች ደግሞ የመጡት ምንም ነገር ካልፈለሰፈች እና ካልገነባች አገር ነው። እንዲያውም ይህች አገር መንገዶችንና ሸንት ቤቶችን ለመገንባት ከውጭ አገር የሚመጡ የውጭ ዜጎች አሏት" ሲል ያስረዳዋል።

ገዥውም፣ “አሃ! ለመሆኑ ዋጋቸው ስንት ስንት ነው?” ሲል ጠየቀው፡፡

ሻጩም መለሰ “የመጀመሪያዎቹ ሦስት የአእምሮ ምድቦች ረከስ ያሉ ናቸው፡፡ አራተኛው ግን በጣም ውድ ነው፡፡”

ገዥውም፣ “ለምንድን ነው? እነዚህ ምንም ነገር ለማስፈጸም በጥቅም ላይ ያልዋሉ አእምሮዎች ለምን ውድ ሊሆኑ ቻሉ?”

ሻጩም፣ “ኦ ይህ በጣም ቀላል ነው እነዚህ አእምሮዎች አዲስ፣ ምንም ያልሠሩ እና ከፍተኛ እምቅ ኃይል ያላቸው ናቸው፡፡ ለምንም አገልግሎት ውስጥ ስለማያውቁ እምቅ ኃይላቸው እስካሁን በውስጣቸው አለ፡፡”

ይህ አሳዛኝ ታሪክ የሚነግረን እግዚአብሔር የሰጠንን አእምሮዎች መጠቀም ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡ ምንም ያህል መንፈሳዊ ብትሆን እንኳን እግዚአብሔር አእምሮአችንን እንድንጠቀም ይፈልጋል፡፡ ታላቅ መሪ ነገሮችን በጥልቀት የሚያሰላስል፣ የሚገያናዝብ፣ የሚያወጣና የሚያወርድ እናም በጥንቃቄ የሚያስብ ነው፡፡ ማሰብ መንፈሳዊነት የጎደለው ነገር አይደለም፡፡ ይህንን የሚያህል ትልቅ አእምሮ ስላለን በእግዚአብሔር መታደል ነው፡፡ የሰው ልጆች ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ በላይ የተለቀና የበለጸገ አእምሮ እንዳላቸው ታውቃለህ? የወፍ ጭንቅላት ምን እንደሚያክል አስብ፡፡ አእምሯቸውስ ምን ያህል አነስተኛ ይሆን? ጌታ ተለቅ ያለ ነገር ስለሰጠህ ደስ አትሰኝም? እያንዳንዱ ታላቅ መሪ ስጦታውን (አእምሮውን) በአግባቡ ይጠቀማል!

## *ምዕራፍ 18*

# ለልቀት ተጋደል

*ልቀት የጥራትና የፍጹምነት ከፍተኛ ደረጃን መጨበጥ ነው። ልቆ መገኘት ልዩ ብቃትን በመላበስ የላቀ ሰው ሆኖ መገኘት ማለት ነው። እውነተኛ መሪ በመስኩ ራሱን ልዩ ለማድረግ የሚፈልግ ሰው ነው። የጌታ በረከት ዓላማ አንተን ራስ እንጂ ጅራት ማድረግ አይደለም።*

**ዛሬም ያዘዝሁህን የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሰምተህ ብትጠብቃት ብታደርጋትም፥ ዛሬም ካዘዝሁህ ከእነዚህ ቃሎች ወደ ቀኝ ወደ ግራም ፈቀቅ ባትል፥ ታመልካቸውም ዘንድ ሌሎችን አማልክት ባትከተል፥ እግዚአብሔር ራስ ያደርግሃል እንጂ ጅራት አያደርግህም፤ ሁልጊዜም በላይ እንጂ በታች አትሆንም።**

**ዘዳግም 28፡13**

*እ*ግዚአብሔር ሕዝቡ ከፍተኛውን የልቀት ደረጃ እንዲቀዳጁ የማድረግ ዕቅዶች አሉት። ለዚህ ነው ራስ ትሆናላችሁ ያለው። ልቀት በድንገት የሚገኝ ነገር አይደለም። እንዲህም ለመሆን ልትጋደል ይገባል። በቀን ለስምንት ሰዓታት ብቻ የምትሠራ ከሆነ፣ በዚህ ሕይወት ውስጥ ታላቅነትን ልትጎናጸፍ አያስችልህም። *ራሳቸውን ለማላቅ የሚፈልጉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ በሳምንት ከስድሳ ሰዓታት በላይ ይሠራሉ።* ልቀት በርትቶ መሥራትን ይጠይቃል። ልቀት፣ በአገልግሎት ውስጥ፣ በአገዛዝ ውስጥ ወይም በንግድ ውስጥ በስርገት አይመጣም። የሚመጣው በትጋት ነው።

ልቀህ ለመገኘት በላቀ ደረጃ ላይ የሚገኙትን ሰዎች ልትመስል ይገባል። *ሁሉንም ነገር ለራስህ ለማወቅ ሕይወት አጭር ነች። ከአባቶችህና ከቀደሙህ ሰዎች ለመማር ግን ሕይወት አጭር አይደለችም።* በሕክምናው ዘርፍ ከላቀ ደረጃ ላይ ለመድረስ የተቻለው ያላማቋረጥ ባለፉት ተመራማሪዎች ሥራ ላይ ተመስርተው ሌሎች ባከናወኗቸው ተግባራት አማካኝነት ነው። ለዚህ ነው ዛሬ የሰውን ልብ እስከመቀየር የተደረሰው። አንድ የልብ ቀዶ ጥገና ሕክምና ባለሙያ ጊዜውን ሁሉ በመውሰድ የደም ዑደት አቅጣጫዎችን ለመለየት ቢሞክር፣ ወደ አሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እየተመለሰ ነው ማለት ነው።

ትሁት በመሆን የሌሎችን ሰዎች ግኝቶች ተጠቀም። እግዚአብሔር በመካከለኛ ደረጃ ላይ እንድትሆን አይፈልግም። ለከፍተኛ ደረጃዎች

ጣር። የተሳካለት ነጋዴ ልትሆን ትችላለህ። ከፍተኛ የሆነ ምርትን የሚሰጥ ፋብሪካ ሊኖርህ ይችላል። በከተማይቱ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንህ የተመረጠች ልትሆን ትችላለች። የላቀ ደረጃ ላይ ለመድረስ ዛሬ ወስን። ከላቀ ደረጃ ላይ የደረሱ ሰዎች የጻፏቸውን መጻሕፍት አንብብ። መጻሕፍትን አንብብ። ካሴቶችን አድምጥ። ልቆ መገኘት ትጨብጠው ዘንድ ያንተው ነው!

## ምዕራፍ 19

# ሁሉም ነገር በአመራሩ ላይ የተደገፈ ነው

*እነሆ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከኢየሩሳሌምና ከይሁዳ ድጋፍንና ብርታትን፥ የእንጀራን ድጋፍ ሁሉ የውኃውንም ድጋፍ ሁሉ፥ ኃያሉንም፥ ተዋጊውንም፥ ፈራጁንም፥ ነቢዩንም፥ ምዋርተኛውንም፥ ሽማግሌውንም፥ የአምሳ አለቃውንም፥ ከበርቴውንም፥ አማካሪውንም፥ ብልሁንም ሠራተኛ፥ አስማት አዋቂውንም ይነቅላል። አለቆቻቸው እንዲሆኑ ብላቴኖችን አስነሣባቸዋለሁ፥ ሕፃናቶችም ይገዙአቸዋል። ሕዝቡም፥ ሰው በሰው ላይ ሰውም በባልንጀራው ላይ፥ ይገፉፉል፤ ብላቴናውም በሽማግሌው ላይ የተጠቃውም በከበርቴው ላይ ይኰራል። ሰውም በአባቱ ቤት ውስጥ ወንድሙን ይዞ። አንተ ልብስ አለህ አለቃም ሁንልን ይህችም ባድማ ከእጅህ በታች ትሁን ሲለው፥ በዚያ ቀን ድምፁን ከፍ አድርጎ። እኔ በቤቴ ውስጥ እንጀራ ወይም ልብስ የለኝምና ባለ መድኃኒት አልሆንም፤ በሕዝቡም ላይ አለቃ አታደርጉኝም ይላል... ሕዝቤንስ አስገባሪዎቻቸው ይገፉአቸዋል፥ አስጨናቂዎችም ይሠለጥኑባቸዋል። ሕዝቤ ሆይ፥ የመሩአችሁ ያስቱአችኋል የምትሄዱበትንም መንገድ ያጠፉሉ።*

ኢሳይያስ 3፥1-7፣12

በዚህ ጥቅስ ውስጥ፣ እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም እና በይሁዳ ላይ የከፋ ጥፋት እንደሚያደርስ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። እግዚአብሔር እነዚህን ሕዝቦች ለመቅጣትና ለማጥፋት ወስኖ ነበር። ይህንን የሚፈጽመው እንዴት ነበር? ጥቅሱ ይህንን ጉዳይ ግልጽ ያደርገዋል። እግዚአብሔር ይህን የሚያደርገው ሁሉንም ዓይነት መሪዎች ከማኅበረሰቡ በማስወገድ ነበር። ማኅበረሰቡም ያለ መሪ ሊቀር ሆነ። ሁሉን የሚችል አምላክ ይህንን መርህ በሚገባ ያውቃል፡- መሪ ከሌለ እድገት የለም! መሪ ከሌለ ልማት የለም! መሪ ከሌለ በረከት የለም! መሪ ከሌለ ከጠላት ጥቃት ነጻ መውጣት የለም! እግዚአብሔር መሪዎችን ከመካከላቸው ካስወገደ ሕዝቡ በፍርድ ውስጥ እንደሚወድቅ ያውቅ ነበር። ይህ የሚሆነው አመራር ለሁሉም ነገር መነሳትም ሆነ መውደቅ ምክንያት ስለሆነ ነው።

ሁሉን የሚችል አምላክ በማንኛውም ግለሰብ፣ አገር ወይም ህብረተሰብ ላይ ሊደርስ የሚችለውን እጅግ የከፋ ቅጣት እያደረሰባቸው ነበር። ይህም መሪዎች እንዳይኖሩ ማድረግ ነበር። ከላይ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ቀረብ ብለህ ከተመለከትህ፣ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ውስጥ ሁሉንም ዓይነት መሪዎች እንደሚያስወግድ እየተነበየ ነበር።

**...እነሆ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከኢየሩሳሌምና ከይሁዳ ድጋፍንና ብርታትን፥ የእንጀራን ድጋፍ ሁሉ የውኃውንም ድጋፍ ሁሉ፥ ኃያሉንም፥ ተዋጊውንም፥ ፈራጁንም፥ ነቢዩንም፥ ምዋርተኛውንም፥ ሽማግሌውንም፥ የአምሳ አለቃውንም፥ ከበርቴውንም፥ አማካሪውንም፥ ብልሁንም ሠራተኛ፥ አስማት አዋቂውንም ይነቅሳል።...**

*ይህንን ዝርዝር በጥንቃቄ ብታጠና፣ ሕዝቡ በየትኛውም ገጽታ አመራር ሊሰጡ የሚችሉ ሰዎች የማይኖሩበት አስፈሪ ሁኔታ እንደሆነ ትገነዘባለህ። መጋቢዎች ተወግደው ነበር፣ ፖለቲከኞች ተወግደው ነበር፣ አንጋፋ የአገሪቱ ዜጎች ተወግደው ነበር፣ አስተዋይ ሰዎች ተወግደው ነበር። እነኚህ ሁሉ ከማኅበረሰቡ ተወገዱ። እንዲህ ዓይነቱን ራስ የሌለው ማኅበረሰብ ብዬ እጠራዋለሁ። ራስ የሌለው አካል አካል አይደለም። እውነተኛ መሪ የሌላት ቤተ ክርስቲያን አሳዛኝ ናት! እውነተኛ መሪ የሌላት አገር የተረገመች ናት! አገሮች የሚነሡትም ሆነ የሚወድቁት በመሪዎቻቸው ነው።*

*ሁሉንም ዓይነት መሪዎች ከማኅበረሰቡ ማስወገድ እግዚአብሔር በአንዲት አገር ላይ ሊያመጣ የሚችለው የከፋ ፍርድ ነው። እንደሚታወቀው፣ ተፈጥሮ ክፍተቶችን የመሙላት ተግባራትን ታከናውናለች። እውነተኛ መሪዎች በማይኖሩበት ጊዜ የውሸት መሪዎች እንደሚመጡ ያህዌ ተንብዮአል።*

**አለቆቻቸው እንዲሆኑ ብላቴናዎችን አስነሣባቸዋለሁ፥ ሕፃናቶችም ይገዙአቸዋል...**

*እነዚህ ብላቴናዎችና ሕፃናት ብቃት የሌላቸውን መሪዎች የሚወክሉ ናቸው። ሕፃን አመጋገብ እንኳ ሳይችል አገርን የሚመራው እንዴት ነው? ከጥቂት ዓመታት በፊት በምርጫ ወቅት ለማን ድምፅ እንደሚሰጥ ጓደኛዬን ጠየቅሁት። መልስ ለመስጠት ሲያመነታ ተጨማሪ ቀጥተኛ ጥያቄ አቀረብሁለት። "ለፕሬዘዳንት እገሌ ድምፅህን ትሰጣለህ?" አልሁት።*

*በዚህ ጊዜ፣ "የአራት ዓመት ዕድሜ ካለው ልጅህ ዴቪድ እና ከፕሬዘዳንት እገሌ አንዱን ምረጥ ብትለኝ፣ የአራት ዓመት ልጅህን ብመርጥ ይሻለኛል" ሲል መለሰልኝ።*

*በመቀጠልም፣ "ከሱ ይልቅ አንድ ፍየል ፕሬዘዳንታችን ቢሆን እመርጣለሁ" አለ።*

የኔው ሕጻን ልጅም ሆነ ፍየል አገራችንን እምብዛም እንደማይረዷት ግልጽ ነው። በልጆች ወይም በሕጻናት ወይም ደግሞ ይህ ሰው እንዳለው በፍየል መመራት በእርግጠኝነት መርገም ነው።

የእንዲህ ዓይነት ተገቢ ያልሆኑ መሪዎች መኖር ውጤት ምን ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ምላሽ አለው።

**ሕዝቡም፥ ሰው በሰው ላይ ሰውም በባልንጀራው ላይ፥ ይገፋፋል፤ ብላቴናውም በሽማግሌው ላይ የተጠቃውም በከበርቴው ላይ ይኰራል።**

እንዲህ ዓይነት ጭቆና፣ ኢ-ፍትሃዊነት፣ ጫናና ሁሉም ዓይነት ክፋት የነገሠበትን ሁኔታ አይተህ አታውቅም? በአፍሪካ አማጺያን እንደ አሸን እንዲፈሉ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ በሺህ በሚቆጠሩ ወጣቶች የእፅ ሱሰኞች እንዲሆኑ የሚያደርግ ባህል እንዲጎለብት ያደረገው ምንድር ነው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታይ የትኛውም መጥፎ ሁኔታ ከመልካም አመራር አለመኖር ጋር ሊያያዝ ይችላል። ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መከፋፈልና አሳፋሪ ድርጊቶች ጠንካራ አመራር ካለመኖሩ የሚመነጩ ችግሮች ናቸው። ከላይ የቀረበው ጥቅስ እግዚአብሔር መሪዎችን በማስወገድ ምድሪቱን እንዴት ሊረግም እንዳለ ይነግረናል። ቤተ ክርስቲያናት የሚነሡትና የሚወድቁት በአመራር ላይ ነው። መልካም እና ጠንካራ መሪ ያላት አንዲት ቤተ ክርስቲያን ወደ ሜጋ ቤተ ክርስቲያንነት እያደገች ትሄዳለች። መጥፎ አመራር ካለ መጋቢው እጅጉን የተቀባ ቢሆን እንኳ ቤተ ክርስቲያናት የትም አይደርሱም። አንዳንድ ጊዜ መጥፎ አመራር ያለው የተቀባ መጋቢ ታያለህ። በአብዛኛው ከመጥፎ አመራር የተነሳ አገልግሎቱ ይፈራርሳል።

አመራር ጥበብ ነው። ይህ የወንጌሉ አገልጋዮች ሊረዱ የሚገባ ዓለማዊ ትምህርት ነው። የማንበብና የመጻፍ ችሎታ መንፈሳዊ ሳይሆን ልንማር የሚገባን ዓለማዊ ትምህርት ነው። ይህ ክህሎት ከሌለህ በዚህ ዓለም ውስጥ የትም ልትደርስ አትችልም። አመራርም እንደዚሁ ነው! የአመራር እውቀትና ክህሎት እስከሌለህ ድረስ አገልግሎትህ የትም ሊደርስ አይችልም።

## አፍሪካ ያለ መሪዎች

ብዙውን ጊዜ ከጓደኞቼ ጋር የማደርገው ክርክር ስለ አፍሪካ አህጉር ሁኔታ ነው። ብዙዉን ጊዜ በአፍሪካ አህጉር ውስጥ ያለው የልማት እጦትና የድህነት ሁኔታ ያስገርመኛል። “ይህ የሆነው ለምንድነው? የራሳችንን መንገዶች መሥራት የለብንም ወይ? የውጭ አገር

ኩባንያዎች መንገዶችንና ሽንት ቤቶችን እንዲሠሩልን የምናደርገው ለምንድነው?” እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ። ወደ አውሮፓ አገሮች ብንሄድ የውጭ አገር ኩባንያዎች መንገዶቻቸውንና ሽንት ቤቶቻቸውን ሲሠሩ አንመለከትም። በድሀ አገሮች ውስጥ ከፍተኛ ሥቃይና በሽታ የተበራከተው ለምንድነው?

ድሀና ያልተረጋጉ አገሮችን ችግሮች ለማብራራት የቀረቡ ብዙ ንድፈ-አሳቦች አሉ። አንዳንድ ሰዎች በጥቁሮች ላይ እርግማን አለ ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ይህ የዴሞክራሲ እጦት ችግር የወለደው ነው ይላሉ። በአፍሪካ ክፍለ አህጉር ላይ ርግማን አለ ብለው የሚያስቡ ሰዎችም አሉ። እንደ እኔ እምነት ከሆነ ግን፣ ለአፍሪካ ድህነት ቀንደኛው ምክንያት የጥሩ መሪዎች አለመኖር ነው።

መልካም መሪ ባለባቸው ስፍራዎች ሁሉ ከፍተኛ ልማትና ብልጽግና ሲስፋፉ ታያለህ። የመሪዎች አለመኖር በሁለት ዓለማት ውስጥ በግልጽ ይታያል። በተፈጥሯዊ ወይም ዓለማዊ ሕይወት ውስጥ የመሪዎችን አለመኖር መረዳት ይቻላል። በመንፈሳዊውም ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥም የመሪዎችን አለመኖር ማጤን ይቻላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዎች በማይኖሩበት ጊዜ የአገልግሎት አለመልማት፣ ድህነት፣ የእውቀትና የማስተማር ጉድለት፣ እንዲሁም የኃጢአት መሰራጨት በስፋት ይታያል።

## ቤተ ክርስቲያናት ያለመሪዎች

መልካም አመራር በስፋት በማይታይባቸው አገሮች ውስጥ የውሸት መሪዎች፣ አማጺያንና ዘራፊዎች ይነሣሉ። በቤተ ክርስቲያንም መልካም መሪዎች በማይኖሩበት ጊዜ ኃጢአት ይስፋፋል ክፉ አድራጊዎችና የሐሰት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይነሳሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዎች በማይኖሩበት ጊዜ ብዙ ሰዎች በክርስቶስ የማመን እድል ሳያገኙ ሞተው ወደ ሲኦል ይወርዳሉ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

እውነተኛ መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምእመናን ነፍሳትን እንዲማርኩና የሚስዮናዊነትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ይመራል። የቤተ ክርስቲያን አመራር ለሚጠፉትና ለሚሞቱት ነፍሳት ያለው ትኩረት ሲቆም ሐሰተኛ ሃይማኖቶችና አማራጭ እምነቶች ሰርገው በመግባት ይቆጣጠሩታል።

ለዚህ ነው ይህንን መጽሐፍ የምጽፈው። በሁሉም የሕይወት ክፍል መሪነት አስፈላጊ ነው። እውነተኛ መሪዎች በዓለም ውስጥ ያስፈልጋሉ። በቤተ ክርስቲያን ዓለም ውስጥ እውነተኛ መሪዎች ያስፈልጋሉ። እግዚአብሔር አንተንና ሌሎችንም ለትውልድህ እንዲያስነሳችሁ ጸሎቴ ነው! በእውነቱ ሁሉም ነገር በአመራር ላይ ይደገፋል!

*ምዕራፍ 20*

# ሰዎችን በዙሪያህ አሰባስብ

. . . የኤልያዳን ልጅ ሬዞንን . . . ሬዞን ሰዎቹን በዙሪያው አሰባስቦ የወንበዴ አለቃ ሆነ. . .

1ኛ ነገሥት 11፡23-24

ይህ ሬዞን የሚባል ሰው በዘመኑ መሪ ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን ወደ ራሱ ሰብስቦ እንደነበር ይነግረናል። ማንኛውም እውነተኛ መሪ ሰዎችን ወደ ራሱ የመሰብሰብ ብቃት አለው። ኢየሱስ አሥራ ሁለት ሰዎች የሚገኙበትን ቡድን ወደ ራሱ ሰብስቦ ነበር። ለሦስት ዓመት ተኩል ከእነርሱ ጋር በመኖር ኅብረት ያደርግ ነበር። የሰዎች መሰባሰቢያ ማዕከል ለመሆን ወስን። አመራርን ከልብህ ከያዝኸው፣ ማንኛውም ሰዎችን የሚያሰናክልና የሚበትን ባሕሪይ በስእብናህ ላይ ካለ ማስወገድ አለብህ። ሰዎችን ሳታስቀይምና ሳትበትን መናገርን ተማር።

## ሰዎችን ከዙሪያህ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ሃያ ሁለት እርምጃዎች

1. ሰዎች በዙሪያህ እንዲሆኑ በእውነት እንደምትፈልግ እንዲሰማቸው አድርግ

2. በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች አድንቅ

በአካባቢህ ያሉት ሰዎች አነስተኛ ስኬትና ድል በሚቀዳጁበት ጊዜ ባገኙት ውጤት አብረሃቸው ተደሰት። የደስታቸው ተካፋይ የሆነ ሰው እንዳለ ሲሰማቸው ደስታቸው ይጨምራል።

3. የሰዎችን ቤቶች፣ መኪኖች፣ የቤት ዕቃዎቻቸውንና ልብሶቻቸውን ከልብህ አድንቅ

መኪኖች፣ ቤቶችና ልብሶች የሰዎችን ምርጫዎችና ድሎች ያንፀባርቃሉ። የሰዎችን ምርጫዎችና ድሎች ካደነቅህና ካከበርህ፣ ሰዎቹን እያደነቅህ ነው! ይህም ለአንተ መልካም አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል!

## 4. ምንም ይሁኑ ምን ወይም ባላቸው ነገር ሳትገደብ እንደምታከብራቸው አሳያቸው

ሰዎች እንደምታከብራቸው በሚገነዘቡበት ጊዜ ልባቸውን ይከፍቱልሃል። በዚህች ዓለም ውስጥ ብዙ ሰዎች የተከበሩ አይደሉም። ጠቅለል ባለ አነጋገር ጥቁሮች በነጮች የተከበሩ አይደሉም። በእኔ አስታያየት፣ አውሮፓውያንና አሜሪካውያን አፍሪካውያንን አያከብሯቸውም። የተናቁና የተጠሉ ብሔሮችም አሉ። ሰዎች ከዘር፣ ከማንነታቸው ወይም ካላቸው የገንዘብ መጠን ባሻገር በእውነተኝነት የሚያከብሯቸውን ይፈልጋሉ። በዚህ ዓይነት ሰዎችን የማክበር ችሎታ ያለው ሰው ማንም ይሁን ማን ሰዎችን በዙሪያው የማሰባሰብ ብቃት ይኖረዋል።

## 5. የበታችነት ስሜት የሚሰማቸውን ሰዎች በጥንቃቄ አስተናግዳቸው

## 6. ቀልድ ከማይወድ ሰው ጋር አትቃለድ

ስትቀልድባቸው የሚከፋቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ። ብዙውን ጊዜ ይህ የሚሆነው በልጅነታቸው ከገጠማቸው ችግር ሳቢያ ነው።

## 7. ከሰዎች ጋር ከተዋወቅህበት ጊዜ ጀምሮ በስማቸው ጥራቸው

ማንም ቢሆን እንደ ቁጥር ማሚያ መታየት አይፈልግም። ስለሆነም ሰዎች በስማቸው በምትጠራቸው ጊዜ ልባቸውን ይከፍቱልሃል። በቁልምጫ ስማቸው ብትጠራቸው ደግሞ የበለጠ ደስ ይላቸዋል።

## 8. ለሰዎች የግል ሕይወት ፍላጎት እንዳለህ አሳይ

ስለ ቤተሰባቸው፣ ስለ ሥራቸውና ስለ ትምህርት ቤታቸው ጠይቃቸው። ሰዎች መሪው ስለ ግል ሕይወታቸው ግድ እንደሚለው ሊሰማቸው ይገባል።

## 9. ለሰዎች ከፍተኛ የተነሳሽነት ስሜቶች፣ ራእዮችና ግቦች ፍላጎት አሳይ

የምታስበው ስለራስህ ራእይና ግብ ብቻ ከሆነ፣ ሰዎች በዝምታ ከአንተ ይሸሻሉ። ነገር ግን እነርሱን ስኬታማ የማድረግ አሳብ እንዳለህ በሚረዱበት ጊዜ ወደ አንተ ይሰባሰባሉ።

## 10. በቻልክ ጊዜ ሁሉ ለእንግዶች የሚበላና የሚጠጣ ነገር አቅርብላቸው

የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሳለሁ በካምፓስ ውስጥ የነበሩትን ብዙ ሰዎች ጎብኝቼአለሁ። በተለይም አዲሴዲ በይደን የምትባል አንዲት እህት አትረሳኝም። ወደ ክፍሏ በሄድን ቁጥር የሆነ የሚባለ ነገር ታቀርብልናለች። ብዙውን ጊዜ እሷ እና የክፍል ጓደኛዋ እራታቸውን ያካፍሉን ነበር። ይህም ክፍሏን የመሰብሰቢያ ማእከል አደረገው! አንተም የመሰባሰቢያ ማዕከል ለመሆን ከፈለግህ በተቻለህ መጠን ለሚመጡ ሰዎች የሚበላና የሚጠጣ ነገር ማቅረብ ልመድ!

## 11. የሰዎችን ችግሮች አድምጥ

ከመናገር ይልቅ የማድመጥን ጥበብ ተማር። ሰዎች ስለራሳቸው እንዲናገሩ በምትፈቅድላቸው ጊዜ ለአንተ ቅርበት እንዳላቸው ይሰማቸዋል። ይህም በዙሪያህ እንዲሰባሰቡ ያደርጋቸዋል።

## 12. ውይይቱ ከአንተና ከድርጊቶችህ ይልቅ በሌሎች ሰዎችና በድርጊቶቻቸው ዙሪያ እንዲያማክል አድርግ

በራስ ላይ ያማከሉ ውይይቶች ማድረግ ከንቱ ነው። ውይይቶችህ የሚያጠነጥኑት ስለ አንተ፣ ስለ ድሎችህና ስለ ራእዮችህ ብቻ ከሆነ፣ ሰዎች ገድልህን መስማት ይሰለቻቸውና መሸሽ ይጀምራሉ።

## 13. የምታበረታታ ሁን

ሁልጊዜም አንድ ሰው አንድን ውጤት ለማስመዝገብ የሚያደርገውን ጥረት አጢን። ምናልባትም መዝሙር ዘምረው ወይም አዲስ የፀጉር አሠራር ፈጥሮ ይሆናል። ምንም እንኳን ባትወደውም ግለሰቡ ላደረገው ጥረት አበረታታው። ያደረጉትን እንዳልውደድክ መናገር አይገባህም። ማድረግ ያለብህ ነገር ቢኖር የተደረገውን ጥረት በማጤን ማድነቅ ነው።

## 14. ለሁሉም ነገር ምስጋናህን ግለፅ

ሰዎች ምስጋና የለውም የሚል ስሜት ከሚሰማቸው ይልቅ ምስጋና ያበዛል ብለው ቢያስቡ ይሻላል።

## 15. ፈገግታ አይለይህ

ሰዎች ፈገግ በሚሉና የጓደኝነት መንፈስ በሚያሳዩ ሰዎች ዙሪያ ይሳባሉ። ሁላችንም ፍጹም አለመሆናችንን ስለምናውቅ፣ ሌላ ሰው

ፊቱን ቅጭም አድርጎ መሳሳታችንን እንዲነግረን አንፈልግም። ሰዎች ውደቀት ቢኖርባቸውም፣ የሚያበረታታቸውንና የሚቀበሏቸውን ሰዎች ይሻሉ።

## 16. አታዳላ

ሰዎች ከመሪዎች ልብ ከሚሿቸው ቀዳሚ ነገሮች አንዱ ሲያደሉ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አድልዎ ጥበብ የጎደለው ተግባር እንደሆነ በያዕቆብ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 17 ላይ ያመለክታል።

> ከሰማይ የሆነችው ጥበብ ግን . . . አድሎዎና ግብዝነት የሌለባት ናት።
>
> ያዕቆብ 3፡17 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ትናንሽ ልጆች ሳይቀሩ ወላጆቻቸው ለአንደኛው ልጅ በሚያዳሉበት ጊዜ ሁኔታውን ይገነዘባሉ። ያለ ምክንያት የተዛባ አመለካከት ያለውንና የሚያዳላን ሰው መከተል የሚፈልግ የለም። ሳታውቅ ድንገት በእርሱ ጥቁር መዝገብ ውስጥ ብትሰፍርስ? መሠረተ-ቢስ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተመሥርቶ የሚጠላህ መሪ ያለበት አገር ውስጥ መኖር ከባድ ነው። መሪው በስሜቱ ላይ ተመሥርቶ ጥላቻ በሚያሳይበት ድርጅት ውስጥ መሥራትም ከባድ ነው።

## 17. አጋጣሚው ሲገኝ ስጦታዎችን አበርክት

ስጦታ ለአንድ ሰው መንገዱን ታሰፋለታለች። “የሰው ስጦታ መንገዱን ታሰፋለታለች፥ በታላላቆችም ፊት ታገባዋለች።” (ምሳሌ 18፡ 16)። ይህ ማለት ስጦታ የሰጠኸው ግለሰብ በልቡ ውስጥ ለአንተ ስፍራ ይኖረዋል ማለት ነው። በግለሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን ስለምታገኝ ከአንተ ጋር ለመሆን ይፈልጋል።

## 18. ከሚያለቅሱ ጋር አልቅስ

ሰዎች በሕይወታቸው ከማይረሷቸው ጊዜያት መካከል የሀዘን ጊዜያት ተጠቃሾች ናቸው። በመሆኑም፣ በሀዘናቸው ወቅት የደረስካቸው ሰዎች ምን ጊዜም አይረሱህም። ወላጆቻቸው ሲሞቱ ከጎናቸው ስለሆንህ የቤተ ክርስቲያኔ አባላት የሆኑ ሰዎች አይቻለሁ።

## 19. ሰዎችን ለመርዳት ተጨማሪ ምዕራፍ ሂድ

ማንኛውንም የተቸገረ ሰው በሚያስፈልገው ነገር ከረዳኸው ያስታውስሃል። እነርሱን ለመርዳት የተጓዝከው ተጨማሪ ምዕራፍ ልባቸውን ይነካዋል። እነዚህ ሰዎች ለአንድ ዓላማ በዙሪያህ እንዲሰባሰቡ ጥሪ ብታደርግላቸው ከጎንህ ይቆማሉ፣ ምክንያቱም

ያደረግላቸውን ያስታውሳሉና። ይህንን አንድ ነገር ላረጋግጥልህ እፈልጋለሁ፡- በሰዎች ሕይወት ውስጥ የመርዳትን ዘር ካልዘራህ ወደፊት ማንም ሊረዳህ አይችልም።

## 20. የወዳጅነትን መንፈስ አሳይ፣ በመልካም ሁኔታ ሰላምታ ስጥ

ቀለል ያልክና ተግባቢ ሁን፡- ከሰዎች ጋር ተጨባበጥ፣ እቀፋቸው፣ ጀርባቸው ላይ ቸብ ቸብ በማድረግ አበረታታቸው፤ ተግባቢና አስደሳች መንፈስ ያለህ ሰው ሁን። የተሟሟቀ ሁኔታ መስብ አለው። ቀዝቃዛ ሰዎች በተፈጥሯቸው ሰዎችን የመሳብ አቅም የላቸውም።

## 21. የሰዎችን ችግሮች በምታደምጥበት ጊዜ ግድ ይበልህ

የሰዎችን ችግሮች ስትሰማ የፊትህ ገጽታ ማዘንህንና ለጉዳዩ ክብደት መስጠትህን ሊያሳይ ይገባል። ዝርዝር ጉዳዮችን በማስታወስ ታሪኩን እየተከታተልክ መሆንህን አስመስክር።

## 22. ሰዎች ከአጠገብህ በሌሉ ጊዜ አስተውል

ሰዎች በሌሉበት ሰዓት እንዳላስታወስኳቸው ሲገነዘቡ ቅር ይላቸዋል። አለመኖራቸውን ጭራሽ የማታስታውስ ከሆነ፣ እንዴት ለአንተ አስፈላጊዎች ሊሆኑ ይችላሉ?

እነዚህ ሃያ ሁለቱ እርምጃዎች ተፈጥሯዊ የመሰብሰቢያ ማዕከልና ተፈጥሯዊ መሪ እንድትሆን ያደርጉሃል።

## *ምዕራፍ 21*

# ከመልካምና ቀላል ነገሮች ይልቅ ከባድና አስቸጋሪ ነገሮችን ምረጥ

*አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ። ነገር ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ።*

**ዮሐንስ 12፡27**

ከመልካምና ቀላል ነገሮች ይልቅ ከባድና አስቸጋሪ ነገሮችን ስትመርጥ ራስህን ወደ ተፈጥሯዊ መሪነት ትቀይራለህ። አብዛኞቹ ሰዎች መልካምና ቀላል ነገሮችን ይመርጣሉ። ለዚህ ነው አብዛኞቹ ሰዎች ወደ ሲኦል የሚያደርሰውን ሰፊ ጎዳና ይዘው የሚጓዙት።

ከቀላልና ለስላሳ ነገሮች ይልቅ ከባድና አስቸጋሪ ነገሮችን ብትመርጥ በሕይወትህ በፍጥነት ወደፊት ትጓዛለህ። መሪ ቀድሞ ለመገኘት ሁልጊዜ አንድ እርምጃ ወደፊት የሚራመድ መሆን አለበት። እውነተኛ መሪ ልትሆን የምትችለው አንድ ደረጃ ቀድመህ ስትገኝ ብቻ ነው።

በሕይወት ውስጥ ወደፊት የሚያሸጋግሩህ ነገሮች በአመዛኙ ከባድና አስቸጋሪ ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ በጣም ወሳኝ ነገሮች ናቸው። ከእነዚህ ነገሮች አንዱ ጸሎት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትም ልታደርጋቸው ከሚገቡህ አስፈላጊ ነገሮች አንዱ ነው። ጾም እያንዳንዱ ክርስቲያን ሊያጎለብት የሚገባው ጠቃሚ ልማድ ነው። ይሁን እንጂ አብዛኞቻችን እነዚህን ነገሮች የማከናወን ፍላጎት የለንም። እውነተኛ መሪ ሰዎች እነዚሁኑ ነገሮች እንዲያደርጉ ማድረግ ይችላል። ብዙውን ጊዜ ሕዝቤን ወደ ጾምና ጸሎት እመራለሁ። ይህ ለኔም ሆነ ለምእመኖቼ ከባድ ነው። ይህም ሆኖ፣ እናደርገዋለን! በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ለረዥም ሰዓታት እንዲጾሙና እንዲጸልዩ ለማድረግ የምችለው እንዴት ነው? ይህንን የማደርገው ራሴው በማድረግ እና ስተገብረው እንዲመለከቱ በማድረግ ነው!

# ቀድመህ ለመገኘት ልታከናውናቸው የሚገቡ ሰባት ከባድ እና አስቸጋሪ ነገሮች

1. ዕለታዊ የጥሞና ጊዜ ይኑርህ።
2. በየቀኑ መጽሐፍ ቅዱስህን አንብብ።
3. በየቀኑ ለሰዓታት ጸልይ።
4. መደበኛ የጾም ጊዜ ይኑርህ።
5. ለአንተ አዳዲስ የሆኑ ነገሮችን ተማር።

በአገልግሎት ዘመኔ ለወትሮው የማልፈልጋቸውን አዳዲስ ነገሮች መማር ያስፈልገኝ ነበር። ወደፊት ያራመደኝም እነዚህን አንዳንድ አስቸጋሪ ነገሮች ማድረጌ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ የፈውስ አገልግሎት መጀመር ካደረግኋቸው ነገሮች ሁሉ በአንደኛ ደረጃ በጣም አስቸጋሪ ነበር። ይህ ከባድና አስቸጋሪ ነበር! ይሁን እንጂ እነዚያን አስቸጋሪና ከባድ እርምጃዎች በመውሰዴ ደስተኛ ነኝ። የፈውስ አገልግሎት ያለ እርሱ ልደርስበት የማልችለውን የመታየት ደረጃ ሰጥቶኛል። ያንን አስቸጋሪና ከባድ እርምጃ በመውሰዴ አገልግሎቴ ይበልጥ የክርስቶስን አገልግሎት እየመሰለ ሲሄድ ተመልክቻለሁ። ስለ ከባድና አስቸጋሪ ነገሮች በማካፍልበት ጊዜ ሁሉ ስለዚህ የፈውስ አገልግሎት አስታውሳለሁ። ከዓመታት ተሞክሮ በኋላ እንኳ ለታመመ ሰው መጸለይ ቀላል ነገር አይደለም።

6. መጻሕፍትን ያለማቋረጥ በማንበብ ራስህን አስተምር
7. ጌታ የሚነግርህን ሁሉ ታዘዝ

ወደፊት ለመራመድ ወሳኝ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ጌታን መታዘዝ ነው። ጌታን በምትታዘዝበት ጊዜ የሚለቀቅልህን ኃይል በቃላት ልገልጽልህ አልችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ ግቡን የመታው እግዚአብሔርን በመታዘዝ ነው። ከባድ እና አስቸጋሪ ቢሆንም አድርጐታል! በነበረበት መንግሥተ ሰማይ መቆየቱ ቀላልና ግሩም ነበር። ትእዛዛቱን መታዘዝ ለእርሱ ከባድ እና አስቸጋሪ ነበር ይሁን እንጂ የታዘዘውን ፈፅሞታል። ኢየሱስ ሊታዘዝ ያለውን ትእዛዝ ባሰበ ጊዜ ፊቱ በሐዘን ተሞላ። ሆኖም ግን ራሱን አበረታታ። በፊቱ የነበረውን መስቀል ባሰበ ጊዜ ኢየሱስ የተናገራቸውን ቃላት አስተውል።

**አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ። ነገር ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ።**

**ዮሐንስ 12፡27**

ኢየሱስ ራሱን በማረጋጋት በዚያ ውስጥ ለማለፍ ወሰነ፡፡ አንተም እንደ ኢየሱስ ደስ ከሚለውና ከቀላሉ ይልቅ ከባድና አስቸጋሪ የሆነውን ምረጥ ይህም ከመልካም ስፍራ ላይ ያደርስሃል፡፡

## ምዕራፍ 22

# አዳዲስ አሳቦችን ለመቀበል የተዘጋጀህ ሁን

አዳዲስ አሳቦችን ለመቀበል ካልተዘጋጀህ አመራርህ አጥጋቢ ውጤት ሊያመጣ አይችልም፡፡ ዓለም ባለማቋረጥ እየተለወጠች ነው፡፡ የድሮ ዘዴዎችና መንገዶች አሁን ውጤት አያመጡም፡፡ ኮምፒዩተሮች የሥራ ማከናወኛ መንገዶችን ለውጠዋል፡፡ ወቅቶች ይለዋወጣሉ፡፡ ፍላጎቶች ይለወጣሉ፡፡ ሰዎችም ይለዋወጣሉ፡፡ ለዚህ ነው እግዚአብሔር ሁልጊዜም አዳዲስ እና የተለዩ ነገሮችን የሚያስተዋውቀን፡፡

በበኩሌ ለአዳዲስ አሳቦች በጣም ክፍት ነኝ፡፡ ለረዥም ጊዜ በተለየ መንገድ ስጠቀምበት የነበረውን አሠራር መለወጥ ቅር አይለኝም፡፡ እግዚአብሔር የአዎንታዊ ለውጥ አምላክ እንደሆነ አውቄአለሁ! እግዚአብሔር የመሻሻል አምላክ ነው!

አዳዲስ አሳቦችን በማቀርብላቸው ጊዜ ሰዎች ሲስቁብኝ አስተውያለሁ፡፡ አንዳንድ የሥነ-ህንፃ ባለሙያዎች (አርክቴክቶች)፣ መሃንዲሶች፣ ቴክኒሺያኖች፣ አናጺዎች፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ የሒሳብ ባለሙያዎችና መጋቢዎች አዳዲስ አሳቦች ለመቀበል አሻፈረኝ ሲሉ በመገረም ተመልክቼአለሁ፡፡ አዲስ አሳብ ሳፈልቅ እርስ በእርሳቸው እንዴት እንደሚስቁብኝ እና እንደሚያፌዙብኝ አስተዋልሁ፡፡ "እኛ ነገሮችን እንዲህ አንሠራም፡፡" "ይህ ከዚህ በፊት ተደርጎ አያውቅም!" "ያለነው አሜሪካ ውስጥ አይደለም፡፡" "በአውሮፓ ውስጥ ያሉት ነገሮች ቢኖሩን ኖሮ ልናደርገው እንችል ነበር፡፡" "ታውቃለህ፣በውጭ አገር ያሉት ሰዎች ብዙ መሣሪያዎች አሏቸው፡፡" "በጋና እንዲህ ዓይነት ነገር ማድረግ አይቻልም፡፡" "ይህ ተጨባጭነት ያለው አይደለም፡፡" እንዲህ ዓይነት አባባሎችን ሰምቼአለሁ እናም እንዲህ ዓይነት መልእክቶችን በቃላት ባይገለጹም እንኳን አለያቸዋለሁ፡፡

አውሮፓውያን ዓለምን በሚያስሱበት እና እኛን ሲያገኙ፣ አፍሪካውያን በክፍለ አህጉራቸው ተቀምጠው ነበር፡፡ እነርሱ መጥተው እስኪያገኙን ድረስ አፍሪካ ውስጥ ለምን ጠበቅን? ከአድማስ ባሻገር ያሉትን አገሮች ለምን አላገኘናቸውም? አፍሪካውያን አዳዲስ አካባቢዎችን በመቃኘት አውሮፓውያንን ለምን ፈልገው አላገኟቸውም? እንደ መሪ ወደፊት ለመራመድ ምስጢሩ ለአዳዲስ

አሳቦች እራስን ክፍት ማድረግ ነው። ከመንፈሳዊነት በስተቀር በሌሎች ነገሮች ሁሉ አውሮፓውያን ቀዳሚ ስፍራ ይዘው መገኘታቸው አስገራሚ ሊሆን አይገባም።

እግዚአብሔር የለውጥ አምላክ ነው። እርሱ አዳዲስ ተግባራትን እያከናወነ ነው። አዳዲስ አሳቦችን በታማኝነት አስተናግድ። አዳዲስ ዘዴዎችን ሞክር። አዳዲስ የአሠራር መንገዶችን መሞከር በመስክህ ከሌሎች ቀድመህ እንድትገኝ የሚያደርግ ቁልፍ ነገር ሊሆን ይችላል። የትርፍ ጊዜ አገልግሎትን የጀመርሁት ሌሎች ሰዎች ሲያደርጉት አይቼ አልነበረም። የጀመርሁት አዲስ ቢሆንም እንኳ መጀመር ስላለበት ነበር። የአዳዲስ ነገሮች አምላክ የሆነውን ሰማያዊ አምላኬን ምሳሌነት መከተሌ ነበር። አንተም የሰማያዊ አምላክህን ምሳሌነት ተከተል። ከእርሱ የተሻለ አሠልጣኝ የለም።

## እግዚአብሔር የሚያከናውናቸውን አዳዲስ ተግባራት የሚያሳዩ አምስት ምሳሌዎች

### 1. እግዚአብሔር አዳዲስ ፕሮጀክቶችን፣ ዕቅዶችንና አሳቦችን ይጀምራል።

እነሆ፥ አዲስ ነገርን አደርጋለሁ፤ እርሱም አሁን ይበቅላል፥ እናንተም አታውቁትምን? በምድረ በዳም መንገድን በበረሀም ወንዞችን አደርጋለሁ

ኢሳይያስ 43፡19

### 2. እግዚአብሔር ለሕዝቡ አዳዲስ ቋንቋዎችን ይሰጣል።

ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ።

ማርቆስ 16፡17

### 3. እግዚአብሔር ለባሪያዎቹ አዳዲስ ትእዛዛትን ይሰጣል።

እያንዳንዱ ትእዛዝ የሚያበቃበት ቀን አለው።

እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

ዮሐንስ 13፡34

### 4. እግዚአብሔር ከዚህ በፊት ያልነበርን ፍጹም አዲስ ሰዎች ያደርገናል።

ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።

2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17

## 5. እግዚአብሔር አዲስ ስምምነቶችን ያደርጋል እናም ለአገልግሎትም አዲስ ጥሪዎችን ያደርጋል፡፡

ግልጽ ክፍት ከሆንህ ድምፁን ትሰማለህ፡፡

አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቶአል፤ አሮጌና ውራጅ የሆነውስ ሊጠፋ ቀርቦአል።

ዕብራውያን 8፡13

## ምዕራፍ 23

# ለሰዎች ትልቅ ዋጋ ስጥ

ሰዎች የሚሳቡት ትልቅ ዋጋ ወደሚያገኙባቸው ስፍራዎች ነው፡፡ ብዙ ድርጅቶች ለሰዎቻቸው ዋጋ አይሰጡም፡፡ ዋጋ እንዳልተሰጠው የሚሰማው ሰው ሁሉ ይርቃል፡፡

ያደጉ አገሮች ሁሉ ለዜጎቻቸው ትልቅ ዋጋ ይሰጣሉ፡፡ ያከበርከው ወደ አንተ ይመጣል፡፡ ያጠቃኸው ይርቅሃል፡፡ ሕዝቦች የአንድ መሪ ወሳኝ ሀብቶች ናቸው፡፡ በመሪዎቹ ላይ ጥቃት የሚሰነዝር ሕዝብ መሪ-አልባ ይሆናል፡፡ ባለ ሀብት የሆኑ ዜጎቿ ላይ ጥቃት የምትሰነዝር አገር ድሀ ትሆናለች፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ባለ ሀብቶች በሀብታቸው ምክንያት ችግር ወደማያደርሱባቸው እና ተቀባይነት ወደሚያገኙባቸው አገሮች ስለሚሸሹ ነው፡፡

## ለሰዎች ትልቅ ዋጋ መስጠት የሚያስፈልግባቸው ምክንያቶች

### 1. ሰዎች ከገንዘብ የላቀ ዋጋ ስላላቸው፡፡

በገንዘብም ሆነ በትምህርት ረገድ ሰዎችን ለማሳደግ ጣር፡፡ ለሰዎች ተገቢውን ደመወዝ ክፈላቸው፡፡ ሰዎችን ለማስተማርና ለማሠልጠን ጊዜ ውሰድ፡፡

### 2. ሰዎች ከሕንፃዎች የላቀ ዋጋ ስላላቸው

ሰዎችን እንደ እግዚአብሔር ስጦታዎች አድርገህ ተመልከታቸው፡፡

### 3. ሰዎች ከኮምፒውተሮች የላቀ ዋጋ ስላላቸው

እግዚአብሔር የሰጠህን ሰዎች ላለማጣት ሞክር፡፡ አንድ ሰው እንኳ ላለማጣት የምትችለውን ጥረት ሁሉ አድርግ፡፡ ሰዎች ዋጋ ስትሰጣቸው ይህንኑ የመገንዘብ አቅም አላቸው፡፡

> ከእነርሱ ጋር በዓለም ሳለሁ የሰጠኸኝን በስምህ እኔ እጠብቃቸው ነበር፤ ጠበቅኋቸውም መጽሐፉም እንዲፈጸም ከጥፋት ልጅ በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም።
>
> ዮሐንስ 17፡12

## 4. ሰዎች ከመኪናዎች የላቀ ዋጋ ስላላቸው

ሰዎች ከዕቃዎችና ከፕሮጀክቶች የበለጠ ዋጋ እንዳላቸው አድርገህ ተመልከት። ኢየሱስ ተከታዮቹን እንደ እግዚአብሔር ስጦታዎች ነበር የተመለከተው። "ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው። የአንተ ነበሩ ለእኔም ሰጠሃቸው። ቃልህንም ጠብቀዋል" (ዮሐንስ 17፡6)።

## ለሕዝቧ ዋጋ የማትሰጥ አገር

ለዶክተሮቿ ዋጋ የማትሰጥ አንዲት አገር አውቃለሁ። በዚህም ምክንያት አብዛኞቹ ዶክተሮች አገሪቱን ለቀው ወጥተዋል። አገሪቱ ለነርሶቿም ዋጋ ባለመስጠቷ የለመለመ መስክ ፍለጋ ወደ ሌሎች አገሮች ፈልሰዋል አሁንም እየፈለሱ ነው። ለመሪዎቿም እንዲሁ ዋጋ የማትሰጥ አገር አውቃለሁ። ለዚህም ነው የቀድሞዎቹ መሪዎቿ በሙሉ የተገደሉት። ለአብያተ ክርስቲያናትም ዋጋ የማትሰጥ አገር አውቃለሁ ባለመስጠቷም መንግሥት በአብያተ ክርስቲያናት ላይ ጥቃት ሊሰነዝር ይችላል።

አንዲት አገር ከባለሙያዎችና አገር ገንቢዎች በላይ ለአትሌቶችና ለቁንጅና ውድድር ተወዳዳሪዎች ትልቅ ዋጋ የምትሰጥ ከሆነ፣ እነዚህ ባለሙያዎችና አገር ገንቢዎች ወደ አገሪቱ ይሳባሉ ብለህ ታስባለህ?

## ለምእመኖቿ  ዋጋ የምትሰጥ ቤተ ክርስቲያን

የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሆንክ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ላሉት የተለያዩ ዓይነት ሰዎች ትልቅ ዋጋ ሊኖርህ ይገባል። እንዲህ ካደረክ ብዙ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያንህ ይሳባሉ፤ ቤተ ክርስቲያንህም ታድጋለች። መሪነት እግዚአብሔር የሰጠህን ሰዎች አክብሮ የመያዝ ሥራ ነው። ተከታዮችህን ከላይ የሆኑ ስጦታዎች አድርገህ በመመልከት ልክ እንደ ኢየሱስ ሁን።

## ምዕራፍ 24

# መጽሐፍ ለማግኘት የትኛውንም ያህል ገንዘብና ጊዜ ከማውጣት ወደኋላ አትበል

## አንድ መሪ መጽሐፍትን የሚወድባቸው ስምንት ምክንያቶች

1. ከመጽሐፍ የተገኘ መረጃ የሕይወቱን አቅጣጫ ሊያስቀይር እንደሚችል ስለሚያውቅ።

ለ

ዚህ ነው አንድ መሪ ለመጽሐፍ የትኛውንም ያህል ገንዘብ ለመክፈል የሚፈቅደው።

2. መጽሐፍን ማንበብ ከመጽሐፉ ደራሲ ጋር በቀጥታ እንድትገናኝ ያደርግሃል።

ብዙውን ጊዜ ደራሲያን ለሰዎች የሚያካፍሉት እውቀት ያላቸው ታላላቅ ሰዎች ናቸው። አንድ መሪ ከተወሰኑ ሰዎች ጋር የመገናኘት እድል ላይገጥመው እንደሚችል ያውቃል፤ በመሆኑም እነዚህ ሰዎች የጻፏቸውን መጽሐፍት በማንበብ ይጠቀማል።

3. መሪ፣ ደራሲያን የእርሱ ሠራተኞችና ተመራማሪዎች መሆናቸውን ይገነዘባል።

4. መሪ፣ የብዙ ዓመታት ተሞክሮ በአንድ መጽሐፍ ሊተላለፍ እንደሚችል ያውቃል።

5. መሪ፣ መጽሐፍ ታጋሽ መምህር መሆኑን ያውቃል።

6. መሪ፣ ከመጽሐፍ ቅባትን ሊያገኝ እንደሚችል ያውቃል።

7. መሪ፣ማንበብ ካልቻልክ መምራት እንደማትችል ያውቃል።

በዘመናት ሁሉ ታላላቅ መሪዎች አንባቢዎች ነበሩ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዳንኤልና ጳውሎስ ለዚህ ጥሩ ምሳሌዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ነቢዩ ዳንኤል መሪ ነበር ደግሞም ጉጉ አንባቢ ነበር። ዳንኤል የነቢዩ ኤርምያስን መጽሐፍ አንብቧል።

> በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት እኔ ዳንኤል የኢየሩሳሌም መፍረስ የሚፈጸምበትን ሰባውን ዓመት፥ እግዚአብሔር በቃሉ ለነቢዩ ለኤርምያስ የተናገረውን የዓመቱን ቍጥር በመጽሐፍ አስተዋልሁ።
>
> ዳንኤል. 9፡2

ጳውሎስ ምሳሌነቱን ልንከተለው የሚገባን ግሩም አንባቢ ነበር። ጳውሎስ መጽሐፍቱና ብራናዎቹ እንዲመጡለት ሲጠይቅ እንመለከታለን። እነዚህ ነገሮች ለእርሱ በጣም አስፈላጊዎች ነበሩ።

> ስትመጣ በጢሮአዳ ከአክርጳ ዘንድ የተውሁትን በርኖሱንና መጻሕፍቱን ይልቁንም በብራና የተጻፉትን አምጣልኝ።
>
> 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡13

ማንበብ ከአንድ መሪ መሠረታዊ ልማዶች አንዱ ነው። የማታነብ ከሆነ፣ እባክህን ማንንም ለመምራት አትሞክር። ማንበብ ለአመራር ወሳኝ ነው።

## እያንዳንዱ መሪ ለምን አንባቢ ሊሆን እደሚገባው የሚገልጹ አሥር ምክንያቶች

### 1. የአእምሮ እውቀት ለማሳደግ አንብብ

በምታነብበት ጊዜ አእምሮህን በሚገባ ታጎለብታለህ።

ብዙ አእምሮዎች ገና ብዙ መጎልበት ይጠበቅባቸዋል።

### 2. ለመንፈሳዊ እድገት አንብብ

በምታነብበት ጊዜ፣ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል መንፈስህን በኃይለኛ ሁኔታ ያንጸዋል። መጽሐፍቶቻቸውን በማንበብ ከሌሎች ታላላቅ መሪዎች ጋር ኅብረት ልታደርግ ይገባሃል።

### 3. የስብከትና የማስተማር ችሎታህን ለማጎልበት አንብብ

የታላላቅ ሰዎችን መልእክቶች በምታነብበት ጊዜ አንዳንድ ጠቃሚ ነጥቦችን መውሰድህ የማይቀር ነው።

### 4. የቋንቋ ክህሎትህን ለማሳደግ አንብብ

የእንግሊዝኛም ሆነ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪ ብትሆንም እንኳ፣ ማንበብ ሁልጊዜም የቋንቋ ክህሎትህን ያሳድጋል። የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለመማር ከሁሉም የሚሻለው መንገድ የእንግሊዝኛ መጽሐፍትን ማንበብ ነው። የቃላት እውቀትህን ለማሳደግ ከፈለግህ አሁኑኑ ማንበብ ጀምር!

## 5. ከታላላቅ አእምሮዎችና ከታላላቅ ሰዎች ጋር ኅብረት እዲኖርህ ለማድረግ አንብብ

ማንበብ በአንተና በሌላው ሰው መካከል የሚፈጠር ግላዊ ኅብረት የማድረጊያ መንገድ ነው። መጽሐፍ በምታነብበት ጊዜ ቅባት ልትቀበል ትችላለህ።

## 6. መጻፍ እንድትለምድ አንብብ።

አንድ ቀን መጽሐፍ ትጽፍ ይሆናል። ለሰዎች ደብዳቤ መጻፍ ይኖርብሃል። በማንበብ መጻፍ ተማር።

## 7. አዲስ መረጃ ለማግኘት አንብብ

አብዛኞቹ ሰዎች መጽሐፍ ማንበብ የሚያስፈልገው አዲስ መረጃ ለማግኘት ብቻ ነው ብለው ያስባሉ። ይህ ግን አንባቢ መሆን ከሚያስፈልግባቸው አያሌ ምክንያቶች አንዱ ብቻ ነው። ከሰው ልጅ ቀንደኛ ጠላቶች አንዱ አላዋቂነት ነው። ካላነበብህ፣ አላዋቂነትህን በራስህ ላይ ያመጣኸው ሲሆን የምታቀርበው ማመሃኛ ሊኖርህ አይችልም።

## 8. የአመራር ችሎታህን ለማጎልበት አንብብ።

ከምግብና ልብስ በላይ ለመጽሐፍት ብዙ ገንዘብ የሚያወጣ ሰው እጣፈንታው መሪነት ነው።

## 9. አንብብ ምክንያቱም፣ ለማንበብ የማይፈልግ ሰው ማንበብ ከማይችል አይሻልም።

## 10. ሃያ መቶኛ ከሚሆኑት ልቀው ከሚገኙት የማኅበረሰብ አባላት አንዱ ትሆን ዘንድ አንብብ።

በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ውስጥ በገበያ ውስጥ ያሉትን መጽሐፍት በሙሉ የሚገዙት ልቀው የሚገኙት ከመቶ ሃያ የሚሆኑት ሰዎች እንደሆኑ ታውቃለህ? ዛሬ ከእነዚህ የማኅበረሰቡ አባላት አንዱ በመሆን አሸናፊ እና መሪ ሁን።

ዝነኛ የመንግሥት ባለሥልጣንና የሕግ ባለሙያ የነበረው ዳንኤል ዌብስተር (እ.አ.አ. ከ1782-1852) በአንድ ወቅት እንዲህ አለ፣

“በዚህች አገር ውስጥ ሃይማኖታዊ መጽሐፍት በሚገባ ካልተስፋፉና ሰዎችም ሃይማኖታዊ ለመሆን ካልቻሉ፣ እንደ አገር ምን ልንሆን እንደምንችል አላውቅም። ይህ እያንዳንዱ አገር ወዳድና ክርስቲያን ሊያስብበት የሚገባው ጉዳይ ነው። እውነት ካልተስፋፋ ውሸት መስፋፋቱ የማይቀር ነው። እግዚአብሔርና ቃሉ ካልታወቀና ተቀባይነት ካላገኘ፣ ዲያብሎስና ሥራዎቹ ከፍ ከፍ ብለው ይታያሉ። የወንጌል ሥነ-ጽሑፎች በየመንደሩ ካልተስፋፉ፣ የተበላሹ ጽሑፎች መስፋፋታቸው የማይቀር ነው።”

## ምዕራፍ 25

# አሻግረህ ተመልከት! ለወደፊት ተዘጋጅ!

ብልህ ሰው ክፉን አይቶ ይሸሸጋል፤ አላዋቂዎች ግን አልፈው ይጐዳሉ

ምሳሌ 22፡3

መሪ ወደፊት አሻግሮ የሚያይ ነው። መሪ የወደፊቱን የሚያውጠነጥን ነው። መሪ ከፊቱ ያለውን ክፉ ነገር ማየት ይችላል። መሪ ከፊቱ ያለውን ዕድገትና መስፋፋት ማየት ይችላል።

## መሪ እየመጡ ያሉ ሶስት ነገሮችን ማየት ይገባዋል

### 1. ዕድገትን አስቀድመህ ተመልከት

እውነተኛ መሪ የሕዝብ ቁጥር እያደገ እንደሚመጣ ይመለከታል። ይህ ማለት ደግሞ ወደ ጌታ ሊመጡ የሚችሉ ሰዎች ቁጥርም ይጨምራል ማለት ነው። ይህም በበኩሉ ካሉን የሚበልጡ ህንፃዎችና አገልግሎት መስጫዎች እንደሚያስፈልጉን ያመለክታል። ተጨማሪ ሠራተኞች ያስፈልጉናል ማለት ነው። የወደፊቱን ዕድገት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሕንፃዎችን ገንባ፤ የወደፊቱን ዕድገት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አገልጋዮችን አሰልጥን። ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑ እንደምታድግ ተንብዮአል። ይህ እንደሚመጣ ኢየሱስ ተመልክቷል!

> እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።
>
> ማቴዎስ 16፡18

የመጀመሪያው የጋና ፕሬዘዳንት ብዙ ዓመታትን ወደፊት አሻግረው በመመልከት ለአገሪቱ ታላቅ የሃይድሮኤሌክትሪክ ግድብ ገነቡ። ይህ ግድብ አነስተኛዋ ጋና ከምትፈልገው እጅግ የተረፈ የኤሌክትሪክ ኃይል ያመነጭ ነበር። እኚህ ፕሬዘዳንት ወደፊት አሻግሮ ለመመልከት ችሎታ ነበራቸው። አንተም ዓይኖችህን ከፍተህ ወደፊት ተመልከት። ዓመታት እያለፉ ሲሄዱ ነገሮች እየተሻሉ እንደሚሄዱ ተገንዘብ።

## 2. የሚመጡ ክፉ ነገሮች አስቀድመህ ተመልከት

ብትፈልግም ባትፈልግም አንዳንድ ክፉ ነገሮች መከሰታቸው የማይቀር ነው። ኢየሱስ ማሰናከያዎች እንደሚመጡ ተናግሯል።

> **ወዮ ለዓለም ስለ ማሰናከያ፤ ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና፥ ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት።**
>
> **ማቴዎስ 18፡7**

ዓመታት በገፉ ቁጥር ክህደት መምጣቱ የማይቀር ነው። ፈተናዎች ይመጣሉ። ሰይጣናዊ ጥቃቶች ይመጣሉ። መጥፎና ክፉ ጊዜያት እንደሚመጡ እርግጠኛ ሁን። የጋብቻ ቃል ኪዳኖች ፤"በመልካምም ሆነ በክፉ ዘመን፣ በብልጽግና ሆነ በመከራ ወቅት"፣ ይላሉ። እውነተኛ መሪ የነገሮችን አቅጣጫ የመተንበይ ችሎታ አለው። የወደፊቱን መመልከት ትችል ዘንድ እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጥህ ጸልይ። በጥበብ የወደፊቱን ልትተነብይ ትችላለህ።

## 3. ለውጦችን አስቀድመህ ተመልከት

ጌታ ከብዙ ዓመታት በፊት በከተማችን የተለያዩ ክፍሎች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን እንድተክል መራኝ። ከተማይቱ እየተስፋፋች በመሄድ ላይ መሆኗን ተገንዝቤ ነበር። ሰዎች ከአንደኛው የከተማይቱ ጫፍ ወደ ሌላኛው ለመድረስ ከሁለት ሰዓታት በላይ ሊወስድባቸው ይችላል። ራቅ ብለው የሚኖሩ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸውን ሊያቆሙ እንደሚችሉ ተሰማኝ። በመሆኑም የከተማ ውስጥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ብዬ የምጠራውን ማስፋፋት ተያያዝኩት። ይህ በሕይወቴ ካደረግኋቸው ስልታዊ (ስትራቴጂክ) እንቅስቃሴዎች አንዱ ነበር። በከተማይቱ ውስጥ ወደ አንድ መቶ የሚጠጉ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በመመሥረት ጌታ የሰጠኝን ሕዝብ ከመበታተን አትርፌአለሁ።

ነጋዴዎች ወደፊት አሻግረው ሊመለከቱ ይገባል። አንዳንዶቻችሁ የተሰማራችሁበት ሥራ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትርፋማነቱን የሚያቆም ሊሆን ይችላል። ብዙውን ጊዜ ሰዎች በአንድ ጊዜ በብዙ ዓይነት የንግድ ዘርፎች እንዲሰማሩ እመክራቸዋለሁ። ለዚህም ምክንያቱ ንግዳቸውን ጊዜ ያለፈበት የሚያደርግ ለውጥ እየመጣ መሆኑን በመገንዘቤ ነው። ታላላቅ የንግድ ሥራዎችን የሚያካሂዱ ሰዎች ከስረው መና ሲቀሩ ታዝቤአለሁ። መሪ የወደፊቱን አሻግሮ የሚመለከት ነው።

## ምዕራፍ 26

# ሁልጊዜ አዳዲስ ነገሮችን ተማር

ድሀና ጠቢብ ብላቴና ተግሣጽን መቀበል ከእንግዲህ ወዲህ ከማያውቅ ከሰነፍ ሽማግሌ ንጉሥ ይሻላል።

መክብብ 4፡13

እንዴት አዳዲስ ነገሮችን መማር አቆማለሁ? ዕድሜ ልክህን እውቀትህ የማይጨምር ከሆነ አዝንልሃለሁ፡፡ እውነተኛ መሪ እውነተኛ ተማሪ ነው፡፡ በየዓመቱ እጅግ ብዙ አስደናቂ አዳዲስ ነገሮችን እማራለሁ፡፡ ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍትን ማዘጋጀት ፍጻሜ የለውም ያለው፡፡

አንዳንድ ሰዎች ሁሉንም ነገር እናውቃለን ብለው ያስባሉ፡፡ ይህ አሳዛኝ ነገር ነው! የትኛውም እውነተኛ መሪ እንደዚህ ብሎ አያስብም፡፡ አንዳንድ ጊዜ አገልጋዮች ሌሎች አገልጋዮችን ሲተቹ እሰማና እደነቃለሁ፡፡ እነዚህ የሚተቿቸው አገልጋዮች ብዙ እውነት ያስተማሩኝ ናቸው፡፡ ሰዎች ካሉበት ደረጃ ፈቅ አለማለታቸው አይደንቅም፡፡ በከተማችን ውስጥ ካሉት ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን ልማር እንደምችል ተረድቻለሁ፡፡ ከመንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ መሪዎች ብዙ ነገሮችን ልማር እችላለሁ፡፡

ራስህን እንደ መሪ ትቆጥራለህ? እንደዚያ ከሆነ መማርህን ላለማቆም ወስን፡፡ መረዳት ያለብህ ትምህርት የሚገኘው መጽሐፍት ከማንበብ ብቻ አይደለም፡፡ በአካባቢህ ካሉት ነገሮች ብዙ ልትማር ትችላለህ፡፡ በየቀኑ ከምትመለከታቸው ሰዎች ብዙ ልትማር ትችላለህ፡፡ አብረውህ ከሚያገለግሉት ወገኖች፣ ከተፎካካሪ ኩባንያዎችና የንግድ ድርጅቶች ብዙ ልትማር ትችላለህ፡፡ ምን ጊዜም አዳዲስ ነገሮችን ከመማር ወደኋላ አትበል!

## *ምዕራፍ 27*

# ጠንካራ ጎኖችህን ተረድተህ ተጠቀምባቸው!

በሁሉም ነገር ብቁ ሆኖ የተፈጠረ ሰው የለም። እኔ ከሞላ ጎደል ሁሉንም የአገልግሎት ዘርፎች ሞክሬአለሁ። በብዙ ነገሮች ውጤታማ ተግባር ላከናውን እንደምችል ተገንዝቤአለሁ። የሙዚቃ መሣሪያዎችን በሚገባ እጫወታለሁ። ዝማሬም እሞክራለሁ። ጥሩ የአምልኮ መሪ ነኝ። የወንጌል ስብከት ያንገበግበኛል። ነቢይነትና የትንቢት አገልግሎት ያስደስተኛል። ቤተ ክርስቲያናትን እመግባለሁ፣ መሪዎችንም አሠለጥናለሁ። በአጭሯ ዕድሜዬ ብዙ ነገሮችን መሥርቻለሁ። ነገር ግን ከነዚህ መካከል እውነተኛው ጥሪዬ የትኛው ነው? በቅርቡ ጌታን፣ "ምን እንዳደርግ ትሻለህ?" ስል ጠየቅሁት። እርሱም በማስተማር የአገልግሎት ዘርፍ ውስጥ የጠራኝ መሆኑን ገለጸልኝ።

ላደርግ የምፈልጋቸው አያሌ ነገሮች ቢኖሩም፣ እግዚአብሔር ለጠራኝ ሥራ ራሴን ለመስጠት እፈልጋለሁ። እውነተኛ መሪ ጠንካራ ጎኖቹን አሳምሮ ያውቃል። አንድ መሪ በርካታ መልካም ተግባራት ሊያከናውን ይችላል። *ጠንካራ ጎኖችህን በምትረዳበት ጊዜ፣ እነዚህን ነገሮች በማድረግ ታላቅ መሪ ሁን።*

ብዙ ሰዎች በአገልግሎት ውስጥ ያሏቸውን ጠንካራ ጎኖች ሳያጎለብቱ ኖረው ይሞታሉ። ሌሎች መጋቢዎች ስለሆኑ ብቻ መጋቢ መሆን የለብህም። በከተማህ ውስጥ አዲሱ ክስተት የነቢይነት አገልግሎት በመሆኑ ብቻ ነቢይ ለመሆን አትጣር።

አገልግሎቴን የጀመርኩት የትርፍ ጊዜ አገልጋይ በመሆን ነበር። አብረውኝ የሚያገለግሉ ሰዎች ባመዛኙ እንደ እኔው የትርፍ ጊዜ አገልጋዮች ነበሩ። ከጠንካራ ጎኖቼ አንዱም ይኸው የትርፍ ጊዜ አገልግሎት ነበር። ሌሎች የሚያደርጓቸውን ነገሮች ብከተል ኖሮ ልዩ የሆነውን አገልግሎቴን አበላሽ ነበር። ሌሎች ሰዎች ተጽእኖ ሊያሳድሩብህ ቢችሉም፣ ጌታ የጠራህን ሥራ ከማከናወን ወደኋላ አትበል።

ልዩ በሚያደርግህ ተግባር ላይ ተሰማራ። ይህንኑ ተግባር በማጎልበት ጠንካራ ሁን። ጠንካራ ጎኖቻቸውን ሳያጎለብቱ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚዘሉ በርካታ ነጋዴዎች አውቃለሁ። የአንደኛውን ሥራ ደካማ ጎኖቹ በሚረዱበት ጊዜ ወደ ሌላው ይዘላሉ። ቀጣዩ ንግድ ፈጣን

ትርፍ የሚያስገኝላቸው ይመስላቸዋል። *በአቋራጭ የሚመጣ ስኬት የለም።*

በሚሊዮን ብሮች የሚቆጠር ገንዘብ ለማካበት የቻሉ ሰዎች ቀደም ብለው ምን ለማድረግ እንደሚፈልጉ የወሰኑና በዚሁ *ሥራ* ላይ ለረዥም ጊዜ የቆዩ ናቸው። *ስኬታማ ሰዎች ብዙውን ጊዜ አንድን ተግባር ለረዥም ጊዜ ያከናወኑ ናቸው።* ከአንዱ አገር ወደ ሌላው *መ*ሮጥ እንድትበለጽግ አያደርግህም። *መ*ኖር የምትፈልግበትን ስፍራ ምረጥና እስክትጠነክር ድረስ በዚያው ሁን!

ሐዋርያው ጳውሎስ *መ*ልካሙን ገድል ተጋድሏል። ሩጫውንም ጨርሷል። አንተም ሩጫህን የምትሮጥበት ጊዜ አሁን ነው።

**መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ።**

**2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡7**

የሌላውን ሰው ሩጫ እርሳው። እግዚአብሔር ለአንተ ያዘጋጀልህ ምንድነው? ልትሠራ የሚገባህ ምንድነው? ንግድ ነው? ፖለቲካ ውስጥ *መ*ባዘን የለብህም! ልትሠራ የሚገባህ ምንድነው? አገልግሎት ነው? ከሆነ ፖለቲካ ውስጥ *መ*ባዘን የለብህም! ብዙ አገልጋዮች ሊያደርጉ የማይገባቸውን ተግባራት በማከናወን ሕይወታቸውን ያሳጥራሉ። *መሪ* ነህ? በመሪነትህ ላይ ቆይና የጌታ ስጦታ በአንተ ላይ *መ*ሆኑን ሁሉም ሰው ይመልከት። የተከበርህ *መሪ* ትሆናለህ።

## *ምዕራፍ 28*

# ለረዥም ተጋድሎ ተዘጋጅ!

**መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫዬን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ።**

**2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡7**

መሪነት አንድ ረዥም ተጋድሎ ነው። ጳውሎስ መልካሙን ገድል እንደተጋደለ ተናግሯል። ሕይወቱ በተጋድሎ የተሞላ ነበር። ከአንድ መጋቢ ጋር ያደረኩትን ውይይት አስታውሳለሁ። ይህ ሰው ባለቤቱ ከአንድ ቀን በፊት ምን እንደጠየቀችው ነገረኝ።

"ምን አለችህ?" ብዬ ጠየቅሁት።

"መቼ ነው ሰላም የሚኖርህ?" ስትል ጠየቀችው።

ባለቤቱ ተጋድሎው መቼ ነው የሚያከትመው እያለች ትገረም ነበር!

ውድ ክርስቲያን ወንድሜ ሆይ፣ መሪ ነኝ ብለህ የምታስብ ከሆነ ለረዥም ተጋድሎ ተዘጋጅ! ከዲያብሎስ ጋር የማትዋጋ ከሆነ፣ ከአጋንንት ጋር መዋጋትህ የማይቀር ነው። አጋንንትን የማትዋጋ ከሆነ ብዙ የማያምኑ ሰዎች ይዋጉሃል። ከማያምኑ ሰዎች ጋር የማትዋጋ ከሆነ፣ ከሚጠሉህ ክርስቲያኖች ጋር ትዋጋለህ።

መሪ ነኝ ትላለህ?፣ ራስህን ለረዥም ውጊያ አዘጋጅ! ይህ መልካም ውጊያ ነው። ይህ ተጋድሎ ለዘላለም አክሊሎች እና "መልካም አደረግህ አንተ በጐ ታማኝ ባሪያ" የሚለውን ቃል ለመስማት የሚደረግ ነው።

**መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫዬን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ።**

**2ኛ ጢሞቴዎስ. 4፡7**

## ምዕራፍ 29

# ሳንቲሞችህን ቁጠር!

**ከጠገቡም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን። አንድ ስንኳ እንዳይጠፋ የተረፈውን ቍርስራሽ አከማቹ አላቸው።**

**ዮሐንስ 6፥12**

ቆጣቢ ሰው ለሳንቲሞቹ ዋጋ የሚሰጥ ነው፡፡ እያንዳንዱ መሪ ራእዩን እውን ለማድረግ ብዙ ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡ ይህ ገንዘብ የሚገኘው እንዴት ነው? ቆጣቢ በመሆን! ከብዙ ዓመት በፊት በቆጣቢነት ላይ መጽሐፍ ጽፌ ነበር፡፡ ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ካስተማርሁት ትምህርት ነበር፡፡ ይህ አሳብ ለአገልግሎቴ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረገ ቁልፍ እንደሆነ አምናለሁ፡፡

በቅርቡ በአሜሪካ ውስጥ ስላሉት ሀብታም ሚሊዮነሮች የሚናገር መጽሐፍ አነበብሁ፡፡ በሀብታም ሚሊዮነሮች ላይ የተደረገው ጥናት እደሚያሳየው ከሀብታም ሰዎች መለያ ባህርያት አንዱ ቆጣቢነት መሆኑን በማወቄ ተገርሜአለሁ፡፡ በቁጠባ ላይ ብዙ ዓመታትን ካስተማርሁና ከጻፍሁ በኂላ ነበር ይህንን መጽሐፍ ያነበብሁት፡፡ ከዚህም መርሆቹ አንድ ዓይነት መሆናቸውን ማየት ትችላለህ፡፡ ቆጣቢ ሰው ለሳንቲሞቹ ዋጋ የሚሰጥ ነው፡፡

አንድ ቦታ ተቀምጦ ያለ ስፍር ቁጥር የሌለው ገንዘብ የለም፡፡ ብዙ ሀብታሞች የገንዘብ እጥረት ያጋጥማቸዋል፡፡ ሁሉም የሞላቸው ሰዎች ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡ ከብዙ ዓመታት በፊት ቤተ ክርስቲያናችን የሕንፃ ግንባታ በጀመረች ጊዜ አንድ ሀብታም ሚሊዮነር የሆነ ሰው የተወሰነ ገንዘብ እንዲረዳን ጠየቅን፡፡ ብድር ማግኘት ይቻል ዘንድ ሕንፃውን ለማስያዝ የፈቀደ አባላችንም ነበር፡፡ ሀብታሙ ግን ጥያቄያችንን ለመቀበል አልፈለገም፡፡ የብድር መያዣውም አሳቡን እንዲቀይር አላደረገውም፡፡ ማንም ሊረዳን አልቻለም፡፡ በዚህ ጊዜ የጌታ መንፈስ፣ "ለሳንቲሞቻችሁ ዋጋ ብትሰጡ ይህንን ራእይ ልታሳኩ ትችላላችሁ" አለኝ፡፡ ቃሉ እውነት ነበር፡፡ እኛም ለሳንቲሞቻችን ዋጋ በመስጠት ራእዩንም ከግብ ለማድረስ ቻልን፡፡

አባካኝም ሆነ ብዙ የሚያጠፋ ሰው ብዙ ተግባር ሊያከናውን አይችልም፡፡ ሰዎችን ለማስደነቅ ትጨነቃለህን? እንዲያ ከሆነ መልካም መሪ አይደለህም፡፡ ውድ ነገሮችን ይዘህ ለመታየት ትፈልጋለህን? እንዲህ ዓይነት ሰው ከሆንህ መሪ አይደለህም ማለት ነው፡፡ መሪ ከግቡ ለመድረስ ለሳንቲሞቹ ዋጋ መስጠት እንዳለበት ይገነዘባል፡፡

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ትራፊውን ምግብ እንዲሰበስቡ የፈለገው ለምን ነበር? ደቀ መዛሙርቱን ለማሳፈር በመፈለጉ ይሆን? አካባቢው እንዳይቆሸሽ በመፈለጉ ይሆን? አይደለም፡፡ እርሱ የፈለገው ብክነትን ለመከላከል ነበር፡፡ "ከጠገቡም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን፡፡ አንድ ስንኳ እንዳይጠፋ የተረፈውን ቍርስራሽ አከማቹ አላቸው" (ዮሐንስ 6፡12)፡፡

*ሀብታም ለመሆን ምርጡ አማራጭ አባካኝነትን መቀነስ ነው*፡፡ የኩባንያ መሪ ከሆንህ ኃላፊነትህ ብክነትንና ስርቆትን መቀነስ ይሆናል፡፡ እነዚህን ሁለት ነገሮች ለማከናወን ከቻልህ ኩባንያህ በቀላሉ ያድጋል፡፡ ፖለቲካዊ መሪ ከሆንህ ሙስናን ለመከላከል ልትጥር ይገባል፡፡ ከአፍሪካ አገሮች የተሰረቀው ገንዘብ መመለስ ቢችል፣ (IMF) ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና ከዓለም ባንክ ብድር መጠየቅ አያስፈልገንም ነበር!

*ምዕራፍ 30*

# እውነትን ተናገር

***እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።***

**ዮሐንስ 8፡32**

*የ*አመራር ዓይነተኛው ባህርይ እውነት ነው፡፡ እውነቱ የደረስክበትንና እና ያልደረስከበትን የማሳየት ብቃት አለው! በተጨማሪም እውነቱ ወዴት እደምትሄድ ይነግርሃል! አንዳንድ መጋቢዎች ስለ ማኅብረ ምእመኖቻቸው ቁጥር እውነቱን አይናገሩም፡፡ የምእመናንን ቁጥር በተመለከተ የተጋነነ ግምት መናገራቸውን ማቆም ይኖርባቸዋል፡፡ የምታገለግላቸውን ሰዎች እውነተኛ ቁጥር ስታውቅ የበለጠ ተግተህ ለመሥራት ትነቃቃለህ፡፡

አንድ ቀን የመረጃ ክፍላችንን ኦፊሰር ምን ያህል ሰዎች በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እንደሚገኙ እንዲነግረኝ ጠየቅሁ፡፡ የነገረኝ ቁጥር ቢያንስ ለአንድ ሳምንት አስቆዘመኝ፡፡ ነገር ግን አሁን ካለሁበት ይልቅ፣ ብዙ ርቄ ልሄድ እንደምችል ተገነዘብሁ፡፡ ለራስህ እውነቱን መናገር ካልቻልህ፣ መልካም መሪ ልትሆን አትችልም፡፡

ምንም ዓይነት ትርፋማነት ሳያሳዩ እየተካሄዱ ያሉ በርካታ የንግድ ሥራዎች መኖራቸው የሚያሳዝን ነው! እንዲያውም የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች በሚደመሩበት ጊዜ በኪሳራ እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ጊዜ ጥበብ የተሞላበት እርምጃ መወሰድ ካለብን ንግዱን መዝጋት ወይም የተወሰኑ ሠራተኞችን መቀነስ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህ እውነተኛ አመራር ነው፡፡ መሪ ነህ? እውነቱን ለማወቅ ትፈልጋለህን? እውነታውን ለራስህ ትነግራለህ?

***ጌታ ሆይ፥ የሚድኑ ጥቂቶች ናቸውን? አለው።***

**ሉቃስ 13፡23**

ኢየሱስም ደጁ ጠባብ ነው የሚድኑትም ጥቂቶች ናቸው ሲል መልስ በመስጠት ገልጾለታል፡፡

*ምዕራፍ 31*

# ትኩረትህን አትሳት

ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ሰዎች በአንድ ጉዳይ ላይ ለረዥም ጊዜ ከፍተኛ ትኩረት ያደረጉ መሆናቸውን ብዙ ሰዎች አይገነዘቡም፡ ፡ በአንድ ጉዳይ ላይ ትኩረት ማድረግ ለስኬታማነት ወሳኝ ነው። መሪ ነኝ ብለህ ታስባለህ? የምታስብ ከሆነ፣ በአንድ ጉዳይ ላይ ትኩረት የማድረግን ጥበብ መማር አለብህ። በራእይህ ላይ አትኩር። በቤተ ክርስቲያንህ ላይ አትኩር። በሥራህ ላይ አትኩር ይህም ታላላቅ ውጤቶችን ያስገኝልሃል።

ብዙውን ጊዜ ለመጸለይ ስፈልግ ስልኮችን በሙሉ አጠፋለሁ። ይህ በጌታ ላይ ትኩረት እንዳደርግ ይረዳኛል። የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሳለሁ ከአያሌ ክርስቲያናዊ ቡድኖች ጋር አብሮ የመሆን እድል ገጥሞኝ ነበር። በኂላም ከአንድ የአገልግሎት ቡድን ጋር ለመሆን ወሰንሁ። በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ ላሉት የተለያዩ ክርስቲያናዊ ቡድኖች ጊዜዬን ላከፋፍል እንደማልችል ተረዳሁ። ይህን እርምጃ በመውሰዴ ምክንያት ከዩኒቨርስቲው ስወጣ ቀደም ሲል ያልነበረ አንድ አዲስ ቡድን ለመመስረት ችያለሁ። ይህ ቡድን ዛሬም ድረስ በመሥራት ላይ ይገኛል።

በአንድ ጉዳይ ላይ በምታተኩርበት ጊዜ ሰዎች ትዕቢተኛ ነው ወይም ከሰዎች ጋር አይግባባም ብለው ሊወቅሱህ ይችላሉ። ውስጥህን ብቻ እንደምትመለከትና ለሌሎች ግድ የማይልህ እንደሆንህ በመግለጽ ትችት ይሰነዝሩብሃል። ፀረ-ማኅበራዊ ሕይወት እንደሆንህም አድርገው ሊያስቡ ይችላሉ። እነዚህን ጉዳዮች ቸል ብለህ እለፋቸው። በሥራህ ላይ አትኩር። ጥበብ በልጆቿ ትፀድቃለች። በሥራህ ላይ ማተኮር እድገትን እንደሚያመጣና ከግጭት እንደሚታደግህ አትርሳ።

ኢየሱስ በሄደ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ልታከናውን ስለሚገባት ተግባር ግልጽ መመሪያ አስቀምጧል።

እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተ ሰዎች ላይ የሾመው ታማኝና ልባም ባሪያ ማን ነው? ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል። ያ ክፉ ባሪያ ግን። ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ፥ ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፥ የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፥ ከሁለትም ይሰነጥቀዋል፥ እድሉንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

ማቴዎስ 24፡45-51

ይሁን እንጂ ኢየሱስ ካረገ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ቤተ ክርስቲያን እርሱ ባላዘዛቸው በርካታ ጉዳዮች ውስጥ እጇን አስገባች፡፡ በሰናይ ምግባራትና ማኅበራዊ ተቀባይነት ስም ቤተ ክርስቲያን ትኩረቷን ለአራት አበይት ተግባራት ከፋፈለች፡፡ እነዚህም ጤና፣ ትምህርት፣ የዕርዳታ ሥራዎችና ክርስቲያናዊ ትምህርት ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር፣ ሌሎች ሃይማኖቶች ከክርስትና በላቀ ፍጥነት እያደጉ መሆናቸው አስገራሚ አይደለም፡፡ ቤተ ክርስቲያን አግዚአብሔር በሰጣት ሥራ ላይ ብቻ ብታተኩር የተለያዩ ስያሜዎች እንደሚሰጧት እሙን ነው፡፡

አንዳንድ የእኔ መጋቢዎች እና ቤተ ክርስቲያኖች በሥራችን ላይ ትኩረት በማድረጋችን የተነሳ ለተለያዩ ትችቶች ተጋልጠናል፡፡ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የሚደረገው ከመጠን ያለፈ ትብብር ለክርስቶስ አካል ማደግ አስተዋጽኦ እንደማያደርግ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህ በአካል አንድነት ላይ ትኩረት ለሚያደርጉ ወገኖች አስገራሚ ይሆንባቸዋል፡፡ *አንድነት ከኅብረት* የተለየ መሆኑን መረዳቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ሰዎች አንድነት ብለው የሚጠሩት የማኅበረ ምእመናንን አካላዊ ኅብረት ነው፡፡

መሪ አንድን ግብ እስከሚያሳካ ድረስ በዚሁ ጉዳይ ላይ ትኩረት የማድረግ ብቃት አለው፡፡ መሪ ጠቀሜታ ያለውን ጉዳይ ጠቀሜታ ከሌለው ለይቶ ያውቃል፡፡ ከመሪነት አገልግሎቴ እንደተገነዘብሁት፣ በፍጥነት በምሠራበት ጊዜ የበለጠ ጉልበት ይኖረኛል፡፡ ቀስ ብሎ መስራት ያደክማል፡፡ ለማከናውነው ተግባር ሁሉ የጥድፍያና የትኩረት መርሆችን ከሥራ ላይ አውላለሁ፡፡ ይህንን ጉዳይ እስከማሳካው ድረስ ሙሉ ኃይሌን እጠቀማለሁ፡፡ ሌሎች ሥራዎችን ለማከናወን ብለህ ጉዳዮችን ለሌላ ጊዜ ባሳለፍህ ቁጥር የበለጠ እየተጨነቅ፣ ደስታ እየራቀህና ተስፋ እየቆረጥህ ትሄዳለህ፡፡

መሪ ነህ? መሪ ከሆንህ፣ በአንድ ጊዜ በአንድ ጉዳይ ላይ ትኩረት ለማድረግ ወስን፡፡ ከንቱ ማኅበራዊ ግንኙነትን፣ ባዶ ወሬንና ከመጠን በላይ ቴሌቪዥን እየተመለከቱ መቆየትን ማስወገዱ ጠቃሚ ነው፡፡

በሥራህ ላይ ማተኮር ለታላቅ ውጤት ያበቃሃል። ጳውሎስ ይህን አደርጎታል አንተም ልታደርግ ትችላለህ!

> . . .ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ።

ፊልጵስዩስ 3፡13

# ምዕራፍ 32

# የታላቅ ሥራን አነስተኛ ጅማሬዎች ለይተህ እወቅ

በርካታ ታላላቅ ሥራዎች የተጀመሩት በአነስተኛ መንገድ ነው፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ግን፣ ብዙ ሰዎች የታላቅነትን ጅማሬዎች አይረዱም፡፡

**ጅማሬህ ታናሽ ቢሆንም እንኳ ፍጻሜህ እጅግ ይበዛል።**

**ኢዮብ 8፡7**

**የጥቂቱን ነገር ቀን የናቀ ማን ነው? እነዚህ ሰባቱ ደስ ብሎአቸው በዘሩባቤል እጅ ቱንቢውን ያያሉ፤ እነዚህም በምድር ሁሉ የሚዘዋወሩ የእግዚአብሔር ዓይኖች ናቸው።**

**ዘካርያስ 4፡10**

መጽሐፍ ቅዱስ አነስተኛ ጅማሬዎችን እንዳንንቅ ያስተምረናል፡፡ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ክርስቲያኖች የታላቅ ሥራዎችን ጅማሬዎች ከአገልግሎታቸው አስወግደዋል፣ ምክንያቱም የታላቅ ሥራን አነስተኛ ጅማሬዎች ለይተው ባለማወቃቸው ነው፡፡

ምን ጊዜም ይህንን አትዘንጋ! ታላላቅ ሥራዎች የጀመሩት ከአነስተኛ ጅማሬ ነው፡፡ ረቂቋ የሰናፍጭ ዘር ታላቅ ዛፍ ታስገኛለች፡፡ የሰናፍጭና የታላቅ ዛፍ መጠን ግን አይገናኝም፡፡

## የታላቅ ሥራን አነስተኛ ጅማሬዎች የተገነዘቡ ስድስት ሰዎች

1. **ኤልሳዕ የነቢይነት አገልግሎቱን የጀመረው የኤልያስን እጅ በማስታጠብ ነበር፡፡**

**ኢዮሣፍጥም፣ በእርሱ እግዚአብሔርን የምንጠይቅበት የእግዚአብሔር ነቢይ በዚህ አይገኝምን? አለ። ከእስራኤልም ንጉሥ ባሪያዎች አንዱ። በኤልያስ እጅ ላይ ውኃ ያፈስስ የነበረው የሣፋጥ ልጅ ኤልሳዕ እዚህ አለ ብሎ መለሰ።**

**2ኛ ነገሥት 3፡11**

### 2. ታላቁ የጦር መሪ ኢያሱ ሥራውን የጀመረው የአዛውንቱ ነቢይ ሎሌ በመሆን ነበር።

ሙሴና ሎሌው ኢያሱ ተነሡ፤ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወጣ።

ዘጸአት 24፥13

### 3. ንጉሥ ዳዊት ሥራውን የጀመረው በንጉሡ ቤተ መንግሥት ውስጥ በገና በመጫወት ነበር።

ሳኦልም ወደ እሴይ። በዓይኔ ሞገስ አግኝቶአልና ዳዊት በፊቴ፥ እባክህ፥ ይቁም ብሎ ላከ። እንዲህም ሆነ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መንፈስ በሳኦል ላይ በሆነ ጊዜ ዳዊት በገና ይዞ በእጁ ይመታ ነበር፤ ሳኦልንም ደስ ያሰኘው ያሳርፈውም ነበር፥ ክፉ መንፈስም ከእርሱ ይርቅ ነበር።

1ኛ ሳሙኤል 16፥22-23

### 4. አሮን አገልግሎቱን የጀመረው የሙሴን እጆች በመደገፍ ነበር።

የሙሴ እጆች ግን ከብደው ነበር፤ ድንጋይም ወሰዱ፥ በበታቹም አኖሩ፥ እርሱም ተቀመጠበት፤ አሮንና ሖርም አንዱ በዚህ አንዱ በዚያ ሆነው እጆቹን ይደግፉ ነበር፤ ፀሐይም እስክትገባ ድረስ እጆቹ ጠነከሩ።

ዘጸአት 17፥12

### 5. ሩት አገልግሎቷን የጀመረችው ስጋት የደረሰባትን አረጋዊት በመንከባከብ ነበር።

ሩትም፣ ወደምትሄጅበት እሄዳለሁና፥ በምታድሪበትም አድራለሁና እንድተውሽ ከአንቺም ዘንድ እንድመለስ አታስቸግሪኝ፤ ሕዝብሽ ሕዝቤ፥ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል፤ በምትሞችበትም ስፍራ እሞታለሁ፥ በዚያም እቀበራለሁ፤ ከሞት በቀር አንቺንና እኔን አንዳች ቢለየን እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ እንዲሁም ይጨምርብኝ አለች።

ሩት1፥16 ፣17

### 6. ኢየሱስ አገልግሎቱን የጀመረው በአናጺነት ነበር።

ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ የያቆብም የዮሳም የይሁዳም የስምዖንም ወንድም አይደለምን? እኅቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን? አሉ፤ ይሰናከሉበትም ነበር።

ማርቆስ 6፥3

## *ምዕራፍ 33*

# ሰዎችን በእኩልነት እያስተናገድክ፣ ልዩነቶችን ግን ግልጽ አድርግ

መልካም መሪ ሰዎች የተፈላጊነት ስሜት እንዲሰማቸው ጥረት ሊያደርግ ይገባል። እውነታው አንተ መሪ መሆንህ ነው፤ በመሆኑም አንተ ትለያለህ።

## በዙሪያህ ያሉት ሰዎች የተፈላጊነት ስሜት እንዲሰማቸው የሚያደርጉ አምስት መንገዶች

### 1. ከሁሉም ዓይነት ሰዎች ጋር አብረህ ሁን

ኢየሱስ ከሌቦች (በመስቀሉ ላይ ከሁለት ሌቦች ጋር)፣ ከቀራጮች (ማቴዎስ)፣ ከዓሣ አጥማጆች (ጴጥሮስ)፣ ከውጭ አገር ሰዎች (ሲሮፊኒቃዊቷ ሴት)፣ አጋንንት ካደረባቸው ሰዎች (መግደላዊት ማርያም)፣ ከአብዶች (የጌርጌሴኖን እብድ)፣ ከካህናት (ኒቆዲሞስ) እና ከመኳንንት (የአርማትያሱ ዮሴፍ) ጋር አብሮ ሆኗል። ኢየሱስ ዘልቆ ያልገባባቸው የሰው ልጅ መደቦች አልነበሩም። ራስህን በአንድ የማኅበረሰብ ቡድን ብቻ መገደብ የለብህም።

### 2. አብረውህ የሚሠሩትን ሰዎች እና አጋሮችህን እንደ ቤት ሠራተኛህ አድርገህ አትጥራ ወይም አትመልከት።

> **ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፥ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና።**
>
> **ዮሐንስ 15፡15**

ባሪያም ቢሆን እንደዚህ ተብሎ ሊጠራ አይፈልግም። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ባሮች ብሎ እንደማይጠራቸው በግልጽ ተናግሯል።

### 3. አብረውህ የሚሠሩትን ባልደረቦችና ታዳጊ መጋቢዎች ጓደኞችህ እንደሆኑ አድርገህ ግለጽ።

> **እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ።**
>
> **ዮሐንስ 15፡14**

በሥሬ የሚሠሩ ሰዎች ወዳጅነት ያስደስተኛል፡፡ ከጎኔ ባይኖሩ ኖሮ ብቸኝነት ይሰማኝ ነበር፡፡

## 4. የሚሠሩልህን ሰዎች እንደ ቤተሰቦችህ አድርገህ ግለጽ፡፡

> እርሱ ግን ለነገረው መልሶ። እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው? አለው። እጁንም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘርግቶ። እነሆ እናቴና ወንድሞቼ፤ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜ እኅቴም እናቴም ነውና አለ።
>
> ማቴዎስ 12፡48-50

ይህ በሕይወቴ ሁሉ ካደረኳቸው ነገሮች አንዱ ነው፡፡ አብረውኝ የሚሠሩትን መጋቢዎችና ሠራተኞች እንደ ሠራተኞች ሳይሆን እንደ ቤተሰቦቼ እመለከታቸዋለሁ፡፡

እንዲያውም “አለቃ” ተብሎ መጠራት እጠላለሁ፡፡ በድርጅትህ ውስጥ የቤተሰባዊነትን መንፈስ አስፍን፡፡ ይህ ከተለመደው መደበኛ ድርጅታዊነት መቶ እጥፍ የተሻለ ነው፡፡ ቤተሰባቸውና የግል ችግሮቻቸው ያንተ ችግሮች እንዲሆኑ ፍቀድ!

## 5. አብረውህ ለሚያገለግሉ መጋቢዎች ወይም ረዳቶችህ ስለ ራስህና ስለ እቅዶችህ ንገራቸው፡፡

> . . .ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፥ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና።
>
> ዮሐንስ 15፡15

ይህ ሰዎችን ያቀርባል፡፡

# በአንተና በእነርሱ መካከል ያለውን ልዩነት ግልጽ የምታደርግባቸው ስድስት መንገዶች

## 1. አስተምራቸው

ኢየሱስ ሁልጊዜም ደቀ መዛሙርቱን ያስተምር ነበር፡፡ ሰዎችን ስታስተምር እነርሱን የምትመራበትን ሥልጣን ታፀናለህ፡፡ የመምራት ሥልጣን በመመገብ ችሎታ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

## 2. ላካቸው

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ምግብ እንዲገዙ ልኳቸዋል፡፡

> ደቀ መዛሙርቱ ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ ሄደው ነበርና።
>
> ዮሐንስ 4፡8

አንድን ሰው በምትልክበት ጊዜ የሥልጣን ደረጃን ተዋረድ ትመሠርታለህ። ይህም የሥልጣን ደረጃ ተዋረድ በመዋቅሩ ውስጥ የሚኖር ነው።

## 3. ባርካቸው

ለተከታዮችህ ጸልይላቸው፤ ባርካቸውም። ትንሹ በታላቁ ይባረካል የሚል የታመነ አባባል አለ።

> ትንሹም በታላቁ እንዲባረክ ክርክር የሌለበት ነገር ነው።
>
> ዕብራውያን 7፡7

## 4. ማን እንደሆንህ ንገራቸው

ኢየሱስ ስለራሱ በልበ-ሙሉነት ተናግሯል። እርሱ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት እንደሆነ ተናግሯል። እርሱ በር መሆኑን ተናግሯል። እርሱ መልካም እረኛ መሆኑን ገልጾላቸዋል። እኔም የትንሽዋ ቤተ ክርስቲያኔ መሪና መሥራች መሆኔን ለመናገር የተገደድኩባቸው ጊዜያት ነበሩ። ማን መሆንህን እንደምታውቅ ሰዎች መረዳታቸው አስፈላጊ ነው።

## 5. መለየትህ ሊያስፈራህ አይገባም

ደቀ መዛሙርቱ በእግራቸው ሲሄዱ ኢየሱስ በአህያ ላይ ተቀምጦ ነበር። ለእርሱ መረማመጃ ልብስ ተነጥፎለት ነበር።

> አህያይቱንና ውርንጫዋንም አመጡለት፥ ልብሳቸውንም በእነርሱ ላይ ጫኑ፥ ተቀመጠባቸውም። ከሕዝቡም እጅግ ብዙዎች ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፥ ሌሎችም ከዛፍ ጫፍ ጫፉን እየቈረጡ በመንገድ ላይ ያነጥፉ ነበር።
>
> ማቴዎስ. 21፡7-8

ለአንተ የተለዩልህን ልዩ ጥቅሞች ተቀበል። ይህንን በማታደርግበት ጊዜ ችግሮችንና የሥርዓት መዛባትን ታስከትላለህ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ከገዥ የሚመነጭ ክፉ ነገር እና ስህተት እንደሆነ ይናገራል።

> ከፀሐይ በታች ያየሁት ክፉ ነገር አለ፥ እርሱም ከገዢ የሚወጣ ስሕተት ነው፤ ሰነፍ በታላቅ ማዕረግ ተሾመ፥ ባለጠጎች ግን በተዋረደ ስፍራ ተቀመጡ። ባሪያዎች በፈረስ ላይ ሲቀመጡ መሳፍንትም እንደ ባሪያዎች በምድር ላይ ሲሄዱ አየሁ።
>
> መክብብ 10፡5-7

## 6. ከሌሎች ክብርን ለመቀበል ፍቀድ

ኢየሱስ ማርያም እንድታከብረው ፈቅዷል። ውድ የሆነውን ሽቶ ከእግሩ ላይ እንድታፈስ ፈቀደ።

> ማርያምም ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፤ በጠጕርዋም እግሩን አበሰች፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ።

ዮሐንስ 12፥3

## *ምዕራፍ 34*

# ጠቅለል ባለ መንገድ የወደፊቱን ሁኔታ ተንብይ

> **እነሆ፥ እያንዳንዳችሁ ወደ ቤት የምትበታተኑበት እኔንም ለብቻዬ የምትተዉበት ሰዓት ይመጣል፥ አሁንም ደርሶአል፤ ነገር ግን አብ ከእኔ ጋር ስለ ሆነ ብቻዬን አይደለሁም። በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።**
>
> **ዮሐንስ 16፡32-33**

መሪ ወደፊት አሻግሮ የመመልከት ብቃት ያለው ሰው ነው፡፡ በአጠቃላይ አነጋገር፣ ጥሩ መሪ ወደፊት የሚሆነውን የመተንበይ ችሎታ አለው፡፡ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ስደት እንደሚደርስባቸው ተናግሯል፡፡ ይህም በርግጥ ተፈጽሞባቸዋል! የአዲስ ቡድን አባላት የሆኑ ሰዎች ችግር እንደሚገጥማቸው ለመተንበይ ልዩ ነቢይ መሆን አይጠበቅብህም፡፡

ታሪክን፣ ተራ መረዳትን፣ የእግዚአብሔርን ቃልና የእግዚአብሔርን መንፈስ በማቀናጀት ሁሉም መሪ የወደፊቱን ሁኔታ ሊተነብይ ይችላል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ከፀሐይ በታች ምንም አዲስ ነገር እንደሌለ ያስተምረናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ወደፊት የሚከሰተው ነገር ቀደም ሲል የተከሰተ መሆኑን በግልጽ ይነግረናል፡፡

> **የሆነው ነገር እርሱ የሚሆን ነው፥ የተደረገውም ነገር እርሱ የሚደረግ ነው፤ ከፀሐይም በታች አዲስ ነገር የለም።**
>
> **መክብብ 1፡9**

ጥሩ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ከአጠቃላይ የሁኔታዎች አካሄድ በመነሳት የተወሰኑ ንግዶች ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደሚያልፍባቸው መተንበይ መቻል አለበት፡፡ አንዳንድ ፖለቲከኞች የሚሄዱበት መንገድ በአሳዛኝ ሁኔታ እንደሚደመደም መመልከት አለባቸው፡፡ የወንጌል አገልጋዮችም የወደፊቱን ሕይወት ጠቅለል ባለ መልኩ መመልከት መቻል አለባቸው፡፡ እዚህ ላይ እየተናገርሁ ያለሁት ክስተቶችንና ቀኖችን መተንበይን አይደለም፡፡ እየተናገርሁ ያለሁት ተራ ግንዛቤን ስለመጠቀም ነው!

ከጥቂት ዓመታት በፊት የቤተ ክርስቲያናችን አባላት በከተማይቱ ውስጥ ወዳሉ የተለያዩ አካባቢዎች እንደሚሄዱ ተገነዘብሁ፡

ከተማይቱም እጅግ እየሰፋች በመሄድ ላይ መሆኗን ለመረዳት ቻልሁ፡፡ በመሆኑም ከሚሄዱበት ቦታ ርቀት የተነሳ በርካታ አባላቶቻችን ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣታቸውን ሊያቆሙ እንደሚችሉ ተነበይሁ፡፡ ይህንን መተንበይ የቻልሁት ደግሞ የሰው ልጆችን ባህርይ ከማወቅ ነው፡፡

መሪ እንደመሆኔ መጠን፣ ምእመኖቻችን ዝናብ በሚሆንበት ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደማይመጡ ተገንዝቤ ነበር፡፡ አንዱን ሳምንት መጥተው ቀጣዩን እንደሚቀሩም አውቅ ነበር፡፡ ሁኔታዎች በጣም አመቺ በማይሆኑበት ጊዜ በጎቻችን ከመከተል እንደሚቦዝኑ መገንዘብ የመሪነት ግዴታዬ ነው፡፡ ለዚህ ነው በአክራ ከተማ ዳርቻዎች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን የጀመርሁት፡፡

ዛሬ በአክራ ከተማ ብቻ ከአምሳ አምስት በላይ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት አሉን፡፡ በእነዚህ በከተማው ውስጥ በተንሰራፉ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ደግሞ በሺዎች የሚቆጠሩ ምእመናን አሉን፡፡ በተረዳሁት ጉዳይ ላይ እርምጃ ባልወስድና ትንበያ ባላካሂድ ኖሮ በሺዎች የሚቆጠሩ አባላት ሳይኖሩኝ ይቀሩ ነበር፡፡ እዚህ ጋር የምናገረው ኢየሱስ መቼ እንደሚመለስ ስለ መተንበይ አይደለም፡፡ እኔ የምናገረው ግልጽ የሆነውን ነገር ስለመመልከትና እንደ አስተዋይ መሪ ወደፊት ስለማየት ነው፡፡

## ምዕራፍ 35

# መራርነት እንዲበክልህ አትፍቀድ

በብሉይ ኪዳን ካህን ቁስል እንዲኖርበት አይፈቀድም ነበር።

> ለአሮን እንዲህ ብለህ ንገረው። ከዘርህ በትውልዳቸው ነውር ያለበት ሰው ሁሉ የአምላኩን እንጀራ ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ። ዕውር፥ ወይም አንካሳ፥ ወይም አፍንጫ ደፍጣጣ፥ ወይም፤ ትርፍ አካል ያለው፥ ወይም እግረ ሰባራ፥ ወይም እጀ ሰባራ፥ ወይም ጐባጣ፥ ወይም ድንክ፥ ወይም ዓይነ መጭማጫ፥ ወይም እከካም፥ ወይም ቋቍቻም፥ ወይም ጃንደረባ፥ ነውረኛ ሁሉ አይቅረብ። ከካህኑ ከአሮን ዘር ነውር ያለበት ሰው የእግዚአብሔርን የእሳት ቍርባን ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ፤ ነውረኛ ነው፤ የአምላኩን እንጀራ ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ። የቅዱሱንና የቅዱስ ቅዱሳኑን የአምላኩን እንጀራ ይብላ፤ ነገር ግን ነውረኛ ነውና መቅደሶቼን እንዳያረክስ ወደ መጋረጃው አይግባ፥ ወደ መሠዊያውም አይቅረብ፤ የምቀድሳቸው እኔ እግዚአብሔር ነኝ። ሙሴም ይህን ለአሮን፥ ለልጆቹም፥ ለእስራኤልም ልጆች ሁሉ ነገረ።
>
> ዘሌዋውያን 21፡17-24

ቁስል የሚያሳየው ያልዳነ ጉዳትን ነው። አመራር የታጀበው በቁስል፣ በቅያሜ በሥቃይ ነው። በመሆኑም፣ የአመራር ቁስሎች አመለካከትህን እንዲያበላሹ ልትፈቅድ አይገባም።

## በመሪ ውስጥ መራርነት ሲኖር የሚፈጠሩ አራት አደጋዎች

### 1. መራር መሪ እግዚአብሔርን ከመተማመን ሊቆጠብ ይችላል።

በክርስቲያን መሪ ሕይወት ውስጥ የሚታዩ ብዙ ማብራሪያ ያልተገኘላቸው ክስተቶች አሉ። በዓለማዊ ፖለቲካ እንኳን በአብዛኛው መልካም የሆኑት አያሸንፉም። መልካም ተሸንፎ መጥፎውና መልካም ያልሆነው በምርጫ የሚያሸንፍበትም ጊዜ አለ።

አብረውኝ የሚያገለግሉ ሁለት ወጣት መጋቢዎች በሦስት ሳምንት ልዩነት ተከታትለው የሞቱበትን ሁኔታ ምን ጊዜም አልዘነጋውም። አንደኛው የሃያ ሰባት ዓመት ወጣት ሲሆን፣ ሌላኛው ሠላሳ ስምንት ዓመቱ ነበር። ለእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ምን ዓይነት ማብራሪያ ሊኖር ይችላል? የእነዚህን ሁለት መጋቢዎች ሚስቶች በማጽናናበት ጊዜ፣

"የሰባት ወራት የጋብቻ ዕድሜ ብቻ ለነበራት ለዚህች ወጣት ሚስት እንደ እግዚአብሔር መልእክተኛ ምን ዓይነት ማብራሪያ ልሰጣት እችላለሁ?" ስል አሰብሁ።

የዮሐንስ ወንድም የሆነውን ያዕቆብን፣ ሄሮድስ በገደለው ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት ማብራሪያ ልትሰጥ ትችል ነበር። ቤተ ክርስቲያን ጽኑ መሠረት ለመጣል የያዕቆብ ድጋፍ አያስፈልጋትም ነበር? ጌታ ያዕቆብ በዚህ ጊዜ እንዲሞት የፈቀደው ለምንድነው? ነፍሳትን መማረክ አስፈላጊ አልነበረም ማለት ነው? የቤተ ክርስቲያን ተከላ አስፈላጊ አልነበረም? ተጨማሪ ሠራተኞች አያስፈልጉም ነበር? እግዚአብሔር እንዴት እንዲህ ዓይነት ነገሮች እንዲከሰቱ ይፈቅዳል?

በዚህ ሕይወት ውስጥ ሊብራሩ የማይችሉ ችግሮች ቢያጋጥሙም፣ መሪ በጌታ መታመኑን ሊቀጥል ይገባል።

## 2. መራር መሪ የሚመራቸውን ሰዎች መጥላት ሊጀምር ይችላል

የሰው ልጆች የክህደት፣ ያለማመስገንና የዝንጉነት ባሕርያቸውን በሚገልጹበት ጊዜ መሪው ቀስ በቀስ በመንጋው ላይ መራርነትን ሊያዳብር ይችላል። በራሴ ላይ የደረሱ ብዙ የሚያሳምሙ ነገሮች አሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ይቅር ብዬ ወደፊት መጓዝ እንዳለብኝ ተምሬአለሁ። ጣፋጭ መንፈስ ሳይኖረኝ እግዚአብሔርን ደስ ላሰኘው አልችልም። እያንዳንዱ መራር ገጠመኝ በፍቅር ለመመላለስ መቻሌን የሚፈትን ነበር። እነዚህን ሁኔታዎች ለማለፍ እንድችል ሁልጊዜ እጸልያለሁ።

## 3. መራር መሪ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያሉ ሌሎች መሪዎችንና የአመራር ባልደረቦቹን ሊጠላ ይችላል

የሚያሳዝነው ከማንም በላይ ክፉ የሚመኙልህ ባለህበት ተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያሉ መሪዎች ይመስላሉ። እንዲያውም ዓለማውያን እነዚህ የአገልግሎት እኩዮችህና ባልደረቦችህ ያለባቸውን ዓይነት አንዳንድ የጥላቻ ስሜቶች ያላቸው አይመስሉም! እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ የሰጠን ምናልባት ለሰዎች ሁሉ ፍቅር እንድናሳይ ይሆናል። በፍቅር ካልተመላለስህ አገልግሎትህ በእግዚአብሔር ፊት ምንም ዋጋ አይኖረውም።

> ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 13፡2

## 4. መራር መሪ የተዘበራረቀ መልእክት ያስተላልፋል።

በዕብራውያን ቋንቋ መራርነት ሰዎችን ሁሉ እንደሚመርዝ ሥር ተገልጾአል። ይህ ከውኃ ብክለት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው። መራርነት ከሚበክላቸው ነገሮች አንዱ መልዕክትህን ነው። መራር ሰው የተበላሸና የተዘበራረቀ መልዕክት ያስተላልፋል። ሥቃይህ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች ከመግለጥ ሊከለክልህ አይገባም።

## *ምዕራፍ 36*

# የሰዎችን አስተሳሰብ ለውጥ

ራስህን መሪ ብለህ የምትጠራ ከሆነ የሰዎችን አስተሳሰብ የመለወጥ ጥበብ ልታዳብረው የሚገባ እጅግ ጠቃሚ ክህሎት ነው። የማሳመን ጥበብ መሠረታዊ የመሪነት ጥበብ ነው። አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር የራሱ አስተያየት ኖሮት አንተ ያንን አስተያየቱን መቀየር ከቻልክ የመሪነትን ተግባር በማከናወን ላይ ነህ ማለት ነው።

ቶማስ ትንሣኤ እውነት አይደለም የሚል አሳብ ነበረው። ኢየሱስ ይህንን አሳብ በመለወጥ ቶማስ የትንሳኤን እውነተኛነት እንዲቀበል አድርጐታል። ሰዎች በመንግሥተ ሰማይ ወይም በሲኦል መኖር ማመን አለማመናቸው ያሳስብሃል? የሰዎች አስተሳሰብ የማያሳስብህ ከሆነ፣ መሪ ልትሆን አትችልም። ምናልባትም ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ሰዎች መጥፎ አመለካከት ይኖራቸው ይሆናል። አንድ መሪ የእንደነዚህ ዓይነት ሰዎችን አስተሳሰብ በመለወጥ ትክክለኛ ግንዛቤ እስከሚጨብጡ ድረስ በአስተሳሰባቸው ለውጥ ላይ ይሠራል!

መጋቢ ሁልጊዜም ሰዎች ስለ ሕይወት ያላቸውን አስተሳሰብ እንዲቀይሩ ያደርጋል። ሥራው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲወዱትና እንዲያገለግሉት ማድረግ ነው። ምናልባት ገንዘብን ሲያገለግሉ ኖረው ሊሆን ይችላል፤ በትክክለኛ መጋቢ (መሪ) አገልግሎት አማካኝነት ግን እግዚአብሔርን ማገልገል ከማንኛውም ነገር ይልቅ ጠቃሚ መሆኑን ያምናሉ።

## ሰዎች አስተሳሰባቸውን እንዲለውጡ ለማድረግ የሚያስችሉ ሰባት መንገዶች

### 1. የእግዚአብሔርን ቃል አስተምራቸው

**የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።**

**ሮሜ 12፡2**

ይህ ጥቅስ አእምሮአችን ሲታደስ እኛ እንደምንቀየር ወይም እንደምንለወጥ ያስረዳናል። ሰዎች አስተሳሰባቸውን እንዲለውጡ የእግዚአብሔር ቃል ምርጥ መሣሪያ ነው። በቃሉ ውስጥ ኃይል አለ፤ ለዚህም ነው ጳውሎስ፣ "በወንጌል አላፍርም፤ *...የእግዚአብሔር ኃይል* ለማዳን ነውና ።" ያለው።

## 2. ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄዱ አድርግ

ቤተ ክርስቲያን ለማንም ሰው መደበኛ አእምሮ ለዋጭ ስብሰባን ታማቻቻለች። ቤተክርስቲያንህን አሳየኝና እንዴት እንደምታስብ አሳይሃለሁ።

## 3. የተወሰኑ ዓይነት ጓደኞች እንዲኖሯቸው አድርግ

አብረውህ የሚያሳልፉ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያንህ በበለጠ ተጽእኖ ያሳድሩብሃል። ይህም በሳምንት ውስጥ ለበርካታ ሰዓታት ከጓዳኞችህ ጋር ስለምትሆንና በአንፃሩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሣምንት ለጥቂት ሰዓታት ብቻ ልትሆን ስለምትችል ነው። "ጓደኛህን ንገረኝና ማንነትህን እነግርሀለሁ።" እንደሚባለው ማለት ነው።

> **አትሳቱ፤ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል።**
>
> **1ኛ ቆሮንቶስ 15፡33**

## 4. እንዲኖራቸው የምትፈልገው ዓይነት አስተሳሰብ ካላቸው ስኬታማ ሰዎች ጋር አስተዋውቃቸው

የፉል ጎስፐል ቢዝነስ ሜን ኢንተርናሽናል ምስጢር ይህ ነው። ስኬታማ የሆኑ ክርስቲያን ነጋዴዎችን ለኃጢአተኞች በማስተዋወቅ ስኬታማ ነጋዴ መሆን እንደሚቻል ያሳይዋቸዋል። በዚህ ዘዴ ብዙ ሰዎች ክርስቶስን አግኝተዋል። (በሌላ አባባል፣ አስተሳሰባቸውን ለውጠዋል።)

## 5. የራስህን ምስክርነት አካፍላቸው

የሰዎችን አሳብ ለመለወጥ የግል ምስክርነት ሁልጊዜም ታላቅ መሣሪያ ነው። ጳውሎስ ለንጉሥ አግሪጳ ይህንን ዘዴ ተጠቅሟል። የሐዋርያት ሥራ ምእራፍ ሃያ ስድስት በሙሉ ጳውሎስ ምስክርነቱን ለንጉሱ ሲያካፍል የሚገልፅ ነው። ከዚህ ኃይለኛ ምስክርነት መጨረሻ ላይ ንጉሥ አግሪጳ የሚከተለውን ነበር የተናገረው።

> **አግሪጳም ጳውሎስን፣ በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህ አለው። (በሌሎች ትርጉሞች፣ ክርስቲያን ልታደርገኝ ምንም አልቀረህም ተብሎ ተገልጾአል፡፡)**
>
> **የሐዋርያት ሥራ 26፡28**

## 6. ጸልይላቸው

የአእምሮ አስተሳሰብ በጣም መንፈሳዊ ነገር ነው። ስለዚህም ነው ጳውሎስ እግዚአብሔር ለኤፌሶን ሰዎች የመገለጥና የጥበብ መንፈስ እንዲሰጣቸው የጸለየው። ስብከትና ትምህርት መስማት ቢቻልም፣ ያለ መገለጥ ለውጥ ሊመጣ አይችልም።

> የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ።
>
> ኤፌሶን 1፡17

## 7. የተወሰኑ ተሞክሮዎችን እንዲኖራቸው ተዋቸው

ምንም ብትናገር ወይም ብትሰብክ አንዳንድ ሰዎች አሳባቸውን አይቀይሩም። ለእንዲህ ዓይነት ሰዎች የተሞክሮ ትምህርት ቤት (ብርቱ ኩርኩም መቅመስ!) አማራጭ የሌለው ነው። ሰዎች በአንዳንድ የሕይወት ተሞክሮ ውስጥ እንዲያልፉ መተው አእምሯቸው በትክክል እንዲሠራ ለማስቻል ብቸኛ መንገድ ነው። አንዳንድ ጊዜ መጋቢዎች በተወሰኑ ተሞክሮዎች ውስጥ እንዲያልፉ እተዋቸዋለሁ። ለምሳሌ፣ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን የመትከል ተሞክሮ ውስጥ ካለፉ ብዙውን ጊዜ ለማስተምራቸው ብዙ ነገሮች ከበሬታን ይሰጣሉ።

በአንድ ወቅት ታማኝነት ያጎደለውን ረዳት አገልጋይ የማስተናግድበት ሁኔታ ያላስደሰተው መጋቢ አጋጥሞኝ ነበር። ይህ መጋቢ ከዓመፀኛው ጋር የነበረኝን ሁኔታ ፍቅር የጎደለው ተግባር እንደማከናውን ነበር የተሰማው። ጉዳዩን ደጋግሜ ባብራራለትም የእኔ ጥፋተኝነት ብቻ ነበር የሚታየው። በመጨረሻም፣ እግዚአብሔር አመፀኛ ረዳት መጋቢ እንዲሰጠው ጸለይሁ። እግዚአብሔር ጸሎቴን በመመለሱ አመፀኛ ረዳቶች ተፈራረቁበት።

አንድ ቀን እርሱም ታማኝ ያልሆኑ ሰዎች ከገጠሙት በኋላ፣ ስልክ ደወለልኝና ታማኝነት ላጎደሉብኝ ረዳት መጋቢዎች ተገቢውን ቅጣት እንዳልሰጠሁና ሩሩህ እንደሆንሁ ገለጸልኝ። ፈገግ አልሁ፣ ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ዓይነት አቋም እንደነበረው አስታወስ ነበር። የዚህ መጋቢ አስተሳሰብ በእርግጥ ተለውጧል፤ እዲያውም ዓመፀኛውን በፍቅር እዳስተናገድሁት ገለጸልኝ።

ይህ የሰዎችን አስተሳሰብ ለመለወጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ነው። ልትጠቀምበት የሚገባ መንገድ ነው ምክንያቱም፣ ሰዎች በልምምድ ብቻ የሚማሯቸው ብዙ ነገሮች አሉ። አብም እራሱ ኢየሱስን በዚህ

መንገድ አስተምሮታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፣ ኢየሱስ መታዘዝን የተማረው ከተሞክሮው እንደነበር ይገልፃል፡፡

**ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፡፡**

**ዕብራውያን 5፡8**

መሪ የሰዎችን አስተሳሰብ ለመለወጥ የሚችለውን መንገድ ሁሉ ይጠቀማል፡፡ አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር የነበረውን አሳብ እንዲቀይር አድርገህ ታውቃለህን?

**ነገር ግን ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከእነርሱ ጋር አልነበረም። ሌሎቹም ደቀ መዛሙርቱ። ጌታን አይተነዋል አሉት። እርሱ ግን። የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው። ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደግመው በውስጥ ነበሩ፥ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ። ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ። ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ከዚያም በኋላ ቶማስን። ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቹን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው። ቶማስም። ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም። ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።**

**ዮሐንስ 20፡24-29**

## *ምዕራፍ 37*

# እየተከናወነ ስላለው ነገር ሁሉ መጠነኛ ግንዛቤ ይኑርህ

ምርጥ መሪዎች ስለሁሉም ነገር መጠነኛ ግንዛቤ ያላቸው ናቸው። መሪ ስለ ሁሉ ነገር በመጠኑ ማወቅ አለበት። ለዚህ ነው ብዙ ድርጅቶች ወደ ሁሉም የሥራ ክፍሎች በመውሰድ መሪዎቻቸውን የሚያሰለጥኑት።

ስለ ሕግ፣ ስለ ሕክምና፣ ስለ ሂሳብ አያያዝ፣ ስለ ሥራ አስኪያጅነት፣ ስለ አስተዳደር ስለ አናጢነት የተወሰነ ነገር አውቃለሁ። ስለ ኮንስትራክሽን በጥቂቱ አውቃለሁ። ስለ ምህንድስና እና ስለ ሕንጻ ዲዛይን ብዙ አውቄአለሁ። በተጨማሪም ስለ ኤሌክትሮኒክስ፣ ሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ስለ ኮምፒውተር፣ እና ወዘተ... መጠነኛ ግንዛቤ አለኝ። ብዙ ጊዜ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር የሙያ ክርክር አደርጋለሁ። ስለ ሙያ መስካቸው የተወሰነ እውቀት እንዳለኝ ያውቃሉ። በቀላሉ እንደ መሃይም ሊያደናግሩኝ እንደማይችሉ ይረዳሉ።

በዙሪያህ ስላለው ነገር መጠነኛ ግንዛቤ ከሌለህ ጥሩ መሪ ልትሆን አትችልም። ስለ አንድ የሥራ መስክ እውቀት ከሌለህ ተግተህ ልታነብና ራስህን ልታስተምር ይገባል ማለት ነው።

በአመራርህ ሥር ስለ ሂሳብ አያያዝ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ኃላፊነቱ ያንተው ነው። ለዚህ ነው ስለ ሁሉም ነገር መጠነኛ ግንዛቤ መጨበጥ የሚያስፈልገው። በፍጹም እንዲህ አትበል፡- “ይህ የሕክምና ሙያ ነው። ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው የለኝም። ምንም አያገባኝም። ለማወቅም አልፈልግም!”። ልታውቃቸው የምትችላቸውና ልታውቃቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ!

## ምዕራፍ 38

# ስሜት ያለው መሪ ሁን

ሰዎች ስሜታቸውን ወደሚገልጹ ሰዎች ይሳባሉ። በመሆኑም ስሜትህን ለመግለጽ አትፍራ። ስሜትህን በምትገልጽበት ጊዜ እውነተኛ ሰብአዊ ሰው መሆንህ ስለሚታይ ሰዎች የምትናገረውን ለማዳመጥ በዙሪያህ ይሰበሰባሉ። መሪ ስለሆንክ ብቻ እያስመሰልክ መኖር አያስፈልግህም። በዚህች ምድር ላይ የተፈጠረ ሰው ሁሉ ይስቃል፣ ያለቅሳል፣ ይቆጣል እናም ይደሰታል። በሁሉም ሰው ሕይወት ውስጥ ከፍታና ዝቅታ ይኖራሉ።

መሪ ለመሆን እውነተኛነትን ማንጸባረቅ አለበህ። የምንኖረው ብዙ ችግሮች ባሉባት እውነተኛ ዓለም ውስጥ ነው። መሪ እውነተኛ ስሜት ያለው እውነተኛ ሰው ነው። አንድ መሪ ተከታዮቹ የሚሰማቸው ስሜት ሁሉ እርሱም ይሰማዋል። ብዙ ሰዎች ስሜታቸውን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው አያውቁም። ከተጨባጭ ስሜቶቹ ባሻገር ውጤታማ የሆነ ሰው ቢያገኙ ከዚህ ዓይነቱ ሰው ጋር ግንኙነት ለመመስረት መፈለጋቸው የማይቀር ነው።

## ስሜታቸውን የሚገልጹ ሰዎች ማራኪ የሚሆኑባቸው ስምንት ምክንያቶች

1. ስሜታቸውን የሚደብቁ ሰዎች ብዙውን ጊዜ አሰልቺዎችና አብሮ ለማሳለፍ የማይጋብዙ ናቸው።

2. ስሜታቸውን የሚደብቁ ሰዎች በዙሪያቸው ሕይወት የመዝራት አቅም የላቸውም።

እየተካሄደ ባለው ውይይት ላይ ምንም ዓይነት አስተያየት ከማይሰጥ ኮስታራና ፈገግታ ከራቀው ሰው ጋር በምትቀመጥበት ጊዜ ውጥረት ይኖራል።

3. ብዙውን ጊዜ ስሜት የሌላቸው ወንዶችና ሴቶች አክራሪ ኮስታራ፣ አምባገነን፣ የማይረኩና አስጨናቂ ናቸው፡

4. ስሜት የሌላቸው ሰዎች ውሸታሞችና አስመሳዮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ሰዎች ከአስመሳዮች ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው አይፈልጉም፡፡

5. ሰዎች አንድ ሰው እውነተኛ ስሜቱን የሚገልጽ ከሆነ፣ የሚናገራቸውም ነገሮች እውነት እንደሆኑ ያስባሉ፡፡

6. ስሜትን ማሳየት የሌሎችን ስሜት ይቀሰቅሳል፡፡

ሰዎች ስሜታቸው ሲቀሰቀስ የበለጠ የተሰጡ ይሆናሉ፡፡

7. ሰዎች የደስታ፣ የንዴት፣ የሐዘንና ልብ አንጠልጣይ ስሜቶችን የሚያንፀባርቅ ሰባኪን ማዳመጥ ያስደስታቸዋል፡፡

8. ታላቁ ምሳሌያችን የሆነው ኢየሱስ ብዙ አጋጣሚዎች ላይ ስሜቱን ገልጿል፡፡

## ኢየሱስ ስሜቱን ያሳየባቸው አምስት ምሳሌዎች

1. **ታላቅ እምነት የነበረውን ሰው ሲያይ ኢየሱስ ተደንቆ ነበር ፡፡**

ኢየሱስም ይህን ሰምቶ በእርሱ ተደነቀ፥ ዘወርም ብሎ ለተከተሉት ሕዝብ። እላችኋለሁ፥ በእስራኤልስ እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም አላቸው።

ሉቃስ 7፡9

2. **ኢየሱስ ስለ ከተሞች አንብቷል፡፡**

ሲቀርብም ከተማይቱን አይቶ አለቀሰላት፡፡

ሉቃስ 19፡41

3. **ኢየሱስ ለጠፉ እና ረዳት ለሌላቸው ሰዎች አዝኖላቸው ነበር፡፡**

ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን። መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡

ማቴዎስ 9፡36-37

## 4. ኢየሱስ በግብዞች ተቆጥቶ ነበር

የአይሁድ ፋሲካም ቀርቦ ነበር፥ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። በመቅደስም በሬዎችንና በጎችን ርግቦችንም የሚሸጡትን ገንዘብ ለዋጮችንም ተቀምጠው አገኘ፤ የገመድም ጅራፍ አበጅቶ ሁሉን በጎችንም በሬዎችንም ከመቅደስ አወጣቸው፥ የለዋጮችንም ገንዘብ አፈሰሰ ገበታዎቻቸውንም ገለበጠ፡፡

ዮሐንስ 2፡13-15

## 5. ኢየሱስ ለግለሰቦች እንባውን አፍስሷል፡፡

ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ። ስለዚህ አይሁድ፣ እንዴት ይወደው እንደ ነበረ እዩ አሉ።

ዮሐንስ 11፡35-36

## ምዕራፍ 39

# የተሰጠህን ልዩ መብት በተገቢው ጊዜ እና ለተገቢ ምክንያት ተጠቀም

ከፀሐይ በታች ያየሁት ክፉ ነገር አለ፥ እርሱም ከገዢ የሚወጣ ስሕተት ነው፤ ሰነፍ በታላቅ ማዕረግ ተሾመ፥ ባለጠጎች ግን በተዋረደ ስፍራ ተቀመጡ። ባሪያዎች በፈረስ ላይ ሲቀመጡ መሳፍንትም እንደ ባሪያዎች በምድር ላይ ሲሄዱ አየሁ።

መክብብ 10፡5-7

አንድ መሪ ትሁት ሰው መሆን አለበት፤ ሆኖም ልበ-ሙሉ መሆን ይገባዋል፡፡ አንድ መሪ በተያዘለት ተገቢ ቦታ አልቀመጥም ቢል ይህ ሞኝነት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ ልዩ መብትህን የምትጠቀምበት ጊዜ ሲደርስ ባትጠቀምበት እንደሞኝ ትቆጠራለህ፡፡ መሪነት መሥዋዕትነት ብቻ አይደለም፡፡ መሪነት ኃላፊነት ብቻ አይደለም፡፡ መሪነት ከተወሰኑ ልዩ መብቶችና በረከቶች ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡

## መታዘዝ ከመሥዋዕትነት ይልቅ ጠቃሚ ነው

የእግዚአብሔር ጥሪ በራሱ ለመሥዋዕትነት ሳይሆን ለመታዘዝ ነው፡፡ መታዘዝ መሥዋዕትነት መክፈል የሚሆንባቸው ጊዜያት አሉ፡፡ እግዚአብሔር ሳይጠይቅህ መሥዋዕትነት ብትከፍል ራስህን ከእግዚአብሔር ትነጥላለህ፡፡ ሳዖል እግዚአብሔር ያልጠየቀውን ነገሮች መሥዋዕት በማድረጉ ከእግዚአብሔር እንዴት እንደተለየ አትርሳ፡፡

> ሳሙኤልም፣ በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ፥ መታዘዝ ከመሥዋዕት፥ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል። ዓመፀኝነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት፥ እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው፤ የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እግዚአብሔር ንጉሥ እንዳትሆን ናቀህ አለ።

1ኛ ሳሙኤል 15፡22-23

## መሣፍንት በፈረስ ላይ መቀመጥ የሚኖርባቸው ጊዜ

መሣፍንት በፈረስ ላይ የሚቀመጡበት እና ባሮች በእግር መሄድ የሚገባቸው ጊዜ አለ፡፡ “ባሪያዎች በፈረስ ላይ ሲቀመጡ መሳፍንትም እንደ ባሪያዎች በምድር ላይ ሲሄዱ አየሁ፡፡” (መክብብ 10:7)፡፡

ተግተህ ለሠራኸው ሥራ ገንዘብን ለመቀበል አትፈር። ምንም እንደማይገባቸው ለማኞች ስለሚቆጠሩ የወንጌል አገልጋዮች አዝናለሁ። የቤት ውስጥ ፍጆታቸው ብቻ ተሟልቶ ለመጋቢዎች ምንም ገንዘብ የማይሰጥባቸውን አብያተክርስቲያናት አውቃለሁ። በቤቱ ውስጥ በቂ ሳሙናና የሽንት ቤት ወረቀት መኖር አለመኖሩን ለማጣራት የቤተ ክርስቲያን አባላት ይመጣሉ። እንዴት ያሳዝናል! መጋቢያኑ የራሳቸውን የሽንት ቤት ወረቀት ለመግዛት የሚያስችል እውቀት የላቸውም?

## ስህተቱ

ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ለመጋቢው መኪና በመግዛቱ ውዝግብ ውስጥ ሲገቡ ተመልክቻለሁ። ልዩ መዋጮ ተደርጎ ለመጋቢው መኪና መግዛቱ የቤተ ክርስቲያን አነጋጋሪ ጉዳይ ሆነ። ሰዎች በሌሎች ተቋማት ውስጥ ተቀጥረው ሲሠሩ፣ የመኪና ግዥ ልዩ ፕሮጀክት ነው? የሚገባቸው አይደለምን? መጋቢዎች እንደማይገባቸው ሥራ ፈቶች የሚቆጠሩት ለምንድን ነው?

እንደ ወንጌል አገልጋይ ተግቼ ሰራለሁ። በደንብ ሊከፈለኝ ይገባል። ወንጌልን የሚሰብኩ የሚያስፈልጋቸውን ከወንጌል እንዲቀበሉ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል።

> እንደዚሁም ወንጌልን የሚሰብኩ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን፣ ከወንጌል እንዲቀበሉ ጌታ አዟል።
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 9፡14

## ያለ ማጨድ መዝራት

> የሚደከመው ገበሬ ፍሬውን ከሚበሉት መጀመሪያ እንዲሆን ይገባዋል።
>
> 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡6

ለደህንነቴ እና ለምቾቴ ሲባል ጥሩ መኪና ሊኖረኝ ይገባል። ቤት የመሥራት አቅሙ ሊኖረኝ ይግባል። ይህ ምንም ችግር የለበትም! ነገር ግን ሰው ዘርቶ የማያጭድ ከሆነ አንድ ችግር አለ። ሁሉም ያንን ያውቃል። አንድ መሪ መቼ ሥፍራውን መያዝ እና ጥቅሞቹን መውሰድ እንዳለበት ሊያውቅ ይገባል። ተራህ ደርሶህ ልዩ መብቶችህንና በረከቶችህን መውሰድ ሲገባህ አለመውሰድ ስህተት ነው። ስህተት ብዬ የጠራሁት እኔ አይደለሁም። መፅሐፍ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከገዥ የሚወጣ ስህተት ይለዋል!

# መሣፍንት ማልደው ሲመገቡ

አንዳንድ አገሮች “የህዝቡን የደም ሥር” በመጠጣት ንግስናቸውን የሚጀምሩ መሪዎችን አሳልፈዋል። ይሁንና ከመቅፅበት መሪዎቹ ሁሉን አሟጠው ጨርሰዋል። እጅግ ብዙ ነዳጅ የምታመርትን አንድ የበለፀገች አፍሪካዊ አገርን በቅርቡ ጐብኝቼ ነበር። በዓለም እጅግ ብዙ ነዳጅ ከሚያመርቱ አገሮች አንዷ የሆነችው ይህች አገር አሳሳቢ የሆነ የነዳጅ እጥረት እንዳለባት ብነግርህ ታምነኛለህ? የሚያስገርም ነበር! በጐበኘኋቸው ከተሞች ሁሉ እጅግ ረዥም ሰልፎች ነበሩ። ነዳጅ የሚሸጠው በህገወጥ ገበያ ላይ ብቻ ነበር።

ቀይቶም የሀገሪቱ መሪ በቢሊዮን ዶላሮች የሚቆጠር ገንዘብ ለጥቃቅን ወጪ የተያዘ ገንዘብ በሚል አካብተው እንደነበር ታወቀ። አንድ ፕሬዝዳንት ለጥቃቅን ወጪዎች የተዘጋጀ ገንዘብ በሚል በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ መያዝ ምን ሊያደርጉበት ነበር? የሀገሪቱ ብዙኃን ኑሮን ለማሸነፍ ሲጣጣሩ እነዚህ ሰው በሊታዎች የራሳቸውን ኪስ አካብተው ነበር። ከዓለማችን ነዳጅ ከመቶ እጅ ትንሽ የማይባል መጠን ያለውን ነዳጅ የምታቀርብ አገር በነዳጅ እጥረት መቸገሯ ግራ የሚያገባ አይደለም? መፅሐፍ ቅዱስ “መኳንንቶሽም ማልደው የሚበሉ…” የሚለው ይህንን ነው። መኳንንት የሚለው መሪን ሲወክል ማለዳው ደግሞ አግባብ ያልሆነን ጊዜን ያመለክታል።

> አንቺ፣ ንጉሥሽ ልጅ የሆነ፣ መሳፍንትሽም በጠዋት ግብዣ የሚያደርጉ ምድር ሆይ፤ ወዮልሽ። ንጉሥሽ የከበረ ልጅ የሆነ፥ ለብርታት እንጂ ለስካር ያይደለ በጊዜ የሚበሉ መኳንንት ያሉሽ፥ አንቺ አገር ሆይ፥ የተመሰገንሽ ነሽ።
>
> መክብብ 10፡ 16፣17

ወዳጄ ሆይ፣ አንድ አገር ወይም ቤተ ክርስቲያን አጋጣሚውን በመጠቀም ራሱን ለመጥቀም የሚፈልግን ሰው በጉዳዮቿ ላይ ከሾሞች ጭንቀትንና ድህነትን ብቻ ጠብቅ!

በእኛ ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንን ከመጋቢው የሚያስቀድም ፖሊሲ አለን። ይህ ስል ምን ማለቴ ነው? ከመጋቢው ደህንነት ቤተ ክርስቲያን ልትቀድም እንዳሚገባት እናምናለን። ይህም ማለት የመጋቢው ጥቅም ከመታየቱ አስቀድሞ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ተገንብቶ ቤተ ክርስቲያኗ የፀና አቋም ይኖራታል ማለት ነው።

# መኳንንት በተገቢው ወቅት ሲመገቡ

ልዩ መብቶች በረከት የሚሆኑት በትክክለኛው ጊዜ ሲመጡ ብቻ ነው። እጅግ ፈጥነው ሲመጡ ሁሉም ነገር ይበላሻል። አንዳንድ

ሰዎች ለመጠገን እንኳን የማይችሉትን መኪና ይገዛሉ። አንድ ሰው እንዲህ አለ፣ "የእሱን ዓይነት ሶስት የመጠገን አቅሙ ከሌለህ መኪና አትግዛ።" አንዳንድ ሰዎች የመጠገን አቅሙ የሌላቸው ቤት ውስጥ ይኖራሉ። ራስህን ለምን ታስጨንቃለህ? ሰዎችን ለማስደመም ለምን ትሞክራለህ? ራስህን ሁን፤ አንዳንድ ልዩ መብቶችን ለመያዝ አትቸኩል። ጌታ ከፍ ሲያደርግህ የሚያስፈልግህን ነገር ሁሉ በትክክለኛው ጊዜ ትቀበላለህ።

ሁሉንም ነገር በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው፤ . . .

መክብብ 3፥11

ውበት፣ ውበት የሚሆነው በ"ትክክለኛው ሰዓት" ብቻ ነው። ከሃያ ዓመታት በፊት የተነሳሃቸውን ፎቶግራፎች ስትመለከት አንዳች የጐደለህ እንደምትመስል አስተውለህ ታውቃለህ? ለምንድን ነው? ምክንያቱ ከ"ጊዜያቸው" ስለወጡ ነው።

## የእርሱ ጊዜ ትክክለኛው ጊዜ ነው።

መኪና ወይም ቤት እውነተኛ በረከት የሚሆነው በትክክለኛው ጊዜ ሲመጣ ነው። ያለ ጊዜው ከመጣ በረከት አይሆንም። እንዲያውም ችግሮች ያመጣብሃል። ያገባች ሴት ስታረግዝ ሁሉም ሰው ይደሰታል። እርግዝና በረከት ነው። ይሁን እንጂ ያላገባች ወጣት ሴት ስታረግዝ አንደሰትም። ይህ ለምን ይሆናል? ምክንያቱ "ያለ ጊዜው" የመጣ እርግዝና በመሆኑ ነው።

መሪ ነህ ወይስ የተራበ አውሬ? ልዩ መብቶችህን "በትክክለኛው" ጊዜ በትዕግሥት ጠብቅ። አትቻኮል፤ ቤተ ክርስቲያንህን፣ እራስህን፣ ሥራህን፣ ወይም አገርህን ታጠፋለህ። የወርቅ እንቁላሎች የምትጥልልህን ዶሮ አትግደላት። በተጨማሪም ብዙ ዓመታት የወርቅ እንቁላሎችን እንድትጥልልህ በሕይወት አቆያት!

## ምዕራፍ 40

# ከግለሰቦች ጋር ግንኙነት ፍጠር ከብዙሃኑም ጋር ግንኙነት ፍጠር

**ከሰማርያ አንዲት ሴት ውኃ ልትቀዳ መጣች። ኢየሱስም፦ ውኃ አጠጪኝ ስለዚህ ሳምራዊቲቱ። አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ? አለችው፤ አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና። ኢየሱስም መልሶ፦ ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደ ገና ይጠማል፤እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፥ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት። ሴቲቱ። ጌታ ሆይ፥ እንዳልጠማ ውኃም ልቀዳ ወደዚህ እንዳልመጣ ይህን ውኃ ስጠኝ አለችው።**

**ዮሐንስ 4፡7፤9፤13-15**

ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን የሚያገለግል ሰው ነበር። የሚያሰለጥናቸው የመጋቢዎች ቡድን ነበረው። እንዲሁም የተጣበበ ጊዜ ነበረው። ነገር ግን ሳምራዊቷን ሴት ሲያገኛት ጥቂት ጊዜ ወስዶ እንደ አንድ ግለሰብ አነጋገራት። መሪ ማለት ከግለሰቦች ጋር እንዴት መዛመድ እንደሚችል የሚያውቅ ነው። ኢየሱስ ይህቺ ሴት ደሃ ትሁን ሀብታም ምንም አያውቅም ነበር። የእርሱን እርዳታ እንደምትፈልግ ሰብዓዊ ፍጡር ብቻ ነው የተቀበላት።

የሰው ዘር በሙሉ ውስብስብ የመንፈስ፣ የነፍስና የሥጋ ጥምረት ነው። ሁሉም ሰብዓዊ ፍጡር የራሱ ፍርሀቶች፣ ስህተቶች እና ስኬቶችን አሳልፏል። ኢየሱስ እጅግ ብዙ ችግሮች የነበሩባትን ሴት ነበር ያነጋገረው። ሊረዳትም ችሎ ነበር። እግዚአብሔር መሪ እንድትሆን ጠርቶህ ከሆነ መፍትሔ የሚፈልጉን ግለሰቦች መርዳት አለብህ። ሰብዓዊ ፍጡርን እንደ ቁጥር ብቻ አትቁጠር። አባላትን እንደ "ከብዙኃኑ አንዱ" ብቻ የሚቆጥር ማንም ሰው የእነርሱን ድጋፍ እንደሚያጣ ብዙም ሳይቆይ ይገባዋል። ኢየሱስ ከድሆች ጋር እንደሚቆራኝ እያወቀ ነበር አገልግሎቱን የጀመረው። የሚያገለግለው ልባቸው የተሰበሩትንና የታሰሩ ሰዎችን ነበር። ውድ መሪ፣ እያንዳንዱ ግለሰብ ልዩ ትኩረት እንደሚፈልግ አስታውስ።

**ኢየሱስም፦ ሰዎቹን እንዲቀመጡ አድርጉ አለ። በዚያም ስፍራ ብዙ ሣር ነበረበት። ወንዶችም ተቀመጡ ቍጥራቸውም አምስት ሺህ የሚያህል ነበር።**

**ዮሐንስ 6፡10**

ኢየሱስ ቁጥራቸው የበዛ የሰዎችን ስብስብም ሆነ ግለሰቦችን እንዴት እንደሚያገለግላቸው ያውቅ ነበር፡፡ ብዙኃኑን በምታገለግልበት ጊዜ ምን ዓይነት ባሕሪይ ልታሳይ እንደሚገባህ ማወቅ አለብህ፡፡ በአግባቡ መልበስና በጥበብ መናገር አለብህ፡፡ በብዙኃኑ ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች እውነቱ ምን እንደሆነ ማወቅ ይፈልጋሉ፡፡ ጥሩ መሪ ተገቢውን መረጃ ለብዙኃኑ ያስተላልፋል፡፡

## ከብዙኃኑ ጋር የመግባቢያ ቁልፎች

### 1. ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ስጣቸው

ደሞዛቸውን የማትጨምር ከሆነ ደሞዛቸውን እንደምትጨምር አትንገራቸው፡፡

### 2. ጥቅም የለሽ ቃል አትግባ

ሰዎች ከንቱ ቃል ይሰለቻቸዋል፡፡

### 3. የምትችለውን ያህል መልካም ወሬ አብስር፡፡

አዲስ አጥቢያ ከተመሠረተ ይህንን አብስር፡፡ ተዓምራት ከተደረገ ለሰዎች ንገራቸው፡፡ ሰዎች እስካልነገርካቸው ድረስ አያውቁም፡፡ መልካም ዜና በብዙኃኑ ውስጥ መልካም ስሜትን ይፈጥራል፡፡ ብልህ የሆነ መንግሥት ሁሉ አጠቃላይ ሕዝቡን እንዲያውቁላቸው የሚፈልጉትን ለማሳወቅ ብዙ ወጪ ያወጣሉ፡፡ ብዙኃኑን አብሯቸው እንዲሆን ማድረግ የቻሉት በዚህ መንገድ ነው፡፡

መልካም ዜና ሁሉንም ሰው ያበረታታል፡፡ ብዙኃኑን መቆጣጠር የሚቻለው እንዲህ ነው፡፡ መጥፎ ዜና የተከታዮችን ልብ ያደክማል፡፡

### 4. ሰዎችን በንግግርህ አታቅልላቸው

ሰዎች መከበር ይፈልጋሉ፡፡ የድምፅህ ሁኔታ ራሱ ሰዎቹን እንደምታከብር ወይም እንደማታከብር ያሳያል! ፍቅርንና አክብሮትን ስትዘራ መደነቅንና ብዙ "ተከታይ" ልቦችን ታጭዳለህ፡፡

*ምዕራፍ 41*

# *ታሪክን በማጥናት የወጣትነትንና የልምድ ማጣትን ጉዳት ተቋቋም*

ለአንድ ወጣት መሪ ታሪክ ከምንም ይልቅ ጠቃሚ የሆነ ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ ወጣት ሰው ከልምድ የሚገኘው ጥቅም የለውም፡፡ ከሌሎች ተሞክሮዎች ወስዶ መጠቀም አለበት፡፡ አንዳንድ ስህተቶችን የማስወገጃ ብቸኛው እድል ከእርሱ የቀደሙትን ማጥናት ነው፡፡

> የነበረው ነገር እንደ ገና ይሆናል፤ የተደረገውም ተመልሶ ይደረጋል፤ ከፀሓይ በታች ምንም አዲስ ነገር የለም፡፡ማንም፣ እነሆ፤ ይህ አዲስ ነገር ነው" ሊል የሚችለው አንዳች ነገር አለን? ቀድሞውኑ በዚሁ የነበረ ነው፤ ከእኛ በፊት የሆነ ነው፡፡
>
> መክብብ 1፡9፣10

ሁሉም ጥሩ መሪ ከታሪክ ብዙ ይማራል፡፡ ታሪክም ራሱ የሚያስተምረን ብዙ ሰዎች ከእርሱ እንደሚማሩ ነው፡፡ ጥሩ መሪ መሆን የምትፈልግ ከሆነ፣ የቤተክርስቲያንንና የዓለምን ታሪክ ማጥናት አለብህ፡፡

## *ሁሉም መሪ ታሪክን ሊያጠና የሚገደድባቸው ሰባት ምክንያቶች*

1. **ከመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥሎ፤ታሪክ ከሁሉም የላቀ የእውቀትና የጥበብ ምንጭ ነው፡፡**

2. **የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እራሳቸው እኛን የሚመሩን ብዙ የታሪክ ትምህርቶችን አካትተዋል፡፡**

3. **እግዚአብሔር ሰዎች እንዳይረሱ ታሪክን እንዲያስተምሯቸው መሪዎቹን አዝዟል፡፡ መርሳት ተመሳሳይ ስህተትን ለመደጋገም ይዳርጋል፡፡**

> እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ፡፡ለልጆችህም አስተምረው፥ በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው፡፡ በኋለኛው ዘመንም ልጅህ፡፡ አምላካችን እግዚአብሔር ያዘዛችሁ ምስክርና ሥርዓት

**ፍርድስ ምንድር ነው? ብሎ በጠየቀህ ጊዜ፥አንተ ልጅህን በለው። በግብፅ የፈርዖን ባሪያዎች ነበርን እግዚአብሔርም በጽኑ እጅ ከግብፅ አወጣን እግዚአብሔርም ከግብፅና በፈርዖን በቤቱም ሁሉ ላይ እኛ እያየን ታላቅና ክፉ ምልክት ተአምራትም አደረገ።**

**ዘዳግም 6፡6-7፤20-22**

## 4. ታሪክ ራሱን ይደግማል

አንተ የምትራመደው እንዳንተ ያሉ ሌሎች በተራመዱበት ነው፡፡ እነርሱ ምን እንደሆኑ ካወቅህ አንተም ምን እንደምትሆን ታውቃለህ፡፡ እንዲህ የሚል አባባል አለ፡- "ታሪክን የማያውቁ እንዲደግሙት የተፈረደባቸው ናቸው፡፡"

## 5. ብዙ ነገሮች በዑደት የሚሰሩ ስለሆኑ

ዓለማችን አብሯት የተፈጠረ ዑደት አላት፡፡ ፕላኔቶች በፀሐይ ዙሪያ ይዞራሉ፡፡ ጨረቃ በመሬት ዙሪያ ትሽከረከራለች፡፡ የሰው ልጅ አካል በውስጡ ከቁጥር ያለፉ ባዮኬሚካላዊና ሆርሞናዊ ዑደቶች አሉት፡፡ የምግቦችን ወደ ካርቦንዳይኦክሳይድና ወደ ውኃ የሚለውጠው ዑደት (ክሬብስ ሳይክል) እና የወር አበባ የዚህ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ሕይወትህ ራሱን እያንቀሳቀሰ ያለ የክፉ ዑደት አንድ አካል ልትሆን ትችላለች፡፡ ታሪክን በማጥናት በሕይወትህና በአገልግሎትህ ላይ ያለን አስከፊ ዑደት መስበር ትችላለህ፡፡

## 6. የታሪክ ተማሪ የወደፊቱን መተንበይ ይችላል፡

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ባጠናህ ቁጥር ትንቢታዊ አይታዎችህ እጅጉን ይዳብራሉ፡፡

## 7. ደፋርነትና በራስ መተማመን ታሪክን የማጥናት ፍሬዎች ናቸው፡፡

ከታሪክ የተማርካቸው ትምህርቶች በመጠቀም መንገድህን በበለጠ በራስ መተማመን ልትገፋ ትችላለህ፡፡

አንድ ቀን ከመኖሪያ ቤቴ ፊት ለፊት ከአንድ ጠቢብ አዛውንት ጋር ቆመን እናወጋ ነበር፡፡ በምመራው ህብረት ውስጥ ያጋጠመኝን ቀውስ አጫውትኳቸው ፈገግ ብለው መቼም ቢሆን የማልረሳውን ነገር ተናገሩ፡፡ እንዲህ አሉ፡- "ሰይጣን ያሉት ጥቂት ማታለያዎች ናቸው፤ እነርሱንም ደጋግሞ ይጠቀምባቸዋል፡፡"

ቀጥለውም "አንድ ዓይነት ማታለያ እንዴት ሁልግዜ እንደሚሰራለት ይገርመኛል።"

ማብራራታቸውን ቀጠሉ፦ "ሰዎች ቀድሞ ምን እንደተከናወነ ስለማያውቁ በሚታወቁ የቆዩ ሽንገላዎች ደግመው ደጋግመው ይወድቃሉ።"

ውድ ወዳጄ ሆይ፣ ቀዳሚው ወንድምህ በወደቀበት ተንኮል አንተም መውደቅ ትወድዳለህን? ትላንት ስለሆነው ነገር ማንበብ አትፈልግምን? ውድ ፖለቲከኛ ሆይ ከአንተ የቀደመው ፖለቲከኛ ፍጻሜው እንዴት እንደነበር ማየት ትችላለህ። ከታሪክ ጥበብንና እውቀትን የምንቀስምበት ጊዜ አሁን ነው።

> የሆነው ነገር እርሱ የሚሆን ነው፥ የተደረገውም ነገር እርሱ የሚደረግ ነው ከፀሐይም በታች አዲስ ነገር የለም።
>
> መክብብ 1፥9

## ምዕራፍ 42

# ኃላፊነትን ተቀበል እና ተጠያቂ ሁን

መገንዘብ ያለብህ ነገር ቢኖር፣ ማንኛውም መሪ ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ተጠያቂ መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ለሰጠህ መንጋ ተጠያቂ ለመሆን ዝግጁ ነህን? ኢየሱስ ከሰጠው መንጋ መካከል ከጥፋት ልጅ በቀር አንዳችም እንዳላጠፋ በተደጋጋሚ ተናግሯል። ሐዋሪያው ጳውሎስም ተጠያቂነት እንዳለበት በተደጋጋሚ ገልጿል።

> **ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት፥ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ።**
>
> **ዕብራውያን 13፡17**

መሪነት ታላቅ ኃላፊነት ነው። አስታውሳለሁ፣ ከዓመታት በፊት በርካታ የአገር መሪዎችና ሚንስትሮች በተኲሽ ቡድን ሲረሸኑ ተመልክቻለሁ። ታላላቅ ሰዎች ሲዋረዱ እና ሲገደሉ ማየት ያሳዝናል። በቤቱ የተቀመጠው ተራ የሆነው የአገሪቱ ሕዝብ እንዲህ ያለው ነገር አልደረሰበትም። ለዚህም ምክንያቱ ተራው ሰው አገርን የመምራት ኃላፊነት ስላልወሰደ ነው። ይሁን እንጂ፣ ኃላፊነቱን የወሰዱ ሰዎች ሕይወታቸውን መክፈል ነበረባቸው።

ለአመራርህ ተጠያቂ እንደምትሆን የምታስተውል ከሆንህ የተሻልህ መሪ መሆን እንደምትችል ትደርስበታለህ። ተጠያቂ የምትሆንበት ቀን እየመጣ እንደሆነ ሁልጊዜ አስታውስ። ይህ ትክክለኛውን ነገር እንድታደርግ ያደርግሃል። እኔ ሁሌም ቢሆን በሕይወቴ ላይ ላለው የእግዚአብሔር ጥሪ ተጠያቂ እንደሆንሁ ልብ እላለሁ። በቤተ ክርስቲያናቴ ውስጥ ላለው መንጋ ተጠያቂ እንደምሆን አውቃለሁ። ለዚህም ነው መንጋውን ለመንከባከብ ከፍተኛ ጥረት የማደርገው።

መሪ ነህ? በየዕለቱ ተጠያቂ ስለምትሆንበት ቀን ታስባለህ? እባክህ አስብ! እንዲህ ስታደርግ ወደ ተፈጥሮአዊ እና ስኬታማ መሪነት ትለወጣለህ።

## ምዕራፍ 43

# የኃይል ምንጭህን አትተው!

እያንዳንዱ መሪ ኃይልን ከአንድ ነገር ያገኛል። ጌታ ኢየሱስ የኃይል ምንጩ ጸሎት እንደሆነ ያውቅ ነበር። ለዚያ ነበር በፍጹም መጸለዩን የማያቋርጠው። ለዚያ ነበር በጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ ከልቡ የጸለየው።

ሐዋሪያው ጴጥሮስ የኃይል ምንጩ ጸሎትና የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ያውቅ ነበር። ለዚያም ነው የኃይል ምንጩን ለመተው እንቢ ያለው!

> . . . የእግዚአብሔር ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም። እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን።
>
> የሐዋርያት ሥራ 6፡2፣4

ሁሉም መሪ የኃይል ምንጩን ማወቅ አለበት። ብዙ ፖለቲከኞች የኃይል ምንጫቸው የሕዝብ አስተያየት እንደሆነ ያውቃሉ። ለዚያ ነው የሕዝብ አስተያየት ላለማጣት ሁሉን ነገር የሚሰዉት። ብዙ ፖለቲከኞች የሕዝብ ድጋፍ ላለማጣት ሲሉ ቤተሰባቸውንና ጓደኞቻቸውን መሥዋዕት ሲያደርጉ አይቼአለሁ።

ከዓመታት በፊት፣ በፖለቲካው ዓለም ተሳትፎ ከሚያደርግ አንድ ወንድም ጋር ተነጋግረን ነበር። ይህ ሰው ከዚያ በፊት ቤተ ክርስቲያናችንን ይደግፍ ነበር። እስከ ተወሰነ ደረጃ ከረዳን በኋላ አንድ ቀን እንዲህ አለኝ፣ “ቢሾፕ፣ ይህ ጉዳይ ባለበት አካሄድ ከዚህ በላይ ልረዳህ አልችልም” አለኝ።

ይህ ወንድም ዳግመኛ የተወለደ፣ በልሳን የሚናገር እና በመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ የሚያምን ክርስቲያን ነው። እንዲያውም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ መሪ ነበር። በመቀጠልም እንዲህ አለ፣ “ይህ ጉዳይ ከፍ ወዳለ ደረጃ ከደረሰ ከዚህ በኋላ ቤተ ክርስቲያንን መርዳት የምችል አይመስለኝም።”

እንዲህም እያለ ማብራራቱን ሲቀጥል ተመለከትሁ፣ “ፖለቲካ ሕይወቴ እንደሆነ ታውቃለህ። ይህ ጉዳይ ከፖለቲካው አንጻር ከተቃረነኝ፣ ሥራዬን ላጣ እችላለሁ። ያ ደግሞ ለእኔ ከባድ ነው።”

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ፣ ጉዳዩ ተፋፋመ። ይህ ክርስቲያን ፖለቲከኛ ጭራሽ ፖለቲከኞቹን ወግኖ ቤተ ክርስቲያንን አጠቃ። ይህ አሳዛኝ ነበር፤ ግን አንድ የሚያሳየው ጥልቅ እውነታ አለ። ይህ ሰው የኃይል ምንጩ እግዚአብሔር ሳይሆን ፖለቲካ እንደሆነ ያስብ ነበር። ኃይል ይሰጠኛል ብሎ ላሰበው በታማኝነት ጸና።

ብዙ ፖለቲከኞች የሚያስቡት የኃይላቸው ምስጢር ህዝባዊ ድጋፍ እንደሆነ ነው። ይህም መርህሆቻቸውን፣ ህሊናቸውን ብሎም እምነተቻውን እንዲሰዉ ያደርጋቸዋል። አንድ ክርስቲያን መሪ ኃይሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ ማወቅ አለበት። ፖለቲከኞች እንኳን ቢሆኑ ጥንካሬያቸውን ከህዝቡ ዘንድ እንደሆነ ቢያስቡ ተሳስተዋል። በስተመጨረሻ የሰዎችን ጉዳይ የሚወስነው እግዚአብሔር ነውና።

ማንኛውም የወንጌል አገልጋይ የኃይል ምንጩ ገንዘብና ሕዝብ ሳይሆን እግዚአብሔር መሆኑን ማወቅ አለበት።

አንድ መሪ የኃይል ምንጩን ካላከበረ ያጣዋል። ሳምሶን የኃይል ምንጩ ላይ ቀለደ። ስለሆነም ሁሉንም ነገር አጥቷል።

> ስለዚህ ሁሉንም ነገር ነገራት፤ እንዲህም አለ፤ ከተወለድሁ ጀምሮ ናዝራዊ በመሆን ለእግዚአብሔር የተለየሁ ስለ ሆንሁራሴን ምላጭ ነክቶት አያውቅም፤ የራሴ ጠጕር ቢላጭ ግን ኃይሌ ተለይቶኝ እንደማንኛውም ሰው ደካማ እሆናለሁ አላት።
>
> መሳፍንት 16:17

መሪ ነህን? የኃይልህ ምንጭ ምን እንደሆነ እወቅ፣ አክብረው፣ ጠብቀው ለምንም ብለህ አሳልፈህ አትስጠው!

## ምዕራፍ 44

# ቆራጥ ሁን! ይህ የአንድ መሪ ትልቁ መገለጫ ነው

ቆራጥነት የአንድ መሪ ትልቅ መገለጫው ነው። ብዙ ሠዎች ውሳኔ መወሰን አይችሉም። እውነታን የሚጋፈጡ እና አስፈላጊ ውሳኔዎችን የሚወስኑ ትክክለኛ መሪዎች ብቻ ናቸው። መወሰን አለመቻል ማለት መምራት አለመቻል ማለት ነው። ብዙ ጊዜ በጥሩ አመራር ሥር ያሉ ድርጅቶች ግድ መሆኑን ሲያስተውሉ ሠራተኞችን የመቀነሰ ከባድ ውሳኔዎችን ይወስናሉ። ይህ ዓይነቱ ውሳኔ ለመወሰን ቀላል አይደለም፤ ዘላቂ የሆኑ ውጤቶችም ይኖሩታል። ውሳኔ ለመወሰን አለመቻል የምትገነባውን ሁሉ እንዲፈርስ ያደርጋል።

## ቆራጥ መሆን ያለብህ አራት ምክንያቶች፣

## 1. እግዚአብሔር አምላክ የውሳኔ አምላክ ነው።

ዘላቂነት ያላቸውን ውሳኔዎች በመወሰን የሚታወቀውን እግዚአብሔርን እንድንመስል ይጠበቅብናል።

> እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፥
>
> ኤፌሶን 5፡1

## 2. ታላላቅ መሪዎች ሁሉ ቆራጦች ናቸው።

በእምነትና በትዕግሥት ታላላቅ ስኬት ላይ የደረሱ ሰዎችን አርአያነት መከተል አለብን።

> በእምነትና በትዕግሥት የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ፣ ዳተኞች እንድትሆኑ አልፈለግም።
>
> ዕብራውያን 6፡12

## 3. ውሳኔ መስጠት አለመቻል ማለት መምራት አለመቻል ነው።

መሪነት ሰማንያ ከመቶው ውሳኔ በመስጠት የተቀረው ሃያ ከመቶው ደግሞ መተግበር ነው። ለዚህም ነው ውሳኔ መስጠት አለመቻል መምራት አለመቻል የሚባለው።

## 4. መወሰን አለመቻል ማለት ምንም ላለማድረግ መወሰን ነው።

ምንም ላለማድረግ የወሰነን ሰው እንዴት ልትከተል ትችላለህ? አንድ ትንሽ ልጅንም በመጫወቻ ስፍራ ላይ ልትከተል ትችላለህ። ይህ ምንም ካለማድረግ ጋር አንድ ነው።

# አስር የእግዚአብሔር ውሳኔዎች

## 1. ምድር ቅርፅ አልባ፣ ባዶና በጨለማ የተሸፈነች ሳለች እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ለመፍጠር ወሰነ።

ምድርም ቅርጽ የለሽና ባዶ ነበረች። የምድርን ጥልቅ ስፍራ ሁሉ ጨለማ ውጦት ነበር። የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሆች ላይ ይሰፍ ነበር።

ዘፍጥረት 1፡2

## 2. ሰው ብቸኛ እንደሆነ ባስተዋለ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ሴትን ለመፍጠር ወሰነ።

እግዚአብሔር አምላክ በምሥራቅ፣ በዔድን የአትክልት ስፍራ አዘጋጀ፤ ያበጀውንም ሰው በዚያ አኖረው።

ዘፍጥረት 2፡18

## 3. ምድር በክፋት ስትሞላ እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቡን ብቻ አስቀርቶ የሰውን ልጆች በሙሉ ለማጥፋት ወሰነ።

እግዚአብሔር አምላክ የሰው ዐመፅ በምድር ላይ የበዛና የልቡም ሐሳብ ዘወትር ወደ ክፋት ብቻ ያዘነበለ መሆኑን ተመለከተ። እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፤ ልቡም እጅግ አዘነ። ስለዚህም እግዚአብሔር ፣ የፈጠርሁትን የሰው ዘር ከምድረ ገጽ አጠፋለሁ፤ ከሰው እስከ እንስሳ በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጡራን እስከ ሰማይ ወፎች አጠፋለሁ፤

ዘፍጥረት 6፡5-7

## 4. እግዚአብሔር የኖኅን መሥዋዕት ባየ ጊዜ ሕይወት ያለውን ሁሉ ፈፅሞ ላለማጥፋት ወሰነ።

እግዚአብሔርም ደስ የሚያሰኘውን መዐዛ አሸተተ፤ በልቡም እንዲህ አለ፤ ምንም እንኳን ሰው ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ሐሳቡ ወደ ክፋት ያዘነበለ ቢሆንም፣ በእርሱ ምክንያት ሁለተኛ ምድርን አልረግማትም፤አሁን እንዳደረግሁት ሕያዋን ፍጡራንን ዳግመኛ አላጠፋም።

ዘፍጥረት 8፡21

## 5. እግዚአብሔር ግብረ ሰዶማዊነትን በሰዶምና ገሞራ ባየ ጊዜ ያቺን ከተማ እስከመጨረሻው ለመደምሰስ ወሰነ።

ደግሞም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ በሰዶምና በገሞራ ላይ የሚሰማው ጩኸት እጅግ በዝቶአል፤ ኀጢአታቸውም እጅግ ከፍቶአል፤ አድራጎታቸው እኔ ዘንድ እንደደረሰው ጩኸት መሆኑን ለማየት ወደዚያው እወርዳለሁ፤

ዘፍጥረት 18፡ 20-21

## 6. እስራኤላውያን በግብፅ እጅግ እየተሰቃዩ እንደሆነ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ከፈርዖን እጅ ሊያድናቸው ወሰነ።

ከዚያም ከብዙ ቀን በኋላ እንዲህ ሆነ የግብፅ ንጉሥ ሞተ የእስራኤልም ልጆች ከባርነት የተነሣ አለቀሱ፥ ጮኹም፥ ስለ ባርነታቸውም ጩኸታቸው ወደ እግዚአብሔር ወጣ። እግዚአብሔርም የለቅሶአቸውን ድምፅ ሰማ፥ እግዚአብሔርም ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን አሰበ። እግዚአብሔርም የእስራኤልን ልጆች አየ፥ እግዚአብሔርም በእነርሱ ያለውን ነገር አወቀ።

ዘጸአት 2፡23-25

## 7. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ አውጥቶ ወደ ከነዓን እየመራቸው ሳለ ማጉረምረም ሲጀምሩ በምድረበዳ ለተጨማሪ አርባ ዓመታት ሊያቆያቸው ወሰነ።

አባቶቻችሁ በዚያ ተፈታተኑኝ፡፡ መረመሩኝ፣ ያደረግሁትንም ሁሉ ለአርባ ዓመት አዩ፡፡በዛም ትውልድ ላይ የተቆጣሁት ለዚህ ነበር፡፡ እንዲህም አልሁ "ልባችሁ ሁልጊዜ ይስታል፡፡ መንገዴንም አላውቅም፡፡ ስለዚህ በቁጣዬ እንዲህ ብዬ ማልሁ "ወደ እረፍቴ ከቶ አይገቡም"፡

ዕብራውያን 3፡9-11

## 8. ሉሲፈር አመፀኛ መሆኑን እግዚአብሔር ሲመለከት፣ ከመንግሥተ ሰማይ ሊያስወጣው ወሰነ።

በውበትህ ምክንያት ልብህ ኰርቶአል ከክብርህ የተነሣ ጥበብህን አረከስህ በምድር ላይ ጣልሁህ ያዩህም ዘንድ በነገሥታት ፊት ሰጠሁህ። በበደልህ ብዛት በንግድህም

ኃጢአት መቅደስህን አረከስህ ስለዚህ እሳትን ከውስጥህ አውጥቻለሁ እርስዋም በልታሃለች፥ በሚያዩህም ሁሉ ፊት በምድር ላይ አመድ አድርጌሃለሁ።

ሕዝቅኤል 28፡17-18

## 9. እስራኤላውያን በነብይ መገዛት እንዳልፈለጉ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር የአመራር ዘይቤውን ከመሣፍንት ወደ ነገሥታት ለመለወጥ ወሰነ፡፡

እግዚአብሔርም ሳሙኤልን እንዲህ አለው፤ ንጉሳቸው እንዳልሆን የናቁት እኔን እንጂ አንተን አይደለምና ሕዝቡ የሚሉህን ሁሉአድምጥ፡፡

1ኛ ሳሙኤል 8፡7

## 10. እግዚአብሔር ፍጥረቱ ሁሉ በኃጢአት ሊጠፉ መሆኑን ሲያይ መልሶ እንዲያመጣቸው ልጁን ለመላክ ወሰነ፡፡

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስከመስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዷልና፡፡ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው፡፡

ዮሐንስ 3፡16-17

ብዙ መጋቢዎች በእነርሱ ደረጃ ያሉ እምነት የማይጣልባቸውን ጉዳዮችን ከማስወገድ ወደ ኋላ ይላሉ፡፡ አጭበርባሪዎችን የማስወገድን ከባድ ውሳኔ መወሰን ካቃተህ ትጠፋለህ፡፡ መሪ ነህ? ወይ መሪ ለመሆን ህልም አለህ? እንግዲያውስ ከባድ ውሳኔዎችን ወደ መወሰን ዓለም እንኳን ደህና መጣህ፡፡

# ውሳኔ ለማድረግ የሚጠቅሙ ስድስት ቁልፎች

## 1. ደፋር ሁን

ደህና ውሳኔ ለማስተላለፍ ድፍረት ይጠይቃል፡፡ ንጉስ ዳዊት ልጁን ሰለሞንን ጠንካራ ሰው እንዲሆን መክሮታል፡፡ ወሳኝ ለመሆን ሰለሞን ጥንካሬ እንደሚያስፈልገው አውቆ ነበር፡፡ ሰለሞን ከምንም በላይ የሚያስፈልገው ባሕሪ ቆራጥነት እንደሆነ ዳዊት አውቆ ነበር፡፡

እነሆ፤ እኔ የምድሩን ሁሉ መንገድ ልሄድ ነው፤ እንግዲህ በርታ፤ ሰውም ሁን፡፡

1ኛ ነገሥት 2፡2

እኔ ራሴ መሪ ስለሆንሁ የዚህ ምክር ጥቅም ምን እንደሆነ ጠንቅቄ አውቃለሁ፡፡ ብርቱ ካልሆንክ የውሳኔ ሰው መሆን አትችልም፡፡ አንድ

ቤተክርስቲያን ወደፊት የሚያስኬዳት ጠንካራ መሪ ያስፈልጋታል። ዲሞክራሲና ኮሚቴ ጠቃሚ አይደሉም፣ የሚያስፈልግህ ጠንካራ አመራር ነው።

ሰለሞን ቀደም ሲል ንግሥናውን ለመንጠቅ ሞክሮ የነበረውን ወንድሙን አዶኒያስን እስከማጥፋት ደርሷል። ሰለሞን ያከናወነው የመጀመሪያው የድፍረት ድርጊት አስጊ የሆኑ ከሀዲዎችንና በንግሥናው ውስጥ ያሉ ክፉ ነገሮችን ማጥፋት ነበር።

አንዳንዶቻችሁ በሕይወታችሁ ያለን አንድ መጥፎ ሰውን እንኳን ለማስወገድ ሰንፋችሁ ይሆናል። ለዚያም ነው መቼም ቢሆን ስኬታማ መሪ የማትሆነው። ወሳኝነት የመሪ ትልቁ መገለጫ ነው። የጌታን ድምፅ ለመታዘዝ ጥንካሬ ያስፈልግሀል።

እግዚአብሔር መጋቢ እንድሆን ሲነግረኝ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መቀጠል ብዙ ጥንካሬን ጠይቆብኝ ነበር። ማንም አልደገፈኝም አልረዳኝም ነበር። ማገልገል በጀመርኩ ጊዜ ራሴን ያገኘሁት በእኔ ላይ አመኔታ በሌላቸው ሰዎች መካከል ነበር። ፌዘኞችን ከሕይወቴ ማስወገድ ነበረብኝ፣ ይህንንም አደረግሁት! አንድን ሰው "ከዛሬ ጀምሮ የዚህ ቤተ ክርስቲያን አካል አይደለህም።" እንዳልኩት አስታውሳለሁ።

ቀጥዬም "ዳግመኛ ወደዚህ ቤተ ክርስቲያን አትምጣ አገልግሎትህ አያስፈልገኝም" አልኩት።

ይህ ወንድም ተደነቀ፤ ሆኖም ይህ ለመሰንበቴ እጅግ አስፈላጊ እርምጃ ነበር። ማንም ሰው በዙሪያው ያሉት ሰዎች ታማኝ ያልሆኑና ተቺ ከሆኑ መስፋፋት አይችልም። አበረታችና ሠላማዊ ቦታ ያስፈልግሃል።

## 2. አሻግረህ ተመልከት

አሁን የምትወስናቸው ውሳኔዎች ለበጐ እንደሚሆኑ እወቅ። ሰለሞን ወንድሙን አዶኒይስን ማሰወገዱ ለሀገሪቷ መልካም እንደሚሆን አውቆ ነበር። ሰለሞን አሻግሮ ባያይ ኖሮ ያንን ውሳኔን አይወስንም ነበር። አንድ ሰነፍ ሥራ አስኪያጅ ለምሳሌ፣ ሠራተኞችን የመቀነስን ከባድ ውሳኔ ባይወስን ድረጅቱ እንደሚፈርስ አይታየውም።

## 3. አለመወሰን የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ከግምት አስገባ

አብርሃም ለሎጥ የቅርብ ዘመዱ ነበር። አንድ ቀን፣ የሎጥ በሕይወቱ ውስጥ መኖር ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የማመዘኑ እውነታ መጋፈጥ ነበረበት። ጥሩ መሪ በመሆኑም ውሳኔን ወስኖ ከሎጥ ተለየ።

ይህንን ውሳኔ ያለመወሰን ውጤት ጥል ሊሆን ይችል ነበር። ጥልም ተገቢ አይሆንም ነበር።

> አብራምም ሎጥን እንዲህ አለው፤ እኛ ወንድማማቾች ነንና በአንተና በእኔ ወይም በእረኞቻችን መካከል ጠብ ሊኖር አይገባም፡፡ይኸው እንደምታየው አገሩ ሰፊ ነው፤ ብንለያይ ይሻላል፡፡ አንተ ግራውን ብትመርጥ፣ እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ፤ አንተ ቀኙን ብትመርጥ፣ እኔ ወደ ግራ እመራለሁ፡፡
>
> ዘፍጥረት 13፡8-9

ልብ በል፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም የእርሱ ስለነበሩት ምድሮችና በረከቶች ምንነት ያስረዳው ከዚህ ውሳኔ በኋላ ነው።

> ሎጥ ከተለየው በኋላም እግዚአብሔር አብራምን አለው። ዓይንህን አንሣና አንተ ካለህበት ስፍራ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ እይ
>
> ዘፍጥረት 13፡14

## 4. ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች በሙሉ ከቀረቡልህ በኋላ ለውሳኔ ፍጠን፣

ባልተሟሉ ቁንጽል መረጃዎች ላይ በመመስረት ውሳኔዎች አትወስን። እንደዚህ ካደረግክ አስከፊ ጥፋት ልታደርስ ትችላለህ። ሰለሞን ኢዮአብምን እንዲያስገወግድ በአባቱ ተመክሮ ነበር። ሰለሞን ያስፈለገው ብቸኛ መረጃ የአባቱ መመሪያ ነበር። ኢዮአብ ዳዊትን በተደጋጋሚ ያልታዘዘ ሰው ነበር። ዳዊት ሰለሞን ኢዮአብምን እንዲያጠፋው ጠየቀው።

> መደረግ ያለበትን በጥበብህ አድርግ፤ ከነሽበቱ በሰላም ወደ መቃብርሐ እንዲወርድ አታድርግ፡፡
>
> 1ኛ ነገሥት 2፡6

አጋጣሚው ሲመቻች ሰለሞን ኢዮአብን ገደለው። መረጃው ሲደርሰው ሰለሞን በአስቸኳይ ኢዮአብን ለመግደል ወሰነ። ዳዊት ሰለሞንን በሳሚም ላይ የሚገባውን እንዲያደርግ ጠይቆት ነበር። ሣሚ ንጉስ ዳዊትን ከአቤሴሎም እየሸሸ እያለ የረገመው ሰው ነበር።

> እኔም ወደ መሃናይም በሄድሁ ጊዜ ብርቱ እርግማን የረገመኝ የብራቂም አገር ሰው የብንያማዊው የጌራ ልጅ ሳሚ ... ያለ ቅጣት አትተወው...
>
> 1ኛ ነገሥት 2፡8፣9

ሰለሞን የአባቱን ትእዛዞች ከፈፀመ በኋላ የእስራኤል መንግሥት በእርሱ አገዛዝ ስር እንደተመሠረተች ታስተውላለህ።

. . . መንግሥትም በሰሎሞን እጅ ጸና።

1ኛ ነገሥት 2፡46

ሰለሞን ቆራጥ በመሆኑ መንግሥቱ ተመሠረተች፡፡ መረጃን እንዳገኘ ውሳኔ ወሰነ ደግሞም ተገበረው፡፡6

## 5. የተወሰኑ ውሳኔዎችን ተፈፃሚ አድርግ

ሰለሞን ሳሚን የቄዳርን ወንዝ እንዳያቋርጥ ጠይቆት ነበር፡፡ ወንዙን ቢያቋርጥ ያ ቀን በምድር ላይ የመጨረሻ ቀኑ እንደሚሆን ለሳሚ ነግሮት ነበር፡፡ ሳሚ ድንበሩን እንዳቋረጠ ሰለሞን በሰማ ጊዜ፣ ሰለሞን አስቀድሞ የወሰነውን ከባድ ውሳኔ አደረገው፡፡ የሰለሞን ቆራጥነት ተግባራዊ ነበር፡፡

## 6. ራስህን እግዚአብሔርን በሚፈሩና መልካም ምክር በሚመክሩ ሰዎች መሃል አኑር

ኢዮርብዓም የሰራውን ስህተት አትስራ፡፡

እስራኤላውያን ሁሉ ሊያነግሡት ወደ ሴኬም ስለ ሄዱ፣ ሮብዓም ወደዚያው ሄደ፡፡2 የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ይህን በሰማ ጊዜ፣ ከንጉሥ ሰሎሞን ሸሽቶ ከሚኖርበት ከግብፅ ተመልሶ መጣ፡፡ 3 ስለዚህም ወደ ኢዮርብዓም ላኩበት፤ እርሱና መላው የእስራኤል ጉባኤም ወደ ሮብዓም መጥተው፣ 4 አባትህ ከባድ ቀንበር ጫነብን፤ አንተ ግን አሁን የአባትህን የጭካኔ አገዛዝ የጫነብንንም ከባድ ቀንበር ብታቀልልን እንገዛልሃለን አሉት፡፡ 5 ሮብዓምም፣ እንግዲያውስ ሂዱ፤ ከሦስት ቀን በኋላ ተመልሳችሁ ወደ እኔ ኑ አላቸው፡፡ ስለዚህ ሕዝቡ ሄዱ፡፡ ከዚያም ሮብዓም አባቱ ሰሎሞን በሕይወቱ ሳለ ..ገለገሉት ሽማግሌዎች ጋር ተማከረ፤ ስለዚህ ሕዝብ ምን መልስ እንድሰጥ ትመከሩኛላችሁ? አላቸው፡፡እነርሱም፣ ዛሬ አንተ ለዚህ ሕዝብ አገልጋይ ብትሆን፣ ብትገዛለትና ደስ የሚያሰኝ መልስ ብትሰጠው፣ ምን ጊዜም የአንተ አገልጋይ ይሆናል ብለው መለሱለት፡፡ ሮብዓም ግን ሽማግሌዎቹ የሰጡትን ምክር ንቆ፣ አብሮ አደግ የሆኑትንና እርሱን የሚያገለግሉትን ወጣቶች፣ 9 ሐሳብ ለማግኘት፣ የእናንተስ ምክር ምንድን ነው? አባትህ የጫነብንን ቀንበር አቅልልን ለሚሉኝ ለእነዚህ ሰዎች ምን መልስ እንስጥ? ሲል ጠየቃቸው፡፡ ወጣት አብሮ አደጎቹም፣ እንዲህ አሉት፣ አባትህ ከባድ ቀንበር ጫነብን፣ አንተ ግን ቀንበራችንን አቅልልን ላሉህ ለእነዚህ ሰዎች፣ የትንሿ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ይልቅ ትወፍራለች፤ 11አባቴ ከባድ ቀንበር ጫነባችሁ፤ እኔ ግን ከዚያ ይብስ አከብደዋለሁ፤ አባቴ በዐለንጋ ገረፋችሁ፤ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ በላቸ..ቃ አሉ፡፡ንጉሡ፣ በሦስተኛው ቀን ተመልሳችሁ ኑ ብሎአቸው ስለ ነበር፣ ኢዮርብዓምና ሕዝቡ ሁሉ በሦስተኛው ቀን ወደ ሮብዓም ተመልሰው መጡ፡፡ 13 ንጉሡም በሽማግሌዎቹ የተሰጠውን ምክር ትቶ፣ ሕዝቡን የሚያስከፋ መልስ ሰጣቸው፤ 14 ወጣቶቹ የሰጡትን ምክርም ተቀብሎ፣ አባቴ ቀንበራችሁን አከበደባችሁ፤ እኔ ደግሞ ከዚያ ይብስ አከብደዋለሁ፤ አባቴ በአለንጋ ገረፋችሁ፣ እኔ ደግሞ በጊንጥ እገርፋችኋለሁ አላቸው፡፡ 15እግዚአብሔር በሴሎናዊው

በአኪያ አማ..ይነት ስለ ናባጥ ልጅ ስለኢዮርብዓም የተናገረው ቀድሞውኑ እግዚአብሔር የወሰነው ስለ ሆነ፣ መፈጸም ነበረበትና ንጉሡ ሕዝቡን አልሰማም፡፡ እስራኤልም ሁሉ ንጉሡ ሊሰማቸው አለመፈለጉን በተረዱ ጊዜ፣ ለንጉሡ እንዲህ በማለት መለሱ፤ ከዳዊት ምን ድርሻ አለን? ከእሴይስ ልጅ ምን የምናገኘው አለ?እስራኤል ሆይ፤ ወደ የድን..ንህ ተመለስ፤ ዳዊት ሆይ፤ እንግዲህ የገዛቤትህን ጠብ ስለዚህም እስራኤላውያን ወደ ድንኳኖቻቸው ተመለሱ፡፡

1ኛ ነገሥት 12፡1-16

## ሁለት የተለመዱ የመሪዎች ስህተት

1. ግልጽ በሆነ ነገር ላይ አለመወሰን፡፡
2. የተወሰነን ውሳኔ ተፈፃሚ አለማድረግ፡፡

*ምዕራፍ 45*

# ስለ ልምዶች ኃይል በማወቅ ጥሩ ልማዶችን አዳብር

ልማድ ሳታስብ ወይም ሳታቅድ የምታደርገው ነገር ነው። እያንዳንዱ መልካም መሪ በርካታ መልካም ልማዶች አሉት። የሆነውን እንዲሆን ያስቻሉት እነዚህ መልካም ልማዶች ናቸው።

## የኢየሱስ ሁለት ልማዶች

### 1. ዘወትር ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ

ኢየሱስ መልካም ልማዶች እንደነበሩት ታውቃለህ? በሰንበት ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን የመሄድ ልማድ እንደነበረው መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል።

> ወዳደገበትም ወደ ናዝሬት መጣ፤ እንደ ልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኵራብ ገባ፥ ሊያነብም ተነሣ።
>
> ሉቃስ 4፡16

### 2. ከመኖሪያ አካባቢ ራቅ ብሎ በመሄድ መጸለይ

ኢየሱስ ራቅ ብሎ ወደ አንድ የአትክልት ስፍራ የመሄድ ልማድም ነበረው። ወደዚህ ስፍራ ዘወትር ይሄድ ነበር። ሁሉም ሰው በአትክልት ሥፍራው የመጸለይ ልማዱን ያውቅ ነበር።

> ኢየሱስም ይህን ብሎ አትክልት ወዳለበት ስፍራ ወደ ቄድሮን ወንዝ ማዶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወጣ፤ እርሱም ደቀ መዛሙርቱም በዚያ ገቡ። ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱም ብዙ ጊዜ ወደዚያ ስለ ተሰበሰቡ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ደግሞ ስፍራውን ያውቅ ነበር።
>
> ዮሐንስ 18፡1-2

## የዳንኤል ልማድ

ዳንኤል በቀኑ በተወሰኑ የተለያዩ ሰዓታት ላይ ይጸልይ ነበር። ይህ የእርሱ ልማድ ነበር። ይህ ከሕይወቱ ታላላቅ ምስጢራት አንዱ ነበር። ዳንኤልም ጽሕፈቱ እንደ ተጻፈ ባወቀ ጊዜ ወደ ቤቱ ገባ፤ የእልፍኙን መስኮቶች ወደ ኢየሩሳሌም አንጻር

ተከፍተው ነበር፤ ቀድሞም ያደርግ እንደ ነበረ በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጕልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ጸለየ አመሰገነም።

ዳንኤል. 6፡10

# ስለ ልማዶች ኃይል እያንዳንዱ መሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ አስር ነገሮች

1. ልማድ ሳይታሰብ ወይም ሳይታቀድ በቀላሉ የሚደገም ድርጊት ነው፡፡
2. ልማድ ብታስተውለውም ባታስተውለውም ባህልህ የሚሆን ድርጊት ነው፡፡
3. ልማድ ብዙውን ጊዜ መጨረሻው ጊዜ ላይ ተፅዕኖ የማድረግ ኃይል የሌለው የሚመስል ተራ ድርጊት ነው፡፡

ብዙ ሰዎች መልካም ልማዶች ማዳበርን ለወደፊት ስኬቶች እንደ ሀይለኛ መሣሪያ የማይቆጥሩት በዚህ ምክንያት ነው፡፡

4. ልማድ ጥሩ ወይም መጥፎ፣ ተፈጥሯዊ ወይም መንፈሳዊ ሊሆን ይችላል፡፡

የማለዳ ጸሎትና ዕለታዊ የጽሞና ጊዜን የመሳሰሉ ነገሮች መንፈሳዊ ልማዶች ሲሆኑ፣ ጥርስህን መቦረሽና በየእለቱ ገላህን መታጠብ ተፈጥሯዊ ልማዶች ናቸው፡፡

5. መልካም ልማዶች ልክ እንደ መጥፎዎቹ ልማዶች በቀላሉ ይደገማሉ፡፡
6. መጥፎ ልማዶች ግለሰቡ ምን እየሆነ እንዳለ ሳይረዳ ወደ ተደጋጋሚ ውድቀትና ሽንፈት ይመራሉ፡፡
7. ጥሩ ልማዶች ግለሰቡ ምን እያደረገ እንዳለ እንኳን ሳይረዳ ወደ ተደጋጋሚ ስኬትና ድል ይመራሉ፡፡
8. መጥፎ ልማዶች ለማዳበር ቀላል፣ አብሯቸው ለመኖር ግን ከባድ ናቸው፡፡ ጥሩ ልማዶች ለማዳበር ከባድ አብሯቸው ለመኖር ግን ቀላል ናቸው፡፡

9. እያንዳንዱ ስኬታማ መሪ ለስኬት ያበቁት ብዙ ጥሩ ልማዶች አሉት።

ከብዙ ዓመታት በፊት አንድ ጓደኛዬ እንዴት በየማለዳው ከእግዚአብሔር ጋር የጽሞና ጊዜ እንደማሳልፍ አስተማረኝ። ይህንን እንደ ግል ልማድ አዳበርኩትና እንደ ክርስቲያንና በኋላም እንደ አገልጋይ የስኬቴ ምስጢር ሆነ። የምሰብካቸው ነገሮች በሙሉ ማለት ይቻላል የሚመጡት ከዚሁ መልካም ልማድ ነው።

10. ልማዶች ለመሪዎች ራሳቸውን የሚከላከሉባቸው መንገዶች ናቸው።

ለዚህ ምክንያቱ አንድ መሪ ጫና ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ እንኳ በልማድ፣ በተፈጥሯዊ መንገድና በቀላሉ አንዳንድ በጎ ተግባራትን ስለሚያደርግ ነው። አንድ መሪ በጫና ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ ምንና እንዴት ማድረግ እንዳለበት ለማሰብ ጊዜ ላይኖረው ይችላል። ከችግር ሊያወጣው የሚችለው መልካም የጸሎት ወይም የጽሞና ጊዜ ልማድ ነው። ልክ እንደ ኢየሱስ እኔም ለመፀለይ አዘውትሬ የምሄድበት ሥፍራ አለ። ብዙ ጊዜ ከመጋቢዎቼም ጋር እሄዳለሁ። ይህ ልማድ አደጋን በማላስተውልበት ጊዜ እንኳን ሳይቀር በመንፈስ የተጠበቅሁ እንድሆን ይረዳኛል።

## እያንዳንዱ መሪ ሊያዳብራቸው የሚገባ ሃያ ጥሩ ልማዶች

1. በሕይወትህ በእያንዳንዱ ቀን መጽሐፍ ቅዱስህን አንብብ።

በችግር ጊዜ ሊያድንህ የሚችለው ያ የመፅሐፍ ቅዱስ ንባብ ነው።

2. በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር የግል የጽሞና ጊዜ ይኑርህ። መጽሐፍ ቅዱስ ሳላነብ ቁርሴን አልበላም የሚል መርህ ተከተል። NBNB (No Bible, No Breakfast)

3. በሕይወትህ በእያንዳንዱ ቀን ቢያንስ ለአንድ ሰዓት ያህል ጸልይ።

ከመመገብህ በፊት የመጸለይ ልማድ አዳብር።

4. በሳምንት ቢያንስ አንድ ጊዜ ጹም።

ለምሳሌ አርብ ቀንን የጾም ቀን አድርገህ ልትመርጥ ትችላለህ።

5. በመኪናህ ወይም በቤትህ የስብከት ካሴቶችን ያለማቋረጥ አድምጥ።

6. ሁልጊዜም የምታነበው መጽሐፍ ይኑርህ።

አንድ መጽሐፍ አንብበህ ስትጨርስ ወዲያውኑ ሌላ ጀምር። ይህ ሳታውቀው እውቀትህንና የመማር ችሎታህን የሚያሳድግ በጣም ጥሩ ልማድ ነው።

7. በቤትህ ወይም በመኪናህ ክርስቲያናዊ መዝሙሮችን ብቻ አጫውት።

አንተ ባለህበት ስፍራ አለማዊ ሙዚቃ እንዲያጫወት አትፍቀድ። ከሬድዮ የሚመጣ ቢሆን እንኳ። ይህ ልማድ ሁል ጊዜ ለመንፈስ ቅዱስ የሚመች አካባቢ በዙሪያህ ይፈጥራል። እግዚአብሔር በምጋናና በአምልኮ ውስጥ ስለሚያድር መንፈስ ቅዱስ ወደ አንተ ይመጣል። በዚያውም ሳታውቀው ክፉ መናፍስትን ታባርራለህ። “እንዲህም ሆነ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መንፈስ በሳኦል ላይ በሆነ ጊዜ ዳዊት በገና ይዞ በእጁ ይመታ ነበር፤ ሳኦልንም ደስ ያሰኘው ያሳርፈውም ነበር፥ ክፉ መንፈስም ከእርሱ ይርቅ ነበር።” (1ኛ ሳሙኤል 16:23)

8. ዓመቱን ለእግዚአብሔር እጅ አሳልፈህ ለመስጠት በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ረዘም ያለ ጾም አድርግ።

9. በሳምንት ቢያንስ አንድ ጊዜ ረዥም የጸሎት ጊዜ ይኑርህ።

10. የቅርብ ጓደኞችህ ከአንተ ጋር ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ይሁኑ።

11. በየቀኑ ከባለቤትህ ጋር ተጫወት።

ስለ “ምንም” ቢሆን እንኳ፣ የሴት ልጅ ትልቁ ፍላጎት የሚያዋራት ሰው ማግኘት እንደሆነ ተረድቻለሁ። ሴቶች የማውራት ስጦታ አብሯቸው ነው የተወለደው። ከስጦታቸው አንዱ ማውጋት ነው። ለሩብ ሰዓት ያህል መጨዋወት ለማንኛዋም ሴት ሊገለፅ የማይችል ደስታ ይሰጣታል።

12. ከልጆችህ ጋር ተጫወት፣ አውራ።

ለልጆችህ የምታወጣላቸውን ገንዘብ በግማሽ ብትቀንስና የምትሰጣቸውን ጊዜ በእጥፍ ብታሳድግ የተሻሉ ልጆች ይሆናሉ።

## 13. ከባለቤትህ ጋር በየጊዜው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽም።

ይህንን በየሁለት ቀኑ ወይም አቅምህ በፈቀደ መጠን ልታደርግ ትችላለህ።

## 14. በሳምንት አንድ ቀን እረፍት አድርግ።

እኔ የማርፈው ሰኞ ቀን ነው። ይህ ቀን ለኔ አስፈላጊ መሆኑን ተረድቻለሁ። ሥራ ማለቂያ እንደሌለው ገብቶኛል።

## 15. ለምታገኛቸው የማያምኑ ሰዎች ሁሉ መስክር።

ጸለይክም አልጸለይክም ይህንን አድርግ። የማያምን ሰው የወንጌልን ቃል ሳይሰማ ከአጠገብህ እንዲሄድ አትፍቀድለት። ይህ ልማድ ጅማ ስብከተ ወንጌል ማድረግ ሳያስፈልግህ ብዙ ሰዎች በክርስቶስ አምነው እንዲድኑ ያደርጋል።

## 16. ገንዘብ ከሰው አትበደር።

አንዳንድ ሰዎች በችገራቸው ቁጥር ገንዘብ የመበደር ልማድ አላቸው። ገንዘብ ያለመበደር ልማድ ማዳበሩ ጠቃሚ ነው።

## 17. በየጥቂት ወራት እግዚአብሔርን ለመጠበቅ የሚያስችል ጊዜ መድብ።

እኔ ይህንን በማደርግበት ጊዜ ለጥቂት ቀናት ከቤት ርቄ በመሄድ ከጌታ ጋር አሳልፋለሁ። ከህይወቴ ታላላቅ ምስጢራት አንዱ ይህ ነው።

## 18. ገንዘብ ቆጥብ።

በየወሩ ጥቂት ገንዘብ ቆጥብ።

## 19. ብዙ ሰዓት ቴሌቪዥን ያለመመልከት ልማድ አዳብር።

ቴሌቪዥን በማንበብ፣ በመጸለይ፣ የጽሞና ጊዜ በማድረግ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋር፣ ከልጆችህ ወይም ከባለቤትህ ጋር በመጫወት ልታሳልፍ የሚገባህን ጊዜ ይወስድብሃል። በተጨማሪም፣ ቴሌቪዥን መጥፎ ነገሮችን ያስለምድሃል። የፍቺ ሐሳብና ሌሎች ክፉ ሀሳቦችን የሚያገኙት ከቴሌቪዥን ነው።

## 20. በየወሩ አሥራትህን ክፈል።

ከገቢህ የመጀመሪያውን አሥር በመቶ ለጌታ ስጥ።

መሪ ነኝ ብለህ ታስባለህ? ምን ዓይነት መልካም ባህርያት አሉህ? በብዙ መልካም ባህርያት የተሞላ ህይወት ለማኅልበት ጣር። ስኬታም መሪዎች ሁሉ በስኬት ለመምራት ያስቻሏቸው ሚስጢራዊ መልካም ልማዶች እንዳሏቸው አትዘንጋ።

## ምዕራፍ 46

# የደረስክበትን እወቅ! ያልደረስክበትንም እወቅ! ከዚያም ወዴት እንደምትሄድ ታውቃለህ!

እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።

ዮሐንስ 8፡32

እውነት የደረስክበትንና ያልደረስክበትን ይነግርሃል! እንዲሁም እውነት ወዴት መሄድ እንዳለብህ ይነግርሃል። ብዙ መጋቢዎች ስለ ምእመኖቻቸው ቁጥር እውነቱን መናገር መጀመር አለባቸው። በየቤተ ክርስቲያኖቻችን ከልክ ያለፈ ግምታዊ አሃዝ መናገራችንን ማቆም አለብን። የምታገለግላቸውን ሰዎች ትክክለኛ ቁጥር በምታውቅበት ጊዜ በትጋት ለመሥራት ትነቃቃለህ።

አንድ ቀን የመረጃ ሠራተኞችን የቤተ ክርስቲያናችን ሰዎች ቁጥር ስንት እንደሆነ ጠየኩት። ቁጥሩን ሲነግረኝ ለአንድ ሳምንት ያህል በጭንቀት ታመስኩ። ቤተ ክርስቲያናች በቁጥር ትንሽ እንደሆነች ተረዳሁ። ብዙ ርቀት መሄድ ይቀረኛል!

ለራስህ እውነቱን መናገር የማትችል ከሆነ ጥሩ መሪ ልትሆን አትችልም።

ብዙ ድርጅቶች ምንም ዓይነት ትርፍ አያተርፉም! ለሥራ ማንቀሳቀሻ የሚያወጡትን ተጨባጭ ወጪ በምታሰላበት ጊዜ በእርግጥ እየከሰሩ መሆኑን ትመለከታለህ። ሥራ አስኪያጆች ታማኝ ቢሆኑ ኖሮ አስፈላጊውን ከባባድ ውሳኔዎች ይወስኑ ነበር። አመራር የሚያደርገው ይህንን ነው።

አንድ ሰውም፣ ጌታ ሆይ፥ የሚድኑ ጥቂቶች ናቸውን? አለው።

ሉቃስ 13፡23

ኢየሱስም ደጁ ጠባብ እንደሆነና የሚገቡበትም ጥቂቶች እንደሆኑ መለሰለት። እውነቱ ይኼ ነበር። መሪዎች ከእውነታ ጋር መጋፈጥ አለባቸው። እውነተኛ መረጃ ሳይኖር የበላይ ሹሙ ትክክለኛ የገንዘብ ውሳኔዎችን ሊሰጥ አይችልም። በመሆኑም እያንዳንዱ መሪ ትክክለኛውን ግንዛቤ ማግኘቱን ማረጋገጥ አለበት።

*ምዕራፍ 47*

# በራስህ የተነሳሳህ ሁን ከውጪ መመሪያና ማበረታቻ አትፈልግ

**ዳዊት ግን በአምላኩ በእግዚአብሔር ልቡን አበረታ።**

**1ኛ ሳሙኤል. 30፡6**

ሁሉም ሰው መሪው እንዲያበረታታው ይፈልጋል፡፡ ነገር ግን መሪውን የሚያበረታታው ማነው? እውነተኛ መሪ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ራሱን ማበረታታት የሚችል ሰው ነው፡፡ እኔ ከውጪ ማበረታቻን አልሻም፡፡ ራሴን ማበረታታት እንዳለብኝ ተምሬአለሁና፡፡ ለመበረታታት በውጫዊ ነገሮች ልደገፍ አልችልም፡፡

በአገልግሎቴ ፍጹም ተስፋ የቆረጥኩባቸውና ያዘንኩባቸው ብዙ ጊዜያት ነበሩ፡፡ ችግሮቼን ለማንም ለማጋራት የማልችልባቸው ሁኔታዎች አጋጥመውኝ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ልክ እንደ ዳዊት ልቤን በጌታ ማበርታት ነበረብኝ፡፡

ራስህን ማበረታታት እስካልተማርክ ድረስ ተከታዮችህን ልታበረታታ አትችልም፡፡ ዳዊት ችግር በደረሰበት ጊዜ ስለዚሁ ጉዳይ ለማንም ለመናገር አልቻለም ነበር፡፡ ራሱን ከማበረታታት ሌላ አማራጭ አልነበረውም፡፡

> **የዳዊትም ሁለቱ ሚስቶቹ ኢይዝራኤላዊቱ አኪናሆምና የቀርሜሎሳዊው የናባል ሚስት የነበረችው አቢግያ ተማርከው ነበር። ስለ ወንዶችና ስለ ሴቶች ልጆቻቸው የሕዝቡ ሁሉ ልብ ተቈጥቶ ነበርና ሕዝቡ ሊወግሩት ስለ ተናገሩ ዳዊት እጅግ ተጨነቀ፤ ዳዊት ግን በአምላኩ በእግዚአብሔር ልቡን አበረታ።**

**1ኛ ሳሙኤል 30፡5-6**

## ራስህን የማበረታቻ ሰባት ደረጃዎች

### 1. ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የግል ሕብረትን አዳብር

እርሱን በግል ሲናገርህ አድምጠው፡፡ ይህንን የምታደርገው በእምነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ተናገረኝ ብለህ ለመናገር መቻል አለብህ፡፡ ብቻህን ስትሆንና የሚያናግርህ ሳይኖር ሲቀር የሚያስፈልግህ መሪ

መንፈስ ቅዱስ ይሆናል፡፡ አብሮህ ያለው ለእዚሁ ነው! ሁልጊዜም በውስጥህ ያለው ታላቅ እንደሆነ አስተውል፡፡ እርሱ በውስጥህ ስላለ አሸንፈሃል፡፡

> ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል፥ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና።
>
> 1ኛ ዮሐንስ 4፡4

በጨለመብኝ ጊዜ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በግል የሚያናግረኝ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን ሌላ አጽናኝ በሚል ገልፆታል፡፡

> ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፡፡
>
> ዮሐንስ 14፡16

ኢየሱስ የመጀመሪያው አጽናኝ ነበር፡፡ ደቀ መዛሙርቱ እርሱን ያናግሩት ነበር፡፡ ጥያቄዎቻቸውን ይመልስላቸው ነበር፡፡ ምሪት ይሰጣቸው ነበር፡፡ ዛሬ ይህንን ሥራ የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ መሪዎች ብዙውን ጊዜ ብቸኞች ናቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስን እንደ ጓደኛው ለማያነጋግር መሪ አዝንለታለሁ፡፡

## 2. በቀላል የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ከእግዚአብሔር ህያው መልእክቶችን ተቀበል

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለአንተ የሰጠህ ሕያው መልእክት በሚሆንልህ ጊዜ ሁልጊዜም የምሪትና የማበረታቻ ምንጭ ይኖርሃል፡፡ ማበረታቻ ወይም አቅጣጫ በምፈልግበት ጊዜ የማነበው የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የጌታ መልእክት እንደሚሆንልኝ አምናለሁ፡፡ ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ ትልቁ የማበረታቻና የመነሳሻ ምንጭ የሆነልኝ፡፡

## 3. እግዚአብሔር ያሻገረህን ሌሎች ችግሮች አስታውስ

ጌታ ቀደም ሲል ያደረገልህን በምታስብበት ጊዜ ትበረታታለህ፡፡ ኢየሱስ ራሳችንን ለማበረታታት ቀደም ሲል ያደረገልንን ሁሉ እንድናስታውስ ይፈልጋል፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ቀደም ሲል የተፈጸሙትን ተአምራት በመዘንጋታቸው እንዴት እንደተቆጣ ተመልከት፡፡

ልባችሁስ ደንዝዞአልን? ዓይን ሳላችሁ አታዩምን? ጆሮስ ሳላችሁ አትሰሙምን? ትዝስ አይላችሁምን? አምስቱን እንጀራ ለአምስት ሺህ በቈረስሁ ጊዜ፥ ቍርስራሹ የሞላ ስንት መሶብ አነሣችሁ? እነርሱም። አሥራ ሁለት አሉት። ሰባቱን እንጀራስ ለአራት ሺህ በቈረስሁ ጊዜ፥ ቍርስራሹ የሞላ ስንት ቅርጫት አነሣችሁ? እነርሱም። ሰባት አሉት። ገና አላስተዋላችሁምን? አላቸው።

ማርቆስ 8፡18-21

## 4. አዎንታዊ አሳቦችን ተናገር

ማበረታቻን በምትፈልግበት ጊዜ እምነትህ ሊናገር ይገባል፡፡ እምነት የጭንቀት ተቃራኒ ነው፡፡ እምነት ጋሻ ነው፡፡ እምነትህ ጥቃትን የሚከላከልልህ ከእግዚአብሔር የተሰጠህ መሣሪያ ነው፡፡ ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ እምነት የጥቃት ፍላጻዎችን የሚከላከል ጋሻ እንደሆነ የሚናገረው፡፡ “Name it! Claim it! Take it” [(ሰይመው፣ ይገባኛል በል፣ ውሰድ) ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ በዚህ ትርጉም ይገኛል] በሚለው መጽሐፌ ውስጥ ማንኛውንም መሪ ሊጠቀሙ የሚችሉ አዎንታዊ አሳቦችን አስፍሬአለሁ፡፡

## 5. ተስማሚ የሆኑ የካሴት መልእክቶችን በመስማት እንደገና ተነቃቃ

## 6. በትክክለኛ ጊዜ ትክክለኛውን መዝሙር አዳምጥ

## 7. ወደ ጭለማ መልሰው ከሚወስዱህ አስጨናቂ እና ተስፋ አስቆራጭ ሰዎች ራቅ፡፡

ጠዋት ደስታ እንደሚሆን አስታውስ፡፡

## ምዕራፍ 48

# ተለማጭ ሁን፣ ግትርነት ዋጋ ያስከፍላል!

ደካሞችን እጠቅም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁ፤ በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ፥ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ።

1ኛ ቆሮንቶስ 9፡22

እውነተኛ መሪ ግትር ያለመሆን ባህርይ ይኖረዋል። ተለማጭ መሆን ማለት እምነትህን ታመቻምቻለህ ማለት አይደለም። መሪ ግትር መሆን የለበትም። ያረጀ ግትር ዛፍ ሊሰበር ይችላል፣ ወጣት ተለማጭ የሆነ ዛፍ ግን ሊታጠፍ ይችላል። ጳውሎስ ሰዎችን ሁሉ ለማዳን ለሁሉም ሰው ሁሉን ነገር እንደሆነላቸው ነው የሚነግረን። መልካም ውጤቶችን ለማግኘት ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ዝግጁ ነህ? በአካባቢህ ያሉትን ሰዎች ለመምሰል ስትል አለባበስህን የምታስተካክልበት ጊዜ ይኖራል። አንተ ሁልጊዜ ትክክል አይደለህም፣ ታውቀዋለዋህም!

በአንዳንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ሰዎች ሰዓት አክባሪዎች አይደሉም። ፕሮግራም በ12 ሰዓት ይጀመራል ስትላቸው ሰዎቹ በ12 ሰዓት ከቤታቸው ይነሱና አንድ ሰዓት ሲሆን ይደርሳሉ። ሰዓትህን በማክበር ግትር ከሆንክ ለባዶ ወንበሮች ስትሰብክ ትቆይና አብዛኞቹ ሰዎች መግባት ሲጀምሩም ስብከትህን ትጨርሳለህ።

አንድ መጋቢ እውቀት ከሌላቸው ሕፃናት በጎች ጋር ተለማጭ መሆን አለበት። አንዳንድ ጊዜ ምእመናን አሁን ሰብከህ ስለተነሣኸው ጉዳይ የምክር አገልግሎት እንድትሰጣቸው ሊጠይቁህ ይችላሉ። መልእክቱ በጣም ግልጽ ቢሆንም ከአንተ ጋር ለመነጋገር ይፈልጋሉ። ተለማጭ በመሆን እነዚህን ሰዎች ማስተናገድ የሚኖርብ ጊዜያቶች ይኖራሉ። ተለማጭ ሳትሆን መንፈስ ቅዱስ በነጻነት በሚሠራበት የተአምራት አገልግሎት ውስጥ ልትሆን አትችልም። አገልግሎትህን በሁለት ሰዓት ለመገደብ ብትፈልግ የተወሰኑ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴዎች ሊያመልጡህ ይችላል።

*መሪ አዳዲስ ነገሮችን ይሞክራል።* አዳዲስ የወንጌል አገልግሎት መንገዶችን ሞክር። የአንተ ላልሆኑ ተመክሮዎች ለመቀበል ወስን። አዳዲስ አሳቦች ያሏቸውን ወጣቶች አድምጥ። በግትርነት እግዚአብሔር የሚናገረው በሽበታሙ ስድሳ ዓመት በሆነው አዛውንት

ነቢይ ብቻ ነው ብለህ አታስብ። ተለማጭነት ከሃያ ዓመቱ የተቀባ ወጣትም አሳብ እንድትቀበል ያስችልሃል።

*መሪ ነህን? መሪ ከሆንክ ተለማጭ በመሆን ራስህን ለአዳዲስ አሳቦች ክፍት ማድረግ አለብህ።*

## ምዕራፍ 49

# ወታደሮችህን እዘዝ

*ደግሞም መለከት የማይገለጥን ድምፅ ቢሰጥ ለጦርነት ማን ይዘጋጃል?*

1ኛ ቆሮንቶስ. 14፡8

አሳብና ምክር መስጠት በቂ የማይሆንባቸው ጊዜያት አሉ። በዚህ ጊዜ ለወታደሮችህ ግልጽ ትእዛዝ መስጠት ይኖርብሃል። የመቶ አለቃው ለኢየሱስ እንዲህ ነበር ያለው። አንዱን "ሂድ" ስለው ይሄዳል፤ ሌላውን "ና"" ስለው ይመጣል። የመቶ አለቃው መሪ መሆኑን ለኢየሱስ እየገለጸ ነበር። መሪ ብዙውን ጊዜ አዛዥ ነው። ትእዛዝ ለመስጠት የማትችል ከሆነ መሪ ልትሆን አትችልም። መሪዎች አሳብና ምክር መስጠት አለባቸው። ነገር ግን መሪዎች ትእዛዝም መስጠት አለባቸው። "ሂድ!" ለማለት የምትገደድበት ጊዜ ይኖራል።

## ትእዛዝ ስጠሁ

አንድ ማታ ከመጋቢዎቻችን አንዱ ታማኝ አለመሆኑን ጌታ ገለጸልኝ። ጌታ፣ "ግልጽ ትእዛዝ ስጠው!" አለኝ። የጌታ መንፈስ በግልጽ የተናገረኝን ያንን ማታ ምን ጊዜም አልረሳውም። የጌታ መንፈስ እየተናገረኝ በመሆኑ መተኛት አልቻልኩም ነበር። እኩለ ሌሊት ላይ ፈጥጬ ቁጭ አልኩ። ጌታ የተናገረኝ ግልጽ ትእዛዝ እንድሰጥ ነበር። ትእዛዝ ከሰጠሁ በኋላ ታማኝ ያልሆነው ነገር እንደሚገለጽ ተናገረኝ።

በቀጣዩ ቀን ሁለት መጋቢዎችን ወደ ቢሮዬ ጠርቼ፣ "ከዚህ በፊት ምክርና አሳብ ሰጥቻችሁ ነበር። አሁን ግን ከዚህ ከተማ ተነሥታችሁ ወደ ቀጣዩ ከተማ እንድትሄዱ በግልጽ አዛችኋለሁ። በሌላ አባባል ወደዚያችኛዋ ከተማ ቀይሬአችኋለሁ" አልኳቸው።

ይህን ስል የቤተ ክርስቲያኔ ጠንካራ መሪ በመሆን ተግባሬን ማከናወኔ ነበር። "ከዚህ ከተማ ውጭ ሄዳችሁ እንድታገለግሉ ቀይሬአችኋለሁ" አልኳቸው።

ከሁለቱ መጋቢዎች አንዱ አንዳንድ ነገሮችን ግልጽ ካደረግን በኋላ እዚያ ሄዶ ለማገልገል የሚፈልግ መሆኑን ገለጸልኝ። ሌላኛው ደግሞ ፈገግ ብሎ፣ "ቀደም ሲል በዚያች ከተማ ውስጥ ሠርቻለሁ። እዚያ

ብሄድ ደስ ይለኝ ነበር። ነገር ግን ይህ አገልግሎቱን ለመልቀቅ መፈለጌን ለማሳወቅ ጥሩ አጋጣሚ ይመስለኛል” አለ።

ይህንን ስሰማ፣ “ነገሩ ተገለጸ ማለት ነው!” ስል አሰብኩ።

ይህ ወጣት ለተወሰነ ጊዜ ዕቅዱን ሲያውጠነጥን ነበር። ነገር ግን ዕቅዱን ይፋ ለማድረግ ወኔ አልነበረውም። ልቡ ከኛ ጋር እንዳልሆነ አውቄ ነበር። ጠንካራ ትእዛዝ መስጠቴ በልቡ ውስጥ ያለውን ነገር እንዲያወጣ አስገድዶታል።

ጽና፥ አይዞህ።

ኢያሱ 1፡6

መልካም መሪ ለመሆን የሚያስችልህን ብርታትና ጥንካሬ ከጌታ ዘንድ እንድታገኝ ጸልይ። ትእዛዝ መስጠት ምክር ከመስጠት በጣም የተለየ ነው። አሳብ ማቅረብ ትእዛዝ ከመስጠት በጣም የተለየ ነው። ምክር መስጠት የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ፤ ትእዛዝ መስጠት የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። ትእዛዝ መስጠት እንደ መሪ ስፍራህን እንድትይዝ ከማስቻሉም በላይ ታማኝ ያልሆኑ ሰዎች ራሳቸውን እንዲገልጹ ያደርጋል። በመሆኑም፣ የማዘዝን ጥበብ ማጎልበቱ ጠቃሚ ነው። ይህ ማለት ሁሉንም ሰው ታዛለህ ማለት አይደለም። ማዘዝ የምትችለው ወታደሮችህን ብቻ ነው።

## *ምዕራፍ 50*

# ቅድሚያ የምትሰጣቸውን ጉዳዮች ሚዛናዊ አድርግ

**አባይ ሚዛን በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ነው፤ እውነተኛ ሚዛን ግን ደስ ያሰኘዋል።**
**ምሳሌ 11፡1**

መሪነት የትኛው ጉዳይ የመጀመሪያውን ስፍራ እንደሚይዝና የትኛው ጉዳይ ቀጥሎ እንደሚመጣ የማወቅ ጉዳይ ነው። ሁሉም መሪ ቤት፣ ቤተሰብ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ሥራ፣ ትምህርት ቤት፣ ወዘተ... አለው። ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ የመጀመሪያውን ስፍራ የሚይዝ ምንድነው? መሪ ሁልጊዜም እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ስፍራ እንደሚይዝ ያውቃል። ብስለት ያለው ማንኛውም መሪ ቤተሰብ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ይነግራችኋል። አንዳንድ ሰዎች በቤተሰባቸው ላይ ከፍተኛ ትኩረት ስለሚሰጡ እግዚአብሔርን ይረሱታል። ሌሎች ደግሞ እግዚአብሔርን እናገለግላለን በሚል ሰበብ ቤተሰባቸውን ይረሳሉ። እነዚህ ሁለቱም የተሳሳቱ ናቸው። መሪ እነዚህን ነገሮች በሚገባ ሚዛናዊ የሚያደርግ ሰው ነው።

እግዚአብሔር የሰጠህን ነገሮች ሁሉ ሚዛናዊነት በአግባቡ ጠብቅ። ማንም ሰው ቢሆን መንግሥተ ሰማይ ደርሶ አንድን ያገልግሎት ክፍል ሁሉ ችል የማለቱን መርዶ ለመስማት አይፈልግም።

መሪ ነኝ ብለህ ታስባለህ? እንደዚያ ከሆነ እግዚአብሔር የሰጠህን ሃላፊነቶች በሙሉ በሚዛናዊነት ተወጣ። ይህ ሲሆን እኛም ምሳሌነትህን ለመከተል ደስተኞች እንሆናለን። ማንም ሰው ቢሆን መንግሥተ ሰማይ ደርሶ አንድን ያገልግሎት ክፍል በሞላ ችል የማለቱን መርዶ ለመስማት አይፈልግም። በአገልግሎቶች መካከልም እንኳን ቢሆን የተለያዩ ጥሪዎችህን ሚዛናዊ ማድረጉ ተገቢ ነው። ምናልባት ያንተ አገልግሎት መጋቢነትና ወንጌላዊነት ሊሆን ይችላል። እነዚህን ሁለት አገልግሎቶች በሚገባ መወጣት ይጠበቅብሃል። በበኩሌ እግዚአብሔር የማስተማር አገልግሎት እንደሰጠኝ አምናለሁ። ይህ የመጀመሪያውን ቅድሚያ የምሰጠው አገልግሎት ነው! ነገር ግን የወንጌላዊነትና የመጋቢነት አገልግሎቶችም ደስ ይሉኛል። ሆኖም፣ ጌታ ለቀዳሚው ነገር ቅድሚያ እንድሰጥ አስተምሮኛል!

## ምዕራፍ 51

# የቡድን ሥራን አመክኒዮአዊ ደንቦች አክብር

## ለቡድን ሥራ የሚያስፈልጉ አሥራ አራት ደንቦች

**1. በአገልግሎት ቡድኑ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ለማከናወን የምትሞክረውን ጉዳይ ማወቅ አለበት፡፡**

ሰዎች ለማከናወን የምትሞክረውን ነገር በሚያወቁበት ጊዜ ራእዩን ለመከተል ይቀላቸዋል፡፡

**2. በአገልግሎት ቡድኑ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ምን ማድረግ እንደሚጠበቅበት ማወቅ አለበት፡፡**

ይህ ነገሮች በሚበላሹበት ጊዜ ማንን መውቀስ እንዳለብህና ጥሩ ሥራ በሚሠራበት ጊዜ ማንን ማመስገን እንዳለብህ እንድታውቅ ያስችልሃል፡፡

**3. በአገልግሎት ቡድኑ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ሌሎች የአገልግሎት ቡድኑ አባላት ምን መሥራት እንዳለባቸው ማወቅ አለበት፡፡**

ከግለሰቦችና ከሁሉም የአገልግሎት ቡድኑ አባላት ጋር ስብሰባ ማድረግ ያለብህ ሁሉም ሰው እየሆነ ያለውን ነገር እንዲያውቅ ነው፡፡

**4. እያንዳንዱ ሰው በተሰጠው ጉዳይ ላይ ሙሉ ሃላፊነት ሊኖረው ይገባል፡፡**

ሰዎች ተግባራትን እንዲያከናውኑ ወክላቸው፡፡ በወከልካቸው ጉዳይ ላይ ደግሞ ሃላፊነት እንዲኖራቸው አድርግ፡፡

**5. ለአገልግሎት ቡድንህ አባላት በይፋ ከፍተኛ ምስጋናና እውቅና ስጣቸው**

አንድ ሰው አንድን መልካም ተግባር ደጋግሞ እንዲያከናውን ከፈለክ ለዚሁ ጉዳይ ምስጋና አቅርብለት፡፡

**6. ለሰዎችህ ትችትና ተግሳጽ በምትሰጥበት ጊዜ ሌላ ሰው በሌለበት ስፍራ አድርግ፡፡**

አንድን ሰው ለማረም በምትፈልግበት ጊዜ በሚያሠሯቸው ሰዎች ፊት ይህንን ማድረግ የለብህም። ይህ በሚያሠሯቸው ሰዎች ፊት ያላቸውን ሞገስ ይቀንሳል።

7. **የአገልግሎት ቡድን መሪ እንደመሆኔ መጠን እኔ የምሰጠው ትችት ገንቢ መሆን አለበት።**

8. **የአገልግሎት ቡድን እንደመሆኔ መጠን ለሚበላሹ ነገሮች ሁሉ ሃላፊነትን እቀበላለሁ።**

ወቀሳውን ተቀበል፤ ክብሩን ተጋራ።

9. **የቡድን አባላትህን አትኮንናቸው፤ አታማርርባቸው**

10. **ተግባራትን እንዴት በሚገባ ማከናወን እንደሚቻል ምክር ስጥ**

11. **እያንዳንዱ ሰው በጣም አስፈላጊ እንደሆነ እንዲሰማው አድርግ**

አስፈላጊ የማይመስል ሰው በምታይበት ጊዜ አበረታታው። አስፈላጊ ባይመስልም አስፈላጊ ነኝ ብሎ እንዲያስብ አድርግ።

12. **ከሁሉም የተሻለ አገልግሎት በሚሰጡበት ደረጃ ላይ እስኪደርሱ ድረስ ሰዎችን ከቦታ ቦታና ከሃላፊነት ሃላፊነት ቀያይር**

13. **ለሰዎች ከባህርያቸው ጋር የሚስማማ ሥራ ስጣቸው**

አንዳንድ ሰዎች ቀለል ያሉ ሲሆኑ፣ ሌሎች ደግሞ ተለዋዋጭ ስሜት ያላቸው ናቸው። ይሁን እንጂ ለሁሉም እንደ ባህርያቸው የሚስማሙ ሥራዎች አሉ።

14. **የቡድን አባላት የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በይቅርታ አለፍ። ቀለል አድርገህም ተመልከት።**

## *ምዕራፍ 52*

# አንዳንድ ጊዜ ተቆጣ

***ኢየሱስም ወደ መቅደስ ገባና በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ አወጣ፥ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠና። ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል፥ እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው።***

**ማቴዎስ. 21፡12-13**

መሪ ከሆንክ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙት ነገሮች አንተንም ደስ ያሰኙሃል። እግዚአብሔርን የሚያሳዝኑት ነገሮች ደግሞ ያሳዝኑሃል። ኢየሱስ ከእምነት *ያፈገፈጉ* ሰዎች የሚፈጽሙትን ክፉ *ሥራ* በተመለከተ ጊዜ ተቆጥቶ ነበር። እነዚህ ሰዎች ቤተ ክርስቲያኒቱን የንግድ ማዕከል አድርገዋት ነበር።

አብዛኞቹ ሰዎች ተፈጥሯዊ *የሥጋ* ቁጣ ይቆጣሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከዚህ ለየት ስላለ ቁጣ ይናገራል። ይህም ቅዱስ ቁጣ የምንለው ነው።

> ***ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት።***

**ኤፌሶን. 4፡26**

ይህ ጥቅስ ክርስቲያኖች አንዳንድ ጊዜ እንዲቆጡ ያዛል። ዋናው ነገር ስትቆጣ ኃጢአትን አለማድረግ ነው። ቅዱስ ቁጣ ዲያብሎስን፣ ክፋትንና በዓለም ውስጥ የሚታዩትን አስከፊ ነገሮች በተመለከተ በውስጥህ የሚፈጠር ነገር ነው። ቅዱስ ቁጣ ትክክለኛ ፍርድ የሌለበት ነገር እና ጭቆናን በመቃወም የሚነሳ ነው።

ቅዱስ ቁጣ በሚፈጠርብህ ጊዜ አንዳንድ ውሳኔዎችን ማድረግ ይኖርብሃል። ኢየሱስ ገንዘብ ለዋጮችን ከቤተ መቅደሱ ውስጥ እንዳስወጣቸው ሁሉ፣ አንዳንድ ታማኝነት የጎደላቸውን ሰዎች ከድርጅታችሁ ውስጥ ማስወገድ ሊኖርብህ ይችላል። ብዙ የንግድ ድርጅቶች የሚከስሩት በአግባቡ ቅዱስ ቁጣን ለመለማመድ ባለመቻላቸው ነው። መሪዎች እንዴት ጻድቅ የሆነውን ቅዱስ ቁጣ እንዴት መቆጣት እንዳለባቸው ማወቅ ይኖርባቸዋል።

*ምዕራፍ 53*

# የምትመራቸውን ሰዎች በትምህርት ኃይል ተቆጣጠር

መሪ ነኝ ብለህ ታስባለህ? መሪ ነኝ ብለህ የምታስብ ከሆነ አሳብህን የማስተላለፍን፣ የማስተማርንና የመስበክን ጥበብ እንድታጠና እመክርሃለሁ። አንድ ነጋዴ እንኳን ምን ለማድረግ እየሞከረ እንደሆነ ሠራተኞቹ እንዲረዱ ማድረግ አለበት። ሰዎች ከአንተ ጋር ግንኙነት የሚያደርጉት በቃልህ መሠረት ነው።

ሰሎሞን ንጉሥ ቢሆንም ሰዎችን አስተምሯል። በማስተማር ሰዎችን ሊቆጣጠር እንደሚችል ተረድቶ ነበር።

> ሰባኪውም (ንጉሥ ሰሎሞን) ጠቢብ ስለ ሆነ ለሕዝቡ እውቀትን አስተማረ፤ እርሱም ብዙ ምሳሌዎችን መረመረና ፈላለገ አስማማም።
>
> መክብብ 12፡9

ማስተማር ሰዎችን ወደምትፈልገው አቅጣጫ የምትመራበት ጥበብ ነው። ሰዎችን መምራት ቀላል አይደለም። ሁሉም ሰው የሚመጣው የየራሱን አሳብ በመያዝ ነው። ማስተማር ሰዎችን በምትፈልገው መንገድ እንድትቀርጽ ያስችልሃል። በማስተማር ኃይል ሰዎች የፈለከውን እንዲያደርጉ ልትመራቸው ትችላለህ። የማስተማር ኃይል ሳይኖር ማንንም ወዴየትም ቦታ ልትመራ አትችልም።

> ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል... ለማስተማር የሚበቃ
>
> 1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡2

የመምራት ሥልጣን ያለው ሰዎችን በማስተማር ችሎታ ውስጥ ነው። አንድ መሪ መረጃዎችን ለመረዳት በሚቀል መንገድ ማስተላለፍ መቻል አለበት። አገልግሎትህ ማስተማር ባይሆንም ማስተማር መቻል አለብህ።

## ሕዝቤን እንዴት ወደ ተአምራት አገልግሎት እንደመራሁ

የተአምራት አገልግሎት ማካሄድ በጀመርኩ ጊዜ አብዛኞቹ መጋቢዎች እየተከተሉኝ እንዳልሆነ ተረዳሁ። ይህ አዲስ ነገር ነበር። ምን

እያደረኩ እንደሆነ ሳላውቅ ስለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ተከታታይ ትምህርት ሰጠሁ። ስለ ቅብአቱ፣ ስለ ፈውስ፣ ተአምራት ለምን እንደሚያስፈልግ አስተማርኩ። ዛሬ የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን ሁሉ ለተአምራት ክፍለ ጊዜ ዝግጁ ናቸው።

ሰዎችን ወደ ተወሰነ አቅጣጫ ለመምራት ከፈለክ መጀመሪያውኑ ማስተማር አለብህ። ንጉሥ ሰሎሞን አስተዋይ በመሆኑ ሰዎችን ያስተምር ነበር። አስተዋይ መሪ ነህን? ከሆንክ ለህዝብህ እውቀትን አስተምር።

## ምዕራፍ 54

# ታላቅ መሪ ሁን ተጨማሪ ምዕራፍ ሂድላቸው

**ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ።**

**ማቴዎስ 5፡41**

እያንዳንዱ እውነተኛ መሪ ለተከታዮቹ ተጨማሪ ምዕራፍ ይሄድላቸዋል። ይህ ማለት ትንሽ ተጨማሪ መሥዋእትነትንና ተጨማሪ ጊዜን መክፈል ሊሆን ይችላል። ለምትወደው ሰው አንድ ተጨማሪ ምዕራፍ መሄድ ከባድ ነገር ሊሆን አይችልም። የአንድ ኩባንያ መሪ ከሥራ ሰዓት በኋላ ቢሮው ውስጥ ቢቆይ ያልተለመደ አይደለም። ይህ ተጨማሪ ምዕራፍ እንደ መሄድ ነው።

መጋቢ በሆንኩ ጊዜ ማንም ሳይጠይቀኝ ተጨማሪ ምዕራፍ እሄድ ነበር። ተጨማሪው ምዕራፍ እንድትሄድ ማንም የማያስገድድህ ነው። ለዚህም ነው ተጨማሪ የተባለው!

መኪናው የቤተ ክርስቲያን አውቶቡስ ሆና ታገለግል ነበር። የራሴ ሳውንድ ሲስተም የቤተ ክርስቲያን ዕቃ ሆኖ ያገለግል ነበር። የመኖሪያ ክፍሌ የቤተ ክርስቲያን ቢሮ ሆኖ ያገለግል ነበር። እነዚህን ነገሮች ለማድረግ ባልጠየቅም እኔ ግን በፈቃደኝነት በደስታ አድርጌአለሁ። ለምን ቢባል ተፈጥሯዊ መሪ የሚያደርገው ይህንኑ ነውና። ማንም ሳይጠይቅህ ተጨማሪ ነገሮችን ታደርጋለህ።

ለቤተ ክርስቲያንህ ወይም ለሥራህ መሳካት ተጨማሪ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። መሪ ነኝ ብለህ ታስባለህ? ሌላው ሰው የሚሄደውን ያህል ምዕራፍ ነው የምትሄደው? እውነተኛ መሪ ሁልጊዜም ተጨማሪ ምዕራፍ እንደሚሄድ እወቅ።

## ምዕራፍ 55

# ምን ተቋቁመህ አልፈሃል?

ሁሉም መሪዎች ከተከታዮቻቸው መካከል የተወሰነ የክህደት ተግባር የሚፈጽሙባቸው ሰዎች እንደሚኖሩ እርግጠኞች ሊሆኑ ይችላሉ። የኢየሱስ አገልግሎት የቀጠለው የይሁዳን ክህደት አልፎ ነው። ክህደት ሕይወት አካል ነው። ማንም ብትሆን ወይም ምንም ዓይነት አገልግሎት ብታካሂድ ክህደት ሊገጥምህ ይችላል። ይሁን እንጂ ክህደቱን ተቋቁመህ ማለፍ አለብህ!

> እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም። በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።
>
> በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው። ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።

መዝሙር 23፡1-6

ንጉሥ ዳዊት በሞት ጥላ መካከል ብሄድ እንኳን ጌታ ከአደጋ እንደሚታደገው ነው የገለጸው። ሁኔታዎችን አልፎ ወደፊት መቀጠል የአገልግሎት ማዕከላዊ ጭብጥ ነው። ሁሉም እውነተኛ አገልጋዮች ሁሉንም አልፎ የመሄድ አስተሳሰብ ሊኖራቸው ይገባል። እግዚአብሔር ልናገለግለው በመረጥን ጊዜ ሁኔታዎች ቀላል እንደሚሆኑልን ቃል አልገባልንም። ጌታ በእኛ ላይ የተሰነዘሩት ጥቃቶች ከተጠናቀቁ በኋላ አገልግሎታችንን እንድንቀጥል ይፈልጋል።

> ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ።

ኤፌሶን. 6፡13

መሪነት ችግሮችን አልፎ መሄድን ስለሚያካትት ችግሮችን አልፈህ መሄድ ካልቻልክ መሪ መሆን አትችልም።

# ችግሮችን ተቋቁሞ የሚያልፍ ሰው የሚያደርጋቸው አሥር ነገሮች

1. ችግሮችን ተቋቁሞ የሚሄድ ሰው አስከፊ ሁኔታዎች ቢኖሩም ጉዞውን መቀጠል አለበት፡፡

እየተዋጋን ያለነው ግልጽ ከሆነ ጠላት ጋር ነው፡፡ ሁኔታዎቹ አመቺ አይደሉም፡፡ ሰይጣን የዚህ ዓለም አምላክ ስለሆነ ያለነው በሱ ግዛት ውስጥ ነው ማለት ይቻላል፡፡

2. ጥሶ ማለፍ

ሁሉም ተዋጊ ችግሮችን ተቋቁሞና ጥሶ ማለፍ አለበት፡፡ አንድ ጊዜ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ስብከት ካቀረበኩ በኋላ መጋቢው ከሲኦል ጥሰህ የወጣህ ነው የሚመስለው ሲል ተናገረ፡፡ በርግጥም በብዙ ችግሮች ውስጥ አልፌአለሁ፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም ድረስ አለሁ፡፡

3. ችግሮችን ተቋቁሞ የሚሄድ ሰው መጓዝ እና አለማቋረጥ አለበት

4. ችግሮችን ተቋቁሞ የሚሄድ ሰው መቀጠል አለበት፡፡

**እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።**

**ዮሐንስ 8፡31**

5. ችግሮችን ተቋቁሞ የሚሄድ ሰው ከተግዳሮቶቹ በኋላ በሕይወት መገኘት አለበት፡፡

6. ችግሮችን ተቋቁሞ የሚሄድ ሰው መጽናት አለበት፡፡

ጳውሎስ የጸና መሪ ነበር፡፡

7. ችግሮችን ተቋቁሞ የሚሄድ ሰው ማዕበሎችን ማለፍ መቻል አለበት፡፡

ማዕበሉ ሲያልፍ አንተ መገኘት አለብህ፡፡

8. ችግሮችን ተቋቁሞ የሚሄድ ሰው ከጉዳቱ ማገገምና ማበብ አለበት፡፡

9. ችግሮችን ተቋቁሞ የሚሄድ ሰው ዳግም ለመዋጋት መኖር አለበት፡፡

10. ችግሮችን ተቋቁሞ የሚሄድ ሰው ከአደጋም አልፎ በሕይወት መኖር አለበት፡፡

## ጳውሎስ ተቋቁሞ ያለፋቸው 15 ነገሮች

1. ተደጋጋሚ እስራቶችን ተቋቁሞ አልፏል
2. ከአይሁዶች የተሰነዘሩበት አምስት ግርፋቶችን ተቋቁሞ አልፏል
3. ሦስት ጊዜ በበትር መመታትን ተቋቁሞ አልፏል
4. በድንጋይ መወገርን ተቋቁሞ አልፏል
5. ከሦስት የመርከብ መሰበር ተቋቁሞ አልፏል
6. ለ48 ሰዓታት በጥልቅ ባህር ውስጥ መቆየትን ተቋቁሞ አልፏል
7. ብዙ ጉዞዎች ተቋቁሞ አልፏል
8. ወንበዴዎችን ተቋቁሞ አልፏል
9. በከተማ ውስጥ ያጋጠሙት አደጋዎችን ተቋቁሞ አልፏል
10. የአገሩ ሰዎችን ተቋቁሞ አልፏል
11. በበረሃ ውስጥ ያጋጠሙት አደጋዎችን ተቋቁሞ አልፏል
12. ታማኝ ያልሆኑ ሰዎችን ተቋቁሞ አልፏል
13. የከፋ ድካምን ተቋቁሞ አልፏል
14. ብዙ ህመምን ተቋቁሞ አልፏል
15. ብርድና ራቁትነት ተቋቁሞ አልፏል

እንደ እብድ ሰው እላለሁ፤ እኔ እበልጣለሁ፤ በድካም አብዝቼ፥ በመገረፍ አብዝቼ፥ በመታሰር አትርፌ፥ በመሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ። አይሁድ አንድ ሲጎድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ።

ሦስት ጊዜ በበትር ተመታሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወገርሁ፤ መርከቤ ሦስት ጊዜ ተሰበረ፤ ሌሊትና ቀን በባሕር ውስጥ ኖርሁ። ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤ በወንዝ ፍርሃት፥ በወንበዴዎች ፍርሃት፥ በወገኔ በኩል ፍርሃት፥ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፥ በከተማ ፍርሃት፥

በምድረ በዳ ፍርሃት፥ በባሕር ፍርሃት፥ በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ፤

በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፥ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ።

2ኛ ቆሮንቶስ. 11፡23-27

# እያንዳንዱ መሪ ሊቋቋም የሚገባው ስድስት ነገሮች

## 1. ስደትን ተቋቁመህ እለፍ

በእምነቴ ምክንያት ከፍተኛ ስደት ደርሶብኝ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያን በመመስረቴም እንዲሁ ስደት ደርሶብኛል፡፡ የአገልግሎት ማህበር በማቋቋሜ ሰዎች ተሳልቀውብኛል፡፡ እ.አ.አ. በ1988 እና በ1989 ሁለት ሰዎች ጂም ጆነስ ብለው ጠርተውኛል፡፡ ከነዚህ ሰዎች አንዱ አብሮኝ ህክምና የሚማር ተማሪ ነበር፡፡ ይህን ስያሜ የሰጠኝ ሁለተኛው ሰው የዩኒቨርስቲው መምህርና የቤተሰባችን የቅርብ ጓደኛ ነበር፡፡ በእግዚአብሔር ጸጋ እነዚህን ስደቶች አልፌአለሁ፡፡

ለሰርጌ አዳራሽ በምፈልግበት ሰዓት ይህ መምህር አዳራሹን ላገኝ የምችለው የከፈትኩትን ቤተ ክርስቲያን ከዘጋሁ በኋላ ብቻ መሆኑን ለቤተሰቦቼ ተናገረ፡፡ ይህንን ያለው እኔ ሌላው ጂም ጆነስ ለመሆኔ እርግጠኛ በመሆኑ ነበር፡፡ ጂም ጆነስ ማን ነበር? ይህ ሰው በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ለሞት የዳረገ የእምነት መሪ ነበር፡፡ ሰዎች እንደዚህ እብድ የአምነት መሪ ነበር የሳሉኝ፡፡ እነዚያ ጊዜያት ከባድ ቢሆኑም አልፌአቸዋለሁ፡፡ ስደቶቹን አልፌ በእግዚአብሔር ጸጋ ዛሬም አለሁ፡፡

ስደት ስለደረሰባችሁ ተስፋ አትቁረጡ፡፡ መሪ ችግሮችን አልፎ የሚሄድ መሆን አለበት፡፡

## 2. ተቀባይነት ማጣትን ተቋቁመህ እለፍ

የወንጌል አገልጋይ እንደመሆኔ መጠን ተቀባይነት የማጣትን ችግር አልፌአለሁ፡፡ በማገባበት ሰዓት ላይ ሰርጌን እንዲያስፈጽም አምኜ የምጋብዘው የውጭ መጋቢ አልነበረም፡፡ ስለዚህ ረዳቴ የሆነው መጋቢ ጋብቻዬን አስፈጸመ፡፡ ለሰርጌ በከተማይቱ ውስጥ ያሉትን መጋቢዎች በሙሉ ብጋብዛቸውም አንዳቸውም ብቅ አላሉም፡፡ እነዚህ መጋቢዎች ለሰርጌ ደንታ አልነበራቸውም፡፡ ከሁሉም መጋቢዎች ጋር ፎቶግራፍ የምነሳበት ሰዓት ሲደርስ ማንም በቦታው አልነበረም፡፡ ሙሉ በሙሉ ተውኝ፡፡ ይሁን እንጂ ጉዞውን ቀጥያለሁ፡፡ በመሆኑም ያን ጊዜ አክብሮት የነሱኝ ብዙ ሰዎች ዛሬ ያከብሩኛል፡፡ ተቀባይነት ማጣት አገልግሎትህን እንዲገድል አትፍቀድ፡፡ መሪነት የደረሰብህን ሁሉ መቋቋምን ይጨምራል፡፡

## 3. መጥፎ ታሪኮችን ተቋቁመህ እለፍ

መሪ መጥፎ ታሪኮችን አልፎ የሚሄድ ሰው ነው፡፡ ኢየሱስ ከሞት በተነሣ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ስለ ደቀ መዛሙርቱ የሐሰት ወሬ ማራባት ጀመሩ፡፡ ደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስን አስክሬን ከመቃብር እንደሰረቁ አስመስለው ማውራት ጀመሩ ፡፡ ይህንንም ያሉት ኢየሱስ ከሞት አልተነሣም ለማለት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ወንጌሉ ይህንን ታሪከ ተቋቁሞህ አልፏል፡፡

> ከሽማግሎች ጋርም ተሰብስበው ተማከሩና ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጥተዋቸው። እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ። ይህም በገዢው ዘንድ የተሰማ እንደ ሆነ፥ እኛ እናስረዳዋለን እናንተም ያለ ሥጋት እንድትሆኑ እናደርጋለን አሉአቸው። እነርሱም ገንዘቡን ተቀብለው እንደ አስተማሩአቸው አደረጉ። ይህም ነገር በአይሁድ ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ ሲወራ ይኖራል።
>
> ማቴዎስ 28፡12-15

ጴጥሮስ አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት ብዙ ሰዎች እንደ ውሸታምና እንደ ሌባ ይመለከቱት ነበር፡፡ ሌሎች ደግሞ በኢየሩሳሌም ከታዩት አታላዮች ሁሉ የከፋ ሰው አድርገው ነበር የተመለከቱት፡፡ ይሁን እንጂ እርሱ እውነተኛ የወንጌል አገልጋይ ነበር፤ የሚናገረውም ያየውን የሰማውን ብቻ ነበር፡፡

የእውነተኛ መሪዎችና የወንጌል አገልጋዮች እጣ-ፈንታ ይህ ነው፡፡ አንተን አስመልክተው የሚነገሩትን የማይታመኑ ወሬዎች አልፈህ መሄድ አለብህ፡፡ ሰዎች ስለ እኔ አስገራሚ ነገሮችን ሲናገሩ ሰምቼ አውቃለሁ፡፡ አንድ ጊዜ አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ገንዘብ እንደምናትም ሲናገር ሰምቻለሁ፡፡ ዕፅ ታዞራላችሁ ብሎ የከሰሰንም ሰው ነበር፡፡ እነዚህን ሁሉ ታሪኮች እንዴት ነው ማብራራት የሚቻለው?

አንዳንድ ጊዜ የመንግሥት ባለሥልጣናት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎችን እንደሚበዘብዙና ሴቶችን እንደሚደፍሩ አድርገው ይናገራሉ፡፡ ብዙዎች ስለኛ የሚያስቡት ይህንን ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ምን ልናደርግ እንችላለን? *ማድረግ የምንችለው ተቋቁሞ ማለፍ ብቻ ነው!* ይህ ማለት ደግሞ የትኛውንም ዓይነት ማዕበል ጥሶ መሄድ ማለት ነው፡፡ መሪ አልፎ ተጓዥ ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ ቆራጥነትና ከፍተኛ እምነት ያስፈልግሃል፡፡ በራስህ ልታምንና የምታደርገው ነገር ትክክል መሆኑን ልታምን ይገባል፡፡ እግዚአብሔር እንደሚረዳህ ማመን አለብህ፡፡

## 4. ሁሉንም ዓይነት ችግር ተቋቁመህ እለፍ

መሪ ሁሉንም ዓይነት ችግር ያልፋል። ሁላችንም ሰላምና ስምምነትን እንደምንፈልግ አውቃለሁ። መሆንም ያለበት እንደዚሁ ነው። ነገር ግን ህይወት የራሷ የሆነ አቅጣጫ አላት። ይህንን ችለህ ማለፍ አለብህ። ልበ-ሙሉነትና ቆራጥነት ንብረትህ ሊሆኑ ይገባል። ትችላለህ! ካመንክ ሁሉንም ታሸንፋለህ!! በችግር ጊዜ መሪ የጓደኞቹንና የቤተሰቦቹን ድጋፍ ይሻል። በዚህ ዓይነቱ ጊዜ ከሁሉም የሚልቀው ጓደኛ እግዚአብሔር እንደሆን ተረድቻለሁ።

ኢየሱስ ችግሮችን ለማለፍ ችሏል። ከፍተኛ ተቀባይነት ማጣትና ጥላቻ ደርሶበት ነበር። ከመጀመሪያው ጀምሮ ሰዎች እንዲገደል ቢፈልጉም እርሱ ግን ተቋቁሞ ለማለፍ ችሏል። ኢየሱስ መቀባቱንና የፈውስ አገልግሎት እንደሚያካሂድ ሲናገር ብዙ ሰዎች ወዲያውኑ ነበር የተቃወሙት።

> የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት፥ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ። የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ተብሎ የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ...በምኩራብም የነበሩ ሁሉ ይህን ሰምተው ቍጣ ሞላባቸው፥ ተነሥተውም ከከተማ ወደ ውጭ አወጡት፥ ይጥሉትም ዘንድ ከተማቸው ተሠርታባት ወደ ነበረች ወደ ተራራው አፋፍ ወሰዱት፤ እርሱ ግን በመካከላቸው አልፎ ሄደ።
>
> ሉቃስ 4፡17-19፣ 28-30

ኢየሱስ ተቋቁሞ አልፏል! ተቋቁመህ ስታልፍ ይታየኛል! ልጆችህ ተቋቁመው ያልፋሉ! ቤተሰቦችህ ተቋቁመው ያልፋሉ!ኢየሱስ ተቋቁሞ አልፏል አንተም እንደዚያው! መሪ ሁሉንም ማስደሰት አይችልም፣ እግዚአብሔር ያለውን ብቻ ያደርጋል!

## 5. ቅንዓትን፣ ምቀኝነትን፣ የታማኝነት ጉድለትንና ክህደትን ተቋቁመህ እለፍ

> ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ።
>
> ዘኍልቁ. 12፡3

በአገልግሎትህ ከፍ እያልክ በምትሄድበት ጊዜ ብዙ ቅንዓትና ምቀኝነት ይገጥምሃል። እነዚህ ነገሮች በአብዛኛው የሚመጡት ከወንድሞችህና ከእህቶችህ ነው።

> እስራኤልም ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ይወደው ነበር፥ እርሱ በሽምግልናው የወለደው ነበርና፤ በብዙ ኅብር ያጌጠችም ቀሚስ አደረገለት። 4፤ ወንድሞቹም

አባታቸው ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ እንዲወደው ባዩ ጊዜ ጠሉት፥ በሰላም ይናገሩትም ዘንድ አልቻሉም።

ዘፍጥረት. 37፥3-4

ዮሴፍ ከአባቱ ዘንድ ሞገስ በማግኘቱ በተለያዩ ቀለማት ያጌጠች ኮት ተሸለመ። በዚህ ጊዜ የገዛ ወንድሞቹ ጠሉት። አንድ መሪ የወንድሞቹን ቅንዓትና ጥላቻ አልፎ መሄድ አለበት።

ስለእኔ እጅግ አስከፊ ነገር የተናገሩት በከተማችን ውስጥ የሚኖሩ የወንጌል አገልጋዮች ናቸው። ነገሮች ወደ አንተ የመድረስ አቅም አላቸው። አንደኛው አገልጋይ፣ "አንድ መጋቢ ስለ አንተ የተናገረውን ብትሰማ ኖሮ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ድርሽ አትልም ነበር" ሲል ነበር የነገረኝ።

መሪ በአሳዛኝ ቅንዓትና ጥላቻ መካከል ያብባል። ዮሴፍ የባርነትን ፈተና አልፎአል። እስራትን፣ ውሸትንና የጶጥፋራን ሚስት የሀሰት ወሬ አልፏል። መሪ ሁሉንም ችሎ የሚያልፍ ሰው ነው። ዮሴፍ ግብጽን በመከራ ጊዜ ለመመራት ከቻለባቸው ምክንያቶች አንዱ በአጠገቡ የነበሩትን ሰዎች ቅንዓትና ምቀኝነት ማለፉ ነበር።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለተቀበልከው በረከት ይቅርታ እንድትጠይቅ ይፈልጋሉ። ጌታ በህይወቴ ውስጥ ላመጣው በረከት እንዴት ነው ይቅርታ የምጠይቀው? ዛሬ ያገኘኋቸው ነገሮች በአብዛኛው በኔ ጥያቄ የመጡ አይደሉም። ዝም ብለው የመጡ ናቸው። መሪ ነኝ ብለህ ታስባለህ? ከሆነ፣ በአካባቢህ ያሉት ሰዎች ጥላቻ ሊያስጨንቅህ አይገባም። ዳዊት ከችግር ጋር መፋጠጥ የጀመረው ጎልያድን በገደለ ጊዜ ነበር። ከዚያ ድል በኋላ የሳኦል ዓይኖች በዳዊት ላይ ማረፋቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

> ሴቶችም። ሳኦል ሺህ፥ ዳዊትም እልፍ ገደለ እያሉ እየተቀባበሉ ይዘፍጥረትኑ ነበር። ሳኦልም እጅግ ተቈጣ፥ ይህም ነገር አስከፋው፤ እርሱም። ለዳዊት እልፍ ሰጡት፥ ለእኔ ግን ሺህ ብቻ ሰጡኝ፤ ከመንግሥት በቀር ምን ቀረበት? አለ። ከዚያም ቀን ጀምሮ ሳኦል ዳዊትን ተመቅኝቶ ተመለከተው።

1ኛ ሳሙኤል 18፥7-9

መሪ ነህን? ከሆንክ፣ ወደ ላይ ከፍ እያልክ በምትሄድበት ጊዜ ምቀኝነት፣ ቅንዓትና ክህደት እንደሚመጡብህ አውቀህ ተዘጋጅ። እነዚህን ሁሉ ለመቋቋም ቆራጥነትና እምነት ያስፈልጉሃል።

የኢየሱስ አገልግሎት የይሁዳን ክህደት አልፎ ቀጥሏል። ክህደት ሕይወት አካል ነው። ማንም ብትሆን ወይም ምንም ዓይነት አገልግሎት ብታካሂድ፣ ክህደት ሊገጥምህ ይችላል። የይሁዳን ሁኔታ

ስንመለከት ከ12 ሰዎች አንዱ ከሀዲ ሊሆን እንደሚችል እንጠረጥራለን፡፡

በቅርብ ጊዜ አዲስ መጋቢ ለመቅጠር ድምፅ ስለሰጠች ቤተ ክርስቲያን የሰማሁት ነገር አለ፡፡ ከምእመናኑ 91 በመቶዎቹ ለዚህ አዲስ መጋቢ የድጋፍ ድምፃቸውን ሰጡ፡፡ ይህ ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ማለት ከምእመናኑ መካከል አዲሱን መጋቢ ያልፈለጉ 9 በመቶ ሰዎች አሉ ማለት ነው፡፡ ይህ ምስኪን መጋቢ እነማን እንዳልፈለጉት እንኳን አያውቅም፡፡ ነገር ግን የእርሱን መቀጠር ያልፈለጉ ሰዎች በምእመናኑ መካከል እንደሚኖሩ ያውቃል፡፡

ሁሉም መሪዎች ከተከታዮቻቸው መካከል የተወሰነ ክህደት እንደሚገጥማቸው እርግጠኞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በተቻለ መጠን የሚክዱህን ሰዎች ቁጥር በመቀነስ በመሪነትህ ላይ የሚመጣውን ተቃውሞ ተቋቁመህ ለማለፍ ሞክር፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ማማረርም የለብህም፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ማልቀስ የለብህም፡፡ አመራር ማለት ይኼ ነው፡፡ ኢየሱስ ክህደት ተፈጽሞበታል፡፡ ጳውሎስም ክህደት ተፈጽሞበታል፡፡ አንተም ለምንድ ነው እንደዚህ አይነት ነገር የማይገጥምህ?

በጣም የቅርብ ጓደኞቼ በኔ ላይ የተነሱባቸው ጊዜያት አሉ፡፡ አብረውኝ የበሉና የጠጡ ሰዎች ከፍተኛ ጥላቻ ያሳዩብኝ ጊዜ አለ፡፡

> ደግሞ የሰላሜ ሰው የታመንሁበት እንጀራዬን የበላ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ።
>
> መዝሙር 41፡9

በአንድ ወቅት ላይ ያጋጠመኝን ክህደት ችዬ እንደማልፍ እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡ የአንድ ጓደኛዬ ክህደት ልቤን እጅግ አወከው፡፡ ለረዥም ጊዜ አብሮኝ የነበረው ጓደኛዬ ያደረሰብኝ የውሸትና የስድብ ጥቃት ለሁለት ሳምንታት እንድታመም አደረገኝ፡፡ ይሁን እንጂ አልፌዋለሁ! መሪ ሁሉንም ተቋቁሞ የሚያልፍ ሰው ነው! ውድ ወዳጄ፣ ሁሉንም ተቋቁመህ ለማለፍ ተዘጋጅ፡፡ በምታልፍበት ማዕበል ሁሉ ጸንተህ ታልፋለህ!

## 6. ውጥረትን ተቋቁመህ እለፍ

እውነተኛ መሪዎች ሁልጊዜም ፊት ፊት ስለሚሄዱ የተለያዩ ከፍተኛ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል፡፡ የሚመጣው በትር ሁሉ የሚያርፈው በእነርሱ ላይ ነው፡፡ ውጥረቱ ሁልጊዜም በእነርሱ ላይ ነው፡፡ ውጥረቶችን ለመቋቋም የማትችል ከሆነ መሪ ልትሆን አትችልም፡፡

ግንባርህን አጠንክረው። አትናደድ። አንዳንድ ሰዎች በውጥረት ይናጣሉ። እግዚአብሔር ሕዝቅኤል የሰዎችን ግንባር እንዳይፈራ ነግሮታል። ከሚመጣብህ ነገር ሁሉ በላይ ጠንካራ ሁን።

ድምፅህን ከፍ አድርገህ፣ "ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ" በል። "ይህን ጦርነት ለማሸነፍ የሚያስችል ኃይል አለኝ። በቀኜ ሺህ በግራዬ አሥር ሺህ ሰዎች ቢወድቁ እንኳ እኔ ግን አልሸነፍም። በኢየሱስ ስም አሸንፋለሁ። ጌታ በመንገዴ ሁሉ ያበረታኛል፤ ይጠብቀኛልም!" ብለህ ተናገር።

## ምዕራፍ 56

# የሌሎችን ሰዎች ስጦታዎች እውቅና ስጥ

*ተመልሰው ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠው እንዲሁ ለእኔ ላልተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠኝ አዩ።*

ገላትያ. 2፡7

ጴጥሮስ ለአህዛብ ወንጌል የማዳረሱ ተግባር የጳውሎስ መሆኑን በግልጽ ተረድቶ ነበር።

እግዚአብሔር ለአንድ ሰው አንድ ነገር እንደሰጠ አምነህ ልትቀበል ትችላለህ? ይህን ለማድረግ የምትችል ከሆነ መሪ ነህ ማለት ነው። መሪ በሌላ ሰው ላይ ያለውን ልዩ ጸጋ መቀበል የሚችል ሰው ነው። የግል ቤተ መጻሕፍቴ ሌሎች አገልጋዮች በጻፏቸው መጻህፍት የተሞላች ናት። በከተማችን ውስጥ የሚገኙ መጋቢዎች የጻፏቸው መጻህፍት በሙሉ አሉኝ። እግዚአብሔር ከእኔ ሌላ ሌሎች ሰዎችን እየተጠቀመ ለመሆኑ እውቅና እሰጣለሁ። መጽሐፍቶቻቸውን የምገዛው እነዚህ ሰዎች የሚያውቋቸውን ነገሮች ለማወቅ ስለምፈልግ ነው። እነዚህ ሰዎች ለጌታ ታላቅ ተግባር በማከናወን ላይ መሆናቸውን በግልም ሆነ በአደባባይ እመሰክራለሁ።

መጋቢዎች ብዙውን ጊዜ የሌሎች ሰዎች ሥራዎች ከማሞጋገስ ይልቅ እርስ በእርስ መናቆርና መተቻቸት ይቀናቸዋል።

ከብዙ ዓመታት በፊት በአገልግሎቴ ልደርስ የማልችላቸው በርካታ ሰዎች መሆናቸውን ተረድቻለሁ። ብዙ ሰዎች አሰባበኬን ላይወዱ ይችላሉ። ለዚህ ነው ጌታ ሌሎች አገልጋዮችን ያስነሳው። የሌሎችን ስብከት የማይወዱ ሰዎችም ሊኖሩ ይችላሉ። ለዚህም ነው ወደ እኔ ቤተ ክርስቲያን የመጡት። አንዳንድ አገልጋዮች ለአገልግሎቴ እውቅና ለመስጠት ሲቸገሩ ሳይ እገረማለሁ። እነዚህ ወገኖች ለሌሎች አገልግሎት እውቅና ለመስጠት የሚፈሩ ናቸው።

ጳውሎስ ለአህዛብ የማገልገል ጸጋ እንደነበረው ጴጥሮስ ተረድቶ እውቅና ሰጥቶታል። ጳውሎስም በበኩሉ ጴጥሮስ ለአይሁድ የማገልገል ጸጋ እንደነበረው ተረድቷል። እግዚአብሔር እውቅና ለሰጠው ነገር እውቅና ልትሰጥና እርሱ ያከበረውን ነገር ልታከብር ይገባል። እውነተኛ አገልግሎት እንዲህ ነው!

## *ምዕራፍ 57*

# የፈጠራ ጥበብ ይኑርህ

*በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።*

ዘፍጥረት. 1፡1

አጽናፈ-ዓለሙ የሚመራው የፈጠራ ጥበብን በተሞላው አምላክ ነው፡፡ ይህች ዓለም የምትመራውም የፈጠራ ጥበብ ባላቸው ሰዎች ነው፡፡ ፈጠራ አንድን አዲስና ታላቅ ነገር አስቦ ከሥራ ላይ ማዋል ነው፡፡ ተራ ሰው ሁሉም ሰው የሚሠራውን ሥራ ለመሥራት ይፈልጋል፡፡ መሪ ግን ፈጣሪ ለመሆንና አዳዲስ ድንበሮችን ለመድፈር የተዘጋጀ ሊሆን ይገባዋል፡፡

በዓለም ውስጥ ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል አንደኛው አዳዲስ ነገሮችን የፈጠረ ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ምንም ነገር ያልፈጠረ ነው፡፡ *የፈጠራ ችሎታ ያላቸው ሰዎች የፈጠራ ችሎታ የሌላቸውን ይገዛሉ፡፡* ይህንን እውነት ለማወቅ ርቀህ መሄድ አያስፈልግህም፡፡

የፈጠራ ችሎታ ያላቸው ከዚህ ፈጠራ ችሎታ የሌላቸውን ይገዛሉ፡፡ በሥራህ፣ በንግድህና በአገልግሎትህ የፈጠራ ጥበብን ተጠቀም፡፡ አንድ ነገር ከዚህ በፊት አልተከናወነም ማለት ስህተት ነው ማለት አይደለም፡፡ በሕይወትህ ክልል አንተም ሰዎችን ልትገዛ ትላለህ፡፡ እኔ የምቆጣጠረው አገልግሎት በአብዛኛው እየሰሩ በሚያገለግሉ አገልጋዮች የተዋቀረ ነው፡፡ እኔም ራሴ አገልግሎትን የጀመርኩት እየሰራ እንደሚያገለግ አገልጋይ ነበር፡፡ ይህን በማደርግበት ጊዜ ሰዎች በትምህርቱ ላይ አያተኩርም የሚል ወሬ በየመድረኩ ያስወሩብኝ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ከዚህ በፊት "እየሰሩ ማገልገል" የሚባለውን አገልግሎት አይተው አያውቁም ነበር፡፡ ስለዚህ ማድረግ የሚችሉት መተቸት ብቻ ነበር፡፡ ዛሬ ይህ በፈጠራ ጥበብ የተጀመረው "እየሰሩ ማገልገል" ተግባር በአገልግሎቴ ውስጥ ከፍተኛ እድገት አስገኝቷል፡፡ አንተም የፈጠራ ጥበብን ለመጠቀም ወስን!

# የፈጠራ ጥበብን ለመጠቀም የሚያስችሉ ሰባት ደረጃዎች

## 1. መንፈስ ቅዱስ ምን ማድረግ እንዳለብህ እንዲነግርህ ጠይቀው

ምናልባትም የፈጠራ ጥበብ በራቀው ክልል ልትሆን እንደምትችል ተገንዘብ። የፈጠራ ጥበብን አለመኖር ምናልባትም በሕይወት ዘመንህ ሁሉ መዋጋት ሊኖርብህ ይችላል።

## 2. ተፈጥሮን አድንቅ

ለተፈጥሮ፣ ለእንስሳትና ለሰብዓዊ ፍጥረት ፍላጎት ይኑርህ። እግዚአብሔር በፈጠራቸው ነገሮች ላይ ትኩረትህን በምታደርግበት ጊዜ የፈጠራ መንፈስ በውስጥ ይነሳሳል። የፈጠራ ጥበብ የሌላቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለተፈጥሮ ደንታ የላቸውም።

## 3. ተፈጥሯዊውን የለውጥ ተቃውሞ አሸንፍ

አብዛኞቹ ሰዎች ለውጥን አይፈልጉም። ለራስህ ታማኝ በመሆን በሕይወትህ ውስጥ ያለውን የፈጠራና የለውጥ ተቃውሞ አሸንፍ።

## 4. በተራ ሰዎች አስገራሚ ፈጠራዎች ተደመም

ለህክምና፣ ለቀዶ ህክምና፣ ለመኪኖች፣ ለኮምፒዩተሮች፣ ወዘተ. ፍላጎት ይኑርህ። የፈጠራ ጥበብ የሌላቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለነዚህ ነገሮች ግድ የላቸውም።

## 5. ለአዲስና ላልተለመዱ ድርጊቶች ራስህን አዘጋጅ

አዳዲስ አስተሳሰብን የሚቃወመው ባህርይ አይኑርህ። ብዙውን ጊዜ አዳዲስ አሳቦችን ሳቀርብ ሰዎች ይስቁብኝ ነበር። በመጨረሻም እነዚያ አሳቦች ለሰዎች ብዙ በረከቶችን አስገኝተዋል።

የፈጠራ ሰዎች በሚነሷቸው አሳቦች ምክንያት ብዙውን ጊዜ ይሳቅባቸዋል።

## 6. ተደርገው የማያውቁ ነገሮችን ለማድረግ ተዘጋጅ

ያልተደረጉ ነገሮችን ማድረግ የፈጠራ እህት ናት።

## 7. ቀደም ሲል ባሉት ነገሮች ላይ ለውጦችን ለማድረግ ሞክር

ለውጥ የፈጠራ ወንድም ነው።

ፈጠራን የሚያውቅ መሪ ሁልጊዜም አዳዲስ አሳቦችን ያመጣል። እነዚህ አዳዲስ አሳቦች ደግሞ ብዙውን ጊዜ የምንፈልጋቸውን መፍትሄዎች የያዙ ናቸው። አዳዲስ አሳቦች ያሉህ ሰው ነህ?

ምዕራፍ 58

# መርሆችን ብታከብር ታላቅ ድርጅት ትገነባለህ

## የመርህ ሶስት ፍቺዎች

1. መርህ የድርጊት መነሻ የሆነ መሠረታዊ ደንብ ነው፡፡
2. መርህ የአስተሳሰባችን መነሻ የሆነ መሠረታዊ እውነት ነው፡፡
3. መርህ የውሳኔ መሠረት የሆነ አጠቃላይ ህግ ነው፡፡

## ዘለቄታ የሌላቸው ሰባት ዓይነት ተቋማት

ተቋማት ውሳኔዎቻቸውንና ምክንያታዊነታቸውን በመርሆች ላይ በማይመሰርቱ መሪዎች ይወድማሉ፡፡ ዘላቂ የሆነ ድርጅት፣ ቤተክርስቲያን ወይም አገር ለመገንባት ከፈለክ ምክንያታዊነትህን፣ ድርጊትህንና ውሳኔዎችህን በመርሆች ላይ ማስደገፍ ይኖርብሃል፡፡ መርሆች ከአድልዎ፣ ከወገንተኝነትና ከፖለቲካዊ አቋም ያለፉ ሊሆኑ ይገባል፡፡ መርሆችን ከጣስክ እነሱም ይጥሱሃል፡፡

### 1. ከመርሆች ይልቅ በፖለቲካዊ አቋም የሚመራ ድርጅት ለውድቀት የተጋለጠ ነው

"ለፖለቲካው ምቹ አይደለም!" ይላሉ ብዙ የፖለቲካ መሪዎች፡፡ እነዚህ መሪዎች አገራትን በሙሉ የሚያጠፉ መጥፎ ውሳኔዎች ይወስናሉ፡፡ በአንድ አገር ውስጥ ውሳኔዎች የሚወሰኑት ትክክለኛውን ነገር ለማስፈፀም ሳይሆን የፖለቲካ ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ አገሪቷ ለጥፋት ትዳረጋለች፡፡

### 2. ከመርሆች ይልቅ ለዘመድ በማድላት የሚንቀሳቀስ ድርጅት ለውድቀት ይዳረጋል

አንድ መሪ ብቃት የሌላቸው የቤተሰቡ አባላት በድርጅቱ ውስጥ ቦታ እንዲያገኙ በሚያደርግበት ጊዜ ይህ ሰው መርሆችን ወደ ዳር በመተው ድርጅቱን በስሜት እየመራ ነው ማለት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ አድልዎና ግብዝነት ጥበብ አለመሆናቸውን ያስተምራል፡፡

> ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፥ በኋላም ታራቂ፥ ገር፥ እሺ ባይ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፥ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት።
>
> ያዕቆብ. 3፡17

ከሰዎች ጋር ያለህ ግንኙነት በጠቃሚ መርሆች ላይ ሳይሆን በቤተሰባዊ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን አገርህ፣ ሥራህ ወይም ቤተክርስቲያንህ ለውድቀት ይዳረጋል።

## 3. የግል የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት ብሎ ውሳኔዎችን በሚወስን መሪ የሚመራ ድርጅት መፍረሱ አይቀርም።

ድርጅቱን አርባ ሚሊዮን ዶላር ብቻ ሊያስወጣ ይገባ ስለነበረ አንድ ፕሮጀክት አውቃለሁ። ነገር ግን ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የወጣው ወጪ አምሳ ሚሊዮን ዶላር ነበር። ለምን? ምክንያቱም የሆነ ሰው ጉቦ በመቀበል የገንዘቡን መጠን ከፍ አድርጎ ነበር። እንዲህ ዓይነት ድርጅት እዳ ውስጥ ለመዘፈቅ ወይም ለገንዘብ እጥረት ለመጋለጥ ይገደዳል። በመርሆች ሳይሆን የራሳቸውን ኪስ ለማደለብ በሚፈልጉ ሰዎች ነው የሚመራው። ቤተ ክርስቲያንን ከመገንባት ይልቅ ራሴን ለማበልጸግ የምፈልግ ከሆነ ቤተ ክርስቲያኒቱ መክሰሟ የማይቀር ነው።

## 4. አንዲት አገር ከመርሆች ይልቅ በስግብግብነት የምትመራ ከሆነ መጨረሻዋ የከፋ ድህነት ነው የሚሆነው

የአፍሪካ ታሪክ ይህ ነው። የሚመሯቸውን አገራት ደም የጠጡ ስግብግብ መሪዎች ታሪክ ነው። በመርህዊ አመራር ፈንታ እያንዳንዱን የደም ጠብታ የመጠጡ ስግብግብ ጭራቆችና ጭልፊቶችን አሳልፈናል። ጨቋኝ አፍሪካዊ መሪዎች በሕይወት ዘመናቸው ተጠቅመው የማይጨርሱትን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር ሲያካብቱ አገሮቻቸውን አራቁተዋል።

## 5. ከደንቦችና ከመርሆች ይልቅ በራስ ወዳድነት የምትመራ አገር ትወድማለች።

ራስ ወዳድ የአፍሪካ መሪዎች የገዛ አገራቸው የትምህርት ሥርዓት መቀመቅ ውስጥ ገብቶ ሳለ ልጆቻቸውን በአውሮፓና በአሜሪካ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ያስተምራሉ። እነዚህ ራስ ወዳድ መሪዎች አሥር ሚሊዮን ልጆች ያልተማሩ ቢሆኑ ጉዳያቸው አይደለም። በማደግ ላይ ያለችው የጋና ሆስፒታሎች ሲበሰብሱ የመንግስት ባለሥልጣናትና ወዳጆቻቸው የሚታከሙት ለንደን በሚገኘው ክሮምዌል ሆስፒታል ነው። ራስ ወዳድነት የመልካም አመራር መሠረት አይደለም።

ዴሞክራሲ በምርጫ አማካኝነት ለሕዝብ ሥልጣን በመስጠት ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት በባሕርይው መሪዎችን ያበላሻል። ራስ ወዳድነት በሥልጣን ላይ ያለወሰን

ለመቀመጥ ይገፋፋቸዋል፡፡ ዲሞክራሲያዊ መሪዎች የሚባሉት በጣፋጭ ቃላት ብዙሀኑን ለማስደሰት ይሞክራሉ፡፡ ለዚህ ነው ብዙ በዲሞክራሲያዊ መርህ የተመረጡ መሪዎች ውሸታሞችና ግብዞች የሆኑት፡፡ ብዙ ተስፋዎች ጭራሽኑ አይፈፀሙም፡፡

### 6. ከመርሆች ይልቅ በአድልዎና በወገንተኝነት የሚመራ ድርጅት ይወድማል

አንድ መሪ ጓደኞቹ ወይም አብረውት የተማሩ በመሆናቸው ለሚወዳቸው አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ካደላ፣ ድርጅቱን የሚመራው በመርህ ሳይሆን በአድልዎ ነው ማለት ነው፡፡ ሰዎች ሹመት ማግኘት ያለባቸው በአድልዎ ሳይሆን በችሎታቸው ሊሆን ይገባል፡፡ ሁሉም ነገር የተመሠረተው በምታውቀው ሰውና የማን ጓደኛ በመሆንህ ላይ ከሆነ ድርጅቱ ይንኮታኮታል፡፡

### 7. ከመርሆች ይልቅ በብሔርተኝነት የሚመራ ድርጅት ክፍፍልና ጦርነት ዕጣ ፈንታው ነው

አስተሳሰቡ በመርሆች ሳይሆን በብሔር ክፍፍሎች የተቃኘ መሪ ድርጅቱን እያወደመ ነው፡፡ ከእርሱ ብሔር የማይወለዱ ሰዎች ቀስ በቀስ እርሱን ይጠሉታል፡፡ በአፍሪካና በአውሮፓ ያሉ የብዙ የእርስ በእርስ ጦርነቶች መሠረት ይህ ነው፡፡ ብዙ የአፍሪካ መሪዎች የሚያስቡት በመርህ ላይ ሳይሆን በብሔር ማንነት ላይ ተመሥርተው ነው፡፡ በዚህ ዓይነቱ አመራር ሳቢያ ብዙ አገሮች ወደ ጦር ቀጠናነት ተለውጠዋል፡፡ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተከፈተው ሂትለር አይሁዶችንና ሌሎችንም አስፈላጊዎች አይደሉም ያላቸውን ብሔሮች ለማጥፋት በመሞከሩ ምክንያት ነበር፡፡ የባልካንስ ግጭት የተፋፋመው ሙስሊሞች፣ ክሮአቶችና ሰርቦች አንዱ ሌላውን ለማጥፋት በመሞከራቸው ነበር፡፡ የሩዋንዳ ቱቲሲና ሁቱዎች በብሔር ላይ የተመሠረተ አመራር እንዴት አንድን አካባቢ በሙሉ ማውደም እንደሚችል የሚያሳስበን ሌላው አሳዛኝ ምሳሌ ነው፡፡

## ድርጅትህን ለመገንባት የሚያስፈልጉህ ሦስት መርሆች

1. በድርጅትህ ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ሕይወቱን ማሻሻል የሚችልበት እኩል እድል ሊሰጠው ይገባል፡፡

2. እያንዳንዱ ሰው ሹመትና ሽልማት ማግኘት ያለበት በምንም ነገር ሳይሆን ባሳየው የሥራ ውጤት መሆን አለበት፡፡

3. ለመልካም ውጤቶች፣ ለትጋት፣ ለታማኝነት፣ ለምርታማነትና ለመልካም ባሕርይ ሁልጊዜም ሽልማት ሊሰጥ ይገባል፡፡

## *ምዕራፍ 59*

# ከምትመራቸው ሰዎች ምን ያህል ገንዘብ ልታገኝ እንደምትችል አታስብ። ምን ያህል ልትረዳቸው እንደምትችል አስብ

**ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው።**

**ማቴዎስ 9፥36**

ኢየሱስ ለመጸለይ ምክንያት ነበረው። ያደረጋቸውን ነገሮች ለማድረግ ምክንያቶች ነበሩት። ሰዎችን የመርዳት ፍላጎት ነበረው። በርህራሄ ነበር የተነሳሳው። ይህም ኢየሱስ ለሰዎቹ አዘኔታ፣ምሕረት፣ ቸርነትና ርህራሄ ተሰምቶታል ማለት ነው። በግልፅ ሲታይ ኢየሱስ ከእነርሱ ምንም ገንዘብ ስለማግኘት እያሰበ አልነበረም። እነርሱን ስለመርዳት ነበር የሚያስበው።

*መሪ ነህ? በአእምሮህ የሚመላለሱት ምን ዓይነት ሀሳቦች ናቸው? ከምትመራቸው ሰዎች ልታገኝ የምትችለው የገንዘብ መጠን ሀሳብ ነው? ለእያንዳንዱ ድርጊትህ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚከፈልህ ነው? አእምሮህን የሞላው የግል ትርፍና የግል ጥቅም ሀሳብ ነው? እንዲህ ከሆነ እንደ ኢየሱስ ዓይነት መሪ አይደለህም! የሚያነሳሳህ ምክንያት ወሳኝ ነው።*

*ሐዋርያው ጳውሎስ ሕዝቡ ለሆኑት እስራኤላውያን ምን ያህል ሸክም እንደተሰማው ጽፏል። ሰዎችን እነርሱን ለመርዳት ካለ ምኞት ውጪ ለሌላ ለማንኛውም ምክንያት እየመራህ ከሆነ የተሳሳተ የሥራ መስክ ውስጥ ነው ያለህው ብዬ እሰጋለሁ። አንተ እነዚያ ችግሮች ባይኖሩብህም እንኳን ሌሎች ሰዎችና ችግሮቻቸው ሊያሳስቡህ ይገባል።*

**ብዙ ኀዘን የማያቋርጥም ጭንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ፤ አልዋሽምም፤ ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል። በሥጋ ዘመዶቼ ስለ ሆኑ ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና።**

**ሮሜ 9፥1-3**

ከምትመራቸው ሰዎች ምን ያህል ገንዘብ ልታገኝ እንደምትችል አታስብ። ምን ያህል ልትረዳቸው እንደምትችል አስብ

እግዚአብሔር የሚያየው ልብን ነውና፣ የሚያነሳሳህ ምክንያት ወሳኝ ነው። እግዚአብሔር አገልጋዮቹ ለገንዘብ ብለው በአገልግሎት ውስጥ መሆን እንደሌለባቸው ግልፅ አድርጓል።

> **በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት፡፡**
>
> **1ኛ ጴጥሮስ 5፡2**

እየሠሩ የሚያገለግሉትን የማበረታታሁ ለዚህ ነው። ሌላ ሥራ እየሠሩ ማገልገል እንደማጣሪያ ያገለግላል። በአገልግሎት ውስጥ ያለኸው ለገንዘብ ብለህ ከሆነ ምእመን ሆነህ ለማገልገል ደስተኛ አትሆንም። እግዚአብሔር በሚቻለው መጠን ሁሉ ለማገልገል የሚመኙ ታማኝ ምእመናን ናቸው ወደ ሙሉ ጊዜ አገልግሎት መምጣት ያለባቸው።

# ምዕራፍ 60

# ተፅዕኖ በማድረግ እደግ

...እነሆ፥ ዓለሙ በኋላው ተከትሎት ሄዶአል ...

ዮሐንስ 12፡19

ኢየሱስ በብዙ ቁጥር ባለው ሕዝብ ላይ ተፅዕኖ ነበረው፡፡መሪ በአመራር ጥበብ ባደገ ቁጥር የተፅዕኖውን ክልል ያሰፋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ዓለም ሁሉ ኢየሱስን እንደተከተለው ይነግረናል፡፡ ፈሪሳውያን በዚህ በጣም ተረብሸው ነበር፡፡ ዲያብሎስ በእውነተኛ መሪ ተፅዕኖ ይሸበራል፡፡ ለዚህ ነው መንግስታት እውነተኛ መሪ የሆኑ መጋቢዎችን የሚፈሩዋቸው፡፡ እውነተኛ መሪ ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ያውቃሉ፡፡

*በተፅዕኖ ለማደግ ቁልፉ በትናንሽ ንዑስ-ቡድኖች ላይ ባለህ ተፅዕኖ ማደግ ነው፡፡* በእነዚህ ንዑስ-ቡድኖች ላይ ያለህ የተፅዕኖህና የመግዛትህ ድምር ውጤት የሰፋ የተፅዕኖ አድማስን ይሰጥሃል፡፡

አንድ ሰው ከልቡ *መሪ* ከሆነ የመሪው ቀዳሚዎች የሆኑ ሰዎች ሳይቀሩ ይከተሉታል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያኑ ባሉ በንዑስ-ቡድኖች ላይ ተፅዕኖውን እንዲመሠርት ለጢሞቴዎስ አስተምሮታል፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን እነዚህን የጢሞቴዎስ ቡድኖች እንላቸዋለን፡፡

## ተፅዕኖ ልታሳድርባቸው የሚገቡ ስምንት ቡድኖች

### 1. የሸመገሉ ወንዶች

ሽማግሌ የሆነውን አትገሥጸው፥ እርሱን ግን እንደ አባት፥ ... በፍጹም ንጽሕና ለምናቸው።

1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡1

### 2. ወጣት ወንዶች -

...ጎበዞችን እንደ ወንድሞች፥ ... በፍጹም ንጽሕና ለምናቸው።

1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡1

### 3. የሸመገሉ ሴቶች

... የሸመገሉትን ሴቶች እንደ እናቶች፥ ...በፍጹም ንጽሕና ለምናቸው።

1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡2

## 4. ወጣት ሴቶች

... ቆነጃጅቱን እንደ እኅቶች በፍጹም ንጽሕና ለምናቸው።

1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡2

## 5. ሠራተኞች

የእግዚአብሔር ስምና ትምህርቱ እንዳይሰደብ፥ ከቀንበር በታች ያሉቱ ባሪያዎች ሁሉ ለገዙአቸው ጌቶች ክብር ሁሉ እንደ ተገባቸው ይቍጠሩአቸው።

1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡1

## 6. ድሆች

በእውነት ባልቴቶች የሆኑትን ባልቴቶች አክብር።

1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡3

## 7. ሀብታሞች

በአሁኑ ዘመን ባለ ጠጎች የሆኑት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ፥ ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለ ጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው።

1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡17

## 8. መሪዎች

በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች፥ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት፥ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል።

1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡17

ጢሞቴዎስ በአገልግሎቱ በማደጉ የተለያዩ ዓይነት ሰዎች የቤተክርስቲያኑ አካል ሆነው ነበር፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ ለአመራር ችሎታው ምላሽ እየሰጡ የነበሩትን ብዙ ዓይነት ሰዎች እንዴት እንደሚያስተዳድር ሊያሳየው ግድ ነበር፡፡

ሽማግሌ የሆነውን አትገሥጸው፥ እርሱን ግን እንደ አባት፥ ጎበዞችን እንደ ወንድሞች፥ የሸመገሉትን ሴቶች እንደ እናቶች፥ ቆነጃጅቱን እንደ እኅቶች በፍጹም ንጽሕና ለምናቸው።

1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡1፤2

የተለያዩ ዓይነት ሰዎች ለተፅዕኖህ ምላሽ እስከሚሰጡ ድረስ የአመራር ጥበብን ስታዳብር አያለሁ፡፡

# የተለያዩ የሰዎች ቡድኖች ላይ ተፅዕኖ የማሳደሪያ ቁልፎች

## 1. በትክክል አክብሮት ለሚገባቸው አክብሮትን አሳይ።

ለምሳሌ በዕድሜ የገፉ ሰዎች ከዕድሜያቸውና ከልምዳቸው የተነሳ የበለጠ አክብሮት ይገባቸዋል። ከወጣቶች የምትቀበለውን ዓይነት የጉልበት አቅርቦት አትጠብቅ። እግዚአብሔር ወደ አንተ ለሚያመጣቸው ለተከበሩ ዜጐች ዕውቅና ስጥ። ኒቆዲሞስና የአርማቴዎስ ዮሴፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀሳቸው ለኢየሱስ የነበራቸው ድጋፍ ያልተለመደ በመሆኑ የተለየ ዕውቅና እንደተሰጣቸው ይነግረናል። ይህ ሀብታምና ጉልበታም ለሆኑ ሰዎች ማድላት ወይም የተዛባ ፍርድ መስጠት አለብህ ማለት አይደለም። ክብር ለሚገባው ክብር ስጥ ማለት ነው።

> *ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ፤ ግብር ለሚገባው ግብርን፥ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን፥ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፥ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ።*
>
> ሮሜ 13፡7

## 2. የተለያዩ ሰዎችን የተለየ ጠባይ አጥና

በወንዶችና በሴቶች መሐከል ሰፊ ልዩነቶች አሉ። ይህ እነርሱን ሊያገለግል በሚፈልግ ማንኛውም ሰው ሊስተዋል ይገባል። በዕድሜ በገፉና በወጣት ሴቶች መካከልም ሰፊ ልዩነቶች አሉ። ወጣት ሴቶች የሚታያቸው ማግባት፣ ባል እና ልጆች ነው። በዕድሜ የገፉ ሴቶች የማያስደንቃቸው ነገር በአብዛኛው ማግባት፣ባል አንዳንዴም ልጆች ነው። በዕድሜ የገፉ ሴቶች ጋብቻና ባል ሊሰጥ ስለሚችለው ነገር እምብዛም ግራ ሊያጋባቸው አይችልም። ከወጣት ሴቶች ይልቅ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ያዘነበሉ ናቸው። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ በዕድሜ የገፉ ሴቶች ወጣት ሴቶችን ማስተማር አለባቸው የሚለው።

## 3. በተለያዩ የሰዎች ቡድኖች መካከል የሚኖሩትን ልዩነቶች አክብር።

የእያንዳንዱን ቡድን ልዩ ጠባይና ድክመቶች አታጣጥል። ጠቅለል ባለ አነጋገር፣ ሴቶች በይበልጥ እንደ ወግ (ወሬ፣ጨወታ) ግብይትና ልብሶች ላሉ ነገሮች ትኩረት ሲሰጡ ወንዶች በይበልጥ በሥራቸው፣ ገንዘብ፣ መኪኖች፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወዘተ... ላይ ያተኩራሉ። የሴቶችን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ባሕሪያት የምትንቅ ከሆነ ስኬታማ የሆነ የሴቶች አገልግሎት ሊኖርህ አይችልም። ልታከብራቸውና ሴትነትን ልታሞግስ ይገባል።

## 4. እያንዳንዱን ቡድን በተለየ የሚመለከቱ ትምህርቶችን አዘጋጅ

ቢሾፕ ቲ.ዲ. ጄክስ ለሴቶች ፍላጐት የበዛ መረዳትን የሚያሳይ አገልጋይ ምሳሌ ነው፡፡ ለዚህ ነው ስኬታማ የሴቶች አገልጋይ የሆነው፡፡ በተለይ ለሴቶች የሆኑ አስተምህሮዎችን አዘጋጅቷል፤ መጽሐፍትንም ጽፏል፡፡

## 5. በመሪዎች ላይ ጠንካራ ተፅዕኖ ማሳደርን አዳብር

እያንዳንዱ መጋቢ ለመሪዎች ጠንካራ የትምህርት አገልግሎት ማዳበር አለበት፡፡ ለመሪዎቻቸው ምን መንገር እንዳለባቸው የማያውቁ መጋቢዎች አሉ፡፡ መሪዎቼን ማስተማር ያስደስተኛል፡፡ እያንዳንዱ መሪ የተፅዕኖ ክልል ስላለው ይበልጥ ባስተማርኩ ቁጥር የበለጠ ተፅዕኖ ይኖረኛል፡፡

*ምዕራፍ 61*

# የግል ምሳሌዎችንና በቅኔ የሚነገሩ አባባሎችን አዳብር

**ሰባኪውም ጠቢብ ስለ ሆነ ለሕዝቡ እውቀትን አስተማረ እርሱም ብዙ ምሳሌዎችን መረመረና ፈላለገ አስማማም።**

**መክብብ 12፡9**

ይህ ሰባኪ ብዙ ምሳሌዎችን ያዳበረ ሰው ነበር። ምሳሌ ምንድን ነው? ጠለቅ ያለ ትርጉም ያለው ጥበባዊ አነጋገር ነው። አንድ ጊዜ አንድ አዛውንት "ቤትን ለመገንባት የሚያስፈልግህ ገንዘብ ሳይሆን ጥበብ ነው።" ሲሉ ሰማኋቸው። ይህ በርካታ ቤቶችን በመገንባት ፈር ቀዳጅ ከነበረ ሰው የተገኘ ጠቢብ አባባል ነበር።

ስኬታማ መሪ እየሆንክ ስትሄድ ጥበብን በልምድ ታዳብራለህ። ይህ ጥበብ በምሳሌዎችህ አማካኝነት ይተላለፋል።

**ጠቢብ እነዚህን ከመስማት ጥበብን ይጨምራል፥ አስተዋይም መልካም ምክርን ገንዘቡ ያደርጋል። ምሳሌንና ትርጓሜን የጠቢባንና ቃልና የተሸሸገውን ነገር ለማስተዋል።**

**ምሳሌ 1፡5፣6**

## ምዕራፍ 62

# ተከታዮችህን ወክለህ ከባለሥልጣኖች ጋር ተደራደር

ይህ የአመራር ወሳኝ ክፍል ነው። ሁሌም ቢሆን ከባለሥልጣኖች ጋር መደራደር ይኖርብሃል። ችግሮችን የሚፈታ ሰው መሆንን ተማር። ምክንያታዊ ካልሆኑና አስቸጋሪ ከሆኑ ባለሥልጣኖች ጋር የምትደራደርበት ጥበብ እንዲኖርህ ጸልይ። ሁልጊዜ እግዚአብሔር ጥበብ ይሰጥሀል።

> ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል።
>
> ያዕቆብ 1፡5

ከተለያዩ አመራሮች ይሁንታን ማግኘት ከጥሩ መሪ ሥራዎች አንዱ ነው። ተማሪ ሳለሁ፣ የመማሪያ ክፍሎቻቸውን እኔ ለፈለግኋቸው ስብሰባዎች እንድጠቀም ከትምህርት ቤት አመራሮች ፍቃድ ማግኘት ነበረብኝ። ማድረግ ለምትፈልገው ነገር ፍቃድ ማግኘት ሁልጊዜ እንደሚታሰበው ቀላል አይደለም። ከማዘጋጃ ቤት ሰዎች፣ ከፖሊስና ከቀበሌ ባለሥልጣናት ጋር መደራደር ሊኖርብህ ይችላል።

ጥሩ መሪ ራእዩን ለማሳካት የሚያስፈልገውን ነገር ከፍ ያሉ ባለሥልጣናት ሊሰጡት እስከሚችሉ ድረስ እንዲያምኑት ማድረግ ይችላል።

## ከባለሥልጣናት ጋር ለመደራደር የሚጠቅሙ አምስት መንገዶች

### 1. ከባለሥልጣናት ጋር መደራደር እንዳለብህ አስተውል

ካሉ ባለሥልጣናት ጋር ሳትደራደር በዚህ ዓለም ላይ አንድም ነገር ልታደርግ የምትችልበት መንገድ የለም። እውነታ እውቅና በመስጠት ራስህን ከእነርሱ ጋር ለመደራደር ማዘጋጀት አለብህ። ልታስወግዳቸው ወይም በጀርባቸው ልትዞር አትችልም።

> ንጉሡም። ምን ትለምነኛለህ? አለኝ። እኔም ወደ ሰማይ አምላክ ጸለይሁ።ንጉሡንም። ... ንጉሡ ደስ ቢለው፥ እስከ ይሁዳ አገር እንዲያደርሱኝ በወንዝ ማዶ ላሉት ገዦች ደብዳቤ ይሰጠኝ
>
> ነህምያ 2፡4፣7

ነህምያ የፈለገውን ነገር ለማድረግ ከንጉሡ ፍቃድ እንዴት ሊያገኝ እንደቻለ ተመልከት። አንዳንድ ሰዎች ለምንም ነገር ይሁንታ ወይም ፍቃድ ማግኘት አይችሉም። ጥሩ መሪ በዚህ የአመራር ክፍል ላይ ስኬታማ መሆን አለበት፤ አለበለዚያ ለእግዚአብሔር ምንም አትገነባም።

## 2. ካሉ ሕጎችና ደንቦች ጋር ለመስማማት ወስን

መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ባለሥልጣናት ለእኛው ጥቅም እንዳሉ ይናገራል።

> ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው።
>
> ሮሜ 13፡1

## 3. ከእነዚህ ባለሥልጣናት ጋር እንድትደራደር የሚረዱህን ተገቢ ሰዎች ተጠቀም።

ለምሳሌ፣ መንግሥትን የሚመለከቱ ህጋዊ ጉዳዮች ውስጥ ካለህ ጥሩ የሕግ ባለሙያዎችን ወይም የሕግ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎችን ማሰማራት ይኖርብሃል።

## 4. ከተገቢው ባለሥልጣኖች ሁሉ ጋር የግል እና ልባዊ ግንኙነቶችን አዳብር ደግሞ ጠብቅ።

በበዓላት ቀኖችና በሌሎች ወሳኝ አጋጣሚዎች ላይ አስታውሳቸው።

## 5. ከእነርሱ ጋር በመንፈሳዊ መንገድ ተደራደር

ለእነርሱ በመጸለይ ከባለሥልጣኖች ጋር መደራደር ጠቃሚ ነው። ለባለሥልጣናት በመጸለይ ከእነርሱ ጋር መደራደርን ተምሬአለሁ። በቀጥታ ለባለሥልጣናት ለሚጸልዩ የተገባ ተስፋ አለ። ይህም ተስፋ እግዚአብሔርን በመምሰል፣ በጭምትነትና ጸጥና ዝግ ብለህ እንድትኖር የሚያስችልህ ነው።

> እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።
>
> 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1-2

## ምዕራፍ 63

# ታላላቅ መሥዋዕትነቶችን እንዲከፍሉ ሰዎችን አሳምናቸው።

**ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።**

**ሉቃስ 14፡26**

በኢየሱስ አመራር ሥር የነበሩ ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን ለታላቅ ዓላማ ሰጥተዋል። ብዙ ሰዎች በእርሱ በማመናቸው ሕይወታቸውን አጥተዋል። በተልዕኮ ሜዳዎች ላይ ጌታን ሲያገለግሉ ስለሞቱ ስለ ብዙ ሚስዮናውያን አውቃለሁ። መሪ ሰዎች ለታላላቅ ዓለማ መሥዋዕትነቶችን እንዲያደርጉ የሚያሳምን ሰው ነው።

በአንድ ወቅት አንድ ወጣት ሐኪምን ራቅ ባለ የጋና ከተማ ውስጥ እንዲኖርና በዚያ ቤተ ክርስቲያን እንዲተክል ነገርኩት። ይህ ሐኪም ወደ አሜሪካ በመሄድ ሀብታም አማካሪ የመሆን አማራጭ ነበረው። እኔስ ለጠየቅሁት ትልቅ መሥዋዕትነትን በማድረግ ወደዚያች ከተማ ሄደ። አንድ ቀን በመንግሥተ ሰማይ ስንሆን ያንን መሥዋዕትነት በማድረጉ እጅግ እንደሚደሰት አምናለሁ!

ከተወሰነ ጊዜ በፊት ቤተ ክርስቲያናችን በችግር ውስጥ እንደነበረችና የብዙ የገንዘብ አቅራቦት አስፈልጉን እንደነበር አስታውሳለሁ። ብዙ ግለሰቦችን የግንባታ ሥራዎቻቸውንና ብዙ ገንዘብ ለወንጌል እንዲሰዉ ማነጋገር ነበረብኝ። በደስታ አደረጉት። ካደረጉት መሥዋዕትነት የተነሳም እግዚአብሔር ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ ባረካቸው!

## ሰዎችን ወደ መሥዋዕትነት የመምሪያ ዋና ቁልፍ

ሰዎች መሥዋዕትነት የሚያደርጉለት ዓይነት መሪ ነህ? እንደዚህ ዓይነት መሪ የምትሆንበትን ቁልፍ ልስጥህ። ቀላል ነው። አንተ ራስህ ታላላቅ መሥዋዕትነቶችን ያደረገ ሰው መሆን አለብህ። ሰዎች ስትናገር ይገምቱሃል! የምትሰብከውን እንደምትተገብር ሲያስተውሉ ነው የሚያምኑት።

**እውነት እውነት እልሃለሁ፥ አንተ ጕልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር፤ ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ፥ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል አለው። በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን አለ። ይህንም ብሎ። ተከተለኝ አለው።**

**ዮሐንስ 21፡18፣19**

ኢየሱስ ለጴጥሮስ እርሱን መከተል ወደ አሰቃቂ የመስቀል ላይ ሞት እንደሚመራ በጣም በግልጥ ነግሮታል፡፡ ኢየሱስ እየመራው ስለነበር ጴጥሮስ ለመሞት ተዘጋጅቶ ነበር፡፡

በ1840፣ አስራ ሁለት ሚስዮናውያን በስዊዘርላንድ ከሚገኘው ከባዝል ሚሽን ወደ ጐልድ ኮስት (ጋና) ተልከው ነበር፡፡ በሕይወት የተረፉት ሁለት ብቻ ነበሩ፡፡

ታሪኩ ሲወራ እንዴት የባዝል ሚሽን አንድ ክፍል ሙሉ ሰዎች “ወደ ጐልድ ኮስት ለመሄድ ፈቃደኛ የሆነ ማን ነው?” ተብለው እንደተጠየቁ ይነገራል፡፡ ማንም ምላሽ አልሰጠም፡፡ ሌላ ጥያቄ ተጠየቀ፣ “ወደ ጐልድ ኮስት ለመሳክ ዝግጁ የሆነ ማን ነው?” ብዙ ሰዎች ለዚያ ምላሽ ሰጡ፡፡ የሚልካቸው ካለ እነዚህ ሚስዮናውያን ለመሞት ዝግጁ ነበሩ፡፡

*አየህ፣ ወደዚያ ከተመሩ ሰዎች መሥዋዕትነቶችን ለማድረግ ዝግጁ ናቸው፡፡* የሌሎችን ሕይወት ውጦ ወዳስቀረ ቦታ ሰዎችን ለመላክ ጠንካራ መሪ ያስፈልግሃል፡፡ ስለጠንካራ አመራር እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ ሰዎች ለበጐ መሥዋዕትነቶችን እንዲያደርጉ የሚያሳምን መሪ ሁን፡፡

ምዕራፍ 64

# ሁሉንም ሰው ከአንተ ጋር ወደ ከፍታ ውሰድ

እግዚአብሔር አመራርህን ሲባርክ ራስህን ወደ ከፍታ ስትወጣ ታገኘዋለህ። ለብቻህ ወደ ከፍታ አለመውጣት ጠቃሚ ነው። ወደዚያ ለብቻህ ብትወጣ ትገለላለህ። የበለፀገና የስኬትን ፍሬ የበላ ብቸኛው ሰው ትሆናለህ።

## ሁሉንም ሰው ከአንተ ጋር ወደ ከፍታ መውሰድ የሚገባህ ሶስት ምክንያቶች

### 1. መገለልን ለማስቀረት

ስትገለል ብቸኛ ነህ ደስታህንም የምታካፍለው ሰው የለህም። የተካፈሉት ደስታ ዕጥፍ ደስታ ነው፤ የተካፈሉት ሐዘን ደግሞ ግማሽ ሐዘን ነው። መልካም ነገሮቼን የማካፍላቸው ሰዎች ስላሉኝ ደስተኛ ነኝ። የተባረከው ብቸኛ ሰው እኔ ስላልሆንኩ እግዚአብሔር በሕይወቴ ስላደረጋቸው በረከቶች በነፃነት መናገር እችላለሁ። በዙሪያዬ ያሉ ሰዎች ከእነዚያ በረከቶች ጋር መቆራኘት ይችላሉ ምክንያቱም በእነዚያን በረከቶች ስለተባረኩ ነው።

ጉልፍ መጫወት ስጀምር የሙሉ ጊዜ መጋቢዎቼ ሁሉ እንዲጫወቱ ለማድረግ ሞከርሁ። ዛሬ አብሬያቸው የምደሰት እና አብሬያቸው የምጫወት ሰዎች ስላሉኝ ደስተኛ ነኝ። ብቻዬን ግን እጅግ ብቸኛ እሆን ነበር።

### 2. የተጋለጠ ዒላማ መሆንን ለማስቀረት

ተነጥለህ በከፍታ ላይ ስትሆን ምቹ ዓላማ ትሆናለህ። አንዳንድ ጥቅማጥቅሞች ያሉት ብቸኛው ሰው በመሆንህ ለመለየት ቀላል ነህ። ቆንጆ መኪና ወይም ቆንጆ ቤት ያለህ አንተ ብቻ ስትሆን ለይቶ ለማውጣት ቀላል ነህ። አብዛኞቹ ባልደረቦቼ እንደኔ ዓይነት ጥሩ ቤትና መኪና አላቸው። በቤተ ክርስቲያኔ በዓለም ዙሪያ የሚጓዝ ብቸኛው ሰው እኔ አይደለሁም። እኔ እቤቴ ተቀምጬ አብዛኞቹ መጋቢዎቼ ዓለምን ይዞራሉ። እኔ በአፍሪካ ያለውን ምሽግ ይዤ እነርሱ ከተለያዩ የዓላማችን ክፍሎች ይደውሉልኛል።

## 3. ወደታች መጐተትን ለማስቀረት

በከፍታ ላይ ያለኸው አንተ ብቻ ስትሆን የተከበብከው ተስፋ በቆረጡ ሰዎች ነው። ተስፋ የቆረጡ ሰዎች አደገኛ ናቸው፤ በማንኛውም ሰዓት ሊጐዱህ ይችላሉ። ወደ እነርሱ የጭንቀት ደረጃ ጐትተው ሊያወርዱህ ይሞክራሉ። ሁላችሁም በከፍታ ላይ ካላችሁ፣ ሊጐትቱህ የሚችሉት ወደጐን እንጂ ወደታች አይደለም።

# ኢየሱስ ሁሉን ሰው ከእርሱ ጋር ወደ ከፍታ ለማውጣት ያደረጋቸው ስድስት ሙከራዎች

1. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንደ ሠርግ ወዳሉ ጥሩ ሥፍራዎች ይወስዳቸው ነበር።

የሚወስዳቸው ወደ ምኩራቦች፣ በጌቴሰማኔ ወዳሉ የጸሎት ስብሰባዎችና የታላቁ ተልዕኮ የሠራተኞች ስብሰባ ብቻ አልነበረም።

**ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ ታደሙ።**

**ዮሐንስ 2፡2**

2. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሁልጊዜ ከፍ ወዳሉ የህብረተሰቡ ክንውኖች ይወስዳቸው ነበር።

**ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ ታደሙ።**

**ዮሐንስ 2፡2**

3. ኢየሱስ ሁልጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ይመገብ ነበር።

   በክብር በተጠራበት ቦታ ሁሉ ደቀ መዛሙርቱን ወደ እራትና ምሳ ግብዣዎች ወስዷል።

**ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና። እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ።**

**ማቴዎስ 26፡26**

4. ኢየሱስ ሠራተኞቹ አብረውት ወደ መንግሥተ ሰማይ መምጣት ይችሉ እንደሆነ አብን ጠይቆታል።

**አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ።**

**ዮሐንስ 17፡24**

5. ኢየሱስ የተለያዩ ዓይነት ሰዎችን ወደ ታላቁ የሉቃስ 14 ግብዣ ጋብዟል፡፡

አካለ ስንኩላንን፣ ለማኞችን፣ ሴተኛ አዳሪዎችንና ማንም ለመምጣት የሚፈልግን ከእርሱ ጋር ወደ ግብዣው እንዲመጡ ለማድረግ ሞክሯል፡፡

**እርሱ ግን እንዲህ አለው፡- አንድ ሰው ታላቅ እራት አድርጎ ብዙዎችን ጠራ፤**

**ሉቃስ 14፡16**

6. ኢየሱስ በመስቀል ላይ የነበረውን ወንበዴ አብሮት ወደ ገነት እንዲመጣ ጋብዞታል፡፡

በእውነት፣ ኢየሱስ ሁሉንም ከእርሱ ጋር ወደላይ ለማውጣት ፈልጎ ነበር፡፡

**ኢየሱስም፡- እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።**

**ሉቃስ 23፡43**

## ምዕራፍ 65

# መሪ ከሆንክ አንድ ነገር ገንባ!

ብዙ ሰዎች ቤትን ለመገንባት ሀብትና ባለጠግነት የሚጠይቅ ይመስላቸዋል። ከተሞክሮዬ፣ የሚጠይቀው ገንዘብን በራሱ ሳይሆን ጥበብን እንደሆነ አውቃለሁ። ብዙ ጊዜ ያላቸውን አቅርቦት በአንድነት በማሰባሰብ በጥበብ የሚጠቀሙ ሰዎች ገንቢዎች ይሆናሉ። በአብዛኛው እንደዚህ ዓይነት ሰው መሪ ነው። ቤት ገንብተሀል? ቤተ ክርስቲያን ገንብተሃል? የምትገነባው ስለመሪነትህ ይመሰክራል። በሕይወት ዘመንህ ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ለመገንባት ወስን።

**ቤት በጥበብ ይሠራል፥ በማስተዋልም ይጸናል።በእውቀት ከከበረውና ካማረው ሀብት ሁሉ ጓዳዎች ይሞላሉ።**

**ምሳሌ 24፡3-4**

የመሪነት ችሎታዎች አንድን መጋቢ ለቤተ ክርስቲያን የመሰብሰቢያ አዳራሽ እንዲያገኝ ያስችሉታል። አውቶቢሶችንና የተለየዩ መሣሪያዎችን ለቤተ ክርስቲያንህ መግዛት የቤተ ክርስቲያን አዳራሽ ከመገንባት የተለየ ነው። ጠቢብ ሥራ አስኪያጅ ለድርጅቱ ርስትን ያስገኛል። አንድን አገር ለመገንባት የአመራር ጥንካሬ እንደሚጠይቅ ላረጋግጥልህ እችላለሁ። ደካማ መሪዎች ምንም መገንባት አይችሉም! ገንቢ ለመሆን ዛሬ ወስን። ለሚስቱና ለልጆቹ ቤት የሚገነባ ባል እውነተኛ መሪ ነው።

የጋና የመጀመሪያው ፕሬዘንዳንት ኳሚ ኑክሩማ ታላቅ መሪ በመባል በአብዛኛው ይወደሳል። ካደረጋቸው ነገሮች አንዱ ለሀገሪቱ ብዙ ነገሮችን መገንባት ነበር። ለምሳሌ፣ በዓለም ታላቅ ሰው ሠራሽ ሐይቅ ያለውን የአኮሶምቦ ግድብን ገንብቷል። የገነባቸው ነገሮች ጋና በአንድ ወቅት ታላቅ መሪ እንደነበራት ይመሰክራል። *መሪነት በሕንፃዎች መኖር ይገለጣል።* ጥሩ መሪ አንድ ነገር ትቶ ያልፋል።

ምዕራባውያን አገሮች ከነበራቸው የአመራር ዓይነት የሚመሰክር በሚገባ የለማ የመሠረተ ልማት አውታር አላቸው። ባልተማሩ አምባገነኖችና ደም መጣጭ አውሬ መሰል ጨቋኝ ገዥዎች የተገዙ የአፍሪካ አገራት እጅግ ትንሽ የመሠረተ ልማት አውታሮች

አሏቸው። በእውነት፣ ሕንፃዎችና ልማት የጥሩ አመራር ምልክቶች ናቸው። ሰለሞን ጠቢብ መሪ ነበር።

**ትልቅ ሥራን ሠራሁ፥ ቤቶችንም አደረግሁ፥ ወይንም ተከልሁ አትክልትንና ገነትን አደረግሁ፥ ልዩ ልዩ ፍሬ ያለባቸውንም ዛፎች ተከልሁባቸው በዱር የተተከሉትን ዛፎች አጠጣበት ዘንድ የውኃ ማጠራቀሚያ አደረግሁ።**

**መክብብ 2፡4-6**

በግንባታ ውስጥ ተሳታፊ ስለነበርኩ ብዙ ሰዎች ለምን እንደሚሸሹት ይገባኛል። ነገር ግን እግዚአብሔር መሪዎችን እንዲገነቡ እንደጠራቸው አምናለሁ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ታላላቅ መሪዎች አንዱ ነህምያ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ተነስተው እንዲገነቡ አነሳስቷል። ታዋቂው ስብከት ቀላል ነበር - ተነስተን እንስራለን!

**...የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፥ እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን ...**

**ነህምያ 2፡20**

## ምዕራፍ 66

# የሕወትህን ራእይ ሁልግዜ አስተውል

**ጲላጦስም። እንግዲያ ንጉሥ ነህን? አለው። ኢየሱስም መልሶ፦ እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ አንተ ትላለህ። እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው።**

**ዮሐንስ 18፡37**

ኢየሱስ ለምን በዚህ ዓለም እንዳለ ያውቅ ነበር፡፡ በታላቅ ውጥረት ጊዜያት ሳይቀር የሕይወቱን ዓላማ አብራርቷል፡፡ መሪ ሁልጊዜ አላማውን የሚያስብ ሰው ነው፡፡ እግዚአብሔር እንዳደርግ የጠራኝን ነገር ሁልጊዜ አስበዋለሁ፡፡ እያንዳንዱ ቀን ሕይወቴ የሚውለው እግዚአብሔር በሕይወቴ ላይ ያለውን ጥሪ ለማሳካት በመጣር ላይ ነው፡፡ ማድረግ የሚገባህን ነገር ስታውቅ ጊዜህን በአግባቡ ወደ መጠቀም በትክክል ትመራለህ፡፡

መጋቢ መሆንህ ትዝ የሚልህ ቤተ ክርስቲያን ስትመጣ ብቻ ከሆነ፣ እንግዲያውስ አንተ ምናልባት ትክክለኛ መጋቢ አይደለህም ማለት ነው፡፡ በሆስፒታል ውስጥ የሚሰራ ተራ ሰው ሳለሁ፣ ለአገልግሎት ስለመጠራቴ ሁልጊዜ አስብ ነበር፡፡ ኢየሱስ ልጅ ሳለ እንኳ "በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን" ብሏል፡፡

**እርሱም፦ ስለ ምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን? አላቸው።**

**ሉቃስ 2፡49**

ውድ መሪ፣ የሕይወትህ ዓላማ ምንድነው? ገንዘብ ለማግኘት እየሞከረ ያለ ነጋዴ ነህ? ታዲያ ንግድህ እንደበጐ አድራጐት የሚንቀሳቀሰው ለምንድነው? ለምን ወጪዎችህን ቀንሰህ ማትረፍ አትጀምርም? የወንጌል አገልጋይ ነህ? እንግዲያውሰ በገንዘብ ፍቅር አትወሰድ፡፡ እግዚአብሔር ብዙ ሀብትን እንድታፈራ አልጠራህም፡፡ በአገልግሎት ውስጥ እንድታገለግል ነው የጠራህ፡፡ በድህነት መኖር ቢኖርብህ እንኳ አገልግሎትን ፈጽም፡፡

እግዚአብሔር ሕልም አሳየኝ፡፡ በህልሙ ላይ እራሴን በረጅም መንገድ ላይ ስራመድ አየሁት፡፡ በመንገዱ ዳር እና ዳር ብዙ የወርቅ ክምሮች ነበሩ፡፡ በመንገዱ ላይ ስራመድ እነዚህን የወርቅ ክምሮች

ከጐን እያለፍኳቸው ነበር። እግዚአብሔር ለይቶ እንዲህ ተናገረኝ፣ “ከእነዚህ ክምሮች በየትኛውም ላይ አትቁም። በዚህ መንገድ ላይ ብዙ የወርቅ ክምሮች አሉ። ከእነርሱ በየትኛውም ላይ መቆም አያስፈልግህም።”

አየህ፣ እግዚአብሔር በራእዬ መጽናት እንዳለብኝ እያሳየኝ ነበር። ወደ ንግድ ወይም ወደ ገንዘብ ፍለጋ እንዳላፈነግጥ እየነገረኝ ነበር። መሪ ነህ እንግዲያውስ ከትክክለኛው ጥሪህ እንዳታፈነግጥ ራእይህ ልብህንና አእምሮህን እንዲሞላ ፍቀድ። አገልጋይ ከሆንክ ጉዳዩ ነፍሳት፣ ነፍሳትና ብዙ ነፍሳት እንደሆኑ አስታውስ። ብር፣ ብር እና ብዙ ብር አይደለም!

## ምዕራፍ 67

# ሁልጊዜ አንድ እርምጃ ቀድመህ ተገኝ

መሪ ከተከታዮቹ ቀድሞ ያለ ሰው ነው። መሪ የሚያደርገውም ይሄው ነው። ከምትመራቸው ሰዎች ቢያንስ አንድ እርምጃ ያህል የቀደምክ ሆነህ መታየት አለብህ። ኢየሱስ ጥሩ መሪ ነበር። ጸሎትን በሚመለከት ያለ ጥርጥር አንድ እርምጃ የቀደመ ነበር። ከደቀ መዛሙርቱ በላይ ይጸልይ ነበር። ከደቀ መዛሙርቱ ይልቅ ይሰብክ ነበር። ከደቀ መዛሙርቱ ይልቅ መሥዋዕትነት ይከፍል ነበር።

ክርስቲያን መሪ ቀድሞ ሊገኝባቸው የሚገቡ የማይታዩ ክፍሎች አሉ። በእነዚህ የማይታዩ ክፍሎች ያለው መሪነት ነው እውነተኛ መሪ የሚያደርገው።

## እያንዳንዱ ክርስቲያን መሪ ቀድሞ ሊገኝባቸው የሚገቡ አስር ክፍሎች

1. በጸሎት ቀድመህ ተገኝ
2. በመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ቀድመህ ተገኝ
3. ክርስቲያናዊ መጽሐፍትን በማንበብ ቀድመህ ተገኝ
4. የስብከት ካሴቶችን በማድመጥ ቀድመህ ተገኝ
5. ለእግዚአብሔር መሥዋዕትነት በመክፈል ቀድመህ ተገኝ
6. በመስጠት ዙሪያ ቀድመህ ተገኝ
7. እግዚአብሔርን በመጠበቅ ቀድመህ ተገኝ
8. በቅድስና ቀድመህ ተገኝ
9. በእግዚአብሔር ፍቅር ቀድመህ ተገኝ
10. ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት ቀድመህ ተገኝ

መሪ ነህ? ከሆንክ ቢያንስ አንድ እርምጃ ቀድመህ መገኘት አለብህ! በሕዝብ ፊት ብቻ አይደለም። ቀድመህ መገኘት ያለብህ፤ በግልህም

ቀድመህ መገኘት አለብህ። በምስጢር የጸሎት ሰው ከሆንክ፣ ተከታዮችህ ያስተውሉና እንደዚያው ያደርጋሉ።

ከተወሰኑ ዓመታት በፊት፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄድኩ ሳለሁ አንድ ሰው አንድ ምክር ለገሰኝ። እንዲህ አለኝ "ቄሱ የሚለውን ሁሉ አድምጥ። የሚለውን አድርግ፣ እርሱ ራሱ የሚያደርገውን ግን አታድርግ።" እውነተኛ መሪ ጳውሎስ እንዳለው ማለት መቻል አለበት፣ "እኔ ክርስቶስን እንደምከተል እኔን ተከተሉ።"

**እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።**

**1ኛ ቆሮንቶስ 11፥1**

መልካሙን ነገር አይተው ሰዎች እንዲከተሉት ሕይወትህን ለማተካከል ዝግጁ ካልሆንክ እንግዲያውስ መሪ ለመሆን ዝግጁ አይደለም።

## ምዕራፍ 68

# ሐሳብ የሚበትንን ነገር አስወግድ

*እርሱም፡- ከእኔ ጋር ወደ ቤቴ ና፥ እንጀራም ብላ አለው። እርሱም፡- ከአንተ ጋር እመለስና እገባ ዘንድ አይቻለኝም በዚህም ስፍራ ከአንተ ጋር እንጀራ አልበላም፥ ውኃም አልጠጣም፡፡ በዚያ እንጀራ አትብላ፥ ውኃም አትጠጣ፥ በመጣህበትም መንገድ አትመለስ በሚል በእግዚአብሔር ቃል ተብሎልኛልና አለ። እርሱም፡- እኔ ደግሞ እንደ አንተ ነቢይ ነኝ መልአክም። እንጀራ ይበላ ዘንድ ውኃም ይጠጣ ዘንድ ከአንተ ጋር ወደ ቤትህ መልሰው ብሎ በእግዚአብሔር ቃል ተናገረኝ አለው። ዋሽቶም ተናገረው። ከእርሱም ጋር ተመለሰ፥ በቤቱም እንጀራ በላ፥ ውኃም ጠጣ። በማዕድም ተቀምጠው ሳሉ የእግዚአብሔር ቃል ወደ መለሰው ነቢይ መጣ፡፡ከይሁዳም ወደ መጣው ወደ እግዚአብሔር ሰው። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- በእግዚአብሔር አፍ ላይ ዐምፀሃልና፥ አምላክህም እግዚአብሔር ያዘዘህን ትእዛዝ አልጠበቅህምና፥ ተመልሰህም። እንጀራ አትብላ፥ ውኃም አትጠጣ ባለህ ስፍራ እንጀራ በልተሃልና፥ ውኃም ጠጥተሃልና ሬሳህ ወደ አባቶችህ መቃብር አይደርስም ብሎ ጮኸ።እንጀራም ከበላ፥ ውኃም ከጠጣ በኋላ አህያውን ጫነለት። ተመልሶም በሄደ ጊዜ በመንገዱ ላይ አንበሳ አግኝቶ ገደለው ሬሳውም በመንገድ ላይ ተጋድሞ ነበር፥ አህያውም በእርሱ አጠገብ ቆሞ ነበር አንበሳውም ደግሞ በሬሳው አጠገብ ቆሞ ነበር።*

1ኛ ነገሥት 13፣15-24

## አገልጋይ ሊያስወግዳቸው የሚገቡ ሰባት እንቅፋቶች

### 1. አንተ እንደሰማኸው ከእግዚአብሔር ካልሰሙ ሰዎች የሚመጡ እንቅፋቶችን አስወግድ

እንደ እኔ ሁሉ ሌሎች ብዙ ሰዎች አገልጋዮች ቢሆኑም በአንድ ደረጃ ላይ እንዳልሆንን ይገባኛል፡፡ ሌሎች እያደረጓቸው ስላሉ ነገሮችን አላደርግም፡፡ አንድ ጊዜ ለአንድ መጋቢ ጓደኛዬ አንዳንድ መንደሮችን እንዴት እየደረስን እንዳለን ነገርኩት፡፡ ፈገግ ብሎ በእንደዚህ ዓይነት ሙከራዎች ላይ ምንም ፍላጎት እንደሌለው አስተያየቱን ሰጠኝ፡፡ ተገቢውን ነገር እያደረግሁ መሆኔን በመጠራጠር ተስፋ ቆረጥኩኝ፡፡ ነገር ግን ራሴን በጌታ አበርትቼ እግዚአብሔር በሰጠኝ ጥሪ ገፋሁበት፡፡ ያንን በማድረጌ ደስተኛ ነኝ፡፡

### 2. ለመፎካከር በመሞከር የሚመጣውን እንቅፋት አስወግድ፡፡

ይህ ሌላውን አገልጋይ ለመብለጥ በምትሞክርባቸው የተለያዩ ዓይነት ተግባሮች ውስጥ ጐትቶ ይከትሀል፡፡

## 3. የስልክ ጥሪ እንቅፋቶች

ስልክ ከእግዚአብሔር መገኘት የሚያርቅህ የዘመኑ እንቅፋት ነው። በሕይወቱ ስልክን በተገቢው ሥፍራ ላይ ማኖርን ያልተማረ ማንኛውም አገልጋይ ያለማቋረጥ ከጸሎትና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይደናቀፋል።

## 4. የሐሰተኛ ወንድሞች እንቅፋት

ሐሰተኛ ወንድሞች በጠላት ጊዜህን ለመፍጀት የሚላኩ ሰዎች ናቸው። ከእውነተኛ በጎችህ ጋር ማጥፋት የሚገባህ ሰዓት ጊዜህንና ጉልበትህን በሚመጥጡ በእነዚህ ሐሰተኛ በጎች ላይ ይባክናል። አንድ ቀን ዞረው የሚወቅሱህና ውለታ ቢስ የሚሆኑት ታዲያ እነዚሁ ሰዎች ናቸው። ሕይወታቸው ላይ እየሠራህ ያጠፋኸውን ሰዓታት አያስታውሱም።

## 5. ሥጋዊ የሆኑ መሪዎችና የአንተን ያህል ያልተሰጡ ሰዎች እንቅፋት

የኔን ያህል የመሰጠት ደረጃ ካላቸው አገልጋዮች ጋር ስቆራኝ፣ እነርሱ ይቀርጹኛል እኔም እንዲሁ እቀርጻቸዋለሁ። ስለ እግዚአብሔር ነገር ያንተን ያህል ግድ ከማይላቸው ሰዎች ጋር መቆራኘት ጤነኝነትህን እንድትጠራጠር ያደርግሃል። የሙሉ ጊዜ አገልጋይ መሆን ያለብህ ከሆነና ሙሉ ጊዜአቸውን ካልሰጡ አገልጋዮች ጋር የምታወራ ከሆነ ትክክለኛውን ነገር እያደረግህ መሆንህን ልትጠራጠር ትችላለህ።

## 6. ትርፋማ ያልሆኑ ክርክሮችና ጭቅጭቆችን እንቅፋት አስወግድ

ነገር ግን ጠብን እንዲያመጣ አውቀህ ከሰነፎችና ካልተማሩ ምርመራ ራቅ፤

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡23

ክርክሮችን አልወድም ስለ አንድ ጉዳይም ለመከራከር ብዙ ጊዜ የለኝም። በእውነት ላይ ምንም ልታደርግ አትችልም የሚለውን ጥቅስ እወደዋለሁ።

ለእውነት እንጂ በእውነት ላይ ምንም ለማድረግ አንችልምና።

2ኛ ቆሮንቶስ 13፡8

ይህ ያንተን ሐሳብ የሚያስተጋቡና የሚያስረዱ ክርክሮች የነገሩን እውነት አይለውጡም ማለት ነው። እውነቱ ሁሉን ውሸት ተቋቁሞ

ይኖራል! ሁሉም እውነተኛ አገልጋይ ይፈዝበታል፣ ይናቃል እንዲሁም ይከሰሳል። በአገልግሎት ከፍ እያልክ በሄድክ ቁጥር ስለ አንተ ከመቼውም ጊዜ የበዙ ውሸቶች ይናፈሳሉ።

> የእውነት ከንፈር ለዘላለም ትቆማለች ውሸተኛ ምላስ ግን ለቅጽበት ነው።
>
> ምሳሌ 12፥19

## 7. የሌሎች ሰዎችን ሥራ መሥራት አስወግድ።

ከመሪዎች ታላላቅ እንቅፋቶች አንዱ ይህ ነው። ደህንነቴን እንዲቆጣጠር አንድን ሰው ቀጥሬ እየተዟዟርኩ በሮቹ መዘጋታቸውን እራሴ የማረጋግጥ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ከራሴ ሥራ በተጨማሪ የሌላ ሰውን ሥራ እየሰራሁ ነው ማለት ነው። ብዙ መሪዎች ተግባር የለሽ እና ኃላፊነት የማይሰማቸውን ሠራተኞች ለማካካስ አስፈላጊ ነገሮችን በማድረግ ይስተጓጎላሉ።

ለመንፈሳዊ ነገር የተጠሩ መጋቢዎች ዓለማዊና አስተዳደራዊ የሆኑ ሌሎች ሊሠሯቸው የሚችሉን ሥራዎች መሥራትን ማስወገድ አለባቸው። እኔ መጋቢ ነኝ፤ ስለዚህ ለምን የሒሳብ ሠራተኛ፣ ፀሐፊ፣ ባንክ ሠራተኛ፣ ጥበቃ ወይም የሥነ ሥርዓት አስከባሪ መሆን እንዳለብኝ አይገባኝም። ጴጥሮስ ከቅዱስ ነገሮች ላለመደናቀፍ ማዕድን ከማገልገል ሸሽቶ ሲሮጥ ያደረገው ይኼንኑ ነው።

> አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው። የእግዚአብሔር ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም።...እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን።
>
> የሐዋሪያት ሥራ 6፥2፣4

## ምዕራፍ 69

# ሰዎች አንተ በሌለህበት እንዲታዘዙህ አድርግ

ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ በምኖርበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ በመልካም ነገር ተፈላጊ ብትሆኑ መልካም ነው።

ገላትያ 4፥18

ሰዎች አንተ ከእነርሱ ጋር ሳትሆን እንኳ ምኞትህን እንዲፈፅሙ ማድረግ መቻል እያንዳንዱ መሪ አጠናቆ ሊያውቀው የተገባ ጥበብ ነው። ያለዚህ ችሎታ ብዙ ሰዎችን መምራት አትችልም። ለመሆኑ ሁልጊዜ አብረውህ የሚሆኑት ምን ያህል ሰዎች ናቸው?

## አንተ በሌለህበት ሰዎች እንዲታዘዙህ የማድረጊያ አራት ቁልፎች

### 1. ታማኝነትን አስተምር

ሰዎች ላንተ ታማኝ ሲሆኑ ይወዱሀል ደግሞም አንተ ከእነርሱ ርቀህ ሳለህ እንኳ አንተ የምትፈልገውን ለማድረግ ይሞክራሉ።

### 2. ሰዎችን ጉዳያቸው ከእግዚአብሔር ጋር እንጂ ከሰው ጋር እንዳልሆነ አስተምራቸው።

እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ አለ፤ የምናደርገውንም ነገር ሁሉ ያያል። ሰዎች ይህንን ሲያውቁ በትክክለኛው መንገድ ለመኖር ይሞክራሉ። አንድ ሰው ታማኝ ልብ ሲኖረው በእርግጥ ጉዳዩ ከእግዚአብሔር ጋር መሆኑን ስለሚገነዘብ ይታዘዝሃል። ሰዎች የሚወላውሉት ጉዳያቸው ከሰዎች ጋር እንደሆነ ሲያስቡ ነው።

ባሪያዎች ሆይ፥ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በልባችሁ ቅንነት በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ ታዘዙ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ።

ኤፌሶን 6፡5፣6

## 3. ሰዎችን የሚሾሙት በሰው ሳይሆን በቀጥታ በእግዚአብሔር እንደሆነ አስተምራቸው፡፡

የሚባርካቸው እግዚአብሔር እንደሆነ ሲረዱ በመሐከላቸው ሆንክም አልሆንክም ባሕሪያቸው አንድ ዓይነት ይሆናል፡፡ አብረውህ የሚሰሩትን ዕድገት ከምስራቅ ወይም ከምዕራብ እንደማይመጣ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚመጣ እንዲረዱ ልታሰለጥናቸው ይገባል፡፡ ለመበረታታት አንተን ማየት አያስፈልጋቸውም፡፡ የእግዚአብሔር ዓይኖች በሁሉም ቦታ እንደሆኑ ያውቃሉ፡፡

> ክብር ከምሥራቅ ወይም ከምዕራብ ወይም ከምድረ በዳ የለምና
>
> መዝሙር 75፥6

እኔ ጉዳዬ ሊሆን የሚገባው ከእግዚአብሔር ጋር እንጂ ከሰው ጋር እንዳልሆነ ከረጅም ጊዜ በፊት ተምሬአለሁ፡፡ በአገልግሎት ያሳደገኝ እግዚአብሔር ነው፡፡ ሰዎች ግን ተስፋ አስቆርጠውኛል ጐድተውኛልም፡፡ ጉዳይህ ከእግዚአብሔር ጋር የመሆኑ እውነታ ሲገለጥልህ ሕይወትህ ለዘለዓለም ይለወጣል፡፡ አንተ ልታያቸው ባትችል እንኳ ሰዎች እንዲከተሉህና እንዲታዘዙህ ከፈለግህ ይህንን ታላቅ መርህ አስተምራቸው፡- ጉዳያችሁ ከእግዚአብሔር ጋር ነው፡፡

> ...በእርሱ ዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፥ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም።
>
> ዕብራውያን 4፥13

ኢየሱስ ምድርን ትቶ ሲሄድ ታላቁን ተልዕኮ በተመለከተ ትዕዛዝን ሰጥቷል፡፡ ይህንን ታላቅ ትዕዛዝ ትቶልናል፡፡ ኢየሱስን ማየት ባንችል እንኳን ብዙዎች ታዝዘዋል አሁንም እየታዘዙት ነው፡፡ ቢታይም ባይታይም የሚታዘዙት መሪ ሁን፡፡

## 4. ምልክቶችንና መገለጫዎችን ፈልግ

ምልክት የተደበቁ ነገሮች መገለጫ ነው፡፡ አንድን ነገር በቀጥታ የማታይ ከሆነ ማስጠንቀቂያ ምልክቶችና ማሳያዎችን የምትፈለግበትን ሥርዓት ማዳበር አለብህ፡፡ ሰዎች ትክክለኛውን ነገር ሲያደርጉ ብዙ ጊዜ ይህንን የሚያሳዩ አንዳንድ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ሁልጊዜ ምልክቶችን እፈልጋለሁ፡፡ ሁሉን ነገር ማየት የለብኝም..... እንዴትም እንደማላይ ደግሞ አውቃለሁ፡፡

## ምዕራፍ 70

# እንደ እባብ ተደብቀህ አብብ

**እነሆ፥ እኔ እንደ በጎች በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ።**

**ማቴዎስ 10፡16**

ኢየሱስ አለ፣ "እንደ እባብ ልባሞች ሁኑ።" የእባብ ብልጠት ምንድነው? *የእባብ ልባምነት ያለአግባብ የጠላትህን ዕይታ ሳትስብ የመንቀሳቀስ ችሎታ ነው።* እባቦች በየቦታው አሉ። ሁላችንም ያገኘነውን እባብ ሁሉ እንገድላለን! በሰዎችና በእባቦች መካከል ያለው ጠላትነት እንዲህ ያለ ነው! ይሁንና እባቦች ይበረክታሉ በዙሪያችንም ሁሉ የበዙ ናቸው። ይህንን የሚያደርጉት እንዴት ነው? በጥበብ!

## መሪ ተደብቆ እንደ እባብ መስፋፋት የሚኖርበት ሶስት ምክንያቶች

### 1. ክርስቲያኖች በዓለም ስለሚጠሉ

ክርስቲያን መሪ ሰይጣንና ወኪሎቹ ለእግዚአብሔር ሰው ያላቸውን የጥላቻ መጠን *መቼም አሳንሶ መገመት የለበትም።* ጋዜጠኞች ያለ ርህራሄ የእግዚአብሔርን ሰው ሲያወድሙ ስታይ ለእግዚአብሔር መንግሥት ቅዕበታዊና ከውስጥ የሆነ ጥላቻ እንዳለ ትረዳለህ።

**በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።**

**ማቴዎስ 10፡22**

### 2. ገና በአገልግሎት በጅማሬ ላይ ጥቃትን ለማስወገድ

በአገልግሎትህ የሆነ ደረጃ ላይ አመራርህ አንዳንድ ጥቃቶችን መቋቋም አይችልም። ገና የተወለደን ዶበርማን ፒንስቸር ወይም አልሳቲያን ውሻን ብትመታ ሊሞት ይችላል። ነገር ግን ያው አልሳቲያን ወይም ዶበርማን ውሻ እንዲዳብርና እንዲያድግ ቢተው፣ ምናልባት ሊገድልህ ይችላል። በአገልግሎትህ የሆነ ደረጃ ላይ የማትፈልጋቸው የሆኑ ጥቃቶች አሉ።

ቤተ ክርስቲያናችን የሚሰበሰበው በህክምና ትምህርት ቤቱ መዝናኛ ቤት በነበረበት ጊዜ ከቤተክርስቲያኑ ውጪ ምንም ዓይነት የማታወቂያ ሰሌዳ ወይም ባነር አላደረግንም ነበር፡፡ ዕይታን መሳብ አልፈለግሁም ነበር፡፡ ባልተገባ ጊዜ ትኩረትን ብንስብ ጥላቻን የተሞሉ ሰዎች ከዚያ ሊያባርሩን እንደሚችሉ አውቄ ነበር፡፡ በጥበብ በአንድ የማስተማሪያ ሆስፒታል መካከል በመንፈስ የተቀጣጠለ ታላቅ ቤተክርስቲያንን ለአራት ዓመታት ያህል ማካሄድ ችለን ነበር፡፡ ይህ የእባብ ብልሀት በተግባር ላይ ሲውል ነበር፡- ተሸሽጐ የመስፋፋት ጥበብ፡፡ ጥቃቶች ሲጀምሩ እኛ ትልቅ የሆነና የጠነከረ ቤተ ክርስቲያን ነበርን፡፡

አንዳንድ የህክምና ተማሪዎች ራሳቸውን አጥፍተው ነበርና የሕክምና ትምህርት ቤቱ ዲን በሆስፒታሉ ውስጥ የእኛን ቤተ ክርስቲያን መገኘት ለማድነቅ መጥተው ነበር፡፡ የሕክምና ማህበረሰቡን ፍላጐት እያሟላን እንደሆነ ተሰምቶት ነበር፡፡ ይህ ለእኛ መገኘት ሐዘኔታ እንዲኖረው አድርጐት ነበር፡፡ በእኛ ላይ መነሳትን አልፈለገም፡፡

ጥቂት ቆይቶ እኛን ከሆስፒታሉ ለማስወገድ ጠንከር ያለ ተቃውሞ ገጠመን፡፡ ይሁንና ቤተ ክርስቲያናችን አብባ ነበር፤ የሕክምና ትምህርት ቤቱ ቦርድ አባል የሆነች ሴትም በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ነበረች፡፡ ከሕክምና ትምህርት ቤቱ መዝናኛ እንድንወጣ የተደረግን መሆኑን ነገርኳት፡፡ ወዲያኑ ባለስልጣኖቹን ጠርታ ለምን ቤተ ክርስቲያኗን እንደሚያስጨንቁ ጠየቀቻቸው፡፡

“የቱ ቤተ ክርስቲያን” አሏት በመደነቅ፡፡

“የኔ ቤተ ክርስቲያን፣ አለቻቸው፡፡ “በመዝናኛው ውስጥ ያለው ቤተ ክርስቲያን የኔ ቤተ ክርስቲያን ነው! የምሄድበት ቤተ ክርስቲያን እዚያ ነው! ለምንድን ነው የምትጨቀጭቁን?”

ደነገጡ፡፡ “የምትሄጅበት ቤተ ክርስቲያን እዚያ እንደሆነ አላወቅንም! እስቲ ይህንን በደንብ እናጤነዋለን፡፡”

ይህ በእኛ ላይ እየተፋፋመ የነበረውን ጫና አበደረልን፡፡ የራሳችንን የቤተክርስቲያን ሕንፃ አግኝተን እስከምንወጣ በቂ ጊዜ አስገኘልን፡፡

መዝናኛውን ለቀን ስንወጣ ሌላ ቤተ ክርስቲያን በተመሳሳይ ቦታ ለመሰብሰብ ወሰነ፡፡ ወዲያውኑ ትላልቅ ባነሮቻቸው ከውጭ ተሰቅለው አየሁ፡፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ የሆስፒታሉ ማህበረሰብ የቤተ ክርስቲያኒቱን እንቅስቃሴ አስተዋሉ፡፡ የሰይጣን ጥላቻ ለአንድ የተለየ ቤተ ክርስቲያን አይደለም፡፡ ለሁሉም ቤተ ክርስቲያኖች እንጂ፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ከጥቂት ወራት በኋላ የመስፋፋት

ዕድሉን ሳያገኙ ከሆስፒታሉ መዝናኛ ተባረሩ። የእባብን ጥበብ ተማር ፣ ተሸሸጉ የመብዛትን ጥበብ!

## 3. ልትቋቋመው የማትችለውን ጠላት መጋበዝን ለማስወግድ

እባቦች በሰው ልጆች ፊት በሕይወት መኖር እንደማይችሉ ያውቃሉ፣ እኔ በበኩሌ የማየውን እባብ መርዛማ ቢሆን እገድላለሁ፤ አንተም እንዲሁ። እባቦች ሊታዩ በማይችሉበት በሣር ውስጥና በቋጥኞች ሥር የሚኖሩበት ምክንያት ይህ ነው። እባቦች በተጠበቀው መኖሪያ አካባቢያቸው ጥሩ ጊዜን ያሳልፋሉ፣ ማድረግ የሚፈልጉትን ሁሉ ያደርጋሉ እንዲሁም ይባዛሉ። ሊቋቋሟቸው የማይችሉ ጠላቶቻቸው የሆኑትን የሰው ዘሮች አይስቡም።

አንድ ጊዜ ስኬታችንን የሚጠሉ ትልልቅ ጠላቶችን እየሳብን እንደሆነ ስላሰብኩኝ ብሔራዊ የቴሌቪዥን ዝግጅቴን አቆምኩ። ነገሩን ሳጣራ የዕድገታችንና የአገልግሎታችን መታየት እንደ መንግሥትና ጋዜጠኞች ያሉ እጅግ ብዙ የወደፊት ጠላቶችን እያነሳሳ እንደሆነ ተሰማኝ። አገልግሎቴ ለማሳካት ግዴታ ቴሌቭዥን እንደማያስፈልገው አውቅ ነበር። ስለዚህ አቋረጥኩት! የእባብ ጥበብ ተደብቆ የመስፋት ጥበብ ነው። ልቋቋማቸው የማልችላቸውን ጠላቶች አልፈልግም።

## ምዕራፍ 71

# ስለማንነትህ የሚነገሩ የወሬዎች፣ የጥያቄዎችና ውዝግቦችን ተፅዕኖ ተቋቋም

ጴጥሮስ አገልግሎቱን ሲጀምር መቃብር ቆፋሪ እንደሆነና የኢየሱስን ሬሳ እንደሰረቀ የሚናፈሱ ጭምጭምታዎች ነበሩ፡፡ ብዙ ሰዎች እስካዛሬው ቀን ድረስ እንኳን ይህንን ታሪክ አምነዋል፡፡

> **ከሽማግሎች ጋርም ተሰብስበው ተማከሩና ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጥተዋቸው። እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ። ይህም በገዢው ዘንድ የተሰማ እንደ ሆነ፥ እኛ እናስረዳዋለን እናንተም ያለ ሥጋት እንድትሆኑ እናደርጋለን አሉአቸው። እነርሱም ገንዘቡን ተቀብለው እንደ አስተማሩአቸው አደረጉ። ይህም ነገር በአይሁድ ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ ሲወራ ይኖራል።**
>
> **ማቴዎስ 28፡12-15**

ነገር ግን ጴጥሮስ በዙሪያው የሚሽከረከሩትን ጭምጭምታዎች ማገልገል ነበረበት እያንዳንዱ ስኬታማ አገልጋይ ሊገጥሙት የሚችሉትን ጭምጭምታዎች፣ ታሪኮች፣ ተረቶች ጥያቄዎችና አለመግባባቶችን መቋቋም መማር አለበት፡፡

## ወሬዎችን፣ አለመግባባቶችንና ጥያቄዎችን የመቋቋሚያ ሰባት መንገዶች

1. አወዛጋቢውን ጉዳይ በፍጹም አታንሳው
2. ስላለፉት ስህተቶችህ ማውራት አቁም
3. ሰዎች ስለ አንተ የሚናገሯቸውን መጥፎ ነገሮች አንተም ደግመህ አታውራው
4. ሁሉም ሰው በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የተገደበ መሆኑን እወቅ
5. ስለ ሕይወትህ ወይም ስለ አገልግሎትህ ያለን ጥያቄ ወይም ወሬ አታጉላው
6. ስለዚህ መናገርም አያስፈልግም

7. በጠላቶችህ የተመረቱትን ጭምጭምታዎች አታስተዋውቅ

8. ለእግዚአብሔር ተወው፡፡ እርሱ ስለአንተ ይዋጋል

እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል፥ እናንተም ዝም ትላላችሁ አላቸው።

ዘጸአት 14፡14

## ከኢየሱስ ተማር

እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ።

ማቴዎስ 1፡20

1. ኢየሱስ የተወለደው ከድንግል ነበር፡፡

እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።

ማቴዎስ 1፡23

2. ማርያምን በማግባቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በዮሴፍ ላይ ስቀውበት ሊሆን ይችላል፡፡

3. ኢየሱስ ታማኝ ያልሆነች ሴት ልጅ ወይም የማይታወቅ ሰው ልጅ እንደሆነ ተቆጥሮ ይሆናል፡፡

4. አንዳንድ ሰዎች የማርያም ልጅ እያሉ ነበር የሚጠሩት፡፡

ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ የያቆብም የዮሳም የይሁዳም የስምዖንም ወንድም አይደለምን? እኅቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን? አሉ፤ ይሰናከሉበትም ነበር።

ማርቆስ 6፡3

5. ምናልባት "አባት የለሹ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ባይ" እያሉ አንጓጠውት ሊሆን ይችላል፡፡

6. ኢየሱስ መቼም ስለ ጉዳዩ አይወያይም ነበር ኢየሱስ ስለ ዮሴፍ ተናግሮ አያውቅም፡፡

7. ስላለፈው ታሪኩም ሆነ ስለቤተሰቡ ማንነት የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጥያቄ አላነሳም፡፡

8. ስለ እናቱና ስለ አባቱ ያለ ጥያቄ በየትኛውም በኢየሱስ ትምህርቶች ውስጥ አንድም ጊዜ አልተነሳም፡፡

## ምዕራፍ 72

# ያንን ውሳኔ ወስን! ያም ሆነ ይህ ብዙ ውሳኔዎች ከሁለት መጥፎ አማርጮች አንዱን መምረጥ ስለሚጠይቁ!

ነገሮች ፍጹም አለመሆናቸውን መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ መሪ ሊወስን ከሚገባቸው ውሳኔዎች አብዛኞቹ በግልጥ ጥሩ እና በግልጥ መጥፎ በሆነው መሐል የሚወሰኑ ውሳኔዎች አይደሉም፡፡ ብዙ ነገሮች በጥቁርና በነጭ ወይም በብርሃንና በጨለማ መካከል ያሉ ቁርጥ ያሉ አማራጮች አይደሉም፡፡ ጥሩ መሪ እንደዚህ ዓይነት አማራጮች ሲቀርቡለት የመወሰንን አስፈላጊነት ማወቅ አለበት፡፡ ጥሩ መሪ እንዴት ከሁለት መጥፎ አማራጮች የተሻለውን እንደሚመርጥ ያውቃል፡፡ ብዙ ጊዜ ሕይወት ሁለት መጥፎ ምርጫዎችን ታቀርብልናለች፡፡ *ብዙ መሪዎች በቀረቡላቸው ፍጹም ያልተለዩ ምርጫዎች ምክንያት ምንም ማድረግ እስከማይችሉ ሽባ ሆነዋል፡፡* ሁለት እጅግ የሚለያዩ አማራጮች ማየት ስላልቻሉ ያንን አስፈላጊ እርምጃ አይወስዱም፡፡

ጋብቻ ከእንደነዚህ ዓይነቱ ውሳኔ አንዱ ነው፡፡ እግዚአብሔር መጥፎ ሴቶችንና ጥሩ ሴቶችን አልፈጠረም፡፡ ወንዶች የሚመርጡት ከጥሩና ከመጥፎ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ማራኪና አስቀያሚ አልፈጠረም፡፡

ምርጫው በልዕልትና በእንቁራሪት መካከል አይደለም፡፡ እያንዳንዷ ሴት የሚስብ የሆነ ነገር አላት፡፡ የሚያሳዝነው እያንዳንዷ ቆንጆ ሴት አንዳንድ የማይስቡ ነገሮች አሏት፡፡ አንዳንድ ወንዶች ፍጹም የሆነችውን ሴት ስለሚፈልጉ ሽባ ሆነው ማለቂያ ወደሌለው ወንደላጤነት ይገባሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነት ነገር የለም፡፡ አንዳንድ ቆንጆ የሚባሉትም ከአስጠሊታ ባህሪ ጋር ይመጣሉ፡፡

ባልን ለሚወስኑ ሴቶችም ይሄ ሊባል ይችላል፡፡ ፍጹም የሆነ ወንድ ብሎ ነገር የለም፡፡ ውድ እህቴ ከሁለት ፍጹም ካልሆኑ ምርጫዎች አንዱን መምረጥ ይኖርብሻል፡፡ "ረጅም እና መልከመልካሙ" ከጭቅጭቅና ከመማታት ጋር አብሮ ሊመጣ ይችላል፡፡ "አጭር እና ወፍራሙ" ዕድሜ ልክ የገንዘብ እጥረትን ይዞ ሊመጣ ይችላል፡፡ ፊቱ የሚያስፈራው የሆነው ሰላምና መንፈሳዊነት አብሮት ሊመጣ

*ያንን ውሳኔ ወስን! ያም ሆነ ይህ ብዙ ውሳኔዎች ከሁለት መጥፎ አማርጮች አንዱን መምረጥ ስለሚጠይቁ!*

*ይችላል፡፡ ሕይወት እንደዚያ ነው! ሁለት በግልጥ የተለያዩ ነገሮች ስላልታዩህ ሽባ ሆነሽ ወደ ተግባር የለሽነት መግባት የለብሽም፡፡*

*ውሳኔ መወሰን አለብሽ! ከሁለቱ የተሻለውን ምረጪ፡፡ መምረጥ ሲያቅትሽ ምንም እንዳይኖርሽ መርጠሻል፡፡ ዛሬ ምንም የሌለሽ ለዚያ ሊሆን ይችላል፡፡*

# ኢየሱስ ይህንን አስተምሯል

*ሁለት እጅ ይዞ ገሃነም ከመግባት አንድ እጅ ያለው ሆኖ ወደ መንግሥተ ሰማይ መግባት እንደሚሻል ኢየሱስ በግልጥ ነግሮናል፡፡*

> **ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አ❶** ቢጠፋ ይሻልሃልና፡፡
>
> ማቴዎስ 5፡29

*ወደ መንግሥተ ሰማይ ባለአንድ እጅ ሆኖ መግባት ጥሩ ነገር አይደለም! ሁሉም ሰው እጆቹን ለአምልኮ ሲያነሳ አንተ አንድ እጅ ብቻ ነው የሚኖርህ! ቅዱሳን ሲያጨበጭቡ አንተ ደረትህን መምታት ይኖርብሀል! ያ በእውነት አሳዛኝ ነው!*

*ይሁንና ወደ ገሀነም መግባት ጭራሽ የባሰ ነው፡፡ ሁለት እጅ ወይም ሁለት እግር ያለው መሆን በገሀነም እሳት ውስጥ ለአንተ ምንም ትርጉም አይሰጥህም፡፡ ኢየሱስ ያስተማረን ከእነዚህ ሁለት አማራጮች የተሻለውን እንድንወስድ ነው፡፡ ኢየሱስ ገሀነምን ከሁለት እጅ ጋር ከምንመርጥ መንግሥተ ሰማይን ከአንድ እጅ ጋር እንድንመርጥ ነው ያስተማረን! አንዳንድ ሰዎች ያላደጉት ይህንን ጠቃሚ መርህ ስላልተረዱ ነው፡፡ በጥቂቱ መጥፎ የሆነውን ነገር ካልመረጡ የሚኖራቸው ሌላ አንድ የባሰ አማራጭ መሆኑን አይረዱም፡፡*

*ከዓመታት በፊት ቤተ ክርስቲያናችንን ከሕክምና ትምህርት ቤቱ መዝናኛ ተገፍታ እየወጣች ነበር፡፡ የኮርልቡ የማስተማሪያ ሆስፒታልን ለቀን እንድንወጣ ባለሥልጣናት ጫና እያደረጉብን ነበር፡፡ ከቆሻሻ መጣያና ከሚፈነዳ ሽንት ቤት አጠገብ ያለን አንድ ድቅቅ ያለና ጣሪያ የሌለው የሲኒማ አዳራሽ አገኘን፡፡ ጓደኞቼን እዚያ ወስጄ "ስለዚህ ቦታ ምን ታስባላችሁ?" አልኳቸው፡፡ ሁሉም በአንድ ላይ "በጣም የሚያስጠላ!" ሲሉ መለሱ ፡፡ ይሁንና መሪ እንደመሆኔ ከሁለት መጥፎ አማራጮች ጋር ተፋጠጥሁ፡፡ ይህንን አስጠያፊ የተጐሳቀለ ሕንፃ መውሰድና መግባት ወይም በመዝናኛው ውስጥ ቆይቶ ሊደርስ የሚችለውን የቤተ ክርስቲያኒቱን መፍረስ መጠባበቅ፡፡*

የበሰበሰውን ሕንፃ መረጥኩኝ፡፡ ያ ከአገልግሎቴ ምርጥ ውሳኔዎች አንዱ ነበር፡፡

ጥሩ መሪ መሆን ትፈልጋለህ? እንግዲያውስ በአብዛኛው ያሉት ሁለት መጥፎ ምርጫዎች ብቻ መሆናቸውን መረዳት አለብህ፡፡ ነገሮችን በጥልቀት የምትመረምር ሁን! በዚህ ፍጹም ባልሆነ ዓለም ውስጥ ብዙም አማራጭ እንደሌለህ በአፋጣኝ ልታስተውል ይገባል፡፡

አንዴ ወደሌላ ከተማ ለመዘዋወር የማይፈልግን አንድ መጋቢ አማከርኩት፡፡ ይህ ወንድም ሁለት አስቸጋሪ አማራጮች እንዳሉት ማየት አልቻለም፡፡ "አገልግሎትህን የመቀጠል እድልህ ይህ ነው" አልኩት፡፡ መዘዋወር ቀላል አይደለም፡፡ ወደ አዲስ ከተማ መሄድ ቀላል አይደለም፡፡ አብራራሁለት" ስምህ በዚህ ስለጎደፈ በአዳዲስ ቦታዎች ይበልጥ ተቀባይነት ታገኛለህ፡፡" "ለቀህ ወጥተህ አዲስ ጅማሬ መጀመር አለብህ….. እግዚአብሔር ሁለተኛ እድል እየሰጠህ ነው!" ብዬ ነገርኩት፡፡ ያለመታደል ሆኖ ይህ መጋቢ ሥፍራ መቀየሩ አገልግሎቱን በሙሉ ከማጣት የተሻለ አማራጭ መሆኑን ሊያይ አልቻለም፡፡ አልሰማ አለ፤ እናም መተረቻ እና መመሰያ እስኪሆን ድረስ አገልግሎቱ ተንኮታኮተ፡፡

## በሁለት ፍጹም ባልሆኑ አማራጮች መካከል ያሉ ውሳኔዎች ሰባት ምሳሌዎች

### 1. ማንን እንደምታገባ

እያንዳንዱ/ዷ የትዳር ጓዳኛ የሚመጣው/የምትመጣው ከራሱ/ሷ በረከቶችና ችግሮች ጋር ነው፡፡ የምትመርጠው/ጭው ከልዑል እና ከእንቁራሪት አይደለም፡፡

### 2. የት እንደምትኖር

እያንዳንዱ አገር የራሱ ጥቅሞችና ጉዳቶች አሉት፡፡ አውሮፓ ያደገች አህጉር ብትሆንም ለመኖር ብዙ ጫና ያለባትና አምላክ የለሽ ማህበረሰብ ያለባት አገር ናት፡፡ አፍሪካ በይበልጥ ፈሪሐ-እግዚአብሔር ያላቸው ሕዝቦች ያሏትና ብዙ ጫና የሌለበት አኗኗር ያለባት ብትሆንም ያላደገች አህጉር ናት፡፡

### 3. ምን እንደምተሠራ

ጠበቃ መሆን ሀብታም ሊያደርግህ ቢችልም ነዝናዣ ሰው ልትሆን ትችላለህ፡፡ ዶክተር መሆን ሊያበለፅግህ ቢችልም የሕይወትህን

*ያንን ውሳኔ ወስን! ያም ሆነ ይህ ብዙ ውሳኔዎች ከሁለት መጥፎ አማርጮች አንዱን መምረጥ ስለሚጠይቁ!*

አብዛኛውን ጊዜ የምታሳልፈው በሆስፒታል ውስጥ ስቃይና ሞትን እየተመለከተክ ይሆናል።

4. ምን እንደምትማር

አናጢነትን መማር ፈጠን ያለና አጭር ጊዜ የሚወስድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የኋላ ኋላ ይበልጥ አስቸጋሪ የሆነውንና የብዙ ዓመት ትምህርት የሚጠይቀውን ሕክምናን መማሩ ይበልጥ ትርፋማ ሊሆን ይችላል።

5. የት ቤተክርስቲያን እንደምትሄድ

ሁሉም ቤተ ክርስቲያን የራሱ ጥንካሬዎች አሉት። በቅባቱ የበረታ ነገር ግን በአስተምህሮ ደካማ በሆነ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሆን ይችላል ያለኸው። አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ምንም ተዓምራት የለባቸውም፤ ቃሉን ግን ያስተምራሉ።

6. ማንን መምረጥ እንዳለብህ

እያንዳንዱ የፖለቲካ ድርጅት የራሱ ጥሩ እና መጥፎ ጐኖች አሉት። በጥሩውና በመጥፎው መካከል እንደምትመርጥ በማሰብ አትታለል። ብዙ የፖለቲካ ምርጫዎች በሁለት መጥፎ አማራጮች መካከል ናቸው።

7. ምን ዓይነት መኪና መንዳት እንዳለብህ

የኮሪያ መኪና ሊረክስ ቢችልም እንደ ጀርመን መኪና ግን ጠንካራ አይደለም። የጃፓን መኪኖች እንደ ጀርመን መኪኖች ጠንካራ ባይሆኑም ለማሽከርከር የሚቀሉና ለጥገናም ብዙ ወጪ የማያስወጡ ናቸው።

ምዕራፍ 73

# የማይገቡ ነገሮችን በሕዝብ ፊት በመናገር አገልግሎትህን አታውድም

በአፍህ ቃል ተጠመድህ በአፍህ ቃል ተያዝህ።

ምሳሌ 6፡2

መሪ ስለሚናገራቸው ነገሮች ጥንቁቅ ሊሆን ይገባል። በቃሎችህ ትጠመዳለህ በቃሎችህ ትገመታለህ። የምትላቸውን ነገሮች ተጠንቀቅ።

ናባልም ለዳዊት ባሪያዎች። ዳዊት ማን ነው? የእሴይስ ልጅ ማን ነው? እያንዳንዳቸው ከጌቶቻቸው የኰበለሉ ባሪያዎች ዛሬ ብዙዎች ናቸው። እንጀራዬንና የወይን ጠጄን ለሸላቾቼም ያረድሁትን ሥጋ ወስጄ ከወዴት እንደ ሆኑ ለማላውቃቸው ሰዎች እሰጣለሁን? ብሎ መለሰላቸው።

1ኛ ሳሙኤል 25፡10፣11

ይህ ዓረፍተ ነገር ናባልን ሕይወቱን ሊያሳጣው ነበር።

ዳዊትም፦ ለዚህ ሰው ከሆነው ሁሉ አንድ ነገር እንዳይጠፋበት በእውነት ከብቱን ሁሉ በምድረ በዳ በከንቱ ጠበቅሁ፥ እርሱም ስለ በጎነቱ ክፋት መለሰልኝ።ለእርሱም ከሆነው ሁሉ እስከ ነገ ጥዋት ድረስ አንድ ወንድ ስንኳ ብተው፥ እግዚአብሔር በዳዊት ላይ እንዲህ ያድርግ እንዲህም ይጨምር ብሎ ነበር።

1ኛ ሳሙኤል 25፡21፣22

መሪ ከሆንክ ቃሎችህን በብዙ ጥንቃቄ ምረጥ። ምን እንደምትናገር ወይም እንዴት እንደምትናገረው የማታውቅ ከሆነ ምንም አትናገር። ሰዎች በቃልህ የሚይዙህን አጋጣሚ እየፈለጉ ነው። ስለ አንተ አንድ ጽሑፍ ሊጽፉብህ እና ያልሆንከውን አድርገው ሊያስቀምጡህ ይፈልጋሉ።

በአውሮፕላን በየትኛው ማዕረግ እንደምትሄድ ለሁሉም መናገር አስፈላጊ አይደለም። ለሰዎች የልብሶችህን ዋጋ መናገር አያስፈልግም። ለሚስትህ ምን እንደገዛህለት ለጉባዔው መናገር አያስፈልግህም። እነዚህን ነገሮች ሁሉም ሰው አያደንቅም። አንዳንድ ሰዎች በገንዘባቸው እየተቀማጠልክበት ስለሚመስላቸው ይጠሉሃል። የቅርብ ጓደኞችህ በሕይወትህ ያሉትን የእግዚአብሔርን በረከቶች

ሊያደንቁልህ ቢችሉም አብዛኞቹ ሰዎች ግን አገልጋዮች ድሀ መሆን እንዳለባቸው ይሰማቸዋል።

እኔ በጣም ግልፅ ሰው ነኝ። በአብዛኛው የማስበውን ያንኑ ነው የምናገረው። በዚህ ምክንያት ለቃለ መጠይቆችና ጋዜጠኞች ከነአካቴው አልገኝም። ለማይረቡ ጥያቄዎች የማይረቡ መልሶችን ወደ መስጠት መገፋፋት አልፈልግም። ሐዋርያው ጳውሎስ እንኳን በአንዳንድ ሰዎች ሞኝነት በመበሳጨቱ አንዳንዴ ይህንን ማድረግ ነበረበት።

በጥቂቱ ሞኝነቴ ብትታገሡኝ መልካም ይሆን ነበር፤ ቢሆንም በእርግጥ ታገሡኝ።

2ኛ ቆሮንቶስ 11፡1

የት እንደምኖር፣ ምን ዓይነት መኪና እንደምነዳና ቁርስ ምን እንደበላሁ ለመጠየቅ ብቻ ወደ ቃለ መጠይቅ መሄድ የሚገባኝ ምንም ምክንያት አይታየኝም። አገልጋዮች በተደጋጋሚ ይህንን ጥያቄ ሲጠየቁ ሰምቻለሁ፤ እነዚህ ጥያቄዎች ከንቱ እንደሆኑም አስባለሁ። በሕዝብ ፊት ትክክለኛውን ነገር የመናገርን ወይም በጭራሽ ምንም ያለመናገርን ጥበብ ተማር! መሪ ትክክለኛ ነገሮችን የሚናገር ሰው ነው። ተገቢውን ነገር በሕዝብ ፊት በመናገር አገልግሎትህን ገንባ።

ምዕራፍ 74

# አርቲፊሻል መሪ አትሁን እውነት የሆኑ የአመራር ክህሎቶችን አዳብር

## በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው አሥራ ስምንት ምልክቶች

1. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው ማነሳሳት ይችላል።
2. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው ያለ ዝግጅት መናገር ይችላል።
3. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው እምነቱን በተግባር ያውላል።
4. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው ተግባራዊ ነው።
5. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው ስሜታዊ ነው።
6. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው በምሳሌነት ይመራል።
7. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው ለእምነት ታላላቅ መሥዋዕትነቶችን ይከፍላል።
8. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው ጥሩ ምሳሌ ስለሆነ ራሱን በምሳሌነት ይጠቀማል።
9. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው በእግዚአብሔር የተበጀና እና የተሾመ ነው
10. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው የሚያምነውን ይናገራል።
11. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው ብዙ ጊዜ የሚተች ነው።
12. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው አነጋጋሪ ነው።
13. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው የእውነት ሸክም አለው።
14. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው የሚያሳስበው የእውነት የሆነው ነገር ነው።
15. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው ብዙ ክርክርና ገለፃ አይችልበትም፤ ወደ ሥራው መግባት ነው የሚፈልገው።

16. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው የሚያሳስበው የሚሰጠው የማዕረግ ስም ሳይሆን ሥራው ነው።
17. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው በገንዘብ አይነሳሳም።
18. በተፈጥሮ መሪ የሆነ ሰው ሰዎችን ይወዳል።

## ከልብ መሪ ያልሆነ ሰው አስራ አምስት ምልክቶች።

1. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው አሰልቺ ነው።
2. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው ብዙ ጊዜ ንግግር የሚያደርገው እያነበበ ነው።
3. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው ሴሚናሮችንና ኮንፈረንሶችን ቢያካሂድም ምንም እርምጃ አይወስድም።
4. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው ንድፈ ሀሳባዊ ነው (ተግባራዊ አይደለም)
5. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው ምንም ስሜት አይገልፅም።
6. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው ሁነኛ ንግግሮችን ያዘጋጃል፣ ትክክለኛ ነገሮችንም ይናገራል፤ ግን ምንም አያደርግም።
7. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው ራሱን በፍጹም እንደምሳሌ አይጠቀምም (ጥሩ ምሳሌ አይደለምና)።
8. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው በሰው የተበጀ እና በሰው የተሾመ ነው።
9. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው ሰዎች እንዲል የሚፈልጉትን ይላል።
10. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው በአብዛኛው ተወቃሽ አይደለም።
11. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው ተቀባይነት ያለውን አኳኋን ያሚላል።
12. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው እንደ ድርጅት እንጂ በእውነተኛ ሁናቴ ሸክም የለውም። ሰዎቹን አይወዳቸውም።

13. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው ስለሚካሄደው ሥነ ሥርዓት እንጂ ሥራው አያሳስበውም።

14. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው ስለ ማዕረግ ስም እጅግ ይጨነቃል።

15. በተፈጥሮ መሪ ያልሆነ ሰው በይበልጥ የሚያሳስቡት ደሞዝና ጥቅማጥቅሞች ናቸው።

## የተፈጥሮ አመራር ብቃትን እንዴት ማምጣት እንደሚቻል

1. አንድን አስተሳሰብ አብጅና የፀና አቋምን አዳብር።

ልተህ እንድትታይ የሚያደርግህ የፀና አቋምህ ነው።

2. የተፈጥሮ መሪዎችን ተመልከት

የተፈጥሮ መሪዎችን ተመልከት ደግሞም አድንቅ። የሚያደርጉትንና የማያደርጉትን ልብ በል። ከልብ ያልሆኑ መሪዎችን እያቸው፤ የሚያደርጉትን አታድርግ።

3. ከተፈጥሮ መሪዎች ጋር ህብረት አድርግ

ከታላላቅ መሪዎች ጋር ጥቂት ደቂቃዎች አብሮ የማሳለፍን እድል አያምልጥህ።

4. የተለያዩ የተፈጥሮ መሪዎችን ሕይወት አጥና።

5. በመጽሐፍቶቻቸውና በስብከት ካሴቶቻቸው አማካይነት ከታላላቅ መሪዎች ጋር ህብረት አድርግ።

6. ታላቅ የተፈጥሮ መሪዎችን አድምጥ።

# ምዕራፍ 75

# ድካም ማመካኛ እንዲሆን አትፍቀድ

አንድ ሰው "ዓለም የምትንቀሳቀሰው በደከማቸው ሰዎች ነው" ብሏል። እውነተኛ መሪ ካልሆንክ ሕይወትህን ለምንም ነገር አሳልፈህ አትሰጥም። መሪ ያልሆነ ለመስራት ዝግጁ አይደለም፤ ደክሞታልና። ድካም ማመካኛ እንዲሆን አትፍቀድ። ድካም ማመከኛ ከሆነ እንግዲያውስ አንተ መሪ መሆን አትችልም። የድካምን ማመካኛ ተጠቅሜ ቢሆን ኖሮ አሁን ያሳካሁትን ሰባ በመቶ እጅ እንኳን አላሳካም ነበር።

ኢየሱስ አለ፣ "መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።" (ዮሐንስ 10፡11) ድካም ሕይወትህን ለበጐች የመስጠት አካል ነው።

ሕይወትህን አሳልፈህ መስጠት እንደጀመርክ፣ ይህ ስለ አንተም ይናገራል። ሁሉም መሪ መዛል አለበት እያልኩ አይደለም። እያልኩ ያለሁት መሪነት እጅግ ዋጋን የሚጠይቅ መሆኑን ነው። አንዳንድ ጊዜ መሪ ያልሆኑ ሰዎች ስለ መድከም ሲያግቶመቱሙ አያለሁ። ማድረግ የሚፈልጉት ሁሉ መሄድ ነው።

ብዙ ሠራተኞች በቅጥር ቦታዎቻቸው ከደሞዛቸው በስተቀር ምንም የሚስባቸው ነገር አለመኖሩ የታወቀ እውነታ ነው።

እንደዚህ ዓይነት ሰዎች (በአብዛኛው መሪ ያልሆኑት) ከልክ በላይ ለመድከም የተዘጋጁ አይደሉም።

> ስለዚህም አንታክትም፥ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል።
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 4፡16

ይህንን መጽሐፍ እየፃፍኩ ባለሁበት ሰዓት እንኳን ዝያለሁ። ግን ማድረግ እንዳለብኝ አውቃለሁ። ጥሩ መሪ ብዙውን ሥራውን የሚሰራው በአብዛኛው በምስጢር ነው። እነዚህ የተደበቁ ሥራዎችና የማይታዩ ጫናዎች ናቸው መሪዎቻችንን የሚያደክሟቸው። የመዝናናትና የምቾት ሕይወት የምትፈልግ ከሆነ ምናልባት አንተ መሪ አይደለህም።

የአገር መሪዎች፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚዎችና ስመጥር መሪዎች በአብዛኛው በውብ የግል አውሮፕላኖች የሚንዙና ብዙ ጥቅማጥቅሞች የተሰጧቸው ተደርገው ይታያሉ። ሕይወቱን ለታላቅ ዓላማ ለሚሰጥ እውነተኛ መሪ እነዚህ ጥቅማጥቅሞች እጅግ ትንሽ ማካካሻ መሆናቸውን ላረጋግጥልህ እችላለሁ።

መሪ ነህ? ማለቂያ የሌለው ምቾትና የደስታ ሕይወት እየኖርህ ካለህ ምናልባት ከእውነተኛ መሪነት እየተሰናበትክ ነው።

## ምዕራፍ 76

# የቤት ውስጥ ሕይወትህን በብቃት ተወጣ

ጳውሎስ ለመሪነት ከሰጣቸው ቀዳሚ መስፈርቶች መካከል አንዱ ሚስት ያለው መሆንና የተገሩ ልጆች ናቸው፡፡ የአገልግሎት መስፈርቶች መሠረታዊና የቤት ውስጥ መሆናቸው የሚያስገርም ነው፡፡

> እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ የማይነቀፍ፥ የአንዲት ሚስት ባል፥ ልከኛ፥ ራሱን የሚገዛ፥ እንደሚገባው የሚሰራ፥ እንግዳ ተቀባይ፥ ለማስተማር የሚበቃ፥.....ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤
>
> ፩ኛ ጢሞቴዎስ 3፡2፣4

## የቤት ውስጥ ጉዳይህን በአግባቡ እያስተዳደርክ መሆኑን የሚያሳዩ ስድስት ምልክቶች

1. ሚስት ወይም ባል ያለው/ያላት የመሆን ምልክት
2. የተረጋጋ ቤት ያለው የመሆን ምልክት፡፡
3. ስኬታማ የሆነ ትዳር ያለው የመሆን ምልክት፡፡
4. በትምህርት ቤቱ ጥሩ ብቃት ያለው ተማሪ የመሆን ምልክት፡፡
5. አስተማማኝ የኢኮኖሚ የገንዘብ አቋም እና ከዕዳ ነፃ የመሆን ምልክት፡፡
6. የተረጋጋ ሥራ ያለው

በገዛ ቤትህ ሰላምና ሥርዓትን ማስፈን ችለሃል? ትዳርህ ስኬታማ ነው? ተማሪ ከሆንክ የትምህርት ሕይወትህን በሚገባ ለማስተዳደር ችለሀል?

የሕክምና ተማሪ ሳለሁ መጋቢ ነበረኩ፡፡ በፈተናዎቼ ጥሩ ውጤት ማመጣቴን አረጋግጥ ነበር፡፡ በትምህርት ቤት ምንም ችግር እንደሌለኝ አረጋግጥ ነበር፡፡ መሪነት የሚጀምረው የቤት ውስጥ ጉዳዮችህን በቁጥጥር ሥር በማድረግ ነው፡፡ የቤት ውስጥ ጉዳዮችህን ተመልከት፤ትምህርት ቤትህን፣ሥራህን፣ቤትህንና ትዳርህን እነዚህ በሥርዓት ካሉ እንግዲያውስ ወደ አመራር ጉዳና በጥሩ ሁኔታ እየተጓዝክ ነው፡፡

ምዕራፍ 77

# እውነተኛ እንጂ ግብዝ አትሁን

ኢየሱስ በሕይወት ሳለ የማይግባባቸው የሰዎች ቡድን ነበሩ። እነዚያም ግብዝ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ነበሩ።

> እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጡ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ፥ ወዮላችሁ።
>
> ማቴዎስ 23፡27

ፈጠነም ዘገየ አንተ የምትጠብቃቸውን የተለያዩ ደረጃዎች ሰዎች ያያሉ። ከውጭ ውበትን ከውስጥ ግን አስቀያሚነትን ይመለከታሉ። ይህ እያንዳንዱን ተከታይ የማሸሽ አቅም አለው። መሪ ተከታዮች እንዲኖሩት ይፈልጋል። ግብዝነት አስጸያፊ መጥፎ ምግባር ነው። በአጭር ጊዜ ተከታዮችህን ሁሉ የመበተን ኃይል አለው። በውጭ የምታደርገው በውስጥ የሆንከውን እንደሆነ እርግጠኛ ሁን።

ብዙ ልጆች ወላጆቻቸውን የማይታዘዙበት ምክንያት በቤት የሚያዩት ነገር ስለሚያበሳጫቸው ነው። ግብዝነትን ያያሉ። ወላጆቻቸው በሰው ፊት ጥሩ ጥሩ ሐሳቦችን ሲናገሩ ቢሰሙም በቤታቸው ግን የሞላው አስቀያሚነት ነው። ይህ ብዙ ልጆችን ለራሳቸው፡- በፍጹም እንደ አባቴ አልሆንም፣ ወይም እንደ እናቴ አልሆንም ብለው እንዲወስኑ ያደርጋል። ወላጆቻቸው ተስፋ ከሚያደርጓቸው ትላልቅ ነገሮች ዘወር ይላሉ። ራስህን መሪ አድርገህ ትቆጥራለህ? ከቁምሳጥንህ ሁሉን አፅሞች አስወግድ። ጥሩ ተከታዮች እንዲኖሩህ በውጭ የሆንከውን ያህል በውስጥህ ንፁህ ሁን።

ጥሩ መሪ ለረጅም ጊዜ አመኔታን ጠብቆ ማቆየት ይችላል። የሚያሳዝነው ጊዜ በሄደ ቁጥር ብዙ እምነት ይሸረሸራል። እግዚአብሔር ግን የሚናገሩትን የሚያደርጉና የሚያደርጉትን የሚናገሩ አዲስ የመሪ ዝርያዎችን እያስነሳ ነው።

## ምዕራፍ 78

# ውስንነቶችህን እወቅ

ሁሉም መሪ ውስንነቶች አሉት። እግዚአብሔር ልዕለ-ሰው አድርጎ አልሰራንም። ኢየሱስ እንኳን ሰዓቱ ሲያበቃ አውቋል። አጽናኙ ሥፍራውን የሚወስድበት ጊዜ ሲደርስ አውቋል። አጽናኝ ስለሆነው ስለ መንፈስ ቅዱስ መናገር ጀመረ። በሕይወታቸው ብዙ ለውጥ እንደሚያመጣ ቃል ገባላቸው። ያለመታደል ሆኖ ደቀ መዛሙርቱ ከኢየሱስ የተሻለ ምትክ ሊኖር እንደሚችል ማመን አልቻሉም።

> ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንዶቹ እርስ በርሳቸው። ጥቂት ጊዜ አለ፥ አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ፥ ታዩኛላችሁም፤ ደግሞ። ወደ አብ እሄዳለሁና የሚለን ይህ ምንድር ነው? ተባባሉ።
>
> ዮሐንስ 16፡7

ሥፍራውን የመልቀቂያ ጊዜአቸው እንደሆነ የሚያስተውሉ ምን ያህል መሪዎች ናቸው? ምን ያህል መሪዎች የተለየ ተሰጥዖ ያሏቸው ሌሎች መሪዎች እንደሚያስፈልጉ ለመቀበል ዝግጁ ናቸው? የምትሸለመው ጥሪህን በማሳካትህ ነው። ሌሎች የሰው ልጆችን በማስደነቅህ ሰማያዊ ሽልማት አትቀበልም።

> እንዲህም አላቸው፡- ራሳችሁን በሰው ፊት የምታጸድቁ እናንተ ናችሁ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ልባችሁን ያውቃል፤ በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኵሰት ነውና።
>
> ሉቃስ 16፡15

በዙሪያህ ያሉ ሰዎች የአድናቆት ፈገግታ በሰማዩ አባትህ ዕይታ ላይ ምንም ተፅዕኖ የለውም። ለዚያ ነው ሌሎች ስለእኔ የሚያስቡት በፍጹም ግድ የማይለኝ። ሰው ስለሆንኩ ለሰዎች እንግዳ ልሆንባቸው እችላለሁ። ብዙ የሕክምና ባልደረቦቼ እንግዳ አድርገው እንደሚያዩኝ ብዙ ጊዜ አስባለሁ። ግን ምን ለውጥ ያመጣል?

ከእንግዲህ ሰዎችን ለማስደሰት አትሞክር! ጌታን ለማስደሰት ሞክር። ሌሎች ሚናቸውን የሚጫወቱበት ጊዜ ሲደርስ ፍቀድላቸው። ሌሎችን አታፍናቸው። ራስህን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደሚገነባና የክርስቶስን አካል እንደሚያንጽ እይ።

ሁሉን ነገር ማድረግ እንደማትችል ተገንዘብ፡፡ ሌሎች የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ፍቀድላቸው፡፡  አንተም እነርሱም ትባረካላችሁ!

ሙሴ ሌሎች ሰባ ሰዎች በአገልግሎቱ እንዲረዱት ፈቀደ፡፡  ያ ውሳኔ በእርግጥ ሕይወቱን አራዝሞለታል፡፡

ኢየሱስ የአጽናኙን አገልግሎት ሲጠራ ሽንፈቱን እየተቀበለ መሆኑ አልነበረም፡፡ የአስተዳደርና ሥራ አስኪያጅነት ክህሎት የሚጎድላቸው አንዳንድ መጋቢዎች አሉ፡፡ ተገቢ የሆኑ ሰዎችን አገልግሎት ካላከልክ አገልግሎትህ ሊንኮታኮት ይችላል፡፡

ራስህን ታላቅ መሪ አድርገህ ትቆጥራለህ? ውስንነቶችህን ተቀበል፡፡

# ምዕራፍ 79

## ብርቱ ሁን

ሰዎችን መምራት ትፈልጋለህ? ብዙ ብርታት ያስፈልግሃል። በኢያሱ ምዕራፍ አንድ ላይ እግዚአብሔር ኢያሱን ጽኑ እንደሆነ ሶስት ጊዜ አደፋፍሮታል።

> ለአባቶቻቸው። እሰጣችኋለሁ ብዬ የማልሁላቸውን ምድር ለዚህ ሕዝብ ታወርሳለህና ጽና፥ አይዞህ። ነገር ግን ጽና፥ እጅግ በርታ ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ፥ አድርገውም በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል። ...በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፥ አይዞህ አትፍራ፥ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን?
>
> ኢያሱ 1፡6፤7፤9

ይህ የኢያሱ የመሪነት ሕይወት መጀመሪያ ነበር። የኢያሱ አገልግሎት እንዲሳካ ጽናት እጅግ ጠቃሚ መሆኑ ግልፅ ነው። ፍርሃት በተሞሉና በሚያሰጉ ሁኔታዎች ውስጥ ወደ ፊት መጓዝ ደፋር ሰው ይጠይቃል። ውጤቱ ምን እንደሆነ እግርጠኛ መሆን በማይቻልበት ሁኔታ ውስጥ ወደ ፊት መግፋት ጽናት ይጠይቃል። ውድቀት ትክክለኛ አማራጭ ሲመስል ብዙ ድፍረት ያስፈልግሀል።

ሽንፈት አንተን ለመቀበል ሽር ጉድ ሲል ወደ ድል ለማቅናት ደፋር መሆን አለብህ። ታዛቢዎች ውድቀታችንን እየተጠባበቁ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን። በአንድ የተወሰነ የተግባር አቅጣጫ ለመቀጠል ጽናት ይጠይቃል። ያለ ጽናት ራስህን መሪ ብለህ ልትጠራ አትችልም። አንድን ቤተ ክርስቲያን ወይንም ሥራ ለመጀመር ጽናት ይጠይቃል። ባይሳካስ? ባይሆንስ? አንድን አዲስ ሐሳብ ለመከተል ጽናት ይጠይቃል።

ጽኑ ሰዎች ብቻ ናቸው መሪ መሆን የሚችሉት። ስኬትም ሆነ ውድቀት ጽኑ በመሆን ላይ የተመሠረተ ነው። ለእውነት ለመቆም ጽናት ይጠይቃል። ብዙ ሰዎች አዳዲስ የአገልግሎት አሠራሮችን የማይሞክሩብት ምክንያት ድፍረት ስለሚጐድላቸው ነው። ለታመሙ ለመጸለይ ድፍት ይጠይቃል። መንፈስን ለማገልገል ድፍረት ይጠይቃል። ለመጀመር ብርታት ይጠይቃል! ማንም ባይፈወስስ? እግዚአብሔር የኢያሱን መንፈስ እንዲሰጥህ ጠይቀው። እጅግ ጽኑ ስትሆን ራስህን ወደ ታላላቅ ከፍታዎች እየተሸጋገርክ ታገኘዋለህ!

## ምዕራፍ 80

# ሰዎች ወደ አንድ ቦታ እንዲከተሉህ አድርግ

ኢየሱስ ሰዎች እንዲከተሉት ማድረግ ችሎ ነበር። በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለ መሪ ከሆንክ ሰዎች እንዲከተሉህ ማድረግ መቻል አለብህ። ይህንን እንዴት ልታደርግ ትችላለህ?

ኢየሱስም፦ በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው።

ማርቆስ 1፥17

## ሰዎች እንዲከተሉህ የምታደርግባቸው ሶስት ደረጃዎች

### 1. ራስህን ሁን

አንድ ወጣት ሰው አንድ ወጣት ሴትን እንድታገባው ሲጠይቃት እንድትከተለው ለማድረግ እየሞከረ ነው። ጥያቄው ከልብህ የመነጨ መሆን አለበት። ሚስቴን ሳጫት የሆነ ጽሑፍ አላነበብኩላትም። እጅግ ስኬታማ የሆኑ መሪዎች "እውነተኛ" የሆኑት ናቸው። ሰዎች ትክክል የሆነውን ነገር የሚናገር ፅሑፍ በማንበብ ንግግር ከሚያደርጉት ይልቅ በቀጥታ የሚናገሩ መሪዎችን መስማት ይወዳሉ። ማንም አስመሳይን መከተል አይፈልግም!

### 2. የምትሄድበትን ሙሉ በሙሉ እመንበት

አመራርህ እየፈጠረ ባለው ነገ ላይ እምነት (አመኔታ) ሊኖርህ ይገባል። ለአንድ ሴት የጋብቻ ጥያቄ ካቀረብክ ላንተም ለወጣቷ ሴትም መልካም ነገን እንደምትሰጥ ማመን አለብህ።

### 3. ሰዎች እንዲከተሉህ ወደምትፈልግበት አንተ ራስህ ሂድ

አንተ ራስህ የማትጸልይ ከሆነ ሰዎች እንዲጸልዩ ማድረግ አትችልም። ሰዎችን በጸሎት ፕሮግራሞች ላይ ጸሎት በመምራት ብቻ እንዲጸልዩ ማድረግ የሚቀል ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የእኔ ሰዎች ስጸልይ ሲያዩ ለመጸለይ እጅግ ይነሳሳሉ። ራሳቸው የሚያደርጉት ሌላ ነገር ሆኖ ሳለ አባሎቻቸው አንድን ነገር እንዲያደርጉ የሚያዙ መጋቢዎች በአብዛኛው ጥሩ ውጤትን አያገኙም።

# ምዕራፍ 81

# የበለጡ ተከታዮች ለማግኘት እውነትን ከጸጋ ጋር አዋህድ

*ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን።*

ዮሐንስ 1፡14

የኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅነት ያለው እውነትን ከጸጋ ጋር በማቅረቡ ውስጥ ነው። ያለ ጸጋ የሆነ እውነት አደገኛ ነው። ያለ ጸጋ የሆነ እውነት የክርስቶስን አብዛኛውን ተከታዮች ያጠፋቸዋል። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ግንኙነት የሚያደርገው በእውነት ላይ ብቻ ተመሥርቶ ቢሆን ኖሮ አብዛኞቹ ክርስትያኖች ወደ ድል አክሊሉ አይደርሱም ነበር። እስቲ እውነቱን እንነጋገር መጋቢዎቻቸው የሚያዟቸውን በእርግጥ የሚያደርጉ ምን ያህል ክርስቲያኖች ናቸው? ምን ያህል ክርስቲያኖች በፍቅር በመመላለስ እርስ በእርሳቸው ይቅር ይባባላሉ? ቤተ ክርስቲያን በስህተት የተሞሉ አባሎቿን ብታስወጣ አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ባዶ ይሆናሉ። ንጉስ ዳዊት ይህንን በመዝሙር 130፡3 ላይ በሚገባ ገልጦታል።

*አቤቱ፥ ኃጢአትንስ ብትጠባበቅ፥ አቤቱ፥ ማን ይቆማል?*

መዝሙር 130፡3

ጥሩ መሪ ከተከታዮቹ ጋር ባለው ግንኙነት ሁልጊዜ እውነትን ከጸጋ ጋር ቀላቅሎ ይጠቀማል። የእውነትና የጸጋ ውህድ አንዳንድ ተከታዮችህን እንዲስተካከሉና ታላቅ አገልጋዮች እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። ሆኖም ግን አንዳንድ ሰዎችን የእግዚአብሔር ጸጋም ቢሆን አይለውጣቸውም። በአገልግሎቴ ውስጥ የጸጋና የእውነት ድብልቅ በሕይወታቸው ላይ በመጠቀም ለመልካም የተለወጡ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች አሉ። ያለ ጸጋ የሆነ እውነት ብዙዎቹን ዛሬ አብረውኝ የሚሰሩትን ድንቅ አገልጋዮችና መሪዎች ያጠፋቸው ነበር።

# የጸጋ እና የእውነት ድብልቅ አጠቃቀም አራት ምሳሌዎች

## 1. ኢየሱስ ስለ ይሁዳ እውነቱን ቢያውቅም ከጸጋ ጋር አጣመረው

ኢየሱስ ይሁዳ ከዳተኛ የመሆኑን እውነታ ያውቅ ስለነበር ሊነሳበት ይችል ነበር! ኢየሱስ ይሁዳ ከእግዚአብሔር ጸጋ እንዲጠቀም ፈቀደለት

ለይሁዳ እድል ለመስጠት እውነትን ከጸጋ ጋር ቢያቀላቅልም ይሁዳ ግን ራሱን በማውደም አበቃ።

ዕጣ ፈንታቸው ያ ከሆነ ሰዎች ራሳቸውን እንዲያፈርሱ እተዋቸዋለሁ ምንንም ነገር ለማረጋገጥ አልቸኩልም። ሰዎች በስተመጨረሻ እንደሚስተካከሉ ወይም ራሳቸውን እንደሚያጠፉ አምናለሁ። ሰዎች በመጋቢዎች ላይ ክስ ይዘው ወደ እኔ ሲመጡ "ይህንን ሰው ባፋጥጠው ክሱን ይክዳል፡፡ ለእግዚአብሔር ጸጋና ለጊዜ እንዲሁ እተወዋለሁ። ራሱን ማጥፋት ዕጣ ፈንታው ከሆነ ራሱን ያጠፋል። ራሱን ማስተካከል ዕጣ ፈንታው ከሆነ ያንኑ ያደርጋል!" እላቸዋለሁ።

## 2. ኢየሱስ ስለ ጴጥሮስ እውነቱን ቢያውቅም ከጸጋ ጋር አዋሃደው።

ኢየሱስ ጴጥሮስ ለሰይጣናዊና ዓለማዊ ተፅዕኖ የተጋለጠ መሆኑን ቢያውቅም ከእርሱ ጋር መሥራቱን አላቋረጠም። ኢየሱስ ከጴጥሮስ አልተነጠለም።

> እርሱ ግን ዞወር ብሎ ጴጥሮስን። ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።
>
> ማቴዎስ 16፡23

ኢየሱስ ስለ ጴጥሮስ እውነቱን ያውቅ ነበር፡- በጸሎት ፕሮግራሞች (ስብሰባዎች) ላይ ይተኛ እንደነበር። የእግዚአብሔር ጸጋ ግን ኢየሱስ ከጴጥሮስ ጋር መሥራቱን እንዲቀጥል ፈቀደለት። ኢየሱስ ከጴጥሮስ ፀባየ ደካማነት አሻግሮ ይመለከት ነበር።

> ወደ ደቀ መዛሙርቱም መጣ፤ ተኝተውም አገኛቸውና ጴጥሮስን። እንዲሁም ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት እንኳ ልትተጉ አልቻላችሁምን?
>
> ማቴዎስ 26፡40

ኢየሱስ ስለ ጴጥሮስ እውነቱን ያውቅ ነበር። ኢየሱስ ጴጥሮስ እንደሚክደው ቢያውቅም ከእርሱ ጋር መስራቱን ቀጥሎ ነበር። ኢየሱስ ራሱን ከጴጥሮስ አልነጠለም። ማረው።

ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰለት። ነፍስህን ስለ እኔ ትሰጣለህን? እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሦስት ጊዜ እስክትክደኝ ድረስ ዶሮ አይጮኽም።

ዮሐንስ 13፡38

ኢየሱስ አገልግሎትን ትቶ ወደ ዓለማዊ ሥራ እንደሚንሸራተት ስለ ጴጥሮስ እውነቱን ያውቅ ነበር። ጴጥሮስ ያንን ሁሉ ስልጠና ወስዶ ሲያበቃ አገልግሎቱን ትቶ አሣ ወደ ማጥመድ ተመለሰ። ኢየሱስ ለጴጥሮስ ያለውን ዕቅድ አለወጠም።

ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ገና ተገለጠላቸው፤ እንዲህም ተገለጠ። ስምዖን ጴጥሮስና ዲዲሞስ የሚባለው ቶማስ ከገሊላ ቃና የሆነ ናትናኤልም የዘብዴዎስም ልጆች ከደቀ መዛሙርቱም ሌሎች ሁለት በአንድነት ነበሩ።

ዮሐንስ 21፡2፣3

እነዚህ ሁሉ የጴጥሮስ መጥፎ ነገሮች እውነት ቢሆኑም የክርስቶስ ውበት ከጸጋ ጋር በሚቀርብ እውነት ውበት ነው ያለው። እኛም ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጅን ክብር አየን። በስተመጨረሻ ጴጥሮስ የቤተ ክርስቲያን ታላቅ መሪ ሆነ። እውነት ከጸጋ ጋር ሲጣመር ማድረግ የሚችለው ይህንን ነው።

## 3. ኢየሱስ ስለ ቶማስ እውነቱን ቢያውቅም ከጸጋ ጋር አዋሃደው።

ቶማስ ክርስቶስ ከሙታን ሊነሳ እንደሚችል አላመነም ነበር። ኢየሱስም ይህን ያውቅ ነበር። ስለዚህ ታላቅ ሐዋርያ ያለው እውነታ በትንሳዔው አለማመኑ ነበር። የእግዚአብሔር ጸጋ አማኝ እንዲሆን ለቶማስ ሌላ ዕድል ሰጠው። እናም አመነ። የእውነትና የጸጋ ድብልቅ ሌላ ጽኑ ተከታይን ወለደ።

ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደግመው በውስጥ ነበሩ፥ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ። ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ። ሰላም ለእናንተይሁን አላቸው። ከዚያም በኋላ ቶማስን። ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው። ቶማስም። ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።

ዮሐንስ 20፡26-29

## 4. ኢየሱስ ስለ አሥሩ ደቀ መዛሙርት እውነቱን ቢያውቅም ከጸጋ ጋር አዋሃደው።

ኢየሱስ ስለደቀ መዛሙርቱ እውነቱን ያውቅ ነበር። እጅግ በሚፈልጋቸው ሰዓት እንደሚከዱት ያውቅ ነበር።

... በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተውት ሸሹ።

ማቴዎስ 26፡56

ኢየሱስ እንደሄደ አብዛኞቹ ደቀ መዛሙርቶች በፊት ወደሚሠሩባቸው ሥራዎች ተመልሰው ነበር።

እንዲህም ተገለጠ። ስምዖን ጴጥሮስና ዲዲሞስ የሚባለው ቶማስ ከገሊላ ቃና የሆነ ናትናኤልም የዘብዴዎስም ልጆች ከደቀ መዛሙርቱም ሌሎች ሁለት በአንድነት ነበሩ። ስምዖን ጴጥሮስ፦ ዓሣ ላጠምድ እሄዳለሁ አላቸው። እርሱም፦ እኛም ከአንተ ጋር እንመጣለን አሉት። ወጥተውም ወደ ታንኳይቱ ገቡ በዚያችም ሌሊት ምንም አላጠመዱም።

ዮሐንስ 21፡2፣3

የእግዚአብሔር ጸጋ ኢየሱስ የተከታዮቹን ፀባየ ደካማነት፣ ድክመትና ስህተቶች ችላ እንዲል አስችሎታል። ከጥፋቶቻቸው አሻግሮ በመመልከት ሰዎቹን ኃይለኛ ሐዋርያት እንዲሆኑ አስችሏቸዋል። የተከታዮችህን ጥፋቶች አይተህ የምታልፍ ከሆነ አብረሃቸው ሥራ፣ ጸልይላቸውም፤ የበዛ ፍሬ ታፈራለህ።

## መሪነት ስህተቶችን በይቅርታ የማለፍ ጥበብ ነው

መሪነት ጥፋቶችን በይቅርታ የማለፍ ጥበብ በሚልም ሊገለፅ ይችላል። የሌሎችን ጥፋቶች፤ ስህተቶችና ጉድለቶች ሆን ብሎ መተው ካልተቻለ በብቃት መምራት የማይቻል ነው ማለት ይቻላል። ይህም እግዚአብሔር መላእክትን ሳይሆን ሰዎችን እንድትመራ ስለጠራህ ነው። እግዚአብሔር የመላእክትን ቡድን እንድትመራ ከጠራህ ምንም ጥፋቶችን ማለፍ አያስፈልግህም። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለምን የሌሎችን ስህተቶች ማለፍ እንደሚቸግራቸው ይገርመኛል።

ጉድለቶቼን ስለቻሉ አሁንም ስለሚችሉ ሰዎች ጌታን አመሰግነዋለሁ። አብሬአቸው የምሰራ ብዙ ጥሩ ሰዎች ጉድለቶች አሉባቸው። ጉድለታቸውን አለማየቴ አይደለም፤ ያንን ደረጃ በዕድገት እንዲያልፉት ብዙ ዕድሎችን ልሰጣቸው እንደሚገባ እረዳለሁ። እንዳይነካ የነገርከውን ነገር ልጅህ ስለነካ እጁን ብትቆርጠው መቼም ቢሆን ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ ወደ መሆን ያድጋል? ጉልማሳ

በሚሆንበት ጊዜ እጅም ሆነ እግር አይኖረውም፤ ምክንያቱም በልጅነቱ ለሚሰራቸው የትየለሌ ስህተቶች አካላቱን ሁሉ ቆርጠህ ትጨርስ ይሆናል! መሪ ጉልህ ጥፋቶችን ሆን ብሎ በማለፍ ሰዎች ታላቅ እንዲሆኑ እድል የሚሰጥ ሰው ነው።

እየለፋህባቸው ባለኸው ሰዎች ላይ ተስፋ አትቁረጥ። መጪውን ጊዜ በመመልከት የዘራኸው ሁሉ በእርግጠኝነት እንደሚታጨድ ዕወቅ። ሰዎችን በማስተማርና በማሰልጠን ጊዜ ከፊጀህ ኃላፊነት የሚሰማቸው መሪዎች ወደ መሆን ያድጋሉ። በሰዎች ሕይወት ላይ ከሠራህ በእርግጠኝነት የሆነ ነገር ያፈራል። በምታምናቸው ሰዎች ጉድለቶች አትዋጥ። ጊዜ ስጠው። መሪ አባት ነው። ሁሉም አባት ደግሞ ልጁ አንድ ቀን ታላቅ ሰው እንደሚሆን ያምናል።

ምዕራፍ 82

# ስምንቱ የመሪ ታላላቅ ውሳኔዎች

## 1. ዳግም መወለድ

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው። የሕይወትህ የመጀመሪያው ውሳኔ ኢየሱስን እንደ አዳኝህ መቀበል ነው። ሌላው ውሳኔ ሁሉ ሞኝነት ነው።

## 2. የተሰጠ ክርስቲያን መሆን

ብዙ ምርጫዎች አሉህ። ለትምህርት፣ ለፖለቲካ ወይም ለስፖርት የተሰጠህ መሆን ትችላለህ። ጊዜውንና ጉልበቱን በመስጠት ለክርስቶስ የተሰጠ ለመሆን የሚመርጥ ሰው ከሕይወቱ ታላቅ ውሳኔዎች አንዱን እንደወሰነ ይገባዋል።

## 3. መጽሐፍ ቅዱስን ከሁሉም ይልቅ ይበልጥ ጠቃሚ መጽሐፍህ ማድረግ

የምታውቃቸውን መጻሕፍት በሙሉ በስተግራህ አስቀምጥ፤ መጽሐፍ ቅዱስን ግን ለብቻው በስተቀኝህ አስቀምጥ፤ መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ምድር ካለ ከማንኛውም ሌላ መጽሐፍ የተለየ ነው።

ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ "ዘ ኒው ቴስትመንት ዶክመንትስ" በተሰኘው መጽሐፍ ገፅ አሥራ አምስት ላይ እንዲህ ብሏል። "የአዲስ ኪዳናችን ማስረጃ ማንም ሰው ትክክለኛነቱን ለመጠራጠር ለማያልመው ለጥንት ሮምና ግሪክ ጽሑፎች ከሚቀርበው ማስረጃ እጅግ በጣም የላቀ ነው። አዲስ ኪዳንም የዓለማዊ ጽሑፎች ስብስብ ቢሆን ኖሮ እውነትነታቸው በጠቅላላው ከጥርጥሬ ውጪ ነው ይባል ነበር። ብዙ የሥነ መለኮት ምሁራን ይልቅ የታሪክ አጥኚዎች በአብዛኛው አዲስ ኪዳንን ለማመን ይበልጥ ዝግጁ የመሆናቸው ለምን የሚያስብል እውነታ ነው።"

## 4. ትክክለኛውን ሰው ማግባት

ማንን እንደምታገባ መወሰን በራሱ ተግዳሮት መሆኑን ትደርስበታለህ። ያ ውሳኔ መቼም ቢሆን ከምትወስናቸው እጅግ ጠቃሚ ውሳኔዎች አንዱ ነው።

## 5. ትክክለኛውን ቤተ ክርስቲያን መምረጥ

ያለህበት ቤተ ክርስቲያን ይሄ ነው የማይባል ልዩነት ያመጣል።

## 6. ትክክለኛውን ሰው መከተል

ብታምንም ባታምንም ሁሉም ሰው ሌላን ሰው ይከተላል። ሁላችንም የምናወራላቸው ወይም የማናወራላቸው ጀግኖች ወይም አማካሪዎች አሉን። የምትመርጠው በሕይወትህ ትልቅ ልዩነት ያመጣል። ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን አባላቱን እንዲከተሉት ነግሯቸዋል።

> እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡1

> በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ፥ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን።
>
> ዕብራውያን 6፡11-12

## 7. በመሐከላቸው የምትኖረው ትክክለኛ ከተማ፣አገርና ሕዝቦች መምረጥ።

ስኬትህ ከሥፍራ ጋር የተያያዘ እስከሆነ ድረስ፣ የት እንደምትኖር የምትመርጠው ምርጫ እጅግ ጠቃሚ ነው። ይህንን ውሳኔ በሕይወትህ እጅግ አስቀድመህ ወስን ፤ እንደመሪ ታላቅ ስኬትን ትለማመዳለህ።

## 8. ጓደኞችህን መምረጥ

የጓደኛ ምርጫህ በሕይወትህ ከምትወስናቸው እጅግ ጠቃሚ ውሳኔዎች አንዱ ነው። ወደድክም ጠላህም ጓደኝነቶችህ ነገህን ይቀርፃሉ። ጓደኞችህን አሳየኝና የወደ ፊትህን እተነብያለሁ።

# ምዕራፍ 83

# መካሪዎችህን በጥንቃቄ ምረጥ

መካሪ ማለት ለአንተ አማካሪ፣ መሪ፣ የግል አማካሪ፣ አስተማሪ እና አስጠኝ የሆነ ሰው ማለት ነው። መካሪህ የወደፊትህ ሥዕል ነው። የወደፊቱን የመተንበያ ብዙ መንገዶች አሉ። ከእነዚህ አንዱ የአንድን ሰው መካሪ መመልከት ነው። ኢያሱን ብታይ መካሪውን ሙሴን በመመልከት የወደፊቱን መተንበይ ትችላለህ። መካሪያቸውን ኢየሱስን በመመልከት የጴጥሮስን፣ የያዕቆብን የዮሐንስን የወደፊት መተንበይ ትችላለህ። አሰልጣኙን ኤልያስን በመመልከት የኤልሳን የወደፊት መተንበይ ትችላለህ።

እኔን ያሰለጠኑኝ ብዙ ሰዎች አሉ። በሕይወቴ እንዲኖሩ የማልፈልጋቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ። ከእኔ በቀደሙ ሰዎች ውስጥ አያቸዋለሁ። በዚህ ምክንያት ማን እንደሚቀርፀኝ በጥንቃቄ ነው የምመርጠው። ረጅም ዕድሜ የኖረ፣ ብዙ ያሳካ፣ በታማኝነት ለጌታ የሰራ እና በትዳር ውስጥ በስኬት የቆየ ጥሩ መካሪ ይሆናል።

## መሪ ስለ ስልጠና ሊያውቅ የሚገባው ስምንት ነገሮች

### 1. ስኬታማ የሆነ ሰው ሁሉ ያንተ አማካሪ ሊሆን አይችልም

በዓለም ያለ ሰው ሁሉ ያንተ አማካሪ ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር እንዲያሰለጥኑህ የተወሰኑ ሰዎችን መርጧል።

### 2. በርቀት ልትሰለጥን ትችላለህ

የማያውቅህ ሰው እንኳን ሊያማክርህ ይችላል። ያሉኝ አብዛኞቹ መካሪዎቼ በአካል እንኳን አያውቁኝም። በመጻሕፍቶቻቸውና በስብከት ካሴቶቻቸው አማካኝነት አሰልጥነውኛል።

### 3. አማካሪህን በመመልከት የወደፊትህን መተንበይ ይቻላል።

የጴጥሮስን፣ የያዕቆብንና የዮሐንስን አስተማሪያቸውን ኢየሱስን በመመልከት ስለወደፊታቸው መተንበይ ትችላለህ።

## 4. ለአሰልጣኝህ ባለህ ቅርበት ልክ በበለጠና ባነሰ ሁኔታ ልትሰለጥን ትችላለህ፡፡

ኢየሱስ በሁሉም ሰው ላይ ተመሳሳይ ተፅዕኖ አልነበረውም፡፡ ከሙታን ከተነሳ በኋላ የተገለጠላቸው አምስት መቶ ሰዎች ነበሩት፡፡ በሰገነት ላይ ሆነው መንፈስ ቅዱስን ይጠባበቁ የነበሩ መቶ ሃያ ሰዎች ነበሩት፡፡ በሄደበት የሚከተሉት ደግሞ አሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ነበሩት፡፡ በግል ንብረታቸው ያገለግሉት የነበሩ ደግሞ እጅግ ብዙ ሴቶች ነበሩት፡፡

> ከዚህም በኋላ እየሰበከና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች እየተናገረ በየከተማይቱ በየመንደሩም ያልፍ ነበር፤አሥራ ሁለቱም ከእርሱ ጋር ነበሩ፥ ከክፉዎች መናፍስትና ከደዌም ተፈውሰው የነበሩ አንዳንድ ሴቶች፤ እነርሱም ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የምትባል ማርያም፥የሄሮድስ አዛዥ የኩዛ ሚስት ዮሐናም ሶስናም ብዙዎች ሌሎችም ሆነው በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር።
>
> ሉቃስ 8፡1-3

ደግሞ በምድር ላይ ባሉት የመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ከመስቀሉ ሥር ቆመው የነበሩት እናቱ ማርያምና መግደላዊት ማርያም ነበሩት፡፡ በውስጠኛው ክፍል ደግሞ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ነበሩ፡፡ የቡድኑ መሪ የነበረው ደግሞ ጴጥሮስ ነበር፡፡ በተለይ ይወደው የነበረው ደግሞ ዮሐንስ ነበረው፡፡

## 5. ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባህሪያት ማለት ይቻላል አሰልጣኝ ነበራቸው፡፡

ሀ. የኢየሱስ አሰልጣኝ አብ ነበር

ለ. ኢየሱስ የጴጥሮስ የያዕቆብና የዮሐንስ አሰልጣኝ ነበር

ሐ. የኢያሱ አሰልጣኝ ሙሴ ነበር

መ. የኤልሳ አሰልጣኝ ኤልያስ ነበር

## 6. ኩሩ ሰውን ማሰልጠን አትችልም፡፡

ከሌላ ለመማር እጅግ ኩሩ ከሆንክ መሰልጠን አትችልም፡፡

## 7. ተፈጥሯዊና መንፈሳዊ አሰልጣኞች አሉ፡፡

ሙሴ በፈርዖን የተፈጥሮ ስልጠና አግኝቷል፡፡ ስለ መሪነትና ስለ መንግሥት ከፈርዖን ተምሯል፡፡ ዳዊትም ሰይጣን በተጠናወተው በአሰልጣኙ በሳዖል አደባባዮች አመራርንና መንግሥትን ተምሯል፡፡

እነዚህ አገልጋዮች በተፈጥሮ ነገሮች ለማሰልጠን ከእግዚአብሔር የተሰጡ የተፈጥሮ አሰልጣኞች ነበሩ፡፡ ከዚህ ተፈጥሯዊ ልምምድ በኂላ መንፈሳዊ ልምምድ ይቀጥላል፡፡ እኔ የተፈጥሮ ልምምዴን ያገኘሁት ከወላጆቼና ከቀለም ትምህርቴ ነው፡፡

የሕክምና ስልጠናዬ ለአገልግሎት ዝግጅቴ ወሳኝ የሆነውን አካል አሟልቶልኛል፡፡

## 8. አሰልጣኝህ የሰው ልጅ ነው

ጥሩውን ወስደህ መጥፎውን ጣል፡፡ ምግብ ሲቀርብልህ በሰሀኑ ላይ ያለን የሆነን ነገር የማትወደው ከሆነ የምትወደውን በልተህ ሌላውን ትተወዋለህ!

## ምዕራፍ 84

# ሰዎችን አነሳሳ

*ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም፤እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላችሁ።እንዲሁ እየደከማችሁ ደውዮችን ልትረዱና እርሱ ራሱ። ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው እንዳለ የጌታን የኢየሱስን ቃል ልታስቡ ይገባችሁ ዘንድ በሁሉ አሳየኋችሁ።ይህንም ብሎ ተንበርክኮ ከሁላቸው ጋር ጸለየ።ሁሉም እጅግ አለቀሱ፥ ጳውሎስንም አንገቱን አቅፈው ይስሙት ነበር፤*

የሐዋርያት *ሥራ* 20፡33-37

**መሪ በዙሪያው ያሉትን ሰዎች የሚያነሳሳ ሰው ነው። የሰው ልጆች ስሜታዊ ናቸው! የየትኛውም ምርጫ ማለት ይቻላል፣ ውጤቶችን ጠጋ ብለህ ብታጠና ሰዎች በስሜት ድምፅ እንደሚሰጡ ትደርስበታለህ። የአገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች በተርታ ለአንድ ሰው ነው ድምፃቸውን የሚሰጡት።**

**እውነተኛ መሪ የሰዎችን ስሜታዊ ተፈጥሮ በመገንዘብ ሰዎችን በዚያ መረዳት መምራት አለበት። ሰዎችን እንዲከተሉህ በሚቀሰቅስ መንገድ መናገር መቻል አለብህ ንግግሮችህ ሕይወት አልባና ስሜት አልባ ከሆኑ ሰዎችን እንዴት ሕይወታቸውን ለጌታ እንዲሰጡ መምራት ትችላለህ? ጳውሎስ ንግግሩን ከጨረሰ በኂላ ሰዎች እንዴት እንዳለቀሱ አስተውል።**

*ሁሉም እጅግ አለቀሱ፥ ጳውሎስንም አንገቱን አቅፈው ይስሙት ነበር፤*

የሐዋርያት *ሥራ* 20፡37

**የሚቀሰቅስና አነሳሽ መሪ ለመሆን ወስን። ሕይወት አልባ የሆኑ ንግግሮችህን ዘወር አድርግና ከልብህ ተናገር። ይህንን ያለምንም ችግር በቀላሉ ስታደርግ ራስህን እስክታገኘው ድረስ ተለማመደው። አስተውል፣ ይህንን ለማድረግ ከልብህ ልትንቀሳቀስ ይገባሃል። ጴጥሮስ አለ፡-**

*ጴጥሮስ ግን። ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ አለው።*

የሐዋርያት *ሥራ* 3፡6

**አንተ ራስህ የተነሳሳህ ካልሆንክ ሰዎችን ልታነሳሳ አትችልም። ስለምታደርገው ነገር አንተ ራስህ ስሜታዊ ካልሆንክ የማንንም ስሜት ልትነካ አትችልም።**

ምዕራፍ 85

# መፍትሔዎችን በማግኘት ችግሮችን ፍታ

መፍትሔ ማግኘትና ችግሮችን መፍታት ከሌሎች ሰዎች ይለይሀል፡፡ ጉዞ ሳደርግ አብረውኝ ለሚሰሩት ከምሰጣቸው የመጨረሻ መመሪያዎች አንዱ፡- “ችግሮችን ፍቱ፣ እመለሳለሁ” ነው፡፡ ችግሮችን የሚፈቱ ሰዎች ስላሉኝ ደስተኛ ነኝ፡፡ የምትሰጠው የትኛውም ትእዛዝ ተያይዘው የሚመጡ ችግሮች አሉት፡፡ ችግሮችን ከጅምሩ ማቃለል የሚችል ሰው በእውነት ጠቃሚና በእውነት መሪ ነው!

የሥራ ኃላፊነት ስሰጥ አሳክቶት ወደ እኔ እንዲመለስ እጠብቅበታለሁ፡፡ የሚያሳዝነው ብዙ ተቀጣሪዎች ጭራሽ ብዙ ችግር ይዘው ይመጣሉ፡፡ አንዳንዴ ስለገጠማቸው ችግር ሁሉ ሊነግሩኝ በአግራሞት እመለከታቸዋለሁ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እነዚያን ችግሮች ፈትተው ከውጤት ጋር እንዲመጡ ብቻ እነግራቸዋለሁ፡፡

የተቀጣሪ ታላቅነት በሥራው ላይ ለሚፈጠሩ ችግሮች በሙሉ መፍትሄዎቹን የማግኘት ችሎታው ነው፡፡

የሙሴ ኃላፊነት ሕዝቡን ከግብፅ አውጥቶ ተስፋ ወደተገባችላቸው ምድር ማስገባት ነበር፡፡ በእርግጥ ብዙ ችግር ውስጥ ገብቷል፡፡ በመጀመሪያ ቀይ ባህር፣ ከዚያ ደግሞ ውኃ አልነበረም፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ ምግብ አልነበረም፡፡ ከዚያም ውኃ አገኙ፤ ነገር ግን መራር ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ደግሞ ሙሴ አስተዳደራዊ ችግሮች ገጠሙት፡፡ ሰዎች ቅሬታ ማቅረብና ማጉረምረሙ ጀመሩ፡፡ ከዚያም የቅጥረኞችና የዘመዶቹ አለመገዛት ችግር ነበሩበት፡፡ እንደምታየው እንግዲህ ሙሴ ሕዝቡን ከግብፅ አውጥቶ ለመምራት ብዙ ዓይነት ችግሮች መፍታት ነበረበት፡፡

ዓለምም እንዲሁ ሊፈቱ የማይችሉ ችግሮች የሞሉባት ናት፡፡ በየሥፍራው ችግሮች አሉ፤ በየመታጠፊያው አስቸጋሪ ነገሮች አሉ፡፡ ሁሉም ሰው ወደፊት የሚያራምዳቸውን ሰው እየፈለጉ ነው፡፡

ሙሴ ቀይ ባህር ጋር ሲቆም ከአደጋ ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጠ፡፡ እየገሰገሱ የነበሩት የግብፅ ሠራዊት ማጅራቱ ላይ እየተነፈሱበት ነበር፡፡ እንዴት ወደፊት መንገድ ሊኖር ይችላል? ሙሴ ግን መፍትሔ አገኘ፡፡

ሙሴም በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ እግዚአብሔርም ሌሊቱን ሁሉ ጽኑ የምሥራቅ ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን አስወገደው፥ ባሕሩንም አደረቀው፥ ውኃውም ተከፈለ።የእስራኤልም ልጆች በባሕሩ መካከል በየብስ ገቡ ውኃውም በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆነላቸው።

ዘጸአት 14፡21፤22

መጋቢ ከሆንክ ከሚገጥሙህ ከባድ ችግሮች አንዱ ቤተ ክርስቲያንህን እንዴት ማሳደግ እንዳለብህ ነው። ሕዝቡን ወደ ዕድገትና ብልፅግና ለመምራት መጣር አለብህ። ቀላል ባይሆንም የመሪ ሥራ ግን ይህ ነው። ስኬታማ መጋቢ ቤተ ክርስቲያንን የማሳደግን ችግር የፈታ ሰው ነው።

ነጋዴ ከሆንክ ጠንካራ ውድድር ባለበት ትርፍ የማፍራት ችግር ይገጥምሃል። የአንተ ሥራ ድርጅትህን ወደ ስኬት መምራት ነው። የፖለቲካ መሪ ከሆንክ በሁሉም ደረጃ ሙስና፣ የሠራተኞች አመፅና ክህደት ይገጥምሀል። ከተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ውስጥ እንዴት አንድ መልካም ነገር ልትፈጥር ትችላለህ? መፍትሔዎችን ማግኘትና ችግሮችን መፍታት የመሪው ሥራ መሆኑን አስታውስ።

## መፍትሔ የማግኘትና ችግሮችን የመፍታት ዋና ቁልፍ

ዋናው ቁልፍ ጥበብ ነው። ሰለሞን እጅግ ጠቢብ ሰው እንደነበርና በዓለማችን ከኖሩ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ባለጠጋ ሰው እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። የተረጋጋ የፖለቲካ መሪ ሆነ። በአገዛዙ ውስጥ ሰላምና መረጋጋት ነበረ። እነዚህ ነገሮች የመጡት በእግዚአብሔር ጥበብ ነበር።

ጥበብ ችግሮችን መፍታት ይችላል? መጽሐፍ ቅዱስ በአስጊ ሁኔታ ውስጥ ስለነበረች አንድ ከተማ ይነግረናል። የጠላት ጦር ስለከበቧት ማንም ተስፋ አልነበረውም። ይሁንና ነፃነት ለከተማዋ በአንድ ጠቢብ ነገር ግን ደሀ በሆነ ሰው በኩል መጣላት። በማይሆን ሁኔታ ውስጥ መፍትሔ የሚመጣው በጥበብ አማካኝነት ነው።

ታናሽ ከተማ ነበረች፥ ጥቂቶች ሰዎችም ነበሩባት ታላቅ ንጉሥም መጣባት ከበባትም፥ ታላቅ ግንብም ሠራባት።ጠቢብ ድሀ ሰውም ተገኘባት፥ ያችንም ከተማ በጥበቡ አዳናት ያን ድሀ ሰው ግን ማንም አላሰበውም።

መክብብ 9፡14፤15

# ጥበብ የመቀበያ ሁለት መንገዶች

## 1. ጥበብ በማንበብ ይመጣል

የምሳሌንና የመክብብን መጻሕፍት በየቀኑ እያነበብክ እግዚአብሔር ለዚህ ሕይወት ጉዳዮች ጥበብን እንዲሰጥህ ጠይቀው። በኔ ይሁንብህ። ሕይወት በማይታለፉ ሁኔታዎች የተሞላች ናት። ሕይወት መፍትሔ በሌላቸው ችግሮች የተሞላች ናት። ለዚህ ነው እግዚአብሔር መልስ ለሌላቸው ጥያቄዎች መልስ ለማምጣት የሚረዱ መሪዎችን የሚያስነሳው።

## 2. ጥበብ በጸሎት ይመጣል

የመሪ እጅግ ጠቃሚ ጸሎት ስለጥበብ የሚፀልየው ጸሎት ነው። መሪ ያለማቋረጥ እግዚአብሔርን ጥበብን ሊጠይቅ ይገባል።

> ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል።
>
> ያዕቆብ 1፡5

# ምዕራፍ 86

# የምታስብ ሁን

ጥሩ የሆነ ዶክተር ሁሉ የታካሚውን ችግር ለይቶ ማወቅ አለበት፡፡ ምርመራ ማድረግ የመፍትሔው ሰማንያ በመቶ እጅ ነው፡፡ እንደመሪ የአንተ ሥራ ስለችግሩ ማሰብ፣ ታሪኩን ማዳመጥ፣ ሁኔታውን መመርመርና እየሆነ ስላለው ነገር ትንታኔ ላይ መድረስ ነው፡፡ ስለምትሠራው ሥራ የማታስብ ከሆነ በአብዛኛው በጥሩ ሁኔታ ልትሰራው አትችልም፡፡ በሥራህ ልትዋጥና ሁልጊዜ ስለእርሱ ልታስብ ይገባል፡፡ ስለሥራው የማይስብ ሰው ሁሉ በጐ ማድረግ አይችልም፡፡ አንድ ሰው እንዳለው "በነገሩ ሀሳብ በመጠመድህ ብቻ ነው የምትታወሰው፡፡" አንዳንድ ቅጥረኞቼ ስለሚሰሯቸው ሥራዎች ከስንት አንዴ ብቻ እንደሚያስቡ አያለሁ፡፡ ሀሳባቸው በነገሩ ላይ የለም፡፡ አልተጠመዱም፤ ይህም በግልጥ ይታያል፡፡

## ስለሥራው የሚያስብ መሪ የመሆን ስድስት ጥቅሞች

### 1. ታላቅ አሳቢ ሁልጊዜ ለማይገፉ ችግሮች መፍትሔዎችን ያገኛል፡፡

እኔም ተመለስሁ፥ ከፀሐይ በታችም የሚደረገውን ግፍ ሁሉ አየሁ እነሆም፥ የተገፉት ሰዎች እንባ ነበረ የሚያጽናናቸውም አልነበረም በሚገፉአቸውም እጅ ኃይል ነበረ፥ እነርሱን ግን የሚያጽናናቸው አልነበረም።

መክብብ 4፡1

### 2. ስለሥራው ያለማቋረጥ የሚያስብ መሪ ማሻሻያ ያመጣል፡፡

ደግሞም የሰውን ድካምና የብልሃት ሥራውን ሁሉ ተመለከትሁ፥ በባልንጀራውም ዘንድ ቅንዓት እንዲያስነሣ አየሁ ይህም ደግሞ ከንቱ ነፋስንም እንደ መከተል ነው።

መክብብ 4፡4

### 3. ስለሥራው ብዙ የሚያስብ የእግዚአብሔር መንፈስ አቅጣጫን በሹክሹክታ ሲጠቁም ይሰማዋል፡፡

ተመለከትሁና አሰብሁ አየሁትና ተግሣጽን ተቀበልሁ።

ምሳሌ 24፡32

### 4. የሚያስብ መሪ ለድንቅና ሕይወት ለዋጭ ሀሳቦች ክፍት ይሆናል፡፡

ከፀሐይ በታችም ይህን ጥበብ አየሁ፥ እርስዋም በእኔ ዘንድ ታላቅ መሰለችኝ።16 እኔም። ከኃይል ይልቅ ጥበብ ትበልጣለች የድሀው ጥበብ ግን ተናቀች ቃሉም አልተሰማችም አልሁ።

መክብብ 9፡13፣16

### 5. አብዝቶ የሚያስብ መሪ አዳዲስ ግቦችንና ራእዮችን ያገኛል

እኔ በልቤ። እነሆ፥ ከእኔ አስቀድመው በኢየሩሳሌም ላይ ከነበሩት ሁሉ ይልቅ ጥበብን አብዝቼ ጨመርሁ ልቤም ብዙ ጥበብንና እውቀትን ተመለከተ ብዬ ተናገርሁ።

መክብብ 1፡16

### 6. ብዙ የሚያስብ መሪ ጥበብን ይቀበላል፡፡

ከሰማይም በታች የተደረገውን ሁሉ በጥበብ እፈልግና እመረምር ዘንድ ልቤን አተጋሁ እግዚአብሔር ይደክሙባት ዘንድ ይህችን ለሰው ልጆች የሰጠ ክፉ ጥረት ናት።

መክብብ 1፡13

## ታላቅ አሳቢ የመሆኛ ሶስት ቁልፎች

1. እግዚአብሔርን ጠብቅ
2. የማለም ችሎታህንና የእውቀት አድማስህን የሚለጥጡ መጽሓፍትን አንብብ
3. ስለምታየውም ሆነ ስለምትሰማው የትኛውም ነገር ይበልጥ በጥልቀት አስብ፡፡

**ጉዳዮች ሲመጡ አእምሮህን ነገሮችን እንዲያጤን ፍቀድለት፡፡ ነገሮችን ከላይ ከላይ ብቻ አትውሰድ፡፡**

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ይደክሙበት ዘንድ የሰጣቸውን ጥረት አይቻለሁ።

መክብብ 3፡10

ከፀሐይ በታች የሚያሳዝን ክፉ ነገር አየሁ ለመከራው በባለቤቱ ዘንድ የተቈጠበች ባለጠግነት ናት።

መክብብ 5፡13

እጄ የሠራቻችን ሥራዬን ሁሉ የደከምሁበትንም ድካሜን ሁሉ ተመለከትሁ እነሆ፥ ሁሉ ከንቱ ነፋስንም እንደ መከተል ነበር፥ ከፀሐይ በታችም ትርፍ አልነበረም።

መክብብ 2፡11

ስለቤተ ክርስቲያኔ ነገሮች ሁኔታ ብዙ ጊዜ ማሰብ ለኔ ግድ ነበር። እየሆነ ያለውን ነገር ያለማቋረጥ አጤናለሁ፤ ስለዚህ ያለማቋረጥ ውሳኔዎችን እየወሰንኩ ነው። አንድ ጊዜ ከመሐንዲሶቼ ከአንዱ ጋር እየተወያየሁ ነበር፤ "ስለዚህ ፕሮጀክት ልታወራ የሚገባህ እጅግ ጠቃሚ ሰው እኔ ነኝ" አልኩት።

ቀጥዬም "ስለዚህ ሥራ የሕንፃ ዲዛይን ባለሙያዎቼ ከሚያስቡት በላይ አስባለሁ።"

ጥሩ መሪ ሥራውንና ተያያዥ ችግሮቹን ሁልጊዜ ያጤናል። ምናልባት እንደመሪ ውጤታማ ያልሆንክበት ምክንያት ልብህና ሀሳብህ ያለማቋረጥ በኃላፊነትህ ላይ አለመሆኑ ነው።

ንጉስ ሰለሞን በዙሪያው ያለውን የድህነት ችግር አጤነ። አብዛኛውን ችግር ከትጋት ማነስ እንዲመጣ ደመደመ (የምርመራ ውጤት)። እንቅልፍንና እጅን አጣጥፎ መቀመጥን ማስቀረት ከቻለ የበለጠ ብልፅግና እንደሚኖር ደረሰበት።

> ተመለከትሁና አሰብሁ አየሁትና ተግሣጽን ተቀበልሁ።ጥቂት ትተኛለህ፥ ጥቂትም ታንቀላፋለህ፥ ትተኛም ዘንድ ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ እንግዲህ ድህነትህ እንደ ወንበዴ፥ ችጋርህም ሰይፍ እንደ ታጠቀ ሰው ይመጣብሃል።
>
> ምሳሌ 24፡32-34

## ምዕራፍ 87

# ራስህን በሌሎች ውስጥ አብዛ

እንግዲህ፥ ልጄ ሆይ፥ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ።

2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1

ጥሩ መሪ መሆን ራስህን በሌሎች ውስጥ ማባዛትን ያካትታል፡፡ እግዚአብሔር በአምሳሉ ሰርቶናል፡፡ የራሱን መልክ በእኛ ውስጥ አበዛ፡፡ ስንራመድ ሲያየን ራሱን ማየት ይችላል፡፡

በሁሉም ነገር በአንተ ላይ የሚደገፍ የአርባ ዓመት ወንድ ልጅ ቢኖርህ እንደመሪ አልተሳካልህም፡፡ ነገር ግን በሕይወት ለመቆየት ከእንግዲህ አንተ የማታስፈልገው የአርባ ዓመት ወንድ ልጅ ቢኖርህ ልጅህን ስኬታማ በሆነ መልኩ ልጅህን አሰልጥነሀል ማለት ነው፡፡ መሪነት እጅግ በርካታ ሰዎችን በአንድ ሰው ላይ የሚደገፉ የማድረግ ጥበብ አይደለም፡፡

ፍጹም የሆነው መሪ ኢየሱስ ያለማቋረጥ ደቀ መዛሙርቱን እርሱ አብሯቸው ለማይሆንበት ጊዜ እያዘጋጃቸው ነበር፡፡ ጥሩ መሪ እርሱ አላስፈላጊ እስከሚሆንበት ደረጃ ድረስ ራሱን በሌሎች እያባዛ ያለ ሰው ነው፡፡ ኢየሱስ "ጊዜው ሲደርስ" ፣ "ጥቂት ጊዜ አለ" እና "በዚያን ቀንም" የመሳሰሉ ሐረጎችን ይጠቀም ነበር፡፡ የሚጠቁመው የቱን ቀን ነው፡- በዚያ ስለማይኖርበት ቀን፡፡ ሁሉም መሪ ራሱን ለዚያ ቀን ማዘጋጀት አለበት፡፡

ነገር ግን ጊዜው ሲደርስ እኔ እንደ ነገርኋችሁ ታስቡ ዘንድ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። ከእንናንተም ጋር ስለ ነበርሁ በመጀመሪያ ይህን አልነገርኋችሁም።አሁን ግን ወደ ላከኝ እሄዳለሁ ከእናንተም። ወዴት ትሄዳለህ? ብሎ የሚጠይቀኝ የለም።

ዮሐንስ 16፡4፡5

ጥቂት ጊዜ አለ፥ አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ፥ ታዩኛላችሁም፥ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና።

ዮሐንስ 16፡16

በዚያን ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል።

ዮሐንስ 16፡23

አመራርህ የተሻለ በሆነ ቁጥር የበዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ይኖሩሀል። ራስህን በሌሎች በብዙዎች ስላበዛህ ያንተ አለመኖር ምንም ማለት አይደለም።

## ራስህን በሌሎች ውስጥ የምታበዛባቸው አምስት መንገዶች

### 1. አባት ሁን

የአባት ልብ ሲኖርህ ካንተ ጋር የሚቆራኙ ሁሉ የሚቆራኙህ እንደ ልጆች ነው።

### 2. አስተማሪ ሁን

ሞለኪውሎች ከትንሽ ስብስብ ወደ ብዙ ስብስብ እንደሚተላለፉበት ሥርዓት (በኦስሞሲስ) ሰዎች እንደሚማሩ አታስብ። እንዲያውቁ የምትፈልገውን በእርግጥ ማስተማር አለብህ።

### 3. ጓደኛ ሁን

በጓደኝነት መደበኛ ባልሆነ መንገድ ብዙ ትምህርቶችን ታስተላልፋለህ።

### 4. ለአገልግሎት ተግዳሮቶች እንዲጋለጡ አድርግ።

ልምድ የመቶ ዓመት ትምህርት ሊያስተምርህ የማይችለውን ያስተምርሃል።

### 5. ወደ አገልግሎት ላካቸው።

ሰዎች ካልተላኩ በቀር የማይማሯቸው የተወሰኑ ነገሮች አሉ።

> በሃይማኖት ኅብረት እውነተኛ ልጄ ለሚሆን ለቲቶ፤ ከእግዚአብሔር አብ ከመድኃኒታችንም ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ምሕረት ሰላምም ይሁን።ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም፥ እኔ አንተን እንዳዘዝሁ፥ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ፤
>
> ቲቶ 1፡4፣5

## ምዕራፍ 88

# እችላለሁ የሚል መሪ ሁን

## እችላለሁ የሚል መሪ ሃያ አምስት ዓረፍተ ነገሮች

### 1. ሁሉም ነገር ይቻላል

ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።

ሉቃስ 1፡37

### 2. ጠንክረን እንስራ

### 3. እንሞክረው፤ ዕድል እንስጠው

### 4. ምንም አናጣም

ኤልሳዕም። የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ነገ በዚህ ጊዜ በሰማርያ በር አንድ መስፈሪያ መልካም ዱቄት በአንድ ሰቅል፥ ሁለትም መስፈሪያ ገብስ በአንድ ሰቅል ይሸመታል አለ።ንጉሡም በእጁ ተደግፎ የነበረ አለቃ ለእግዚአብሔር ሰው መልሶ፦ እነሆ፥ እግዚአብሔር በሰማይ መስኮቶች ቢያደርግ ይህ ነገር ይሆናልን? አለው። እርሱም፦ እነሆ፥ በዓይኖችህ ታየዋለህ፥ ከዚያም አትቀምስም አለ።በበሩም መግቢያ አራት ለምጻም ሰዎች ነበሩ እርስ በርሳቸውም። እስከንሞት ድረስ በዚህ ለምን እንቀመጣለን?

2 ኛ ነገሥት 7፡1-3

### 5. በብቃት ካደረገው እንገልብጥ

በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ፥ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን።

ዕብራውያን 6፡11-12

### 6. ማንም ባይረዳኝ እንኳን አደርገዋለሁ

### 7. የተወጡትን የሌሎቹን ያህል ጥሩ ነን

### 8. አዲስን ነገር ለመማር መቼም አይረፍድም

### 9. አሁን ለውጥን እናድርግ

### 10. ለመጀመር መቼም አይረፍድም

11. አሁኑኑ እንጀምር

12. እስኪያልቅ ድረስ እንሥራ

13. እስክናሳካው ድረስ ቤት አንሂድ

14. መቼም ተስፋ አልቆርጥም

15. ለተቃዋሚ ጊዜ የለኝም

16. እግዚአብሔር ያው ነው በተመሳሳይ መንገድ ይረዳናል

ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።

ዕብራውያን 13፡8

17. ለምን አይሆንም?

18. እተርፋለሁ

19. አበራለሁ

20. እስከመጨረሻ ወድቄ አልቀርም

ጠላቴ ሆይ፥ ብወድቅ እነሣለሁና፥ በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ።

ሚክያስ 7፡8

21. ጠላቶቼ ያዝናሉ

22. የአንተን አስተያየት እፈልጋለሁ

ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን። ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ።

ማቴዎስ 16፡13

23. ጅማሬዬ ታናሽ ቢሆንም ፍፃሜዬ ታላቅ ይሆናል

24. እንሂድ

25. አዲሱን ዕቅድ እንሞክር

## እችላለሁ የሚል መሪ ሚስጢሮች

1. እችላለሁ የሚል መሪ ከአናሳው ወገን መሆኑ ግድ አይለውም።

ከእርሱ ጋር የወጡ ሰዎች ግን፦ በኃይል ከእኛ ይበረታሉና በዚህ ሕዝብ ላይ መውጣት አንችልም አሉ።

ዘኍልቁ 13፡31

2. እችላለሁ የሚል መሪ መደረግ ስላለበት ነገር የራሱ የሆነ አስተያየት አለው፡፡

ካሌብም ሕዝቡን በሙሴ ፊት ዝም አሰኘና። ማሸነፍ እንችላለንንና እንውጣ፥ እንውረሰው አለ።

ዘኁልቊ 13፡30

3. እችላለሁ የሚል መሪ የሚታየው መልካምና አዎንታዊ ነገር ነው፡፡

ለእስራኤልም ልጆች ማኅበር ሁሉ። ዞረን የሰለልናት ምድር እጅግ መልካም ናት።

ዘኁልቊ 14፡7

4. እችላለሁ የሚል መሪ ወዲያውኑ ወደ ተግባር ይገባል፡፡

ካሌብም ሕዝቡን በሙሴ ፊት ዝም አሰኘና። ማሸነፍ እንችላለንንና እንውጣ፥ እንውረሰው አለ።

ዘኁልቊ 13፡30

5. እችላለሁ የሚል መሪ እያንዳንዱ ሥራ መሳካት ካለበት ወዲያውኑ መጀመር እንደሚችልና መጀመር እንዳለበት ያውቃል፡፡

ካሌብም ሕዝቡን በሙሴ ፊት ዝም አሰኘና። ማሸነፍ እንችላለንንና እንውጣ፥ እንውረሰው አለ።

ዘኁልቊ 13፡30

በአብዛኛው ጊዜ ራእዮች ሲዘገዩ እንደሚሞቱ ያውቃል፡፡

6. እችላለሁ የሚል መሪ ለአባቱ ታማኝ ነው፡፡

ኢያሱ ለሙሴ ታማኝ ነበር፡፡

ምድርን ከሰለሉት ጋር የነበሩት የነዌ ልጅ ኢያሱና የዮፎኒ ልጅ ካሌብ ልብሳቸውን ቀደዱ

ዘኁልቊ 14፡6

7. እችላለሁ የሚል መሪ አሉታዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ተፅዕኖ እንዲያደርጉበት አይፈቅድም፡፡ ይልቁኑ እርሱ ተፅዕኖ ያደርግባቸዋል፡፡

ምድርን ከሰለሉት ጋር የነበሩት የነዌ ልጅ ኢያሱና የዮፎኒ ልጅ ካሌብ ልብሳቸውን ቀደዱ

ዘኁልቊ 14፡6

8. እችላለሁ የሚል መሪ በእግዚአብሔር እምነት አለው፡፡

እግዚአብሔርስ ከወደደን ወተትና ማር ወደምታፈስሰው ወደዚች ምድር ያገባናል እርስዋንም ይሰጠናል።

ዘኍልቍ 14፡8

9. እችላለሁ የሚል መሪ ለመዋጋት ዝግጁ ነው፡፡

10. እችላለሁ የሚል መሪ ለመሞት ዝግጁ ነው፡፡

11. እችላለሁ የሚል መሪ አደጋን ለመጋፈጥ ዝግጁ ነው፡፡

12. እችላለሁ የሚል መሪ ራሱን እንደ አንበጣ አያይም፡፡

በዚያም ከኔፊሊም ወገን የሆኑትን ኔፊሊም፥ የዔናቅን ልጆች፥ አየን እኛም በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች ነበርን፥ ደግሞም እኛ በዓይናቸው ዘንድ እንዲሁ ነበርን አሉ።

ዘኍልቍ 13፡33

13. እችላለሁ የሚል መሪ ኋላ ቀርና መሻሻል በሚያሳይ ሕብረተሰብ ዘንድ ተወዳጅ አይደለም፡፡

ማኅበሩ ሁሉ ግን በድንጋይ ይወግሩአቸው ዘንድ ተማከሩ። የእግዚአብሔርም ክብር ለእስራኤል ልጆች ሁሉ በመገናኛው ድንኳን ተገለጠ።

ዘኍልቊ 14፡10

14. እችላለሁ የሚል መሪ በጠላቱ ፍርሃት አያድርበትም፡፡

ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ አታምፁ እንደ እንጀራ ይሆኑልናልና የምድሪቱን ሰዎች አትፍሩ ጥላቸው ከላያቸው ተገፍፎአል፥ እግዚአብሔርም ከእኛ ጋር ነው አትፍሩአቸው ብለው ተናገሩአቸው።

ዘኍልቊ 14፡9

15. እችላለሁ የሚል መሪ የደፋርነት መንፈስ አለበት፡፡

16. እችላለሁ የሚል መሪ ወደ ልማት የሚመራ የጀብዱና የግኝት መንፈስ አለበት፡፡

17. እችላለሁ የሚል መሪ በቆይታ ውስጥ እውነተኛነቱ ይረጋገጣል፡፡

ማኅበሩ ሁሉ ግን በድንጋይ ይወግሩአቸው ዘንድ ተማከሩ። የእግዚአብሔርም ክብር ለእስራኤል ልጆች ሁሉ በመገናኛው ድንኳን ተገለጠ።

ዘኍልቊ 14፡10

## ምዕራፍ 89

# የብቸኝነትን እውነታ ተቀበል

*በፊተኛው ሙግቴ አንድ ስንኳ አልደረሰልኝም፥ ሁሉም ተዉኝ እንጂ፤ ይህንም አይቍጠርባቸው፤*

2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡16

መሪነት በባሕርይው ብቸኛ ሰው ያደርግሃል። መሪ መሆን ማለት ከብዙኃኑ ወደፊት መቅደም ማለት ነው። መሪዎች ብቸኛ ሰዎች ናቸው። ብዙ ውሳኔዎች ለእነርሱ ይተዋሉ። አንዳንድ ነገሮችን በሚመለከት የሚረዳቸው ማንም የለም።

ብቸኝነት የሁሉም መሪዎች መንገድ ነው። ብዙውን ጊዜ ችግሮቻቸውን የሚያጋሩት ማንም የላቸውም። ፍርሃቶቻቸውን በግልጥ መናገር አይችሉም። ብዙ ተከታዮች መሪዎቻቸው ፍርሃት የለሽ እንደሆኑ ቢሰማቸውም ማንኛውም ሀቀኛ መሪ አእምሮውን በየዕለቱ ስለሚያጠቁ እውነተኛ ስጋቶች ይነግርሃል።

ብዙ ተከታዮች መሪዎቻቸው ለዘለዓለሙ የሚኖሩ ይመስላቸዋል። ነገር ግን መሪው በድንገት ሊሞት እንደሚችል አዘውትሮ ይሰጋል። ስለ ትዳር ችግሮቹ መሪ ለማን ማውራት ይችላል? መጋቢውም ራሱ ችግሮች እንዳሉት ማን ይረዳል? ማንም! ይህ ነው መሪዎችን ብቸኛ የሚያደርጋቸው። መሪዎች ከሌሎች መሪዎች ጋር ሕብረት ማድረግ አለባቸው። ለመሪዎች ያሏቸው መሪዎች ብቻ ናቸው።

መሪ አዲስ ራእይ ይዞ ሲመጣ በአብዛኛው የድሮ ጓደኞቹ ይሸሻሉ። ስለዚህም መሪው በድጋሚ ለብቻው ይቀራል። ጌታ በእስያ ላሉት ቤተ ክርስቲያናት መልዕክት ሲልክ መልዕክቱ የተላከው ለቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ነበር። መሪዎች እግዚአብሔር ሲናገራቸው የሚሰሙት በአብዛኛው ብቻቸውን ሆነው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ሙሴ ወደ ተራራ ወጥቶ በዚያ ለአርባ ቀንና አርባ ሌሊት እግዚአብሔርን እንደጠበቀ ይነግረናል።

"ኮንስክሬሽን" (መቀደስ) የሚለው ቃል "መለየት" (ተነጥሎ መቀመጥ) የሚል ትርጉም አለው። እንደ መሪ ተቀድሰህ ከሆነ በብዙ መንገድ ተለይተሃል ማለት ነው። ያ የመሪ ኃላፊነት ነው። ለዚህ ነው

መሪዎች በአብዛኛው ከተከታዮች ይልቅ የሚከፈላቸው፡፡ መሪነት ለሚያስከትለውን ወጪ ለማካካስ የሚደረግ ጥረት ነው፡፡

## ብቸኝነትን የተለማመዱ ስምንት መሪዎች

1. ሁሉም ተኝቶ ሳለ ኢየሱስ ብቻውን በጌተሰማኒ የመናፈሻ ሥፍራ ጸልዮአል፡፡

ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ። አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ። ...ደግሞም መጥቶ ዓይኖቻቸው በእንቅልፍ ከብደው ነበርና ተኝተው አገኛቸው። ደግሞም ትቶአቸው ሄደ፥ ሦስተኛም ያንኑ ቃል ደግሞ ጸለየ።

ማቴዎስ 26፡39፣43፣44

ሁሉም ሸሽተው ሲሮጡ እርሱ ብቻውን ወደ መስቀል ሄዷል፡፡

ነገር ግን ይህ ሁሉ የሆነ የነቢያት መጻሕፍት ይፈጸሙ ዘንድ ነው አለ። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተውት ሸሹ።

ማቴዎስ 26፡56

2. ኤልያስ በቁራ ሲመገብ በምድረበዳ ብቻውን ነበር፡፡

የእግዚአብሔርን ጥሪ የሰማው በዚያ ነው፡፡

እርሱም አንድ ቀን የሚያህል መንገድ በምድረ በዳ ሄደ መጥቶም ከክትክታ ዛፍ በታች ተቀመጠና። ይበቃኛል አሁንም፥ አቤቱ፥ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ ብሎ እንዲሞት ለመነ።በክትክታውም ዛፍ በታች ተጋደመ እንቅልፍም አንቀላፋ እነሆም፥ መልአክ ዳሰሰውና። ተነሥተህ ብላ አለው።

1ኛ ነገሥት 19፡4፣5

3. መጥምቁ ዮሐንስ በምድረበዳ የብቸኝነትን ሕይወት ኖሯል፡፡

በምድረበዳ የሚጮህ ድምፅ ተብሎ ተገልጿል፡፡

በነቢዩ በኢሳይያስ ቃል መጽሐፍ። የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ፤...

ሉቃስ 3፡4

በምድረ በዳ ያለ ብቸኛ ድምፅ ብትመስልም አትዘን፡፡ የመሪነት ጥሪ አንዱ አካል ነው፡፡

4. ዳዊት ከንጉስ ሳዖል ሲሸሽ ብዙ የብቸኝነት ዓመታትን አሳልፏል፡፡

**የውጭ ሰዎች እንኳን ብቸኝነቱን አስተውለዋል።**

ዳዊትም ወደ ካህኑ ወደ አቢሜሌክ ወደ ኖብ መጣ አቢሜሌክም እየተንቀጠቀጠ ዳዊትን ሊገናኘው መጣና። ስለ ምን አንተ ብቻህን ነህ? ከአንተስ ጋር ስለ ምን ማንም የለም? አለው።

1ኛ ሳሙኤል 21፥1

## 5. ዮናስ ከመርከቧ የተጣለው ብቸኛው ሰው ነበር።

**ብቻውን በአሳው ሆድ ውስጥ ገባ። ከዚያ ጨለማ ጉድጓድ ሆኖ ፀለየ፤ እግዚአብሔርም ሰማው።**

እግዚአብሔርም ዮናስን የሚውጥ ታላቅ ዓሣ አሰናዳ ዮናስም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣው ሆድ ውስጥ ነበረ።

ዮናስ 2፥1

## 6. ኖኅ ወደ መርከቡ የገባው ብቸኛው ሰው ነበር።

**ዓለም በሙሉ በክፋት የተሞላች ነበረች። ሌላ አንድ የሰው ልጅ ቤተሰብ እንኳን ከእርሱ ጋር አልሄደም።**

እግዚአብሔርም ኖኅን አለው፦ አንተ ቤተሰቦችህን ሁሉ ይዘህ ወደ መርከብ ግባ በዚህ ትውልድ በፊቴ ጻድቅ ሆነህ አይቼሃለሁና።

ዘፍጥረት 7፥1

## 7. አብርሃም ከቤተሰቡ ወጥቶ ነበር።

**እግዚአብሔር ከአገሩና ከሚያውቀው ቤተሰቡ አርቆ ለብቸኝነት ሕይወት ለየው።**

እግዚአብሔርም አብራምን አለው፦ ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ።

ዘፍጥረት 12፥1

## 8. ሙሴ በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ ጌታን ሲገናኝ ብቻውን ነበር።

**ወደ ተራራውም ሲወጣ እንዲሁ ብቻውን ነበር።**

ሙሴም ብቻውን ወደ እግዚአብሔር ይቅረብ፥ እነርሱ ግን አይቅረቡ ሕዝቡም ከእርሱ ጋር አይውጡ አለው።

ዘጸአት 24፥2

## ምዕራፍ 90

# የረዱህን አትርሳቸው

*አምላክህ እግዚአብሔር ይፈትንህ ዘንድ፥ በልብህም ያለውን ትእዛዙን ትጠብቅ ወይም አትጠብቅ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ፥ ሊያስጨንቅህ በእነዚህ በአርባ ዓመታት በምድረ በዳ የመራህን መንገድ ሁሉ አስብ።*

ዘዳግም 8፡2

**ጌታ እስራኤላውያንን ከግብፅ ካስወጣቸው በኋላ ያደረገላቸውን ሁሉ ስለመርሳት አስጠነቀቃቸው።**

**በፍጥረታዊው ዓለም የማን ዘር እንደሆንክ ማስታወስ ጠቃሚ ነው። አባትህንና እናትህን ማስታወስ ጠቃሚ ነው። ያደርጉልህን አቅራቦት አስታውስ። ወደ ትምህርት ቤት እንድትሄድ የረዳህንና በሳህን ላይ ምግብ ለብዙ ዓመታት ያስቀመጠው ማን እንደሆነ ማወቅ አለብህ። የሚያሳዝነው ጊዜ ባለፈ ቁጥር ብዙ ሰዎች ከየት እንደመጡ ይረሳሉ። ያሏቸው በረከቶች እንዴት እንደኖሯቸውም ይረሳሉ። ሌሎች ደግሞ ሰዎች እነርሱ ራስ-ፈጠር እና ከሌላ ቦታ ምንም ዓይነት ግብዓት ያላገኙ እንደሆኑ እንዲያስቡ ይፈልጋሉ።**

> ትበላማለህ፥ ትጠግብማለህ፥ ስለሰጠህም ስለመልካሚቱ ምድር አምላክህን እግዚአብሔርን ትባርካለህ።ዛሬ እኔ አንተን የማዝዘውን ትእዛዙንና ፍርዱን ሥርዓቱንም ባለመጠበቅ አምላክህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ ተጠንቀቅከበላህና ከጠገብህ በኋላ፥ መልካምም ቤት ሠርተህ ከተቀመጥህበት በኋላ፥የላምና የበግ መንጋ ከበዛልህ በኋላ፥ ብርህና ወርቅህም ያለህም ሁሉ ከበዛልህ በኋላ፥ ልብህ እንዳይጓደድከግብፅም ምድር ከባርነት ቤት ያወጣህን፥

ዘዳግም 8፡10-14

**ጥሩ መሪ ማን እንዳነሳሳው፣ እንዳበረታታውና ተፅዕኖ እንዳሳደረበት የሚያስታውስ ሰው ነው። ጥሩ መሪ አስተማሪዎቹን የሚያስታውስ ነው። የሕክምና ባለሙያዎች የሚገቡት መሐላ የሚያስተምራቸው የመጀመሪያ ትምህርቶች መካከል አንዱ የሚናገረው ሐኪሞች አስተማሪዎቻቸውን እንዲያስታውሱ ነው። መታሰቢያ በእያንዳንዱ የሕይወት ክፍል አስፈላጊ ነው። ጥሩ መሪ ምንም ባልሆነበት ወቅት በእርሱ ያመነበትን ሰው ያስታውሳል። ጥሩ መሪ በገንዘብ የረዳውንና ያማከረውን ያስታውሳል።**

መሪዎች ሲረሱ በአብዛኛው ዓመፀኛ ይሆናሉ። ደካማ የማስታወስ ችሎታ ያላቸው መጋቢዎች እግዚአብሔር ስላደረገው ነገር ምስክርነት መስጠት ስለማይችሉ በአብዛኛው በሚገባ አይሰብኩም። የእኔ ስብከት እግዚአብሔር በእነርሱ ውስጥ ባሳላፈኝ ምስክርነቶች የተሞላ ነው። ደካማ የማስታወስ ችሎታ ያለው መጋቢ እውነተኛ ርህራሄ ይጎድለዋል። ከየት እንደመጣ ማስታወስ አይችልም። እርሱ ከጥቂት ዓመታት በፊት በነበረበት ሁኔታ ውስጥ ያለን ሰው ሲመለከት ከዚያ ሰው ጋር ሊቆራኝ አይችልም። ይህ አለመታደል ነው! መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ቀን ሌሎችን መርዳት እንድንችል እግዚአብሔር በሁኔታዎች ውስጥ እንደሚያሳልፈን ያስተምረናል።

> ዳሩ ግን መከራ ብንቀበል፥ ስለ መጽናናታችሁና ስለ መዳናችሁ ነው፤ ብንጽናናም፥ እኛ ደግሞ የምንሣቀይበት በዚያ ሥቃይ በመጽናት ስለሚደረግ ስለ መጽናናታችሁ ነው።
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 1፡6

ጳውሎስ እጅግ ግልፅ በሆነ ሁኔታ የነበሩት ልምምዶች ለሌሎች ጥቅም እንደሆነ ተናግሯል። ማስታወስ የማይችል መሪ አንዱ አደገኛ ገፅታው በአንድ ወቅት የረዱትን ሰዎች ሊያንጓጥጥ መቻሉ ነው። ከበታቹ ያሉትንም ሊንቅ ይችላል።

እነዚህ ሁሉ ባሕሪያት አደገኛ ውጤቶችን ያስከትላሉ። ለዚህ ነው ጥሩ መሪ ጥሩ የማስታወስ ችሎታ ሊኖረው እንደሚገባ እያስተማርኩ ያለሁት። በአገልግሎት ውስጥ ያሳለፍኳቸውን አስቸጋሪ ጊዜያት ለማስታወሰ እሞክራለሁ። በአገልግሎት ውስጥ የሰራኋቸውን ስህተቶች ለማስታወስ እሞክራለሁ። ከእኔ በኋላ ለሚከተሉት ብዙ ርህራሄ እንዲኖረኝ ያደርገኛል። አዲስ ቤተ ክርስቲያን መጀመሬን የተፈዘብኝንና የተወቀስኩባቸውን ቀናት አስታውሳለሁ። አዳዲስ እየወጡና እየመጡ ላሉ መጋቢዎች በጣም የምራራው ለዚህ ነው።

## ምዕራፍ 91

# ራእይህን ወደ እውነታ ለውጥ

ምን ምን ሕልሞች አሉህ? መሪ ከሆንክ እነዚያን እውነታ ማድረግ ትችላለህ። ሁሉም ያልማል። መሪ ሲያልም ግን እውነታ ይሆናል። እኔ የብዙ ነፍሳት መዳን ህልም አለኝ። የብዙ አብያተ ክርቲያናት መመሥረት ህልም አለኝ። አገልግሎቴን የመፈጸም ህልም አለኝ። እነዚህ ህልሞች ሲፈፀሙ ማየት እንደምችል አምናለሁ።

ሕልሞችህን በሚመለከት ምን እያደረግህ ነው? በውስጥህ መሪ ካለ ተነስና ሕልሞችህ እውን እንዲሆኑ የሚገባውን ዋጋ ክፈል። ራእዮችህንና ህልሞችህን እውን የማድረጊያ ቁልፍ ምንድን ነው? የተሰጠህና ታላላቅ መሥዋዕትነቶችን ለመክፈል የተዘጋጀህ መሆን አለብህ።

ምዕራፍ 92

# ቀድመህ ሂድ ሰዎችም ወደ ምትሄድበት ይከተሉሃል

በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፦ እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።

ማቴዎስ 16፡24

ወደየትም ብትሄድ ሰዎች አንተን ተከትለው ወደዚያ ለመሄድ ዝግጁ ይሆናሉ፡፡ በ1990 የሕክምና ሙያዬን ትቼ የአገልግሎትን መንገድ ተከተልኩ፡፡ ዛሬ በተመሳሳይ መንገድ እኔን የተከተሉ ብዙ ሐኪሞች አሉ፡፡ በአገልግሎት መበልፀግ አለመበልጸጋቸው ዋናው ጉዳይ አልነበረም፡፡ መስቀሎቻቸውን ተሸክመው ወደሚመራቸው ለመሄድ ምሪትን ተቀብለው ነበር፡፡ ሌሎች ሐኪሞችና ባለሙያዎች በዚህ መንገድ የተከተሉኝ ለምንድነው? ምክንያቱም እኔ ቀድሜ ገብቼ እነርሱን እንዲከተሉኝ ስለጠራኋቸው ነው!

ሰዎችን ወደ የትኛውም ሥፍራ የመምራት ዋናው ቁልፍ አንተ ራስህ በመንገዱ መራመድ ነው፡፡ ኢየሱስ እርሱ እራሱ ያላደረገውን ነገር እንዲያደርጉ ለደቀ መዛሙርቱ ተናግሮ አያውቅም፡፡

አንዲት ወጣት ሴት አንድን ወጣት ወንድ በቀሪው ዘመኗ ሁሉ ለመከተል ስትወስን በእርግጥ የትም ቢሆን እየተከተለችው ነው፡፡ የጋብቻ ቃል ኪዳንህን ታስታውሳለህ? "በክፉም በደጉም፣ በሀብት ቢሆን በድህነት" ጋብቻ አንድን ሰው የትም ሥፍራ እንዲከተልህ ማሳመን ነው፡፡ ጋብቻን ለየት የሚያደርገው ሁለታችሁም እኩል አብራችሁ መግባታችሁ ነው፡፡

ዛሬ አንተን እራስህን በእርግጥ መሪ መሆንህን ልጠይቅህ እፈልጋለሁ፡፡ ሰዎች ወደ ስኬት ቢሆን ወደ መከራ አንተን ለመከተል ዝግጁ ናቸው? ተከታዮችህ አንዳንድ ነገሮችን ለምን እንደማያደርጉ ገርሞህ ያውቃል? ምናልባት አንተ አርአያ አልሆንክም ይሆናል፡፡ ማንም ባልተጓዘበት ለመሄድ ይፈራሉ፡፡ ለራሳቸው እንዲህ ያስባሉ "አንተ የማትሄድ ከሆነ እኔ ለምን እሄዳለሁ?"

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እስከ መስቀል ማስከተል እስኪችል ድረስ (የቻለ) ጥሩ መሪ ነበር፡፡ "መስቀላችሁን ተሸክማችሁ ተከተሉኝ" ብሎ እንኳን ነግሯቸዋል፡፡ በሌላ ቋንቋ "ወደ አስክሬን ቤት ሄደን በዚያ አብረን እንጋደም" ማለት ነው፡፡ እርሱ ራሱ መስቀሉን ስለተሸከመ ይህን የማለት ሥልጣን ነበረው ፡፡ አንተ ቀድመህ በመሄድ ሰዎች ወደ ማንኛውም ሥፍራ እንዲሄዱ አሳምናቸው፡፡

ሰዎች እንዲሁ መሄድ ወደሚያስፈልግበት ቦታ ሁሉ እንዲከተሉህ የማሳመንን ጥበብ አዳብር፡፡

> ጴጥሮስ፡- ከአንተ ጋር መሞት እንኳ የሚያስፈልገኝ ቢሆን፥ ከቶ አልክድህም አለው። ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ደግሞ እንደዚሁ አሉ።
>
> ማቴዎስ 26፡35

ኢየሱስ ጥሩ መሪ ነበር፡፡ እስከሞት ድረስ እንኳ ሊከተሉት ወደሚችሉበት ደረጃ ደቀ መዛሙርቱን ማድረስ ችሎ ነበር፡፡

ምዕራፍ 93

# ተከታዮችህ እንዲወዱህ አድርግ በአንተ ቅር እንደማይሰኙ እርግጠኛ ሁን

ጥሩ መሪ ፈቃደኛ በሆነ ሠራተኞች የተከበበ ነው። ጥሩ መሪ ፍላጐቱን ለማሟላት ደስተኞች በሆኑ ሰዎች የተከበበ ነው። መሪ ከሆንክ የተከታዮችህን ዓይን በጥልቀት ተመልከት። እነዚያ ዓይኖች በጉጉት የሚያንፀባርቁ ናቸው ወይስ ቅሬታንና መራርነትን ይፈነጥቃሉ? ንጉሥ ዳዊት በብዙ ኃያላን ሰዎች የተከበበ ነበር። አብዛኞቹ እርሱ ቢጠይቃቸው ሕይወታቸውን ለእርሱ ይሰዉለት ነበር።

> በቤትመዓካ ባለ በአቤልም መጥተው ከበቡት፥ በከተማይቱም ላይ እስከ ቅጥርዋ ድረስ የአፈርን ድልድል ደለደሉ ቅጥሩንም ያፈርሱ ዘንድ ከኢዮአብ ጋር የነበሩ ሕዝብ ሁሉ ይደባደቡ ነበር። ከከተማይቱም አንዲት ብልሃተኛ ሴት። ስሙ፥ ስሙ ኢዮአብንም። እነግርህ ዘንድ ወደዚህ ቅረብ በሉት ስትል ጮኸች።
>
> 2ኛ ሳሙኤል 20፡15፧16

የዳዊት ኃያላንን እርሱ ውኃ መጠጣት ይችል ዘንድ ነፍሳቸውን ለመስጠት እጅግ የተዘጋጁ ያደረጋቸው ምንድነው? ልትመራ የምትፈልጋቸውን ሰዎች ዓይን በጥልቀት ተመልከት። ይወዱሃል? ካንተ ጋር ለመሆንና አንተን ለመከተል የእውነት ደስተኞች ናቸው? የሚከተሉህ ሰዎች በእውነት አንተን ለመታዘዝና ከአንተ ጋር አብረው ለመፍሰስ ፍቃደኞች እንዲሆኑ ለማድረግ ምን ማድረግ ትችላለህ? የሰው ልጆች ሁሉ ተፈላጊነት፣ ተወዳጅነትና መከበር እንዲሰማቸው የማይነገር ፍላጐት አላቸው።

## ተከታዮችህ እንዲወዱህና ቅር እንዳይሰኙብህ እንዴት ማድረግ እንደሚቻል

### 1. ሰዎች በአጠቃላይ በአንተ እንደሚከበሩ እንዲሰማቸው አድርግ

ለራስ ዋጋ መስጠትና ትክክለኛ አክብሮት ስሜት አንዴ ካለ ተከታዮችህን እንዲወዱህ በማድረጉ ረጅም መንገድ ተጉዘሀል። ሰዎች በተፈጥሮ የሚያከብራቸውን ይወዳሉ።

## 2. የሚከተሉህን ሰዎች የላቁ፣ የታወቁ፣ ዝነኛ እና አስደናቂ ሰዎች ወደ መሆን ለውጣቸው፡፡

ኢየሱስ ተከታዮቹን እኛ የምናውቃቸውን ሐዋርያት ወደ መሆን ለወጣቸው፡፡ በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ መኖሪያንና ሌሎች ብዙ ነገሮችን ቃል ገብቶላቸዋል፡፡ ኢየሱስ ተከታዮቹን እንዲህ ነበር የሚይዛቸው፡፡ ለእርሱ መሞታቸው አይገርምም፡፡

እውነተኛ መሪ የሚመራቸው ሰዎች ታላቅ እንዲሆኑ ይፈልጋል፡፡ የምትመራቸው ሰዎች አንተን በመከተል በዚህ ሕይወት ታላቅ እንደሚሆኑ ሲሰማቸው የቅርብ ለመሆን እጅግ ፈቃደኞች ይሆናሉ፡፡ ራስህን ይህንን ጥያቄ ጠይቅ፡- የሚከተሉህ ሰዎች ወደፊት ዋጋ ያላቸው ይሆናሉ? ታላቅ ይሆናሉ? አንተ በፈጠርከው ሥርዓት ውስጥ ስኬታማ መሆን ይችላሉ፡፡ አንተ በምትመራው አገልግሎት ውስጥ ኃያላን ሰዎች መሆን ይችላሉ? በአገልግሎት የተወሰነ የታላቅነት ደረጃ የሚኖርህ አንተ ብቻ ነህ የምትሆነው?

## 3. ለተከታዮችህ መሥዋዕትነት ክፈል

እውነተኛ መሪ ፈቃደኛ ተከታዮች አሉት፡፡ ከዛሬ ጀምረህ በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች ስለ ሥራቸውና ካንተ ጋር ስለ መጣመራቸው ትልቅ ተነሳሽነት ያላቸው እንዲሆኑ ለማድረግ ወስን፡፡ ይህንን ለማድረግ እነርሱን ለማስደሰት መሥዋዕትነት ማድረግ ይኖርብሃል፡፡ የወደፊት ቀጣይነትና ተስፋ መስጠት አለብህ፡፡ ጉባዔው አንድ መጋቢ ለእነርሱ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ሲገነባላቸው ሲያዩ ለቤተ ክርስቲያኑ እጅግ በጣም የተነሳሱ ይሆናሉ፡፡ መጋቢው ለራሱ ጥሩ ነገሮችን ሲሰበስብ የሚያዩ ከሆነ ግን ከእርሱ ጋር አብሮ ለመፍሰስ ያላቸው ዝግጁነት በብዙ በአደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ ጥሩ ደሞዝ ክፈል፤ እንዲሁም ላንተ የሚሰሩ ሰዎች ሁሉ ቤት፣ መኪኖችና በቂ ገንዘብ እንዳላቸው አረጋግጥ፡፡

ምዕራፍ 94

# ቅሬታን ተጠንቀቅ ደግሞም ወሳኝ በሆነ ሁኔታ ምላሽ ስጠው

ቅሬታ ተከታዮችህን ይበታትናል። በምርጫ የሚሸነፍ ማንም የሚሸነፈው ሰዎች ከእንግዲህ በአመራሩ ደስ ስለማይሰኙ ነው። "ደስ መሰኘት" ማለት በአንድ ነገር "መርካት፣ መፈፀም፣ መባበልና መደሰት" ማለት ነው። እንዲሁም ባለህ ነገር "በደስታ ስሜት መነካት፣ መኮርኮር፣ እንዲፈዙ መደረግ፣ መማረክ፣ መደመም እና መመሰጥ" ማለት ነው። የተከታዮችህን የደስታ ደረጃ ሁልጊዜ ተቆጣጠር። ከእኔ ጋር በአገልግሎቱ ውስጥ ባላቸው ሥራ ከተነኩ፣ ከተማረኩ፣ ከተደመሙና ከተመሰጡ ሰዎች ጋር መስራት እፈልጋለሁ።

ቅሬታ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ ክፉ መንፈስ ነው። ከአንተ ጋር በመሆናቸው ያልተነኩ፣ ያልረኩ እና ደስ ያልተሰኙ ሰዎችን መምራት አትችልም። የትኛውም ሁኔታ ፍጹም አይደለም። ቅሬታ የልብ ውጤት እንጂ የሁኔታ ውጤት አይደለም። ብዙ የሌላቸው ነገር ግን ደስተኛ የሆኑ ሰዎችን አውቃለሁ።

## የቅሬታ ብቸኛውና ዋና መገለጫ

የቅሬታ ብቸኛውና ዋናው መገለጫ ማወዳደር ነው።

> *ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ከአንዳንዶች ጋር ራሳችንን ልንቆጥር ወይም ራሳችንን ልናስተያይ አንደፍርምና፤ ነገር ግን እነርሱ ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር ሲያመዛዝኑ፥ ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር ሲያስተያዩ፥ አያስተውሉም።*
>
> 2ኛ ቆሮንቶስ 10፡12

ሰዎች ሌሎች ባሏቸው ነገሮች ላይ ባተኩሩ ቁጥር ቅር ይሰኛሉ። ከዚህ በታች ባለው ታሪክ ላይ ጌታው ለሠራተኞቹ ጥሩ ክፍያን ቃል ገብቶላቸው ነበር። በመጀመሪያ ጥሩ እንደሆነ ስላሰቡ ስለ ደመወዛቸው ቅሬታ አላቀረቡም። በቀኑ መጨረሻ ግን አዳዲስ ሠራተኞች ተቀጥረው ተመሳሳይ ክፍያ ተሰጣቸው።

> *መንግሥተ ሰማያት ለወይኑ አትክልት ሠራተኞችን ሊቀጥር ማልዶ የወጣ ባለቤት ሰውን ትመስላለችና። ሠራተኞችንም በቀን አንድ ዲናር ተስማምቶ ወደ ወይኑ አትክልት ሰደዳቸው። በሦስት ሰዓትም ወጥቶ ሥራ የፈቱ ሌሎችን በአደባባይ ቆመው*

አየ፥ እነዚያንም። እናንተ ደግሞ ወደ ወይኔ አትክልት ሂዱ የሚገባውንም እሰጣችኋለሁ አላቸው። እነርሱም ሄዱ። ደግሞም በስድስትና በዘጠኝ ሰዓት ወጥቶ እንዲሁ አደረገ። በአሥራ አንደኛውም ሰዓት ወጥቶ ሌሎችን ቆመው አገኘና። ሥራ ፈትታችሁ ቀኑን ሁሉ በዚህ ስለ ምን ትቆማላችሁ? አላቸው። የሚቀጥረን ስለ አጣን ነው አሉት። እርሱም፦ እናንተ ደግሞ ወደ ወይኔ አትክልት ሂዱ የሚገባውንም ትቀበላላችሁ አላቸው። በመሸም ጊዜ የወይኑ አትክልት ጌታ አዛዡን። ሠራተኞችን ጥራና ከኋለኞች ጀምረህ እስከ ፊተኞች ድረስ ደመወዝ ስጣቸው አለው። በአሥራ አንደኛው ሰዓትም የገቡ መጥተው እያንዳንዳቸው አንድ ዲናር ተቀበሉ። ፊተኞችም በመጡ ጊዜ አብዝተው የሚቀበሉ መስሎአቸው ነበር፤ እነርሱም ደግሞ እያንዳንዳቸው አንድ ዲናር ተቀበሉ። ተቀብለውም፦ እነዚህ ኋለኞች አንድ ሰዓት ሠሩ፥ የቀኑንም ድካምና ትኩሳት ከተሸከምን ከእኛ ጋር አስተካከልሃቸው ብለው በባለቤቱ ላይ አንጐራጐሩ። እርሱ ግን መልሶ ከእነርሱ ለአንዱ እንዲህ አለው፦ ወዳጄ ሆይ፥ አልበደልሁህም በአንድ ዲናር አልተስማማኸኝምን? ድርሻህን ውሰድና ሂድ፤ እኔ ለዚህ ለኋለኛው እንደ አንተ ልሰጠው እወዳለሁ፤ በገንዘቤ የወደድሁትን አደርግ ዘንድ መብት የለኝምን? ወይስ እኔ መልካም ስለ ሆንሁ ዓይንህ ምቀኛ ናትን?

ማቴዎስ 20፡1-15

ድንገት ቅሬታ አስቀያሚ ጭንቅላቱን ብቅ አደረገ፡፡ የመጀመሪያዎቹ የሠራተኞች ቡድን ከእንግዲህ በክፍያቸው ደስተኞች አልነበሩም፡፡ ብዙ ሰዎች ጐረቤትን በመመልከት ሌላ ሰው ያለውን እስከሚያዩ ድረስ ባላቸው ነገር ደስተኞ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር በሰጠኝ ደስተኛ ነኝ፡፡ ቤኒ ሂን፣ ኦራል ሮበርትስ ወይም ቲዲ.ጄክስ ያላቸው ላይኖረኝ ይችላል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በሰጠኝ ደስተኛ ነኝ፡፡ ራሴን ከእነዚህ የተወሰኑ ሰዎች ጋር ማነፃፀር ብጀምር ብቁ እንዳልሆንኩ ማሰብ ልጀምር እችላለሁ፡፡ ራስህን ከሌላ ሰው ጋር ማወዳደር ከጀመርክ በቅሬታ ትበላሻለህ፡፡ ተማራሪ ተጠራጣሪና ውለታ ቢስ ሰው ትሆናለህ፡፡

ጠቢብ መሪ በመሆን ይህንን ቁስል ገና ከመታየቱ ለየው፡፡ ተከታዮችህ እኩል አይደሉምና ሁሉንም በተመሳሳይ ሁኔታ መሸለም አይቻልም፡፡ ተከታዮችህ ማጉረምረምና እና ቅር መሰኘት እንደጀመሩ እንደ ሙሴ ተልዕኮህን በመሳት ለውድቀት ልትዳረግ ትችላለህ፡፡

## ቅሬታን የማስተናገጃ ሶስት መንገዶች

1. ጥሩ ደሞዝና ክፍያ በመስጠት ሰዎች ጥሩ ነገር እያገኙ መሆኑን ልበ ሙሉ ሁን፡፡

በአጠቃላይ ሰዎች በቂ ዋጋ እየተቀበሉ ካልሆነ ቅር ለመሰኘት ትክክለኛ ምክንያት አላቸው፡፡ እንዳለህበት ሁኔታ ልክ ለሰዎች ጥሩ ዋጋ ስጥ፡፡ የሚከተሉህ ስለ ወደፊቱ ብቻ ተስፈኞች ሳይሆኑ አሁን

የረኩ መሆን አለባቸው፡፡ የድርጅት ሥራ አስኪያጅ ከሆንክ ሠራተኞችህ አሁን ላይ ደስተኛ መሆናቸውን ራስህን ጠይቅ፡፡ ለወደፊቱ ያበቡ ተስፋዎች መኖራቸው መልካም ነው፤ ግን አሁንስ? ኢየሱስ ለወደፊቱ ብቻ በረከቶችን ቃል አልገባም፤ ለአሁን ደስታንና እርካታን አቅርቦ ነበር!

ጴጥሮስም፡- እነሆ፥ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ይለው ጀመር።ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፡- እውነት እላችኋለሁ፥ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ቤትን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ፥አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን ወንድሞችንና እኅቶችንም እናቶችንም ልጆችንም እርሻንም መቶ እጥፍ፥ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም።

ማርቆስ 10፡28-30

ለአሁን ቤቶችና ባለጠግነት ነበር፤ ለወደፊት ደግሞ የዘላለም ሕይወት፡፡ ስኬታማ ሥራ አስኪያጅ መሆን የምትፈልግ ከሆነ ለአሁኑ አንድ ነገር አቅርብ ለወደፊቱ ደግሞ የምትሰጠው ተስፋ ይኑርህ፡፡ ይህ የኢየሱስ ስልት ነበር፡፡ ስለወደፊቱ ተስፋዎች እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ ሰዎች ግን አሁንም የሆነ ነገር ይፈልጋሉ!

## 2. ስለ መደሰት አስተምር

የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ከሰይጣን የሚመጣውን ሽንገላ ይዋጋል፡፡ ማስተማር በድርጅትህ ውስጥ ያሉትን ሊፈወሱ የሚችሉ የቅሬታ ቅንጣቶችን ሁሌም ቢሆን ይፈውሳል፡፡

አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም፤ ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፥ እርሱ ይበቃናል።

1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡8

አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን፥ ያላችሁም ይብቃችሁ፤ እርሱ ራሱ። አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና፤

ዕብራውያን 13፡5

## 3. የማይፈወስን ቅሬታ ለይተህ ዕወቅ የተበከሉትንም አሰናብት

ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ።

መዝሙር 1፡1

ገንዘብን እጅግ አብዝተው ከመውደዳቸው የተነሳ የምታደርግላቸው ምንም ነገር ቢኖር መቼም አጥጋቢ የማይሆንላቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ፡፡

ብርን የሚወድድ ሰው ብርን አይጠግብም ባለጠግነትንም የሚወድድ ትርፉን አይጠግብም ይህም ደግሞ ከንቱ ነው።

መክብብ 5፡10

እንደዚህ ያሉ ሰዎች ከፍተኛ ደሞዝና የበለጡ ጥቅማጥቅሞች ይቀበላሉ፤ ነገር ግን ምንም ዓይነት ምስጋና አያሳዩም። ተጨማሪ ጉርሻ ወይም ስጦታ ሲቀበሉ እንደ "እስቲ ልውሰደው!" ዓይነት የማይመስጥ ምላሽ ይሰጣሉ። በሌላ ቋንቋ "በበቂ ሁኔታ ጥሩ አይደለም ግን እንደሚሆን አደርጋለሁ!" እንደ ማለት ነው።

በአንድ ወቅት ያለማቋረጥ ስለደሞዛቸው የሚያጉተመትሙ ቅጥረኞች ነበሩኝ። ሊፈወስ በማይችል ቅሬታ እየተሰቃዩ መሆኑን ተረዳሁ። አንድ ቀን ጠርቼ "በደሞዛችሁ ደስተኛ የሆናችሁ አይመስለኝም"

አስተዳዳሪዬን ጥሩ የስንብት ክፍያ እንዲያዘጋጅላቸው ጠየቅሁትና አሰናበትኳቸው። በዓለማዊው የጉልበት ሥራ ገበያ ውስጥ ጥቂት ወራት ካሰለፉ በኋላ አንደኛው ተመልሶ ወደ እኔ መጣና "ካንተ ጋር ሳለሁ በአገሪቱ እጅግ ምርጥ ከተባሉት ሥራዎች አንዱ እንደነበረኝ አሁን አስተዋልሁ" አለኝ። ይህ መገለጥ በመጨረሻ በመገኘቱ ደስ አለኝ። አንዳንድ ሰዎች ከቅሬታቸው የሚፈወሱት የሕይወት እውነታ ሲለማመዱ ብቻ ነው።

ምዕራፍ 95

# በተቺ ሰዎች ላይ ምንም ጊዜ አታጥፉ

## ስለትችትና ስለተቺ ሰዎች ሁሉም መሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ ሃያ ነገሮች

1. ተቺ ሰው በምታደርገው ነገር ውስጥ ምንም መልካም ነገር የማይታየው ሰው ነው።

እነዚያ ኢየሱስን ይነቅፉ የነበሩት እንዴት ኃይለኛ ትምህርቱንና ተዓምራቶቹን አላዩም? ተቺ ሰው በምታደርገው በየትኛውም ነገር ውስጥ ምንም በጐ ነገር አይታየውም። የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባሕርይ ይኸው ነው። ምንም ቢሆን በገዥው ፓርቲ ውስጥ አንዳች መልካም ነገር አይታያቸውም።

2. ተቺ ሰዎች በአብዛኛው በሕይወታቸው ያልተሳካላቸው ተስፋ የቆረጡ ሰዎች ናቸው።

ተስፋ መቁረጥ መራርነትን ይፈጥራል። መራርነት የሚገለጠው በነቀፋ ነው።

3. ተቺ ሰዎች በአብዛኛው በግል ሕይወታቸው ቅር የተሰኙና እንዳሰቡት ያልሆነላቸው ናቸው።

በብዛት እየተቸህ ስላለው ሰው ጥቂት መጠየቅን አትርሳ። ግብረገባዊ ያልሆነ፣ ውሸታምና ዘራፊ ግለሰብ መሆኑን ስትደርስበት ትደነቃለህ።

4. ተቺ ሰዎች በአብዛኛው የሌሎችን ሕይወት በማፍረስ የራሳቸውን የሚገነቡ ሰዎች ናቸው።

እነዚህ ሰዎች በምንም ነገር አልተሳካላቸውም። ለማድረግ የሚሞክሩት ነገር ቢኖር ሌሎችን ሰዎች እነርሱ ወዳሉበት የውጤት አልባነት ደረጃ ጐትቶ ማውረድ ነው።

## 5. ተቺ ሰዎች በአብዛኛው ረጅም ዕድሜ አይኖራቸውም፡፡

**መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ መርህ ላይ በጣም ግልፅ ነው፡፡ ሕይወትን የምትወድድ ከሆነ አንደበትህን ያልተገቡ ነገሮችን ከመናገር ከልክል፡፡**

ሕይወትን ሊወድ መልካሞችንም ቀኖች ሊያይ የሚፈልግ ሰው፥ መላሱን ከክፉ ከንፈሮቹንም ተንኰልን ከመናገር ይከልከል፤

1ኛ ጴጥሮስ 3፡10

## 6. ተቺ ሰዎች በአብዛኛው ሥነ አእምሮ-ማህበረሰባዊ ችግሮች አሉባቸው፡፡

**እንዲህ ያሉ ሰዎች በአብዛኛው የአባትን ወይም የእናትን ፍቅር ያላገኙ የተገፉና የማይወደዱ ሰዎች ናቸው፡፡ ወቀሳቸው በአብዛኛው ትኩረት ለማግኘት የሚደረግ ጩኸት (ለቅሶ) ነው፡፡**

## 7. ኢየሱስ ለተቺዎቹ አልመለሰላቸውም

**ኢየሱስ ምላሽ የሰጠው ለጠላቶቹ ጥላቻ ሳይሆን ለብዙሃኑ ረሃብና ጥማት ነበር፡፡**

ከሄሮድስም ግዛት እንደ ሆነ ባወቀ ጊዜ ወደ ሄሮድስ ሰደደው፤ እርሱ ደግሞ በዚያ ጊዜ በኢየሩሳሌም ነበረና።ሄሮድስም ኢየሱስን ባየው ጊዜ እጅግ ደስ አለው፤ ስለ እርሱ ስለ ሰማ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሊያየው ይመኝ ነበርና፥ ምልክትም ሲያደርግ ሊያይ ተስፋ ያደርግ ነበር።በብዙ ቃልም ጠየቀው፤ እርሱ ግን አንድ ስንኳ አልመለሰለትም። የካህናት አለቆችና ጻፎችም አጽንተው ሲከሱት ቆመው ነበር።

ሉቃስ 23፡7-10

## 8. ትችት የአገልግሎቱ አካል ነው፡፡

**ትችት የሌለበት አገልግሎት ብሎ ነገር የለም፡፡ ኢየሱስ ፍጹም ነበር፡፡ እርሱ ከተተቸ ከተከሰሰና ከተገደለ እንደ አንተ ዓይነቱ ፍጹም ያልሆነ ሰው ምን የሚደርስበት ይመስልሀል?**

## 9. ያለክስ ማገልገል አይቻልም

**የጥቅሉ አንድ አካል ነው፡፡ ኢየሱስ ከስደት ጋር ሽልማትን ቃል ገብቷል፡፡**

አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን ወንድሞችንና እኅቶችንም እናቶችንም ልጆችንም እርሻንም መቶ እጥፍ፥ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም።

ማርቆስ 10፡30

10. አንድ ሰው እንዲህ አለ፣ "ትችት የማይሳካለት ሰው ገዳይ መርዝ ነው"

አስብበት!

11. ጥሩ ሰው የሆነ ተቺ እስካሁን ድረስ አልገጠመኝም።

ትችት በአንድ ሰው ውስጥ የተከማቹ የብዙ ክፋቶች መገለጫ ይመስላል። አእምሮአቸውን የተበከለ እና የማያምኑ ሰዎች ናቸው። በነገር ሁሉ ውስጥ ቆሻሻ የሚታያቸው። "ሁሉ ለንጹሖች ንጹሕ ነው፤ ለርኩሳንና ለማያምኑ ግን ንጹሕ የሆነ ምንም የለም፥ ነገር ግን አእምሮአቸውም ሕሊናቸውም ረክሶአል።" (ቲቶ 1፡15)

12. ተቺ ሰዎች በአብዛኛው በዘዴ ወደ ክርክርና ንትርክ ሊያስገቡህ ነው የሚሞክሩት።

አትታለል። ሰይጣን ስሜቶችህ ሊታመኑ በማይችሉ ክሶችና ትችቶች ምክንያት እንዲጨናነቁ ይፈልጋል።

13. ተቺ ሰዎች በአብዛኛው በቃሎችህ ሊያጠምዱህ ነው የሚፈልጉት።

ትችቶች በጥርጣሬ የተሞሉ ናቸው። በብዙ ዓይነት ክፉ ነገር ይጠረጥሩሃል። ጥርጣሬአቸውን የሚያረጋግጥ ተጨማሪ ማስረጃ ይፈልጋሉ።

14. ከተቺዎችህ የሆነ ነገር መማር ትችላለህ።

ጓደኞችህ ስህተቶችህን ነቅሰው ላያወጡ ይችላሉ። ጠላቶችህ አንተን ለመጣል በሚያደርጉት ሙከራ በይበልጥ ጉድለቶችህን ሊያጐሉ ይችላሉ። አስፈላጊውን ማስተካከያዎች ማድረግ እንድትችል የሚሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ነው።

15. ጠላቶች "ገንቢ" ትችቶችን አይሰነዝሩም።

ጠላቶችህ ሕይወትህን ለማነጽ (ለመገንባት) እየሞከሩ አይደለም። እንዴት "ገንቢ" የሆነ የትኛውንም ነገር እንዴት ሊሰጥህ ይችላል? ከጠላትህ የሚመጣውን ነገር ሁሉ በአፍራሽነት መመደቡ ስህተት አይደለም። ሳትበከል ከዚህ አደገኛ ትችት ጥበብንና ምሪትን ለመውሰድ ወስን።

16. አንዳንድ ትችቶች ልብህን ለመጉዳት የታለሙ የክስ ቀስቶች ስለሆኑ እነርሱን መስማት እንቢ በል።

የሕይወት ጉዳዮች መውጫ ከእርሷ ነውና ልብህን በፍጹም ትጋት ጠብቅ።

17. ተቺ ሰዎች በአብዛኛው ጭፍኖች ናቸው።

ብዙ ትችት ባልተሟላ መረጃ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ብዙ ተቺ ሰዎች እውቀት የጐደላቸው ናቸው።

18. ተቺ ሰዎች በአብዛኛው ልምድ የሌላቸው ናቸው።

ብዙ ትችቶች የሚመጡት እርባና ቢስ መላምት ከሚሰጡ ሰዎች አንደበት ነው። እነዚህ ምንም ቁም ነገር የሌለባቸው ሰዎች ናቸው። እውቀትም ሆነ ልምድ የላቸውም።

19. ተቺ ሰዎች በሚሰሟቸው ዘንድ የሚሠራጭን መርዝ ያስተላልፋሉ።

የሚተቹህ ሰዎች በአብዛኛው በኃይል ይጠሉሃል። ሌሎችም እንዲሁ እንዲጠሉህ ይፈልጋሉ።

20. ለሁሉም ትችት መልስህ “አራት ነጥብ፤ ለራስህ መልሰው!” ነው መሆን ያለበት።

ልጆቼም የሚመክሩት ይህን ነው!

ምዕራፍ 96

# መላመድ የአመራር አደጋ ነው። በአስቸኳይ ምላሽ ስጠው

## ስለመላመድ እያንዳንዱ መሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ ሃያ ነገሮች፡፡

### 1. መላመድ የነብይን አገልግሎት የሚገድለው በሽታ ነው፡፡

ኢየሱስም፦ ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ዘመዶቹ ከገዛ ቤቱም በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው።

ማርቆስ 6፡4

### 2. በኢየሱስ አገልግሎት ላይ ለነበረው ቅባት እጅግ ኃይለኛው ተገዳዳሪ ነበር፡፡

በዚያም በጥቂቶች ድውዮች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወስ በቀር፥ ተአምር ሊያደርግ ምንም አልቻለም።

ማርቆስ 6፡5

### 3. መላመድ ከመሪ ጋር ያለ ተደጋጋሚ መስተጋብር (ግንኙነት) ውጤት ነው፡፡

ሰንበትም በሆነ ጊዜ በምኵራብ ያስተምር ጀመር፤ ብዙዎችም ሰምተው ተገረሙና። እነዚህን ነገሮች ይህ ከወዴት አገኛቸው? ለዚህ የተሰጠችው ጥበብ ምንድር ናት? በእጁም የሚደረጉ እንደነዚህ ያሉ ተአምራት ምንድር ናቸው?ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ የያቆብም የዮሳም የይሁዳም የስምዖንም ወንድም አይደለምን? እኅቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን? አሉ፤ ይሰናከሉበትም ነበር።

ማርቆስ 6፡2፤3

### 4. መላመድ መሪን ከመጠን በላይ የማወቅ ውጤት ነው፡፡

#### ለዚህ ነው ሁሉም መሪ የተወሰነ የግል ሚስጢር መጠበቅ ያለበት፡፡

በዚያም በጥቂቶች ድውዮች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወስ በቀር፥ ተአምር ሊያደርግ ምንም አልቻለም።

ማርቆስ 6፡5

## 5. መላመድ ንቀትንና ማብጠልጠልን እንዲፈለፈሉ ያደርጋል።

የኢየሱስ ያደገበት ከተማ ነዋሪዎች በስብከቱ ተናድደው ነበር። ከምንም ያልወገኑ አልነበሩም። ተቆጥተዋል፣ ደግሞም ኢየሱስ ፀጥ እንዲል መደረግ እንዳለበት አስበዋል።

> በምኩራብም የነበሩ ሁሉ ይህን ሰምተው ቍጣ ሞላባቸው፥ ተነሥተውም ከከተማ ወደ ውጭ አወጡት፥ይጥሉትም ዘንድ ከተማቸው ተሠርታባት ወደ ነበረች ወደ ተራራው አፋፍ ወሰዱት፤
>
> ሉቃስ 4፡28፡29

## 6. ጓደኝነት ለመላመድ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል።

ኢየሱስ ከጴጥሮስ ጋር የነበረው ጓደኝነት የመላመድን ችግር ፈጥሯል። ይህም ኢየሱስ ጴጥሮስን ስለ አገልግሎቱ ያለውን አስተያየት በጠየቀው ጊዜ ተንፀባርቋል።

> እርሱም፡- እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው።ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡- አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።
>
> ማቴዎስ 16፡15-17

ጴጥሮስ ጭራሽ ያልገባውን ነገር እንኳን የማለት መብት እንዳለው አስቦ ነበር።

## 7. ሹመት መላመድን ይፈጥራል።

ኢየሱስ ጴጥሮስን የቤተክርስቲያን ራስ (ዋና) እንዲሆን ሹሞታል።

> እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።
>
> ማቴዎስ 16፡18

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ትንሽ ከፍ ሲደረጉ ከቀዳሚዎቻቸውና ከአስተማሪዎቻቸው ጋር እኩል የሆኑ ይመስላቸዋል። ይህ የሚያሳዝን ነው።

## 8. የበታቾች ስለ አንዳንድ ነገሮች አስተያየት ሲሰጡ መላመድ ይታያል።

ይህ ልበ ሙሉነት ነው። መሪህ የግል ነገሮችን ከአንተ ጋር መወያየቱ አንተ ከሥርዓት መውጣት አለብህ ማለት አይደለም።

## 9. የበታች መሪውን ለማረም ሲሞክር መላመድ ይታያል።

ጴጥሮስ "ከልክ በላይ ነፃ" እንደሆነ ይሰማው ጀመር። አሁን ኢየሱስን ማረም እንደሚችል አሰበ።

> ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ። አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።
>
> ማቴዎስ 16፡22

መሪ የራሱ የሆነ መጠነኛ መስተካከል ቢያስፈልገውም የበታቹ ይህንን ለማድረግ ብቁ አይደለም።

## 10.ተከታይ መሪውን መምራት ሲፈልግ መላመድ ይታያል።

ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ አገልግሎት መግለጫዎችን መስጠት ጀመረ። ጴጥሮስ ከክርስቶስ ጋር የነበረው ጓደኝነት ኢየሱስን የመምራትና የማረም ሥልጣን የሰጠው መሰለው። ሰዎች ስለኢየሱስ ስለነበራቸው አስተያየት ያደረገው ውይይት ሀሳቡ የሚፈለግ ሰው (አስተያየት ሰጪ) ያደረገው መሰለው። ምናልባትም ኢየሱስ የእርሱን ተጨማሪ ግብዓት እንደሚፈልግ አስቦ ሊሆን ይችላል።

## 11.ጥቃቅን የመላመድ ምልክቶችን ለመለየት ፈጣን ሁን።

ጴጥሮስ ከመስመር መውጣቱን ለመለየት ኢየሱስ ፈጣን ነበር።

አንድ ጊዜ ቢሮዬ ስገባ አንድ የበታች መጋቢ ከሌሎች የተወሰነ መጋቢዎች ጋር ስብሰባ ላይ ነበር። ከጠረጴዛዬ በስተጀርባ ባለው የእኔ ወንበር ላይ ተቀምጦ ሌሎቹ ሁሉ ደግሞ በዙሪያው ተቀምጠው ነበር። ስብሰባውን የምመራው እኔ የሆንኩ ይመስል አንድ ነገር እያስተማራቸው ነበር። ወዲያውኑ እንዳየሁት የሆነ ነገር ትክክል እንዳልነበር ገባኝ። ወዲያውኑ "ዳግመኛ በዚያ ወንበር ላይ እንዳትቀመጥ፤ ከዚያ ጠረጴዛ ጀርባ በድጋሚ በፍጹም አትቀመጥ! አልኩት። ቀጥዬም ለሁሉም ሰው እንዲህ አልኩ፣ "እኔ እዚህ ከሌለሁ ማንም ሰው በፍጹም ከጠረጴዛዬ ጀርባ ወይም በወንበሬ ላይ መቀመጥ የለበትም።"

## 12.በማያሻማ አነጋገር፣ በጣም የተላመደን ተከታይ ሁሉ ወደ ቀድሞ መጠኑ አውርደው።

በድንገት ኢየሱስ ከደግና ጨዋ ኢየሱስ ወደ ብረት ኢየሱስ ተለወጠ። የቅርብ ጓደኛውንና ረዳቱን በሚቻለው በመጨረሻ ከባድ ሁኔታ ገሰፀው። ጴጥሮስን "ሰይጣን" ብሎ ጠራው! አስበው! ጴጥሮስ ከመቅፅበት ወደ መጠኑ ወረደ።

## 13.መላመድን ባገኘህበት ሥፍራ ሁሉ ተናገር ደግሞም ግጠመው

በምሰብክበት ወቅት መላመድን የማይባቸው ጊዜያት አሉ። ተናግሬ ሁሉም ሰው ያንን ክፉ መንፈስ እንዲያውቀው አደርጋለሁ።

## 14.ማዛጋት የመላመድ ልዩ ባሕርይ ነው።

ሰባኪዎችና አስተማሪዎች ማዛጋትን መጠንቀቅ አለባቸው፤ በተለይ ማዛጋቶቹ ከመልዕክቱ መጀመሪያ ላይ ሲመጡ። "ቶሎ አዛጊዎች" እንዳይኖሩ ተጠንቀቅ፤ በአብዛኛው መላመድ እያሰቃያቸው ነው።

## 15.እንደ ኢየሱስ፣ ሁሉም መሪ መላመድ ሥር የሰደደባቸውን ቦታዎች መተው አለበት።

ኢየሱስ የመላመድን መንፈስ በናዝሬት ሲለይ ዋና መሥሪያ ቤቱን ወደ ቅፍርናሆም አዘዋወረ።

> ወደ ገሊላ ከተማም ወደ ቅፍርናሆም ወረደ። በሰንበትም ያስተምራቸው ነበር፤
>
> ሉቃስ 4፡31

## 16.ሁሉም መሪ ዝነኛ የሆነበትና የደስታና የመደነቅ አቀባበል የሚያገኝበት ሥፍራ የበለጠ ጊዜ ማሳለፍ አለበት።

እንደ ኢየሱስ፣ ሁሉም መሪ መላመድ ሥር በሰደደባቸው ቦታዎች መገኘት የለበትም።

## 17.መላመድን ለመከላከል በመሪዎችና በተከታዮቹ መካከል ግልፅ ልዩነቶች አድርግ።

ደቀ መዛሙርቱ ሲቀዝፉና ከባድ ሥራ ሲሰሩ ኢየሱስ ጀልባ ውስጥ ተኝቶ ነበር።

> ከዕለታቱም በአንዱ እርሱ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ታንኳ ገብቶ። ወደ ባሕር ማዶ እንሻገር አላቸው፤ ተነሡም።ሲሄዱም አንቀላፋ። ዓውሎ ነፋስም በባሕር ላይ ወረደ፥ ውኃውም ታንኳይቱን ይሞላ ነበርና ይጨነቁ ነበር።
>
> ሉቃስ 8፡22፣23

ኢየሱስ በአህያ ላይ ሲጓዝ ደቀ መዛሙርቱ ይራመዱ ነበር። ሁሉም መጋለብ እንዲችሉ ኢየሱስ አስራ ሁለት አህዮችን አልተከራየም ነበር።

## 18.በተወሰነ ደረጃ ለብቻ መሆን እንድትችል ገደብ አብጅ

ለብቻ መሆን መላመድን ያባርራል። ሁሉም ሰው ስለ አንተ ሁሉን ነገር የሚያውቅ ከሆነ በመላመዳቸው አትደነቅ።

## 19.አሰልቺነትን ስበር። አዳዲስ ሐሳቦችን አስተዋወቅ። ልዝዝ ያለ ነገር መላመድን ይፈጥራል።

ተደጋጋሚነት፣ ለዛ ቢስነትና ተመሳሳይነት ለመላመድ ሁነኛ ዓውድ ናቸው። ተመሳሳይ ስብከቶች በተመሳሳይ መንገድ ከተመሳሳይ ሰው በተመሳሳይ ሰዓት መላመድን የሚያመጡበት ሁኔታ አለ። ሕዝቡ ኢየሱስ መጥቶ በተመሳሳይ መንገድ እንዲሰብክ ሲፈልጉ እርሱ የእነርሱን አሰልቺ አካሄድ መቀላቀልን እምቢ ብሎ ወደ ቀጣዩ ከተማ ለመሄድ ወሰነ። ወዲያውኑ ማዛጋት እንደሚጀምሩ ስላወቀ ለመጓዝ ወሰነ። ዓመታዊ ፕሮግራሞችን ማካሄድ መልካም ነው፤ ይሁንና አንዳንዴ ድግግሞሹን ማቋረጥ አስፈላጊ ነው።

> ባገኙትም ጊዜ፡ ሁሉ ይፈልጉሃል አሉት።እርሱም፡- በዚያ ደግሞ ልሰብክ ወደ ሌላ ስፍራ በቅርብ ወዳሉ መንደሮች እንሂድ ስለዚህ ወጥቻለሁና አላቸው። በምኩራባቸውም እየሰበከ አጋንንትንም እያወጣ ወደ ገሊላ ሁሉ መጣ።
>
> ማርቆስ 1፡37-39

## 20.ሁልጊዜ ሰዎች እንድታደርግ የሚጠብቁህን አታድርግ

ሁልጊዜ የምታደርገውን ያንኑ እንድታደርግ ጫና የሚያደርጉብህ ሰዎች ራሳቸው ናቸው የሚላመዱት። ሰዎች የሚላመዱት ልታደርግ ያለውን ስለሚያውቁ ነው። አስታውስ፡- እጅግ የበዛ እውቀት መላመድን ያፋጥናል። አንዳንድ ጊዜ የጸሎት ስብሰባ ወይም የአምልኮ ጊዜ በሚጠበቀው ስብከት ፈንታ ማድረግ መላመድን ለመስበር ይረዳል።

## ምዕራፍ 97

# ልታሸንፍ የምትችላቸውን ውጊያዎች ብቻ ተዋጋ

ዳዊትም ተነሣ በዚያም ቀን ሳኦልን ፈርቶ ሸሸ፥ ወደ ጌትም ንጉሥ ወደ አንኩስ ሄደ። የአንኩስ ባሪያዎችም። ይህ ዳዊት የአገሩ ንጉሥ አይደለምን? ሳኦል ሺህ፥ ዳዊትም እልፍ ገደለ ብለው ሴቶች በዘፈን የዘመሩለት እርሱ አይደለምን? አሉት።ዳዊትም ይህን ቃል በልቡ አኖረ፥ የጌትንም ንጉሥ አንኩስን እጅግ ፈራ።በፊታቸውም አእምሮውን ለወጠ፥ በያዙትም ጊዜ እንደ እብድ ሆነ፥ በበሩም መድረክ ላይ ተንፈራፈረ፥ ልጋጉም በጢሙ ላይ ይወርድ ነበር። አንኩስም ባሪያዎቹን፦ እነሆ፥ ይህ ሰው እብድ እንደ ሆነ አይታችኋል ለምን ወደ እኔ አመጣችሁት? በፊቴ ያብድ ዘንድ ይህን ያመጣችሁት እብድ ጠፍቶብኝ ነውን? እንዲህ ያለውስ ወደ ቤቴ ይገባልን? አላቸው።

1ኛ ሳሙኤል 21፡10-14

በዚህ ታሪክ፣ ዳዊት ንጉሱን ሊዋጋ በሚችልበት ሁኔታ ላይ እንዳልነበር አስተዋለ፡፡ ባሕርይውን ቀይሮ እብድ መሰለ፡፡ የፍልስጤማውያንን ወገን እንደተቀላቀለም እንኳ አስመሰለ፡፡ እውነተኛ መሪ ሊያሸንፍ በማይችልባቸው ውጊያዎች ውስጥ አይገባም፡፡ ኢየሱስ ራሱ ወደ ጦርነት ከመግባትህ በፊት ዋጋውን ልትተምን እንደሚገባ አስተምሯል፡፡ መጋቢዎች ሊጨርሷቸው በማይችሏቸው የግንባታ ሥራዎች ሲጠመዱ ተመልክቻለሁ፡፡ እያደረጉ ያሉት ቢኖር ሊያሸንፉ የማይችሉበትን ጦርነት መዋጋት ነው፡፡

ውድቀት ውድቀትን ይወልዳል፡፡ ስኬት ስኬትን ይወልዳል፡፡ የምታስመዘግበው እያንዳንዱ ውድቀት ተከታዮችህን ተስፋ ያስቆርጣል፡፡ (ወኔ ይገፍፋል)፡፡ እባብን የምትሸሸውን ያህል ወደ "ውድቀት" የመግባትን ሁኔታ መሸሽ አለብህ፡፡

እውነተኛ መሪ የትኛው ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት ሊሄድ እንደሚገባ ማወቅ አለበት፡፡ አንዳንድ ነገሮችን በፍርድ ቤት በመታገል መጨናነቅ የለብህም፡፡ በቤተ ክርስቲያኔና በእኔ ላይ ወንጀል የፈፀሙ በግል የማውቃቸው ሰዎች አሉ፡፡ ማስረጃም ጭምር አለኝ፤ ሆኖም በሕግ ላልታገላቸው ወስኛለሁ፡፡ ለምን? የማላሸንፈው ትግል ይታወቀኛል!

አንድን ግጥሚያ ዳኛው ባለጋራህ መሆኑን እያወቅህ ለምን ትጫወታለህ? ጠቢብ የሆነ መሪ ሁሉ ዳኛውና መስመር ዳኛው በግልጥ ለሌላኛው ቡድን የሆኑበትን ጨዋታ መተው አለበት! አንተ ልታገባ ስትል "ከጨዋታ ውጪ"! በማለት ፊሽካ ይነፋሉ፡፡ እነርሱ ሊያገቡ ሲሉ ደግሞ በአንተ ላይ የፍጹም ቅጣት ምት እንዲመታ ፊሽካው ይነፋል፡፡ እውነታው ግጥሚያው ሳይጀመር ግጥሚያውን መሸነፍህ ነው፡፡ 100 ለ 0 የሆነ ውጤት ሊቆጠርብህና ለጥረትህ የጊነስ የክብረወሰን መጽሐፍ ላይ ልትፃፍ ትችላለህ፡፡

ታመን የአለመሆን ዘር ከዳተኛ በሆነ ሰው ልብ ውስጥ ሲገባ የእርሱን ሀሳብ ለመቀየር መሞከር በአብዛኛው ጊዜን ማጥፋት ነው፡፡ ኢየሱስ ለምን አስቆሮቱ ይሁዳን መክሮት እንደማያውቅ ገርሞህ አያውቅም? ጊዜ ሊሰጠው የተገባ አልነበረም!

አንድ ሰው መልቀቂያ ደብዳቤ በሚያስገባበት ጊዜ በአብዛኛው ምንም ጥያቄዎችን አልጠይቅም፡፡ የወሰንን ሰው ለመቀየር በመሞከር ለምን ጊዜህን ታባክናለህ? አስፈላጊ ከሆነው ጊዜ በላይ ያ ሰው እንዲቆይ አልፈልግም፡፡ አንዳንድ ጊዜ በወር ጊዜ ውስጥ መልቀቅ ይፈልጋሉ፤ እኔ ግን በአፋጣኝ እንዲለቁ እረዳቸዋለሁ፡፡

መሪ ነህ? ፍልሚያዎችህን በጥንቃቄ ምረጥና ሁልጊዜ አሸንፍ!

## ምዕራፍ 98

# እንዲመሩህ መገለጫዎችንና ምልክቶችን ተጠቀምባቸው

እነሆ፥ እኔ ያየሁት መልካምና የተዋበ ነገር ሰው እግዚአብሔር በሰጠው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ይበላና ይጠጣ ዘንድ፥ ከፀሐይ በታችም በሚደክምበት ድካም ሁሉ ደስ ይለው ዘንድ ነው ይህ እድል ፈንታው ነውና።እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ባለጠግነትንና ሀብትን መስጠቱ፥ ከእርስዋም ይበላና እድል ፈንታውን ይወስድ ዘንድ በድካሙም ደስ ይለው ዘንድ ማሠልጠኑ ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።

መክብብ 5፡18፣19

"እነሆ እኔ ያየሁት..." የሚለውን ሐረግ ታስተውላለህ፡፡ ንጉስ ሰለሞን በአብዛኛው ስለተመለከታቸው ነገሮች ነበር የሚናገረው፡፡ ምናልባት የሕክምና ታሪኬ ለምልክቶችና መገለጫዎች ፅንሰ ሀሳብ ንቁ አድርጎኝ ይሆናል፡፡ መገለጫዎችና ምልክቶች የተደበቁ ነገሮችን ይገልጣሉ፡፡ ግልፅ ስላልሆነው ነገር ይነግሩሀል፡፡

## መገለጫዎችንና ምልክቶችን ተጠቅመህ የምትለያቸው ሰባት ነገሮች

1. ታማኝ አለመሆንን ለመለየት መገለጫዎችንና ምልክቶችን ተጠቀም፡፡

ታማኝነትና ታማኝ አለመሆን በሚለው መጽሐፌ ብዙ ታማኝ ያለመሆን ምልክቶች አካፍያለሁ፡፡ ከዳተኝነት ራሱን የማያስተዋውቅ ነገር ነው፡፡ ምልክቶቹን መፈለግ አለብህ፡፡ መሪዎች ሊያስተውሏቸው የሚገቡትን ምልክቶች ማየት ካቃተህ በከሃዲዎች እጅ ትወድቃለህ፡፡

2. መላመድን ለመለየት መገለጫዎችንና ምልክቶችን ተጠቀም

በሰዎች ባሕርይ ያሉ ትናንሽ ለውጦችን በማየት መላመድን መለየት ትችላለህ፡፡ አስተያየቶቻቸው፣ ፍላጐት ማጣትና በስብሰባዎች ላይ ማዛጋት ሁሉ ጠቃሚ ጠቋሚዎች ናቸው፡፡

3. ወደ ኋላ ማፈግፈግን ለመለየት መገለጫዎችንና ምልክቶችን ተጠቀም

ወደ ኋላ ማፈግፈግ በሚለው መጽሐፌ ሃያ አምስት የሚሆኑ ወደ ኋላ የመንሸራተትን ምልክቶች አካፍያለሁ። እነዚህን መገለጫዎች ብትጠቀም ወደ ኋላ መንሸራተትን ገና ከጅምሩ መለየት ትችላለህ።

4. ይቅር ባይ አለመሆንን ለመለየት መገለጫዎችንና ምልክቶችን ተጠቀም

ብዙ ሰዎች ሌሎችን ይቅር እንዳሉ ይናገራሉ። እውነታው ግን መራርነትን ተሞልተዋል። (Forgiveness made easy) በተሰኘው መጽሐፌ ላይ የማይለቅን ይቅር አለማለት ምልክቶች ዘርዝሬአለሁ።

5. ተቀጣሪዎችን ለመቆጣጠር መገለጫዎችንና ምልክቶችን ተጠቀም

ሰዎች በሚገባ እየሰሩ ይሁኑ አይሁኑ ለማየት ሁልጊዜ አንተ አትኖርም። ለእኔ የሚሰሩትን ሰዎች ለመቆጣጠር የተወሰኑ ጠቋሚዎችን እጠቅማለሁ። በጊዜ ገደብ ውስጥ ግቦችን ማሳካት ለእኔ በጣም አስፈላጊው ጠቋሚ ነው።

6. የወደፊት መሪዎችን ለመለየት መገለጫዎችንና ምልክቶችን ተጠቀም

ጳውሎስ ይህንን አድርጓል። በ1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 3 ላይ የመምራት እምቅ ችሎታ ባላቸው ሰዎች ውስጥ ጢሞቴዎስ ሊፈልጋቸው የሚገቡን ነገሮች ዘርዝሮ አስቀምጧል።

7. በሰዎች ሕይወት ላይ ያለን የእግዚአብሔርን ጥሪ ለመለየት መገለጫዎችንና ምልክቶችን ተጠቀም

የእግዚአብሔር ጥሪ ታላቁ ምልክት የአገልግሎት ፍላጐት እንደሆነ አስባለሁ። ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ለመሥራት ፍላጐት ያላቸው ሰዎች እንዳሉ በጥንቃቄ እመለከታለሁ።

ውድ መሪ ዓይኖችህን ክፈትና ሌሎች የማያዩአቸውን ነገሮች እይ። በአብዛኛው የቤተ ክርስቲያን አባሎቼን ስመለከት ችግር ካለ አውቃለሁ። ለምንድነው? ምክንያቱም እኔ መሪ ነኝ። መገለጫዎችንና ምልክቶችን እጠቀማለሁ።

## ምዕራፍ 99

# ታማኝ መሪ ሁን

## ታማኝ ልትሆንላቸው የሚገቡ አምስት ሰዎች

እንደዚህም ሲሆን፥ በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ይፈለጋል።

1ኛ ቆሮንቶስ 4፡2

ለመሪ ዓቢይ ከሆኑ መስፈርቶች አንዱ ታማኝነት ነው። ለአምላክህ፣ ለቤተ ክርስቲያንህ፣ ለሚስትህና ለጓደኞችህ ታማኝ መሆን አለብህ። መሪ ለሚከተሉት ሰዎችም ታማኝ መሆንን መማር አለበት። ተከታዮችህ የሚሸለሙበት ጊዜ ሲሆን ታማኝ በመሆን ሽልማቶቹ ለሚገባቸው ሰዎች እንዲሸለሙ አድርግ።

## 1. ለአንተ ለሰሩት ሰዎች ታማኝ ሁን

ከአንተ ጋር አብረው የለፉትን ሰዎች በረከት አታስቀር። ከተከታዮችህ አንዱ ችግር ውስጥ ቢሆን ታማኝነትህን አሳይ። ተከታዮችህ በቅርበት እየተመለከቱህ ነው። ያዩትን ያደርጋሉ። በችግራቸው ጊዜ ካልከዳሃቸው በችግርህ ጊዜ አይከዱህም።

## 2. ለበላዮችህ ታማኝ ሁን

መሪ ለበላዮቹ ታማኝ መሆን አለበት። ዳዊት ሳዖልን የመግደል አጋጣሚው ሳለው አላደረገውም! ለንጉሱ ታማኝ ነበር። የገዛ አባቱን አልገደለም።

አቢሳም ዳዊትን፦ ዛሬ እግዚአብሔር ጠላትህን በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶታል አሁንም እኔ በጦር አንድ ጊዜ ከምድር ጋር ላጣብቀው፥ ሁለተኛም አያዳግምም አለው። ዳዊትም አቢሳን፦ እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን የሚዘረጋ ንጹሕ አይሆንምና አትግደለው አለው።ደግሞም ዳዊት፦ ሕያው እግዚአብሔርን! እግዚአብሔር ይመታዋል፥ ወይም ቀኑ ደርሶ ይሞታል፥ ወይም ወደ ሰልፍ ወርዶ ይገደላልእኔ ግን እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጄን እዘረጋ ዘንድ እግዚአብሔር ከእኔ ያርቀው አሁንም በራሱ አጠገብ ያለውን ጦርና የውኃውን መንቀል ይዘህ እንሂድ አለ።

1ኛ ሳሙኤል 26፡8-11

ከብዙ ዓመታት በኋላ ዳዊት ራሱ ስህተት ሠራ። ከወታደሮቹ መካከል ኡሪያ የተባለውን ገደለ። በዚያ ስህተት አማካኝነት ዳዊት

ሕይወቱን ሊያጣ ይችል ነበር። ብዙ መሪዎቹ ሊያምጹ ይችሉ ነበር። ይሁንና ይህ አልተከሰተም። ሰዎቹ ለንጉሡ ሥልጣን ታማኝ ነበሩ። በምሳሌ ሰለተማሩ በጌታ የተቀባውን መግደልን እንቢ አሉ።

## 3. ለጓደኞችህ ታማኝ ሁን

መሪ ለጓደኞቹ ታማኝ መሆን አለበት። ዳዊት ንጉስ ሲሆን ያለበት ሥፍራ ልዩ ጥቅም ያለው መሆኑን ተረዳ። በነገሰ ጊዜም ለቀድሞ ጓደኛው በጐነትን የሚያደርግበትን መንገድ ጠየቀ።

> ዳዊትም፦ ስለ ዮናታን ቸርነት አደርግለት ዘንድ ከሳኦል ቤት አንድ ሰው ቀርቶአልን? አለ።
>
> 2ኛ ሳሙኤል 9፡1

እነዚህ ለጓደኞችህ የመታመን ተግባራት ሌሎችን ስለ መሪያቸው እውነተኛ ባሕሪይ ያስተምራል። ጥሩ ባሕሪይ የሚስብ ነው። ሰዎች በይበልጥ ጥሩ ልብ ያለውን ሰው ወደ መከተል ያዘነብላሉ።

## 4. ለባለቤትህ ታማኝ ሁን

መሪ ለባለቤቱ ታማኝ መሆን አለበት። ጋብቻ ለብዙዎች አስቸጋሪ ነገር ሰለሆነ ትዳሩ ስኬታማ የሆነ ማንም ሰው ተፈጥሯዊ መሪ ተብሎ ይወደሳል። የቤት ውስጥ ጉዳዮችህ በቁጥጥርህ ሥር በመሆናቸው ምክንያት በሕብረተሰቡ ውስጥ ተፈጥሯዊ መሪ ትሆናለህ። ለባለቤትህ መታመን ራስን መግዛትንና ክርስቲያናዊ ፍቅርን ያካትታል። ሁሉም ሰው ራሱን የሚገዛና ፍቅር ያለው መሪ እንዲኖረው ይፈልጋል።

> እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ የማይነቀፍ፥ የአንዲት ሚስት ባል፥ ልከኛ፥ ራሱን የሚገዛ፥ እንደሚገባው የሚሰራ፥ እንግዳ ተቀባይ፥ ለማስተማር የሚበቃ፥
>
> 1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡2

## 5. ለራእይህ ታማኝ ሁን

መሪ ለራእዩ ታማኝ መሆን አለበት። ቀጣዩ እርምጃው ምን እንደሆነ የማይታወቅን ሰው ማንም መከተል አይፈልግም። ከብዙ ዓመታት በፊት ነፍሳትን የመማረክና ሰዎችን በክርስቶስ ላይ የማነፅ ፍላጐት እንዳለኝ አውጃለሁ። አሁንም ከዚህ ራእይ ጋር ነው የምንቀሳቀሰው። በመሰረቱ ላይ ብዙ ጎርፍ ቢያልፍም ራእዩ አሁንም አልተለወጠም- ነፍስ ነፍስ ነው። ለእግዚአብሔርም ክቡር ነው። ጠበቃ ወይም ዶክተር ሊሆን ይችላል ነፍስ ነፍስ ነው፣ ለእግዚአብሔርም ክቡር

ነው። አቶሎኒ ሻጭ፣ ሴተኛ አዳሪ ወይም ነርስ ልትሆን ትችላለች ነፍስ ነፍስ ነው፣ ለእግዚአብሔርም ክቡር ነው።

ራእይህን ጠብቅ። መጽሐፍ ቅዱስ በድንገት የመለዋወጥ ዝንባሌ ካላቸውና አደገኛ አዟዟር ከሚታጠፉ ሰዎች ጋር ልትቆራኝ እንደማይገባ ያስተምራል።

ሹፌሩ በተደጋጋሚ በድንገት የሚታጠፍበት መኪና ውስጥ መሆን እጅግ አደገኛ ነው።

> ልጄ ሆይ፥ እግዚአብሔርንና ንጉሥን ፍራ፥ ከዓመፀኞችም ጋር አትደባለቅ።
>
> መከራቸው ድንገት ይነሣልና ከሁለቱ የሚመጣውን ጥፋት ማን ያውቃል?
>
> ምሳሌ 24፡21-22

መሪ ነህ? የሚታመን፣ የማያቋርጥ እና ታማኝ ሰው ሁን። ብዙ ተከታይ ይኖርሃል።

ምዕራፍ 100

# ጥላቻንና ተቃውሞን ተቋቋም

## እያንዳንዱ ክርስቲያን ስለተቋውሞ ሊያውቃቸው የሚገቡ ስድስት ነገሮች

1. ተቃውሞን ማስተናገድ ካልቻልክ መሪ መሆን አትችልም።

በ

አመራር ጎዳና ላይ ባቀናሁበት ጊዜ ሁሉ ከባድ ተቃውሞ ገጥሞኛል። አንተን መቃወም ዕጣ ፈንታዎች የሆኑ ጠላቶችን እንዳመጣጣቸው ማስተናገድ ካልቻልክ ታላቅ መሪ መሆን አትችልም። ሁሉም ታላቅ መሪ ብዙ ጠላቶች አሉት!

2. መሪው ታላቅ በሆነ ቁጥር ጥላቻውና ተቃውሞውም እንዲሁ ታላቅ ነው።

የኤልያስን ሕይወት ተመልከት። በንጉሱና በንጉሱ ሚስት ይጠላ ነበር። በሕይወቱ ላይ የሞት አዋጅ ታውጆበት ነበር። ኤልያስ በአገልግሎቱ ምክንያት ይጠላና ይታደን ነበር።

> አብድዩም አለ። እኔን ባሪያህን እንዲገድል በአክዓብ እጅ አሳልፈህ ትሰጠኝ ዘንድ ምን ኃጢአት አድርጌአለሁ?አምላክህ ሕያው እግዚአብሔርን! ጌታዬ ይፈልግህ ዘንድ ያልላከበት ሕዝብ ወይም መንግሥት የለም ሁሉም። በዚህ የለም ባሉ ጊዜ አንተን እንዳላገኙ መንግሥቱንና ሕዝቡን አምሎአቸው ነበር። አሁንም፥ እነሆ። ሂድ፥ ኤልያስ ተገኘ ብለህ ለጌታህ ንገር ትለኛለህ።
>
> 1ኛ ነገሥት 18፡9-11

ኤልያስ ከታላላቅ ነብያት አንዱ እንደነበር ሁላችን እናውቃለን። በአመራርህ ታላቅ በሆንክ ቁጥር የበለጠ ትጠላና ትታደናለህ። የሰው ተፈጥሮ የሌላውን የሥራ ባልደረባ ስኬት መታገስ አይችልም። ለጥላቻና ለተቃውሞ ዝግጁ ካልሆንክ፣ እባክህ ከመሪነት ሥፍራህ በአስቸኳይ ልቀቅ። ሁሉም ሰው ስለአንተ ጥሩ የሚያወራ ከሆነ ምናልባት ግብዝ ልትሆን ትችላለህ።

ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ፥ ወዮላችሁ፤ አባቶቻቸው ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲሁ ያደርጉላቸው ነበርና።

ሉቃስ 6፡26

## 3. እያንዳንዱ አዲስ የአመራር እርምጃ አዲስ የጥላቻና የተቃውሞ ቀስቶችን ያስከትላል፡፡

እያንዳንዱ የጠንካራ አመራር እርምጃ ዕውን የሆነ ጥላቻ ይገጥመዋል፡፡ ቤተክርስቲያኔን ስጀምር ልታስቡት በምትችሉት ስም ሁሉ ተጠርቼ ነበር፡፡ ኢየሱስ ራሱ የብልኤልዘቡልን ኃይል ትጠቀማለህ ተብሎ ተከሶ ሰለነበር ስለእርሱ ክብርን በሚነካ በማንኛውም ስም መጠራትን እንደ እድል እቆጥረዋለሁ፡፡ መተቸት የማትፈልግ ከሆነ አንተ መሪ መሆን አትችልም፡፡ ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ዳግም ለመገንባት ደፍሮ በተነሳ ጊዜ ሁሉም ሰው ደስተኛ እንደነበረ ልታስብ ትችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ሰንባላጥና ጦብያ እርሱን በመቃወም ተነሱ፡፡

ሖሮናዊውም ሰንባላጥ፥ ባሪያውም አሞናዊው ጦብያ፥ ዓረባዊውም ጌሳም በሰሙ ጊዜ በንቀት ሳቁብን፥ ቀላል አድርገውንም። ይህ የምታደርጉት ነገር ምንድር ነው? በውኑ በንጉሡ ላይ ትሸፍቱ ዘንድ ትወድዳላችሁን? አሉ።

ነህምያ 2፡19

## 4. ተቃውሞ በአብዛኛው የሚመጣው አሳማኝ በሆነ ክስ መልክ ነው

ዳዊት ጐልያድን ስለመግደል ሲያወራ ወንድሞቹ በንዴት ምላሽ ሰጡ፣ ትዕቢትና የልብ ክፋት አለብህ ብለው ከሰሱት፡፡ በአብዛኛው ለጥሩ ሰዎች ከሁሉም የባሰ ስም መስጠቱ አያስገርምም?

ታላቅ ወንድሙም ኤልያብ ከሰዎች ጋር ሲነጋገር ሰማ የኤልያብም ቍጣ በዳዊት ላይ ነድዶ። ለምን ወደዚህ ወረድህ? እነዚያንስ ጥቂቶች በጎች በምድረ በዳ ለማን ተውሃቸው? እኔ ኵራትህንና የልብህን ክፋት አውቃለሁና ሰልፉን ለማየት መጥተሃል አለው።

1ኛ ሳሙኤል 17፡28

ዳዊት በመጀመሪያ የገዛ ወንድሞቹን ጥላቻ ከዚያም የአባቱን የሳዖልን ጥላቻ ማስተናገድ ነበረበት፡፡ ጥላቻና ተቃውሞ የአመራር አካል ናቸው፡፡

## 5. ለተቃውሞ ጠንካራን ግንባር አዳብር።

> እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ፥ ይላል እግዚአብሔር፡-
>
> ኤርምያስ 1፡8

**በተቃውሞ አትረበሽ፣ አትከልከልም። ትንሹ ተቃውሞ ሊያቆምህ ከቻለ አንተ ደካማ መሪ ነህ።**

> እነሆ፥ ፊትህን በፊታቸው ግምባርህንም በግምባራቸው አጠንክሬአለሁ።ከቡላድ ድንጋይ ይልቅ እንዳለ አልማዝ ግምባርህን አጠንክሬአለሁ እነርሱ ዓመፀኛ ቤት ቢሆኑ አትፍራቸው ከፊታቸውም የተነሣ አትደንግጥ።
>
> ሕዝቅኤል 3፡8፣9

## 6. ተቃውሞ በአብዛኛው በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የመሆንህ ምልክት ነው።

**ደስ ተሰኝ፣ መልካም ዜና አለ። ሰይጣን ሕይወት የሌለውን ቁራጭ ግንድ አያጠቃም። አሁን አንተ ለሰይጣን አስጊ ነህ፤ ለዚያ ነው የሚያጠቃህ።**

> በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።
>
> 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡12

ምዕራፍ 101

# የአንተ "ዓይነት" ያልሆኑ ሰዎችን ጨምሮ ከሁሉም ዓይነት ሰዎች ጋር ተዛመድ

መሪ ሰዎች እንዲከተሉት ለማድረግ እየሞከረ ያለ ሰው ነው። አንዳንድ ጊዜ መሪዎች ተከታዮች ሊኖሯቸው እንደሚገባ የሚረሱት ይመስለኛል። መሪ ከሆንክ እየተከተሉህ ያሉ ሰዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ አለብህ። አለበለዚያ አንተ መሪ አይደለህም። የአንተ "ዓይነት" ሰው በዚህ ምድር ላይ ውስን ዝርያ መሆኑን መገንዘብ አለብህ። በአንተ የዕድሜ ክልል የሆኑ የአንተ ዓይነት ታሪክ፣ የቆዳ ቀለምና አነጋገር ያላቸውን ብዙ ሰዎች ላታገኝ ትችላለህ። እንደመሪ ስኬታማ መሆን የምትፈልግ ከሆነ ከሁሉም ዓይነት ሰዎች ጋር፣ በተለይም እንዳንተ ዓይነት ካልሆኑ ሰዎች ጋር መዛመድ መቻል እንዳለብህ እጅግ በጊዜ መገንዘብ አለብህ።

> አይሁዳዊ ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይተባበር ወይም ይቃረብ ዘንድ እንዳልተፈቀደ እናንተ ታውቃላችሁ፤ ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኩስና የሚያስጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ፤
>
> የሐዋርያት ሥራ 10፡28

ጴጥሮስ ስለ አመራር ባለው መረዳት እጅግ ጥብቅ ከመሆኑ የተነሳ አገልግሎቱን በትንሽ የአይሁድ ቡድኖች አስቀረው። እግዚአብሔር ግን ለእርሱ የገዘፈ ዕቅድ ነበረው። እግዚአብሔር ሌሎች ብዙ ሰዎችን እንዲደርስ ፈለገ። ይህንን መጽሐፍ እያነበብክ እያለህ እግዚአብሔር የሰፋ የአገልግሎት አድማስ ሊሰጥህ እንደሚፈልግ ይሰማኛል። አጭር እይታ ያለው ሰው አትሁን። የአንተን ዓይነት ከሆኑ ይልቅ የበዙ ከአንተ የተለዩ ሰዎች አሉ።

አባቴ ከጋና እናቴ ደግሞ ከስዊዘርላንድ ናት። የተወለድኩት በእንግሊዝ ቢሆንም ዕድሜዬን በሙሉ በጋና ኖሬአለሁ። መልኬ ጥቁርም ነጭም አይደለም። በማድግበት ጊዜም አብዛኞቹ ጓደኞቼ አውሮፓዊ ወይም ነጭና ጥቁር ድብልቅ ወላጆች ነበሯቸው። ይህም የሆነው እናቴ ስዊዘርላንዳዊ በመሆኗ ብዙ አውሮፓዊ ጓደኞች ስለነበሯት ነበር።

አባቴ ለየት ያለ ሰው ነበር። ቆየት ያሉ ሙዚቃዎችን ይወድ ነበር፣ ካርታ ይጫወት ነበር እንዲሁም የውድድር ፈረሶች ነበሩት። በዚህ ምክንያት አብዛኞቹ ጓደኞቹ ጋናውያን አልነበሩም። አብዛኞቹ ጓደኞቹ እንግሊዛውያን፣ ሕንዳውያን ወይም ሊባኖሳውያን ነበሩ። ሳድግ የትርፍ ጊዜ ተግባሮቼ ቴኒስ፣ ስኳሽ (እንደ ሜዳ ቴኒስ ዓይነት ጨዋታ) ፈረስ ግልቢያ እና ዋና ነበሩ። በዓለም ላይ የእኔ ዓይነት አስተዳደግ ያላቸው እጅግ ጥቂት ሰዎች እንደሆኑ ላረጋግጥልህ እችላለሁ። ልዩ ስለሆንኩ ሳይሆን ይሄ ያልተለመደ የባህልና የሁኔታዎች ቅንብር ነው።

መሪ እንድሆን ተደርጌ ከሆነ ያደግሁት፣ በቁጥር ስንት ሰዎች አሁን እንዳካፈልኩህ ዓይነት ተመሳሳይ ታሪክ እንዳላቸው አንተ ንገረኝ? ብዙ አይደሉም! የብዙ ሰዎች መሪ ለመሆን የእኔ ዓይነት ታሪክ ከሌላቸው ሰዎች ጋር መዛመድ አለብኝ። አብዛኞቹ ጓደኞቼ እጅግ የተለየ ታሪክ ነበራቸው። ከእነርሱ ጋር ግን እንዲሁ በተፈጥሮና በቀላሉ እዛመዳለሁ።

ደካማ የትምህርት ታሪክ ያለህ መጋቢ ከሆንክ ሀብታሞችን ጨምሮ ከሁሉም ዓይነት ሰዎች ጋር ተዛመድ በእርግጠኝነት የተወሰኑ ሀብታም ሰዎች በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያስፈልጉሃል። አንተ ትምህርት ስለጐደለህ ብቻ የተማሩ ሰዎችን ሁሉ አትግፋ። ራስህን ማስተማር ትችላለህ!

ራስህን መሪ እንደሆንክ ትቆጥራለህ? ራስህን ጠይቅ "ምን ዓይነት ሰው ነኝ? ምን ዓይነት ሰው አይደለሁም?" ከሁሉም ዓይነት ሰው ጋር ለመዛመድ ወስን።

> ደካሞችን እጠቅም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁ፤ በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ፥ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ።በወንጌልም ማኅበረተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ።
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 9፡22፣23

ምዕራፍ 102

# በውለታቢስነት አትደነቅ

ሁሉም መሪ ከውለታቢስነት ጋር ፊት ለፊት ይፋጠጣል። ሰዎች ለምትሰጣቸው አገልግሎት አመስጋኝ አይደሉም። ይህንን እስክትደርስበት ጊዜ አይፈጅብህም። ከብዙ ዓመታት በፊት የምወዳቸው ሰዎች ዞረው ሊጎዱኝ እንደሚችሉ ደረስኩበት። ያሰለጠንኳቸው ሰዎች እርዳታ ማግኘታቸውን አላስታወሱም። ይህም ሆኖ በሰዎች ማመንና ሰዎችን ማመንን ቀጥያለሁ። ምንም አማራጭ የለኝም። ለውለታቢሲስነት አጸፋ ብመልስ ሥፍራዬን አጣለሁ።

> ኢየሱስ፦ ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው።
>
> ዮሐንስ 10፡32

ኢየሱስ ውለታቢስነትን ተለማምዷል። የተገደለው ምስጋና በሌላቸው አይሁዳውያን ነበር ። ለሃያ ዓመታት ካገለገሉ በኋላ መጋቢዎች ከከተማ ሲባረሩ አይቻለሁ። ለዚህ ነው የቤተ ክርስቲያኔ መተዳደሪያ ደንብ እኔን በማንኛውም ሁኔታ ለማባረር ለማንም ሰው መብት የማይሰጠው። ከዚህ ቀደም አይቸዋለሁና የሰው ተፈጥሮ እንዳሻው እንዲሄድ ከተፈቀደለት የእኔም መጨረሻ ከጌታዬ የተሻለ እንደማይሆን አውቃለሁ። ኢየሱስ የተገደለው በበጎ ተግባሮቹ ምክንያት ነበር ። በወንበዴ ለወጡት። ይሁንና ክፉ መንፈስ ለሆነው ለውለታቢስነት ምንም መልስ አልሰጠም።

ከሰዎች ምስጋናን አትጠብቅ። መሪ ሽልማት ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር ነው የሚያየው።

> ባሪያ ቢሆን ወይም ጨዋ ሰው፥ እያንዳንዱ የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና።
>
> ኤፌሶን 6፡8

መጽሐፍ ቅዱስ ብድራትህ በእግዚአብሔር እንጂ በረዳሃቸው ሰዎች የሚወሰን አለመሆኑን ያስተምራል። በበቂ ሁኔታ ሊሸልምህ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከሰው ብዙ አትጠብቅ ብድራትህን ከእግዚአብሔር ጠብቅ።

ከብዙ ዓመታት በፊት ስብከት ከጨረስኩ በኋላ ሰዎች እንዲያመሰግኑኝ መጠበቅ አቆምኩ። ሰዎች ቢያመሰግኑኝ ባያመሰግኑኝ ግድ አይለኝም! አድናቆትን ከሰዎች እየጠበቅሁ አይደለም። የእኔ ሥራ መጽሐፍ ቅዱስን መስበክ ነው። ግዴታዬን ተወጥቻለሁ። የሰውን አድናቆት ላለመፈለግ ስወስን የነፃነት ስሜት ተሰማኝ። ከሰዎች ነፃ ሆንኩ ተጠሪነቴም ለእግዚአብሔር ሆነ።

ምዕራፍ 103

# ሰዎች አንተን ማመንና መከተል እንዲችሉ እንዲያውቁህ ፍቀድላቸው፡፡

ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፤ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን፥ ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኋለን፤

1ኛ ዮሐንስ 1፡1፣2

ሰዎች የእውነት መሆንህን እንዲያውቁ አድርግ! ሁሉም ሰው በፍጥነት እውነተኛ መሪን ይከተላል፡፡ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ለምንድነው? እኛ እንድናውቀውና እንድናምነው ነው፡፡ ስለዚህም እንድንሰማው፣ እንድናየውና እንድንነካው ፈቀደልን፡፡ ሰዎች አንተን የመስማት፣ የማየትና የመዳሰስ እድል አላቸውን? ምንም ስህተቶች የሌሉበት ምስጢራዊና ኃያል ሰው ነህ? ግልጽነት ተከታዮችን ያፈራል፡፡

መሪ ነህ? እንግዲያውስ ሰዎች እውነተኛ ማንነትህን እንዲያውቁ መፍቀድ አለብህ፡፡ ማንም ሰው የተሰወረን ነገር መከተል አይፈልግም፡፡ የተደበቀ ነገር የማይታወቅ ነገር እንዳለ ያሳየናል፡፡ ድብቅ ሰው ሊመጣ ስላለ የሆነ ነገር ያስተገባል፡፡

አንድ መጥፎ ነገር ሊደርስበት ወደ ሚችል ጭለማ ሸለቆ ድብቅ ሰውን ተከትሎ መግባት ማን ይፈልጋል? ስለ መሪነት አንድ ጠቃሚ ምስጢር ልንገርህ፡፡ ግልፅ በሆንክ ቁጥር ሰዎች በፍጥነት አመራርህን ይከተላሉ፡፡ ይበልጥ ፍጹም ስትሆን ይበልጥ ሰዎች ይከተሉሃል አላልኩም፡፡ ሁሉም ሰው ጐረቤቱ ፍጹም እንዳልሆነ ያውቃል፡፡ በምድር ላይ ፍጹም የሆነ ሰው አለመኖሩ ምስጢር አይደለም፡፡ ስለ ድክመቶቹ ግልፅ እና እውነተኛ የሆነ ሰው የበለጠ ተከታዮች ይኖሩታል፡፡ መጋቢ ከሆንክ ሰዎች የእውነት መሆንህን እንዲያውቁ አድርግ! ሁሉም ሰው እውነተኛን መሪ በፍጥነት ይከተላል፡፡

## ምዕራፍ 104

# በምሳሌነት በሰዎች ላይ ተፅዕኖ አሳድር

እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤

ዕብራውያን 5፡7

እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን።

የሐዋርያት ሥራ 6፡4

ከላይ ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለምን እንደጠቀስኩ ሊገርምህ ይችላል። በሁለቱ መካከል ያለው አንድነት ምንድነው? የመጀመሪያው በምድር ሳለ ኢየሱስ ስለነበረው የጸሎት ህይወት የሚናገር ነው። ሁለተኛው ኢየሱስ ከሄደ በኋላ ጴጥሮስ ስለነበረው የጸሎት ሕይወት የሚናገር ነው። ኢየሱስ ጸሎትን በምሳሌነት ለደቀመዛሙርቱ  አስተማራቸው። የኢየሱስ የጸሎት ሕይወት በጴጥሮስ ላይ ተፅዕኖ አድርጎበት ነበር።

## የሚናገሩትን አድምጥ የሚያደርጉትን ግን አታድርግ

ከብዙ ዓመታት በፊት አንድ ሰው ቄሱ የሚናገረውን እንዳደምጥ የእርሱን አርአያነት ግን እንዳልከተል እንደመከረኝ አስታውሳለሁ። እንዴት እንግዳ ነገር ነው! የአንድን ሰው ቃል እንጂ አርአያነቱን አለመከተል እጅግ አስቸጋሪ ነው። በቀድሞው የሕክምና ትምህርት ቤቴ የሰው አካል ጥናት ቤተ ሙከራ ውስጥ የታተመ አንድ የቆየ የቻይና ምሳሌአዊ አነጋገር ነበር።

እንዲህ ይል ነበር፣ “ሰምቼ እረሳለሁ፣ አይቼ አስታውሳለሁ፣ አድርጌ እረዳለሁ።” ይህ ምሳሌ ሰዎችን በሚያዩት ተፅዕኖ ስለማድረግ ኃይል ይነግረኛል። ያየኸውን መቼም አትረሳም። ከምትሰማው አስራ አንድ በመቶ እጅ ብቻ እንደምታስቀር ታውቃለህ?

ኢየሱስ ስለጸሎት ትምህርት ብቻ አላስተማረም። ጸሎትን ተገበረው። ጸሎትን ኖረው። ለዚህ ነው ጴጥሮስ ከጸሎት ህይወቱ ላለመረበሽ እጅግ የተሰጠ የነበረው። ዛሬ ብዙ አገልጋዮች የጸሎትን ጠቀሜታ አያውቁም። ከሚፀልይ ሰው ጋር ኖረው አያውቁም። ሲተገበር

አይተውት አያውቁም፡፡ ከቃሎችህ ይልቅ አርአያነትህ ይበልጥ ጠቃሚ መሆኑን አስታውስ፡፡

ወዳጄ፣ መሪ መሆን ትፈልጋለህ? እባክህ አርአያነትህ ከቃሎችህ ይልቅ ወሳኝ መሆኑን አስታውስ!

## ምዕራፍ 105

# ፍላጐትህ ለመሪነት የመጠራትህ መገለጫ መሆኑን ዕውቅና ስጠው

መሪ ነህ? መሪ መሆን ትችላለህ? መልሱ አዎን ነው! በዚህ ምዕራፍ ከውስጥ ያለውን መሪ የሚገልጡ አንዳንድ መገለጫዎችን አሳይሃለሁ። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ የመሪነት ብቃት ያላቸውን ሰዎች እንዲፈልግ ነግሮታል።

## መሻት

ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው።

1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡1

ጳውሎስ ለአገልግሎቱ ፍላጐት የነበራቸውን ሰዎች ሲፈልግ መመልከት ይገርማል። ጢሞቴዎስ ለአገልግሎቱ ፍላጐት ባላቸው ሰዎች ውስጥ አንዳንድ ብቃቶችን እንዲፈልግ ታዝዞ ነበር። የመምራት ፍላጐት በውስጥ ያለ መሪ መገለጫ ነው። ሌሎችን ሰዎች የመርዳት ፍላጐት እግዚአብሔር የመሪነትን ስጦታ እንደሰጠህ የሚያሳይ ትልቅ መገለጫ ነው። ባሉህ ጥሩ ነገሮች ሌሎችን ለማገልገል መፈለግ ትልቅ የመሪነት ምልክት ነው።

ወንድሞች ሆይ፥ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው።

ሮሜ 10፡1

ጳውሎስ አይሁዶችን የመርዳት ፍላጎት ነበረው። ያለማቋረጥ በዚህ ፍላጎት ይቸገር ነበር። እውነተኛ መሪነት ሁሉ የምትወዳቸውን ሰዎች ለመርዳት ካለ ሸክም የሚመጣ ነው። ከሁሉም የሚልቀው የመሪነት ምልክት መሪን ወደ ተግባር አስገድዶ የሚያስገባው ሸክምና ፍላጎት ነው። ያ የሚያይል ሸክም/ፍላጎት በሁሉም ታላቅ መሪ ውስጥ የሚገኝ የጋራ ገጽታ ነው።

ብዙ ኅዘን የማያቋርጥም ጭንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ፤ አልዋሽምም፤ ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል።በሥጋ

ዘመዶቼ ስለ ሆኑ ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና።

ሮሜ 9፡1-3

አንዳንድ ሰዎች በሕይወት ባሉ ችግሮች ውስጥ ያልፋሉ። ከሕመማቸው ካገገሙ በኋላ እነርሱ ባለፉበት ሕመምና ጭንቀት ውስጥ ሌሎች እንዳይገቡ የመርዳት ጠንካራ ፍላጎት አላቸው። እውነተኛ አባት ልጆቹ እርሱ ሊኖረው ያልቻለው እንዲኖራቸው ይፈልጋል። እውነተኛ መሪ ተከታዮቹ ከራሱ የተሻሉ እንዲሆኑ ይፈልጋል። ኢየሱስ አለ፣

እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፥

ዮሐንስ 14፡12

ኢየሱስ እርሱ ካደረጋቸው የላቁ ነገሮችን ተከታዮቹ እንዲያደርጉ ይፈልግ ነበር። ሰዎች ታላቅ እንዲሆኑ የመርዳት ፍላጎት ከሌለህ ምናልባት መሪ አይደለህም። ራስህን የመርዳት ፍላጎት ብቻ ከሆነ ያለህ፣ ያ መሪነት አይደለም! መሪነት ሌሎች ሰዎች ለራሳቸው ታላላቅ ነገሮችን ማሳካት እንዲችሉ የመርዳት ፍላጎት ነው። የጠፉትን የትኛውንም ዋጋ ከፍሎ የመማረክ ፍላጎት ያለው ሰው ለወንጌል ዓላማ መሪ ነው።

በአገልግሎቴ ጅማሬ ወቅት የመጋቢ፣ ወንጌላዊ ወይም ሐዋርያ ሥራ ምን እንደሆነ እንኳን አላውቅም ነበር። እነዚህ መቼም የማልጨብጣቸው ርቀው የተቀመጡ ሥፍራዎች እንደሆኑ አስብ ነበር። ማድረግ የምፈልገው ነገር ቢኖር ሰዎች ኢየሱስን እንዲተዋወቁት መርዳት ብቻ ነበር። ማድረግ የምፈልገው ሰዎች በክርስቶስ እንዲያድጉ ማድረግ ብቻ ነበር። ሰዎች አንዴ በጌታ ካደጉ ብዙ ችግሮቻቸው እንደሚሄዱ ይሰማኝ ነበር። ሰዎችን የመርዳት ፍላጎት የእግዚአብሔር ጥሪ መገለጫ ነው።

## መሪነትን አለአግባብ መጠቀም

የገንዘብ፣ ስልጣንና ዝና ፍላጎት ያላቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ። ሳይታወቃቸው የመሪነትን ሥፍራ እንዚህን ነገሮች ለማግኘት ለመጠቀም ያስባሉ። ያ መሪነት አይደለም! ያ የቫምፓየርነት ጥበብ ብዬ የምጠራው ነው። ቫምፓየር ደም መጣጭ የሌሊት ወፍ፣ ወይም በሰው አገላለፅ፣ ያለርህራሄ ሌሎችን የሚያድን ሰው ነው።

አፍሪካና ብዙ የዓለም አገራት የአገራቸውን ሀብት በሚጠጡ ቫምፓየር መሰል መሪዎች የታደሉ ናቸው። የሚያሳዝነው አንዳንድ

ቤተክርስቲያናት እንደ ቫምፓየሮች የቤተክርስቲያኒቱን ሀብትና ሕይወት የመጠጡ መሪዎችን አሳልፈዋል። ቫምፓየር መሪ አይደለም፤ መሪ ደግሞ ቫምፓየር አይደለም! ጴጥሮስ ለቤተክርስቲያን በፃፈው ደብዳቤ ይህንን በመቃወም አስጠንቅቋል።

> እንግዲህ እኔ፥ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ፥ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆንጐብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤
>
> ፩ኛ ጴጥሮስ 5፡1-3

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው፣ የተሳሳተ መነሻ ሀሳብ የነበራቸው መሪዎች በጴጥሮስ ጊዜ ያልተለመዱ አልነበሩም። በእርግጠኝነት በእኛ ዘመን ያልተለመዱ አይደሉም። እግዚአብሔር የመሪነትን ቀንበር ለመሸከምና የሚጠይቀውን ዋጋ ለመክፈል የሚስማሙ ወንዶችንና ሴቶችን እየፈለገ ነው። በውስጥህ ያለው ሌሎችን የመርዳት ፍላጐት እግዚአብሔር በሕይወትህ ላይ ያለው ጥሪ ምልክት ነው። የመርዳት ጊዜ ነው። ይህንኑ ለማድረግ እግዚአብሔር አንተን ለማስነሳት ይፈልጋል። ይህንን መጽሐፍ ስታነብ የመምራት ቅባት በኢየሱስ ስም በአንተ ላይ ይሁን።

ምዕራፍ 106

# ከአንድ ድንገተኛ ሁኔታ ወደ ሌላ አትቻኮል

## ሁለት የአመራር ዓይነቶች

### 1. የአደጋ ጊዜ የአመራር ዘይቤ

ይህ ከአንድ ቀውስ ወደ ሌላ መሯሯጥን ያካትታል። ውጤታማ የሆነ የአመራር ዘይቤ አይደለም። የአደጋ ጊዜ አመራር ዘይቤ ላለው መሪ አንድን ችግር መፍታት እውነተኛ ያልሆነን የደህንነት ስሜት ይሰጠዋል። አንድን ችግር ካረጋጋ በኋላ አንድ ታላቅ ነገር እንዳሳካ ይሰማዋል። ቀጣዩ ችግር እየተጠነሰሰ መሆኑን ግን አያውቅም። የአመራር ችግሮችን፣ የገንዘብ ችግሮች በአመፅ የመጡ ችግሮችን፣ የዕዳ ችግሮችንና የመከፈል ችግሮችን የሚፈቱ መጋቢዎች ሁልጊዜ ሙሉ በሙሉ የተጠመዱ ናቸው። ከዚህ የተሻለ መንገድ ግን አለ!

### 2. የመከላከል አመራር

የመከላከል አመራር የእነዚህን ሁሉ ችግሮች መከሰት የሚከላከልን የአመራር ዘይቤ ያካትታል። በዚህ የአመራር ዘይቤ ሥር ቁጥራቸው ያነሰ ችግሮች ናቸው ያሉት። የመከላከል የአመራር ዘይቤ ያላቸው ሰዎች በአብዛኛው የስልጠና ኮንፈረንሶችን፣ የእረኞች ካምፕ፣ የትምህርት ሴሚናሮች ወዘተ... ያዘጋጃሉ። እንደዚህ ዓይነት መሪዎች ይበልጥ ፈታ ያሉ እና ቤተክርስቲያኖቻቸውን ወይም ድርጅቶቻቸውን በይበልጥ የሚቆጣጠሩ ናቸው።

## ሰባት የመከላከል አመራር ደረጃዎች

### 1. ሰዎችህ እንዲያውቁ የምትፈልገውን አስተምራቸው።

ሁሉንም ነገር ማስተማር እንደሚቻል ደርሼበታለሁ። የበታችህ ከሆኑት ማግኘት የምትፈልገውን የትኛውንም ነገር በማስተማር ማግኘት ትችላለህ። በምድር ላይ ያለ ትምህርት ሁሉ የሚሰጠው በሰው ነው። የምትፈልገውን ውጤት ለማግኘት ማስተማርን ተማር።

## 2. ሰዎች ታማኝ እንዲሆኑ አሰልጥናቸው፡፡

ታማኝ አለመሆን በድርጅቶች ውስጥ ለሚከሰቱ ችግሮች አንዱ ምክንያት ነው፡፡ አመፀኞችና ከዳተኞች ሙሉ ቤተክርስቲያናትን የሚያናጉበት ሁኔታ አለ፡፡ ታማኝነትን በማጉላት ችግሮችህን መቀነስ ትችላለህ፡፡

## 3. መደበኛ ኮንፈረንሶችን፣ ወጣ የሚባልባቸውን ፕሮግራሞችና ካምፖችን አዘጋጅ

እነዚህ የማስተማሪያና የመወያያ አጋጣሚዎች ናቸው፡፡

## 4. ገንዘብን አትበደር፡፡

ዕዳዎች አለመረጋጋትን ይፈጥራሉ! በዕዳ ምክንያት ዓለምህ በሞላ በአንተ ላይ ሊደረመስ መቻሉ የሚረብሽ ነው፡፡ ዕዳን እጠላለሁ፡፡ አልበደርም፡፡ ገንዘብን እንድትበደርም አልመክርህም፡፡ ያለብድር መኖር ይቻላል፡፡

> እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፥ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና።
>
> ሮሜ 13፡8

## 5. ጠቃሚ ያልሆኑ ነገር ግን አስቸኳይ ጥያቄዎችንና ጠቃሚ የሆኑ ግን አስቸኳይ ያልሆኑ ተግባሮችን ለይተህ እወቅ፡፡

ኢየሱስ በአስቸኳይ ወደ አልዓዛር እንዲሄድ ተጠርቶ ነበር፤ ይሁንና ለእርሱ ሌሎች ነገሮችን ማከናወን ይበልጥ አስፈላጊ ነበር፡፡ ግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ባልታቀዱ ተግባሮች አይሯሯጥም ነበር፡፡ ቅደም ተከተል የወጣላቸውን ተግባሮች ማስቀረትን የሚጠይቁና የማይጠይቁ ጥያቄዎችን መለየት ለአንድ መሪ አስፈላጊ ነው፡፡ ጠቢብ መሪ የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ባልታቀዱ ተግባሮች አይጣደፍም፡፡

> ከማርያምና ከእኅትዋ ከማርታ መንደር ከቢታንያ የሆነ አልዓዛር የሚባል አንድ ሰው ታሞ ነበር።ማርያምም ጌታን ሽቱ የቀባችው እግሩንም በጠጕርዋ ያበሰችው ነበረች፤ ወንድምዋም አልዓዛር ታሞ ነበር።ስለዚህ እኅቶቹ ጌታ ሆይ፥ እነሆ የምትወደው ታሞአል ብለው ወደ እርሱ ላኩ።ኢየሱስም ሰምቶ። ይህ ህመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት አይደለም አለ። ኢየሱስም ማርታንና እኅትዋን አልዓዛርንም ይወድ ነበር።እንደ ታመመም በሰማ ጊዜ ያን ጊዜ በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ዋለ፤
>
> ዮሐንስ 11፡1-6

መጋቢ ብዙ አስቸኳይ ያልሆኑ ጠቃሚ ተግባሮች አሉት። መጋቢ በጸሎትና ከቃሉ ጋር ጊዜ ማሳለፍ አለበት። መፀለይና ቃሉን ማጥናት በሆስፒታል ሊሞት እንዳለ ሰው ያህል አስቸኳይ መስሎ አይታይም። ጌታን መጠባበቅ ቼኮችን እንደመፃፍና የአስተዳደር ጉዳዮችን መስመር እንደማስያዝ አስቸኳይ አይመስልም። ይሁንና አስቸኳይ ያልሆኑ ነገር ግን ጠቃሚ ተግባሮቸ ላይ የሚገኝ መሪ የበለጠ ያሳካል።

## 6. ራስህን ከሚገባው በላይ አትወጥር።

በሕይወትህ ከብዙ በላይ ልታደርግ አትችልም። ራስህን መወጠር ማለት እግዚአብሔር እንድትሰራ ያልላከህን ነገሮች ትሰራለህ ማለት ነው። ይህ ጭንቀትና ችግር ይፈጥራል። መጋቢ የሚሆኑ ወንጌላውያን ያለማቋረጥ የአመራር ችግሮች ይገጥሟቸዋል። እግዚአብሔር እነርሱን ላልሾመበት ክፍል ራሻቸውን መስጠጥ አይችሉም። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እንድናደርግ አይጠብቅብንም። ልናስብ የምንችለውን ያህል ወሳኝ አይደለንም። ያን ያህል አስፈላጊ ብንሆን ኖሮ የትኛውም ወጣት መጋቢ በፍጹም አይሞትም ነበር! በነገሮች ድልድል ውስጥ ያን ያህል ጠቃሚ ብንሆን ኖሮ የዮሐንስ ወንድም ያዕቆብ በአገልግሎቱ መሀል ላይ አይሞትም ነበር። የአንተን ድርሻ ተወጣና ቀሪውን ለእግዚአብሔር ተወው። እግዚአብሔር ማረፍ አለብህ የሚልበትን ቦታ አንብበህ አታውቅም?

> እንግዲያስ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶላቸዋል።ወደ ዕረፍቱ የገባ፥ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፥ እርሱ ደግሞ ከሥራው አርፎአልና።እንግዲህ እንደዚያ እንደ አለመታዘዝ ምሳሌ ማንም እንዳይወድቅ ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንትጋ።
>
> ዕብራውያን 4:9-11

## 7. ስትችል ሌሎችን ወክል

ኢየሱስ ለሶስት ዓመታት ካገለገለ በኋላ ቀሪውን ሥራ ለደቀመዛሙርቱ አስረከበ። በራሱ ሊያሳካ ስለሚችለው የተሳሳተ ግምት አልነበረውም። ለአገልግሎት የእስራኤልን ድንበር ለመሻገር እንኳን አልሞከረም። ያንን የአገልግሎቱን ክፍል ለደቀመዛሙርቱ በውክልና ሰጣቸው።

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ወደ አለም ዳርቻ እንደላካቸው ታስታውሳለህ? ኢየሱስ ወደ አለም ዳርቻ ለመሄድ እንዳልሞከረ አስተውለሃል? ወደ ምድር ዳርቻ የመሄዱን ሥራ ለደቀመዛሙርቱ አስተላለፈ። እርሱ ራሱ ወደ ምድር ዳርቻ መሄድ እንደሚችል ለማንም ለማሳየት አልሞከረም።

**የእርሱ ሚና አይሁዶችን ማገልገልና በመስቀል ላይ መሞት ነበር። የኢየሱስ ሥራ በማቴዎስ 15፡24 ላይ ተገልጿል። ከራሱ ኃላፊነት ጋር ለመጣበቅ አስቦ ነበር። ቀሪውን ለእኛ በውክልና አስተላለፈልን።**

እርሱም መልሶ፡- ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ።

ማቴዎስ 15፡24

## ምዕራፍ 107

# ሁልጊዜ አስታውስ፡ “ሁላችን እስክናሸንፍ ድረስ ማንም አያሸንፍም!”

በሕክምና ትምህርት ቤት በነበርኩበት ጊዜ ይህ እውነት ለእኔ በጣም ግልፅ ነበር። የዓመት መዝጊያ ፈተናዎቻችን በጣም አጨናናቂ ነበሩ። ከሕይወቴ እጅግ አስጨናቂ ደቂቃዎች አንዱ የመጨረሻ ፈተና ውጤቴን ስጠብቅ ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ ሁሉንም ፈተናዎች አልፌአለሁ። ይሁንና ሁልጊዜ ያልሆነለት አንድ ጓደኛ ወይም ሌላ ሰው ይኖር ነበር። ሁላችንም ካላለፍን በስተቀር ደስታችን ፍጹም እንዳልነበር ገባኝ። የቅርብ ጓደኛህ ዓመቱን ሊደግም እያለ እንዴት ልትደሰት ትችላለህ? ስድስት ሰዎች ዶክተር ሲሆኑ አንዱ ዓመቱን መድገም ካለበት እንዴት ልትደሰት ትችላለህ?

እያንዳንዱ መሪ ሁላችንም እስካላሸነፍን ድረስ ማንም እንደማያሸንፍ ማስታወስ አለበት። ጋብቻህ ስኬታማ ቢሆን የጓደኛህም ጋብቻ እንዲሁ ስኬታማ እስካልሆነ ድረስ ሙሉ በሙሉ ደስተኛ አትሆንም።

## “ሁላችንም እስካላሸነፍን ድረስ ማንም አያሸንፍም” ይህን የሚያስተምሩን አምስት ትምህርቶች።

### 1. *ያዕቆብ አሥራ ሁለት ልጆች ኖረውት ዮሴፍን በባርነት አጣ*

ዮሴፍ ከጠፋ በኋላ እንኳን ገና አስራ አንድ ልጆች ቢቀሩትም ሊደሰት አልቻለም። ያዕቆብ ጠቢብ ሰው ነበር። ሁላችንም እስክናሸንፍ ድረስ ማናችንም እንዳላሸነፍን ያውቅ ነበር።

> እርሱም አውቆ። የልጄ ቀሚስ ነው ክፉ አውሬ በልቶታል ዮሴፍ በእርግጥ ተበጫጭቋል አለ።ያዕቆብም ልብሱን ቀደደ፥ በወገቡም ማቅ ታጥቆ ለልጁ ብዙ ቀን አለቀሰ።ወንዶች ልጆቹና ሴቶች ልጆቹም ሁሉ ሊያጽናኑት ተነሡ መጽናናትን እንቢ አለ፥ እንዲህም አለ። ወደ ልጄ ወደ ሙታን ስፍራ እያዘንሁ እወርዳለሁ። አባቱም ስለ እርሱ አለቀሰ።እነዚያ የምድያም ሰዎች ግን ዮሴፍን በግብፅ ለፈርዖን ጃንደረባ ለዘበኞቹ አለቃ ለጲጥፋራ ሸጡት።
>
> ዘፍጥረት 37፡33-36

## 2. የጠፋውን አንዱን ሊፈልግ ዘጠና ዘጠኙን በጐች ትቶ ስለሄደው እረኛ ኢየሱስ አስተምሯል፡፡

ምን ይመስላችኋል? ለአንድ ሰው መቶ በጎች ቢኖሩት ከእነርሱም አንዱ ቢባዝን፥ ዘጠና ዘጠኙን በተራራ ትቶ ሄዶም የባዘነውን አይፈልግምን?ቢያገኘውም፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ካልባዘኑቱ ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ በእርሱ ደስ ይለዋል።

ማቴዎስ 18፡12፣13

## 3. አንድ የጠፋን ሳንቲም ለማግኘት ሙሉ ቤቱን ስለጠረገችው ሴት ኢየሱስ አስተምሯል፡፡

ወይም አሥር ድሪም ያላት አንድ ድሪም ቢጠፋባት፥ መብራት አብርታ ቤትዋንም ጠርጋ እስክታገኘው ድረስ አጥብቃ የማትፈልግ ሴት ማን ናት?

ሉቃስ 15፡8

## 4. አንድ ልጅ እያለው በተስፋ የአባካኙን ልጅ መመለስ ይጠባበቅ ስለነበረው የአባካኙ ልጅ አባት ኢየሱስ አስተምሯል፡፡

ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም። ደስም ይላቸው ጀመር።

ሉቃስ 15፡24

## 5. መቀመጫዎቹ በሙሉ እስኪሞሉ ስላልተጀመረው ግብዣ ኢየሱስ አስተምሯል፡፡

ባሪያውም ደርሶ ይህን ለጌታው ነገረው። በዚያን ጊዜ ባለቤቱ ተቆጥቶ ባሪያውን። ወደ ከተማ ጎዳናና ወደ ስላች ፈጥነህ ውጣ ድሆችንና ጉንድሾችን አንካሶችንና ዕውሮችንም ወደዚህ አግባ አለው።ባሪያውም። ጌታ ሆይ፥ እንዳዘዝኸኝ ተደርጎአል፥ ገናም ስፍራ አለ አለው።ጌታውም ባሪያውን። ቤቴ እንዲሞላ ወደ መንገድና ወደ ቅጥር ውጣና ይገቡ ዘንድ ግድ በላቸው፤

ሉቃስ 14፡21-23

ምዕራፍ 108

# የብዙ ሰዎችን ስም እወቅ

ለእርሱ በረኛው ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፥ የራሱንም በጎች በየስማቸው ጠርቶ ይወስዳቸዋል።

ዮሐንስ 10፡3

ሰዎች ስማቸውን የሚያውቅን ሰው ይከተላሉ! መሪ አብሯቸው የሚሰራቸውን ሰዎች ስም ማወቁ በጣም አስፈላጊ ነው። ማንም ሰው ቁጥር ወይም ዕቃ አይደለም። ሰዎችን ለመምራት የምትፈልግ ከሆነ ስማቸውን ለማስታወስና በስማቸው ለመጥራት ሞክር።

## የብዙ ሰዎችን ስም ማወቅ ያለብህ አምስት ምክንያቶች

1. ስኬታማ የሆነ መሪ ሁሉ የብዙ ሰዎችን ስም ያውቃል።

2. ሰዎች ስማቸውን ስታውቅ ልዩ እንደሆኑ ይሰማቸዋል።

ሰው ሁሉ ልዩ እንደሆነ ወደሚሰማው ሥፍራ ያዘነብላል። ሰዎች በስማቸው ስትጠራቸው ችላ እንደተባሉ ወይም እንደተናቁ አይሰማቸውም።

3. የሰዎችን ስም ስታውቅ ሰው ወዳድና ሰብአዊ ፍጡር እንደሆንክ ይሰማቸዋል።

ሰዎች ሰው ወዳድና ተግባቢ ወደሆነ ሰው ይሳባሉ።

4. ሰዎችን በስማቸው ማወቅ ከእነርሱ ጋር በግል ያቀራኝሃል

ይህ የመሪና የተመሪ ትስስርን ይፈጥራል።

5. የሰዎችን ስም ማወቅ ወደ እነርሱ ያቀርብሃል።

አንዳንድ ጊዜ ስልሳ አባላት ብቻ ኖረዋቸው የሁሉንም ስም ማስታወስ በማይችሉ መጋቢዎች እደነቃለሁ። የሰዎችን ስም ማስታወስ የማትችል ከሆነ አንተን መከተል አይወዱም። የአንድን ሰው ስም ስታውቅ የእውነት እንደሆንክና የሚፈለገውን ያህል የቅርብ

**እንደሆንክ ይሰማቸዋል፡፡ ሰዎችን ሩቅና ለስሙ ያህል የተሾመን ሰው ለመከተል እምብዛም አይሳቡም፡፡**

**ንጉሥ ዳዊት ታላቅ መሪ ነበር፡፡ ተወዳጅ የነበረበት አንዱ ምክንያት ለሚመራቸው ሰዎች ቅርብ መሆኑ ነበረ፡፡**

ነገር ግን በፊታቸው ይወጣና ይገባ ስለ ነበረ እስራኤልና ይሁዳ ሁሉ ዳዊትን ወደዱ።

1ኛ ሳሙኤል 18፡16

## ምዕራፍ 109

# በራስህ ላይ ሥራ

ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፥ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ፥ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና።

1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡16

በራሱ ላይ የሚሰራ መሪ ሁሉ መሪ እርሱ ሆኖ እንደሚቀጥል ያረጋግጣል፡፡

## ሁሉም መሪ በራሱ ላይ መስራት የሚገባው ሶስት ምክንያቶች

### 1. ማርጀት ሕግ ምክንያት

ይህ ሕግ ሁሉም ነገር በተፈጥሮ እየበሰበሰ እንዳለ ይናገራል፡፡ በምድር ላይ ያለ ምንም ነገር በመጀመሪያው ጤናማ ይዞታ ላይ አይቆይም፡፡ ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ዘውድ (የመሪነት ሥፍራህ) ለዘለዓለም ዋስትና እንደሌለው የሚያስጠነቅቀው፡፡

የበጎችህን መልክ አስተውለህ እወቅ፥ በከብቶችህም ላይ ልብህን አኑርባለጠግነት ለዘላለም አይኖርምና፥ ዘውድም ለትውልድ ሁሉ አይጸናምና።

ምሳሌ 27፡23፡24

### 2. አንድ እርምጃ ቀድሞ በመገኘት መርህ ምክንያት

አንድ እርምጃ እስካልቀደምክ ድረስ አመራር የለም፡፡ ከተከታዮቼ ቢያንስ አንድ እርምጃ ቀድሜ ለመገኘት ያለማቋረጥ በራሴ ላይ እየሰራሁ ነው፡፡ ይህንን ባላደርግ በእርግጥ ከሥፍራዬ ላይ እወድቃለሁ፡፡

### 3. ሌላውን ሰው መታደግ ከመቻልህ በፊት ራስህን በመታደግ መርህ ምክንያት

በአውሮፕላን ላይ ማንኛውም ችግር በሚከሰትበት ጊዜ ሁሉ አዋቂ ሰዎች ልጆቻቸውን ከመታደጋቸው በፊት ራሳቸውን እንዲታደጉ ይነገራቸዋል፡፡ ጳውሎስ ተመሳሳይ ነገር ተናግሯል፡፡ ራስህን ካላዳንክ በስተቀር ሌሎችን ልታድን የምትችልበት መንገድ የለም፡፡ ሐኪም

ከታመመ ሌሎችን ማገልገል አይችልም። ዕውር ዕውርን ሊመራ አይችልም።

ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፥ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ፥ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና።

1ኛ ጢሞቴዎስ 4:16

# ሁሉም መሪ በራሱ ላይ ሊሰራ የሚችልባቸው ሰባት መንገዶች

## 1. መጽሐፍ ቅዱስን በየዕለቱ አንብብ

በ1986 በተማሪነት ወደ ለንደን ተጓዝኩ። ለራሴ አንድ ነገር ገዛሁ….. ልዩ የማጣቀሻ መጽሐፍ ቅዱስ። ጥቂቱን የተማሪ የኪስ ገንዘቤን በሙሉ ራሴ ላይ ለመሥራት ተጠቀምኩበት። ያ ወጪ (ኢንቨስትመንት) መቼም ቅር ብሎኝ አያውቅም።

...በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል።

ገላትያ 6:8

## 2. ክርስቲያናዊ መጻሕፍትን በየቀኑ አንብብ

ስለማታውቃቸው ነገሮች መጻሕፍትን አንብብ።

## 3. የስብከት ካሴቶችን አድምጥ

ካሴቶች የሚሰሙበት ሰዓታት ተደማምረው የብዙ መንፈቀ ዓመታት የዩኒቨርሲቲ ትምህርቶች ጋር ይስተካከላሉ።

## 4. ሴሚናሮችን፣ ኮንፈረንሶችንና የቤተክርስቲያን ኘሮግራሞችን ተካፈል።

እነዚህ የተሻለ ሰው ያደርጉሃል።

## 5. ከአልባሳትህና ከፀጉርህ ይልቅ በመጻሕፍትህ ላይ ይበልጥ ገንዘብ አውጣ።

## 6. የተቀቡ የእግዚአብሔር ሰዎች ጥበብን የሚያስተምሩባቸውን የቪዲዮ ካሴቶች ተመልከት።

## 7. የግልህ የመጻሕፍትና የካሴቶች ቤተመጻሕፍትን አደራጅ።

ምዕራፍ 110

# ለጊዜ ዋጋ ስጥ፤ ጊዜን ተቆጣጠር

## ጊዜህን የምትቆጣጠርባቸው ስድስት መንገዶች

### 1. አስፈላጊ ነገሮችንና አስቸኳይ ነገሮችን ለይተህ እወቅ

ብዙ ሰዎች ጊዜ ስለሌላቸው አንዳንድ ነገሮችን ማከናወን እንደማይችሉ ይናገራሉ። ይሁንና እውነታው ጊዜአቸውን መቆጣጠር አለመቻላቸው ነው። ራስህን መሪ ብለህ ትጠራለህ? መሪ ከሆንክ በአስፈላጊ ነገሮችና በአስቸኳይ ነገሮች መካከል መለየት መቻል አለብህ። ብዙ አስቸኳይ የሆኑ ነገሮች አስፈላጊ አይደሉም፤ ብዙ አስፈላጊ ነገሮችም አስቸኳይ አይደሉም። እውነተኛ መሪ ጠቃሚ ያልሆኑ ነገሮችን በማስወገድ ማድረግ የሚገባውን የሚያደርግ ሰው ነው።

### 2. በዕቅድህ ላይ በሌሉ ነገሮች ውስጥ አትጠመድ

መሪ ከሆንክ ብዙ መልካም ነገሮች ግዴታ አንተ ማድረግ ያለብህ ነገሮች እንዳልሆኑ ታውቃለህ። ጊዜዬን በጸሎትና ቃሉን በማገልገል እንደማሳልፍ ወስኛለሁ። ይህንን መጽሐፍ እየፃፍኩ እያለ እንኳን ብዙ ነገሮችን እንዳደርግ በጫና ውስጥ ነኝ። ለእኔ በዚህ ሰዓት እጅግ አስፈላጊው ነገር ይህንን መጽሐፍ መጻፍ እንደሆነ ወስኛለሁ።

> ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ።
>
> ኤፌሶን 5፡16

### 3. ራስህን አንዳንድ ወሳኝ ሥራዎችን በሚሰሩልህ ብቁ ሰዎች ክበብ

አስፈላጊ ነገሮችን የሚከወንልህ ኃላፊነት የሚሰማው ሠራተኛ ላንተ ዋጋ ያለው ንብረት (ጸጋ) ነው። እኔ ብቻ ላደርጋቸው ለምችላቸው ነገሮች ጊዜ እንዲኖረኝ ሊደረጉልኝ የሚገቡ ነገሮች አሉ።

ከሁለት መቶ ቤተ ክርስቲያናት በላይ የምቆጣጠር መጋቢ ነኝ፤ በየቀኑ የሚነሱትን ችግሮች ቁጥር መገመት ትችላለህ። ምን እንደምሰራ መወሰን አለብኝ፡ ሰዎችን ማማከር፣ ለሰዎች መጸለይ፣ የገንዘብ ችግሮችን ማስተካከል፣ የሥራ አመራር ጉዳዮችን መፍታት፣

ዝርዝሩ ይቀጥላል። በብልህ አስተዳዳሪዎችና ችግር ፈቺዎች እርዳታ ለእኔ ሥራ ጊዜ ይኖረኛል።

## 4. የተሰጣቸውን ሥራ መሥራት የማይችሉን ሰዎች አስወግድ

እነዚህ ሰዎች ለአንተችግር ይፈጥራሉ፣ ተሰርተው ማለቅ ወደ ነበረባቸው ነገሮችም ጐትተው ያስገቡሃል።

## 5. በጥሪህ ውስጥ ጽና

ጊዜህን በብልሃት የመጠቀምን ጥበብ እንዴት ልታዳብር ትችላለህ? ጊዜህን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመቆጣጠር ቁልፍ ነው ብዬ የማምነውን አንድ ምስጢር ላካፍልህ እፈልጋለሁ። የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ለመፈፀምም ጭምር ቁልፍ ነው። የምትኖርባቸው ሰባ ዓመታት ብቻ እንዳሉህ ታውቃለህ (በዛም አነሰም)? ይህ ማለት ጌታን ለማገልገል የተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው ያለህ ማለት ነው። እግዚአብሔር የተወሰኑ ነገሮችን እንድታደርግ እየጠበቀህ ነው። እውነተኛ መሪ ማድረግ የሚገባውን ከለየ በኋላ ከእርሱ ጋር ይጣበቃል።

በጥሪህ ውስጥ ጽና። ወደ ሌሎች ሰዎች ክልል ቅርንጫፍ አትውጣ። አስተማሪ ከሆንክ ቃሉን አስተምር። መጋቢ ከሆንክ ራስህን ለመጋቢነት ስጥ፤ ነብይ ለመሆን አትሞክር።

## 6. የማይረባን ሕብረት አስወግድ

በጨዋታና በተግባቢነት የምታሳልፈው ጊዜ በአብዛኛው ከሰማያዊ አባትህ ጋር ሕብረት በማድረግ ልታሳልፍ የምትችልበት ጊዜ ነው። ሰዎች ተግባቢ አይደለህም ሊሉህ ይችላሉ አንተ ግን ምን እያደረግህ እንዳለህ ታውቃለህ። ጊዜህን በማይጠቅሙ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ላይ ማጥፋትን አስወግድ። ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ የማጠፋው ጊዜ አይኖረኝም!

## ምዕራፍ 111

# ታላላቅ ውጤቶች ታላቅ ሥነ ሥርዓትን ይጠይቃሉ

"ሥርዓት መያዝ" ማለት "ቁጥጥር የሚደረግበት መሆን፣ ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበት መሆን፣ በሚገባ መዘጋጀት፣ መደበኛ፣ በሥርዓት መሆንና መሰለፍ ማለት ነው።

ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፥ አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ።

ማቴዎስ 4፡1፣2

ኢየሱስ ራሱን ለአርባ ቀንና ለአርባ ሌሊት ለመፆም ጥብቅ ሥነ ሥርዓት አስገዝቷል። ያ ቀላል ውጤት አይደለም! ለሶስት ቀንና ሌሊት የፆመ ሰው እንኳ ራስን በመግዛት ላይ የሚያመጣውን ድካም ይደርስበታል።

ታላቅ መሪ ለመሆን ራስህን በጸሎት፣ በፆምና መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ሥነ ሥርዓት ልታስይዝ ይገባሃል። ከጌታ ጋር በጸሎት ሆኜ በአንድ ክፍል ውስጥ ለስምንት ሰዓታት የምቆይባቸው ጊዜያት አሉ። በመንፈስ ቅዱስ መገኘት ውስጥ ብቻዬን ለሰዓታት መቆየት እችላለሁ። ራስን ያለመግዛት ይህንን ልታደርግ አትችልም።

ታላቅ መሪ መሆን ትፈልጋለህ? ራስህን በሁሉም አቅጣጫ ሥነ ሥርዓት የምታስይዝበት ጊዜ ነው። ይህንን መጽሐፍ መጻፍ ታላቅ ራስን መግዛትን ይጠይቃል። አንተ የምታነባቸውን ቃሎች ለብዙ ሰዓታት ወደ ወረቀቱ አስተላልፋለሁ። ቀላል ሥራ አልነበረም! ነገር ግን ያለ ታላቅ ራስን መግዛት ታላቅ ውጤት እንደማይኖር አውቃለሁ።

## ሁሉም መሪ ራሱን ሊገዛባቸው የሚገቡ አምስት ነገሮች

1. የዕለት የጥሞና ጊዜ
2. ብዙ ሰዓታትን በጸሎት ማሳለፍ
3. መጽሐፍ ቅዱስን በየቀኑ ማንበብ
4. ዘወትር መፆም
5. መጻሕፍትን ማንበብ

## ምዕራፍ 112

# ራእይ ይኑርህ

የራእይ ታላቁ ምስጢር ይህ ነው፡ ራእይህ መሆን የምትፈልገውን ያደርግሃል። ሁሉም ታላቅ መሪ ወዳስቀመጠው ራእይና ግብ ይሄዳል።

*ራእይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል ሕግን የሚጠብቅ ግን የተመሰገነ ነው።*

ምሳሌ 29፡18

አንድ ሰው ያለው ሪእይ መሪ ያደርገዋል። የሚነዳህና የሚያስፈነጥርህ ራእይህ ነው። መሪ ከሆንክና ከፊትህ ራእይ ከሌለ መሪ መሆን አለመሆንህን እጠራጠራለሁ።

ከፊቴ የማየው ነው ጉዞዬን እንድቀጥል የሚያደርገኝ። በአእምሮዬ ዓይን (በዕዝነ ሕሊናዬ) ግዙፍ ቤተክርስቲያን (ሜጋ ቸርች) ይታየኛል! በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ሲመጡ ይታየኛል። በሕይወቴና በአገልግሎቴ ብዙ ተዓምራቶች ሲፈፀሙ ይታየኛል። ያ ነው ወደፊት የሚያስኬደኝ። አንተ ራእይህን አታበጅም ራእይህ ነው አንተን ሚያበጅህ!

ታላቅን ራእይ የመያዣ ቁልፍ ምንድን ነው? ጥሩ ምስጢርን እሰጥሃለሁ። በዙሪያህ አንተ ማድረግ የምትወዳቸውን ነገሮች የሚያደርግን ማንኛውንም ሰው ዞር ዞር ብለህ ተመልከት። ያ ሰው ያሳካውንና ከዚያም በላይ ማሳካትን ራእይህ አድርገው። ያለ እንደዚህ ዓይነት ራእይ በዓላማ የለሽነት ባህር ውስጥ ትጠፋለህ (ትዋትታለህ፣ ትቅበዘበዛለህ፣ ትፍጨረጨራለህ)።

## ምዕራፍ 113

# ታላቅ መሪ በተገኘበት የምታሳልፈውን እያንዳንዱን ደቂቃ ዋጋ ስጠው

## ከታላላቅ መሪዎች ጋር ለነበራቸው ሕብረት ዋጋ የሰጡ ሶስት ሰዎች

1. ደቀ መዝሙሩ ዮሐንስ ከኢየሱስ ጋር ስለነበረው የእርስ በእርስ ግንኙነት ተናግሯል።

እ

ንዴት ጌታን በእጆቹ እንደዳሰሰውና ሲናገር እንደሰማው አካፍሏል

ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፤ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን፥ ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኋለን፤

1ኛ ዮሐንስ 1፡1፣2

ይህ ከሕይወቱ ልምምዶች ሁሉ የላቀው ነበር። በታላቅ መሪ መገኘት የሚያልፍ ትንሽ ደቂቃ ብዙ ነገሮችን ያስተምርሃል።

2. ኤልሳ ከኤልያስ መገኘት መራቅን እንቢ አለ።

ቅርብ መሆን ምን ያህል እንደሚጠቅመው አውቆ ነበር። በአራት የተለያዩ አጋጣሚዎች መለየትን እንቢ ብሏል።

ኤልያስም ኤልሳዕን፡- እግዚአብሔር ወደ ቤቴል ልኮኛልና በዚህ ቆይ አለው። ኤልሳዕም። ሕያው እግዚአብሔርን! በሕያው ነፍስህም እምላለሁ፥ አልለይህም አለ። ወደ ቤቴልም ወረዱ።

2ኛ ነገሥት 2፡2

3. ኢያሱም ከሙሴ ጋር በነበረው የቅርብ ግንኙነት በብዙ ተፅዕኖ አድሮበታል።

ኢያሱ ከሙሴ ጋር ወደ ተራራው የወጣው ብቸኛው ሰው እንደነበር አስታውስ፡፡ እግዚአብሔርም ሙሴን፦ ወደ እኔ ወደ ተራራው ውጣ፥ በዚያም ሁን እነርሱን ታስተምር ዘንድ እኔ የጻፍሁትን ሕግና ትእዛዝ የድንጋይም ጽላት እሰጥሃለሁ አለው። ሙሴና ሎሌው ኢያሱ ተነሡ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወጣ።

ዘጸአት 24፡12፣13

ሁሉም የመጀመሪያዎቹ የሙሴ ቡድኖች ጊዜ ባለፈ ቁጥር "የሆነ ያህል" ብቻ ሆኑ፡፡ አሮን ወደ ጣዖት አምልኮ ገባ፡፡ ማርያም ታማኝ ያልሆነች ተቺ ሆነች፡፡ ኢያሱ ግን ለሙሴ ከነበረው ቅርበት የተነሳ በሙሉ ጥበብ ውስጥ ነበር፡፡

ሙሴም እጆቹን ስለ ጫነበት የነዌ ልጅ ኢያሱ የጥበብን መንፈስ ተሞላ የእስራኤልም ልጆች ታዘዙለት፥ እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ።

ዘዳግም 34፡9

## በታላቅ መሪዎች መገኘት መሀል ሊስተዋሉ የሚገቡ ሰባት ነገሮች

1. ራእያቸውን አስተውል፡፡

የላቀ ራእይ እንዲኖርህ ትነሳሳለህ፡፡

2. ስኬቶቻቸውን አስተውል

ምን የሚቻል እንደሆነ ያሳይሃል፡፡

3. ትኩረታቸውን አስተውል

በሥራ ላይ የማተኮርን ምስጢር ታያለህ፡፡

4. ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት አስተውል

ወደ እግዚአብሔር እንድትቀርብ ያነሳሳሃል፡፡

5. የውጪ ገፅታቸውንና ቋንቋቸውን አስተውል

የታላቅነት ድባብ ይሰማሃል፡፡

6. ሁኔታዎችን እንዴት እንደሚፈቱ አስተውል

ለራስህ ሁኔታ ጥበብን ትቀበላለህ፡፡

7. ድክመቶቻቸውን አስተውል

ድክመቶቻቸው እያሉ ታላላቅ ስኬቶቻቸውን ስትመለከት ትበረታታለህ፡፡

# ምዕራፍ 114

# ኃላፊነት ውሰድ!

ወደ ታንኳም ሲገባ ደቀ መዛሙርቱ ተከተሉት።እነሆም፥ ማዕበሉ ታንኳይቱን እስኪደፍናት ድረስ በባሕር ታላቅ መናወጥ ሆነ፤ እርሱ ግን ተኝቶ ነበር። ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው። ጌታ ሆይ፥ አድነን፥ ጠፋን እያሉ አስነሡት።እርሱም፡- እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ ስለ ምን ትፈራላችሁ? አላቸው፤ ከዚህ በኋላ ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ፥ ታላቅ ጸጥታም ሆነ።ሰዎቹም። ነፋሳትና ባሕርስ ስንኳ የሚታዘዙለት፥ ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው? እያሉ ተደነቁ።

ማቴዎስ 8፡23-27

ኢየሱስ ችግር ሲኖር ተጠራ። እየዘነበ ነበር ሁሉም ሰው ደግሞ እየሰመጠ ነበር። ኢየሱስ ሲጠራ ኃላፊነትን ወሰደ። በኮርልቡ ሆስፒታል የድንገተኛ ክፍል ሃላፊ ሐኪም ተደርጌ ለብቻዬ ያሳለፍኩትን የመጀመሪያ ምሽቴን አስታውሳለሁ። ለእኔ አስፈሪ ልምምድ ነበር። አዲስ ሐኪም ብሆንም በእያንዳንዱ ሁኔታ መንገዱን መምራትና ምን መደረግ እንዳለበት ማወቅ ይጠበቅብኝ ነበር። ምሽቱን በሙሉ ራሳቸውን የሳቱ፣ የታመሙ እና የሞቱ ሰዎች ጭምር ይመጡ ነበር። ነገር ግን ተነስቼ በአጋጣሚው የድንገተኛ ክፍሉ መሪ ሆንኩ። እንዴት አደረግኩት? ከወሰድኩት ሥልጠና በመነሳት ትክክል ነው ብዬ ያሰብኩትን አደረግሁ። ጊዜ ባለፈ ቁጥር እየቀለለኝ መጣ።

ሳኦል አዲስ መሪ ሲሆን ሳሙኤል ይህንኑ መመሪያ ነው የሰጠው፡- “ትክክል የመሰለህን አድርግ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሆናል።”

እነዚህም ምልክቶች በደረሱህ ጊዜ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና እጅህ የምታገኘውን ሁሉ አድርግ።

1ኛ ሳሙኤል 10፡7

እንደመሪ ኃላፊነትን ለመውሰድ ቁልፉ ምንድን ነው? በቀላሉ፣ ኃላፊነትን የመውሰድ ቁልፉ ኃላፊነትን መውሰድ ነው። ተነሥና ብቻ በድፍረት ተናገር! ምርጥ ነው ብለህ የምታስበውን አድርግ እግዚአብሔርም ካንተ ጋር ይሆናል።

## ምዕራፍ 115

# ገንዘብን የመሰብሰብ ጥበብ ተካን

ሁሉም መሪ ተልዕኮውን ለማሳካት የተወሰነ ገንዘብ መፈለጉ አይቀርም። ገንዘብን እንዴት እንደምትሰበስብ ካላወቅህ ስኬታማ መሪ አትሆንም።

ነብዩ ኤልሳ ደፋር ገንዘብ ሰብሳቢ ነበር። የመጨረሻ ምግቧን ልትበላ ከነበረች ባሏ ከሞተባት ሴት ጋር ተገናኘ። ኤልሳ የመጨረሻ ምግቧን ለአገልግሎቱ እንድትተው ይህችን ሴት አሳመናት። ሴትየዋ ያንን ስታደርግ ወደ ታላቅ የገንዘብ ተዓምራት ገባች። ለአገልግሎት ሥራ ገንዘብ ለማሳባሰብ ደፋር የእግዚአብሔር ሰውን ጠይቋል።

## የስኬታማ ገንዘብ ማሰባሰብ አምስት ቁልፎች

### 1. አመኔታ

ገንዘብን ማሰባሰብ የመሪነት ሥራዬ አንዱ ክፍል መሆኑን አሁን አሁን እየተቀበልኩት ያለ እውነታ ነው። በአብዛኛው ለብዙ ሥራዎች ገንዘብ አሰባስባለሁ። ለስኬታማ ገንዘብ ማሰባሰብ ቁልፉ ምንድን ነው? ሰዎች ሊያምኑህ ይገባል! አመኔታ በዓመታት የሚገነባ ነገር ነው። ሰዎች ባመኑህ ቁጥር ሀብታቸውን ለመልቀቅ የበለጠ ዝግጁ ይሆናሉ። ብጠይቃቸው በሺዎች የሚቆጠሩ ዶላሮች የሚሰጡኝ ሰዎች አሉ። ከእኔ ጋር ለብዙ ዓመታት ስለነበሩ ያምኑኛል።

ውድ መሪ፣ ለገንዘብ ማሰባሰብ ችሎታህ ቁልፉ ሀቀኝነት ነው። ለአንድ ዓላማ ገንዘብ ሲሰበሰብ ገንዘቡን ለዚያ ዓላማ ብቻ ተጠቀም። ጊዜ ባለፈ ቁጥር ሰዎች ያምኑሃል።

### 2. ለመጠናቀቅ ረጅም ጊዜ የሚወስዱ ፕሮጀክቶች ላይ ጥንቃቄ አድርግ

የማይጠናቀቅን ነገር ከጀመርክ ሰዎች እንዳታለልካቸው ያስባሉ። ገንዘብን ሰብስበህ ለሌላ ነገር እንደተጠቀምከው ያስባሉ።

## 3. ተገቢ ላልሆኑ ፕሮጀክቶች ገንዘብ አታሰባስብ

የመጋቢዎችን የግል ፍላጐት ለማሟላት ገንዘብ አታሰባሰብ፡፡ አልባሳትና መኪኖች ለመግዛት ወይም ለመጋቢውና ለሚስቱ የበዓል ቀን ወጪን ለመቻል ብለህ ገንዘብ እንዳትሰበስብ እመክርሃለሁ፡፡ እነርሱ ራሳቸው ለሌሏቸው ቅንጦቶች ለመክፈል ጉባዔው ደስተኛ አይሆኑም፡፡ ሰዎች ገንዘብን ለሚስዮናዊ ሥራ፣ ለወንጌል ስርጭት እና የግንባታ ሥራዎች (ኘሮጀክቶች) መስጠት ይመርጣሉ፡፡

## 4. በተደጋጋሚ ገንዘብ አታሰባስብ

የገንዘብ ማሰባሰብ እጅግ በተደጋጋሚ ሲሆን የሰጪ መዛል ይመጣል፡፡ ለብዙ ነገሮች በመደበኛ መባና ስጦታዎች ላይ ተደገፍ፡፡

## 5. ገንዘብን በምታሰባስብበት ጊዜ የ80-20 ደንብን ልብ በል

ብዙ ሰዎች ትንሽ መስጠት ይችላሉ፡፡ ይሁንና ጥቂት ሰዎች እጅግ የበዛ መስጠት ይችላሉ፡፡ የ80-20 ደንብ 80% ገቢያችን የሚገኘው ከ20% ሰው እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ከሰማንያ በመቶው እጅ ገንዘብ አሰባስብ፤ ነገር ግን ከባለጠጋ ሃያ በመቶዎቹ እጅ እጅግ የበለጠ ጠብቅ፡፡

ይህንን እውነታ መቼም እንዳትረሳ፡፡ መሪ የእግዚአብሔርን ራእይ ለመፈጸም ሁሌም ገንዘብን ይፈልጋል፡፡ የገንዘብ ሥራ አዋቂዎች እንዲኖሩህ ፀልይ፡፡ የሀቅ ሰው ሁን፡፡ እግዚአብሔር ይረዳሃል፣ መቼም አይጐድልብህም!

## ምዕራፍ 116

# ምሕረትን የምታደርግ ሁን

የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥ ይማራሉና።

ማቴዎስ 5፡7

መሪ ምሕረት የማድረግን ጥቅም የሚያውቅ ሰው ነው። የሆኑ የፖለቲካ መሪዎች በሥፍራው እሳትን ድኝ እየተፉ መጡ። ለጥቃቅን ወንጀሎች በሌሎች ላይ ፍርድን አስተላለፉ የሞት ፍርድም ፈረዱባቸው። ከዓመታት በኋላ የራሳቸው መንግስት አባላት የባሱ ነገሮችን እያደረጉ መሆኑን ደረሱበት። በእነዚህ ግለሰቦች ላይ ተመሳሳይ መለኪያ ቢጠቀሙ ምናልባት መንግስታቸውን በሙሉ መግደል ይኖርባቸዋል። ምሕረት የሚያደርግ ብፁዕ ነው፤ ምሕረትን ያገኛልና። ጠበቢ መሪ እርሱ ራሱ አንድ ቀን ምሕረት ሊፈልግ እንደሚችል ያውቃል። እውነተኛ መሪ ለተከታዮቹ መሀሪ የሚሆነው ለዚያ ነው።

## መንፈሳዊ ነህ?

ወንድሞች ሆይ፥ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ፥ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ።

ገላትያ 6፡1

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መንፈሳዊ የሆኑ ሰዎች መሀሪ ለመሆን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይናገራል። ዛሬ ሌባ ይዘሃል? እባክህ ምሕረት አድርግ! አንድ ቀን ሌባ ተብለህ ብትከሰስ ሁኔታውን ለመቀበል እንደሚከብድህ አውቃለሁ።

ሁሉም የእግዚአብሔር ሰው ይወድቃል ብዬ እየተነበይኩ አይደለም። እያልኩ ያለሁት ፈራጅ ከመሆን መሀሪ መሆን ጥበበኝነት ነው ። ምሕረት ፍርድን ድል ያደርጋል። በእርግጥም በሕይወትህ ውስጥ የእግዚአብሔር ምሕረት ያስፈልግሃል። እግዚአብሔር ለሌሎች ሰዎች ምን ያህል ምሕረት እንደምታደርግ ያያል።

የመሐሪ ሰዎች በረከት እርሱም ምሕረትን መቀበላቸው ነው። መሪ እርሱም አንድ ቀን ሊወድቅ የሚችል እንደሆን የሚያውቅ ትሁት ሰው ነው።

ከዓመታት በፊት ኬኔት ሔገን ላይ በጣም የሚፈርድ አንድ መጋቢ ገጠመኝ። ረጅም ንግግር በማድረግ የኬኔት ሔገን ጥፋቶች ገለፀልኝ። ቀጥሎም ኬኔት ሔገንን በመውቀስ የተሞላ መጽሐፍ ሰጠኝ። መጋቢው ሲናገር በተጠናወተው የትችት መንፈስ ተገረምኩ። ከተወሰኑ ዓመታት በኂላ ይህ ተቺ መጋቢ ሚስቱን ፈታ አገልግሎቱንም አጣ። ቀጥዬ ስለ እርሱ የሰማሁት እስር ቤት መሆኑን ነበር። ፈራጅ መሆን አያስፈልግም። መሪ ነህ? ምሕረትን የምታደርግ ሁን፡- አንድ ቀን አንተም ምሕረትን ትፈልግ ይሆናልና።

## ምዕራፍ 117

# የልብ ጓደኞች ይኑሩህ

ትክክለኛ መሪ ከሚያደርጋቸው የመጀመሪያ ነገሮች አንዱ ጓደኛ ማፍራት ነው። እነዚሁ ጓደኞች ናቸው የሚረዱህ። የሚደግፉህ ሰዎች ተከታዮችህ ይሆናሉ። ጓደኛ የሚያፈራ ሰው ነህ ወይስ ሰዎችን የሚበትን? ጓደኝነቶችህ ለታማኝነት፣ ለመሥዋዕትነትና ለድጋፍ ጭምር መሠረት ይሆናሉ።

የልብ ጓደኞች የማግኘት ምስጢር ምንድን ነው? አንተ ራስህ የልብ ጓደኛ ሁን።

> ብዙ ወዳጆች ያሉት ሰው ይጠፋል ነገር ግን ከወንድም አብልጦ የሚጠጋ ወዳጅ አለ።
>
> ምሳሌ 18፡24

የዘራኸውን እንደምታጭድ አትርሳ። ከሃዲ ከሆንክ ከሃዲዎችና አመፀኞች ይከብቡሃል። ታማኝ ሰው ከሆንክ ታማኝ ሰዎች ይከብቡሃል። የቱንም ያህል ታማኝ ብትሆን የተወሰኑ ከሃዲዎች አይቀሩልህም። ክህደት የሕይወት አካል ነው። ኢየሱስ ታማኝ ጓደኛና መሪ ነበር፤ ሆኖም ይሁዳ ነበረው።

ይህ ቢሆንም እውነተኛ ሰዎችን በዙሪያህ ለመሰብሰብ የእውነት ጓደኛ ለመሆን ወስን። ታማኝ ከሆንክ ታማኝ ያልሆኑ ሰዎች ካንተ ጋር አብረው አይሄዱም። ቅዱስ ከሆንክ ቅዱስ ያልሆኑ ሰዎች ጓደኞችህ ለመሆን አይቀላቸውም። “አንድ ዓይነት ወፎች በአንድነት ይበራሉ” እንደሚሉት።

## ምዕራፍ 118

# በዙሪያህ ካሉት ሁሉ ይልቅ ጠንክረህ ሥራ

እንደመሪ ስኬታማ ለመሆን በዙሪያህ ካሉት ሁሉ ይልቅ ጠንክረህ መሥራት ይኖርብሃል። መሪ መሆን ብዙ ጥሩ ነገሮች መደሰት እንደሆነ የምታስብ ከሆነ ያላሰብከው ሁኔታ ውስጥ ትገባለህ። መሪ መሆን እንደ "ቦርጫም" ገዢ መዝናናት እንደሆነ የምታስብ ከሆነ እንደዚህ አለመሆኑን ትደርስበታለህ!

እውነተኛ መሪ በዙሪያው ካሉት ሁሉ ጠንክሮ የሚሰራ ሰው ነው። የትልቅ ቤተ ክርስቲያን መሪ ብሆንና ከበታቼ ብዙ ሰዎች ቢኖሩም በአብዛኛው ከምመራቸው ሁሉ ይልቅ እጅግ በርትቼ እሰራለሁ። መሪነት ከባድ ሥራ ነው። አእምሮህን ለከባድ ሥራ አዘጋጅ! መጋቢ ከተከታዮቹ ይልቅ መጸለይ አለበት። ከማንኛውም ሰው ይበልጥ ትጉህ መሆን አለበት። ከተከታዮቹ ይልቅ የበለጠ ሰዓት ይሰጣል። ኢየሱስ ከተከታዮቹ ይልቅ ጠንክሮ እንደሠራ ልብ በል።

> ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ። አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ። ወደ ደቀ መዛሙርቱም መጣ፤ ተኝተውም አገኛቸውና ጴጥሮስን። እንዲሁም ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት እንኳ ልትተጉ አልቻላችሁምን?ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው።....ደግሞም መጥቶ ዓይኖቻቸው በእንቅልፍ ከብደው ነበርና ተኝተው አገኛቸው።ከዚያ ወዲያ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጥቶ። እንግዲህስ ተኙ ዕረፉም፤ እነሆ፥ ሰዓቲቱ ቀርባለች የሰው ልጅም በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል።
>
> ማቴዎስ 26፡39-41፣43፣45

ደቀ መዛሙርቱ እየተኙ ሳለ ኢየሱስ እንዴት ይጸልይ እንደነበር ልብ በል። ከተከታዮቹ ይልቅ ጠንክሮ እየሰራ ነበር። መሪ እንደመሆኑ ምን በአደጋ ላይ እንዳለ ተረድቶ ነበር። በዚያ ምሽት ከሁሉም ሰው ይልቅ አከናውኗል። እውነተኛ መሪዎች በአብዛኛው የበለጠ ጥረት በማድረግ ምሽቱን በሙሉ ደክመው ሲሰሩ በተከታዮቻቸው ብቻቸውን ጥለዋቸው ይሄዳሉ።

የበላይ መሪዎች ከበታቾቻቸው ይልቅ ለምን እጅግ የበለጠ እንደሚከፈላቸው የማይረዱ ብዙ ሰዎች አሉ። ብዙ ያልተማሩ ሰዎች በዚህ እውነታ ላይ ያምፃሉ። ስኬታማ መሪዎች በእርግጥ

ከሁሉ ይልቅ ጠንክረው እየሰሩ እንዳሉ አያውቁም፡፡ ከበላይ ሥራ አስፈፃሚዎች ጋር የሚያያዙ እንደ አልሰር፣ የልብ ድካም፣ የልብ ሕመምና ከፍተኛ የደም ግፊት የመሳሰሉ አንዳንድ የበሽታ ዓይነቶች እንኳን አሉ፡፡ የሥራ ዕቅዳቸው ለብዙ ከመጨናነቅ ጋር የተያያዙ ህመሞች መነሻ ይሆናል፡፡ በአብዛኛው የበላይ አመራሮች ልዩ ጥቅሞች የአስጨናቂ የሥራ ሕይወታቸውን ተፅዕኖ ለማስታገስ ብቻ ቢጠቅሙ ነው፡፡ ውድ መሪ፣ ወደ ከባድ ሥራ ዓለም እንኳን ደህና መጣህ፡፡

ምዕራፍ 119

# በትህትና ጀምር በትህትና ጨርስ

ብዙ መሪዎች በጭምትነት ይጀምሩና በራሳቸውና በውጤቶቻቸው በኩራት ተሞልተው ይጨርሳሉ።

ትምክህት ውድቀትን ትቀድማለች እናም ይህ ራስን የማውደም ቁልፍ ነው በብዙ መሪዎች ሕይወት ጉልቶ የሚታየው። በሕይወት ከኖሩት ታላላቅ መሪዎች ሁለቱ በጭምትነት ጀምረው በጭምትነት ጨርሰዋል። ከእነርሱ ምሳሌነት ተማር።

## ኢየሱስ አገልግሎቱን በጭምትነት ጀምሮ በጭምትነት ነው የጨረሰው

1. ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን በበረት ውስጥ ነው የጀመረው

የበኵር ልጅዋንም ወለደች፥ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው።

ሉቃስ 2፡7

2. ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን በመስቀል ላይ ነው ያበቃው።

ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ። አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ።

ሉቃስ 23፡46

## የጳውሎስ ጭምትነት አራት ደረጃዎች

ጳውሎስ በአራት ተከታታይ ጭምትነቶች አልፏል።

1. ከማናቸውም ሐዋሪያት እንደማያንስ ተናግሮ ነበር።

በመመካቴ ሞኝ ሆኜአለሁ፤ እናንተ ግድ አላችሁኝ፤ እናንተ እኔን ልታመሰግኑ ይገባ ነበርና። እኔ ምንም ባልሆን እንኳ፥ ከዋነኞቹ ሐዋርያት በምንም አልጎድልምና።

2ኛ ቆሮንቶስ 12፡11

2. እያደገ በመጣ ቁጥር ከሐዋርያቱ ታናሽ እንደሆነ ተሰማው

እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፤

1ኛ ቆሮንቶስ 15፡9

3. ከጥቂት ተጨማሪ ጊዜ በኋላ ጳውሎስ የቅዱሳን ሁሉ ታናሽ እንደሆነ አሰበ፡፡

ፍሊጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለ ጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ፥ ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረው የምሥጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ አገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለኔ ተሰጠ፤

ኤፌሶን 3፡8-9

እንደምታየው፣ ጳውሎስ በአገልግሎት ይበልጥ ልምድ እያገኘ ሲሄድ ስለራሱ ያለው ግምት እያነሰ ሄደ፡፡ በጌታ ከፍ እያልክ በሄድክ ቁጥር ምን ያህል እምብዛም የማያስፈልግ መሆንህን በይበልጥ ትገነዘባለህ፡፡ በሥራ ላይ ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ የአንተ የግል ጥረቶች እንዳልሆኑ ትደርስበታለህ፡፡

4. በአገልግሎቱ ፍፃሜ ላይ ጳውሎስ የአመፀኞች ዋና እንደሆነ ወሰነ፡፡

ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤ ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ፤

1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡15

ጳውሎስ የሆነ አሳዛኝ ሐጢያት ስለስራ አልነበረም፡፡ ከብስለት ጋር የእርሱና በእርግጥም የሰው ሁሉ ኃጢአት ማንነት መረዳት አብሮ መጣ::

## ያከናወንካቸው ነገሮች እንዲያስመኩህ አትፍቀድ

ውጤቶችህ ስለራስህ ያለህን አስተሳሳብ እንዲቀይሩ አትፍቀድ፡፡ ናቡከደነፆር በቤተመንግሥቱ በገነት ላይ ሲመላለስ አሰቃቂ ስህተት ሰራ፡፡ በራሱ ብርታት ታላላቅ ነገሮችን እንዳከናወነ አሰበ፡፡

ከአሥራ ሁለት ወር በኋላ በባቢሎን ቤተ መንግሥት ሰገነት ላይ ይመላለስ ነበር። ንጉሡም። ይህች እኔ በጉልበቴ ብርታት ለግርማዬ ክብር የመንግሥት መኖሪያ እንድትሆን ያሠራኋት ታላቂቱ ባቢሎን አይደለችምን? ብሎ ተናገረ።ቃሉም ገና በንጉሡ አፍ ሳለ ድምፅ ከሰማይ ወደቀና። ንጉሥ ናቡከደነፆር ሆይ። መንግሥት ከአንተ ዘንድ አለፈች ተብሎ ለአንተ ተነግሮአል

ዳንኤል 4፡29-31

ናቡከደነፆር ስለራሱ የተጋነነ ግምት ሲያዳብር እግዚአብሔር ቀጣው። መሪ ከሆንክ ስለ ክንውኖችህ የማይረባ ቃላትን አትናገር። የፖለቲካ መሪዎች በሥልጣን ላይ ለተወሰነ ጊዜ ከቆዩ በኋላ የማይረባ ንግግሮችን ሲናገሩ ሰምቻለሁ። አንዳንድ መሪዎች ጭራሽ ለዘለዓለም የሚኖሩ ይመስላቸዋል። ነገር ግን በጣም በቀላሉ ልትነሳ ትችላለህ። አባትህንና ቅድመ አያቶችህን ለዘለዓለም ኖረው እንደሆነ ጠይቃቸው።

አባቶቻችሁ ወዴት ናቸው? ነቢያትስ ለዘላለም በሕይወት ይኖራሉን?

ዘካርያስ 1፡5

## በሌሎች መሪዎች ላይ አትሳቅ

ሥጋ ለባሽ ብቻ ስለሆንክ ስለራስህ ጭምት የሆነ አስተሳሰብ ይኑርህ። በችግር ውስጥ ባለ ሌላ መሪ ላይ አትሳቅ። ፈራጅ መሪዎች ለውድቀት ያዘነበሉ መሆናቸውን ታሪክ አስተምሮናል። ሌሎች መሪዎች በኃጢአት ውስጥ ሲወድቁ አታፌዝ። ሳዖል በጦርነት ሲገደል የዳዊት ምላሽ ምን ነበር? "የእጁን አገኘ" በፍጹም አላለም! ከሚያዝኑ ጋር እዘን አብረሃቸው ፀልይ። በሌላ ታላቅ መሪ ውድቀት የሐዘን እንጉርጉሮ ያሰማን የአንድ ታላቅ መሪን ቃላት አስተውል።

ማልደው ተነሥተው በእግዚአብሔር ፊት ሰገዱ፥ ተመልሰውም ወደ አርማቴም ወደ ቤታቸው መጡ። ሕልቃናም ሚስቱን ሐናን አወቃት እግዚአብሔርም አሰባት የመፅነስዋም ወራት ካለፈ በኋላ ሐና ወንድ ልጅ ወለደች እርስዋም፡- ከእግዚአብሔር ለምኜዋለሁ ስትል ስሙን ሳሙኤል ብላ ጠራችው።ሰውዮውም ሕልቃና ከቤተ ሰቡ ሁሉ ጋር የዓመቱን መሥዋዕትና ስእለቱን ለእግዚአብሔር ያቀርብ ዘንድ ወጣ።

1ኛ ሳሙኤል 1፡19-21

## ምዕራፍ 120

# ሰዎችን እንዲያምኑብህ አሳምናቸው

ናትናኤልም። ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን? አለው። ፊልጶስ። መጥተህ እይ አለው።ኢየሱስ ናትናኤልን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ ስለ እርሱ። ተንኰል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው እነሆ አለ።ናትናኤልም። ከወዴት ታውቀኛለህ? አለው። ኢየሱስም መልሶ፦ ፊልጶስ ሳይጠራህ፥ ከበለስ በታች ሳለህ፥ አየሁህ አለው።

የሐንስ ወንጌል 1:47-49

ኢየሱስ ናትናኤልን እንዲያምንበት አድርጓል። ናትናኤል ኢየሱስ ጥሩ ሰው እንደሆነና ሊከተለው እንደሚገባ የግል የሆነ እምነት ነበረው፡፡ ማንም ሰው በአንተ ካላመነብህ ማንም ሀሳቦችህን ሊከተል አይችልም፡፡ መሪዎች ግልፅ መሆን ካለባቸው ምክንያቶች አንዱ ሰዎች በግል እንዲያውቋቸው እድሉን እንዲያገኙ ለማድረግ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ስለግል ሕይወታቸው ምንም የማይናገሩን ሰባኪዎች ስመለከት ይገርመኛል፡፡ የማሰጡት ምሳሌ ወይም የሚያካፍሉት ምስክርነት ስለሌላቸው ይሆን? ውድ ጓደኛዬ የምትመራቸው ሰዎች እንደ አንድ ግለሰብ በአንተ ላይ እምነት ሊኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ ለእነርሱ ክፍት ካልሆንክ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ሰዎች በልብህ ውስጥ ያለውን የሚያውቁት በቃሎችህ ነው፡፡

እናንተ የእፉኝት ልጆች፥ ክፉዎች ስትሆኑ መልካም ለመናገር እንዴት ትችላላችሁ? በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና።

ማቴዎስ 12፡34

ሰዎች በአንተ ልብ ውስጥ ካሉ ነገሮች ጋር መዛመድ ከቻሉ እንዲሄዱ ወደ ምትፈልገው ሥፍራ ሁሉ በፍጥነት ይሄዳሉ፡፡ የተፃፈላቸውን ንግግሮች በሚያነቡ ሰዎች አልገረምም፡፡ ከልቡ ሲናገር ካልሰማሁት በስተቀር ስለ ሰውየው ብዙ ላውቅ አልችልም፡፡ ወሳኙ ልብ ነው፡፡ ሰዎች ወኔህን፣ ተነሳሽነትህንና ራእይህን ሊሰማቸው ከተቻለ መምራት ቀላል ይሆናል፡፡ ለምንም ነገር ወኔ ከሌለህ ወይም የሆነን ነገር ለማከናወን ተነሳሽነት ከሌለህ መሪ አይደለህም፡፡

ወኔ እና የፀና እምነት እንዲኖርህ ጸልይ፡፡ ስለ ውክልና፣ ስልጣንና ሥራ አስኪያጅነት የተወሰኑ ደንቦችን መማር መሪ አያደርጉህም፡፡ ያ ከልብ የሆነውን መሪነትህን ማሳደግ ብቻ ነው የሚችለው፡፡ ብዙ

የአመራር ትምህርት ቤቶችና መጻሕፍት እያሉን እንዲህ ጥቂት መሪዎች የመኖራቸው ምክንያት መሪነት ከልብ በመሆኑ ነው። ሰዎች ከልባቸው ካላመኑብህ በስተቀር ከልባቸው አይከተሉህም።

## ሰዎች እንዲያምኑብህ የማድረጊያ ሰባት መንገዶች

### 1. ስለ ግል ሕይወትህ ግልፅ ሁን

ሕይወትህን የከበቡ ብዙ እንቆቅልሾች ካሉ ሰዎች በተፈጥሮ ወደ አንተ አይሳቡም።

### 2. ስለ ችግሮችህ እውነተኛ ሁን

መሪዎችን ጨምሮ ሁሉም ሰው ችግሮች አሉበት። ሰዎች እውነተኛ ብለው በሚያስቧቸው መሪዎች ዙሪያ ይሰበሰባሉ። እውነተኛ መሪ ሁሉም ያለበትን ዓይነት ችግሮች አሉበት ነገር ግን የሚወጣቸው ሰው ነው። የትዳር ችግሮች ካሉብህ በግልጥ ተናገራቸውና እግዚአብሔር አንተንና ባለቤትህን እንድትወጡት እንደሚረዳችሁ ለሌሎች አካፍል።

### 3. ከልብህ ስበክ

በፍጹም ስብከትን ለሕዝቡ አታንብብ።አንድ ጊዜ አንድ ዓለማዊ የአገር ገዢ በቄሱ ሲማረር ሰማሁ። እንዲህ "ንግግሮችን ሳደርግ ከልቤ እናገራለሁ፤ ከእግዚአብሔር የሚሰማ ቄስ ለምን መልእክቱን ለእኔ ማንበብ አስፈለገው?" ስብከቶችን ስታነብ አድማጮችህ እውነተኛነትህን ሊጠራጠሩ ይችላሉ። የተፃፈ ነገር ሁሉ በጥንቃቄ የታሰበ ነው። መስማት የምንፈልገው በልብህ ያለውን ነው።

> እኔ እላችኋለሁ፥ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤
>
> ማቴዎስ 12፡36

### 4. ከእግዚአብሔር ጋር ያሉህን ልምምዶች አካፍል።

ከእግዚአብሔር ጋር የግል ልምምድ መኖሩ ለመሪ ተዓማኒነትንና ሥልጣንን ይሰጠዋል። ሲጀመርም የክርስትናህ መሪነት የተመሠረተው አንተ ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት ላይ ነው። የመልአክ ወይም የኢየሱስ ጉብኝት ደርሶህ ከሆነ ለሌሎች አካፍለው፤ አስፈሪውን የእግዚአብሔር መገኘት ያወርዳል።

## 5. እግዚአብሔር የነገርህን ለሰዎች ንገራቸው

እግዚአብሔር ከተናገርህ አካፍል። ለሰዎች እግዚአብሔር እንደተናገርህ መናገር መቻል ታላቅ የእምነት እርምጃ ነው። ጌታ በግል አንተን እንደወከለህ ያሳያል። ሰዎች እግዚአብሔር መከተል ይፈልጋሉ፤ ስለዚህ አንተ ከእግዚአብሔር ከሰማህ አንተን መከተል ይፈልጋሉ።

## 6. ለራእይህ መሥዋዕትነትን አድርግ

ሰዎች ለምታምነው ነገር የምታደርቻውን መሥዋዕትነቶች ማየት ይችላሉ። መሥዋዕትነትህ ከመቶ ስብከቶች ይልቅ ጮኾ ይናገራል። እኔ የሕክምና ሙያዬን ለአገልግሎቱ ሰውቻለሁ። ያ አንድ ተግባር ከምንም ነገር የበለጠ ተአማኒነት ሰጥቶኛል። ሰዎች መሥዋዕትነትህን ሲያዩ በአንተ ያምናሉ።

## 7. የምትጸልይ ሁን። ጸሎት መንፈሳዊ ሥልጣንን ያስገኛል። ሥልጣን ያ "የእግዚአብሔርን ሰው የሚከብበው በቀላሉ የማይገለጽ፣ የማይታይ፣ የሚስብ መንፈስ" ነው።

ሥልጣን ለእግዚአብሔር ካለህ ቅርበት የሚመነጭ ነው። አንድን ሰው በቀረብከው ቁጥር ስለ እርሱ የበለጠ በድፍረት መናገር ትችላለህ። ሰዎች በጸሎት ሕይወትህ ምክንያት በአንተ ያምናሉ። ይህ ብዙ ጸሎት አለባ ሰዎች የማያውቁት ምስጢር ነው። ሰዎች ጸሎት የለሽ መሪዎችን አይከተሉም። የግል ጸሎትህ ሰዎች በአንተ እንዲያምኑ ያደርጋቸዋል።

## ምዕራፍ 121

# የምታናግረውን ሰው እንደማንነቱ አይተህ ብዙ ተናገር ወይም ምንም አትናገር

**መሪ የሚያናግረውን ሰው ማንነት ላይ ተመስርቶ ብዙ ወይም ጥቂት መናገርን መማር አለበት፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በጉጉ አድማጮች ተከቦ ሳለ ለሰዓታት ይናገር ነበር፡፡ ሰዎች ለመስማትና ለመፈወስ ኪሎሜትሮችን አቋርጠው ይመጡ ነበር፡፡ ሰዎች ተመልሰው ወደ ቤታቸው መሄድ እስከማይችሉ ድረስ ለሰዓታት ይሰብክ ነበር፡፡**

> በደጅ ያለው ስፍራም እስኪጠባቸው ድረስ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ፤ ቃሉንም ይነግራቸው ነበር።
>
> ማርቆስ 2:2

> ሕዝቡም የእግዚአብሔርን ቃል እየሰሙ ሲያስጠብቡት ሳሉ፥ እርሱ ራሱ በጌንሳሬጥ ባሕር ዳር ቆሞ ነበር፤
>
> ሉቃስ 5:1

**ኢየሱስ በሚጠሉትና በሚንቁት ሰዎች መካከል ሲሆን ምንም አልተናገረም፡፡ ጊዜ ሁሉን እንደሚፈታ (እንደሚናገር) ያውቅ ነበር፡፡**

## ኢየሱስ ሊያናግራቸው ያልፈለገ ሶስት ሰዎች

### 1. ኢየሱስ ለሃይማኖት መሪዎች የሚለው አልነበረውም፡፡

> ሊቀ ካህናቱም በመካከላቸው ተነሥቶ። አንዳች አትመልስምን? እነዚህስ በአንተ ላይ የሚመሰክሩብህ ምንድር ነው? ብሎ ኢየሱስን ጠየቀው።እርሱ ግን ዝም አለ አንዳችም አልመለሰም። ደግሞ ሊቀ ካህናቱ ጠየቀውና። የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን? አለው።
>
> ማርቆስ 14:60-61

### 2. ኢየሱስ ለገዥው ለጲላጦስ የሚለው አልነበረውም፡፡

> ጲላጦስም። አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን? ብሎ ጠየቀው። እርሱም፡- አንተ አልህ ብሎ መለሰለት።የካህናት አለቆችም ብዙ ያሳጡት ነበር፤ እርሱ ግን ምንም አልመለሰም። ጲላጦስም ደግሞ። አንዳች አትመልስምን? እነሆ፥ በስንት ነገር ያሳጡሃል ብሎ ጠየቀው።ኢየሱስም ከዚያ በኋላ ጲላጦስ እስኪደነቅ ድረስ ምንም አልመለሰም።
>
> ማርቆስ 15:2-5

3. ኢየሱስ ለሄሮድስ የሚለው አልነበረውም

ፋሲካንም ሊያርዱበት የሚገባው የቂጣ በዓል ደረሰ፤ጴጥሮስንና ዮሐንስንም። ፋሲካን እንድንበላ ሄዳችሁ አዘጋጁልን ብሎ ላካቸው።እርሱም፦ ወዴት እናዘጋጅ ዘንድ ትወዳለህ? አሉት።እርሱም አላቸው። እነሆ፥ ወደ ከተማ ስትገቡ ማድጋ ውኃ የተሸከመ ሰው ይገናኛችኋል፤ ወደ ሚገባበት ቤት ተከተሉት፤

ሉቃስ 23፡7-10

እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን የሚጠሉት ነበሩ፤ እርሱም ያውቀው ነበረ። እርሱ የሚናገረው ምንም ነገር አስተሳሰባቸውን እንደማይቀይር ያውቅ ነበር። የንግግር ባለሙያን ምክር ከመከተል የኢየሱስን ምሳሌነት መከተል እመርጣለሁ። ብዙ ጉዳዮችን ለእግዚአብሔርና ለጊዜ ትቻለሁ። ለሁሉም ክስ እርሱ የተሻለ መልስ አለው። ኢየሱስ በኃይል ቢከሰስም ለክሶቹ አስተያየትም ሆነ መልስ መስጠት አላፈለገም። ኢየሱስ መናገር ስለማይችል አልነበረም። በተራራው ላይ እንዴት እንደሰበከ እናያለን። በባሕር ዳር እንዴት እንዳስተማረ እናያለን። ከስብከቱ በኋላ ሰዎችን መመገብ እስኪኖርበት ድረስ እንዴት ረጅም ሰዓት እንደሰበከ እናያለን።

ብዙ መጋቢዎች ቃለመጠይቆችና ውይይቶች ላይ መገኘት እንዳለባቸው ይሰማቸዋል። ስማቸውን የማጥራትና ገጽታቸውን የማሻሻል ግዴታ ያለባቸው ይመስላቸዋል። ልብ በል መጋቢዎች ጋዜጠኞችን ማናገርም ሆነ ቃለ መጠይቅ ማድረግ የለባቸውም እያልኩ አይደለም። የምለው ምንም ቢሆን ሀሳባቸውን የማይለውጡ፣ ጥላቻን የተሞሉና ተቃዋሚ ቃለ መጠይቅ አድራጊዎችን ለማነጋገር ኢየሱስ አልተጨናነቀም ነው። ሁሉም አገልጋይ የኢየሱስ ክርስቶስን አርአያነት እንዲከተል እመክራለሁ።

## መጋቢዎች ጋዜጠኞችን ማነጋገር የማይገደዱበት ሶስት ምክንያት

1. መገናኛ ብዙሃኑ የወንጌልን አገልጋይ የመገንባትም የማፍረስም ኃይል የላቸውም።

ብዙ የመገናኛ ብዙሃን ሰዎች ይህ ኃይል እንዳላቸው አድርገው እንደሚያስቡ አውቃለሁ። ጲላጦስም ኢየሱስን ለማጥፋትም ሆነ ለማጽናት ኃይል እንዳለው አስቦ ነበር።

ስለዚህ ጲላጦስ። አትነግረኝምን? ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው።

ዮሐንስ 19፡10

## ኢየሱስ ግን አረመው

ኢየሱስም መልሶ፦ ከላይ ካልተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልነበረህም፤ ስለዚህ ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአቱ የባሰ ነው አለው።

ዮሐንስ 19፡11

በተመሳሳይ መንገድ ብዙ ጋዜጠኞች ከፈለጉ የእግዚአብሔርን ሰው ወይም አንዲትን ቤተክርስቲያን የማውደም ጉልበት እንዳላቸው ይሰማቸዋል። እግዚአብሔር ካልፈቀደ በስተቀር ማንም ምንም የማድረግ ሥልጣን የለውም። ኢየሱስ በእነዚያ መልስ ባልሰጠባቸው ክሶች ምክንያት አገልግሎቱ እየፈረሰ እንደሆነ ቢያስብ ኖሮ መልስ ይሰጥ ነበር። ይህንን ምስጢር ተማር፣ ማንምኛውም ሰብዓዊ ፍጡር እግዚአብሔር የገነባውን ሊያውድም አይችልም። እነዚያ ክሶች ወደፊት በእነዚያ ሐሰተኞች ላይ ለሚፈርደው ፍርድ እንደ መነሻ ሆነው ብቻ ነው የሚያገለግሉት። የሆነን ነገር ያወደሙ ሊመስል ይችላል፤ እውነታው ግን የእግዚአብሔርን የእጅ ሥራ ማንም ሊያወድም አይችልም።

2. መጋቢዎች ቃሎቻቸውን በእውነት ለሚያደንቁት ለጉባዔዎቻቸው መቆጠብ አለባቸው።

ለአገልግሎት ተገቢው መሰባሰብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንጂ ለሚያጣጥሉ ለሚንቁ የ"ቶክ ሾው" አዘጋጆች እንዳልሆነ መጋቢዎች ሊያወቁት የሚገባ ነው ። ከጅምሩ የሚያደሉና ጥላቻን የተሞሉ ቃለ መጠይቅ አድራጊዎች ኢየሱስን ሲጠይቁት የሚናገረው ምንም አዲስ ነገር እንደሌለው አስረዳቸው። ማለት የሚገባውን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ብሎ ነበር።

ሊቀ ካህናቱም ኢየሱስን ስለ ደቀ መዛሙርቱና ስለ ትምህርቱ ጠየቀው። ኢየስስም መልሶ፦ እኔ በግልጥ ለዓለም ተናገርሁ፤ አይሁድ ሁሉ በሚሰበሰቡበት በምኵራብና በመቅደስ እኔ ሁልጊዜ አስተማርሁ፥ በስውርም ምንም አልተናገርሁም።ስለምን ትጠይቀኛለህ? ለእነርሱ የተናገርሁትን የሰሙትን ጠይቅ፤ እነሆ፥ እነዚህ እኔ የነገርሁትን ያውቃሉ አለው።

ዮሐንስ 18፡19-21

እንዲህ ዓይነቱ መልስ ብዙ ዘጋቢዎችን ያበሳጫል። በእርግጥ በዚያ ቀን የነበሩትን ሰዎች አንገብግቧቸዋል።

ይህንም ሲል በዚያ ቆሞ የነበረው ከሎሌዎች አንዱ። ለሊቀ ካህናቱ እንዲህ ትመልሳለህን? ብሎ ኢየሱስን በጥፊ መታው።ኢየሱስም መልሶ፦ ክፉ ተናግሬ እንደ ሆንሁ ስለ ክፉ መስክር፤ መልካም ተናግሬ እንደ ሆንሁ ግን ስለ ምን ትመታኛለህ? አለው።

ዮሐንስ 18፡22፡23

3. መጋቢ ራሱን ለሰዎች ትክክል እንደሆነ የማስረዳት ግዴታ የለበትም።

**በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለህ ከሆንክ ለማህበረሰቡ አስደሳች ሆነህ መታየተ አያስፈልግህም። ራስህን በሰዎች ፊት ተቀባይነት እንዲኖርህ ጥረቶችን ማድረግ እግዚአብሔርን ሊያሳዝኑ ይችላሉ።**

እንዲህም አላቸው፦ ራሳችሁን በሰው ፊት የምታጸድቁ እናንተ ናችሁ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ልባችሁን ያውቃል፤ በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኵሰት ነውና።

ሉቃስ 16፡15

ምዕራፍ 122

# የደረጃ የማዕረግን መርህ ተቀበል

እንደ ኃያላን ይሮጣሉ፥ እንደ ሰልፈኞችም በቅጥሩ ላይ ይወጣሉ እያንዳንዱም በመንገዱ ላይ ይራመዳል፥ ከእርምጃቸውም አያፈገፍጉም።

ኢዮኤል 2:7

## ስለ ማዕረግ እያንዳንዱ መሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ አስር ነገሮች

1. ሁላችንም አንድ ዓይነት እንድንሆን አልተፈጠርንም። ማዕረግ መስጠት ለዚህ እውነታ ዕውቅና መስጠት ነው።

አ

ንዳንድ የፖለቲካ ዘይቤዎች ሁሉንም ሰው አንድ ዓይነት ለማድረግ ሞክረዋል። እግዚአብሔር እኩል እንድንሆን አልፈጠረንም። መሪ በነገሮች ድልድል ውስጥ ሥፍራ እንዳለው የሚረዳ ሰው ነው።

2. ማዕረግህ የተግባርህን ደረጃ ያሳያል

ምን ያህል ከፍ ወይም ዝቅ እንዳልክ ይነግርሃል። ማዕረግህ በእግዚአብሔር ወይም በሰው የበላዮችህ ሊሰየም ይችላል።

3. ማዕረግ ሰውንና ድርጅትን ማምታታትን ያስቀራል።

4. ማዕረግ ከዚህ በላይ ምን ያህል ከፍ ብለህ ልትሄድ እንደምትችል ያሳይሃል።

ከእኔ ይልቅ በአገልግሎታቸው የበለጠ ዕድገት ስላላቸው ሰዎች አውቃለሁ። ጌታ በሚያደርገው ነገር ከእነርሱ ጋር ደስ እሰኛለሁ። ሊኖር በሚችለው ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዳልሆንኩ አውቃለሁ። ከእኔ የሚቀድሙትን አከብራለሁ።

5. ማዕረግ ምን ያህል ወደታች ልትሰጥም እንደምትችል ያሳይሃል።

ሁልጊዜ ከአንተ የቀደሙ ወይም ከአንተ በኋላ ያሉ ሰዎች መኖራቸውን ተረዳ።

6. ማዕረጐች ሊለወጡ የሚችሉ ናቸው ደግሞም በአብዛኛው ይለወጣሉ።

የአሁኑ ማዕረግህ የሕይወትህ ዘመን ሁሉ ደረጃ አለመሆኑን ስታውቅ ለወደፊቱ ለመሾም ተስፋ ይኖርሃል።

7. ወደ ቀጣዩ ማዕረግ ከመግባትህ በፊት እያንዳንዱ ማዕረግ በደንብ ሊታወቅ ይገባል።

እግዚአብሔር በመጋቢነት ደረጃ ላይ ካስቀመጠህ በደንብ መርምረህ እወቀው በመጋቢነት ሥራ ውስጥ ያለውን በሙሉ ድረስበት።

8. ከማዕረግ ወደ ማዕረግ መሾምን የሚወስኑ መርሆች አሉ።

ለምሳሌ፣ ባለህበት ማዕረግ ታማኝ እና ፍሬአማ መሆን ለሹመት እጅግ አስፈላጊ ናቸው።

9. ትክክለኛ የማዕረግ ለውጥ የሚመጣው እግዚአብሔር ራሱ ሲሾምህ ነው።

ዓመፀኞችን፦ አትበድሉ አልኋቸው፥ ኃጢአተኞችንም። ቀንዳችሁን አታንሡ

መዝሙር 75፡4

ሹመት ከእግዚአብሔር ነው የሚመጣው። በጌታ ያለኝ ሥፍራ በእግዚአብሔር የተሰጠ ነው፤ ያንተም እንዲሁ። እርስ በእርሳችን እንከባበር፤ እግዚአብሔርም ከፍ ወዳለ ማዕረግ ያሸጋግረናል።

10. ከፍ ወዳለ ማዕረግ ማደግ በአብዛኛው ከአዳዲስ ጥቃቶች ጋር ነው አብሮ የሚመጣው። አዲስ ደረጃዎች አዲስ ዲያቢሎሶችን ያመጣሉ።

የዳዊት ችግሮች የጀመሩት ጎልያድን ሲገድል ነው። ጐልያድን በመግደል ከአንድ ከማይታወቅ ወጣትነት ወደ ዕውቅ ጦረኛነት ማዕረግ ተሸጋገረ። ያኔ ነው ሳዖል ያየው እና ያሰቃየው የጀመረው።

ከእግዚአብሔር የሆነ ሹመት ከስቃይ ጋር አብሮ ነው የሚመጣው። ከፍ ያለ ማዕረግ ያሉትን እንደምታዎች ማወቅ አለብህ። አሁን የለሁበት የአገልግሎት ደረጃ ላይ እግዚአብሔር ከፍ እንደሚያደርገኝ

**በፍጹም አላውቅም ነበር። እንደዚህ ዓይነት ስቃይ እንደሚገጥመኝም በፍጹም አልጠበቅሁም።**

> አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን ወንድሞችንና እኅቶችንም እናቶችንም ልጆችንም እርሻንም መቶ እጥፍ፥ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም።

ማርቆስ 10፡30

## ምዕራፍ 123

# በዙሪያህ ያሉትን ሰዎች ወደተሻሉ ሰዎች ለውጣቸው

*ወደ ፊትም ደግሞ ደስ ይለኛል፤ ይህ በጸሎታችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ መሰጠት ለመዳኔ እንዲሆንልኝ አውቃለሁና፥*

ፊልጵስዩስ 1:19

ጥሩ መሪ ተከታዮቹን ይለውጣል። ተፅዕኖ የምታደርግባቸው ሰዎች መቼም አይረሱህም። ለዘለዓለም ባለውለታቸው ትሆናለህ። እግዚአብሔር መሪ እንድትሆን ከነገረህ ራስህን በምትመራቸው ሰዎች ሕይወት ላይ እየሰራህ ልታይ ይገባል። መሪነት ሊቀመንበር ወይም ፕሬዝዳንት ተብሎ መጠራት ብቻ አይደለም። መሪነት የሚያጓጉ ማዕረጎችን መንበሽበሽ አይደለም። መምራት የተሻሉ ሰዎች እስኪሆኑ ድረስ ሰዎች ላይ መስራት ነው።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በመራባቸው ሶስት ዓመታት ሕይወታቸው ሙሉ በሙሉ ተለውጧል።

*ጴጥሮስና ዮሐንስም በግልጥ እንደ ተናገሩ ባዩ ጊዜ፥ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው አደነቁ፥ ከኢየሱስም ጋር እንደ ነበሩ አወቁአቸው፤*

የሐዋርያት ሥራ 4:13

ጥሩ መሪ መሆን ሕይወትህን ለዘለዓለም ይለውጣል። ጥሩ መሪ በሕይወታቸው ሊረሳ እስከማይችል ድረስ የተከታዮቹን ሕይወት ይቀይራል። ጥሩ መሪ የእርሱ ዕዳ እንዳለባቸው እስከሚሰማቸው ድረስ የተከታዮቹን ሕይወት ይቀይራል። በጳውሎስና በፊልሞና መካከል የሆነው ይኸው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወቱ ላይ ምን ያህል ተፅዕኖ እንዳደረገ ፊልሞናን አስታውሶታል። ሕይወቱን እንኳን ሊሰጠው እንደሚገባው ነግሮታል።

*እኔ ጳውሎስ፡- እኔ እመልሰዋለሁ ብዬ በእጄ እጽፋለሁ፤ ከዚህም በላይ ለእኔ የራስህ ደግሞ ብድር እንዳለብህ አልልህም።*

ፊልሞና 19

# የማይረሳ መሪ የመሆኛ ስምንት መንገዶች

1. አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ምራ

አንድን ሰሙ ወደ ክርስቶስ ስትመራ ወደ ጌታ ስላመጣኸው ለዘለዓለም የአንተ ባለዕዳ ይሆናል።

2. አንድን ሰው በመንፈስ ቅዱስ ወደ መሞላት ምራ

ዛሬ በምድር ላይ ወዳለው ወደ ታላቁ ኃይልና ረዳት ስለመራሃቸው ለዘለዓለም የአንተ ባለዕዳ ይሆናሉ።

3. አንድን ሰው በእግዚአብሔር ቃለ አፅና

ለሰው ልጆች ታላቁ የጥበብና የምሪት ምንጭ ወደሆነው ስለመራሃቸው ለዘለዓለም የአንተ ባለዕዳ ይሆናሉ። እኔ የጥሞናን ጊዜ እንዴት እንደማሳልፍ ላስተማረችኝ በጌታ እናቴ ለሆነችው ለዘለዓለም ባለዕዳ ነኝ። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያለኝ የየዕለት የጥሞና ጊዜ የሕይወቴ ታላቁ ምስጢር ሆኗል። በእርግጠኝነት ይህንን ታላቅ ምስጢር ላስተማረኝ ባለዕዳ ነኝ።

4. አንድን ሰው ወደ ትክክለኛው ቤተክርስቲያን ምራ።

ትክክለኛው ሕብረት በክርስቲያኖች መካከል ልዩነትን ያመጣል። አንድን ክርስቲያን ከድነት በኂላ በትክክለኛው መንገድ ላይ እንዳይቆይ የሚያደርግ ምክንያት ነው።

5. አንድን ሰው ወደ አገልግሎት እንዲገባ እርዳ

አገልግሎት በምድር ላይ ያለ ከፍተኛ ጥሪ ነው። ለሰው ልጅ ከሁሉም ምርጥ የሆነ ሥራ ነው። ዘለዓለማዊ ዋጋ ያለው ብቸኛው ሥራ ይህ ነው። በአገልግሎት ውስጥ ለማገልገል ከመጠራት የሚልቅ ከፍ ያለ ልዩ ጥቅም እንደሌለ ሁላችንም መረዳታችን አይቀርም። የጊዜ ጉዳይ ነው።

6. አንድ ሰው እንዲያገባ እርዳው

ኢየሱስን ከመምረጥ በኂላ በሕይወት ከሚወሰኑ ታላላቅ ውሳኔዎች አንዱ የትዳር ጓደኛን ማግኘት ነው። ሊያጠፋህ ይችላል። አንድን ሰው ወደ ትክክለኛው ሰው በትክክለኛው ሰዓት እንዲያገባ ከረዳህ ሕይወቱን በሙሉ ባለውለታው ትሆናለህ።

## 7. የአንድ ሰው ጋብቻ እንዲተርፍ እርዳ

ጋብቻ እንደ ብርጭቆ ነው፣ በቀላሉ ይሰበራል፡፡ ችግር ውስጥ የገቡ ትዳሮች ለመፈወስ አስቸጋሪ ናቸው፡፡ የአንድን ሰው ትዳር ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲፈወስ ከረዳህ ሕይወቱን በሙሉ ያስታውስሃል፡፡

## 8. በሕይወቱ ወይም በሕይወቷ አቋራጭ ላይ ትክክለኛ ውሳኔዎችን እንዲያደርግ/እንድታደርግ እርዳ፡፡

ውሳኔዎች በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ትልቅ ልዩነት ያመጣሉ፡፡ ለምሳሌ የምትኖርበት ሥራህ፣ ትምህርት ቤት፣ ወዘተ... አንድን ሰው በትክክለኛው አቅጣጫ እንዲሄድ ተፅዕኖ ካደረግህበት ለእርሱ የማትረሳ ሰው ትሆናለህ፡፡

> እኔ ጳውሎስ፡- እኔ እመልሰዋለሁ ብዬ በእጄ እጽፋለሁ፤ ከዚህም በላይ ለእኔ የራስህ ደግሞ ብድር እንዳለብህ አልልህም።
>
> ፊልሞና 19

## ምዕራፍ 124

# ወደ ትክክለኛው ምድር በመሄድ ሽቅብ ውጣ

ብዙ ሰዎች ውድ የሆነውን ሕይወታቸውን ከአንድ ሥፍራ ወደሌላ በመወላወል ያባክናሉ። የምትኖርበት ቦታ ለስኬትህ በጣም ጠቃሚ ነው። ለዚህም ምክንያቱ እግዚአብሔር በየቦታው ሳይሆን በአንድ ቦታ ስለጠራህ ነው! ማንም በሁሉም ሥፍራ ስኬታማ አይደለም። ኢየሱስ እንኳን ሁሉም ቦታ አልተሳካለትም። ባልተፈለገበት በፍጹም አልቆየም። ኢየሱስ በየቦታው ኃይለኛ ተአምራትን ሊያደርግ እንዳልቻለ ይናገራል።

> ከዚያም ወጥቶ ወደ ገዛ አገሩ መጣ ደቀ መዛሙርቱም ተከተሉት።... በዚያም በጥቂቶች ድውዮች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወስ በቀር፥ ተአምር ሊያደርግ ምንም አልቻለም።
>
> ማርቆስ 6፡1፣5

ደህና ተከታዮች በነበሩት ሥፍራ እንኳን ኢየሱስ የተለያዩ የስኬት ደረጃዎች ነበሩት። ብዙ ኃያል ሥራዎችን ሰርቷል፤ አብዛኞቹ የተከናወኑት ግን በተወሰኑ ከተሞች ነበር። በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ የበለጠ ስኬት የታየባቸው መልክአ ምድራዊ ቦታዎች ነበሩ። ወደማታውቅባቸው ሥፍራዎችም ቢሆን እግዚአብሔር ከጠራህ ለመሄድ ፈቃደኛ ሁን። ሁላችንም የተላመድነውን አካባቢና የምቾት ክልሎቻችን እንወዳለን። ስለእርሱ ዓላማ በታዛዥነት ሥፍራህን በመቀየር ዝግጁ ስትሆን የእግዚአብሔር ሹመት እየተጠባበቀህ ነው።

> በዚያን ጊዜ የሚበዙ ተአምራት የተደረገባቸውን ከተማዎች ንስሐ ስላልገቡ ሊነቅፋቸው ጀመረ እንዲህም አለ፦ወዮልሽ ኮራዚ፤ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤ በእናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን፥ ማቅ ለብሰው አመድም ነስንሰው ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበርና....አንቺም ቅፍርናሆም፥ እስከ ሰማይ ከፍ አልሽን? ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ፤ በአንቺ የተደረገው ተአምራት በሰዶም ተደርጎ ቢሆን፥ እስከ ዛሬ በኖረች ነበርና።
>
> ማቴዎስ 11፡20፣21፣23

## በመሄዳቸው ስኬታማ የሆኑ ሰባት ሰዎች

1. የተወለደበትን ሥፍራ ለቆ በመሄድ ዋና መስሪያ ቤቱን በቅፍርናሆም ባደረገ ጊዜ የኢየሱስ አገልግሎት አበበ።

የተወለደበት ከተማ ያሉ ሰዎች ሲሰብክ ተናደዱ።

እርሱ ግን እንዲህ አለው፡- አንድ ሰው ታላቅ እራት አድርጎ ብዙዎችን ጠራ፤..ከእናንተ ግንብ ሊሠራ የሚወድ ለመደምደሚያ የሚበቃ ያለው እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ ከሳራውን የማይቈጥር ማን ነው?

ሉቃስ 4፡16፣28

ይሁንና የቅፍርናሆም ሕዝቦች አገልግሎቱን ወደዱት፡፡ በቅፍርናኖም ኢየሱስ አስተማረ፣ ሰበከ፣ እንዲሁም ብዙ ታላላቅ ሥራዎቹን አከናወነ፡፡

ወደ ገሊላ ከተማም ወደ ቅፍርናሆም ወረደ። በሰንበትም ያስተምራቸው ነበር፤ቃሉ በሥልጣን ነበርና በትምህርቱ ተገረሙ።

ሉቃስ 4፡31፣32

የአገልግሎቴን ታላላቅ ተአምራት በአንዳንድ ሥፍራዎች አይቻለሁ፡፡ እግዚአብሔር ታላላቅ ነገሮችን የሚያደርግባቸው የተወሰኑ ቦታዎች እንዳሉት አውቃለሁ፡፡

2. ዮሴፍ ወደ ግብፅ ለመኖር በሄደ ጊዜ ስኬታማ ሆነ፡፡

አንዳንዴ እግዚአብሔር እንድንሆን ወደሚፈልገን ሥፍራ ለመሄድ ፈቃደኞች አይደለንም፡፡እንደ ዮሴፍ እኛም አንዳንዴ እስረኞች ሆነን መሄድ አለብን፡፡

ዮሴፍ ግን ወደ ግብፅ ወረደ የፈርዖን ጃንደረባ የዘበኞቹም አለቃ የሚሆን የግብፅ ሰው ጲጥፋራ ወደ ግብፅ ካወረዱት ከእስማኤላውያን እጅ ገዛው።

ዘፍጥረት 39፡1

3. ሩት ከሞአብ ወጥታ በኢየሩሳሌም ለመኖር ስትሄድ ስኬታማ ሆነች፡፡

ሩትም። ወደምትሄጅበት እሄዳለሁና፥ በምታድሪበትም አድራለሁና እንድተውሽ ከአንቺም ዘንድ እንድመለስ አታስቸግሪኝ ሕዝብሽ ሕዝቤ፥ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል

ሩት 1፡16

አንዳንድ ጊዜ ሁኔታዎች ሰዎች ሥፍራቸውን እንዲቀይሩ ያደርጓቸዋል፡፡ ሩት ባሏ የሞተባት ሴት ሆነች፡፡ ሕይወቷ መሪር አቅጣጫን ያዘ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ራሳቸው ነበሩ ታዋቂ እንድትሆን ወደታየችበት ሥፍራ የሚመሯት፡፡ ሩት የንጉስ ዳዊት ቅድመ አያት ስለሆነች ወሳኝ ነበረች፡፡ በምድር ከኖሩ ሁሉ ባለጠጋ የነበረው የሰለሞን ቅም አያት ስለነበረችም ታዋቂ ነበረች፡፡

4. ዳንኤል ከእየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ሲወሰድ ስኬታማ ሆነ

ለሶስት የተለያዩ አገዛዞች ጠቅላይ ሚኒስቴር እንዲሆን ታይቶ ነበር፡፡ ዳንኤል በናቡከደነፆር መንግስት፣ ብልጣሶር መንግስትና በፐርሺያዊው ዳርዮስ ከፍተኛ ቢሮ ውስጥ አገልግሏል፡፡ ብዙ ከአፍሪካ የሄዱ የኢኮኖሚ ስደተኞች እግዚአብሔርን በማያምኑ በአውሮፓ አገር ውስጥ እንዲሰሩ እግዚአብሔር እየተጠቀመባቸው ነው፡፡

5. ከአገሩ ወጥቶ ወደ ከነአን ሲገባ የአብርሃም ሕይወት ተለወጠ፡፡

እግዚአብሔርም ታላላቆች አንበሪዎችን፥ ውኃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኘቻቸውንም ተንቀሳቃሾቹን ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ፥ እንደ ወገኑ የሚበሩትንም ወፎች ሁሉ ፈጠረ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ።

ዘፍጥረት 12፡1

እግዚአብሔር አብርሃምን ከጣዖት አምላኪ ዘመዶቹ መነጠል ፈልጐ ነበር፡፡ አብርሃም መራቁ አስፈላጊ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወትህ መከናወን ከመጀመሩ በፊት ሥፍራን መቀየር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡

6. ከአጎቱ ከላባ ጋር ለመኖር ሲሄድ የያዕቆብ ሥራ አበበ

ላባም። በዓይንህ ፊት ሞገስን የማገኝ ብሆንስ ከዚሁ ተቀመጥ እግዚአብሔር በአንተ ምክንያት እንደ ባረከኝ ተመልክቼአለሁና አለው።....ያ ሰውም እጅግ ባለ ጠጋ ሆነ ብዙም ከብት ሴቶችም ወንዶችም ባሪያዎች ግመሎችም አህዮችም ሆኑለት።

ዘፍጥረት 30፡27፣43

7. እግዚአብሔር ከጠራው በኂላ ጳውሎስ በአሕዛብ መሐል ኖረ

የእርሱ አገልግሎት ለአህዛብ እንጂ ለአይሁድ አልነበረም፣ ይህንንም ያውቅ ነበር፡፡ እንደ ጠቢብ መሪ ስኬታማ የሚሆነው በአካል ትክክለኛው ቦታ ሲገኝ ብቻ እንደሆነ ያውቅ ነበር፡፡ ከጅማሬው ጳውሎስ በኢየሩሳሌም መኖርን ተወ፡፡ ቀሪው ሕይወቱ በአሕዛብ መካከል ነበር፡፡ እንደመሪ ከጳውሎስ ስኬት ቁልፎች አንዱ ይህ ነበር፡፡

ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፥ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም፥ከእኔም በፊት ሐዋርያት ወደ ነበሩት ወደ ኢየሩሳሌም አልወጣሁም፥ ነገር ግን ወደ ዓረብ አገር ሄድሁ እንደ ገናም ወደ ደማስቆ ተመለስሁ።

ገላትያ 1፡15-16፣17

ምዕራፍ 125

# የሥጋዊ ስሜቶችህን ተቆጣጠር

እግዚአብሔር በመላእክት አይደለም የሚሰራው፣ "ሥጋዊ ስሜቶች" ያላቸው ብዬ በምጠራቸው ወንዶችና ሴቶች ሰዎች ነው።

ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን፤

2ኛ ቆሮንቶስ 4:7

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሸክላ ዕቃ የሚለው የሚያመለክተው ሥጋን ነው። ሌሎችን ለመቆጣጠር ከመሞከርህ በፊት ራስህን መቆጣጠር አለብህ። መሪ ለሥጋዊ ነገሮች ያለውን ተፈጥሯዊ ፍላጐት መቆጣጠርና መምራትናን መማር አለበት። ይህ ሥጋዊ ስሜት ካልተገታ አንድ ሰው ማንንም ሊመራ እንደማይችል ይደርስበታል። አንዳንድ ሰዎች መጾም አይችሉም። ሆዳቸውን መቆጣጠር አይችሉም። የተፈጥሮ ስሜቶችህ ተፈትተው ከተለቀቁ ጥሩ መሪ መሆን አትችልም።

አንዳንድ ሴቶች የመቅናትና የመነጫነጭ ተፈጥሮአዊ ስሜት አላቸው። እነዚህን ሥጋዊ የተፈጥሮ ስሜቶች ካልገታሽ ማንንም መምራት አትችይም። ከቤተክርስቲያን አባላቱ (ከሚስቱ ሌላ) ልጆችን በተከታታይ ይወልድ የነበረን የቤተክርስቲያን መጋቢ አስታውሳለሁ። በቀላሉ የቤተክርስቲያኑ አባላት ማንም እስከማይቀር ድረስ እየተመናመኑ ሄዱ። መጋቢ ሥጋዊ የተፈጥሮ ስሜቶቹን በቁጥጥሩ ሥር አላደረገም ነበር።

## ኢየሱስ የሥጋ የተፈጥሮአዊ ስሜቶቹን አሸንፏል

ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም።

ዕብራውያን 4:15

ኢየሱስ በጌተሰማኔ የመናፈሻ ሥፍራ ሳለ የተፈጥሮ ሥጋዊ ስሜቶቹ ከመስቀሉ ሀሳብ እንዲያፈገፍግ አደረጉት። ይሁንና አጥብቆ ስለዚህ ነገር ፀለየ፤ እናም ራሱን መቆጣጠር ቻለ። ለአንተና ለእኔ ወደ መስቀል ሄደ። በመስቀል ላይ ሆኖ እንኳን የተፈጥሮ ስሜቶቹ

መላእክትን እንዲያድኑት መጣራትን እንዲያስብ አደረጉት። አሁንም ግን ራሱን ገታ።

መሪዎችን ከተከታዮች የሚለያቸው እነዚህን የተፈጥሮ ስሜቶች መቆጣጠር ነው። መሪዎች ምንም ስሜቶች፣ የሚፈትኑ ነገሮችና የሥጋ ምኞቶች የሌሏቸው አድርገህ አታስብ። እንደማንኛውም ሰው የተፈጥሮ ስሜቶች አሏቸው።የመሪነት ቁልፉ እነዚህን ስሜቶችን በመቆጣጠር ነው። የተፈጥሮ ስሜቶቻችንን ብንከተል ኖሮ መቼም አንፀልይም፣ አንፆምም ወይም መጽሐፍ ቅዱሶቻችንን አናነብም ነበር።

ሐዋርያው ጳውሎስ የተፈጥሮ ስሜቶቹን እንዴት እንደገታ ተናግሯል። ጳውሎስ ማድረግ ከቻለ እንግዲያውስ እኛም እንችላለን።

> ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።
>
> 1ኛ ቆሮንቶስ 9፡27

## ምዕራፍ 126

# በሀሳባዊውና በእውኑ መካከል ያለውን ልዩነት ተረዳ

ልምድ ያለው ሰው ከሀሳባዊውና በእውኑ መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳውቅ ሰው ነው። "ሀሳባዊው" እንደሰማይ ከዋክብት ነው። የት መሄድ እንደምንፈልግ ይነግረናል። እውነታው "በምድር ላይ ያለው" ነው። በእርግጥ የት እንዳለን ያሳየናል። ንድፈ ሃሳቢዊ ዕውቀት ሃሳባዊውን ይነግርሃል፤ ልምምድ ግን እውን የሆነውን ይነግርሃል።

ወጣትና ልምድ የሌላቸው ፖለቲከኞች በአብዛኛው ወደ ፖለቲካው ዓለም የሚገቡት ብዙ ዓይነት ሀሳባዊ ፍልስፍናዎችን ይዘው ነው። አብዛኞቹ እነዚህ ሰዎች የኮሚኒስት እና ሶሻሊስት ዝንባሌ አላቸው። ከጊዜና ልምድ ሲመጡ ግን በአብዛኛው ነገሮች እንዳሰቡት ቀጥ ያሉ እንዳልሆኑ በአብዛኛው ያስተውላሉ። በአብዛኛው እንዲህ ዓይነት ሰዎችን ወደ ካፒታሊስት አስተሳሰብ ሲለውጡ ታገኛለህ።

ሀሳባዊውና እውኑ በአገልግሎት ውስጥም ይታያሉ። የሆኑ ነገሮችን ብታደርግ የሆኑ ውጤቶችን እንደምታገኝ ልታስብ ትችላለህ። እየበሰልክ ስትሄድ ነገሩ እንደዚህ ቀላለ አለመሆኑን ትደርስበታለህ። የቤተክርስቲያን ዕድገት መርሆች ቢተገበሩም ቤተክርስቲያኒቷ አሁንም አታድግም። ይህ የሆነበት ምክንያት ሀሳባዊው ከዕውኑ የተለየ ስለሆነ ነው። ልምድ ያንን ያስተምርሃል።

ለሰባ ዓመታት ያህል መኖር ደስ የሚያሰኝ ነገር ቢሆንም ገና ወጣት የሆኑ መጋቢዎች በዕድሜአቸው አጋማሽ ላይ ሳሉ ሲሞቱ አይቻለሁ። ሁሉም ሰው ቢፈወስ ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው። ይሁንና እውነታው ይህ አይደለም። ኢየሱስ እንኳን ሁሉን ሰው ሊፈውስ አልሞከረም። ልምድ በሳል ያደርግሃል እንዲሁም የበለጠ እና ችሎታ ያለው መሪ ያደርግሃል።

እየተማርክ ያለኸውን የብስለት ትምህርቶች አትናቅ። በልምምዶችህ ምክንያት የሥነ መለኮት አስተምሆሮዎችህን አትቀይር። የእግዚአብሔር ቃል አሁንም እውነት ነው። እውነታው እኛ ሁሉን ነገር አለማወቃችን ነው። እውነታው ከሀሳባዊው በብዙ የሚለይበት ምክንያት አለ። በአብዛኛው እኛ ያልተገነዘብናቸው በሥራ ላይ ያሉ

ሌሎች ምክንያቶች አሉ። የምናውቀው ወይም የምንረዳው ሁሉን ነገር አይደለም። ጳውሎስ ሁሉን ነገር አልተረዳም። በድብዝዝ መስታወት እንደማየት አድርጐ ነው የገለፀው።

ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ።

1ኛ ቆሮንቶስ 13፡12

## ሀሳባዊነትና ከንቱ አስተሳሰቦች

መሪነት በአብዛኛው ብስለትን ይጠይቃል። ብስለት የሚመጣው ከልምድ ነው። የሕይወት ልምምድ ያጠነክርሃል። ለአመራር ብስለት ይፈለጋል። ብስለት ከንቱ አስተሳሰቦችንና ሀሳባዊነትን ያባርራል።

በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፥ አዲስ ክርስቲያን አይሁን።

1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡6

ዕጩ ፕሬዝዳንት ቢያንስ አርባ ዓመት ለምን መሆን እንዳለበት ጠይቀህ ታውቃለህ! በአርባ ዓመት ልምድ ከንቱ አስተሳሰቦችንና ሀሳባዊነትን ያስወግዳል። በሚያጠነክርህና የበለጠ ልምድ ያለው በሚያደርግህ መንገድ ተጓዝ። ከምታሳልፈው እያንዳንዱ ልምምድ ተማር።

ይህንን መጽሐፍ እየፃፍኩ የኬት ግሪንን መዝሙር እያደመጥሁ ነው። የእንደዚህ ዓይነት ሰው ዕድሜ ሃያ ስምንት ዓመት ላይ ለምን እንደሚቀጭ ሊገባኝ አይችልም። የእርሱ ዝማሬ ወኔ፣ ቅናት እና ቅባት ከዘቀጠው የዛሬ ቀን የክርስቲያን ዝማሬ ጋር ሊወዳደር አይችልም። ይሁንና ኬት ግሪን በዕድሜው አጋማሽ ላይ ተወስዷል። ሚስቱንና ትናንሽ ልጆቹን ለብቻቸው ተዋቸው። ለዚህ ማብራሪያ አለህ? እኔ የለኝም! ምስጢር የሆኑ ነገሮች ለጌታ ናቸው። በሳል ሁን!

ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው።

ዘዳግም 29:29

ምዕራፍ 127

# በድርጅትህ ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ዓይነት ሠራተኞች ለይተህ እውቅ።

በአንድ መሪ ሥር ሆነው የሚሰሩ ብዙ ዓይነት ሰዎች አሉ። ያሉትን ትክክለኛ ልዩነቶች መለየት ጠቃሚ ነው።

## ሁሉም መሪ መርምሮ ማወቅ የሚገባው አምስት ዓይነት ሠራተኞች

### 1. ከመስራት ይልቅ ማረፍን የሚመርጡ ሠራተኞች

እግዚአብሔር ለስድስት ቀናት ሠርቶ አንድ ቀን አረፈ። ይህም ከማረፍ መሥራት ይሻላል ማለት ነው። ከመሥራት ይልቅ ማረፍን የሚመርጥ ማንኛውም ሠራተኛ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ሥራ አላገኘውም።

### 2. ምንም ተጨማሪ ወይም አዲስ ነገር ለመስራት ዝግጁ ያልሆኑ ሠራተኞች

እንዲህ ያሉ ሠራተኞች ዋጋ የላቸውም፣ ሁልጊዜ ሲሰሩ የነበሩትን ነው መስራት የሚፈልጉት። ለውጥን አይፈልጉም።

### 3. ማንኛውንም ሥራ ለመስራት ዝግጁ የሆኑ ሠራተኞች

እንዲህ ያሉ ሠራተኞች ጠቃሚ ናቸው። ለመማር ዝግጁ ናቸው። ለመሻሻል ይፈልጋሉ። ሊያስደስቱህ ይፈልጋሉ።

### 4. ውጤት - አምጪ ሠራተኞች

ከሠራተኛ ችሎታዎች ሁሉ ይበልጥ ጠቃሚ ከሆኑት መካከል አንዱ ውጤት የማምጣት ችሎታው ነው።

### 5. በሥራቸው የሚውሉና የሚዋጡ ሠራተኞች

ይህ ከፍተኛው የሠራተኛ ዓይነት ነው። ዋጋ ስጣቸው ከፍተኛ ክፍያም ክፍላቸው።

## ሁሉም መሪ ሠራተኛውን ማስተማር ያለበት ሰባት ነገሮች

1. ሁሉንም ሠራተኛህን አንተ ስትናገር መመሪያዎችን እንዲፅፉ አስተምራቸው
2. የተሰጣቸውን መመሪያ ደግመው እንዲናገሩት አድርግ፤ የሰጣሃቸውን መመሪያ በሚመለከትም ጥያቄዎችን ጠይቅ።
3. አዘውትረው እንዲደውሉልህ፣ እንዲያናግሩህና እንዲያማክሩህ አስተምራቸው።
4. ሥራቸውን ለመቀየርና አዳዲስ ኃላፊነቶችን ለመቀበል ዝግጁ እንዲሆኑ አስተምራቸው።
5. በሥራ ላይ በአግባቡ እንዲለብሱ አስተምራቸው።

እንደባንክ ያሉ ሀብታም ድርጅቶች ሠራተኞቻቸውን በጣም በሥርዓት እንዲለብሱ እንደሚያዝዟቸው አላስተዋልክም?

6. በሥራቸው ላይ የሚገጥሟቸውን ችግሮች መፍታት አስተምራቸው።

ችግሮችን ከማውራት ይልቅ ችግሮቹን እንዴት እንደፈቷቸው ማውራት አለባቸው!

7. በቤት ሳሉ ስለሥራቸው ማሳብን አስተምራቸው።

ስለሥራው በቤቱ ሳለ የሚያስብ ሰው በሥራው የተሳበና የተዋጠ ነው። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ስለ ሥራቸው መጻሕፍትን ያነብባሉ። ገንዘባቸውንና ጊዜአቸውን ለሥራቸው በይበልጥ ለመዘጋጀት ይጠቀማሉ።

## በሥራህ እንዴት መዋጥ እንደሚቻል

1. ስኬታማ የምትሆነው ሙሉ ማንነትህን በዋጡ ነገሮች ብቻ መሆኑን እወቅ።
2. ስለ ሰዓት እንድታስብ የማያደርግህን ሥራ ፈልግ

   ይህ እግዚአብሔር የሰጠህ ሥራ ነው።
3. በቤትህም ሆነህ በሀሳብህ ሥራህን ቀጥል።
4. ስለሥራህ መጻሕፍትን ገዝተህ አንብብ

5. በአንተ ዓይነት ሥራ ውስጥ ያሉ ጓደኞች በብዛት ይኑሩህ።

   ይህም የዕረፍት ሰዓቶችህ ሳይቀሩ ከሥራህ ጋር ተያያዥነት አላቸው ማለት ነው።

6. ለሥራህ የበለጠ የሰለጠነና የተዘጋጀ ለመሆን ገንዘብን አውጣ።

## ምዕራፍ 128

# ሰዎችን በአንድነት የማቆየት ጥበብን አዳብር

## ሰዎችን በአንድነት የማቆያ አምስት ቁልፎች

1. ሁሉንም ሰው በአንድነት ለማቆየት ጠንካራ ፍላጐት ይኑርህ፡፡ የአንድን ሰው እንኳ መጉደል ለማስቀረት ታገል፡፡ የኢየሱስ ዓላማ እግዚአብሔር ከሰጠው ሰዎች አንዱንም አለማጉደል ነበር፡፡

መጋቢነት ሰዎችን በአንድነት የማቆየት ጥበብ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሰዎችን የመከፋፈል አቅም ያላቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ ሰዎችን በአንድነት የማቆየትን ጥበብ ማዳበር አለብህ፡፡ ሰዎችን አንድ የማድረጊያው ቁልፍ ምንድን ነው? ሰዎች በአንድነት መሆን እንዳለባቸው በሚገባ ማመን አለብህ፡፡ "ከፈለግህ ገደል ግባ" ዓይነት አቋም ካለህ ከቡድንህ ብዙ ሰዎች ይጠፋሉ፡፡

## ሙሴ ሰዎችን በአንድነት አቆይቷል

የሮቤልና የጋድ ልጆችም እጅግ ብዙ እንስሶች ነበሩአቸው እነሆም፥ የኢያዜር ምድርና የገለዓድ ምድር ለእንስሶች የተመቸ ስፍራ እንደ ነበረ ባዩ ጊዜ፥...እኛስ በአንተ ዘንድ ሞገስን አግኝተን እንደ ሆነ ይህን ምድር ለባሪያዎችህ ርስት አድርገህ ስጠን ወደ ዮርዳኖስም ማዶ አታሻግረን።...ሙሴም አላቸው። ይህንስ ነገር ብታደርጉ፥ ተዘጋጅታችሁም በእግዚአብሔር ፊት ወደ ሰልፍ ብትሄዱ፥እርሱም ጠላቶቹን ከፊቱ እስኪያሳድድ ድረስ ምድሪቱም በእግዚአብሔር ፊት ድል እስክትሆን ድረስ ከእናንተ ሰው ሁሉ ጋሻ ጦሩን ይዞ በእግዚአብሔር ፊት ዮርዳኖስን ቢሻገር፥ከዚያ በኋላ ትመለሳላችሁ፥ በእግዚአብሔርም ፊት በእስራኤል ዘንድ ንጹሐን ትሆናላችሁ ይህች ምድርም በእግዚአብሔር ፊት ርስት ትሆንላችኋለች።

ዘኁልቁ 32፡1፤5፤20-22

ሙሴ አደገኛ ሁኔታ ገጠመው፡፡ የእስራኤል አንዳንድ ነገዶች የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገር አልፈለጉም፡፡ ሣሩ ለከብቶቻቸው መልካም በነበረበት መቅረት ፈለጉ፤ ወዲያውኑም ጦርነት ሊነሳ ሆነ፡፡ እስካሁኑ ጊዜ በአንድ ላይ ነበሩ፤ አሁን ግን የእስራኤል ሕዝብ

ለሁለት ክፍሎች ሊከፈል ነበር። እግዚአብሔር እስራኤልን አንድ አድርጐ ለማቆየት የሚያስችል ጥበብ ለሙሴ ሰጠው።

ሙሴ እነዚያን ነገዶች ረግሞ ከፈለጉ ገዛነም እንዲገቡ ሊናገራቸው ይችል ነበር። የተረገሙ እንደሆኑ ሊነግራቸው ይችል ነበር። ይሁንና የሚናፍቁትን ምድር እንዲወርሱ እንዲሁም የእስራኤል አካል ሆነው እንዲቀጥሉ አስቻላቸው።

## 2. እግዚአብሔር የሚሰጥህን ሰዎች ሁሉ ውደድ

ሌላኛው ቁልፍ ሰዎችን ከልብ መንከባከብና መውደድ ነው። አንድን ሰው ከልብ ሰትወደው በቀላሉ ልትለየው አትፈልግም። መሪ ለሰዎች እውነተኛ ፍቅር ሊኖረው ይገባል። ሰዎች ከልብ እንደሚወደዱ በሚያስቡበት ይቆያሉ። ተከታዮችህ የሚለያዩበት ምክንያት ቢኖራቸው እንኳን አንተ ለሁሉም ቡድኖች ያለህ ፍቅር በአንድ ላይ እንዲቆዩ ያደርገዋል።

## 3. አደገኛ ሁኔታዎችን ለመወጣት የእግዚአብሔርን ጥበብ ተጠቀም

በዚያን ጊዜም ሁለት ጋለሞቶች ሴቶች ወደ ንጉሥ መጥተው በፊቱ ቆሙ። አንደኛይቱም ሴት አለች። ጌታዬ ሆይ፥ እኔና ይህች ሴት በአንድ ቤት እንኖራለን እኔም ከእርስዋ ጋር በቤት ሳለሁ ወለድሁ።እኔ ከወለድሁ ከሦስት ቀን በኋላ ይህች ሴት ደግሞ ወለደች እኛ በቤት ውስጥ አብረን ነበርን፥ ከሁለታችንም በቀር ማንም በቤት ውስጥ አልነበረም።እርስዋም በላዩ ስለ ተኛችበት የዚህች ሴት ልጅ በሌሊት ሞተ። እርስዋም በእኩለ ሌሊት ተነሥታ፥ እኔ ባሪያህ ተኝቼ ሳለሁ፥ ልጄን ከአጠገቤ ወሰደች፥ በብብትዋም አደረገችው፥ የሞተውንም ልጅዋን በእኔ ብብት አደረገች። ልጄንም አጠባ ዘንድ በማለዳ ብነሣ፥ እነሆ፥ ሞቶ ነበር ነገር ግን ብርሃን በሆነ ጊዜ ተመለከትሁት፥ እነሆም፥ የወለድሁት ልጄ አልነበረም።ሁለተኛይቱም ሴት። ደኅነኛው የኔ ልጅ ነው፥ የሞተውም የአንቺ ልጅ ነው እንጂ አንቺ እንደምትዪው አይደለም አለች። ይህችም። የሞተው የአንቺ ልጅ ነው፥ ደኅነኛውም የእኔ ልጅ ነው አለች እንዲሁም በንጉሥ ፊት ይነጋገሩ ነበር።በዚያን ጊዜም ንጉሡ። ይህች። ደኅነኛው የእኔ ልጅ ነው፥ የሞተውም የአንቺ ልጅ ነው ትላለች ያችኛይቱም። አይደለም፥ የሞተው የአንቺ ልጅ ነው ደኅነኛውም የእኔ ልጅ ነው ትላለች አለ።ንጉሡም። ሰይፍ አምጡልኝ አለ ሰይፍም ይዘው ወደ ንጉሥ ፊት መጡ።ንጉሡም። ደኅነኛውን ሕፃን ለሁለት ከፍላችሁ ለአንዲቱ አንዱን ክፍል፥ ለሁለተኛይቱም ሁለተኛውን ክፍል ስጡ አለ። ደኅነኛውም የነበራት ሴት አንጀትዋ ስለ ልጅዋ ናፍቆአልና። ጌታዬ ሆይ፥ ደኅነኛውን ለእርስዋ ስጣት እንጂ አትግደል ብላ ለንጉሥ ተናገረች። ያችኛይቱ ግን:- ይከፈል እንጂ ለእኔም ለአንቺም አይሁን አለች።ንጉሡም መልሶ:- ይህችኛይቱ እናቱ ናትና ደኅነኛውን ሕፃን ለእርስዋ ስጡአት እንጂ አትግደሉት አለ።ንጉሡም የፈረደውን ፍርድ

> እስራኤል ሁሉ ሰሙ ፍርድን ለማድረግ የእግዚአብሔር ጥበብ እንደ ነበረበት አይተዋልና ንጉሡን ፈሩ።
>
> 1ኛ ነገሥት 3፡16-28

ንጉሥ ሰለሞን አደገኛ ሁኔታን ተጋፈጠ። በማን ወገን ነበር? ብዙ ጊዜ ሰወች መሪው ይህን ሰው ወይም ሌላኛውን ሰው ይደግፋል ማለት ይፈልጋሉ። በጋብቻ የማማከር ጊዜያት ላይ ብዙ ጊዜ በሚስቶች ወይም በባሎች ወገን ነህ በሚል እወቀሳለሁ። ሰዎች በዚህ ወይም በዚያ ወገን ነህ ማለት ይፈልጋሉ። እንደዚህ ዓይነት አደገኛ ሁኔታዎችን መፍታት የእግዚአብሔርን ጥበብ ይጠይቃል። ጋብቻ ጥንቃቄን የሚፈልግ ነገር ነው። በቤተ ክርስቲያንህ ያሉ ጥንዶች አብረው እንዲቀጥሉ የጋብቻ ችግሮችን በጥንቃቄ ፍታ። እውነተኛ መሪ ጥንቃቄ የሚፈልጉ ነገሮችን የመፍታት ችሎታው እንዲፈታ ያደርጋል። ካልተሳካልህ፣ ሰዎችህ አብረው አይቆዩም።

## 4. በሰዎች መሐል ሰላም አስፍን

አብዛኞቹ የዚህ ዓለም መሪዎች ግጭቶችን በማብረድ የተጠመዱ ናቸው። እውነታው የሰው ልጆች ያለማቋረጥ ሰላም ሊኖር እስከማይችል ድረስ እጅ ብዙ የእርስ በእርስ ግጭቶችና ጦርነቶች አሏቸው። መሪ የሆነ ሰው ሁሉ ሰላም የማስፈንን ጥበብ መማር ያስፈልገዋል።

> ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።
>
> ዕብራውያን 12፡14

ብዙ ፕሬዝዳንቶች በጦረኛ አንጃዎች መካከል ሰላም የሚያውርዱት እነርሱ መሆን እንደሚመኙ አላስተዋልክም? ተከታታይ የአሜሪካ ፕሬዝዳንቶች በመሐከለኛው ምስራቅ ሰላም የሚያወርዱት እነርሱ እንዲሆኑ ናፍቀዋል። በማይታረቁ ጥለኞች መሐከል ቆመው ፎቶ ይነሳሉ። እነዚህ ፎቶግራፎች ስለመምራት ችሎታቸው ስለሚመሰክሩ ይጠቅሟቸዋል። ለዚህም ዓለም ሰላም ማምጣት የሚችል ማንኛውም ሰው የመሪነት ችሎታዎች አሉት።

መሪ ነህ? በጠላቶች መሐል ሰላም እንዲመጣ ትተባበራለህ? ወይስ ጥላቻንና ሁከትን ታባብሳለህን? መሪ ሰላምን እንጂ የበለጠ አለመግባባትን አያመጣም።

## 5. ከሌሎች ጋር ሰላም ይኑርህ

አንዳንድ ሰዎች ያለማቋረጥ በጦርነት ላይ ናቸው፡፡ ከሚያጋጥማቸው ሰው ጋር ሁሉ ጭቅጭቅ ይፈጥራሉ ማለት ይቻላል፡፡ ከቤተ ክርስቲያናቸው ብዙ ሰዎችን ያሸሹ አንዳንድ የመጋቢ ሚስቶችን አውቃለሁ፡፡ ያለማቋረጥ የምትጣላቸውን ሰዎች መምራት አትችልም፡፡ ለምን ማንም እንዳማይከተልህ ገርሞህ ይሆናል፡፡ ደጋግሞ ከጀርባ የሚወጋቸውን ሰው እንዴት ሊከተሉ ይችላሉ? በየደቂቃው እየዞረ ድንጋይ የሚወረውርብህን ሰው ትከተላለህ? በፍጹም!

መሪ መሆን ትመኛለህ? በዙሪያህ ካሉት ጋር በሰላም የመሆንን ጥበብ አዳብር፡፡ ያለማቋረጥ አትዛትባቸው፡፡ በእርግማኖች አታስፈራራቸው፡፡

አንዴ ከአንድ የእግዚአብሔር ሰው ጋር ለመጎብኘት ተጋበዝኩ፡፡ መሄድ አልፈለግሁም፡፡ ሰዎችን ብዙ ጊዜ ሲረግም ያንን ሰውዬ አይቸዋለሁ፡፡ በሀሳቤ “ምናልባት ዛሬ እኔን ይረግመኛል” አልኩኝ፡፡ ትንሽ ሳይከብደው የሚራገም ሰው አጠገብ መሆን አልፈልግም፡፡

የመሪነት ጥበብ በዙሪያህ ካሉት ጋር በሰላም የመሆን ጥበብ ነው፡፡ በሌሎች ስኬት አትረበሽ፡፡ አንተ የሌለህ የሆነ ነገር ስላላቸው አትዋጋቸው፡፡ ኑሮዬ ይበቃኛል በል፡፡ የሌሎች ሰዎችን ስኬት ተቀበል፡፡ ደግሞም አትዋጋቸው፡፡

ከሌሎች ጋር በሰላም የመሆን ቁልፍ ምንድን ነው? እንደማንነታቸው ተቀበላቸው፡፡ በዙሪያህ ያለውን ሰው ሁሉ ለመለወጥ አትሞክር፡፡ እኛ ሰዎች ብቻ ነን ስህተቶችም አሉብን፡፡

## ምዕራፍ 129

# ስለምተጠየቅበት ቀን ያለማቋረጥ አስብ

እያንዳንዱ መሪ እያደረገ ወይም እያደረገ/ች ስላለው/ችው ነገር ይጠየቃል። ስለሰጠህ በጐች ለእግዚአብሔር መልስ ለመስጠት ዝግጁ ነህ? ኢየሱስ ከጥፋት በስተቀር እግዚአብሔር ከሰጠው በጎች አንዱንም እንዳላጐደለ ደጋግሞ ይናገር ነበር። ጳውሎስም መልስ መስጠት እንደሚኖርበት ይናገር ነበር። እነዚህ ያለማቋረጥ ስለሚጠየቁበት ቀን የሚያስቡ መሪዎች ነበሩ።

> ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት፥ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ።
>
> ዕብራውያን 13፡17

መሪነት ትልቅ ኃላፊነት ነው። ከዓመታት በፊት ብዙ የጋና ሀገር መሪዎችና ሚኒስቴሮች በተኳሽ ጓዶች ሲረሸኑ እንደተመለከትኩ አስታውሳለሁ። ወሳኝ ሰዎች ሲዋረዱና ሲገደሉ ማየት አሳዛኝ ነበር። ብዙ ተራ ዜጐች እንደዚህ ዓይነት ነገር አልደረሰባቸውም። ይህም የሆነበት ምክንያት ብዙ ተራ ሰዎች አገሪቱን የመምራትን ኃላፊነት ስላልወሰዱ ነው። ይሁንና የመሪነትን ኃላፊነት የወሰዱት በሕይወታቸው መክፈል ነበረባቸው።

ለአመራርህ መልስ እንደምትሰጥ ያለማቋረጥ የምታስታውስ ከሆነ የተሻለ መሪ ትሆናለህ። የምትጠየቅበት ቀን እየመጣ እንደሆነ ሁልጊዜ አስታውስ። ይህ ትክክለኛውን ነገር እንድታደርግ ያደርግሃል። ስለ አገልግሎቴ ለእግዚአብሔር መልስ እንደምሰጥ ያለማቋረጥ አሰላስላለሁ። በአብያተ ክርስቲያኖቼ ላሉ አባላት መልስ መስጠት እንደሚኖርብኝ አውቃለሁ። ለዚህ ነው እነርሱን ለመጠበቅ ትልቅ ጥረት የማደርገው።

መሪ ነህ? ያለማቋረጥ ስለምትጠየቅበት ቀን እያሰብክ ነው? እባክህ አስብ! የላቀው የውስጥ መነሳሳት ቁልፍ ይህ ነው።

# የመሪነት ጥበብ

ሁለተኛ እትም

ለአገልግሎት መጠራት ለመሪነት መጠራት ነው፡፡ በድጋሚ፣ በቀላሉ በቀረበና ሊተገበር በሚችል አቀራረብ ዶክተር ሂዋርድ ሚልስ ልዩ ክርስቲያን መሪ ያደረጉትን መርሆች ያብራራል፡፡ በዚህ የተገለጠው እውነት ብዙዎችን ለመሪነት ጥበብ ያነሳሳል፡፡

## ዳግ ሂዋርድ ሚልስ

በርካታ ተፈላጊ መጽሐፍ የጻፉና ከእነዚሁም ውስጥ “ታማኝነትና ታማኝ አለመሆን”የተባለው በአለም ላይ ታዋቂ በሆነውን መጽሐፋቸው ሲታውቁ፣ ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆኑ “የላይትሃውስ ቻፕል ኢንተርናሽናል”ዓለምአቀፋዊ ዲኖምኔሽን ቤተ ክርስቲያን መስራች ናቸው፡፡
ዳግ ሂዋርድ ሚልስ፣ በአለማቀፍ ደረጃ ወንጌላዊ ሲሆኑ “ፈዋሹ ኢየሱስ ክሩሴድ (HEALING JESUS CRUSADE) ” በተሰኘው እና በአለም ዙሪያ በተያዩ ኮንፈረንሶች ላይ በአገልግሎታቸው ይታወቃሉ፡፡ይበልጥ መረጃ ከፈለጉ ዌብሳይታቸውን ይጎብኙ፣ www.daghewardmills.org.

The Art of Leadership